# የኢትዮጵያ ታሪክ

# ኑብያ

(ናፓታ - መርዌ)

ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ ።

፩ኛ መጽሐፍ


አዲስ አበባ የካቲት ፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ።

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ በሙሉም ፡ በከፊልም ፡ መተርጐምም ፡ ማተምም ፡
ክልክል ፡ ነው ።

All rights reserved

፪ኛ ፡ ተሻሽሎ ፡ የታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

# ማ ው ጫ ።


| ምዕራፍ | አርእስት ፡ | ገጽ |
|---|---|---|
| | ፩ኛ ፡ ክፍል ። | |
| ፩ | የኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የነገድ ፡ ስም ፡ ---- | ፩-፲፩ |
| ፪ | የቀድሞው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጽሑፍ ፡ ሁኔታ ፡ -- | ፲፩-፲፯ |
| ፫ | ባገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኘው ፡ የነገድ ፡ ካምና፡ የነገድ ፡ የቅጣን ፡ አመሠራረት - የነገሥታቱ ፡ የተለመደ ፡ ዝርዝር- በውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድና ፡ ልማድ ፡ -----------------። | ፲፯-፴፯ |
| ፬ | በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ንግድ- በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ ንጉሥና ፡ አንድ፡ አንድ ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ -ሃይ ማኖት-ጋብቻ ። ------------------ | ፴፯-፵፫ |
| ፭ | ከግብፅና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ ማን ፡ ይቀድማል ? ------------------- | ፵፫-፵፰ |
| ፮ | የግብፅ ፡ መንግሥት፡ አመሠራረትና ፡ አምልኮ | ፵፰-፷፰ |
| ፯ | ፩ኛ ፡ የግብፅ ፡ ፊደል ፡ --------------- | ፷፰-፸፮ |
| ፰ | ዓባይና ፡ የቀድሞ ፡ ኢትዮጵያ-የግብፅ ፡ ገዥ ነት ፡ በኢትዮጵያ፡ላይ-ቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ ራም ሲስ ፡ ፪ኛ ፡-------------------- | ፸፮-፩፻፫ |
| ፱ | ባገራችን ፡ የተለመደው ፡ የነገሥታት ፡ ዝር ዝርና ፡ የዶክተር፡ራይዝነር፡ዝርዝር ፡ ልዩነት፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ እስከ፡ ባዚን፡ ያሉት ፡ --- | ፩፻፫ - ፩፻፰ |
| ፲ | ከፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ በፊት፡የነበሩት ፡ ነገሥታት | ፩፻፰-፩፻፲፫ |
| ፲፩ | የኢትዮጵያውያን ፡ ገዥነት ፡ በግብፅ ፡ ላይ ፡ ፒያንኪ ፡ ሚሪአሙን፡በተፍንክታ፡ ላይ ፡ ያገ ኘው ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ----------- | ፩፻፲፫-፩፻፴፯ |

## ማ ው ጫ ።


| ምዕራፍ | አርእስት ፡ | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| ፲፪ | የሻባካ፡ (ሰባቆን ፡) ዘመነ፡መንግሥት ። የሻባካና ፡ የቦኮንራፍ፡(በቦኮሪስ ፡) ጦርነት- አፍ - አውጥቶ ፡ የተናገረው ፡ በግ - የጣዖቱ ፡ ኮርማ ፡ በሬ ፡ ከተራ ፡ ኮርማ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንደተሸነፈ ፡ | ፩፻፵፯-፩፻፶፭ |
| ፲፫ | የሻባቶካ ፡ (ሰቢኮስ ፡) ዘመነ ፡ መንግሥት ። ታርሐቃና ፡ ሕዝቅያስ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ከአሶሩ ፡ ንጉሥ፡ከሰናክሬም ፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ የጦር ፡ ሠልፍ ፡ | ፩፻፶፭-፩፻፶፱ |
| ፲፬ | የታርሐቃ፡ዘመነ፡መንግሥት። የሚቀጥለው ፡ የአሜኒሪቲስ ፡ (ሕንደኬ፡) ሥልጣን-የታርሐቃና ፡ የአሣርሐዶንን ፡ ጦርነት ፡ ሁለቱ ፡ ለየግላቸው ፡ ያሠሩት ፡ ሐውልት-የታርሐቃ ፡ ፍጻሜ | ፩፻፶፱-፩፻፷፬ |
| ፲፭ | ታኑታሙን ። | ፩፻፷፬-፩፻፸ |
| ፲፮ | በግብፅ ፡ የኢትዮጵያ፡ግዛት፡ ፍጻሜ- የኢትዮጵያ ፡ የግዛት ፡ ዘመን ። | ፩፻፸-፩፻፸፬ |
| ፲፯ | የመዠመሪያው ፡ የባቢሎን ፡ መንግሥትና ፡ ንጉሡ ፡ ሐሙራቢ ፡ የጐረቤቱ ፡ የአሶር ፡ መንግሥት ፡ መነሣት ። | ፩፻፸፬-፩፻፹ |
| ፲፰ | የግብፆችና፡የአሶራውያን ፡ ልዩነት- የአሶራውያን ፡ ጭካኔ ፡ | ፩፻፹-፩፻፹፯ |
| ፲፱ | ሁለተኛው፡ የባቢሎን፡መንግሥት፡አነሣሥና፡ ሲአክሳር፡የሜዶን፡ንጉሥ፡የባቢሎን ፡ ንጉሥ፡ ናቡከደነፆርና ፡ የእስራኤል ፡ ምርኮ ፡ | ፩፻፹፯-፩፻፺፱ |
| ፳ | የአሶርና ፡ የባቢሎን ፡ የከለዳውያን፡ ፊደልና ፡ ጽሑፍ-አንዳንድ ፡ ልማድና፡ሃይማኖታቸው ፡ | ፩፻፺፱-፪፻ |




## ማ ው ጫ ።


| ምዕራፍ | አ ር እ ስ ት ፡ | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| ፳፩ | በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሁናቴ ፡ ካምቢዝ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ናስቶሴኔን ፡ የኢትዮጵያ ፡ (ናፓታ ፡) ንጉሥ - አርአንዲዝና ፡ ሔዳስፕ ፡ (ሐድ- አስ- ኤው ) | ፪፻ - ፪፻፲፬ |
| ፳፪ | ግሪኮች ፡ | ፪፻፲፬- ፪፻፲፰ |
| ፳፫ | የግሪኮች ፡ አማልክት ፡ | ፪፻፲፰-፪፻፳፱ |
| ፳፬ | የሆሜር ፡ ድርሰቶች - የአማልክቱ ፡ የዘር ፡ ግንዶች ፡ | ፪፻፳፱-፪፻፴፩ |
| ፳፭ | አከራካሪዋ ፡ ፍሬና ፡ የትሮያ ፡ ጦርነት ፡ | ፪፻፴፩-፪፻፴፱ |
| ፳፮ | የመቄዶንያ ፡ መንግሥትና ፡ ንጉሡ ፡ ፊልጶስ ፡ የትልቁ ፡ እስክንድር ፡ አነሣሥ ፡ | ፪፻፴፱-፪፻፵፫ |
| ፳፯ | ትልቁ ፡ እስክንድርና ፡ ዳርዮስ ፡ በአርቤላ ፡ (አሶር) ያደረጉት ፡ ጦርነትና ፡ የዳርዮስ ፡ አሟሟት - የፋርሶችና ፡ የመቄዶናውያን ፡ መቀናናት ፡ የወዳጁ ፡ የክሊቶስ ፡ አሟሟት - የእስክንድር ፡ ምኞትና ፡ ፍጻሜ ፡ | ፪፻፵፫-፪፻፶፩ |
| ፳፰ | እስክንድርና ፡ ዲዎጋን- ከትልቁ ፡ እስክንድር ሞት ፡ በኋላ ፡ ግዛቱን ፡ የተካፈሉት ፡ አለቆች፡ | ፪፻፶፩-፪፻፶፱ |
| ፳፱ | የመርዌ ፡ ንግሥት ፡ የሕንደኬና ፡ የትልቁ ፡ እስክንድር ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ - የመርዌ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ የነፕቶሎሜ ፡ ( በጥሊሞስ ፡ ) ግንኙነት ። | ፪፻፶፱-፪፻፷፯ |
| ፴ | የኑብያው ፡ የኢትዮጵያና ፡ የአክሱም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግንኙነትና ፡ ልዩነት ። | ፪፻፷፯-፪፻፸፫ |

# መቅድም ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የነገሥት ፡ ዘመን ፡ ረዥም ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በዚሁ ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ባገሪቱ ፡ ላይ ፡ የውስጥ ፡ ጦርነትም ፡ የአስተዳደርና ፡ የዳኝነት ፡ የንግድና ፡ የሽቀጥ ፡ መለዋወጥ ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ የግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ መፈጸሙ ፡ ሳይቀር ፡ በድንጋይም ፡ በብራናም ፡ ላይ ፡ መኖር ፡ የምናገኘው ፡ እስካሁን ፡ የምናውቀው ፡ የታሪክ ፡ ጽሑፍ ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። የየዘመኑን ፡ ታሪክ ፡ እግር ፡ በእግር ፡ እየተከተለ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ያከታተለው ፡ ካለመኖሩ ፡ የተነሣ ፡ ሙሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለማግኘት ፡ ለማስረዳትና ፡ ለመረዳት ፡ ጸሐፊም ፡ አንባቢም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ችግረኛ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለቀድሞው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ እዳር ፡ ቆመን ፡ መመልከት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ያዘጋጀውን ፡ አነስተኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ለይተን ፡ ማንበብና ፡ መተረክ ፡ ሳይሆን ፡ እውስጥ ፡ ገብተን ፡ የረዥሙን ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ በድንጋይና ፡ በብራና ፡ ከተጻፈው ፡ ላይ ፡ ለማዳረስ ፡ የፈለግን ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተበታትኖም ፡ ተወሳስቦም ፡ እንደሚገኝ ፡ መረዳታችን ፡ አይቀርም ።

ከ፪ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ (፲፫፻፲፮—፲፫፻፵፮ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ ምላ ፡ ከጐንደር ፡ የነገሥታቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ እተጻፈበት ፡ ውስጥ ፡ ያገሪቱ ፡ ታሪክ ፡ ባጫጭሩ ፡ እየተወሳ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ እንደሌሎቹ ፡ መንግሥታት ፡ ታሪክ ፡ በአማርኛ ፡ እንኳ ፡ ቢቀር ፡ በዚያው ፡ በዘመኑ ፡ በሚጻፍበት ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ አጥጋቢ ፡ ታሪክ ፡ አይገኝም ። ከነገሥታቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ ያንዱ ፡ ንጉሥ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ የሌላው ፡ ይጠፋል ፡ ወይም ፡ የተገኘው ፡ ላንድ ፡ ምዕራፍ ፡ የሚበቃ ፡ ሐተታ ፡ ለመስጠት ፡ የማያስችል ፡ ይሆናል ። የዚህም ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ የፊተኛው ፡ በዮዲትና ፡ የኋለኛው ፡ በግራኝ ፡ አሀመድ ፡ እነግሥና ፡ አጥፊነት ፡ ቢመካኝ ፡ ከግራኝ ፡ ወዲህ ፡ ያለውም ፡ በጐንደር ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ያንዳንዶቹ ፡ ሙሉና ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ ይጐድለዋል ።

ከዚያ ፡ የበለጠ ፡ ደግሞ ፡ ያገሪቱና ፡ የመንግሥቱ ፡ ታሪክ ፡ የፖለቲካውና ፡ የኢኮኖሚው ፡ ሁኔታ ፡ የሚታወቀው ፡ በልክ ፡ ነው ። እንደዘመኑ ፡ ልማድ ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊዎች ፡ በየዘመኑ ፡ ያሉት ፡ ጸሐፍት ፡ ትእዛዛት ፡ ናቸው ። የነርሱም ፡ የጸሐፊነት ፡ አቅማቸው ፡ በዚሁ ፡ በጠባቡና ፡ የንጉሥን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በመጻፍ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ስለሆነ ፤ ወይም ፡ ከዚህ ፡ አልፈው ፡ በሰፊው ፡ መጻፍ ፡ ቢያስቡ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በራሳቸው ፡ ስሜት ፡ አደራጅተው ፡ ለመጻፍ ፡ ነፃነትም ፡ የገንዘብ ፡ አቅማቸውም ፡ አይፈቅድላቸውም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ካፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሲገኝ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ የአክሱሞችና ፡ የዛጉዬዎች ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ነው ። ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከጻድቃንና ፡ ከሰማዕታት ፡ ከገድልና ፡ ድርሳን ፡ ጋር ፡ ተሰባጥሮ ፡ የሚገኘው ፡ የነገሥታቱ ፡ ታሪክ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ከመለያየቱ ፡ በቀር ፡ ዛሬ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐውልት ፡ ከሳባውና ፡ ከግሪኩ ፡ ከግዕዙም ፡ ላይ ፡ ወደአማርኛ ፡ የተተረጐመ ፡ እንደሆነ ፡ የዚህ ፡ ትርጉም ፡ እስካሁን ፡ ሲነበብና ፡ ሲታመንበት ፡ የኖረውን ፡ የዚያኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ ሲሽረው ፡ ስሙንም ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ሲጠራው ፡ እናገኘዋለን ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ አብርሃ ፡ ያለውን ፡ የሐውልቱ ፡ ጽሑፍ ፡ ኢዛና ፡ ሲለው ፤ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ አሬታዊ ፡ ያደረገውን ፡ ንጉሥ ፡ ሐውልቱ ፡ አረማዊ ፡ ሲያደርገው ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ የተለያየበትን ፡ ምክንያት ፡ እዋናው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስንገባ ፡ እናገኘዋለንና ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ መዘርዘር ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሚገኘውን ፡ ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ እንደዚሁ ፡ እንዳለ ፡ ያንባቢን ፡ አሳብ ፡ እያባዘነ ፡ ኑሮውን ፡ እንዲቀጥል ፡ ልንተወው ፡ አይገባም ። ሊዛመድ ፡ የሚችለውን ፡ ጠበኛ ፡ ታሪክ ፡ ማዛመድ ፤ የተዘበራረቀውን ፡ መልክ ፡ ሰጥቶ ፡ ማከታተል ፤ ሊታረቅ ፡ የማይችለውንም ፡ አስታራቂ ፡ ማስረጃ ፡ እስኪገኝ ፡ ድረስ ፡ በግልጽ ፡ ለየብቻ ፡ አስቀምጦ ፡ ፍርዱን ፡ ለአንባቢ ፡ መተው ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ የንባብና ፡ የጽሕፈት ፡ የመተረክም ፡ ልማድ ፡ አለኝ ፡





ለሚለው ፡ ሁሉ ፡ ግዴታውም ፡ ባይሆን ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ያንዳንድ ፡ አገሮችም ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሲኖር ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ሊተከልና ፡ ሊደራጅ ፡ የቻለው ፡ በየዘመኑ ፡ በተነሡት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ትጋት ፡ ነው ። ባገራችንም ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እነአቶ ፡ አፅሜ ፡ እነ አለቃ ፡ ታዬ ፡ እነብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ የደከሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ሳናስታውስ ፡ አስታውሰንም ፡ ሳናመሰግናቸው ፡ ማለፍ ፡ አይገባንም ።

እላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በአመለከትኋቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ትምህርት ፡ ሊሰጥበት ፡ የሚችል ፡ በአማርኛም ፡ በግዕዝም ፡ የታተመ ፡ መደዳውን ፡ የተጻፈ ፡ ደንበኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ካለመኖሩ ፡ የተነሣ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ተቀጥረው ፡ የመጡት ፡ መምህራን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መጽሐፍና ፡ በየግል ፡ ቋንቋቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪካችንን ፡ ለወጣቶቻችን ፡ ማስተማራቸውን ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ በምሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ተረዳሁ ። ከሌላው ፡ ልንደርስበት ፡ ካልቻልነው ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ አልፈው ፡ ፊደልም ፡ ወረቀትም ፡ ብርዕም ፡ ዕውቀትም ፡ ሳናጣ ፡ የገዛ ፡ ታሪካችንን ፡ ፈረንጆች ፡ በመጽሐፋቸውና ፡ በቋንቋቸው ፡ ወጣቶቻችንን ፡ ማስተማራቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የውርደት ፡ ስሜት ፡ እንደሚሰጥ ፡ ላንባቢ ፡ መግለጽ ፡ የሚያስፈልግ ፡ አይመስለኝም ።

ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ስለአሳዘነኝ ፡ ባነሰው ፡ ዕውቀቴ ፤ በልጅነቴ ፡ አስተያየቱ ፡ መንግሥታችን ፡ በተመለሰበትና ፡ አገሯ ፡ የማገልገል ፡ እምርት ፡ በሚያጣድፍበት ፡ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከደንበኛው ፡ ሥራዬ ፡ ውጭ ፡ የዚያን ፡ ጊዜው ፡ የመረዳት ፡ አቅሜ ፡ በፈቀደልኝ ፡ መጠን ፡ ካፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚባለውን ፡ ጽፌ ፡ አሳተምሁ ። ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ካንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የነቀፋ ፡ ጠጠር ፡ ቢወረወርበትም ፡ በጠቅላላው ፡ ሕዝብንም ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችንም ፡ መጥቀሙ ፡ አይካድም ። የዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ ከርሱ ፡ የተሻለ ፡ እስኪገኝ ፡ ድረስ ፡ ከትምህርት ፡ መስጫ ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ተመድቦ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ፱ ፡ ጊዜ ፡ እየተደጋገመ ፡ መታተሙ ፡ ነው ።

መቅድም ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ የኑብያ ፡ (ናፓታና ፡ መሮዌ) ፤ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የአክሱም ፤ በሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ የዛጒዬ ፡ ሆኖ ፡ ከሦስት ፡ ላይ ፡ ተከፍሎ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ድረስ ፡ (፲፪፻፸ ዓ ፡ ም ፡) ያለው ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪካችንን ፡ በኔ ፡ አስተያየትና ፡ አገላለጥ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይገኝበታል ። አሁን ፡ የያዝ ነው ፡ ሥልጣኔና ፡ ቋንቋ ፡ ምንጩ ፡ ከኑብያ ፡ ይልቅ ፡ አክሱም ፡ መሆኑን ፤ በኑብያና ፡ በአክሱም ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ ልዩነት ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ እንረዳለን ። ስጊዜው ፡ ግን ፡ ስንባብና ፡ ለአያያዝ ፡ እንዲመች ፡ ከኑብያ ፡ እስከ ፡ አክሱም ፡ ያለው ፡ ባንድ ፡ ቅጽ ፤ ቀጥሎ ፡ የአክሱሙና ፡ የዛጒዬው ፡ በ፪ኛ ፡ ቅጽ ፡ ተለይቶ ፡ እንዲታተም ፡ ተደርጓል ።

መቼም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ማወቅ ፡ ብቻውን ፡ አይበቃም ። የቀድሞ ፡ ጸሐፍት ፡ ትእዛዛት ፡ ከድካማቸው ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ የኑብያን ፡ ለማወቅ ፡ የግብፅን ፡ ታሪክ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ ለመረዳት ፡ የግሪክንና ፡ የሮማን ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ (ታናሽ ፡ ሮም ፡) እንደዚሁም ፡ የደቡብ ፡ ዓረብን ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ፡ በዝርዝርም ፡ ባይቻል ፡ በመጠኑ ፡ ማወቅ ፡ ያሻል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ታሪኩ ፡ አስገድዶ ፡ እንጂ ፡ ገጹን ፡ ለማብዛት ፡ ሳይሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስኳቸውን ፡ አገሮች ፡ እንደዘመኑና ፡ እንደክፍሉ ፡ ከገራችን ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ ያወራረስሁት ፡ እዚያው ፡ እየታሪኩ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የአንባቢንና ፡ የተማሪን ፡ አእምሮ ፡ እንዲያገለግል ፡ እመኛለሁ ። ይኽን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ያገለገሉኝን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ እዚያው ፡ እየናው ፡ መጽሐፍ ፡ አካል ፡ ውስጥ ፡ በየምዕራፉ ፡ ስለጠቀስኳቸው ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መዘርዘር ፡ አስፈላጊ ፡ አልመሰለኝም ።

ይኽን ፡ መጽሐፍ ፡ (ሌሎችንም) ፡ ለማዘጋጀት ፡ የተጠቀምሁባቸው ፡ ቋንቋዎች ፡ ግዕዝ ፡ ፈረንሳዊኛና ፡ ኢጣልያንኛ ፡ ሲሆኑ ፡ በነዚህ ፡ ቋንቋዎች ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ በየመሥመሩ ፡ እየተከታተልሁ ፡ በመሰብሰብ ፡ በማገናኘት ፡ ከጻፍሁ ፡ በኋላ ፡ በራሴ ፡ አስተያየት ፡ ለማብራራት ፡ ሞክሬያለሁ ። ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በመ



መቅድም ።

ይኽን ፡ የመጀመሪያውን ፡ መጻፈ ፡ ሁለተኛውን ፡ ለመጻፍ ፡ ስለገፋፋኝ ፡ ከትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዳለሁ ፡ ያጋመስሁትን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ባቡር ፡ መቈጣጠሪያ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከተዛወርሁ ፡ ወዲህ ፡ ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ ታሪክ ፡ አዘጋጅቼ ፡ ለማሳተም ፡ ቻልሁ ። በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ በገጽ ፡ ፲፩ ፡ እንዳመለከትሁት ፡ ካፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወዲህ ፡ ያለውን ፡ ጽፌ ፡ ካሳተምሁ ፡ በኋላ ፡ በአሳቤ ፡ የተተከለው ፡ ከሥር ፡ መንግሥታችን ፡ ከተመሠረተበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ለማጥናትና ፡ ለመጻፍ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ለዚሁ ፡ የሚጠቅመኝን ፡ ከአንዳንድ ፡ መጻሕፍት ፡ ላይ ፡ እየለቀምሁ ፡ ጽሑፉን ፡ መጻፍ ፡ ጀምሬ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ገጽ ፡ ግድም ፡ የሚሆን ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳዘጋጀሁ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ለሥራ ፡ ታዝዤ ፡ ሄድሁ ። በፓሪስ ፡ አምባሳድ ፡ የተመደበልኝን ፡ የጸሐፊነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራሁ ፡ የታሪኩንም ፡ ዝግጅት ፡ በድርብ ፡ ለመቀጠል ፡ ሞክሬ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ የመቀጠል ፡ አምሮት ፡ ቢኖረኝ ፡ በአምባሳድ ፡ ካለው ፡ ከተርታ ፡ የጸሐፊነት ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ለመቀጠል ፡ ጣዕም ፡ ስላጣሁበት ፡ የታሪኩን ፡ ሥራ ፡ ወደፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነፃ ፡ ጊዜ ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በደብዳቤ ፡ አመለከትሁ ። ግርማዊነታቸውም ፡ በተለመደ ፡ የጽሑፍ ፡ ደጋፊነታቸው ፡ የጠየቅሁትን ፡ ጊዜ ፡ ፈቀዱልኝ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀድሞውኑ ፡ ከማውቀውና ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ይዣቸው ፡ ከሄድሁት ፡ ጽሑፎች ፡ በቀር ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እየተመላለስሁ ፡ የታሪካችንን ፡ ጽሑፍና ፡ ማስረጃ ፡ የተገኘውን ፡ ያህል ፡ እየሰበሰብሁ ፡ ከሥር ፡ ከኑብያ ፡ መንግሥት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ በቃሁ ። በዚሁም ፡ የፈረንሳዊን ፡ መንግሥት ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ አገልጋዮች ፡ ስለአቀባበላቸውና ፡ ስላደረጉልኝ ፡ የዘወትር ፡ አገልግሎት ፡ ምስጋናዬ ፡ ይድረሳቸው ።

## መቅድም ።

ድከምና ፡ በመሰልቸት፡ ጊዜም ፡ በማጠር ፡ ለየጕዳዩ፡ በቂ ፡ ሐተታ፡ ሰጥቼ ፡ የማስበውን ፡ ያህል፡ የንባብ ፡ ወዝ፡ ሳልሰጥ ፡ ማበሌ፡ ትዝ፡ የሚለኝን ፡ ለመደበቅ ፡ አልሻም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ተከታትሎ ፡ ለወደፊት ፡ ጺሑፌ ፡ እንደሚመች ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መቀመጡ ፡ ደግሞ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ፡ እንዳለው፡ ስለማውቅ ፡ ከድካም፡ የመነጨውን ፡ ደስታዬን ፡ ሊቀንስብኝ፡ አይችልም ። ከኔ ፡ በፊት ፡ እንደዚህ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ባገኘው ፡ ኖሮ ፡ ለፍለጋ፡ ለማገናዘብ ፡ ያጠፋሁትን ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ለማብራራትና፡ በጥሩ ፡ ዘመናዊ፡ ያነጋገር ፡ ቅርጽ ፡ ለማቃናት ፡ ለሠዋው ፡ ዛሬ ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ጽሑፍ ፡ ለማቅረብ ፡ በተቻለኝ ፡ ነበር ።

ግናቸውም ፡ እምላካዊ ፡ ሥራና ፡ ፍጥረት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ አስፈላጊው ፡ ነው ። ከዚያም ፡ በታች ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ የሚሠራው ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ እንደመብልና ፡ እንደመጠጥ ፡ ግዴታ ፡ አስፈላጊውም ፡ ባይሆን ፡ ጠቃሚው ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መጽሐፍም ፡ በማኅበራዊ ፡ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ የያዘው ፡ የጠቃሚነት ፡ ደረጃ ፡ ከቀድሞ፡ ዠምሮ ፡ የነበረው ፡ ዛሬ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ሄዷል ።

ተማሪ ፡ ይማርበታል ፡ መምህር ፡ ያስተምርበታል ።

ወታደር ፡ ገበሬ ፡ ነጋዴ ፡ የእጅ ፡ ሞያተኛ ፡ ሁሉ ፡ ያባስተማሪ፡ አእምሮውን ፡ ያስፋፋበታል ።

የታመመ ፡ ያዘነ ፡ የታሠረ ፡ አቤት፡ የዋለ ፡ ሽማግሌ ፡ አገሬ ፡ መንገዱን ፡ እየተማረ፡ በመጽናናት፡ መጥፎውን፡ የችግር ፡ ዘመንና፡ የሥራ ፡ መፍታት፡ ጊዜ፡ ያሳልፍበታል ። መጽሐፍ ፡ የማያስቀይም ፡ ውለታ ፡ ሊመለስለት ፡ የማይጠይቅ ፡ የሕይወት ፡ መካር ፡ ጓደኛ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በምንችለውና ፡ ስጦታችን፡ በሆነው ፡ መንገድ ፡ የጽሑፍ ፡ ምርት ፡ ለወገናችን ፡ እያበረከትን፡ በዚሁም ፡ ወደኋላ ፡ የቀረውን ፡ ያገራችንን ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ፡ ጕድለት ፡ በየትርጓሜቱ ፡ እንድናሟላው ፡ በትንነት ፡ እመኛለሁ ።

ጥር ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ።

ተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መኵሪያ ።



## ፩ኛ ፡ ክፍል ።

## የኑብያ ፡ መንግሥት ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የነገድ ፡ ስም ።

ዛሬ ፡ ባንድ ፡ በኢትዮጵያና፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ስም ፡ የረጋው ፡ ያገራችንና ፡ የሕዝቡ ፡ ስም ፡ ቀድሞ ፡ ብዙ ፡ ነበር። በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫፡ በዚሁ፡መጽሐፍ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ ከቍጥር ፩ ፡ እስከ ፡ ፴፪ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ፡ የኖኅ ፡ ልጆች ፡ ሴም ፡ ካም ፡ ያፌት ፡ መሆናቸውን፡ የካም፡ ልጆች ፡ ኩሽ ፡ (ኩስ ፡ ቁስ) ፡ ሚስራይ ፡ ፋጥ ፡ ከነዓን ፡ መሆናቸውን ፡ እንደሚገልጸው ፡ የኩሽም ፡ ዘር ፡ በእስያ ፡ ደቡብ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ ተሻግረው ፡ ተራብተው ፡ በርከተው ፡ ከዛሬው ፡ ሱዳን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ይዘው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፫፻ና ፡ በ፩፻ ፡ ዓመት ፡ መካከል፡ ሁሉ፡ ግብፆች ፡ በሐውልታቸውና ፡ በብራና ፡ (ፓፒሩስ) ፡ ጽሑፋቸው ፡ (ሂዬሮግሊፍ) ፡ ላይ ፡ እንደተዉት ፡ በሰፊው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ፡ የደቡብ፡ ምድር ፡ ወይም ፡ የነሕስ ፡ የነሕሴ ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የፑንት ፡ አገር ፡ እያሉ ፡ ይጠሩት ነበር ። በዝርዝሩ ፡ እንደምናገኘው ፡ ነሕሴ ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ ፩ኛው ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ የተመደበ ፡ ስለሆነ ፡ ጅማ ፡ ያባ ፡ ጅፋር ፡ አገር ፡ ሸዋ ፡ የእምኃየስ ፡ አገር ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ በመሬው ፡ ስም ፡ የነሕሴ ፡ አገር ፡ ማበታቸው ፡ ይሆናል ። ግማሾቹ ፡ ነሕሴ ፡ ማለት ፡ ጥቁር ፡ ማለት ፡ ስለሆነ ፡ የጥቁር ፡ አገር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ደግሞ ፡ ከዐባይ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ግብፆች ፡ ፑንት ፡ ብለውት፡ ይገኛል ። ለአማልክቶቻቸውና፡ ለቤተ ፡ መቅደሳቸው ፡ የሚሆን ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ ብርጕድ ፡ ለመውሰድ ፡ወደ ፑንት ፡ ዘመትን ፡ ሲሉ ፡ አምላካቸው ፡ አሞን ፡ ፑንትን ፡ ሰጥቼሻለሁና ፡ ውጋና ፡ ውሰድ ፡ እንዳላቸው ፡ በጽሑፍ ፡ ይገኛል ።

ጌታችን ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ይኸን ፡
ሕዝብ ፡ ለመፋረድ ፡ ትነሣለች ፡ --- ያለውን ፡ በኛ ፡ በግዕዝ ፡ አዜብ ፡
ማለት ፡ በደቡብና ፡ በምዕራብ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ፡ (፩) ፤ ነገር
ግን ፡ በፈረንጅ ፡ ሁሉ ፡ የወንጌል ፡ ትርጓሜ ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡
የምንለውን ፡ የደቡብ ፡ ንግሥት ፡ ስለሚል ፡ ነሕሴንና ፡ ፑንትን ፡
ወደጎን ፡ እናድርግና ፡ ለዚሁ ፡ ጥንት ፡ ግብፆች ፡ በጉርብትናም ፡
በግዛትም ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የደቡብ ፡ አገር ፡ ከሚሉት ፡ ጋር ፡ ይገ
ናኛል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ግብፆች ፡ የኩሽ ፡ ሕዝብ ፡ የሠፈረበትን ፡ አገር ፡
የደቡብ ፡ ወይም ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ሲሉ ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ በኋላ ፡
ከመጡት ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነች ፡ በመሬትና ፡ በገሩ ፡
ከኩሽ ፡ ሕዝብ ፡ ትገናኛለች ፡ እንጂ ፡ የርሷ ፡ ዘር ፡ የመጣበት ፡ ከሴም ፡
ዘር ፡ የወለደው ፡ የሳባና ፡ የዮቅጣን ፡ ዘር ፡ ከካምና ፡ ከኩሽ ፡ ዘር ፡
ልዩነት ፡ እንደአለው ፡ አንዘነጋም ።

የቀረው ፡ ደግሞ ፡ እንደዛሬው ፡ አጠራራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲል ፡
ይገኛል ። ለምሳሌ ፡ ከግሪኮቹ ፡ ውስጥ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡
በ፱ነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ የአዲሴውስና ፡ የኤሊ
ያስ ፡ ጸሐፊ ፡ ሆሜር ፡ በተለይ ፡ በኤሊያስ ፡ (ድ) ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡
ምዕራፍ ፡ ፩ና ፡ በሌላውም ፡ ክፍል ፤ የታሪክ ፡ አባት ፡ የሚባለው ፡
በ፭ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ሄሮዶት ፡ በታሪክ ፡ መጽ
ሐፉ ፡ በ፪ኛውና ፡ በ፫ኛው ፡ በ፯ኛውና ፡ በ፱ኛው ፡ ክፍል ፡ ኢትዮ
ጵያ ፡ ይላሉ ። ከእስራኤሎችም ፡ ወገን ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ ከክርስቶስ ፡
ልደት ፡ በፊት ፡ በ፩ሺ፩መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ዳዊት ፡ በመ
ዝሙሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲል ፡ በ፰ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የነበረው ፡ ኢሳይ
ያስ ፡ ደግሞ ፡ በትንቢቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ ቍጥር ፡ ፲፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡
ቍጥር ፡ ፩-፪ ፤ ሶፎንያስም ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡
ሲሉ ፡ ይገኛሉ ። ጓደኛቸው ፡ ዕንባቆም ፡ ደግሞ ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ፡
ቍጥር ፡ ፯ ፡ መልሶ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይላል ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የጥንት ፡
ጸሐፊዎችና ፡ ነቢያት ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተግሣፅና ፡ ምክር ፡
ወይም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የጸሎትና ፡ የምስጋና ፡ ቃል ፡ ሲያቀርቡ ፡
አግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ያገራችን ፡ ጕዳይ ፡ ሲያጋጥማቸው ፡ አንዳ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ሲሉን ፡

(፩) የማቴ ፡ ወን ፡ ም ፡ ፲፪ ፡



ቆዩ ። በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ የሴም ፡ ዘሮች ፡ ነገደ ፡ ሳባና ፡
ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ እየተሻገሩ ፡
ከካምና ፡ ከኩሽ ፡ ዘር ፡ ጋር ፡ ተደባልቀው ፡ በመጣተኝነት ፡ ከቆዩ ፡
በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ በጦር ፡ አሸንፈው ፡ አብረው ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡
በስም ፡ ላይ ፡ ስም ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ። የቀድሞዎቹ ፡ በኑብያ ፡ መን
ግሥታቸውን ፡ አስፍተው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ እየተባሉ ፡
ሲቀመጡ ፡ በሥልጣኔና ፡ በሃይማኖት ፡ በጽሑፍና ፡ በቋንቋ ፡ የግብፅን ፡ ሲከ
ተሉ ፡ በኋላ ፡ የመጡት ፡ ደግሞ ፡ በትግሬና ፡ በሐማሴን ፡ እንደዚሁም ፡
በዙሪያው ፡ በደቡቡ ፡ በአማራ ፡ አገር ፡ ከተማቸውን ፡ እየከተሙ ፡
ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ይዘውት ፡ የመጡትን ፡ ከአሶር ፡ ከከለዳውያን ፡
ከፊንቄ ፡ የመነጨውን ፡ የሳባ ፡ ቋንቋና ፡ ፊደል ፡ ለዛሬ ፡ ፊደላችን ፡
ቋንቋንና ፡ አባት ፡ የሆነውን ፡ ከሥልጣኔያቸውና ፡ ከልማዳቸው ፡
ጋር ፡ ይዘው ፡ ተቀመጡ ።

ይኸን ፡ የልዩነት ፡ ሁኔታ ፡ የዛሬ ፡ ሊቃውንት ፡ ዮሴፍ ፡
ሀለቪ ፡ (JOSEPH HALEVI) ኤድዋርድ ፡ ግላዘር ፡ (EDUARD
GLASER)ኮንቲ ፤ ሮሲኒ (CONTI—ROSSINI) ፤ ገር ፡ ሪክማን ፡
(G. RYCKMANS ሌሎችም ፡ በዚህ ፡ ገጽ ፡ ስማቸውን ፡ ዘር
ዝሬ ፡ የማልጨርሰው ፡ ለማጣራት ፡ እንደ ፡ ደከሙ ፡ ወደፊትም ፡
ያሉት ፡ ጨርሰው ፡ ማጣራት ፡ እስኪችሉ ፡ ድረስ ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡
ጸሐፊዎች ፡ በብዙ ፡ ምርመራ ፡ እያጣሩና ፡ እየለዩ ፡ እጸፉበት ፡
እዛሬው ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፤ ነቢያት ፤ ነገሥ
ታት ፡ ነገሩን ፡ እቅርብ ፡ ሆነው ፡ ሳይከታተሉ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ ሲና
ገሩም ፡ ሲጽፉም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኩሽ ፤
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነገደ ፡ ካም ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነገደ ፡ ሴም ፡ እያሉ ፡
ይጠሩት ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ ነገደ ፡ ኩሽን ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡
የደቡብ ፡ ዓረብን ፡ ነገድ ፡ ሳባ ፡ ከናቢያው ፡ ሳባ/ ፡ ሰባ-ሻባ/ ፡ ጋር ፡
እያደባለቁ ፡ ይጽፉሉ ፡ ያኛው ፡ የሠራውን ፡ ለዚህኛው ፡ ይኸኛው ፡
የሠራውን ፡ ለዚያኛው ፡ እየሰጡ ፡ ሲጽፉም ፡ ይገኛሉ ። አንዳንድ ፡
ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ መልሰው ፡ የሚለዩበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

ለምሳሌ ፡ ዳዊት በ፸፭ኛው ፡ መዝሙር ፡ በአማርኛው ፡ ላይ ፡ የተርሴስና ፡ የደሴቶች ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ያገባሉ ፡ ካለው ፡ ቀጥሎ ፡ የሻባና፡ የሳባም፡ ነገሥታት፡ ገጸ፡ በረከት፡ ያቀርባሉ ፡ብሎ ፡ ለይቷል ። በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ዓረብኛ ፡ ፊደል ፡ ሰለሌለ ፡ ሻባ ፡ ያለውን ፡ ሳባ ፤ ሳባ ፡ ያለውን ፡ ደግሞ ፡ በዓረብ ፡ አገር ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፤ ነገሥተ ፡ ሳባ ፡ ወዓረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ፡ ብሎታል ። ይህም ፡ አጭር ፡ የዳዊትን፡ ቃል ፡ የዛሬ፡ መርማሪ ፡ ሊቃውንት ፡ በሰፊው ፡ ከመረመሩት ፡ ጋር ፡ ተገናኝቷል ። በኖብያ ፡ ውስጥ ፡ ከኩሽ ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ ሻባ ፡ ይባሉ ፡ እንደነበረ ፡ በርሱም ፡ ነገደ ፡ ሻባ ፡ የሚባል ፡ ዘር ፡ እንደነበረ ፡ ለመረዳት ፡ ሳባ ፡ ኖባ ፡ ከሚባለው ፡ ካገራችን ፡ ጽሑፍም ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙርም ፡ በቀር ፡ በኑብያ ፡ በ፺ኛው ፡ምቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ስሙና ፡ ሥራው ፡ በግብፃውያኑ ፡ ሐውልትና ፡ ብራና ፡ በትክክል ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ ግብፅን ፡ የገዛው ፡ ንጉሥ ፡ ሻባካ ፡ የሚባለው ፡ ስሙ ፡ ይገልጻል ።

በሻባ ፡ ላይ ፡ ካ ፡ የተጨመረበትን ፡ ምክንያት ፡ ሙሴ ፡ ብሩግሽ ፡ (BRUGSCH) የሚባሉት ፡ የጀርመን ፡ ሊቅ ፡ እኤቲዎፒካ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ካ ፡ በጥንታውያን ፡ የግብፆች ፡ የሰዋስው ፡ ሥርዓት ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ፡ ይኸውም ፡ ሻባ ፡ ካ ፡ ማለት ፡ የሻባ ፡ ማለት ፡ ነው ። የርሱም ፡ ተከታይ ፡ ልጁ ፡ መጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ካባቱ ፡ ሳይርቅ ፡ ሻባቶ ፡ ካ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እላይ ፡ እንዳልነው ፡ በኑብያ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ መንግሥት ፡ ሻባ ፡ (ሳባ) ፡ የሚባል ፡ ሲኖር ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣንም ፡ መገን ፡ በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የነበረው ፡ ወደ ፡ ዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜንም ፡ የዘለቀው ፡ ንግሥተ ፡ ሳባም ፡ የተጠራችበት ፡ የሳባ ፡ ዘር ፡ ለየብቻ ፡ መኖሩን ፤ ይኸም ፡ ሁለቱ ፡ እየተደባለቀ ፡ የጥንቱን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያስቸግራቸው ፡ እንደነበረ ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ።

እነዚሁ ፡ ሁሉ ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግብፃችም ፡ እስራኤሎችም ፡ ግሪኮችም ፡ ግማሾቹ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ የቀሩት ፡ ኢትዮጵያ ፡ እያሉ ፡ ሲጠሩን ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ የፖለቲካና ፡ ያገር ፡ ክፍል ፡ የምንገኘውን ፡ ኢትዮጵያውያኖችን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡



ከዛሬው ፡ ቱኒዚና ፡ ማሮክ ፡ ከሊቢያና ፡ ግብፅ ፡ ከፍልስጥኤም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የዛሬውን ፡ የዓረብንም ፡ የሱዳንንም ፡ በመካከል ፡ የሚገኘውን ፡ ያሁኑን ፡ የኛንም ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየለዩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየደባለቁ ፡ ነው ።

ይኸም ፡ እንደሙሉ ፡ ስሕተት ፡ እንዳይቆጠር ፡ በዙሪያችን ፡ ከሚገኙት ፡ ከነዚሀ ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ ዘራችን ፡ ልማዳችን ፡ ቋንቋችን ፡ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ እየተገናኘ ፡ ተደባልቆ ፡ በመኖሩ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ረኃብ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ነገድ ፡ ተሰዶ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ነገድ ፡ አገር ፡ ሄዶ፡ ይደባለቃል ። ከመካከላቸው ፡ አንድ ፡ ኃይለኛ ፡ የነገድ፡ አለቃ ፡ ተነሥቶ፡ ማስገበር ፡ ሲፈልግ ፡ የሌላውን ፡ አገር ፡ ምርኮ ፡ ይዞ ፡ ወደራሱ ፡ አገር ፡ ሲሔድ ፡ የራሱን ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ በወራሪነት ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ ሲተወው ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ ሁኔታ ፡ ሕዝብ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ሲዘዋወርና ፡ ሲደባለቅ ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ዘሩ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ጽሕፈቱና ፡ ቋንቋው ፡ መጠሪያ ፡ ስሙም ፡ ልማዱና ፡ ጥበቡም ፡ እየተደበላለቀና ፡ እየተዳቀለ ፡ ለመለየት ፡ ያስቸግራል። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ችግር ፡ ማለፍና ፡ መለየት ፡ የማይችል ፡ በሩቅ ፡ ያለ ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊ ፡ አገራችንን ፡ በደፈና ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብሎት ፡ ያልፋል ።

የዛሬ ፡ ጸሐፊና ፡ መርማሪም ፡ ነገሩን ፡ ላበጥር ፡ ብሎ ፡ ሲነሣ ፡ የዘመኑ ፡ ርቀት ፡ በዘመኑ ፡ የተደራጀው ፡ ጽሑፍ ፡ በማነሱ ፤ የፊደሉና ፡ የቋንቋው ፡ የባህሉና ፡ የልማዱ ፡ ድብልቅነት ፡ እየተደቀነበት ፡ ችግሩን ፡ በሙሉ ፡ ማለፍ፡ እያቃተው፡ በጥንታዊው ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሌላውም ፡ አገር ፡ የቀድሞ ፡ ታሪክ ፡ ቢሆን ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ በጽሑፍ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያቀርበው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ሞላ ፡ ከጐደሉ ፡ ከመሆን ፡ አይዘልም ።

እኛ ፡ የጉዳዩ ፡ ባለቤቶች ፡ ለሥራው ፡ ችላ ፡ ባልንበት ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የጻፉት ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ሞሪዮ ፡ ኩልቦ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ ካሜረር ፡ ባጅ ፡ እንደዚሁም ፡ ሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የጥንቱን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለማግኘት ፡ ከኛ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትና ፡

ክብረ ፡ ነገሥት ፡ ተፈላልገው ፡ የሚበቃቸውን ፡ ያህል ፡ ሲያጡ ፡
ስለኛ ፡ አገር ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ በ፲፱
ኛመት ፡ ውስጥ ፡ ግብፅን ፡ ከሚገዙት ፡ ከነበጥሊሞስ ፡ ቤተ ፡ መን
ግሥትና ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከሮማውያኖቹ ፡ ውስጥ ፡ አገር ፡ ለማየት ፡
ንግድ ፡ ለማግኘት ፡ የአገር ፡ ካርታና ፡ ታሪክ ፡ ልማድና ፡ ባህል ፡
ለማጠራቀም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ እየመጡ ፡ ሲመለሱ ፡
የተዉትን ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ መመርመር ፡ ይሔዳሉ ።

የነዚህም ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያብዛኞቹ ፡ ስም ፡ ኤራቶስቴን ፤
አናሲክራት ፤ አጋታርሺድ ፡ ጥሊን ፡ ስትራቦን ፤ ሲምኒድ ። ዲዮ
ዶር ፤ አርቴሚዶር ፤ ቶሎሚ ፤ ኮስማስ ፡ . . . ይባላል ። እነርሱም ።
ግማሾቹ ። የግሪክ ፡ ግማሾቹ ፡ የሮማ ፡ የቀሩትም ፡ የግብፅ ፡ ተወላ
ጆች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ዞረው ፡ በያገሩም ፡
ተጉዘው ፡ ያዩትን ፡ የተረኩበት ፡ መጽሐፍ ፡ ፔሪፕሎ ፡ ማሬ ፡ ኤሪት
ሬዎ ፡ ይባላል ። ትርጓሜውም ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ማለት ፡
ነው ። እንደዚሁም ፡ የስትራቦንና ፡ የቶሎሚ ፡ ጽሑፍ ፡ ያገር ፡ ካር
ታና ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ ጭምር ፡ ይተርካል ። በነዚህ ፡ ጸሐፊዎች ፡
አጠራር ፡ በአሁኒቱ ፡ ኢትዮጵያና ፡ በቀድሞዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡
(ኑብያ ፡ በያለበት ፡ በነገድ ፡ በቋንቋ ፡ እየተለያየ ፡ ለተቀመጠው ፡
ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ዝርዝር ፡ ገብተው ፡ ስም ፡ ሲሰጡ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡
ዳር ፡ በረዥም ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ በዋሻ ፡ ነዋሪ ፡ (ትሮግሎዲት) ፡
በዓባይ ፡ ዳር ፡ የሚኖሩትን ፡ ሲሆን ፡ በሊታ ፡ (ስትሩቲኦፋዥ) ፤
የቀረውንም ፡ በሚመገበው ፡ ምግብ ፡ ዓይነት ፡ የመልኩ ፡ ቅርጽ ፡
በሚሰጠው ፡ ዓይነት ፡ ዓሣ ፡ በሊታ ፤ ቀጭኔ ፡ መሳይ ፡ እያሉ ፡ ስይ
መውት ፡ ይገኛል ። የዚህን ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳይ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡
ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ላይ ፡ ስለምናገኘው ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡
እንመለስ ።

እነዚህን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ወደጐን ፡ ትተን ፡ ያገ
ራችን ፡ ጽሑፍ ፡ አገራችንን ፡ ወይም ፡ ያገራችንን ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡
እንደሚለው ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ፡ የቀረውን ፡ እንኳን ፡ በየአ
ጋጣሚው ፡ መንካቱ ፡ ባይቀር ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ደጋግሞ ፡ ሲጠራ ፡
የምናገኘው ፡ የመጀመሪያውን ፡ ሕዝብ ፡ ነገደ ፡ ካም ፤ በኋላ ፡



የመጣውን ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፤ ከባዕድ ፡ ግዛት ፡ ራሱንም ፡ ነገደ ፡
ካሙንም ፡ አወጣው ፡ ለማለት ፡ ነገደ ፡ አግዓዚ ፡ ሕዝቡን ፡ አግ
ዓዝያን ፤ አገሩን ፡ ብሔረ ፡ አግዓዚ ፡ ቋንቋውን ፡ ልሳነ ፡ ግዕዝ ፡
ሲለው ፡ እናገኛለን ።

ዓረብ ፡ መታወቅ ፡ ከዠመረ ፡ በኋላ ፡ በንግግሩም ፡ በጽሕ
ፈቱም ፡ ሐበሻ ፡ (ድብልቅ) ፡ ብሎን ፡ ይገኛል ። ግማሾቹ ፡ ደግሞ ፡
ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከሳባ ፡ ክፍል ፡ ግማሾቹ ፡
ሐበሳን ፡ የሚባሉት ፡ የኤርትራ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ በኢትዮጵያ ፡
በሜን ፡ ስለተቀመጠ ፡ ሐበሻ ፡ የሚባለው ፡ ስያሜ ፡ የመጣው ፡
ከነርሱ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አዋቂዎች ፡ ሞልተዋል ። ከዚህ ፡ በፊት ፡
ስማቸውን ፡ የጠቀስነው ፡ ምስተር ፡ ሪክማን ፡ (J. RYCKMANS)
የሳባውያን ፡ ታሪካዊ ፡ ጽሑፍ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ እንደ
ሚያስረዱት ፡ በዛሬው ፡ የመን ፡ ምዕራብ ፡ የሚገኘው ፡ ያገሩ ፡ ስም ፡
ሐበሳት ፡ ሰዎቹ ፡ ሐበሳን ፡ የሚባሉት ፡ ሐበሳ ፡ ከሚባል ፡ የነገድ ፡
አባት ፡ የወረዱ ፡ ከአገራቸው ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ተሻግረው ፡ በኢ
ትዮጵያ ፡ በሜን ፡ ተቀምጠው ፡ ሐበሻ ፡ የሚባለው ፡ ስም ፡ የመጣው ፡
ከነርሱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከሌሎቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ጋር ፡ ያረጋግጣሉ ።
ፓሪስ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ በሶርቦን ፡ የምሥራቅ ፡ ቋንቋ ፡ ትምህርት ፡
ቤት ፡ አማርኛ ፡ ከሚያስተምሩት ፡ ሊቅ ፡ ከማርሴል ፡ ኮሄን ፡ ጋር ፡
የዚህኑ ፡ ጉዳይ ፡ አንሥተን ፡ በንነጋገር ፡ እናንተ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡
ሐበሾች ፡ ሲሏችሁ ፡ ቅር ፡ ይላችኋል ፡ ማለትን ፡ ሰምቻለሁ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ እውነተኛ ፡ ስማችሁ ፡ ሐበሻ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ፡ ያሉ
ኝን ፡ እስታውሳለሁ ፡ ይኸንንም ፡ ከማለት ፡ ያደረሳቸው ፡ ሐበ
ሳን ፡ ከአገራቸው ፡ ከሐበሳት ፡ (ደቡብ ፡ ዓረብ) ፡ መጥተው ፡ በኢ
ትዮጵያ ፡ መቀመጣቸው ፡ እነርሱም ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ አንድ ፡
ክፍል ፡ መሆናቸውን ፡ በሳባውያን ፡ ፊደል ፡ ሳ ፡ የነበረው ፡ በኋላ ፡
በዓረብኛ ፡ ሳ ፡ ወደ ፡ ሻ ፡ ተለውጦ ፡ ሐበሻ ፡ በንባል ፡ የኖርነውን ፡
ደንበኛ ፡ ታሪክ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

በብሉይ ፡ ኪዳን ፤ በኖኅ ፡ ዘር ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሳባ ፡ እንዳሉ ፡ በትውልዱ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ እንመለከታለን ፡ (፩) ። አንደኛው ፡ የኖኅ ፡ ልጅ ፡ የካም ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ የኩሽ ፡ ልጅ ፡ ሳባ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሌላው ፡ ለመለየት ፡ ሳባ ፡ ሻባ ፡ ይሉታል ። ይኸውም ፡ የካሙ ፡ ነገድ ፡ የኑብያው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የነገድ ፡ አባት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ሳባ ፡ ኖባ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራል ። የሁለተኛው ፡ ትውልድ ፡ ደግሞ ፡ ኖኅ ፡ የካምን ፡ ወንድም ፡ ሴምን ፡ ሴም ፡ አርፋክስድን ፤ አርፋክስድ ፡ ሳላህን ፤ ሳላህ ፡ አቤርን ፤ አቤር ፡ ዮቅጣንን ፤ ዮቅጣን ፡ ሳባን ፡ ይወልዳል ። የዚህኛውን ፡ የሳባን ፡ ነገድ ፡ ነው ፡ በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ የካምን ፡ ዘሮች ፡ አሸንፎ ፡ ባለቤት ፡ ሆነ ፡ የምንለው ፡ ንግሥተ ፡ ሳባም ፡ ነገሠች ፡ የምትባለው ፡ በነዚሁ ፡ ነገዶች ፡ ላይ ፡ ነው ። ሐበሳን ፡ ሳባ ፡ ሂሚያሪት ፡ እየተባለ ፡ መለያየት ፡ የመጣውም ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ በትውልድ ፡ መበርከት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ የኩሹ ፡ ሳባ ፡ ( ሶባ ፡ ሻባ ፡ ) ከምሥራቅ ፡ መጥቶም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ግማሹ ፡ የርሱና ፡ ያባቱ ፡ የካም ፡ ወገኖች ፡ ተደባልቀው ፡ ባሁኒቱ ፡ ኢትዮጵያና ፡ በቀድሞዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኑብያ ፡ ሲኖሩ ፡ በኑብያ ፡ ያሉት ፡ ብዙውን ፡ ዘመን ፡ በነፃነት ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ በ፳፫ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ላይ ፡ በግብፅ ፡ ተገዙ ። በመጨረሻም ፡ ደግሞ ፡ በ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ እነዚሁ ፡ በግብፅ ፡ የተገዙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መልሰው ፡ ግብፅን ፡ ገዙ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ባሁኒቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚገኙት ፡ አግዓዝያን ፡ ወይም ፡ ሐበሳን ፡ የሚባሉት ፡ ሲመቻቸው ፡ በነፃነት ፡ ሳይመቻቸው ፡ ግብፅ ፡ በፊት ፡ ናፓታ ፡ በኋላ ፡ በየጊዜው ፡ እየወረራቸውና ፡ እየገበሩ ፡ በመካከላቸው ፡ ኃይለኛ ፡ ሲነሣ ፡ እየጠቀለላቸው ፡ ሲጠፉም ፡ በየነገዳቸው ፡ እየተከፋፈሉ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ወይም ፡ ቢበዛ ፡ ፪ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ኖሩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በግብፅና ፡ በኑብያ ፡ የአሶር ፤ የፋርስ ፤ የግሪክ ፤ የሮማ ፡ ገዥ ፡ እየተፈራረቀ ፡ የኖብያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡

(፩) ዘፍ ፡ ም ፡ ፲ ፡



ሲደክም ፡ በጐኑ ፡ ያለው ፡ የሐበሳት ፡ ወይም ፡ የአግዓዝያን ፡ ሕዝብ ፡ የአክሱምን ፡ መንግሥት ፡ እያቀና ፡ ተነሣ ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ መንግሥት ፡ የሮማና ፡ የቢዛንቲን ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ በያውራጃው ፡ ለሚገኘው ፡ ሕዝብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ መስጠቱ ፡ ሳይቀር ፡ ዋነኛውን ፡ መንግሥት ፡ አክሱም ፡ መሥርተው ፡ ጽሕፈት ፡ ሲያስቀርጹ ፡ ንጉሡ ፡ የአክሱም ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቡም ፡ አክሱማውያን ፡ እየተባሉ ፡ አገሩም ፡ ብሔረ ፡ አኩስም ፡ በሚል ፡ ይጠራ ፡ ጀመር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ግዕዝኛ ፡ አነጋገር ፡ የመጣ ፡ ከክርስትና ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የፊተኛው ፡ አነጋገርና ፡ ጽሑፍ ፡ ቀድሞ ፡ በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ሳሉ ፡ የሚጽፉበትና ፡ የሚነጋገሩበት ፡ የሳባ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ይኸም ፡ የሳባ ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ለግዕዙ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ደግሞ ፡ በአክሱሙ ፡ መንግሥት ፡ የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ሲሠለጥን ፡ በየሐውልታቸው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሳባውያን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባልሠለጠነው ፡ ግዕዝኛ ፡ ወይም ፡ ሁለቱ ፡ ግሪኩንና ፡ ሳባውን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እያደረጉ ፡ ሲያጽፉ ፡ የነበረው ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በየሐውልታቸው ፡ ላይ ፡ ይታያል ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከክርስትና ፡ በኋላ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ እላይ ፡ እንዳልነው ፡ ብሔረ ፡ አክሱም ፡ ንጉሠ ፡ አክሱም ፡ አክሱማውያን ፡ ሲል ፡ ይገኛል ። ይኸም ፡ ስያሜ ፡ በዘመኑ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ በአክሱሞቹ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያዊነትን ፡ ይልቁንም ፡ የሳባንና ፡ የሐበሳትን ፡ ስያሜ ፡ እያጠፋው ፡ ሳይሆን ፡ እያደበዘዘው ፡ ሔዷል ።

እያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ በጊዜውና ፡ በሥፍራው ፡ በነገዱ ፡ የየራሱን ፡ ከተማ ፡ ስም ፡ ናፓታ ፡ መርዌ ፡ አክሱም ፡ እያለ ፡ ይኸንኑ ፡ ስም ፡ በማድመቁ ፡ ጸሐፊም ፡ በዚሁ ፡ እየሠየመው ፡ የዋናውን ፡ የጥንታዊውንና ፡ የጠቅላላውን ፡ የኢትዮጵያዊነት ፡ ስም ፡ ሲዘነጋ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር ። ከጸሐፊዎችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ለወዲህኛው ፡ በፊት ፡ የሐበሳትን ፡ በኋላም ፡ የአክሱምን ፡ ስም ፡ እየሰጡ ፡ ኢትዮጵያዊነትን ፡ ለኑብያ ፡ (ለናፓታና ፡ ለመርዌ ፡ ) የሚሰጡ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደሆሜርም ፡ እንደ ሄሮዶትም ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያዊነት ፡ ስም ፡ ለናፓታና ፡ ለመርዌ ፡ ብቻ ፡ ሊወሰን ፡ አይገባም ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡ መብረድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በፍጹም ፡ ሲጠፋ ፡ በኛ ፡ በዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከ፫፻ና ፡ ከ፬፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ መንግሥት ፡ ከአክሱም ፡ ላስታ ፤ ከላስታ ፡ ሸዋ ፤ ከሸዋ ፡ ጐንደር ፡ በተዛወረበት ፡ ጊዜ ፡ . . . ሐበሻ ፡ . . . . . . . የሚባለው ፡ ስም ፡ ጣልቃ ፡ መግባቱ ፡ ባይቀርም ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስያሜ ፡ በዜና ፡ መዋዕልም ፡ በገድልና ፡ በድርሳንም ፡ ከደብዳቤም ፡ እንደገና ፡ ይነግ ፡ ዠመር ። በ፱፻ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ድልነዓድ ፡ ለኑብያው ፡ ንጉሥ ፡ ለጊዮርጊስ ፡ ደብዳቤ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሲጽፍ ፡ ስሙን ፡ ሳይጠቅስ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብሏል ። የላሊበላና ፡ የነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትም ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲላቸው ፡ ይገኛል (፩) ።

ከውጪ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ውስጥ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አራተኛው ፡ ፓውሊ ፡ (ጳውሎስ) ፡ በ፩ሺ ፡ ፭፻ ፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለአፄ ፡ ገላውዴዎስ ፤ ፊልጶስ ፡ ፪ ፡ የኢስፓኝ ፡ ንጉሥ ፡ ለአፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ደብዳቤ ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ሲጽፉ ፡ (IMPERATOREM AETHIOPIAE) የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እያሉ ፡ የጻፉት ፡ በካሬ ፡ በሰበሰበው ፡ የፖርቱጋዝና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግንኙነት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግቦ ፡ ይገኛል ።

ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ጥንት ፡ በሰፊው ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አቅፎ ፡ ቢገኝም ፡ ግሪኮቹ ፡ እነሆሜር ፡ እነሄሮዱቱስ ፡ እስራኤሎቹ ፡ እነዳዊት ፤ እነኢሳይያስ ፡ የመሠረቱትን ፡ ስያሜ ፡ ሳይለቅ ፡ ኩሽ ፤ ሐበሻ፤በቀሻ ፡ ነዋሪ ፡ የሚባለውን ፡ ሁሉ፡ደምስሶ ፡ በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ በፖለቲካና ፡ በወሰን ፡ ተከልሎ ፡ አሁን፡ላለው፡ሕዝባችን ፡ ኢትዮጵያዊነት ፡ የግሉ ፡ መጠሪያ ፡ ሆኖ ፡ መቅረቱን ፡ እንመለከታለን ። ይኸም ፡ ሲሆን፡ የሳባውያን ፡ የሐበሳን ፡ ነገድ ፡ ዘሮች ፡ መሆናችንን፡ ሳንረሳ ፡ ሀበሻ ፡ መባልንም ፡ ሳንጠላ ፡ ነው ።

(፩) ያፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጕንዘልማን ፡ ያሳተመው ፡ ገጽ ፡ ፪ ፡ ፵፮ ፡ ፵፱ ። ያምደ ፡ ጽዮን ፡ ታሪክ ፡ ገዎል ፡ ፔሩሾ ፡ ያሳተመው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴፰ ። በካሬ ፡ X ገጽ ፡ ፻፲፰ ፡— ፻፲፱ ።



## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### የቀድሞው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጽሑፍ ፡ ሁኔታ ።

የአክሱሙ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ ከፊደሉ ፡ ከሥልጣኔው ፡ ከልማዱ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሁም ፡ ያንጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ የኑብያ ፡ ሕዝብ ፡ የሥልጣኔው ፡ መደብ ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የነበረው ፡ በሃይማኖትም ፡ በሥልጣኔም ፡ በልማድም ፡ ከግብፅ ፡ ሕዝብ ፡ የተገናኘ ፡ ነበር ። ባጭሩ ፡ የተገናኘ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ የኑብያው ፡ ሕዝብ ፡ ፊደሉና ፡ ሃይማኖቱ ፡ የዋነኞቹና ፡ የሥልጡኖቹ ፡ ወገኖች ፡ የግብፅ ፡ ፊደል ፡ (ሂዬሮግሊፍ) የሚባለው ፡ ነበር ። በሃይማኖትም ፡ ረገድ ፡ የግብፃውያንን ፡ አማልክት ፡ እነአሞንን ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ። ተራው ፡ ባለገር ፡ ደግሞ፡ ከግብፅ ፡ ባሳገር ፡ ከወዲህም ፡ ከዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባላገር ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ከፍጡራን ፡ የመነጨ ፡ የፍጡርና ፡ የመናፍስት ፡ አምልኮ ፡ ነበረው ።

ስለዚህ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ አክሱም፡ ሲገን ፡ (ሲነግ) ፡ ሃይማኖትንና ፡ ፊደልን ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ይዞ ፡ የመጣውን ፡ ለዛሬው ፡ ፊደላችን ፡ አባት ፡ የሆነውን ፡ የሳባውያንን ፡ ፊደል ፡ በግዛቱ፡ ስለ፡ አስፋፋ ፡ በኋላም ፡ ይኸው ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተለውጦ፡ ዛሬ ፡ ጽሑፉ ፡ ሁሉ ፡ በዚያው ፡ በመጠኑ ፡ ስለአክሱም ፡ መንግሥት፡ ሲናገር ፡ ኑብያን ፡ እንደባዕድ ፡ በመመልከት ፡ በጕዳዩ ፡ ሳያገባው ፡ ቀርቶ ፡ ገዛነው ፡ አስገበርነው ፡ ብሎ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ ስለኑብያ ፡ መንግሥት ፡ ሁኔታ ፡ በሰፊው ፡ የሚናገር ፡ ምንም፡ ያህል ፡ የለም ። የኑብያውም ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የተፈጸመው ፡ በሂዬሮግሊፍ ፡ የተጻፈው ፡ ታሪኩ ፡ እንደቴብና ፡ እንደ ፡ መምፊስ ፡ ታሪክ ፡ ተደብቆ ፡ ሲኖር ፡ ሻምፖልዮን ፡ የፊደሉን ፡ ምሥጢር ፡ ከፈታው፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ መርማሪዎች ፡ ጥንታዊውን ፡ የግብፅን ፡ ታሪክ ፡ እየመረመሩ ፡ ሲያወጡ ፡ የኑብያውም ፡ ታሪክ ፡ እየተመረመረ ፡ መው

ጣት ፡ ዠመረ ። ኑብያን ፡ ከግብፅ ፡ ጋር ፡ ደርበው ፡ ሲገዙ ፡ የኖሩት፡ ፈርዖኖች ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያውያኑ ፡ ደግሞ ፡ ከኑብያ ፡ ተነሥተው ፡ ግብፅን ፡ በሙሉ ፡ እስከ ፡ ሊቢያ ፡ እስከፓለስቲን ፡ የገዙት ፡ የግብፅ ፡ ፳፭ኛ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ) ፡ ተብለው ፡ የተመደቡት ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ነገሥታት ፡ የናፒያንኪ ፡ የነታርሐቃ ፡ ታሪክ ፡ ከሐውልትና ፡ ከጣዖታቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ እየተተረጐመ ፡ ይወጣ ፡ ዠመር ። ይኸንንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሥፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እናገኘዋለን ።

የሆነ፡ ሆኖ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የጥንታዊ ፡ ግዛት ፡ ነበር ፡ አስቀድሞ ፡ ሲገዙ ፡ ቢኖሩም ፡ በኋላ ፡ መልሰው ፡ ግብፅን ፡ ገዝተዋል ፡ እያልን ፡ ስምንመካባቸው ፡ ስለ ፡ ኑብያ ፡ ሕዝቦች፡ በተለይ ፡ ስለ፡ ናፓታና ፡ ስለመርዌ ፡ ደንበኛ ፡ ታሪክ ፡ የሚናገር ፡ በግዕዝም ፡ በአማርኛም ፡ የተጻፈው ፡ በልክ ፡ ነው ። በዮሐንስ ፡ መደብር ፡ ስለ ፡ ሰባቆን ፡ (ሻባካ) ፡ ስለ ፡ ንግሥት ፡ ሕንደኬና ፡ ስለ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ግንኙነት ፡ በትንሹ ፡ ሲኖር ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ ሰፊ ፡ የኑብያ ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ለዚያን ፡ ዘመንም ፡ ለዛሬዪቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የተዳፈነ ፡ ጨለማ ፡ ነበር ። የዚህ ፡ የኑብያ ፡ ታሪክም ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ከናፓታና ፡ ከመርዌ ፡ ዝቅ ፡ ብሎም ፡ ከኩቡብ ፡ (ካርናቅ) ፡ ከዙሪያውም ፡ ከየሐውልቱ ፡ ከየመቅደሱ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ፍራሽ ፡ ቢገኝም ፡ በግብፆቹ ፡ ጥንታዊ ፡ ፊደል ፡ የተጻፈ ፡ ሆኖ ፡ የሚተርከውም ፡ ስለ ፡ ኑብያ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የናፓታንና ፡ የመርዌን፡ መንግሥት፡ እንጂ! አሁን ፡ ከያዝነው ፡ ፊደልና ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ ተወራራሽ ፡ ስለሆነው ፡ ስለአክሱም ፡ አይናገርም። በዘርና ፡ በአንዳንድ ፡ ልማድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡ የኑብያው ፡ ሥልጣኔና ፡ ታሪክ ፡ ሃይማኖቱም፡ ከአክሱም ፡ ሥልጣኔ ፡ ጋር ፡ የማይገናኝ ፡ ነው ፤ ቢባልና ፡ የኑብያውን ፡ ችላ ፡ ብንልም ፡ ስለራሱ ፡ ስለአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ እንኳን ፡ በታሪክ ፡ ነገሥትም ፡ በክብረ ፡ ነገሥትም ፡ በብዕለ ፡ ነገሥትም ፡ በነገሥታቱና ፡ በጳጳሳቱ ፡ ድርሳንና ፡ ገድል ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውም፡ ቢሆን ፡ በደረቅ ፡ ታሪክ ፡ ረገድ ፡ የሚሰጠን ፡ ጥቅም ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይኸውም ፡



ዛሬ፡ የሚገኘው ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለው ፡ ጽሑፍ ፡ የጥንቱ ፡ በዮዲት ፡ መነሣትና ፡ በሌላውም ፡ ምክንያት ፡ ጠፋፍቶ ፡ እንደገና ፡ መዘጋጀት ፡ የቻለው ፡ ከ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ ከአፄ፡ ዓምደ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በመሆኑ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ሞላ፡ ከጐደል ፡ የመንግሥትም ፡ የመንፈሳዊም ፡ ታሪክ ፡ ይገኛል ። ግልባጩ ፡ ሳይሆን ፡ አንዳንድ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጽሑፍ፡ በይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጊዜ ፡ የተዘጋጀ ፡ አለ ። ከዚሁ ፡ ጽቱ፡ ብሔረ ፡ ኦሪት ፡ የሚባለው ፡ ዛሬ፡ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት፡ የሚገኘው፡ እንደብርቅ ፡ ይታያል ።

ከአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ያለፈውን ፡ የላስታና ፡ ይልቁንም ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ መነኰሳትና ፡ እጨጌዎች ፡ የመንግሥቱም ፡ ጸሐፊዎች፡ ሲያያዝ ፡ በወሬ፡ የመጣውን ፡ ከራሳቸውም ፡ እየጨመሩ ፡ ሲያዘጋጁ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የአክሱምና ፡ የላስታ ፡ ንጉሥ ፡ በዘመኑ ፡ የፈጸመውን ፡ አጫጭር ፡ የጦርነትና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ሲያዘጋጁ ፡ በየዘመኑ ፡ የነበረውን ፡ ልማድና ፡ አስተዳደር ፡ የዕቃና፡ የመማሪያ ፡ የሸቀጥና ፡ የገንዘቡን ፡ ዓይነት ፡ ሌላውንም ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለውንም ፡ ጽፈው ፡ ለማቅረብ ፡ የዘመኑ ፡ የጸሐፊነት ፡ ልማድ ፡ አላስቻላቸውም ። ጽፈው ፡ ጠፍቶም፡ እንደሆን ፡ አይታወቅም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ዓይነት ፡ በደንብና ፡ በዝርዝር ፡ ተጽፎ ፡ ወደ ፡ ጊዜያችን ፡ የተላለፈ ፡ አላገኘንም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ፈረንጆች ፡ የኛን ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ደረጃ ፡ ከጓደኞቻችን፡ አገሮች ፡ ከዓረብና ፡ ከግብፅ ፡ ከፋርስና ፡ ከግሪክ ፡ በዝቅተኛነት ፡ ለመገመት ፡ ግዴታ ፡ ሆኖባቸዋል ።

በዚሁ ፡ ባለን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ፡ እንደምንመለከተው፡ ከአዳም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ ከሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ ይሰጥና ፡ ከዚያ ፡ ጣልቃ ፡ እያገባ፡ የንግሥተ፡ ሳባንና ፡ የሰሎሞንን ፡ ግንኙነት ፡ የቀዳማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ልደትና ፡ ንግሥ ፤ የአብርሃንና ፡ የአጽብሐን ፡ ትንሽ ፡ ታሪክ ፡ ከአቡነ ፡ ሰላማ፡ (ከሣቴ ፡ ብርሃን) ፡ ጋር ፡ ያፄ ፡ ካሌብን ፡ ከአባ ፡ ጰንጠሌዎን ፤ ያፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀልን ፡ ከያሬድና ፡ ከአቡነ ፡ አረጋዊ፡ ጋር ፡ እያያያዘ፡

ይጽፋል ። ከዚያ ፡ የላሊበላንና ፡ የነአኩቶ ፡ ለአብን ፡ የይኩኖ ፡ አምላክንና ፡ የአቡን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይተረካል ። አተራረኩም ፡ በደረቅ ፡ ታሪክና ፡ ወይም ፡ ለታሪኩ ፡ ብቻ ፡ ቀጥተኛ ፡ ሐተታ ፡ በመስጠት ፡ ሳይሆን ፡ በመንፈሳዊና ፡ በተአምራታዊ ፡ አገላለጽ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ይኸም ፡ እንደማናቸውም ፡ ሥራ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተለመደና ፡ የማያስነቅፍ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አላይ ፡ እንዳመለከት ነው ፡ ያብዛኞቹ ፡ ነገሥታት ፡ ከስማቸው ፡ ዝርዝር ፡ በቀር ፡ በዕለት ፡ ተግባራቸው ፡ የፈጸሙት ፤ የፍርዱ ፡ የሥርዓቱ ፡ የጦርነቱ ፡ የንግዱ ፡ አኳኋን ፡ የሸቀጡ ፡ የጦር ፡ መሣሪያው ፡ ለኑሮና ፡ ለትዳር ፡ ወንዱና ፡ ሴቱ ፡ የሚገለገሉበት ፡ ዕቃና ፡ መሣሪያ ፡ በአማርኛ ፡ እንኳ ፡ ተስፋ ፡ ለማድረግ ፡ የራሱ ፡ የቋንቋው ፡ አለመኖር ፡ አያስችልም ፡ ብንል ፡ በዘመኑ ፡ በሚሠራበት ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ በቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ቋንቋ ፡ በግዕዝ ፡ እንኳ ፡ አይገኝም ። ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ በብርቅ ፡ ቢገኝም ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ከግማሽ ፡ ገጽ ፡ ስለማይደርስ ፡ ለዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊና ፡ አንባቢ ፡ የማያጠግብ ፡ ይሆናል ።

–ክርስትናን ፡ ጌታችን ፡ ከመሠረተው ፡ ሐዋርያትና ፡ ሰማዕታት ፡ በያለበት ፡ ካስፋፉትና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያም ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ካገቡት ፡ ወዲህ ፡ እንደዛሬው ፡ ዘመን ፡ ልማድ ፡ አላይ ፡ የዘረዘርነውን ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ የዕቃና ፡ የመሣሪያ ፡ ዓይነት ፡ በዝርዝር ፡ ለመጻፍ ፡ አባቶቻችን ፡ አሳባቸውን ፡ ማድከም ፡ አልፈለጉም ። ዛሬ ፡ የፈለግነውን ፡ ያህል ፡ ለኋላ ፡ ትውልድ ፡ ይጠቅመዋል ፡ ብለው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እምብዛም ፡ የተገነዘቡት ፡ አይመስልም ። በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ አዲሱ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ስለሐዋርያትና ፡ ስለሰማዕታት ፡ ስለመላእክትና ፡ ስለጻድቃን ፡ ከነዚሁ ፡ ጋር ፡ ስለተያያዙት ፡ ነገሥታት ፡ በመንፈሳዊ ፡ አያያዝ ፡ ብቻ ፡ ለመጻፍና ፡ ለመድከም ፡ የዘመኑ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሆኑት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ አባባቸውን ፡ በሙሉ ፡ ወደዚህ ፡ ሥራ ፡ አዘነበሉ ። የማይካደውን ፡ ትጋታቸውንና ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ለዚሁ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ጽሕፈት ፡ ሠዉት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በገዳማትና ፡ በየአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ውስጥ ፡



በውጪ ፡ አገር ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ የገድል ፡ የድርሳን ፡ የመልካመልክ ፡ የጸሎት ፡ የምንና ፡ መጻሕፍት ፡ በጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ብራና ፡ በሚያማምር ፡ ጽሕፈትና ፡ ድጉስ ፡ በደመቁ ፡ ሐረጎች ፡ አጊጦ ፡ ሲገኝ ፡ የታሪኩ ፡ የመሣሪያውና ፡ የዕቃው ፡ የሥርዓቱ ፡ ጽሑፍ ፡ አንሶና ፡ ጐድሎ ፡ ይገኛል ። አባቶቻችን ፡ ይኸኛውን ፡ ሥራ ፡ ወደሚያልፍ ፡ ወደሥጋዊ ፡ ወደምድራዊ ፡ ስለቆጠሩት ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ብቻ ፡ አበረከቱልን ።

ስለዚህ ፡ የታሪኩ ፡ ወገን ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ ችላ ፡ ስለተባለ ፡ ዛሬ ፡ ታሪክ ፡ እያለን ፡ የታሪክ ፡ ድኃ ፡ ሆነን ፡ ስንኖር ፡ እኛም ፡ ራሳችን ፡ በራሳችን ፡ የራሳችንን ፡ ታሪክ ፡ ቆፍረን ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ ከቆመው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ለመገልበጥና ፡ ለመረዳት ፡ ስለአቃተን ፡ ወይም ፡ ስለአላሰብንበት ፡ የዚህ ፡ ሥራ ፡ ልማድ ፡ ያላቸው ፡ ለታሪክ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ የቻሉ ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አፍሪካን ፡ ለማየት ፡ አደን ፡ ለማደን ፡ ታሪክ ፡ ለመመርመር ፡ በየምክንያቱ ፡ ካገራቸው ፡ ሲወጡና ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ሲመጡ ፡ በአክሱምና ፡ በዙሪያው ፡ ካለው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጽሑፍ ፡ እየቀዱ ፡ እየተረጐሙ ፡ የታሪካችንን ፡ ብልጭታ ፡ አሳዩን ። እነዚህም ፡ እንደነጀምስ ፡ ብሩስ ፤ ኤድዋርድ ፤ ሩፔል ፤ ሀንሪ ፡ ሳልት ፤ ኮንቲ ፡ ሮሲኒና ፡ ሌሎችም ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ እየተነጣጠሉ ፡ የተቻላቸውን ፤ ለየብቻ ፡ በጽሑፍ ፡ ገልጸው ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስሜን ፡ ጸሐፊ ፡ ፎቶግራፍ ፡ አንሺ ፡ ቆፋሪ ፡ ፕላን ፡ ሠሪ ፡ ሆነው ፡ ባንድ ፡ ጓድ ፡ የመጡት ፡ እነሊትማን ፡ በአክሱምና ፡ በሌላም ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቆሞና ፡ ወድቆ ፡ ካገኙት ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ያገኙትን ፡ የሳባ ፡ የግሪክ ፡ የግዕዝ ፡ ጽሑፍ ፡ እየቀዱ ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታም ፡ በቁፋሮ ፡ እያገኙ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ አዘጋጁ ። ደች ፡ አክሱም ፡ ኤክስፔዲሽን ፡ (DEUTSCHE AXUM EXPEDITION) የሚባለውን ፡ በአራት ፡ ቮሊም ፡ በጀርመን ፡ ቋንቋ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የታተመውን ፡ መጽሐፍ ፡ መመልከት ፡ ነው ። የጀርመንን ፡ ቋንቋ ፡ ለመረዳት ፡ እንደኔ ፡ ያቃተው ፡ ሰው ፡ በአራተኛው ፡ ቮሊም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ከየሐውልቱ ፡

በቀጥታ ፡ የተወሰደውና ፡ የታተመው ፡ የሳባውና ፡ የግዕዙ ፡ ጽሑፍ ለታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል ።

ከነርሱ ፡ የተረፈውን ፡ ደግሞ ፡ እነሆ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ የአርኬዎሎጊ ፡ ሠራተኞች ፡ በኅብረት ፡ በአክሱምና ፡ በዙሪያው ፡ እየተፈላለጉ ፡ አንዳንድ ፡ የተነጣጠለ ፡ ታሪካዊ ፡ ዕቃ ፡ ማግኘታቸውን ፡ አይተናልና ፤ ድካማቸው ፡ በመጨረሻ ፡ ፍሬ ፡ አግኝቶ ፡ የተደበቀና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የደከሙት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያላገኙት ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳለ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እንዲያመጡልን ፡ እንመኛለን ።

እስከዚያ ፡ ግን ፡ ሥራ ፡ ሳንፈታ ፡ እስካሁን ፡ ከተገኘው ፡ የሐውልትና ፡ ያብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ከገድሉና ፡ ከድርሳኑ ፡ ውስጥ ፡ በትዕግሥት ፡ እየለቀምን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የዛሬው ፡ ሕዝባችን ፡ በሚናገረው ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ አብራርተን ፡ ለመጻፍ ፡ ዓላማችን ፡ ሆኖ ፡ እነሆ ፡ እማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነን ፤ ሐውልትና ፡ አጭሩ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ አብዛኛው ፡ የታሪክ ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ሲያገለግል ፡ ገድሉና ፡ ድርሳኑ ፤ በሙሉ ፡ የሚጽፈው ፡ ያንድ ፡ ጻድቅ ፡ ወይም ፡ መልአክ ፡ ታምራታዊ ፡ ታሪክ ፡ ቢሆንም ፡ ከዚሁ ፡ ከመንፈሳዊ ፡ እነጋገሩ ፡ ውስጥ ፡ የመልአኩና ፡ የጻድቁ ፡ ወዳጅ ፤ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ንግሥት ፡ መስፍን ፡ ወይም ፡ መኰንን ፡ ስማቸው ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ ይገኛል ። ያንዳንዱም ፡ ታሪካዊ ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ አይጠፋበትምና ፡ እነዚህን ፡ ከየቦታው ፡ አግኝቶ ፡ ለመልቀም ፡ ሰፊውን ፡ ረዥሙን ፡ መንፈሳዊ ፡ ንግግር ፡ በትዕግሥት ፡ ማንበብ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉም ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ ሳባና ፡ እንደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ አብርሃ ፡ አጽብሐ ፡ እንደ ፡ ላሊበላና ፡ እንደ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ላሉት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አብዛኞቹ ፡ የአክሱም ፡ የላስታ ፡ ነገሥታት ፡ ገድልና ፡ ድርሳን ፡ ያልተጻፈላቸው ፡ ስላሉ ፡ ከስማቸው ፡ ዝርዝር ፡ በቀር ፡ ታሪካቸው ፡ እየተቋረጠ ፡ መቅረቱ ፡ ነው ። የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ ዝርዝር ፡ ማግኘትም ፡ ተስፋ ፡ የለም ። እንኳን ፡ ታሪካቸው ፡ ወደፊት ፡ በሥፍራው ፡ እንደምናስረዳው ፡ የነገሥታቱ ፡ ስማቸውና ፡ የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ እየተፋለሰ ፡ ያስቸግራል ።



እንደዚሁ ፡ ሆኖ ፡ አሁን ፡ ጥንታዊውን ፡ የኑብያን ፡ መንግሥት ፡ ቀጥሎ ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ ስንነሣ ፡ ከኛ ፡ ወገን ፡ ጽሑፍ ፡ ሲያጥርብን ፡ በግድ ፡ የጥንት ፡ የግሪክና ፡ የሮማ ፡ የግብፅ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ መርማሪዎች ፡ እያዩም ፡ በወሬም ፡ እየጻፉ ፡ ለዛሬ ፡ ጸሐፊ ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ተተርጉሞ ፡ ሊነበብ ፡ ከቻለው ፡ ወደ ፡ መፈለስግ ፡ መሔድ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

ስለዚሁ ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ወደፊት ፡ የምናነበው ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ የኑብያ ፡ ታሪክ ፡ ከግብፅ ፡ ተያይዞ ፤ የአክሱሙ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ተዛምዶ ፡ ለአሁኑ ፡ መንግሥታችንም ፡ ለሥልጣኔውም ፡ ለፊደሉም ፡ ለቋንቋውም ፡ ለዘሩም ፡ ለልማዱም ፡ ሳባና ፡ ሐበሳን ፡ የመጡበት ፡ ይኸው ፡ ደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መሆኑን ፡ በበሬው ፡ እናያለን ። ለዛሬው ፡ ሥልጣኔያችንና ፡ ፊደላችን ፡ ቋንቋና ፡ ልማዳችን ፡ አባት ፡ ያልሆነውን ፡ የኑብያን ፡ ታሪክም ፡ በበሬው ፡ ስንመለከት ፡ ከአክሱም ፡ ጋር ፡ የልዩነቱን ፡ ወይም ፡ የግንኙነቱን ፡ መጠን ፡ አንባቢ ፡ ራሱ ፡ እንዲገነዘበውና ፡ የራሱን ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ጭምር ፡ ነውና ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ስለኢትዮጵያና ፡ ስለግብፅ ፡ ቅድሚያ ፡ ስለነገደ ፡ ካምና ፡ ስለነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ብናምነውም ፡ ብንጠራጠረውም ፡ እስካሁን ፡ በየመጽሐፉ ፡ ስለሚገኙ ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ ስለኑብያውና ፡ ስለአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ልዩነትና ፡ ግንኙነት ፡ በየምዕራፉ ፡ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ባገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኘው ፡ የነገደ ፡ ካምና ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ አመሠራረት ― የነገሥታቱ ፡ የተለመደ ፡ ዝርዝር ፡ ―<br>
በውጪ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡<br>
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድና ፡ ልማድ ።

ባ፩ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የእስራኤልና ፡ የግሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነሙሴ ፤ እነሆሜር ፤ እነሄሮዶቱስ ፡ ነቢያቱ ፡ እነ ኢሳይያስ ፡ ይህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘር ፡ በኩሽ ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ መውረዱ ፡ ሲታወቃቸው ፡ እንደግብፃውያን ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ብኋላ ፡ መጥቶ ፡ በተደባለቀበት ፡ ምክንያት ፡ የፊም ፡ ዘርነቱ ፡ ሲሰማቸው ፡

የሳባ ፡ አገር ፡ ይሉታል ። ስለዚህ ፡ ከነሱ ፡ ወዲህ ፡ የተነሣው ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በስፋው ፡ ግዛቱ ፡ የካምና ፡ የሴም ፡ ድብልቅ ፡ ዘር ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ በዚሁ ፡ ጽሑፉን ፡ ሲቀጥል ፡ ይኸን ፡ እያያዘ ፡ የቅርብ ፡ ዘመን ፡ ደንበኛ ፡ መርማሪዎች ፡ እነዮሴፍ ፡ ሐለቪ ፡ እነግላጸር ፡ እነኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ አጽድቀውታል ።

ከኛም ፡ ወገን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለነገደ ፡ ካም ፡ (የኩሽ ፡ አባት) ፤ ስለነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ስለመደባለቁም ፡ ይጽፋል ። የሁለቱንም ፡ ነገድ ፡ የነገሥታት ፡ ስምና ፡ የነገሡበትን ፡ ዘመን ፡ ዘርዝሮ ፡ ይጽፋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እስካሁን ፡ እየተጻፈ ፡ የቆየውን ፡ ከመጻፍ ፡ በቀር ፡ ስለስማቸው ፡ ዝርዝር ፤ ስለቅደም ፡ ተከተላቸው ፡ ስለዘመኑ ፡ ትክክልነት ፡ ለማመንም ፡ ለመካድም ፡ የዘመኑ ፡ ርቀትና ፡ የማስረጃው ፡ ጕድለት ፡ አያስችለንም ። ሐተታም ፡ ለመስጠት ፡ በመጠኑ ፡ ብንፈልግ ፡ የእንዚህ ፡ የነገሥታቱ ፡ ዝርዝር ፡ በኑብያ ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የነበሩት ፡ የኩሽ ፡ ዘር ፡ የሆኑት ፡ ነገሥታት ፡ በዓረብ ፡ አገርና ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተሻገሩት ፡ የሳባ ፡ ነገሥታት ፡ ተደባልቀው ፡ የተጻፉ ፡ ይመስላል ። ለምሳሌ ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ዘር ፡ ከሚላቸው ፡ ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ አምስተኛ ፡ የሆነውን ፡ አሜን ፡ ሖቴብ ፡ ይላል ። አሜን ፡ ሖቴብ ፡ አጠራሩ ፡ ግብፃዊ ፡ ያም ፡ ቢቀር ፡ የናፓታ ፡ የኩሽ ፡ እንጂ ፡ የሳባ ፡ አጠራር ፡ አይደለም ። በ፲፭፻፹ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ አሜን ፡ ሖቴብ ፡ አንደኛ ፡ የሚባል ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አጠራር ፡ በስሕተት ፡ መድረሱ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በሞግዚነት ፡ ተወስዶ ፡ እንደሆነ ፡ እናውቅም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ ወጥቶ ፡ የተዘጋጀው ፡ ከአዳም ፡ የወረደው ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ እንደሚያሳየን ፡ መሠረቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ሆኖ ፡ ከዚያ ፡ ያገራችን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሁሉ ፡ አጭር ፡ መነሻ ፡ ጨምረው ፡ በየመጽሐፋቸው ፡ የሚዘረዝሩት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ለኖኅ ፤ ሴም ፤ ካም ፤ ያፌት ፡ የሚባሉ ፡ ፫ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። ከነዚሁ ፡ ካም ፡ ኩሳን ፡ (ኩሽን) ፡ ምሥራይን ፤ ፋጥን ፤ ከነዓንን ፡ ይወልዳል ። በፋንታው ፡ ኩሳ ፡ ( ኩሽ ) ፡ ሳባ ፡ ሐዊላ ፤ ሰጥታም ፡



ረዕማ ፤ ነምሩድ ፡ የሚባሉትን ፡ ፭ ፡ ልጆች ፡ ወልዶ ፡ የነርሱ ፡ ዘሮች ፡ በርክተው ፡ እስከ ፡ ኑብያ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አቅንተው ፡ ሲኖሩ ፡ ለነርሱም ፡ እስከ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ መምጣት ፡ ድረስ ፡ ፳፪ ፡ ነገሥታት ፡ ነበርዋቸው ፡ ይልና ፡ ስማቸውንና ፡ የነገሡበትን ፡ ዘመን ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ያከታትላል ።

| ተራ ፡ | ስ ም ፡ | የግዛት ፡ ዘመን ፡ | ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ከክር ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ሰጥታህ ፡ (ሳቢታ) ፡ | ፵ | ፪ሺ፭፻፶፩—፪ሺ፭፻፲፩ |
| ፪ | ኤሌክትሮን ፡ | ፵ | ፪ሺ፭፻፲፩—፪ሺ፬፻፸፩ |
| ፫ | ነቢር ፡ | ፵ | ፪ሺ፬፻፸፩—፪ሺ፬፻፴፩ |
| ፬ | አሜን ፡ አንደኛ ፡ | ፳፩ | ፪ሺ፬፻፴፩—፪ሺ፬፻፲ |
| ፭ | ነሕሴት ፡ ናይስ ፡ | ፬ | ፪ሺ፬፻፲—፪ሺ፬፻፮ |
| ፮ | ታርኪም ፡ | ፳፱ | ፪ሺ፬፻፮—፪ሺ፫፻፸፯ |
| ፯ | ሳባ ፡ ፩ኛ ፡ | ፵ | ፪ሺ፫፻፸፯—፪ሺ፫፻፴፯ |
| ፰ | ሶፋሬድ ፡ | ፵ | ፪ሺ፫፻፴፯—፪ሺ፪፻፺፯ |
| ፱ | አስክንዲ ፡ | ፳፭ | ፪ሺ፪፻፺፯—፪ሺ፪፻፸፪ |
| ፲ | ሆህይ ፡ ስጥዎ ፡ | ፵፭ | ፪ሺ፪፻፸፪—፪ሺ፪፻፳፯ |
| ፲፩ | አህያጥ ፡ | ፳ | ፪ሺ፪፻፳፯—፪ሺ፪፻፯ |
| ፲፪ | አድጋስ ፡ | ፵ | ፪ሺ፪፻፯—፪ሺ፩፻፷፯ |
| ፲፫ | ባኩንዶን ፡ መሊስ ፡ | ፳፭ | ፪ሺ፩፻፷፯—፪ሺ፩፻፵፪ |
| ፲፬ | ማንቱራይ ፡ ሀቀቢ ፡ | ፵፭ | ፪ሺ፩፻፵፪—፪ሺ፺፯ |
| ፲፭ | ራክሁ ፡ ድድሜ ፡ | ፵ | ፪ሺ፺፯—፪ሺ፶፯ |
| ፲፮ | ሶቢ ፡ አንደኛ ፡ | ፵ | ፪ሺ፶፯—፪ሺ፲፯ |
| ፲፯ | አዜጋን ፡ ፈርያን ፡ | ፵ | ፪ሺ፲፯—፲፱፻፸፯ |
| ፲፰ | ሱስሑል ፡ አቶዛኔስ ፡ | ፳ | ፲፱፻፸፯—፲፱፻፶፯ |
| ፲፱ | አሚን ፡ ሁለተኛ ፡ ጾዊዛ ፡ | ፲፭ | ፲፱፻፶፯—፲፱፻፵፪ |
| ፳ | ራሚንጳሀቲ ፡ መስልኔ ፡ | ፳ | ፲፱፻፵፪—፲፱፻፳፪ |
| ፳፩ | ዋኑና ፡ | ፫ ቀን | |
| ፳፪ | ጲአሪ ፡ አንደኛ ፡ | ፲፭ | ፲፱፻፳፪—፲፱፻፯ |

CITY - HALL LIBRARY of ADDIS ABABA

ሁል፡ጊዜ፡እንደአገራችን፡የተለመደ፡አጻጻፍ፡ እነዚህ፡ ከዚህ፡በላይ፡የተጻፉት፡ነገደ፡ካም፡ የተባሉት፡ ነገሥታት፡ ናቸው። እንደዚሁም፡የካም፡ወንድም፡ሴም፡፱፡ልጆች፡ይወል ዳል፡ከ፱ኙ፡አንዱ፡አርፋክስድ፡ነው። እርሱም፡ሳላህን፡ሳላህ፡ ኤቦርን፤ ፋሌቅንና፡ዮቅጣንን፡ይወልዳል። ዮቅጣን፡ደግሞ፡፲፫፡ ልጆች፡ይወልዳል። ከነዚሁ፡፰ቱ፡ሳባ፤ አባል፤ኦፌር፤ አቢማር፡ ሐዊላ፡ከወንድሞቻቸው፡ተለይተው፡ የመካከል፡ ምሥራቅን፡ አገር፡ትተው፡ወደየመን፡መጥተው፡ ተቀመጡ። በየመንም፡ ባሉ፡የሕንድ፡ነገሥታት፡እየወጉ፡ ቢያስቸግርዋቸው፡ እሳይ፡ የተጫፈው፡እንደሚያመለክተው፡የካሙ፡ዘር፡ ጲአሪ፡በነገሠበት፡ ዘመን፡፩ሺ፱፻፹፡ዓመት፡ከክርስቶስ፡ልደት፡በፊት፡የመንን፡ ለቀው፡ወደ፡ኢትዮጵያ፡ተሻግረው፡መጡና፡ሦስቱ፡ነገዶች፡ ሳባ፡በትግሬ፤ አባል፡በአዳል፤ ኦፌር፡በውጋዴን፡ተቀመጡ። እንደመጡም፡መዠመሪያውን፡፰ቱን፡ዓመት፡በካሙ፡ነገድ፡ ንጉሥ፡ለጲአሪ፡ገብረዋል።

በዚህ፡መካከል፡የሕንድ፡ንጉሥ፡ራማ፡ወደ፡ኢትዮጵያ፡ መጥቶ፡ጲአሪን፡ወግቶ፡አሸንፎ፡መንግሥቱን፡ቀማው። ሕዝ ቡንም፡እንደባሪያ፡ይገዛው፡ዠመር። በዚያን፡ ጊዜ፡እነዚህ፡ ሦስቱ፡የዮቅጣን፡ልጆች፡ነገደ፡ዮቅጣን፡ ከያሉበት፡ ተሰብስ በው፡ራማን፡ወግተው፡ሠራዊቱን፡አሸንፈው፡እርሱንም፡ገደ ሉና፡ሕዝቡን፡ከባርነት፡ነፃ፡አወጡት። በዚህም፡ እነዚሁ፡ ነገደ፡ዮቅጣን፡ነገደ፡አግዓዝያን፡(ነፃ፡አውጪዎች)፡የሚባል፡ ስም፡ወጣላቸው፡ይላል፡ይሁን፡እንጂ፡የመንግሥቱ፡መሪነት፡ ወደ፡ነገደ፡ካም፡ሳይመለስ፡ነገደ፡ዮቅጣን፡ተዋግተው፡ያዳኑ ትን፡አገር፡ ለራሳቸው፡ ያዙት፡ ማለት፡ ነው። ከዚህ፡ጊዜ፡ ዠምሮ፡ነገደ፡ዮቅጣን፡በነገደ፡ካም፡ተተክተው፡ኢትዮጵያን፡ ማስተዳደራቸውን፡ይገልጽና፡በታሪክ፡ነገሥታችን፡እርሱንም፡ መሠረት፡ አድርገው፡ በጻፉት፡ በነዣን፡ ሞሪዬ፡ በኑብላቴን፡ ጌታ፡ኅሩይ፡መጽሐፍ፡የነገሥታቱ፡ ዝርዝራቸው፡እንደዚህ፡ ኢያል፡ይቀጥላል።



| ተከታታይ | ስም፡ | የግዛት፡ዘመን | ከክርስቶስ፡ልደት፡በፊት፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | አክናውስ፡ ሳባ፡ ፪ኛ፡ | ፶፭ | ፩ሺ፱፻፹፭—፩ሺ፱፻፴ |
| ፪ | ነከህቲ፡ ካልንሶ፡ | ፭ | ፩ሺ፱፻፴ —፩ሺ፱፻፳፭ |
| ፫ | ከሲዮፒ፡ | ፲፱ | ፩ሺ፱፻፳፭ —፩ሺ፱፻፮ |
| ፬ | ሳቤ፡ ፪ኛ፡ | ፲፭ | ፩ሺ፱፻፮—፩ሺ፰፻፺፩ |
| ፭ | ኢትዮጲስ፡ ፩ኛ፡ | ፶፮ | ፩ሺ፰፻፺፩—፩ሺ፰፻፴፭ |
| ፮ | ላክንዱን፡ ኖወር፡ኦሪ፡ | ፴ | ፩ሺ፰፻፴፭ —፩ሺ፰፻፭ |
| ፯ | ቱትኤምሔብ | ፳ | ፩ሺ፰፻፭ —፩ሺ፯፻፹፭ |
| ፰ | ሔርሖቶር፡ | ፳ | ፩ሺ፯፻፹፭ —፩ሺ፯፻፷፭ |
| ፱ | ኢትዮጲስ፡ ፪ኛ፡ | ፴ | ፩ሺ፯፻፷፭ —፩ሺ፯፻፴፭ |
| ፲ | ሰኑካ፡ ፪ኛ፡ | ፲፯ | ፩ሺ፯፻፴፭ —፩ሺ፯፻፲፰ |
| ፲፩ | ቦኑ፡ ፩ኛ፡ | ፰ | ፩ሺ፯፻፲፰—፩ሺ፯፻፲ |
| ፲፪ | ሙማዜስ፡ | ፬ | ፩ሺ፯፻፲—፩ሺ፯፻፮ |
| ፲፫ | አሩአሳ፡ | ፯ ወር፡ | |
| ፲፬ | አሚን፡ አስሮ፡ | ፴ | ፩ሺ፯፻፮ —፩ሺ፮፻፸፮ |
| ፲፭ | ኦሪ፡ ፪ኛ፡ | ፴ | ፩ሺ፮፻፸፮ —፩ሺ፮፻፵፮ |
| ፲፮ | ጲኦሪ፡ ፪ኛ፡ | ፲፭ | ፩ሺ፮፻፵፮ —፩ሺ፮፻፴፩ |
| ፲፯ | አሚንኤምሐት፡ ፩ኛ፡ | ፵ | ፩ሺ፮፻፴፩ —፩ሺ፭፻፺፩ |
| ፲፰ | ፃውዕ፡ | ፲፭ | ፩ሺ፭፻፺፩ —፩ሺ፭፻፸፮ |
| ፲፱ | አክቲሳኒስ፡ | ፲ | ፩ሺ፭፻፸፮—፩ሺ፭፻፷፮ |
| ፳ | ማንዴስ፡ | ፲፯ | ፩ሺ፭፻፷፮—፩ሺ፭፻፵፱ |
| ፳፩ | ፕሮቶውስ፡ | ፴፫ | ፩ሺ፭፻፵፱ —፩ሺ፭፻፲፮ |
| ፳፪ | አሞይ፡ | ፳፩ | ፩ሺ፭፻፲፮—፩ሺ፬፻፺፭ |
| ፳፫ | ኮንሲ፡ | ፭ | ፩ሺ፬፻፺፭ —፩ሺ፬፻፺ |
| ፳፬ | ቦኑ፡ ፪ኛ፡ | ፪ | ፩ሺ፬፻፺ —፩ሺ፬፻፹፰ |
| ፳፭ | ሳቤ፡ ፫ኛ፡ | ፲፭ | ፩ሺ፬፻፹፰ —፩ሺ፬፻፸፫ |
| ፳፮ | ጃጎንስ፡ | ፳ | ፩ሺ፬፻፸፫—፩ሺ፬፻፶፫ |
| ፳፯ | ሰኑካ፡ ፫ኛ፡ | ፲ | ፩ሺ፬፻፶፫ —፩ሺ፬፻፵፫ |
| ፳፰ | አንጋቦስ፡ ፩ኛ፡ | ፶ | ፩ሺ፬፻፵፫ —፩ሺ፫፻፺፫ |
| ፳፱ | ሚአሙር፡ | ፪ ቀን | |

| ተከታታይ | ስም ፡ | የግዛት ፡ ዘመን ፡ | ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ |
|---|---|---|---|
| ፴ | ክሊና ፡ | ፲፩ | ፩ሺ፫፻፶፰ — ፩ሺ፫፻፵፯ |
| ፴፩ | ዘግዱር ፡ | ፵ | ፩ሺ፫፻፵፯ — ፩ሺ፫፻፯ |
| ፴፪ | ሐርሐቶር ፡ ፪ኛ ፡ | ፴ | ፩ሺ፫፻፯ — ፩ሺ፪፻፸፯ |
| ፴፫ | ሐርሐቶር ፡ ፫ኛ ፡ | ፩ | ፩ሺ፪፻፸፯ — ፩ሺ፪፻፸፮ |
| ፴፬ | ኔክቴ ፡ ፪ኛ ፡ | ፳ | ፩ሺ፪፻፸፮ — ፩ሺ፪፻፶፮ |
| ፴፭ | ቲቶን ፡ ሶትዮ ፡ | ፲ | ፩ሺ፪፻፶፮ — ፩ሺ፪፻፵፮ |
| ፴፮ | ሐርመንቴ ፡ ፩ኛ ፡ | ፭ ወር | |
| ፴፯ | አሜን ፡ ኢምሐት ፡ ፪ኛ ፡ | ፭ | ፩ሺ፪፻፵፮ — ፩ሺ፪፻፵፩ |
| ፴፰ | ኮንሳብ ፡ ፩ኛ ፡ | ፭ | ፩ሺ፪፻፵፩ — ፩ሺ፪፻፴፮ |
| ፴፱ | ኮንሳብ ፡ ፪ኛ ፡ | ፭ | ፩ሺ፪፻፴፮ — ፩ሺ፪፻፴፩ |
| ፵ | ሰኑካ ፡ ፪ኛ ፡ | ፭ | ፩ሺ፪፻፴፩ — ፩ሺ፪፻፳፮ |
| ፵፩ | አንጋቦ ፡ ፪ኛ ፡ ሕዝባይ ፡ | ፵ | ፩ሺ፪፻፳፮ — ፩ሺ፩፻፹፮ |
| ፵፪ | አሜን ፡ አስታት ፡ | ፴ | ፩ሺ፩፻፹፮ — ፩ሺ፩፻፶፮ |
| ፵፫ | ሐርሆር ፡ | ፲፮ | ፩ሺ፩፻፶፮ — ፩ሺ፩፻፵ |
| ፵፬ | ፒያንኪያ ፡ ፩ኛ ፡ | ፱ | ፩ሺ፩፻፵ — ፩ሺ፩፻፴፩ |
| ፵፭ | ጥኖትሲም ፡ ፩ኛ ፡ | ፲፯ | ፩ሺ፩፻፴፩ — ፩ሺ፩፻፲፬ |
| ፵፮ | ጥኖትሲም ፡ ፪ኛ ፡ | ፵፩ | ፩ሺ፩፻፲፬ — ፩ሺ፸፫ |
| ፵፯ | ማሳሒርታ ፡ | ፲፯ | ፩ሺ፸፫ — ፩ሺ፶፮ |
| ፵፰ | ራሜንኮፐርም ፡ | ፲፬ | ፩ሺ፶፮ — ፩ሺ፵፫ |
| ፵፱ | ጥኖትሲም ። ፫ኛ ፡ | ፯ | ፩ሺ፵፫ — ፩ሺ፴፮ |
| ፶ | ሳቢ ፡ ፪ኛ ፡ | ፲ | ፩ሺ፴፮ — ፩ሺ፳፮ |
| ፶፩ | ተዋስያ ፡ ዴውስ ፡ | ፲፫ | ፩ሺ፳፮ — ፩ሺ፲፫ |
| ፶፪ | ማክዳ ፡ ንግሥት ፡ | ፴፩ | ፩ሺ፲፫ — ፱፻፹፪ |

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታት ፡ የምንላቸው ፡ አብዛኞቹ ፡ ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ እንዳሉት ፡ እንደ፡ ባላባት ፡በውስጣቸው፡ ያለውን ፡ ነገድ ፡ ያስተዳድሩት ፡ ነበር ፡ እንጂ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ዘውድ፡ ደፍተው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ተደርጎላቸው፡ በንጉሥነት ፡ ስም ፡ የገዙ ፡ አይመስልም ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የዚህ ፡



ዕድል ፡ የገጠማቸው ፡ የግብፅ ፡ መንግሥትና ፡ ሐሙራቢ ፡ የመሠረ ተው ፡ የባቢሎን ፡ ከዚያም ፡ የቻይናና ፡ የሕንድ ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው ። የነዚህ ፡ መንግሥታት ፡ ሥልጣኔ ፡ ቀዳሚነት ፡ የታወቀው ፡ ሊቃውንት ፡ የነበሩበትን ፡ ከተማ ፡ እያስቆፈሩ ፡ ልዩ ፡ ያማልከትና፡ የነገሥታት ፡ሐውልት ፡ እያገኙ ፡ በሐውልቱ ፡ የተቀረጸውን፡ ጽሑፍ፡ በጥልቅ ፡ ምርመራ ፡ እየተረጐሙ ፡ በሰጡት ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በአክሱም፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ እንደምናገኘው ፡ ማክዳ፡ ንግሥት ፡ ከአርዌና ፡ ከአንጋቦ ፡ ተከታትላ ፡ መምጣቷን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ስለሚገልጽና ፡ ይኸ ፡ ያሁኑ ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ዝርዝር ፡ ስለሚሰጥ ፡ በዝርዝሩ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ ማድረግ ፡ ችግር ፡ ነው ።

ምናልባት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ከተማ ፡ እየተቆፈረ ፡ የተደ በቀ ፡ ሐውልት ፡ ተገኝቶ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ እን ደዚሁ ፡ እንዳለ ፡ አንብበን ፡ እንለፍና ፡ የዚህኑ ፡ የጥንት ፡ ሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ እንመልከት ።

የቀድሞ ፡ ሕዝባችን ፡ ኑሮ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደነበረ ፡ በዝር ዝር ፡ የሚገልጽ ፡ጽሑፍ ፡ አይገኝም ። አጭር ፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ የሚባለው ፡ የአለቃ ፡ ታዬ ፡ መጽሐፍም ፡ በሰፊው ፡ አይገ ልጽም ። ቢሆንም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከአምስት ፡ መቶ፡ ዓመት ፡ ወዲያ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ ሥልጣኔ ፡ የነበረውን ፡ የኑሮው ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አይመስልም ። ስለዚህም ፡ የሚናገር ፡ ጽሑፍ ፡ ከኛ ፡ ወገን ፡ የለንም ።

ስለዚህ፡ ከራሳችን ፡ ስናጣ ፡ የነዚህ ፡ የነዋሪዎቹ ፡ የነገደ፡ ካምና፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡት ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ሕዝቦች ፡ እንዴት፡ ይኖሩ፡ እንደነበረ ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ ተራምደን ፡ የሚያኮራ ውንም ፡ የሚያስቀይመውንም ፡ እየፈለግን ፡ መመልከት ፡ አለብን። የሚያኮራው ፡ በ፱ነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የነበረው ፡ ሆሜርና ፡ ይል ቁንም፡ በ፭ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የነበረው ፡ ሄሮዱት ፡ የጻፉት ፡ ነው። እነሱም ፡ ከብዙዎቹ ፡ ንግግሮቻቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ይላሉ ። ኢትዮጵያውያን ፡ ታላላቆች ፡ መልካቸው ፡ ያማረ ፡ የሰውነታቸው ፡

ቅርጽ ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ ጺድቆች ፡ በጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ለሥራ ፡ የማይደክሙ ፡ ቀበበኞች ፡ በሩቅ ፡ ሥፍራ ፡ የሚኖሩ ፡ አማልክት ፡ የሚወዷቸው ፡ ባንደበታቸው ፡ ሐሰት ፡ የማይገባ ፡ በጦርነትና ፡ በር ጅና ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በበሽታ ፡ የማይሞቱ ፡ ናቸው ።

በተረፈ ፡ በመዠመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ እንዳልነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ነቢያቱ ፡ እነኢሳይያስ ፡ እነሶፎንያስ ፤ ወደዝርዝር ፡ ጕዳይ ፡ ሳይ ገቡ ፡ በትንቢታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደአጋጣሚ ፡ እየጠቀሱት ፡ አል ፈዋል ። በነሱም ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ስም ፡ ማውሳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ስለኢትዮጵያውያን ፡ ኑሮ ፡ የሚናገር ፡ ዝርዝር ፡ ጽሑፍ ፡ አይገኝም ።

ስለዚህ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ከኖብያ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተበታትኖ ፡ ስለሚኖረው ፡ ሕዝባችን ፡ በሰ ፊው ፡ የጻፉ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የጠቀስናቸው ፡ አጋ ታርሺድ ፡ ኤራቶስቴን ፡ ዲዮዶር ፡ የሚባሉ ፡ የግሪክ ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ። ኤራቶስቴን ፡ በ፫ተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፤ አጋታርሺድ ፡ በ፪ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ። አጋታርሺድ ፡ የበጥሊሞስ ፡ ሰባተኛ ፡ (የግብፅ ፡ ንጉሥ) ፡ መምህር ፡ የነበረ ፡ ነው ። እሱም ፡ በዘመኑ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ጠፍቶ ፡ MARE ERYTHREO የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ብቻ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይገኛል ። የሱ ንም ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ እያደረጉ ፡ ዠኘ ፡ ሞሪዩና ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተበታትኖ ፡ የሚኖረውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ ጠቅሰውት ፡ ይገኛል ። ቃሉም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

፩ኛ/ ፤ አባ ፡ ታሊች ፡ ወይም ፡ ስትሩቲአፋኝ ፡ ትርጓሜውም ፡ ሰጎን ፡ የምትባለዋን ፡ እንስሳ ፡ የሚበሉ ፡ ግማሾቹ ፡ አዕዋፍ ፡ የሚ በሉ ፡ ዓባይ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ የሚኖሩ ፡ ልብሳቸውም ፡ ሥጋዋን ፡ የሚበሉት ፡ የሰጎን ፡ ቆዳ ።

፪ኛ/ ፤ አዱሊት ፡ የሚባሉት ፡ ከግብፅ ፡ ጠፍተው ፡ መጥተው ፡ የአዱሊስን ፡ ቅጽር ፡ ምሽግ ፡ ሠርተው ፡ ግማሾቹ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፫ኛ/ ፤ አኦኰሴፋል ፡ ራሳቸው ፡ ጥንዚዛ ፡ የሚመስል ፡ ጥንዚዛ ፡ የሚበሉም ፤



፬ኛ/ ፤ አሴኰሲዩሴፋል ፡ ኔት ፡ ለምትባለው ፡ ሴት ፡ ጣዖት ፡ የሚሰግዱ ።

፭ኛ ፤ አክሪሎፋኝ ፡ አንበጣን ፡ የሚበሉ ፡ ቁመታቸው ፡ አጫ ጭር ፡ ሰውነታቸው ፡ ቀጭን ፡ በጣም ፡ የሚሮጡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ የማይበልጥ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ በቁምጥና ፡ በሽታ ፡ እያለቁ ፡ በቶሎ ፡ የሚሞቱ ።

፮ኛ/ ፤ አሮቴር ፡ የሚባሉ ፡ ከአዱሊስ ፡ በሰሜን ፡ የሚኖሩ ።

፯ኛ ፤ አርታባቂት ፡ የሚባሉ ፡ በሜካ ፡ የሚኖሩ ።

፰ኛ ፤ አሳኪያን ፡ ኤሌፋንቶፋኝ ፡ ዝሆን ፡ እያደኑ ፡ የሚበሉ ፡ ስማቸው ፡ አሰማክ ፡ ማስሁአሽ ፡ የሚባሉ ፡ በዛሬው ፡ ሐማሴንና ፡ ሠናሂት ፡ የሚቀመጡ ፡ በቀን ፡ ዝሆንና ፡ ሌላም ፡ አውሬ ፡ ቢያድኑ ፡ እየዋሉ ፡ አዳራቸውን ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉ ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡ የሚለብሱ ፡ ናቸው ። በነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴትና ፡ ልጅ ፡ የጋራ ፡ ነው ። ከመካከላቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ሽምግሎ ፡ የማይሞት ፡ ቢሆን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ እንዲሞት ፡ ይጠይቁታል ። እምቢ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ እንደልማዳቸው ፡ አሮጌውን ፡ ሰው ፡ ከኮርማ ፡ በሬ ፡ ጭራ ፡ ጋር ፡ አሥረው ፡ እያስጐተቱ ፡ ይገሉታል ።

፱ኛ ፤ አባሊት ፡ ከባብ ፡ ኤል ፡ ማንዴብ ፡ ባሕር ፡ ጀምሮ ፡ ከር ቤና ፡ ብርጉድ ፡ በብዙ ፡ በሚገኝበት ፡ በዛሬው ፡ የአዳልና ፡ የሱማሌ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ (እነዚህም ፡ ከ፲፫ቱ ፡ ከዮቅጣን ፡ ልጆች ፡ ያንዱ ፡ የአባል ፡ ዘሮች ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። )

፲ኛ ፤ አክሱማውያን ፡ በዛሬው ፡ አክሱም ፡ አጠገብ ፡ የሚኖሩ ፡

፲፩ኛ ፤ ባርጂን ፡ የሚባሉ ፡ በዛሬው ፡ ባርከ ፡ በሚባለው ፡ አው ራጃ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፲፪ኛ ፤ ብሌሚ ፡ (ብሌማ) ፡ የሚባሉ ፡ ከአትባራ ፡ (አስታቦራስ ፡) ወንዝ ፡ በሰሜን ፡ እስከ ፡ ላዕላይ ፤ ግብፅ ፡ ድረስ ፡ የሚቀመጡ ፡ ዘራቸው ፡ ከከነዓን ፡ ልጅ ፡ ከኼት ፡ ወይም ፡ ከኬት ፡ የወረዱ ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ የበጃ ፡ ዘር ፡ የሚሉዋቸው ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አብዛኞቹ ፡ በዋሻ ፡ የሚቀመጡ ፡ ቢሆኑ ፡ ሠላሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ፊደሎች ፡ ስለነበሯቸውና ፡ በራሳቸው ፡ ቋንቋ ፡ የሚ

ናገሩ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በዚያው ፡ በመጠኑ ፡ ሥልጡኖች ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳል ። እነሱም ፡ በቀይ ፡ ድርጭት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ። ኑሮአቸው ፡ እየተራራው ፡ ሥር ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ራሳቸው ፡ በሠሩት ፡ በዋሻ ፡ ከተማ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በጠባዩ ፡ ዋሻነት ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ አይመርጡም ፡ ነበር ። እነሱም ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ ፺፩ ሺህ ፡ ወታደር ፡ ፱፻ ፡ መንኰራኵር ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

፲፫ኛ ፤ ሲናሞልጕ ፡ የሚባሉ ፡ ጭንቅላታቸው ፡ የውሻ ፡ የሚመስል ፡ የውሻ ፡ ወተት ፡ የሚጠጡ ፡ ተኩላ ፡ የሚበሉ ፡ መልካቸው ፡ ጥቁር ፡ ፉንጋ ፡ ረጃጅሞች ፡ ጫማቸው ፡ ትልልቅ ፡ ማናቸውንም ፡ አውሬ ፡ አድነው ፡ ሥጋውን ፡ በልተው ፡ ቆዳውን ፡ አለስልሰው ፡ የሚለብሱ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ አውሬና ፡ ነብ ፡ ለማደን ፡ እንዲያግዛቸው ፡ እንደከብት ፡ የውሻ ፡ መንጋ ፡ ያረቡ ፡ ነበር ።

የነሱ ፡ አማልክቶቻቸው ፡ ነገሥታቶቻቸው ፡ ነበሩ ። ነገሥታቱም ፡ ተገልጠው ፡ በመታየት ፡ ምክንያት ፡ እንዳይናቁ ፡ ዘወትር ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ተሸፍነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ዘሮች ፡ ዛሬ ፡ ቈናማ ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩ ፡ ናቸው ።

፲፬ኛ ፤ ሲኔኽ ፡ በድርቅ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ በረጅም ፡ አንካሴ ፡ በፍላፃ ፡ በድንጋይ ፡ አውሬ ፡ እያደኑ ፡ የሚኖሩ ፡ ቍጥራቸው ፡ ያነሰ ።

፲፭ኛ ፤ ዳሬማስ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፲፮ኛ ፤ ደማዘን ፡ በዛሬው ፡ ደምበኸን ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፲፯ኛ ፤ ኤላፎሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ ዘንዶ ፡ ወይም ፡ ድኩላ ፡ ጢንዝዛ ፡ የሚመስል ፡ ሴት ፡ በሚባል ፤ ረኸም ፡ ዋልያ-አላማ-እሀያ ? ጣዖት ፡ የሚያመልኩ ።

፲፰ኛ ፤ ጋሊ ፡ ጋላ ? በዋሻ ፡ የሚኖሩ ፡ በጥሊሞስ ፡ ፊላደልፍ ፡ ፱፻፹፭-፱፻፵፯ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ያስገበራቸው ።

፲፱ኛ ፤ ሐርፒ ፡ ወይም ፡ ሒዬራኮሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ የእሞራ ፡ ጭንቅላት ፡ የሚመስል ፡ በዐባይ ፡ ዳር ፡ የሚኖሩ ፡ እነዚህም ፡ የግሪክ ፡ የተረት ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚለው ፡ ከባሎቻቸው ፡ ተጣልተው ፡ ከነልጆቻቸው ፡ ከግሪክ ፡ አገር ፡ የመጡ ፡ የአምስት ፡ ልዑላት ፡ የግሪክ ፡ ሴቶች ፡ ዝርያዎች ፡ ናቸው ። አገራቸውን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አንበጣ ፡ ስለሚያጠቃው ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ጐረቤቶቻቸውን ፡ በዘረፉ ፡ የሚያስፈሩ ፡ ከልጆቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ለጣዖት ፡ እያረዱ ፡ የሚሰዉ ፡ ናቸው ።



፳ኛ ፤ ሔሊንስ ፡ በዛሬው ፡ ባሕር ፡ ኤል ፡ ጋዛል ፡ በሚባለው ፡ ረግረግ ፡ ቦታ ፡ የሚኖሩ ።

፳፩ኛ ፤ ሔማንቶፖድ ፤ ቅልጥማቸው ፡ ደረቅ ፡ በሩጫ ፡ ዛፍና ፡ ተራራ ፡ በመውጣት ፡ ማንም ፡ የማይቀድማቸው ።

፳፪ኛ ፤ ሒፖኽ ፡ ፈረሰኞች ፡ ምግባቸውም ፡ የፈረስ ፡ ሥጋ ፤ ልብስ ፡ በደንብ ፡ የሚለብሱ ፤ ጠጕራቸውን ፡ የሚሠሩ ፤ መልካቸው ፡ ያማረ ፤ ቁመታቸው ፡ የረዛዘመ ፡ ከግብፆች ፡ ጋር ፡ በጦርነትም ፡ በንግድም ፡ ስለሚገናኙ ፡ አምልኮአቸውም ፡ እንደ ፡ ግብፆች ፡ እሲሪስና ፡ ኑም ፡ በሚባሉ ፡ ጣዖቶች ፡ ነበር ።

፳፫ኛ ፤ ሂፖፖታሞሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ ጉማሬ ፡ የመሰሉ ።

፳፬ኛ ፤ ሒሎፋኽ ፡ የዛፍ ፡ ሥርና ፡ የዛፍ ፡ ቀምበጥ ፡ የሚመገቡ ፡ ከተማቸው ፡ ኬብሐ ፡ የሚባል ። በነሱ ፡ ዘንድ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ የነገድ ፡ አልቅና ፡ የሴት ፡ ነው ። የመንግሥት ፡ መብት ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ነች ። ሕዝቦቹ ፡ ሰውነታቸው ፡ ቀጭን ፡ ቀልጣፋ ፡ ራቁታቸውን ፡ የሚሔዱ ፡ ኑት ፡ በሚባል ፡ ወርካ ፡ አድባር ፡ የሚያመልኩ ፡ ናቸው ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴት ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የግል ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ ጋብቻና ፡ ኑሮ ፡ ሳይሆን ፡ ተደባልቆ ፡ በማኅበር ፡ መኖር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፳፭ኛ ፤ ሒአሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ ጥንዚዛ ፡ የሚመስል ። በሴት ፡ (ፀሐይ) ፡ የሚያመልኩ ።

፳፮ኛ ፡ ኤቢዮሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ አሞራ ፡ የሚመስል ።

፳፯ኛ ፤ ቈድሮሴያን ፡ ወይም ፡ አከቲዮፋኽ ፡ ዓሣ ፡ የሚመገቡ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ የሚኖሩ ፡ ጭንቅላታቸው ፡ የዓሣ ፡ የሚመስል ፡ ራቁታቸውን ፡ የሚሔዱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸው ፡ ሰይፋማ ፡ ድንጋይና ፡ የፍየል ፡ ቀንድ ። በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ በመካከላቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሲኖር ፡

ከጎረቤቶቻቸው ፡ ጋር ፡ በንግድም ፡ በጋብቻም ፡ አይገናኙም ፡ ነበር ። ምግባቸው ፡ ዓሣ ፡ ስለነበረ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ እርጥቡን ፡ እየበሉ ፡ የቀረውን ፡ በፀሐይ ፡ አያደረቁ ፡ ለከርሞ ፡ ያከማቻሉ ። ዓሣን ፡ በብዙ ፡ የሚይዝ ፡ እንደመረብ ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ መጣሪያና ፡ ብልሃት ፡ ነበራቸው ። ሬሳቸውንም ፡ ባሕር ፡ በሞላ ፡ ወይም ፡ ሞገድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ባሕር ፡ ወስዶ ፡ እንዲጥለው ፡ አዳሩ ፡ በሚገኝ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጡታል ። በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ውጊያቸው ፡ አደገኛ ፡ ነው ። እነሱም ፡ እያባረሩ ፡ ከሚገሉ ፡ እየሸሹ ፡ በውርወራ ፡ የሚገሉት ፡ ይበልጣል ።

፳፰ኛ ፤ ካሊብ ፡ በዋሻ ፡ ከሚኖሩት ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ።

፳፱ኛ ፤ ኬሎኖፋጕ ፡ ኤሊን ፡ የሚመገቡ ፡ ከባሕር ፡ የሚወጣ ፡ ዓሣና ፡ ሌላም ፡ አውሬ ፡ እየበሉ ፡ በቅራሬውና ፡ በኤሊ ፡ ቆዳ ፡ ጀልባ ፡ እየሠሩ ፡ የሚሔዱ ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸውንም ፡ በዚሁ ፡ የሚከድኑ ፡ ናቸው ።

፴ኛ ፤ ክሬዮፋጕ ፡ እርጥብ ፡ ሥጋ ፡ የሚመገቡ ፡ በሰናር ፡ ደቡብ ፡ የሚኖሩ ።

፴፩ኛ ፤ ላጉቤፋል ፡ መልካቸው ፡ የሚዳቋ ፡ ጭንቅላት ፡ የሚመስል ።

፴፪ኛ ፤ ማክሮቢያን ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ የሚኖሩ ፡ የመርዌ ፡ ነገዶች ፤ ዕድልና ፡ ጽድቅ ፡ ያላቸው ፡ አትክልትና ፡ ወሃ ፡ ጥብስ ፡ ሥጋ ፡ የሚመገቡ ፡ ዘፈን ፡ ጭፈራ ፡ ንጽሕና ፡ (እጥበት) ፡ የሚወዱ ፤ ቍጥራቸው ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚደርስ ፡ አገራቸው ፡ አሎ ፡ ወይም ፡ ሄሊዎትራፔዝ ፡ (የፀሐይ) ፡ አገር ፡ በሚባለው ፡ የዛሬው ፡ የሰናርና ፡ የሱዳን ፡ ግዛት ፡ ነው ። ከተማቸው ፡ መርዌ ፡ ነው ። መሬታቸውም ፡ በሀብት ፡ በፍሬያማነት ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ነበር ። እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እየተባበሩ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እየተለያዩ ፡ ለየብቻ ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ የሚደርሱ ፡ ነገሥታት ፡ ነበሩዋቸው ። የነገሥታቱም ፡ ስም ፡ የአብዛኞቹ ፡ በታችኛው ፡ የግብፅ ፡ (ሜምፊስ) ጣዖት ፡ በጥታህ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ግሪኮች ፤ በሂሊዎስ ፡ (ፀሐይ) ፡ ተሰይሞ ፡ ይገኛል ። የነዚህ ፡ የማክሮባውያን ፡ (መርዌ) ፡ መንግሥት ፡



ከግብፅ ፡ ከግሪክ ፡ መንግሥታት ፡ ታሪካቸው ፡ ከታሪካቸው ፡ የነገሥታቱም ፡ ዘር ፡ ከነገሥታቱ ፡ ዘር ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ ተደባልቆ ፡ ይገኛል ።

፴፫ኛ ፤ ማቱት ፡ (ማዲት) ፡ በተከዜና ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ መካከል ፡ የሚኖሩ ።

፴፬ኛ ፤ ሜጋባር ፡ (ከባዶች) ፡ ወይም ፡ ኢቃኖሪያ ፡ (ድል ፡ አድራጊዎች ፡ ) የሚባሉ ፡ ዛሬ ፡ የባሪያ ፡ ዘር ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። መልካቸውም ፡ ጥቁር ፡ ቁመታቸው ፡ ረጃጅም ፡ ኃይለኞች ፡ የጦር ፡ መጣሪያቸው ፡ እንካሴ ፡ ጦርና ፡ የቆዳ ፡ ጋሻ ፡ ነበር ፤ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴት ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ አላት ፤ ሴትን ፡ የመታ ፡ እንድትልቅ ፡ ወንጀለኛ ፡ ይቈጠራል ። አሮጊት ፡ ሴት ፡ የተገኘበት ፡ ጉባኤና ፡ ሸንጎ ፡ ሁሉ ፡ የተከበረ ፡ ነው ። በወንድ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ለምሳሌ ፡ ወገቡ ፡ ጉባጣ ፡ እግሩ ፡ እንካሳ ፡ ወይም ፡ የማይድን ፡ በሽታ ፡ ያለው ፡ የተገኘ ፡ ( ወይም ፡ የተወለደ ፡ ) እንደሆነ ፡ ገድለው ፡ ይጥሉታል ። ይኸውም ፡ በነሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የሁሉም ፡ ሰው ፡ ቁመናው ፡ ያማረ ፡ ሕይወቱ ፡ ጤናማ ፡ የሆነ ፡ ብቻ ፡ እንዲገኝ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ልማድ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ በስፓርትና ፡ በኤስኪሞ ፡ በአውስትራሊያ ፡ ይገኛል ።

እንደ ፡ ፳ኛው ፡ ቍጥር ፡ ነገዶች ፡ በጣም ፡ አርጅተው ፡ አልሞትም ፡ ያሉትን ፡ አሮጊትና ፡ ሽማግሌዎች ፡ አበሬ ፡ ኮርማ ፡ ጭራ ፡ ላይ ፡ አሥረው ፡ እያስጐተቱ ፡ ይገድሏቸዋል ። ይኸንን ፡ [illegible] ፡ ያለ ፡ በግድ ፡ ታንቆ ፡ ይገደላል ። ሰው ፡ ሲሞት ፡ ጭኑን ፡ ከአንገቱ ፡ ጋር ፡ አስረው ፡ እጉብታ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ወስደው ፡ ያስቀምጡና ፡ ጨርሶ ፡ እስኪሸፈን ፡ ድረስ ፡ ድንጋይ ፡ ይቆልሉበታል ። በተቆሸለው ፡ ድንጋይ ፡ ጫፍ ፡ የፍየል ፡ ቀንድ ፡ ይሰኩበታል ።

፴፭ኛ ፤ ሞልሽርያ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ፡ ክፍሎች ።

፴፮ኛ ፤ ሞኖፖድ ፡ አንድ ፡ እግር ፡ ሞኖኮል ፡ አንድ ፡ ክንድ ፤ ሞኖሴል ፡ አንድ ፡ ጭን ፡ ብቻ ፡ ያላቸው ፡ አባብ ፡ የሚበሉ ፡ (አንድ ክንድ ፡ አንድ ፡ ጭን ፡ አንድ ፡ እግር ፡ ብቻ ፡ ነበራቸው ፡ ሲል ፡ የተረት ፡ አነጋገር ፡ ይመስላል ። )

፲፯ኛ ፤ ሞበኮፋኸ ፡ የበሬ ፡ ሥጋ ፡ የሚመገቡ ፡ በሱአኪንና ፡ በአቦክ ፡ መካከል ፡ የሚኖሩ ።

፲፰ኛ ፤ ሚአሴፋል ፡ (ቀንድ ፡ አውጪ ፡ የሚመስሉ ፡ ወይም ፡ የሚመገቡ ። )

፲፱ኛ ፤ ኖብያ ፡ ኑብያ ፡ ኖባት ፡ በዛሬው ፡ ጎርዶፋን ፡ የሚገኙ ፡ ከፒግሜይ ፡ ( አጫጭር ፡ ሰዎች ፡ ) ዘር ፡ የወረዱ ፡ ውሻን ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ እንስሳ ፡ የሚያከብሩ ።

፳ኛ ፤ አኖሴፋል ፡ (ከፊታቸው ፡ የአህያ ፡ ጭንቅላት ፡ የሚመስሉ ፡ ) በኢትዮጵያ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚኖሩ ፡ እህያን ፡ ለመገርመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለጭነት ፡ ለኮርቻ ፡ ያሠለጠኑ ፡ በአገራቸው ፡ ብርቱድና ፡ ዕጣን ፡ የሚገኝ ፡ በጉናቸው ፡ እንደሚገኙት ፡ ፒግሚ ፡ በበሬና ፡ በዝኖን ፡ ተቀምጠው ፡ የሚሔዱ ። በመኻከላቸው ፡ ሰውን ፡ የሚበላ ፡ ጭራቅ ፡ ) ይገኛል ። ወንጀለኛ ፡ ሲሞት ፡ እንደቅጣት ፡ እንደውርደት ፡ እንዲቀጠር ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ይቀብሩታል ። የቀረውን ፡ ደኅናውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉታል። ምግባቸው ፡ ዕንቍራሪት ፡ (ባትራኮፋኸ) ፡ ስማቸው ፡ ሴሴኒት ፡ ሉኤሪያን ፡ ይባላል ።

፳፩ኛ ፤ ፋሊኸ ፡ የዛሬው ፡ ፈላሾች ።

፳፪ኛ ፤ ፒግሚ ፡ ቁመታቸው ፡ አንድ፡ ክንድ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ቅልጥም ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ መዳፍ ፡ የሚሆን ፡ መልካቸው ፡ ጥቁሮች ፡ ጢማሞች፡ ራቁታቸውን፡ የሚሔዱ ፡ በዝኖንና ፡ በበሬ፡ ተቀምጠው፡ የሚጓዙ ፡ በዝኖን ፡ የሚያርሱ ፡ በአትባራ ፡ ወንዝና ፡ በጋላበት ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። ቍጥራቸው ፡ እምስት ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ይደርሳል ። ዛሬ ፡ በአፍሪካ ፡ መካከል ፡ በኮንጎ ፡ ወንዝና ፡ በማዳስካር፡ ይገኛሉ ፡ (ቦሽማን) ፡ አቦሽማኒ? የሚባሉትም ፡ ቍጥራቸው ፡ ወደነዚሁ ፡ ነው ።

፳፫ኛ ፤ ራብሲ ፡ ከመርዌ ፡ ከደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚኖሩ ።

፳፬ኛ ፤ ሪዞፋኸ ፡ ሥራ ፡ ሥር ፡ የሚበሉ ፡ በአትባራ ፡ ወንዝ ፡ በረሃ ፡ የሚኖሩ ፡ የበረሃ ፡ ዝንብ ፡ እየነደፈ ፡ በሚያስቸግራቸው ፡ ጊዜያት ፡ ወደ ፡ ረግረግ ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ተደብቀው ፡ የሚኖሩ ።



፳፭ኛ ፤ ማምብር ፡ የጋማና ፡ የቀንድ ፡ ከብታቸውን ፡ የቤት ፡ እንስሳቸውን ፡ ሁሉ ፡ ጆሮ ፡ እየቆረጡ ፡ በማሳደግ ፡ ስመ ፡ ጥሮች ፡ ናቸው ።

፳፮ኛ ፤ ሳከሲማን ፡ ( የዛሬው ፡ ሳሳናብ ፡ ናቸው (፩) ። )

የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በዘመኑ ፡ ቋንቋቸው ፡ በግሪክኛ ፡ ጽፈው ፡ በነገድ ፡ በልማድ ፡ በታትነው ፡ የሚያሳዩንን ፡ ሕዝብ ፡ በኛ ፡ ወገን ፡ ያለው፡ ጽሑፍ፡ የነገደ ፡ ካም ፡ ወገኖች ፡ በሆኑ፡ ነገሥታት ፡ እየተመሩ ፡ በደንብ ፡ የሚተዳደሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ከሚያሳየን ፡ ጋር ፡ አሳቡ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይጣላል ። ባለፈው ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ እንደአየነው ፡ ያገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ (ያለቃ ፡ ታዬም ፡ የብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይም) ፡ ለነገሥታቱ ፡ ስም ፡ እየጠቀሰ ፡ የግዛቱን ፡ ዘመን ፡ እየወሰነ ፡ እከታትሎ ፡ ሲያመጣው ፡ የቀረው ፡ ሰፊው ፡ አገር ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ ስሜናዊው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባንድ ፡ ካማዊ ፡ በሆነ ፡ ንጉሥ ፡ የሚተዳደር፡ እስመስሎታል ። የነዚህ፡ የግሪኮቹና ፡ የሮማውያኖቹ ፡ የታሪክ ፡ ምንጭ ፡ ለየብቻው ፡ በየጐሳው ፡ መልኩን ፡ ልማዱን ፡ ዕምነቱን ፡ ምግቡን ፡ ልብሱን ፡ እየለያየ ፡ ለየብቻው ፡ የሚኖር ፡ አስመስሎታል፡ እንጂ ፡ ሁሉንም ፡ ባንድ ፡ ንጉሥ ፡ ባንድ ፡ ሥልጣኔና ፡ ልማድ ፡ ጠቅልሎ ፡ አያሳይም ። የዚያን ፡ ጊዜ ሕዝብ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ኃይለኛ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ መጠቅለሉ ፡ ባይቀር ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ተበታትኖ ፡ ለየብቻው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ በራሱ ፡ ቀንደኛ ፡ ባላባት ፡ ብቻ ፡ መተዳደርን ፡ መውደዱ ፡ አይቀርምና ፡ የግሪኮቹን ፡ ጸሐፊዎች፡ ሀሳብ ፡ በሙሉ፡ መቀበልም ፡ ቅር፡ ቢያሰኝ ፡ በሙሉ ፡ መተውም ፡ አይቻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ጢንዚዛ ፡ አሞራ ፤ ጉማሬ ፤ . . . . . . የሚመሳስሉ ፡ ወይም ፡ እየተመገቡ ፡ የሚኖሩ ፡ ባለአንድ ፡ ጭን ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ብሰው ፡ ለጻፉት ፡ ከሰውነት ፡ እርኢያና ፡ አምሳል ፡ የራቀ ፡ ስለሚያስመስሉት ፡ አጻጻፋቸው ፡ ተረትና ፡ ቀልድ ፡ የተደባለቀበት ፡ ይመስላል ።

(፩) J. MORIE — Histoire d'Ethiopie 1er Vol. ም ፡ ፪ ገጽ ፡ ፳፩ — ፳፪ ፡ CONTI-ROSSINI — Storia d'Etiopia ም ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፶፯ - ፷፫ ፡

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኑሮአቸውን ፡ ኃይለኛ፡ ሲገኝ ፡ እየተበበሰቡ ፡ ሲጠፋ ፡ በጕሳቸው ፡ እንደ ፡ አለቃ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ እየአበጁ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተዋጉ ፤ እየታረቁ ፡ በዙረት ፡ ሥፍራ ፡ ስሥፍራ ፡ እየተለዋወጡ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ የግብፅ ፡ የፒራሚድና፡ የሐውልት ፡ ሥራ፡ አስመርሯቸው ፡ ከሹማምንት ፡ አምልጠው ፡ በአዱሊስ ፡ የተቀመጡት ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ከባቢሎንና፡ ከአሶር ፡ ሥልጣኔን ፡ ይዘው፡ በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ቆይተው ፡ ከዚያ ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተሻግረው ፡ የተቀመጡት ፡ በሥልጣኔ፡ ከሌሎች ፡ ነገዶች ፡ በመሻላቸው ፡ እንደ ፡ ቅጥር ፡ ያለ ፡ ከተማ ፡ እየከተሙ ፡ ፈደል ፡ አበጅተው ፡ ቋንቋቸውን ፡ ለይተው ፡ የሚኖሩ ፡ እንደ ፡ ሳባውያን ፡ እንደ ፡ ሐበሳን፡ ያሉት፡ አሉባቸው ። ሌላውንም ፡ ነገድ ፡ ለመግዛት ፡ የበላይነት ፡ ያሳዩ ፡ እነዚሁ ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ፡ ፊት፡ ተጽፎ፡ እንደምናገኘው ፡ በተለይ ፡ ከአትባራ ፡ ወዲያ ፡ ያሉት፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከሺህ ፡ ስድስት፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ፡ በግብፆች ፡ ተገዝተው ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ በ፰፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ መልሰው ፡ ግብፆችን ፡ የገዙበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ግብፅን ፡ መልሰው ፡ የገዙት ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንጂ ፡ ሳባውያንና ፡ ሐበሳን ፡ አይደሉም ። ሳባውያንና፡ ሐበሳን ፡ ከየመን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ የገቡበት ፡ ጊዜ ፡ የዛሬ ፡ ሊቃውንትና ፡ መርማሪዎች ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ቢበዛ ፡ ፰፻ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ላይ ፡ አድርገውታል ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ሥልጣኔና ፡ ፈደል ፡ የሌላቸው ፡ ሳባውያን ፡ ገብተው ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ።

እስከ ፡ እዚህ ፡ ጊዜ፡ እስከ ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ግን ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከግብፅ ፡ ጋር ፡ ንግዳቸውን ፡ በሰላም ፡ ይቀጥሉ ፡ ነበር፡ የንግዱም፡ ዓይነት ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ ብርጉድ፡ የዝኆን ፡ ጥርስና ፤ የአውራሪስ ፡ ቀንድ ፤ የአውሬ ፡ ቆዳ ፡ ለቤተ ፡ መቅደስና ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚያገለግል ፡ እንጨትና ፡ ባርያ ፡ ሌላም ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለ ፡ ነው ።



በ፪ሺ፯፻፶፱—፪ሺ፭፻፺፰ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የአምስተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ የግብፅ፡ ንጉሥ ፡ ነፈርቃል፡ በነገሠ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ (ከኩሽ፡ አገር)፡ ውስጥ፡ ድንክዬዎች ፡ የኔን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የሐጾርን ፡ (ሐትሆር ፡ ሴት ፡ ጣዖት) ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በጭፋሮ ፤ በዘፈን ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኙ ፡ ይዘህልኝ ፡ና ፡ ብሎ፡ ሖረሐዋይ ፡ ለሚባለው ፡ ሹም ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎለት ፡ ይገኛል ። በደብዳቤውም ፡ ላይ ፡ እነዚህን ፡ ድንክዬዎች ፡ ከአገራቸው ፡ ይዘህ ፡ ስትመጣ ፡ በመንገድ ፡ እንዳይጠፉ ፡ በመርከብ ፡ አድርገህ ፡ በጉዞም፡ ጊዜ ፡ ባሕር ፡ እንዳይገቡ ፡ ሌሊት ፡ አሥር ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ እየተነሣህ ፡ እየፈተሽህ፡ በጥንቃቄ፡ ይዘህ፡ አምጣልኝ ። ለኔ፡ ከዕንቍም፡ ከወርቅም ፡ ይበልጥ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘኝ ፡ እነዚህን ፡ ድንክዬዎችን ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ይኸንን ፡ ስታደርግ ፡ ለልጅ ፡ ልጅህ ፡ የሚተላለፈው፡ የምሰጥህ ፡ ሽልማት ፡ ትልቅ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ጨምሮ፡ ገልጾለታል ።

እንግዲህ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ የግብፅና ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ መንግሥቶች ፡ ለየብቻ ፡ ንግድና ፡ ሥልጣኔ፡ እየተለዋወጡ፡ ሲኖሩ ፡ የአምልኮአቸውም ፡ ዓይነት ፡ ፀሐይዋን ፡ ወርካውን ፡ ተራራውን ፡ ወንዙን ፡ (ዓባይን) ፡ አሞራን ፡ በማምለክ ፡ ይመሳሰላል ። ለነዚህም ፡ የሚያቀርቡት ፡ የእንስሳና ፡ የእዝርዕት ፡ መሥዋዕት ፡ ይቀራረባል ። ነገሥታቶቻቸውንም ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ እያዩ፡ በማክበር ፡ ይገናኛሉ ። በተረፈ፡ ከቤት፡ መሣሪያ፡ ውስጥ ፡ ቢላዋው ፡ ምጣዱ ፡ ዶማው ፡ ማረሻው፡ የጦር ፡ መሣሪያው ፡ እንካሴው፡ ጦሩ፡ ሾተሉ ፡ ይመሳሰላል ።

እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የግብፅና ፡ የኑብያ ፡ አገሮች ፤ እስከ ፡ እዚህ ፡ እስከ ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት፡በፊት፡ ድረስ ፡ በጉርብትና ፡ በሰላም፡ ሲኖሩ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ የውጭ፡ ወረራ ፡ እንደአጠቃቸው ፡ እነሆ ፡ እንመለከታለን ።

በ፪ሺ፳ ፡ በ፩ሺ፰፻ ፡ መካከል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ ያነሣነው ፡ ራማ ፡ (የማጋዳና ፡ የእዮዲያ ፡ ማሐራጃ) ፡ የሚባለው ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ፡ ሕንድን ፡ ሰይላንን ፡ ዓረብን ፡ ፋርስን ፡ ከለዳውያንን፡

አሸንፎ ፡ ግብፅን ፡ ወረረ ። የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ሲዋጋ ፡ ሞተ ። ተከታዮቹም ፡ መዋጋት ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ሲረዱት ፡ ገበሩ ። እንደዚሁም ፡ ይኸው ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ራማ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ ውስጥ ፡ ኢ.ኦሬ፡ አንደኛ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ ኢ.ኦሬን ፡ ወግቶ ፡ መንግሥቱን ፡ ያዘበት። በኋላ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ አከናውሰ ፡ ሳባ ፡ ሁለተኛን ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ የራማን ፡ ንጉሥ ፡ ተዋግተው ፡ ገደሉት ፡ ሲል ፡ ባንዳንድ ፡ የውጭ ፡ አገርም ፡ በአገራችንም ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ራማ ፡ የሚባል፡ የሕንድ፡ ንጉሥ፡ የግብፅን ፡ ንጉሥ ፡ ገድሎ ፡ አገሩን ፡ ገዛ ፡ የሚል ፡ በግብፆች ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አይገኝም ። ከ፪ሺ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፯፻፹፰፡ ድረስ ፡ በ፲፪ኛው፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ተመሥርተው ፡ ግብፅን ፡ ያስተዳድሩ ፡ የነበሩት ፡ የቴብ፡ ዘር ፡ የሆኑት ፡ ነገሥታት ፡ አሜኔምሐት ፡ ፩ኛ ፡ ሳኑስትሪ ፡ ፩ኛ ፡ ( ሴሶስትሪስ ) ፡ አሜኔምሐት ፡ ፪ኛውና ፡ ፫ኛው ፡ ሳኑስትሪ ፡ ፪ኛው ፡ በሚገዙበት ፡ በሁለት ፡ ሺና ፡ በሺ፯፻፹ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ራማ ፡ የሚባል ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ገዛቸው ፡ የሚል ፡ የለም ። ከ፩ሺ፯፻፹ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፭፻፹ ፡ ባለው ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የጠቀስናቸው ፡ የሂክሶስ ፡ ዘሮች ፡ ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ ግብፅን ፡ ገዝተዋል ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ራማ ፡ የሚሉ ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ የለም ።

ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ራማን ፡ ተዋግተው ፡ የገደሉ ፡ ሒክሶስ ፡ የሚባሉ ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡ ፡ ኃይለኛ ፡ ሕዝቦች ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበሩ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን፡ ወይም ፡ የነገደ ፡ ሳባ ፡ ዘሮች ፡ አይደሉም ፡ የሚሉ ፡ አሉና ፡ ስለራማ ፡ ወደፊት ፡ እስኪጣራ ፡ ድረስ ፡ እንዳለ ፡ እንተወው ።

ግማሾቹ ፡ ሒክሶስ ፡ የተባሉት ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ አይደሉም ፡ የሚሉ ፡ ግማሾቹም ፡ ሒክሶስ ፡ የተባሉት ፡ እነዚያው ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ናቸው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ስማቸው ፡ ሒክሶስ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ እየተባለ ፡ ቢለያይም ፡ ሁለቱም ፡ የመጡበት ፡ ሥፍራ ፡ ያው ፡ ምሥራቅ፡ ዘራቸውም ፡ ሁለቱም ፡ ሴማዊ ፡ ስለሆነ



ነገሩ ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ። ምናልባት ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣንም ፡ ሒክሶስም ፡ የዘራቸው ፡ ግንድ ፡ ያው ፡ ዮቅጣን ፡ ሆኖ ፡ ሒክሶስ ፡ በላይ፡ በሰሜን ፡ በሦርያ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ የምንላቸው ፡ በታችኛው ፡ ዓረብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተው ፡ ይሆናል ።

እነዚሁም ፡ ሒክሶስ ፡ የሚባሉት ፡ ዘሮች ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ግብፅን ፡ ገዝተው ፡ ሲወጡ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተመሥርተው ፡ መቅረታቸውን ፡ እንጂ ፡ ተመልሰው ፡ ወጡ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ የለምና ፡ ሁለቱ ፡ የተለያዩ ፡ የነገድ ፡ ቅርንጫፎች ፡ መሆናቸውን ፡ ይኸም ፡ የሚያበረዳ ፡ ይመስላል። ነገር ፡ ግን ፡ ዘሩ ፡ አንድ፡ ሆኖ ፡ ቅርንጫፉ ፡ ለየብቻ ፡ የሆነ ፡ ሁለት ፡ ነገድ ፡ ለየብቻ ፡ በሁለት ፡ አገር ፡ ገብቶ ፡ በግዛት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ አንደኛው ፡ ተሸንፎ ፡ መውጣት ፡ አንደኛው ፡ ተመሥርቶ ፡ መቅረት ፡ የተለመደ ፡ ነው። ስለዚህ ፡ ከምሥራቅና ፡ ይልቁንም ፡ ከወደ ፡ እሶር ፡ መጥተው ፡ ግብፅን ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የገዙት ፡ ሒክሶስ ፡ ብዙ፡ ጊዜ ፡ በግብፅ፡ ሕዝብ፡ ላይ ፡ የጭቆና ፡ ሥራ ፡ ስለአሳዩ ፡ ሕዝቡና ፡ ሹማምንቱ ፡ ጠልተዋቸው ፡ የሚያስወጡበትን ፡ ጊዜና ፡ መንገድ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ገዥዎቹ ፡ ሒክሶስ ፡ አብዛኛው ፡ መቀመጫቸው ፡ በሰሜናዊ ፡ ግብፅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የደቡብን ፡ ሕዝብ ፡ ክፍል ፡ በደንብ ፡ ለመቈጣጠር ፡ አልቻሉም ፡ ነበርና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ የግብፅ ፡ መሳፍንትና ፡ ሕዝብ ፡ በሰሜን ፡ ያሉትንም ፡ ወገኖቻቸውን ፡ እየቀሰቀሱ ፡ አንድነት ፡ ተዘጋጅተው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ተጉዘው ፡ ሒክሶስን ፡ ተዋግተው፡ ከአስወጡ ፡ በኋላ ፡ የራሳቸውን፡ መንግሥት ፡ መልሰው ፡ አቆሙ ።

የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ግን ፡ ሁኔታው ፡ እንደታሪኩ ፡ ከሒክሶስ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ መጀመሪያ ፡ በምሥራቅ ፡ ምናልባት ፡ በባቢሎን ፡ ሲኖሩ ፡ የባቢሎንን ፡ ሥልጣኔ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መጡ ። በደቡብ ፡ ዓረብም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ሕንዶች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ እየወጉ ፡ ስለአስቸገሩዋቸው፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለምለም ፡ አገር ፡ ፍለጋ፡

ይሁን ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ተሻግረው ፡ ተቀመጡ ።

ከዚያም ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ግማሾቹ ፡ በትግሬ ፡ ግማሾቹ ፡ በእዳል ፡ ግማሾቹ ፡ በውጋዴን ፡ አገር ፡ ተከፋፍለው፡ በሰላም ፡ ሲኖሩ፡ እንደባላገር ፡ ይኸም ፡ ቢቀር ፡ እንደ፡ መልካም ፡ እንግዳ ፡ ይቆጠሩ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሒክሶስ ፡ በግብፆች ፡ እንደተጠሉ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የአገር ፡ ተወላጅነት ፡ ባለው ፡ በነገደ ፡ ካም ፡ ዘንድ ፡ የተጠሉ ፡ አይመስልም ። ተገኘ ፡ የባዕድ ፡ ገዥን፡ መጥላቱ፡ ገዥም፡ እየገበረ ፡ በሰላም ፡ የሚቀመጠውን ፡ አለመጥላቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው። የሩቁን ፡ ዘመን ፡ የሚተርከው ፡ የዛሬው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ የሚለው ፡ እርግጥ ፡ እንደሆነ ፡ የሕንድ፡ ንጉሥ፡ ራማ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ፡ መጥቶ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ንጉሥ ፡ ኪአሪን ፡ ወግቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባስገበረ ፡ ጊዜ ፡ እነዚሁ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከያለበት ፡ ተሰብስበው ፡ ከመካከላቸው ፡ አከናሁስን ፡ አንግሠው ፤ የሕንዱን ፡ ንጉሥ ፡ ራማን ፡ ተዋግተው ፡ ስለአስወጡ ፡ ነገደ ፡ አጋዓዝያን ፡ (ነፃ ፡ አውጭዎች) ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ተሰጣቸው ።

ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ነፃ ፡ ባወጡት ፡ አገር ፡ በነገደ ፡ ካም ፡ ነገሥታት ፡ ምትክ ፡ ገብተው ፡ መንግሥታቸውን ፡ መሠረቱና ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ሕዝብ ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ ዘር ፡ ጋር ፡ ተደባልቀው ፡ ይኖሩ ፡ ጀመር ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን፡ በኢትዮጵያ ፡ የቆየው፡ የካም ፡ ሕዝብ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የመጣው ፡ የዮቅጣን ፡ ሕዝብ ፡ በልማድ፤ በወግና ፡ በሥርዓት ፡ በእምልኮ ፤ በቋንቋ ፡ መለያየታቸው፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ ከመርዌ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ባለው ፡ በሰፌው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ እየተለያዩም፤ እየተገናኙም ፡ ኃይለኛ፡ ሆኖ ፡ ለነገሠው ፡ እየገበሩ ፡ ያም ፡ ሲጠፋ፡ እየተለያዩ ፡ በየነገዳቸው፡ እንደልማዳቸው ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከመካከላቸው ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ሥልጡኖችና ፡ ጽሑፍ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ፡ ቢባልም ፡ ይህ ፡ እስካሁን ፡ የተገኘው ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ ዘመኑ ፡ በግምት ፡ ከ፳፻ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ነውና ፡ ምናልባት ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ፊደል ፡ የሌለውና ፡ ያልሠለጠነ ፡ የሴምና ፡ የዮቅጣን ፡ ዘር ፡ መጥቶ ፡ ከካሙና፡ ከኩሹ ፡ ጋር፡



ተደባልቆ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደተባለው ፡ በዛሬዪቱ፡ ኢትዮጵያና፡ በጥንታዊቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኑብያ ፡ (ሱዳን) ፡ ጭምር ፡ ሲኖሩ ፡ የነገዳቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ስም ፡ የሚቀመጡበትን ፡ ሥፍራ ፡ የሚመገቡትን ፡ እንስሳ ፤ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ እንደ ፡ አጋርታቪድ ፡ እውነትም ፡ ስሕተትም ፡ የተደባለቀ ፡ ባይጠፋበት ፡ እነሆ ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ። ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ ደግሞ ፡ እነዲዮዶር ፡ ከጻፉት ፡ ከጥንታውያኑ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ልማድ ፡ የለቀምን ፡ እንደሆን ፡ ከዚህ፡ የሚከተለው ፡ ምዕራፍ ፡ የሚያበረዳንን ፡ እናገኛለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

### በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ንግድ- በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ- ንጉሥና ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ያገር ፡ ልማድ- ሃይማኖት ፡ -ጋብቻ ።

ይኸው ፡ የካምና ፡ የሴም፡ ዘር ፡ የሠለጠነው፡ የሳባና ፡ የሀባሳን ፡ ዘር፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፳፻ ፡ መቶ ፡ ዓመት ግድም ፡ መጥቶ ፡ ደምበኛ ፡ ሥልጣኔውን ፡ እስኪተክል ፡ ድረስ ፡ ከተከለም ፡ በኋላ ፡ ከኑብያ ፡ ወዲህ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ያሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ያላቸውን ፡ የንግድ ፡ የልማድ ፡ የሃይማኖትና ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

### ንግድና ፡ ሸቀጥ ።

የሸቀጡ ፡ ዓይነት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደጻፍነው ፡ ዕጣን ፤ ከርቤ ፤ እንጨት ፤ የአውሬ ፡ ጥርስና ፡ ቀንድ ፡ ባርያ ፤ ደግሞ ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡት ፡ ሥልጡኖቹ ፡ ልብስ ፤ ሽቱ ፤ እንደ ፡ እንባር ፤ እንደ ዶቃ ፡ ያሉ ፡ ጌጣጌጥ ፡ አያጡም ። ሸቀጥ ፡ ለሸቀጥ ፡ ሲገበያዩ ፡ መለኪያቸው ፡ ዛሬም ፡ በባላገር ፡ ሲደረግ ፡ እንደምናየው ፤ ከንድ ፤ መዳፍ ፤ ጣት ፡ ነው ። በተረፈ ፡ እንደ ፡ መቃ ፡ እንደ ፡ ዘንግ ፡ ያለ ፡ መለኪያ ፡ አላቸው ። እንደ ፡ እህል ፡ የመሰለውንም ፡ የሚለኩበት ፡ የሸክላ ፡ ማሰሮና ፡ እንዳንዶቹም ፡ የነሐስ ፡ ማሰሮ ፡ የመበለ ፡ ነበራቸው ። ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ እነሆ ፡ መሻሻል ፡ ባላገኙ ፡ ባላገሮቻችን፡

ዘንድ ፡ ዛሬም ፡ ሲሠራበት ፡ ስለምናይ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ርቀት ፡ የመሣሪያውና ፡ የሸቀጡ ፡ ዓይነት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሊያስደንቀን ፡ አይችልም ።

## በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ ።

ሁለት ፡ ነገድ ፡ ሲጣላ ፡ ሁለቱም ፡ የጠላት ፡ ወገኖች ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ጉዞ ፡ ያደርጋሉ ። በጉዞ ፡ ንጉሣቸው ፡ የግማሾቹ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ (ጋሪውን)፡ ከፊት ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ እየጐተተው ፤ የግማሹ ፡ ንጉሥ ፡ በመሐል ፡ በእግሩ ፡ ወይም ፡ በኳብት ፡ እየተጓዘ ፡ በዘፈን ፡ በጭፋር ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ይሔዳል ። ጦርነቱም ፡ ሊጀመር፡ አቅራቢያ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ለመቀስቀስ ፡ ጭፋሮው ፡ ከፊተኛው ፡ ይደምቃል ። በሁለቱም ፡ እጅ ፡ ያለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በትንሹ ፡ ይለያያል ፡ እንጂ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ያው ፡ የታወቀው ፡ ደንጊያ ፡ ( የሾለ ፡ ወይም ፡ ስለት ፡ ያለው ፡ ) ቀንድ ፤ ወንጭፍ ፤ አንካሴ ፤ ጦር ፤ ቢላዎ ፤ መጥረቢያ ፡ ቀስት ፤ ፍላጻ ፡ መመከቻው ፡ የቆዳ ፡ ጋሻ ፡ ከጋሻም ፡ በተለይ ፡ ዓይነት ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ውጊያው ፡ የሚጀመረው ፡ ከሁሉ ፡ መሣሪያ ፡ በሚረከሰው ፡ በደንጊያ ፡ ነው ። ከሩቅ ፡ ጀምረው ፡ እየተወራወሩ ፡ በተጠጋጉ ፡ ጊዜ ፡ የቀስቱ ፡ ከዚያም ፡ የአንካሴው ፡ የጦሩ ፡ በትር ፡ ይቀጥልና ፤ ሲገናኙና ፡ ሲደባለቁም ፡ የቢላዋና ፡ የጩቤው ፡ ሥራ ፡ በተራው ፡ ይደርሳል ። መቼም ፡ ሁለት ፡ ወገኖች ፡ ተዋግተው ፡ አንደኛው ፡ መሸነፉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የተሸነፈውና ፡ የተማረከው ፡ ወገን ፡ ወዮለት ። ከምርኮ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ማናቸውንም ፡ የእብሪት ፡ ሥራ ፡ አሸናፊዎቹ ፡ በተሸናፊዎቹ ፡ ይፈጽሙባቸዋል ። ንጉሥ ፡ የነበረው ፡ የአሸናፊውን ፡ ንጉሥ ፡ ሠረገላ ፡ በእግሩ ፡ እየሄደ ፡ መጐተት ፡ የቀረውም ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ቀንበር ፡ ተሸክሞ ፡ በገመድ ፡ የፈጥኝ ፡ መታሠርና ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ተቆጥሮ ፡ መሥራት ፡ መዋረድ ፤ መገጠጥ ፤ አለበት ። በገርግንነት ፡ መዋጋቱንም ፡ አውቀው ፡ አሸናፊዎቹ ፡ በልባቸው ፡ ሲያከብሩትም ፡ ከምርኮ ፡ በኋላ ፡ የውርደት ፡ ሥራ ፡ በራሱም ፡ በሚስቱም ፡ በቤት ፡ ሰቡም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይፈጽሙበታል ። የተሸናፊው ፡ ቆንጆ ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ልጅ ፡



ወዲያው ፡ ያሸናፊው ፡ ሚስቶች ፡ ይሆናሉ ። የቀሩት ፡ ይኸን ፡ የጋብቻ ፡ ዕድል ፡ ያላገኙት ፡ የባርነት ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። ሳይዋጋም ፡ በቶሎ ፡ የገበረና ፤ ያመነም ፡ ሲኖር ፡ ከውርደት ፡ አይድንም ። እንደ ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ እየተቆጠረ ፡ መሰደብንና ፡ መወቀስን ፡ ይጨምራል ።

## ንጉሥና ፡ አንዳንድ ፡ ያገር ፡ ልማድ ።

እንደ ፡ ዲዎዶር ፡ አጻጻፍ ፡ ግብፆች ፡ ንጉሣቸውን ፡ ፈርዖን ፡ እንደሚሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ደግሞ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፪ሺ-፺፱ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ንጉሣቸውን ፡ ሱተን ፡ ይሉት ፡ ነበር። ሱተን ፡ ማለት ፡ በጥንታዊ ፡ የግብፅ ፡ ቋንቋ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የንጉሥ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ማለት ፡ ነው ። በተረፈ ፡ የኢትዮጵያውያኖቹ ፡ እንደ ፡ ግብፆች ፡ ንጉሥ ፡ ከመንገሡ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ ( ስመ ፡ መንግሥት ) ይሰጠዋል ። የዚህም ፡ ልማድ ፡ እነሆ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሲቀጥል ፡ እናያለን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የእምላክነት ፡ ደረጃ ፡ ሲሰጡት ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ አማልክት ፡ ስም ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ አድርገው ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ይጨምሩለታል ። እንደዚህ ፡ የበረከተ ፡ ያንድ ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ በአጻጻፍ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እየአሳሳተ ፡ አስቸግሯል ።

ያመራረጣቸው ፡ ወገን ፡ ያንዱ ፡ ነገድ ፡ ከሌላው ፡ መለያየት ፡ አለበት ። ለምሳሌ ፡ የናፓታና ፡ የመርዌዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ንጉሥ ፡ የሚያነግሡት ፡ ከሕዝቡ ፡ ውስጥ ፡ መልኩ ፡ ከአምላካቸው ፡ ከአሞን ፡ (አሜን-አሙን) ፡ ምስል ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለውን ፡ ነው ፡ መራጮቹ ፡ ካህናቱ ፡ ናቸው ። ከተመረጠም ፡ በኋላ ፡ በክብር ፡ ከአምላኩ ፡ ጋር ፡ ባይተካከልም ፡ ወደዚያው ፡ ይጠጋል ። የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ከላይ ፡ ሲያያዝ ፡ በባላባትነት ፡ የወረደውን ፡ ወይም ፡ ቀንደኛ ፡ ሆኖ ፡ የተነሣውን ፡ ወይም ፡ ኸግና ፡ ሆኖ ፡ ጠላትን ፡ የመለሰውን ፡ አገር ፡ በመውረርና ፡ በጉብዝና ፡ የታወቀውን ፡ ያነግሣሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ማንኛውም ፡ አብዛኛው ፡ ንጉሥ ፡ ከነገሠበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ክብርና ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ። በነገሠበት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከዛሬ ፡ ዘመን ፡ ዲክታተር ፡ ይበልጥ ፡ የልቡን ፡ ይሠ

ራል ። የሚስቶቹ፡ ቍጥር፡ ወሰን፡ የለውም ። ልቡ፡ ከፈቀደ፡ እንቁንም፡ ልጆቹንም ፡ የልጅ ፡ ልጆቹንም ፡ ማግባት ፡ ይችላል ። እንደርሱ ፡ ክጣዖት ፡ ካህናት ፡ በስተቀር ፡ የቀሩት ፡ ሹማምንቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ያገቡ ፡ ነበር ።

ባንድ ፡ ምክንያት፡ ወይም ፡ ባደጋ ፡ የንጉሡ ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ እግር ፡ የተቆረጠ ፡ እንደሆን ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ተለይተው ፡ ሙሉ ፡ ሰውነት ፡ ይዘው ፡ ደስታ ፡ እንዳያገኙ፡ እንደልማድ ፡ ሆኖ ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ የሚቆረጡ ፡ ነበሩ ። ሲሞት ፡ አብረው ፡ የሚሞቱ ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ የንጉሥ ፡ ሕይወትና ፡ አካል ፡ የሁሉም ፡ የሕይወት ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፡ አክብረው ፡ ተጠንቅቀው ፡ ይጠብቁታል ።

ያንደኛው ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም፡ ትልቅ፡ ሰው ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ በአቧራ ፡ ራሳቸውንና ፡ ፊታቸውን ፡ እየፈተጉ ፡ የሚያለቅሱ ፡ እንጂ ፡ ራሳቸውን ፡ የማይገድሉ ፡ አሉ ። የነገዱ ፡ ልማድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ። ከወንድ ፡ ንጉሥ ፡ የሴት ፡ ንግሥት ፡ መርጠው ፡ በሴት ፡ የሚገዙ ፡ አሉ። እነሱም፡ እንደ፡ ቤግሜይ፡ እንደ፡ አስማክ፡ ያሉት፡ ናቸው ። በመርዌም፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥታት ፡ የሚባሉ ፡ በሕንደኬ ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ እንደነበሩ ፡ ከሥፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እናገኛለን ።

ባለፈው ፡ በዝርዝሩ ፡ እንደ ፡ ሰማነው ፡ አንዱ ፡ ነገድ ፡ በዝኆን ፡ ሌላው ፡ በዓሣ ፡ ሥጋ ፡ ሌላው ፡ በጥራጥሬ ፡ እህል ፡ አንዱ ፡ በፍራፍሬና፡ በዛፍ፡ ሥር፡ ምግብ፡ የሚኖሩ፡ አንዱ፡ በዛፍ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ በዋሻ ፡ የሚቀመጥ ፡ አንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ ሰው ፡ ሲሞትበት ፡ አሥሮ ፡ እዛፍ ፡ ላይ፡ የሚያንጠለጥል ፡ ሌላው ፡ በመሬት፡ የሚቀብር፡ ወይም፡ እሜዳ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ። ድንጋይ ፡ የሚቆልል ፡ አንዱ፡ ወደ ፡ ባሕር፡ የሚጨምር ፡ አለ ። ልብሱም ፡ እንደደረጃቸው ፡ ቅጠል ፡ ቆዳ ፡ ኬሻ ፡ ልብስ ፡ የሚለብሱ ፡ አሉ ። የጥንት ፡ የካም ፡ ወይም ፡ የኩሽ፡ ነገድ ፡ በየሥፍራው ፡ የሚኖርበት ፡ ሕይወት ፡ ዛሬም ፡ ሲሆን ፡ በአማራም ፡ በትግሬም ፡ ባላገር ፡ ይልቁንም፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ፡ በአሩሲ ፡ በባሌና ፡ በሌላውም ፡ በልዩ፡ ልዩ፡ በአፍሪካ፡ በእስያና፡ በአውስትራልያ ፡ አህጉር ፡ ከሚኖረው ፡ ሕዝብ፡ ሕይወት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ አይመስልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥልጣኔን፡ ከባቢሎንና፡ ከምሥራቅ፡ ይዘው ፡ የመጡት ፡ ወይም ፡ ከግብፅ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ በማድረግ ፡ ሥልጣኔን ፡



የተካፈሉት ፡ ወገኖች ፡ ከሌላው ፡ ነገድ ፡ በቤትም ፡ ሥራ ፡ በመጣሪያም ፡ በልብስም ፡ በማናቸውም ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ይገኛሉ ፡ መጻፊያ ፡ ፊደልና ፡ ንግግራቸውን ፡ የሚቀርጹበት ፡ የሰዋሰው ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ነበራቸው ።

## ሃይማኖት ።

የቀድሞ ፡ ኢትዮጵያም ፡ የሌላውም ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ስለጋብቻ ፡ ሕግ ፡ ስለአልተሰጠው፡ ራሱ፡ በአሰበውና፡ በፈቀደው ፡ መንገድ፡ ይኖር፡ ነበር ። በሥልጣኔ፡ ዝቅ ፡ ያለው ፡ በዛፍ፡ በተራራ ፡ ያመልካል ፡ የሠለጠነው ፡ ወገን ፡ አምላክ ፡ መኖሩን ፡ ያምንና ፡ አምላኩን ፡ በሰው ፡ በፀሐይ ፡ በጨረቃ ፡ እየመሰለ ፡ ከዚያም ፡ በበሬም ፡ በበግም ፡ በአሞራም ፡ . . . ሊያድር ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ በነዚሁ ፡ እንስሶች ፡ ምስሉንና ፡ ሐውልቱን ፡ በድንጋይም ፡ በብረትም ፡ በብርም ፡ በወርቅም ፡ እየሠራ ፡ ለአማልክቱ ፡ ምስል ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እያነፀ ፡ ለቤተ ፡ መቅደሱና ፡ ለአማልክቱ ፡ በየደረጃው ፡ ካህናትና ፡ ነቢያት ፡ አበልና ፡ ደረጃ ፡ እየተወሰነ ፡ የአምልኮ ፡ ሥራቸውን ፡ ያከናውናሉ ።

የጥንት ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ አምልኮ ፡ ከዚያውም ፡ ከግብፅ ፡ የሚዋሰኑት ፡ የናፓታና ፡ የመርዌዎቹ ፡ አምልኮአቸው ፡ ከግብፅ ፡ ይገናኛል ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በመገምሪያ ፡ ካምን ፡ የኖኅን ፡ ልጅ ፡ እንደአምላክ ፡ ያመልኩት ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የታወቁት ፡ አማልክት፡ አሞን ፡ ኦሲሪስ ፡ ኑም ፡ ቶት ፡ አሲስ ፡ ቤትባቴ ፡ ሖዖር ፡ (ሐትሖር) ፡ ባራፖስ ፡ ናቸው ። ዐባይም ፡ ራሱ ፡ ፀሐይም ፡ ራሷ ፡ አማልክት ፡ ናቸው ። የተራቀቁት ፡ ደግሞ ፡ ዐባይና ፡ ፀሐይ ፡ ሁለቱም ፡ የአምላክ ፡ ይኸውም ፡ የአሞን ፡ ስጦታ ፡ ስለሆኑ ፡ ግማሽ ፡ አማልክት ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ ይገኛል ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ክርስትና ፡ እስኪሸረው ፡ ድረስ ፡ አሞን ፡ ሁሉን ፡ ደምስሶ ፡ ፀሐይም ፡ ዋናውም ፡ አምላክ ፡ እሱ ፡ ሆኖ ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ ገናናነት ፡ በቴብ ፡ በመርዌ ፡ በናፓታ ፡ ሲመለከበት ፡ ሲሰገድለት ፡ኖርዋል ። የርሱንም ፡ አምላክ

ነት ፡ ከዚህ ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በናፓታው ፡ በሮምያን ኪና ፡ በታላቁ ፡ ፈርዖን ፡ በራምሲስ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ጽፈንስታል ።

በተረፈ ፡ የአገር ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ በኅብረት ፡ የሚያከብረው ፡ አንዱ ፡ አውራጃ ፡ ከሌላው ፡ ይበልጥ ፡ ለግሉ ፡ የሚወደውና ፡ የሚያከብረው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ አለው ። ከሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለችው ፡ ፀሐይ ፡ ግን ፡ በአሞን ፡ ስም ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ (መርዌ) ፡ ተከብራ ፡ ይሰገድላት ፡ ነበር ። ከኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ከግብፅ ፡ ደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚገኙት ፡ የብለሚ ፡ (አገው ፡ ?) ሰዎች ፡ የሰው ፡ ቍርባን ፡ ለፀሐይ ፡ ያቀርቡላት ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በጥሻ ፡ ነዋሪ ፡ በበረሃ ፡ ተቀማጭ ፡ የተባሉት ፡ ሁሉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ፀሐይን ፡ (አሞንራ)ያመልኩ ፡ ነበር ። የመርዌ ፡ ነገሥታት ፡ እንደቴብ ፡ እንደመምፊስ ፡ የግብፆች ፡ ነገሥታት ፡ የአሞንራ ፡ (የፀሐይ) ፡ ካህናት ፡ ሲሆኑ ፡ ሚስቶቻቸው ፡ ደግሞ ፡ የሙት ፡ (የጨረቃ) ፡ ካህንነት ፡ ነበራቸው ።

ጋብቻ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ የአሪትና ፡ የክርስትና ፡ የቡድሀ ፡ ወይም ፡ የእስላም ፡ ሕግ ፡ ስለሌለው ፡ ነገሥታቱም ፡ ሹማምንቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ብዙ ፡ ሚስት ፡ ያገባሉ ፡ ከባዕድ ፡ ወገን ፡ ካገቡ ፡ በኋላ ፡ አባታቸው ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ እናታቸውን ፡ አኅታቸውን ፡ ልጃቸውንም ፡ ሊያገቡ ፡ ይችላሉ ። ባለፈው ፡ እንደ ፡ አነበብነው ፡ በአንዳንድ ፡ ነገድ ፡ ዘንድ ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ እናት ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እገሌት ፡ የእገሌ ፡ ሚስት ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ መወሰን ፡ አልነበረም ። ይኸም ፡ ለዛሬ ፡ ጊዜ ፡ አሠቃቂ ፡ ሲመስለን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የተለመደ ፡ በመሆኑ ፡ ምንም ፡ አይሰጋበትም ፡ ነበር ።

ጳውሎስ ፡ እንዴት ፡ ያምናሉ ፡ መምህር ፡ የሌላቸው ፡ ሐዋርያ ፡ ያልተላከላቸው ፡ እንዳለው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እንኳን ፡ ሌላው ፡ ሕዝብ ፡ የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ እንኳን ፡ ሙሴ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ አሥርቱ ፡ ትእዛዛትን ፡ ተቀብሎ ፡ ሕጉን ፡ በእስራኤሎች ፡ ዘንድ ፡ እስኪያጠናው ፡ ድረስ ፡ ይኸ ፡ ልማድ ፡ ሳይደርስባቸው ፡ አልቀረም ፡ አባታቸው ፡ አብርሃም ፡ ሚስቱ ፡ ሣራ ፡ ያባቱ ፡ ልጅ ፡ እኅቱ ፡ ነበረች ፡ ወንድሙ ፡ ሎጥ ፡ በሽመገለ ፡ ጊዜ ፡ ከሴት ፡ ልጆቹ ፡ ጋር ፡ ይተኛ ፡ እንደነ




በር ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይናገራል ። ከዚያ ፡ ወዲህም ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ዘራችንን ፡ ከሌላ ፡ አንደባልቅም ፡ በማለት ፡ ከቤተሰባቸው ፡ ውጭ ፡ የማይጋቡ ፡ ነበሩ ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሚገኙ ፡ ነገዶቻችን ፡ ውስጥ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የወንድምን ፡ ሚስት ፡ ያልወለደችን ፡ ያባትን ፡ ሚስት ፡ ማግባት ፡ ስለነበረ ፡ ይህ ፡ ክርስትና ፡ በሠለጠነበት ፡ ዘመን ፡ ሲደረግ ፡ ያኛው ፡ ከ፫ሺ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ እምብዛም ፡ ሊያስገርመን ፡ አይችልም ።

ምዕራፍ ፭

ከግብፅና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ ማን ፡ ይቀድማል ? ።

በዚህ ፡ በያዝነው ፡ በ፳ያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያለው ፡ አንባቢ ፡ ሁሉ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ግብፅ ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ እንደነበረ ፡ በ፲፰ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ውስጥ ፡ የነገሡት ፡ ነገሥታትም ፡ ኢትዮጵያን ፡ አስገብረው ፡ እንደገዙና ፡ እንዳሠለጠኑ ፡ ያምናል ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ በየቋንቋው ፡ የተጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስንል ፡ የኑብያውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንጂ ፡ የአክሱሙን ፡ አለመሆኑን ፡ ላንባቢ ፡ እናስገነዝባለን ።

ነገር ፡ ግን ፡ የታሪክ ፡ አባት ፡ የሚባለው ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ሄሮዱት ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ መጥቶ ፡ ዓባይንም ፡ ጐብኝቶ ፡ በጻፈው ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፉ ፡ እንደዚሁም ፡ ዲዮዶር ፡ የሚባለው ፡ የሮማ ፡ ጸሐፊ ፡ ከግብፅ ፡ በፊት ፡ ሥልጣንና ፡ ገናና ፡ የነበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሆኗን ፡ እሷም ፡ በመዠመሪያ ፡ ግብፅን ፡ ወርራ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ አድርጋ ፡ መያዟን ፡ ግብፅንም ፡ ፲፰ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እንደገዟት ፡ ራሷ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ በማንም ፡ ተገዝታ ፡ የማታውቅ ፡ አገር ፡ መሆኗን ፡ ነገሥታቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ሥልጡን ፡ ደግ ፡ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡ ሰላማዊ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ዠግና ፡ ጐበዝ ፡ መሆናቸውን ፡ እያጋነኑ ፡ ጽፈዋል ። ኢትዮጵያም ፡ በአገር ፡ (ዢዮግራፊ)አቀማመጧ ፡ ከፍተኛ ፡ (ላዕላይ) ግብፅ ፡ ግን ፡ ወደታች ፡ (ታሕታይ) ስለሆነች ፡ ዓባይም ፡ ከላይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደታች ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ እየፈሰሰ ፡ እንደሚ




ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ግብፅን ፡ ሚያሳይ ፡ የካርታ ፡ ሥዕል ፡ (ተ ፡ ጸ ፡ መ)

ያጠጣት ፡ አፈርም ፡ እያቀበለ ፡ እንደሚመግባት ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ውሃው ፡ አወራረድ ፡ ሥልጣኔን ፡ ለግብፅ ፡ መዠመሪያ ፡ የሰጠች ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሆንዋን ፡ እነዚሁ ፡ የታወቁት ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነሱንም ፡ የተከተሉት ፡ ሁሉ ፡ አስፋፍተው ፡ ጽፈዋል ። በኋላ ፡ ግን ፡ ግብፅ ፡ ደግሞ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ያገኘችውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ይበልጥ ፡ አስፋፍታ ፡ እንደገና ፡ የ፲፰ኛውና ፡ የ፲፱ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ነገሥታት ፡ ኢትዮጵያን ፡ መልሰው ፡ እንደገዙ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ አይለው ፡ እንደገና ፡ ግብፅን ፡ ይዘው ፡ የ፳፭ኛውን ፡ ዲናስቲ ፡ (ሥርወ ፡ መንግሥት) ፡ እንደመሠረቱና ፡ እንደገዙ ፡ ተጽፏል ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ መና (መኔስ) የሚባለው ፡ ግብፃዊ ፡ የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ አገሮች ፡ ተብሎ ፡ ተከፍሎ ፡ የነበረውን ፡ በ፫ሺ ፡ ፩፻ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ መሥርቶ ፡ ከማቋቋሙ ፡ በፊት ፡ የሆነውን ፡ አናውቅም ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በ፩ሺ፯፻፹ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ሂክሶሶች ፡ መጥተው ፡ ፩ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከመግዛታቸውም ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ ባዕድ ፡ ግብፅን ፡ ወርሮ ፡ ገዝቶታል ፡ የሚል ፡ እስካሁን ፡ አልተገኘም ። እስከ ። ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከሂክሶሶች ፡ ጋር ፡ ፳፮ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ሲቀባበል ፡ ሁሉም ፡ የራሳቸው ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይኸን ፡ የመጨረሻውን ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ በየተራ ፡ መግዛዛት ፡ ሳይከዱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መዠመሪያ ፡ ሥልጡን ፡ ሆና ፡ ግብፅን ፡ መግዛቷን ፡ አይቀበሉም ። አስቀድሞ ፡ ሥልጡን ፡ የነበረና ፡ እንዲያውም ፡ ኢትዮጵያን ፡ (የኑብያውን ፡ ) በመጀመሪያ ፡ አስገብሮ ፡ ያሠለጠነ ፡ ግብፅ ፡ መሆኑን ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ የተከተለው ፡ በርክቷል ። ይኸንንም ፡ ለማለት ፡ ያደረሳቸው ፡ አሁን ፡ በመጨረሻው ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ የፈረንሣዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ የጀርመንና ፡ ያሜሪካ ፡ መርማሪ ፡ ሊቃውንት ፡ በመምፊስ ፡ በቴብ ፡ በናፓታ ፡ በጥንታውያን ፡ ከተሞች ፡ ያለውን ፡ መሬት ፡ እያስቆፈሩ ፡ የሚያገኙትን ፡ የነገሥታትና ፡ የአማልክት ፡ ሐውልት ፡ የቤት ፡ ዕቃና ፡ መጣሪያ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተቀረጸ




ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ግብፅን ፡ ሚያሳይ ፡ የካርታ ፡ ሥዕል ፡ ( ተ ፡ ጸ ፡ መ )



ያጠጣት ፡ አፈርም ፡ እያቀበለ ፡ እንደሚመግባት ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ውሃው ፡ አወራረድ ፡ ሥልጣኔን ፡ ለግብፅ ፡ መገመሪያ ፡ የሰጠች ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሆንዋን ፡ እነዚሁ ፡ የታወቁት ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነሱንም ፡ የተከተሉት ፡ ሁሉ ፡ አስፋፍተው ፡ ጽፈዋል ። በኋላ ፡ ግን ፡ ግብፅ ፡ ደግሞ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ያገኘችውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ይበልጥ ፡ አስፋፍታ ፡ እንደገና ፡ የ፲፰ኛውና ፡ የ፲፱ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ነገሥታት ፡ ኢትዮጵያን ፡ መልሰው ፡ እንደገዙ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ አይለው ፡ እንደገና ፡ ግብፅን ፡ ይዘው ፡ የ፳፭ኛውን ፡ ዲናስቲ ፡ ( ሥርወ ፡ መንግሥት ) ፡ እንደመሠረቱና ፡ እንደገዙ ፡ ተጽፏል ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ መና ( መኔስ) የሚባለው ፡ ግብፃዊ ፡ የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ አገሮች ፡ ተብሎ ፡ ተከፍሎ ፡ የነበረውን ፡ በ፫ሺ ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ መሥርቶ ፡ ከማቋቋሙ ፡ በፊት ፡ የሆነውን ፡ አናውቅም ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ፺ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በ፩ሺ፺፻፹ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ሂክሶሶች ፡ መጥተው ፡ ፩ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከመግዛታቸውም ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ ባዕድ ፡ ግብፅን ፡ ወርሮ ፡ ገዝቶታል ፡ የሚል ፡ እስካሁን ፡ አልተገኘም ። እስከ ። ፺ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከሂክሶሶች ፡ ጋር ፡ ፳፬ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ሲቀባበል ፡ ሁሉም ፡ የራሳቸው ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይኸን ፡ የመጨረሻውን ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ በየተራ ፡ መገዛዛት ፡ ሳይክዱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መገመሪያ ፡ ሥልጡን ፡ ሆና ፡ ግብፅን ፡ መግዛቷን ፡ አይቀበሉም ። አስቀድሞ ፡ ሥልጡን ፡ የነበረና ፡ እንዲያውም ፡ ኢትዮጵያን ፡ (የኑብያውን ፡) በመጀመሪያ ፡ አስገብሮ ፡ ያሠለጠነ ፡ ግብፅ ፡ መሆኑን ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ የተከተለው ፡ በርክቷል ። ይኸንንም ፡ ለማለት ፡ ያደረሳቸው ፡ አሁን ፡ በመጨረሻው ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ የፈረንሣዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ የጀርመንና ፡ ያሜሪካ ፡ መርማሪ ፡ ሊቃውንት ፡ በመምፌስ ፡ በቴብ ፡ በናፓታ ፡ በጥንታውያን ፡ከተሞች ፡ ያለውን ፡ መሬት ፡ እያስቆፈሩ ፡ የሚያገኙትን ፡ የነገሥታትና ፡ የአማልክት ፡ ሐውልት ፡ የቤት ፡ ዕቃና ፡ መሣሪያ ፡ በላዩ ፡ላይ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተቀረጸ




ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ግብፅን ፡ ሚያሳይ ፡ የካርታ ፡ ሥዕል ፡ ( ተ ፡ ጸ ፡ መ )



ያጠጣት ፡ አፈርም ፡ እያቀበለ ፡ እንደሚመግባት ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ውሃው ፡ አወራረድ ፡ ሥልጣኔን ፡ ለግብፅ ፡ መገርመሪያ ፡ የሰጠች ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሆንዋን ፡ እነዚሁ ፡ የታወቁት ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነሱንም ፡ የተከተሉት ፡ ሁሉ ፡ አስፋፍተው ፡ ጽፈዋል ። በኋላ ፡ ግን ፡ ግብፅ ፡ ደግሞ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ያገኘችውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ይበልጥ ፡ አስፋፍታ ፡ እንደገና ፡ የ፲፰ኛውና ፡ የ፲፱ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ነገሥታት ፡ ኢትዮጵያን ፡ መልሰው ፡ እንደገዙ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ ኢትዮ ጵያውያኖች ፡ አይለው ፡ እንደገና ፡ ግብፅን ፡ ይዘው ፡ የ፳፭ኛውን ፡ ዲናስቲ ፡ ( ሥርወ ፡ መንግሥት ) ፡ እንደመሠረቱና ፡ እንደገዙ ፡ ተጽ ፈዋል ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ መና ( መኔስ ) የሚባለው ፡ ግብፃዊ ፡ የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ አገሮች ፡ ተብሎ ፡ ተከፍሎ ፡ የነበረ ውን ፡ በ፫ሺ ፡ ፩፻ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ መሥርቶ ፡ ከማቋቋሙ ፡ በፊት ፡ የሆነውን ፡ አናውቅም ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በ፩ሺ፯፻፹ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ሂክሶሶች ፡ መጥተው ፡ ፩ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከመግዛታቸውም ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ ባዕድ ፡ ግብፅን ፡ ወርሮ ፡ ገዝቶታል ፡ የሚል ፡ እስካሁን ፡ አልተገኘም ። እስከ ። ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከሂክሶሶች ፡ ጋር ፡ ፳፩ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ሲቀባበል ፡ ሁሉም ፡ የራሳቸው ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይኸን ፡ የመጨ ረሻውን ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ በየተራ ፡ መገዛዛት ፡ ሳይከዱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መገርመሪያ ፡ ሥልጡን ፡ ሆና ፡ ግብፅን ፡ መግዛቷን ፡ አይቀበሉም ። አስቀድሞ ፡ ሥልጡን ፡ የነበረና ፡ እንዲያውም ፡ ኢትዮጵያን ፡ (የኑ ብያውን ፡ ) በመጀመሪያ ፡ አስገብሮ ፡ ያሠለጠነ ፡ ግብፅ ፡ መሆኑን ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ የተከተለው ፡ በርክቷል ። ይኸንንም ፡ ለማለት ፡ ያደረሳቸው ፡ አሁን ፡ በመጨረሻው ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ የፈረንሣዊና ፡ የእ ንግሊዝ ፡ የጀርመንና ፡ ያሜሪካ ፡ መርማሪ ፡ ሊቃውንት ፡ በመም ፈስ ፡ በቴብ ፡ በናፓታ ፡ በጥንታውያን ፡ ከተሞች ፡ ያለውን ፡ መሬት ፡ እያስቆፈሩ ፡ የሚያገኙትን ፡ የነገሥታትና ፡ የአማልክት ፡ ሐውልት ፡ የቤት ፡ ዕቃና ፡ መጣሪያ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተቀረጸ

ውን ፣ ጽሑፍ ፣ (ሂዩሮግሊፍ ፣) የብራናውንም ፣ ጭምር ፣ እየተረጐሙ ፣ ተረዳን ፣ ባሉት ፣ መሠረት ፣ ነው ። ከዚህም ፣ ውስጥ ፣ በትክክል ፣ ስመለየትና ፣ ለመፍረድም ፣ እየአስቸገራቸው ፣ የዚህን ፣ ጉዳይ ፣ የተረኩበትን ፣ ምዕራፋቸውን ፣ በውልውል ፣ የተውት ፣ አሉ ። ደግሞ ፣ ምናልባት ፣ ወደፊት ፣ በናፓታና ፣ በመርዌ ፣ በናጋአ ፣ በዋጂኤ ፣ ሱፍራ ፣ . . . . በአክሱም ፣ ዙሪያ ፣ በዬሃ ፣ በከስከሴ ፣ በቆሃይቶ ፣ በደቅምሐሬ ፣ በማታራ ፣ በባረከናሃ ፣ በድሆና ፣ በደብረ ፣ ዳሞ ፣ በአዱሊስ ፣ በዳሕላቅ ፣ በሌላውም ፣ ሁሉ ፣ የኑብያና ፣ የአክሱም ፣ ይዞታ ፣ የሆነው ፣ ታሪካዊ ፣ ሥፍራ ፣ ሁሉ ፣ ያልተቆፈረው ፣ እየተቆፈረ ፣ የኢትዮጵያን ፣ ቀደምትነት ፣ የግብፅን ፣ ተከታይነት ፣ የሚያስረዱ ፣ ሐውልትና ፣ የጽሑፍ ፣ ቅርጽ ፣ የተገኘ ፣ እንደሆነ ፣ ጽሑፉ ፣ ሁሉ ፣ ሊለወጥ ፣ አንባቢም ፣ አባቡን ፣ ሊለውጥ ፣ ይችላል ። እስከዚያን ፣ ግን ፣ ከኑብያው ፣ ኢትዮጵያ ፣ በሥልጣኔ ፣ ግብፅ ፣ እንደሚቀድም ፣ እያሰብን ፣ የመጭውን ፣ ጊዜ ፣ ታሪክ ፣ መጠባበቅ ፣ ሳይሻል ፣ አይቀርም ።

አንዳንድ ፣ ጸሐፊዎች ፣ ከነዚያውም ፣ ጀምስ ፣ ብሩስ ፣ የሚባለው ፣ ወደኑብያና ፣ ወደ ፣ አበሻ ፣ ጉዞ ፣ በሚባለው ፣ መጽሐፉ ፣ ግብፅን ፣ ከክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በፊት ፣ ከ፩ሺ፯፻፶ ፣ እስከ ፣ ፩ሺ፮፻፶ ፣ ዓመት ፣ ድረስ ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ገዝተው ፣ ያስገበሩት ፣ የሂክሶስ ፣ ዘሮች ፣ በኢትዮጵያ ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ የተባሉት ፣ ናቸው ፣ በማለት ፣ ብዙ ፣ ማስረጃ ፣ ለማቅረብ ፣ ደክሟል (፩) ።

በዚህ ፣ ዓይነት ፣ ሂክሶስ ፣ የሚባሉት ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ በዓረብ ፣ አገር ፣ በኩል ፣ መጥተዋል ፣ የምንላቸው ፣ ለኢትዮጵያም ፣ ከነገደ ፣ ካም ፣ በኋላ ፣ እንደነገድ ፣ አባት ፣ የምናደርጋቸው ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ እንደሆኑ ፣ ግብፅ ፣ ኢትዮጵያን ፣ ከመግዛቷ ፣ በፊት ፣ (፩ሺ፮፻፹—፩ሺ፭፻) ፣ ዓመት ፣ ከክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በፊት ፣ አስቀድሞ ፣ ኢትዮጵያን ፣ በነዚሁ ፣ በሂክሶስ ፣ (ነገደ ፣ ዮቅጣን) ፣ ጊዜ ፣ ግብፅን ፣ ገዝታለች ፣ ማለት ፣ ነው ። ምንም ፣ እንኳን ፣ ሞኙ ፣ ኃይል ፣ ሲያገኙ ፣

(፩) JAMES BRUCE – VOYAGE... የካስቴራ ፣ ትርጉም ፣ ወደ ፣ ፈረንሳዊኛ ፣ ቮሊም ፣ ገጽ ፣ ፪፻፴፱ — ፪፻፵ ፣



ብልሑን ፣ ደካማው ፣ እንዳጋጣሚ ፣ ኃይለኛውን ፣ ለመግዛት ፣ የሚችልበት ፣ ጊዜ ፣ ባይጠፋ ፣ ግብፅን ፣ በዚያን ፣ ጊዜ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ከገዛች ፣ ከግብፅ ፣ ይበልጥ ፣ ኃይልና ፣ ሥልጣኔ ፣ ነበራት ፣ ያሰኛል ። ሂክሶስ ፣ የተባሉት ፣ እንደ ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ ተቆጥረው ፣ ግብፅን ፣ ገዙ ፣ የተባለውን ፣ ወደ ፣ ማመን ፣ ብንቀርብም ፣ ሂክሶስ ፣ ግብፅን ፣ ከመውረራቸው ፣ ፩ሺ፯፻፶ ፣—፩ሺ፮፻፶ ፣ ከክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በፊት ፣ ባለው ፣ ጊዜ ፣ ሁሉ ፣ ግብፆች ፣ መሠልጠናቸው ፣ መግነናቸው ፣ የታወቀ ፣ ስለሆነ ፣ በ፲፪ነኛውና ፣ ይልቁንም ፣ በዚሀ ፣ በያዝነው ፣ በ፯ያኛው ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ የሚጸፈው ፣ ሁሉ ፣ አብዛኛው ፣ ከኢትዮጵያ ፣ በፊት ፣ ግብፅ ፣ ሥልጡን ፣ ኃይለኛ ፣ ሆና ፣ መኖሯን ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ ታሪኩን ፣ እንደምናገኘው ፣ ከሂክሶስ ፣ ተገዥነት ፣ ከወጣች ፣ በኋላ ፣ ኢትዮጵያን ፣ በመጀመሪያ ፣ መግዛቷን ፣ በኋላ ፣ ደግሞ ፣ የናፓታዎቹ ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ መልሰው ፣ ግብፅን ፣ መግዛታቸውን ፣ ነው ። ይኸንንም ፣ ወደፊት ፣ በሚገኘው ፣ ታሪክ ፣ ውስጥ ፣ በዝርዝር ፣ እናነባለን ።

ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የገቡት ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣንም ፣ ምንም ፣ እንኳን ፣ ከሂክሶስ ፣ ጋር ፣ የዘርና ፣ የሥልጣኔ ፣ አንድነት ፣ ባያጡ ፣ እነዚያ ፣ ላዩን ፣ በከነዓንና ፣ በፍልስጥኤም ፣ አድርገው ፣ ወደ ፣ ግብፅ ፣ ሲገቡ ፣ እነዚህ ፣ ታቹን ፣ ባሕረ ፣ ኤርትራን ፣ ተሻግረው ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ገብተው ፣ የካሙን ፣ ዘር ፣ አሸንፈው ፣ ባለቤት ፣ ሆነዋል ። ግማሾቹ ፣ በዛሬዪቱ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሰሜን ፣ ሲመሠረቱ ፣ የቀሩት ፣ ወደ ፣ ኑብያ ፣ እያለፉ ፣ ከኩሽና ፣ ከካሙ ፣ ዘር ፣ ተደባልቀው ፣ የቀድሞዪቱ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የምትባለውን ፣ የናፓታውንና ፣ የመርዌውን ፣ መንግሥታት ፣ አቋቁመዋልና ፣ እነዚህን ፣ የታችኞቹን ፣ የኛን ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣንንና ፣ ሂክሶስን ፣ አንድ ፣ ማድረግና ፣ ማደባለቅ ፣ የሚቻል ፣ አይመስልም ።

ስለዚህ ፣ መደምደሚያውን ፣ እላይ ፣ እንዳልነው ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ አዲስ ፣ ማስረጃ ፣ እስኪገኝ ፣ ድረስ ፣ የዛሬው ፣ ዘመን ፣ መርማሪና ፣ ጸሐፊ ፣ እንደሚለው ፣ የግብፅን ፣ ቀደምትነት ፣ የኢትዮጵያን ፣ ተከታይነት ፣ እንያዝና ፣ ነገሩን ፣ ከሥሩ ፣ ለመረዳት ፣ ቀጥሎ ፣ ባለው ፣ ምዕራፍ ፣ ውስጥ ፣ የግብፅን ፣ አጭር ፣ የጥንት ፣ ታሪክ ፣ እንብበን ፣

ከዚያ ፡ ግብፅ ፡ የኑብያውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዴት ፡ እንደገዛችና ፡ መልሳ ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ እንዴት ፡ እንደተገዛች ፡ እን መልከት ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፮ ፡፡

### የግብፅ ፡ መንግሥት ፡ አመሠራረትና ፡ አምልኮ ፡፡

ጥንት ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ መንግሥቱ ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፡ አውራጃዎቹ ፡ ለየብቻ ፡ በየባላባት ፡ ተከፋፍለው ፡ ይገዙ ፡ ነበር ፡፡ እነዚህን ፡ የተከፋፈሉትን ፡ እየወጋ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ የመጀ መሪያውን ፡ መንግሥት ፡ የመሠረተ ፡ ሜኔስ ፡ ይባላል፡፡ሜኔስ ፡ መን ግሥቱን ፡ መሥርቶ ፡ የመጀመሪያ ፡ ንጉሥ ፡ የሆነበትን ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡ ለማወቅ፡ሊቃውንት ፡ ሁሉ ፡ መቸገራቸውን ፡ በጽሕፈታ ቸው ፡ ይገልጻሉ ፡፡ የግብፅን ፡ ታሪክ ፡ በመጻፍ ፡ ከታወቁት ፡ ጸሐ ፊዎች፡ውስጥ ፡ እነማኔቶን ፡ MANETHON ፡ ፍላቪውስ ፡ ዮሴፍ ፡ (FLAVIOUS JOSEPH) ሻምፖሊዮን ፡ ( CHAMPOLLION) ፩ሺ፰፻፳፪ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ቦክህ ፡ ( (BOKH ) ፩ሺ፰፻፶፱ ፡ ማሪዮት ፡ (MARIETTE) ፩ሺ፱ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሲያደርጉትና ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ጸሐፊው ፡ሁሉ፡ የግብፅን ፡ ታሪክ ፡ ሲጽፍ ፡ ኖረ ፡፡

በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ምስተር ፡ ብሪስትድ ፡ (BREASTED) የሚባሉት ፡ አሜሪካዊ ፡ የጥንቱን ፡ የግብፅ ፡ ጽሑፍ ፡ (ሂዬሮግሊፍ) ፡ ሐውልቱን ፡ መቃብሩን ፡ በታላቅ፡ ትዕግሥትና ፡ በረቀቀ ፡ ጥበብ፡ መርምረው ፡ የግብፅን ፡ መንግሥት ፡ አመሠራረትና ፡ የሜኔስን ፡ የመ ዠመሪያ ፡ ንጉሥነትን ፡ በ፫ሺ፬፻ ፡ ዓመት ፡ከክርስቶስ ፡ልደት ፡ በፊት ፡ አድርገውታል ፡፡ እንደዚሁም ፡ ስቴይንዶርፍ ፡ (STEINDORFF) የሚባል ፡ የጀርመን ፡ ሊቅ ፡ በ፫ሺ ፡ ፪፻ ፡ (ሦስት ፡ ሺ ፡ ሁለት ፡ መቶ) ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ አድርገዋል ፡፡ የበዛውንም ፡ ዘመን ፡ ወደ፡ ማሳጠር ፡ የደረሱት ፡ በቀድሞው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በተባለው፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተመደቡት ፡ ቀኖችና፡ ወራቶች ፡ እንደዛሬው ፡ ወሩ፡ በ፴ ፡ ቀን ፡ ዓመቱ ፡ በ፫፻፷፭ ፡ ቀን ፡ ከሩብ ፡ ሳይሆን ፡ ከዚያ ፡ ባነሰ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ በማለት፡ ነው ፡፡ የዛሬም ፡ ጸሐፊ ፡ እነዚህ፡ ሊቃውንት ፡



ሐፒ ፡ የሚባለው ፡ የበሬ ፡ ኮርማ ፡ የ፳፮ኛውን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ፈርዖን ፡ ፐሳሜ ቲክ ፡ የሚባለውን ፡ ( ሐትሆር ፡ ካህኑ ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፡ ) አቅፎ ፡ እንደሚጠብቀው ( ሐውልቱ ፡ በቡላክ ፡ ይገኛል ፡፡ )




አማሲስ ፡ የሚባለው ፡ የ፳፮ኛው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ፈርዖን ፡ ለኮርማው ፡ ምስል ፡ ሲሰግድ ፡፡ ( ሐውልቱ ፡ በሉቭር ፡ የሚገኝ ፡፡ )

ይልቁንም ፡ የጀርመናቹ ፡ ሊቃውንት ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ ፫ሺ፪፻ ፡ ብለው ፡ የመደቡትን ፡ መነሻ ፡ እየአደረገ ፡ መጻፍ ፡ ስለጀመረ ፡ እኛም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ወደፊት ፡ ያለውን ፡ የግብፅን ፡ ገናንነቱን ፡ ባጭሩ ፡ እንመልከት ።

ሜኔስ ፡ ከመንገሡ ፡ በፊት ፡ የግብፅ ፡ ነገድና ፡ ሕዝብ ፡ ሲያብርም ፡ ሲበተንም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ከሁለት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተከፍሎ ፡ የሰሜንና ፡ የደቡብ ፡ ግዛት ፡ ይባል ፡ ዠመር ። ሰሜኖችም ፡ አዚት ፡ በምትባል ፡ በሴት ፡ አንቀጽ ፡ በሚጠራ ፡ እባብ ፤ የደቡቦቹ ፡ ነቅቤት ፡ በሚባል ፡ ጆፌ ፡ አሞራ ፡ ያመልኩ ፡ ነበር። ሕዝቡንም ፡ የሚያስተዳድሩት ፡ የነዚሁ ፡ አማልክት፡ ካህናት ፡ ነበሩ ። ሜኔስ ፡ እነዚህ ፡ ከሁለት ፡ የተከፈሉትን ፡ ወገቶ ፡ አማት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አድርጎ፡ በበላያቸው ፡ ነገሠ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የርሱ ፡ ዘር ፡ እየተከታተለ ፡ ሲገዛ ፡ ቆይቶ ፤ ካካው ፡ (የወንዶች ፡ ወንድ) ፡ የሚባል ፡ ከሜኔስ ፡ ዘር ፡ ዙፋኑን ፡ ቀምቶ ፡ ሁለተኛውን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ) ፡ መሠረተ ። በርሱ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ አምልኮ ፡ ተፈጠረ ፤ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፤ በሰው ፡ አምሳል ፡ የሚቀረጸው ፡ ፐታህና ፡ የርሱ ፡ ማደሪያ፡ የሆነው ፡ አፒስ ፡ ወይም፡ ሐፒ ፡ የሚባለው ፡ ኮርማ ፡ ነው ።

የኮርማውም ፡ አመራረጥ ፡ እንደዚህ ፡ ነው። ከበሬ ፡ ጥጃዎች፡ ውስጥ ፡ ከላይ ፡ ከገርባው ፡ ቀለሙ ፡ ጥቁር ፡ ሆኖ ፡ የጆፌ ፡ አሞራ ፡ የሚመስል ፡ የተጋደመበት፤ በግንባሩ ፡ ባለ ፡ ሦስት ፡ ማዕዘን ፡ የነጭ፡ ቦቃ ፡ ያለበት ፡ ደረቱ ፡ ላይ ፡ የሩብ ፡ ጨረቃ ፡ የሚመስል ፡ ነጭ ፡ ፍንጣቂ ፡ የጣለበት ፤ በመላሱ፡ ላይ ፡ ከታችኛው ፡ ወገን ፡ ጢንዚዛ፡ የሚመስል ፡ መልክ ፡ የተገኘበት ፡ ሲወለድ ፡ በካህናቱ ፡ ምርመራና ፡ ምርጫ ፡ በዚህ ፡ ዋናው ፡ አምላክ ፡ ፐታህ ፡ አድሮበታል ፡ ብለው ፡ ይወስዱትና ፡ ጥጃውን ፡ ካህናቶቹ ፡ አከባክበው ፡ ያሳድጉታል ። ቲንሽ ፡ ከፍ ፡ ብሎ፡ ወደ ፡ ኰርማነት ፡ ሲደርስ ፡ ለፀሐይ ፡ የተቀደሰው፡ ውሃ ፡ ወደሚባለው ፡ ወስደው ፡ ይነክሩታል ፡ ( ያጠምቁታል ) ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማናቸውንም፡ የአምላክነት ፡ ክብር ፡ ሰጥተው፡ ይቀድሱትና ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አስቀምጠው ፡ ይሰግዱለታል ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ከበሬታና ፡ በዓል ፡ እንደ



የአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የውጪው ፡ መግቢያ ። አምላኩ ፡ ለመሥዋዕት ፡ የሚወዳቸው ፡ የበግ ፡ ሙክቶች ፡ ሐውልቶች ፡ ግራና፡ ቀኝ ፡ ኮልኩለው ፡ ይታያሉ። (ሻምዱር፣)

CITY - HALL LIBRARY of ADDIS ABABA

ሚደረግለት ፡ የሞተ ፡ ለት ፡ የኀዘኑ ፡ የቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በታላቅ ፡ አከባበር ፡ ይፈጸምና ፡ እጓደኞቹ ፡ አማልክትና ፡ ነገሥታት ፡ ጐን ፡ ይቀበራል ። በምትኩም ፡ የርሱ ፡ ዓይነት ፡ እንደገና ፡ ይመረጣል ። እንደርሱ ፡ ያለም ፡ ለጊዜው ፡ የጠፋ ፡ እንደሆነ ፡ አምላክ ፡ ራቀን ፡ ብለው ፡ ያዝናሉ ፤ ሲገኝም ፡ አምላክ ፡ ቀረበን ፡ ብለው ፡ ይደሰታሉ ።

የዚህ ፡ የጥጃ፡ ወይም ፡ የኮርማ ፡ ምስል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት፡ በደንጊያና ፡ በብረት ፡ በነሐስ ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ ይሠራና ፡ በገርባው ፡ ላይ ፡ እንደግላስ ፡ የሚመስል ፡ የተጠለፈና ፡ ያማረ ፡ ጨርቅ ፡ ይጋደምበታል ፤ የፀሐይ ፡ ምስል ፡ ክብ ፡ ነገርና ፡ የእባብ ፡ ምስል ፡ በቀንድና ፡ በቀንዱ ፡ ማህል ፡ ወደማዥራቱ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጡበታል። በዚያም ፡ ውስጥ ፡ ክንፉን ፡ የዘረጋ ፡ ጢንዚዛ ፡ ወይም ፡ ክንፉን ፡ አጥፎ ፡ የተቀመጠ ፡ ጆፌ ፡ አሞራ ፡ እየተደረገ፡ ይቀረጽና ፡ በቤተ፡ መቅደስ ፡ ተቀምጦ ፡ በየአገሩ ፡ ይመለክበታል ።

እስራኤሎች ፡ ከ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ በኖሩ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ያባቶቻቸው ፡ የአብርሃምና ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ መኖሩን፡ ቢያውቁ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት፡ በግብፆች ፡ ልማድ ፡ በዚህ ፡ በኮርማ ፡ አምልኮ ፡ ተውጠው ፡ እንደነበረ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በኦሪት ፡ ዘጸአት ፡ ላይ ፡ እንደምናገኘው ፡ እስራኤሎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ታምራት ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ መሪነት ፡ ከግብፅ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ በሚጓዙበትና ፡ ሲና ፡ በረሃ፡ ላይ ፡ በሠፈሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ከነርሱ ፡ ተለይቶ ፡ ወደሲና ፡ ተራራ ፡ ወጥቶ ፡ ቢዘገይ ፡ አሮንን ፡ ይህ ፡ ሙሴ ፡ ወዴት ፡ እንደ፡ ሔደ፡ አናውቅምና፡ በፊታችን፡ የሚሔድ ፡ አምላክ፡ ሥራልን ፡ ብለው ፡ እንዳስጨነቁት ፡ እርሱም ፡ ከሚስቶቻችሁና ፡ ከየሴት ፡ ልጆቻችሁ ፡ ጆሮ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ሎቲና ፡ ጌጥ ፡ ሰብስቡ ፡ ብሎ ፡ ያንን ፡ በእሳት ፡ አስቀልጦ ፡ የጥጃ ፡ ምስል ፡ እንደሠራላቸውና ፡ ያውና ፡ ከግብፅ ፡ አገር ፡ ያወጣችሁ ፡ አምላካችሁ ፡ ብሎ ፡ እንደሰጣቸው ፡ እነሱም ፡ ለተሠራው ፡ የጥጃ ፡ ምስል ፡ እየሰገዱ ፡ ደስ ፡ እንዳላቸው ፡ በዚሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡ ሲያጠፋ



ለአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አገልጋዮች ፡ ዕጣንና ፡ ሌላም ፡ ዓይነት ፡ ፍራፍሬ፡ሲያግዙ ፡
( ሳክራህ ፡ ) ፒራምፖሊሲ ።



የእዝመራ ፡ በዓል ፡ ለመሥዋዕት ፡ ከቀረበ ፡ ከነጭ ፡ በሬ ፡ ጋር ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ ፈርዖን ፡ በወርቅ ፡ ማጭድ ፡ የእሸት ፡ ነዶ ፡ ሲቆርጥ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ ምሥዋዑ ፡ ሲጥል ይታያል ። ( ከሐነቶ ፡ መጽሐፍ ። )

ቸው ፡ ሲል፡ በሙሴ ፡ ልመና ፡ ይቅርታ ፡ እንደተደረገላቸው ፡ ከዚያ፡ ሙሴ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዛት ፡ ያሉበትን ፡ ጽላት ፡ ይዞ ፡ ከሲና ፡ ተራራ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ የጥጃውን ፡ ጣዖት ፡ (ስብኮ ፡ ላሕሙን ፡) ዓይቶ ፡ እንደተቆጣና ፡ በያዘው ፡ ጽላት ፡ የጥጃውን ፡ ምስል፡ እንደ፡ ሰበረው ፡ ተጽፏል (፩) ። በክርስትና ፡ ዘመን ፡ ይኸንኑ ፡ ጥጃ ፡ (ስብኮ ፡ ላሕም) ፡ ፊላታዎስ ፡ ሰማዕት ፡ እንደገደለው ፡ ይነገራል ።

በተረፈ ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ያሉት ፡ የቀሩት ፡ አማልክት ፡ (ጣዖታት) ፡ ብዙ ፡ ስለሆኑ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ጽፈን ፡ እንጨርሳቸውም ። ባጭሩ ፡ እንደግሪኮችና ፡ እንደሮማውያን ፡ ለአ ማልክቶቻቸው ፡ የሰውነት ፡ መልክና፡ አርዓያ፡ እስኪሰጡ ፡ ድረስ ፡ ለአማልክቶቻቸው ፡ ማኅደር ፡ የሚያደርጉት ፡ ወይም ፡ አማልክቶ ቻቸውን ፡ የሚመስሉት ፡ በእንስሳና ፡ በዕፀዋት ፡ ነበር ።

ለምሳሌ ፡ ይኸው ፡ የዋናው ፡ ከተማ ፡ የመምፊስ ፡ ቅዱስና ፡ ጠባቂ ፡ የዋናው ፡ አምላክ ፡ የፐታህ ፡ ማኅደር ፡ ወይም ፡ ሕይወት ፡ ተብሎ ፡ በኮርማ ፡ ሲመሰል ፤

ሐጾር ፡ (ሐትሆር ፡) በወይፈን ፤ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በላም ፡
ኔፈርቱም ፡ በአበባ ፤
ኔትህ ፡ ሁለት ፡ ቀስት ፡ በተመሳቀለበት ፡ ጋሻ ፤
ክሊኑም ፡ በበግ ፤
ሆሩስ ፡ በአሞራ ፡
ሴቤቅ ፡ በአዞ ፤
ቡባስቲስ ፡ በድመት ፤

ቡቶ ፡ በእባብ ፡ እየተመሰሉ ፡ ይከበሩ ፡ ነበር (፪) ።

ወደፊት ፡ የምናገኘው ፡ የአሞን ፡ አምልኮ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ገና፡ አልገነነም ፡ ነበር ፤ ምናልባት ፡ ባንድ ፡ መንደር ፡ ብቻ ፡ ይከበር ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ በአሁኑ፡ ጊዜ፡ ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡ ፈጣሪ ፡ አምላክ ፡ አማልክት ፡ የሚያደርጉት ፡ ፐታህ ፡ የሚባለውን ብቻ ፡ ነው ። ለቀሩት ፡ የእንስሳ ፡ መልክ ፡ ሲሰጡ ፡ ለፐታህ ፡ የሰው

(፩) ኦሪት ፡ ዘጸአት ፡ ም ፡ ፴፩—፴፪ ፡
(፪) የሲራም ፡ መጽ. ገጽ ፡ ፺፩፮ ፡



ካንደኛው ፡ ፒራሚድ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ ገጹ፡የሰው ፡ በሀመኑ ፡ ባለው ፡ ፈርዖን፡ ገጽ ፡ ሆኖ ፡ እግሮቹን ፡ ወደፊት ፡ ዘርግቶ ፡ የተኛ ፡ የአንበሳ ፡ ምስል ፡ ያለበት ፡ (ስፊንክስ) ።

ነት ፡ አርዓያ ፡ ይሰጡታል ። ምስሉ ፡ ሲሳል፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ሆኖ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የዘለዓለማዊነት ፡ ምልክት ፡ የሆነውን ፡ የጢንዚዛን ፡ ምስል ፡ ደፍቶ ፡ የጨለማ ፡ ምልክት ፡ የሆነችውን ፡ አዞ ፡ ሲያባርር፡ ይታያል ። ስሙና ፡ መልኩ ፡ እንደግብሩ ፡ ብዛት ፡ ይለዋወጣል ።

ይኸን ፡ ማስታወሳችን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እነዚህ ፡ የጥንት ፡ የግብፅ ፡ አማልክት ፡ ዛሬ ፡ ባገራችን ፡ ባንዳንድ ፡ ባላገሮች ፡ ዘንድ ፡ የሚደረገውን ፡ አስበን ፡ ለማመዛዘን ፡ እንደምንችል ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የግብፁን ፡ ታሪክ ፡ ከነገሥታቱ ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ የያዘው ፡ የአማልክቱ ፡ ታሪክ ፡ ስለሆነ፤ ስለቀድሞ፡ የግብፃውያን ፡ አምልኮ፡ ለአንባቢ፡ አሳብ ፡ ለመስጠት ፡ ያህል ፡ ነውና ፡ አሁን ፡ ወደታሪኩ፡ እንመለስ ።

ከሁለተኛው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ) ፡ በኋላ ፡ እስከ አስረኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ድረስ ፡ (፪ሺ፱፻፹—፪ሺ፪፳ ፡ ዓመት) ፡ ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ሲያልፉ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደራቸውን ፡ ከማደራጀት ፡ ጥበባቸውን ፡ ከማስፋፋት ፡ በቀር ፡ ግዛት ፡ ለማስፋፋት ፡ ገና ፡ አልተቀሰቀሱም ፤ ትንሽ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ሲና ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ ሔደው ፡ አስገብረዋል ።

ባገር ፡ ውስጥ ፡ የሠሩት ፡ የጥበብና ፡ የሕንፃ ፡ ሥራ፡ግን ፡ ብዙ ፡ ነው ። ከዚያውም ፡ እንደዋና ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠረው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ተመልካችን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስደንቀው ፡ የፒራሚድ ፡ ሥራ ፡ ነው ። አብዛኛውንም ፡ የሠሩት ፡ ያራተኛው ፡ ዲናስቲ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ። በተለይ ፡ በግብፆቹ ፡ ኩው፡ ((KHOUWOU) በግሪኮቹ ፡ ክሄኦፕስ፡ (CHEOPS) የሚባለው ፡ ለመቃብሩ ፡ ያሠራው ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ይደነቃል ። የቀሩትም ፡ ፒራሚዶች ፡ በያለበት ፡ ያሉት ፡ ለየቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ያሠሩት ፡ ይገኛል ። በጊዜህ ፡ የሚገኘው ፡ ከሁሉ ፡ ትልቅ ፡ የሆነው ፡ የክሄኦፕስ ፡ ፒራሚድ ፡ ፪ ፡ ሚሊዮን ፡ ፫፻ሺ ፡ ድንጊያ ፡ በሰው ፡ ትከሻ ፡ እየተጋዘ ፡ ቁመቱ ፡ ከመሠረቱ ፡ በላይ ፡ ፩፻፵፮ ፡ ሜትር ፡ የሚሆነው ፡ ፒራሚድ ፡ በሰው ፡ ክንድ ፡ ተሠራ ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ተሠርቶ ፡ ዛሬ ፡ ለተመልካቾችና ፡ ለሰሚው ፡ ሲያስደንቅ ፡ ሠራተኞቹ ፡ በዚህ፡ ሥራ፡ ያን፡ጊዜ፡ የደረሰባቸው ፡ ሥቃይ፡ ለሕሊና ፡ አያስደስትም። አሠሪውንም ፡ ንጉሥ ፡ በማስደነቅ ፡ ፈንታ፡ ለምኞቱና ፡ ለግል ፡ ክብሩ ፡ ሲል ፡ የፈጸመውን ፡ ጭካኔውን ፡ ያሳስ



የአራተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ነገሥታት ፡ እነኼዎፕስ ፡ እነኼፍሬን ፡ ያሠሩት በጊዜህ ፡ የሚገኙት ፡ ፒራሚዶች ። ( ጋስቶን ፡ ፓርሉ ፡ )

ባል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ በመዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ሲሠራ ፡ ፩፻፵፮ ፡ ሜትር ፡ ቁመት ፡ የነበረው ፡ ባሁን ፡ ሁኔታው ፡ ሲታይ ፡ ፩፻፴፯ ፡ ሜትር ፡ ነው ፡ (፩) ። ፓል ፡ ፒዬሬ ፡ (PAUL PIERRET) ፡ ያዘጋጀውን ፡ የአርኬውሎዥ ፡ ዲክሲዮኔር ፡ ( መዝገበ ፡ ቃላት ) ፩፻፴፫ ፡ ገጽ ፡ ተመልከት ።

ይኸን ፡ ፒራሚድ ፡ ቍጥራቸው ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ የሚደርሱ ፡ ባሮችና ፡ ባላገሮች ፡ ሸሽተው ፡ እንዳያመልጡ ፡ አንገታቸውን ፡ በገመድና ፡ በሰንሰለት ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ አቀጣጥለው ፡ እያሰሩ ፡ ራቁታቸውን ፡ አድርገው ፡ ከኋላ ፡ ዠርባቸውን ፡ አሠሪ ፡ ወታደርና ፡ የወታደር ፡ ሹም ፡ እየገረፏቸው ፡ ከሩቅ ፡ ሥፍራ ፡ ድንጋይ ፡ እያጋዙ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ሰው ፡ በእንጨት ፡ ላይ ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ ሊሸከም ፡ የሚገባው ፡ አንድ ፡ ሜትር ፡ ኲብ ፡ ድንጋይ ፡ ነው ። ከንጉሡ ፡ ዠምሮ ፡ ሹማምንቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ከነወታደሮቻቸው ፡ ጨካኞችና ፡ እብሪተኞች ፡ ስለነበሩ ፡ የሥራውን ፡ መፋጠንና ፡ መድረስ ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ ላቡንና ፡ ደሙን ፡ እያንጠፈጠፈ ፡ በሚሠራው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በጭካኔ ፡ ላይ ፡ ጭካኔ ፡ እየጨመሩ ፡ ከመግረፍ ፡ በቀር ፡ ቢጮህ ፡ ቢያለቅስ ፡ አዝነው ፡ እረፍት ፡ አይሰጡትም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይህ ፡ ከሁሉ ፡ የሚረዝመው ፡ የጊዜህ ፡ ፒራሚድ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እየተሠራ ፡ ሥራው ፡ በ፳ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ሌሎቹም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ፈጅቶ ፡ ተፈጸመ ፡ ይባላል ።

የዚህም ፡ የፒራሚድ ፡ አገልግሎት ፡ ነገሥታቱ ፡ ለክብራቸውና ፡ ለገናንነታቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንደዚያን ፡ ጊዜ ፡ አሳባቸውና ፡ እምነታቸው ፡ ሞተው ፡ ነፍሳቸው ፡ ከወጣች ፡ በኋላ ፡ ተመልሳ ፡ በአካላቸው ፡ ላይ ፡ ገብታ ፡ እንደገና ፡ ሕይወት ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ እነሱም ፡ አማልክቶቻቸውም ፡ እንዲቀመጡበት ፡ ሲሆን ፡ በጠቅላላው ፡ በዛሬው ፡ አነጋገር ፡ ግን ፡ ፒራሚዱ ፡ የነገሥታቱ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ ነው ። ወይም ፡ ፒራሚድ ፡ ዛሬ ፡ የነገሥታቱ ፡ መቃ

(፩) PIERRET (PAUL) – DICTIONNAIRE ARCHELOGIQUE ገጽ ፡ ፩፻፴፫ ፡
C.W. CERAM – DIEUX, TOMBEAUX et SAVANTS ም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴፩ ፡ — ፩፻፵፱ ፡





ፀሐዩ ፡ አሞን ፡ ፀሐይነቱን ፡ ለማስረዳት ፡ ከዘውዱ ፡ ፊት ፡ ከግንባሩ ፡ በላይ ፡ ክብ ፡ ነገር ፡ የፀሐይ ፡ ምልክት ፡ አድርጓል ። ( ሉቭር ፡ )

አሞን ፡ ቱትአንክአሙን ፡ የሚባለውን ፡ ፈርዖን ፡ ታቅፎ ፡ ይታያል ። የፈርዖኑ ፡ ሐውልት ፡ ከደረቱ ፡ በላይ ፡ ተሰብሯል ። ( ሉቭር ፡ )

ብር ፡ ቤት ፡ ሳይሆን ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ እምነታቸው ፡ ግን ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ትንሣኤ ፡ አድርገው ፡ የሚቀመጡበት ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ፈርዖኖቹ ፡ ለዚህ ፡ ለ፪ኛው ፡ ጊዜ ፡ ሕይወት ፡ አጥብቀው ፡ ስለሚያስቡ ፡ በመጀመሪያው ፡ ሕይወታቸው ፡ ጊዜ ፡ መኖሪያቸውን ፡ ማዘጋጀት ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። የዚህንም ፡ የሁለተኛውን ፡ ኑሮ ፡ ታሪክ ፡ እንድግንዘት ፡ በሬሳ ፡ ፊት ፡ ካህናቱ ፡ የሚደግሙት ፡ የምውታን ፡ መጻሕፍት ፡ ወይም ፡ የቀብር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ላይ ፡ ዘርዝረውት ፡ ይገኛል ።

ከአንደኛው ፡ እስከ ፡ አሥረኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ድረስ ፤ ያሉት ፡ ነገሥታት ፡ ዋና ፡ መቀመጫ ፡ ከተማቸው ፡ መምፊስ ፡ (በታችኛው ፡ ግብፅ) ፡ አምላካቸውም ፡ ፐታህ ፡ የሚባለው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከአሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ጀምሮ ፡ ይልቁንም ፡ ከአሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ወዲህ ፡ የመምፊስ ፡ የከተማው ፡ ገናንነት ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ (ላዕላይ ፡ ግብፅ) ፡ ወደ ፡ ቴብ ፡ የፐታህ ፡ የአምላክነት ፡ ገናንነትም ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ እያደር ፡ ዞረ ።

አሞን ፡ በፊት ፡ እንደአልነው ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያንድ ፡ መንደር ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ በቴብ ፡ ዋና ፡ ከተማቸውን ፡ አድርገው ፡ በሥልጣኔ ፡ በጥበብ ፡ በግዛት ፡ ከፍ ፡ እያሉ ፡ ሲሔዱ ፡ የአሞን ፡ አምልኮ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የነገሥታቱና ፡ የከተማቸው ፡ የቴብ ፡ ወዳጅና ፡ ጠባቂ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ፈጣሪ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ ያምኑበት ፡ ነበር ። በቴብ ፡ በተለይ ፡ በካርናቅ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተሠራለት ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሕንፃው ፡ ፍራሽ ፡ ዛሬ ፡ ተመልካችን ፡ ሁሉ ፡ አስደንቋል ። ካርናቅ ፡ ማለት ፡ የአሞን ፡ መቀመጫ ፡ ( መንበረ ፡ አሞን ) ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ አስደናቂ ፡ መቅደስ ፡ ያሠሩት ፡ እነሴት ፡ ፩ኛ ፡ እነአሜኖፊስ ፡ ፫ኛ ፡ ናቸው ። በያለበት ፡ አዳራሹ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ የዋነኛው ፡ አዳራሽ ፡ ጕኑና ፡ ቁመቱ ፡ 102 X 51 ፡ ሜትር ፡ ሆኖ ፡ በውስጡ ፡ ፻፴፬ ፡ ዓምዶች ፡ ነበሩበት ፡ የተሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፲፬ኛውና ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ነው ።



እንደ ኤው ቀ በ1922 ዓ. ም. ሎርድ ካርናቮንና ካርተር በቁፋሮ ያገኙት ከታላላቆቹ ፈርዖኖች ያንዱ የቱትአንክ አመን ሥዕል ።

የአሞን ፡ ምስሉ ፡ እንደ ፡ ፕታህ ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ነው ፡፡ ሲሠራ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የአንድ ፡ ዝይ ፡ የሚመስል ፡ አሞራ ፡ የጭራ፡ ላባው ፡ በዘውዱ ፡ ላይ ፡ ተሠርቶ ፡ እንደደፋ ፤ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ጫፉ ፡ የውሻ ፡ ጭንቅላት ፡ የሚመስል ፡ ያለበት ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ጨብጦ ፤ በግራ ፡ እጁ ፡ መስቀል ፡ የሚመስል ፡ ያለበት ፡ የሕይወትን ፡ ምልክት ፡ ይዞ ፡ በዙፋኑ ፡ እንደተቀመጠ ፡ ወይም ፡ ቆሞ፡አለዚያም ፡ ሲራመድ ፡ ይሳላል ፡፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ነገሥታትና ፡ ካህናት ፡ ወይንና ፡ ዕጣን ፡ ሲያቀርቡለትና ፡ ሲቀበል ፡ የአሕዛብና፡ የአረመኔ ፡ ሕዝብ ፡ ምልክቶች ፡ የሆኑትን ፡ ፱ ፡ ቀስት ፡ በእግሩ ፡ ሲገፋ ፡ ይታያል ፡፡

አሞን፡ የስሙ ፡ ትርጓሜ ፡ ሥውሩ ፡ ወይም ፡ ምሥጢራዊው ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ «ራ» ፡ ማለት ፤ በግብፆች ፡ፀሐይ ፡ ማለት ፡ ስለሆነ ፡ አሞን ፡ ራ ፡ እየተባለ ፡ ሲጠራ ፡ አምላክ ፡ በፀሐይ ፡ መልክ ፡ ተገለጠ ፡ ይባላልና፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ከአሞን ፡ ምስል ፡ ጋር፡ የፀሐይ፡ ሥዕል ፡ አይጠፋም ፡፡

ፕታህ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ (የመምፌስ) ፡ አሞን ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ (የቴብ) ፡ አማልክት ፡ ሆነው ፡ ሁለቱም ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ሲሳሉ፡ በሥራና ፡ በተግባር ፡ በቅድሚያ ፡ ይለያያሉ ፡፡ ፕታህ ፡ ለአሞን ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ባይሆንም ፡ የአሞን ፡ ዘር ፡ የወረደው ፡ ከፕታህ ፡ ነውና ፡ በሥራም ፡ የርሱ ፡ ተከታይ ፡ ነው ፡፡ ፕታህ ፡ ከዓለም፡ ፍጥረት ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ ዓለምን ፡ እንደ ፡ ፈጠረ ፡ ይኸውም ፡ በነርሱ ፡ አነጋገር ፡ ፕታህ ፡ ከዋክብትንና ፡ ጨረቃን ፡ ለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የምትሰጠውን፡ ፀሐይን ፡ ዕንቊላልነታቸውን ፡ከፈጠረ ፡ በኋላ ፡ አሞን ፡ ከርሱ ፡ ወርሶ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ወደሙሉ ፡ፍጡርነት ፡ ደርሰው ፡ መሬት ፡ ፍሬዋን ፡ እንድትሰጥና ፡ ሁሉም ፡ በየበኩሉ ፡ ተግባሩን ፡ እንዲፈጽም ፡ አደረገ ፡ ይሉታል ፡፡ እንደ ፡ ግብሩ ፡ ልዩነት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የበግ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የአሞራ ፡ መልክ፡ እየተጨመረ ፡ ይሳላል ፡፡ የፖል ፡ ፒዬሬን ፡ ዲክሲዮኔር ፡ ከ፴፭ ፡ እስከ ፡ ፴፮ ፡ ገጽ ፡ ድረስ ፡ ተመልከት (፭) ፡፡

(፭) DICT. ARCHEOL – PIERRET ገጽ ፡ ፴፭ ፡— ፴፮ ፡



በካርናቅ ፡ የነበረው ፡ የአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በውስጡ ፡ የሚታዩት ፡ ዓምዶች ፡ (ሻምዱር ፡፡)

ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ የአሞን ፡ አምልኮ ፡ የገነነው ፡ ገና ፡ ወደ ፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅና ፡ በናፓታ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ ገና ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ሌሎች ፡ ጭምርግሪዎች ፡ መኖራቸውን ፡ ሳንዘነጋ ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ በሰው ፡ እምባል ፡ የሚሳለው ፡ ፕታህና ፡ የርሱ ፡ ማደሪያ ፡ ሐፒ ፡ ናቸው ። ደግሞ ፡ ሂክሶሶች ፡ ሲገቡ ፡ የራሳቸውን ፡ የምሥራቅ ፡ አምልኮ ፡ ሱትኩ ፡(SOUTKOU) የሚባለውን ፡ ይዘው ፡ ገብተው ፡ እንደነበረ ፡ ቀጥሎም ፡ አከናቶን ፡ የሚባል ፡ ፈርዖን ፡ አቶን ፡ወይም ፡ አዶን ፡ ( አዶናይ ? ) ፡ የሚባል ፡ የፈንቂዎችን ፡ እውነተኛ ፡ ፀሐይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አስገብቶ ፡ እነዚህን ፡ ሊሽር ፡ ሞክሮ ፡ ሳይሳካለት ፡ እንደቀረና ፡ የአሞን ፡ ገናንነት ፡ ከ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ እንደቀጠለ ፡ እንመለከታለን።

በአሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ውስጥ ፡ ሳኑስሪት ፡ ( እንደ ግሪኮች ፡ አጠራር፡ ሴሶስትሪስ) ፡ የሚባሉት ፡ በየተራ ፡ በነገሡበት ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ (ከ፳፻ ፡ እስከ ፡ ፩፻፰፻) ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ አብርሃምና ፡ ሚስቱ ፡ ሣራ ፡ ከኡር ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ሄደው ፡ ሲኖሩ ፡ በኋላ ፡ ከከነዓን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ የወጡት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ነው ። ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ ቍ/ ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፳ ።

በአሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ያሉት ፡ ነገሥታት ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐውልት ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ የመንገድ ፡ የውሃ ፡ የቦይ ፡ ሥራ ፡ ሲያከናውኑ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ በምዕራብ ፡ የሊቢያን ፡ በምሥራቅ ፡ የሲናን ፡ አገር ፡ እየወጉ ፡ አስገበሩ ። ወደ ፡ ደቡብም ፡ እየገፉ ፡ እስከናብያ ፡ ሰሜን ፡ ደረሱ ። እነዚህ ፡ ያሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ (ሥርወ ፡ መንግሥት) ፡ ነገሥታት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ( ከ፳፻ ፡ እስከ ፡ ፩፻፰፻ ) ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ያደረጉትን ፡ ቴብን ፡ በውበቱ ፡ የነገሥታት ፡ የጣዖታት ፡ የሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ሐውልት ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፤ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እያሠሩ ፡ አደመቁት ። ፈርዖኖቹ ፡ በቀረው ፡ ዓለም ፡ ፊት ፡ የገነኑ ፤ አገራቸው ፡ ግብፅና ፤ ከተሞቻቸው ፡ መምሬስና ፡ ቴብ ፡ የሥልጣኔ ፡ ምንጭ ፡ ሆኑ ።



ነገር ፡ ግን ፡ ግብፆች ፡ እንደዚህ ፡ በገነኑበትና ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ግዛታቸውን ፡ ባስፋፉበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይታሰብ ፡ ከምሥራቅ ፡ የፈለሱ ፡ ሂክሶስ ፡ የሚባሉ ፡ ዘሮች ፡ ፩፻፯፻፰ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ፱ፊት ፡ መጥተው ፡ የግብፆችን ፡ ነገሥታት ፡ ገልብጠው ፡ ነገሡ ። እነሱም ፡ የታሪክ ፡ ሁሉ ፡ መጽሐፍ ፡ «እረኞች ፡ ወይም ፡ ዘላኖች ፡ ነገሥታት» ፡ ይሉዋቸዋል ።

ምክንያቱም ፡ የሂክሶስ ፡ አለቆች ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ከተማ ፡ ከትመው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ሳይቀመጡ ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፤ በብዛት ፡ እየዋዠቁ ፡ ይኖሩ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ታችኛውን ፡ ግብፅ ፡ በሙሉ ፡ ወረሩትና ፡ የግብፅ ፡ ገዥዎች ፡ ሆኑ ።

ማኔቶ ፡ እንደጻፈው ፡ እነዚሁ ፡ ሂክሶሶች ፡ በሦስት ፡ ዲናስቲ ፡ ይከፋፈላሉ ። በአሥራ ፡ አራተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ውስጥ ፡ የነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ አገርን ፡ ከተማን ፡ መንደርን ፡ እየወረሩ ፡ በለንግነቱና ፡ በለቀድሞዎቹ ፡ ፈርዖኖች ፡ ቅናት ፡ የሚከላከለውን ፡ እየወጉ ፡ ያጠፉ ፡ ናቸው ። ባሥራ ፡ አምስተኛውና ፡ ባሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ የገዙት ፡ የፊተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ የወረረውንና ፡ ያጠፋውን ፡ አገር ፡ መልሰው ፡ እያቀኑ ፤ በአገር ፡ ውስጥ ፡ በሳማዊ ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ የሂክሶስ ፡ ነገሥታት ፡ ደንበኛ ፡ ሥርዓትን ፡ እየፈጸሙ ፡ ዘውድ ፡ ጭነው ፡ እየነገሡ ፡ እንደፈርዖኖች ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ። ስማቸውም ፡ የብዙዎቹ ፡ በየሐውልታቸው ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ «አፒፒ» ፡ ይባላል ።

የአብርሃም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ዮሴፍ ፡ ወንድሞቹ ፡ ሸጠውት ፡ የመጣውና ፡ የታሠረው ፡ በሕልም ፡ አፈታት ፡ ምክንያት ፡ ተፈትቶ ፡ እንደራሴ ፡ የሆነውም ፡ አባቱን ፡ ያዕቆብንም ፡ ከነቤተ ፡ ሰቡ ፡ ከከንዓን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ያስመጣው ፤ በነዚሁ ፡ በሂክሶስ ፡ ነገሥታት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ፡ ፴፯፡ ቍጥር ፡ ፵፯ ። ባለሟልና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ የሆነውም ፡ ከነዚሁ ፡ ነገሥታት ፡ ባንደኛው ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ዮሴፍ ፡ በሂክሶስ፡ ነገሥታት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ፡ ከነቤተ ፡ ሰቡ ፡ በደስታ ፡ ኖሮ ፡ ሲሞትና ፡ በኋላም ፡ ግብፆቹ ፡ የሂክሶስን ፡ ነገሥታት ፡ አባር

ረው ፡ የራሳቸውን ፡ ተወላጅ ፡ ንጉሥ ፡ ሲመሠርቱ ፡ የሂክሶስ ፡ ባለ ሟሎች ፡ በነበሩት ፡ እስራኤላውያን ፡ ላይ ፡ መከራና ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙባቸው ፡ ይመስላል ።

ቀዳሚ ፡ ሰማዕት ፡ እስጢፋኖስ ፡ በክርስቶስ ፡ እምነት ፡ የተነሣ ፡ በደንጊያ ፡ ተደብድቦ ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ በምስር ፡ በረከተ ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ ዮሴፍን ፡ የማያውቅ ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ በዘመዶቻችን ፡ ተንኰል ፡ ያሰው ፡ ስለዚህ ፡ ነው (፩) ።

የሂክሶስ ፡ ነገሥታት ፡ ላገር ፡ የሚጠቅም ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ቢሠሩም ፡ ለሕዝቡም ፡ በጎነት ፡ ቢያደርጉም ፡ ሕዝቡ ፡ እንደባዕድ ፡ እያየ ፡ ከልቡ ፡ አልተገዛላቸውም ። የነርሱን ፡ አማልክት ፡ እያገቡ ፡ የአማልክቶቻችንን ፡ መቅደስ ፡ አረከሱት ፤ ተወላጅ ፡ ንጉሣችንን ፡ አጠፉ ፤ እያለ ፡ በጠብ ፡ ዓይን ፡ ይመለከታቸው ፡ ጀመር ። ስለዚህ ፡ የቴብ ፡ የአሞን ፡ ካህናት ፡ ከላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ሹማምንት ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ በበላያቸው ፡ ሳቅኑሬ ፡ አንደኛ ፡ የሚባለውን ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ ሦስተኛ ፡ አፒፒ ፡ (ፈርዖን) ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ውጊያ ፡ ጀመሩት ።

ስለዚህ ፡ የሂክሶስ ፡ ነገሥታት ፡ ከ፩ሺ፯፻፹፰ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፭፻፹፰ ፡ እንደግማሾቹ ፡ (፩ሺ፯፻፹፰-፩ሺ፭፻፹፰) ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያኸል ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ በ፲፯ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ነገሥታት ፡ ይልቁንም ፡ በአህሞሲስ ፡ መሪነት ፡ ከአገር ፡ ተወላጁ ፡ ከግብፅ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ተዋግተው ፡ ተሸንፈው ፡ ከነሕዝባቸው ፡ ወደ ፡ መጡበት ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ተመለሱ ፤ ግማሾቹም ፡ በየመንገዱ ፡ በከነዓናውያን ፡ አገር ፡ ተውጠው ፡ ቀሩ ፡ ይባላል ።

አሕሞሲስ ፡ እንደባዕድ ፡ እየታዩ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሲገዙ ፡ የነበሩትን ፡ ሂክሶስን ፡ ካስወገደ ፡ በኋላ ፤ እነዚያ ፡ የመሠረቱዋቸውን ፡ አዳዲስ ፡ አማልክትና ፡ ቤተ ፡ መቅደሳቸውን ፡ እያፈረሰ ፡ የግብፅን ፡ አማልክት ፡ ከነዚያውም ፡ በጣም ፡ የታወቁትን ፡ በቴብ ፡ የአሞን ፡ — ራን ፡ በመምፊስ ፡ የፕታህን ፡ መቅደስ ፡ አሳድሶ ፡ በደንብ ፡ አሠራ ።

(፩) የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍጥር ፡ ፲፰—፲፱ ።



በኑብያ ፡ ሰሜን ፡ የሸፈቱትንም ፡ እየወጋ ፡ አሳምና ፡ ሲገዛ ፡ ኖረና ፡ በመጨረሻ ፡ አርጅቶ ፡ በ፩ሺ፭፻፶፯ ፡ ዓመት ፡ ሲሞት ፡ ከጠላት ፡ ቀንበር ፡ አገሩን ፡ ያዳነ ፡ በመሆኑ ፡ መላው ፡ የግብፅ ፡ ተወላጅ ፡ አዘነለት ። ካህናቱም ፡ ተማከረው ፡ አሕሞሲስንና ፡ ሚስቱን ፡ (ወዲያውም ፡ እናቱን) ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የአማልክትነት ፡ ደረጃ ፡ ሰጡዋቸው ።

ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ የነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ልጁ ፡ አሜን ፡ ሆቴፕ ፡ ፩ኛ ፤ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ቱትሞሲስ ፡ አንደኛው ፡ ሁለተኛውና ፡ ሦስተኛውም ፡ አገራቸው ፡ ከመገዛት ፡ ከዳነ ፡ በኋላ ፡ እነሱ ፡ ደግሞ ፡ አሳባቸውን ፡ አሁን ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ማስፋፋት ፡ ላይ ፡ መደቡ ። የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እያደራጁ ፡ የጦር ፡ እሰታ ፡ እየመለመሉ ፡ የሞዓባውያንን ፡ የኤዶማውያንን ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ የሒቲትን ፡ ( ፓለስቲን ) የዓረብያን ፡ ሰሜን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ ከአሶርና ፡ ከባቢሎን ፡ በቀር ፡ የታናሽ ፡ እስያን ፡ አገር ፡ እንደዚሁም ፡ የኑብያን ፡ ሰሜን ፡ በሙሉ ፡ ወግተው ፡ እያስገበሩ ፡ በየገቡበት ፡ አገር ፡ የሚገኘውን ፡ ወርቅና ፡ ሀብት ፡ በዘረፋም ፡ በግብርም ፡ ምክንያት ፡ እየሰበሰቡ ፡ የግብፅን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ አከበሩት ። ነገሥታቱ ፡ ከነቤተሰባቸው ፡ በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸው ፡ ዙፋናቸው ፡ የመብል ፡ ማዕዳቸው ፡ መጠጫቸው ፡ ሲሞቱ ፡ ምስላቸው ፡ የምስላቸው ፡ መቃብር ፡ ከነግድግዳው ፡ በወርቅ ፡ ይሠራ ፡ ጀመር ። የባቢሎንና ፡ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ ወርቅ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደአሸዋ ፡ ነውና ፡ እባክህ ፡ ላክልን» ፡ እያሉ ፡ የዚህን ፡ ዘመን ፡ የግብፅን ፡ ፈርዖኖች ፡ ይለምኑ ፡ ጀመር ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ስለግብፆች ፡ ፊደል ፡ እንመልከት ። የዚህም ፡ ፊደል ፡ ቅርጽ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ማተሚያ ፡ ቤቶች ፡ በፍጹም ፡ የማይገኝ ፡ በመሆኑ ፡ ጽሑፉን ፡ በእጄ ፡ ጽፌ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ከልሼ ፡ አሠርቼ ፡ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ ምዕራፍ ፡ ይገኛል ። የፊደሎቻቸውን ፡ (ሂዬሮግሊፍ) ፡ መልክ ፡ ራሴ ፡ የባልሁዋቸው ፡ ስለሆነ ፡ ደንበኛ ፡ ሥዓሊ ፡ ካለመሆኔ ፡ የተነሣ ፡ መልካቸውን ፡ እንደግብፃውያኑ ፡ ጸሐፊ ፡ ማስተካከል ፡ አልቻልኩም ።

## ምዕራፍ ፯ ።


### ፩ኛ፡ የግብጽ፡ ሥዕል

ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት፡ ከአራተኛው፡ ሺ፡ ዓመት፡ ጀምሮ፡ የግብጽ፡ ሕዝብ፡ መንግሥት፡ አቁሞ፡ ከተማ፡ እየከተመ፡ በሥልጣኔ፡ መምሩን፡ አዊቀው፡ ሁሉ፡ በየመፃሕፉ፡ ገልጿል። የስዕዜህ የስእል፡ ሥዕላቸውንም፡ የሠጠሩበት፡ ዘመን፡ በዚሁ፡ ጊዜ፡ ሳይ፡ መሆኑ፡ ነው። ሥዕልን፡ የሠጠሩት፡ ሊቃውንት፡ ባን፡ እኛ፡ ሬጠርነው፡ በማለት፡ ሬንቃ፡ ቁት፡ የሚባለው፡ አምላካቸን፡ አዘጋጅቶ፡ ስጠን፡ ብለው፡ አስተማሩ፡ ይኸም፡ ሥዕሉን፡ በሕዝብ፡ ዘንድ፡ ለማስከበር፡ የተፈረገ፡ መሳይመስላል።

እነሱም፡ ቢሆኑ፡ በመዝመሪያ፡ ዘመናቸው፡ ስእልን፡ እንደ ሥዕል፡ የሚሠሩቱ፡ ዘዴ፡ በቀጥታ፡ አላገኙትም። ስለዚህ፡ ግሪኮች፡ እንዲ፡ ሠየሙት፡ በመግመሪያ፡ የተገኘው፡ ብልሐት "ፒክቶግራም" የተባለው፡ ባዙ፡ አሳብን፡ አንድነት፡ በተሣለ፡ ስእል፡ የመግለጽ፡ ሥራ፡ ነው። ለምሳሌ፡ አንበሳ፡ ተኮሳን፡ ሪገጦ፡ ሲታይ፡ ኢትዮጵያ፡ ጣልያንን፡ ወጋም፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሥ፡ የኢጣልያኑን፡ አሸነፈው፡ ወይም፡ ተኮሳ ባንበሳ፡ ሳይ፡ ቆሞ፡ ሲታይ፡ ጣልያን፡ ኢትዮጵያን፡ ማሸነፉ፡ ነው ኳቶቹም፡ እንደሚተረጉሙ፡ አንድ፡ አሞራ፡ ያንድ፡ ሶርያዊ፡ መሰክ ከነጠሙ፡ ባለበት፡ በ፮ አበባዎች፡ ላይ፡ ተቀምጦ፡ በእጁ፡ ሶርያዊውን፡ ከነአበባዎቹ፡ በገመድ፡ እየጐተተ፡ እንደሚሄድ፡ ተሥሎ፡ የታየ፡ እንደሆነ፡ አሞራው (የግብጹ፡ ንጉሥ) ፮ ሺ፡ አበባዎች (ሬሺየሶርያ፡ ምርኮኞች) ይዞ፡ መመለሱ፡ ነው፡ ተብሎ፡ ይነበባል፡ ቶሪውም ንጉሡ፡ የሚገዛቸው፡ አገሮች፡ የሚወጹቸውን፡ የሚሸልማቸው፡ መኳንንቶችና፡ ካህናቶች፡ የርሱና፡ የአምላኩ፡ ባንድነት፡ ንግግር፡ ይኸን፡ በመሳሉ፡ ስእል፡ ይፈጸማል።


CITY - HALL LIBRARY
of
ADDIS ABABA





ሻምፖሊዎን ፣ በግሪክኛ ፣ በዴሞቲክ ፣ በሂዬሮግሊፍ ፣ በሮቱ ፣ ዓይነት፣ ፊደሎች፣ ተጽፎበት ፣ ያገኘው ፣ የደንጊያ ፣ ጽሑፍ ። ( ጋስቶን ፣ ፓርሎ ፣ )

የዚህ ሁኔታ ምስጢራዊ ስለሆነ በነገሩ ከተስማሙት ሊቃውንት በቀር ሕዝብና መኳንንት ሲተረጕሙት ይሰማል እንጂ ነገሩን ራሱ አውቀውት ለሥራና ለጉዳይ አይጠቀሙበትም ነበር። ነገር ግን ቀጥሎ ባለው ጊዜ ውስጥ በ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ግሪካውያን "ሂሮግሊፍ — ቅዱስ የፊደል ቅርጽ" ብለው የሠየሙትን ከዚያው ከስእል ያልወጣውን ፊደል አወጡ።
የዚህ የሂሮግሊፍ ቅርጽና ሥራው አስቦ ከዚያው ከፒክቶግራም የመነጨ በመሆኑ ፊደሉ እያሉ ያዘጋጁት ነፍስ ያለውን ፍጥረት ሰውን እንስሳን ወይም የሰውነቱን ክፍሎች እስከ ዛሬ ድረስ ዐይን የሚስብ ነገር ነው። ለምሳሌ የእጅ ስእል "ዲ" ያፍ ስእል "ሬ" የወፍ ስእል "መ" የቤት ስእል "ሀ" ተብሎ ይነበባል፤ ለምሳሌ ከዚህ በታች የሚገኙትን የስእል ፊደሎች እንመልከት፤



| የስእሉ መልክ | የምናውቀው የመልክ ስም | የፊደልነት ከ[illegible] |
|---|---|---|
| | ቤት | ሀ |
| | የተኛ አንበሳ | ለ |
| | ጉጉት | መ |
| | እግር | በ |
| | እጅ ● | ዲ |
| | አፍ | ሬ |
| | የወሀ [illegible] | ነ |
| | ዳቦ | ተ |
| | ክንድ | እ |
| | የተጠመጠመ ገመድ | አ |
| | የእንትክልት ቅጠል | ኪ |
| | ክር | ስ |
| | ጫጩት | ወ |



እንደዚሁ ፳፭ ጊዜ ሁለቱና ስድስቱ የስእል ፊደል እንደ ቃል እንደሚሆን ፳፭ ጊዜ እንዲሁ የስእል ፊደል ብቻውን ተደጋግሞ ሙሉ ቃል ሙሉ ስም ሙሉ አገባብ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ እንደ "☥" የመስቀል ምልክት "ነሀ" ተብሎ ይነበብና እንደ ነገሩ አካሄድ "ሕይወት" ወይም "ሕያው ይሁን" ተብሎ ይተረጐማል፤ እንደ የጉጉት ስእል "መ" ተብሎ ተነቦ "በውስጥ" ተብሎ ይተረጐማል፤ የቤት ስእል "ሀ" ሲባል ይኸን ዓይነት የተሳለ እንደሆነ "ፐ ረ" ተብሎ "መውጣት" ተብሎ ይተረጐማል። ባጭሩ በግብጻውያን "ፐ ረ" ማለት በኛ "መውጣት" ማለት ነው። ዳግም ማናቸውም ስእል በፊደልነት በሚያገለግልበት ጊዜ የራሱን ስም የሚያገኘው በራሱ አጠራር ነው። ለምሳሌ በፊደልነት የእጅ ስእል "ዲ" ተብሎ ሲነበብ ራሱ እጅ የሚጠራበት ስሙ "ዲረተ" ተብሎ ተለውጦ በሌላ ስም ይጠራል።

እነዚህን የመሰሉ ለፊደልም ለስምም ለአገባብም ለቃልም የሚጠቀሙባቸው ቁጥሮቻቸው እስከ ፯፻ የሚደርሱ የስእል ፊደሎች ነበሩዋቸው። ግብፆች በነዚህ ፊደሎቻቸው በቤተ መቅደሳቸውና በቤተ መንግሥታቸው ግድግዳ ላይ በመቃብርና በሐውልት ዙሪያ ላይ ሲጽፉ እንደ ፊደሎቻቸው ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ ከላይ ከግራ ወይም ከቀኝ ወገን ከምሪው ቁልቁል ይጽፉ ነበር። አብዛኛ ጊዜ ግን [illegible] የተገኘው ጽሑፍ እኛ እንደምንጽፈው ከግራ ወደ ቀኝ ተጽፎ የሚነበብ ነው።

ይኸንን የመሰለው የግብፆች ጥንታዊ የስእል ፊደል በሌሎች መበርከት በትርጉሙ በአገባቡ ብዛትና መስፋፋት ቢያስቸግርም የቀለም ስፋትና የሆኑት ጸሐፊዎችና ካህናቶች እያ

ጠኑ፡ከሁለት፡ሺ፡ዓመት፡ይበልጥ፡ጸንቶ፡ሲሠራበት፡ኖረ። በጅ
ጎጋይና፡በሸክላ፡በብረትና፡በብር፡በወርቅ፡ዕቃ፡መሣሪያ፡ሐውልት
ላይ፡ከሚቀረጸው፡በቀር፡ከመልእክት፡ለአዋጅ፡ከድጓም ትና
ለጸሎት፡በጠቅላላው፡ለዘመትር፡ሥጋዊና፡መንፈሳዊ፡ጉዳይ፡መጻ
ሕፍ፡እንዲሆን፡እፎቅ፡ከሰለቦ፡በተዘጋጀ፡"ፓፒሩስ"፡በሚባለ
ው፡በዛፍ፡ልጥ፡ላይ፡የተጻፈው፡ብዙ፡ነው። በዚህ፡ፊደልና፡በዚህ፡
ልጥ፡ብዙ፡መጻሕፍት፡ይኖሩ፡ነበር። ከሁሉ፡ይበልጥ፡በ፲፯፻
ምዕራፍ፡የተከፈለው፡ለምዕራፍ፡እንደ፡ግንዘቤ፡ይደግሙበ
ትና፡ይጸልዩበት፡የነበረው፡መጽሐፍ፡በፓሪስ፡በሉቭር፡ሙዚየ
ያዩት፡በጣም፡ያደንቃል።

ነገር፡ግን፡ይህ፡የሥእል፡ፊደል፡እያንዳንዱ፡በመግ
ብዙ፡ጊዜ፡መፍጀቱ፡ስለተሰማቸው፡በ፳፫፻ ዓመ
ት፡ከክርስቶስ፡በፊት፡በእጅ፡ቶሎ፡ቶሎ፡እያፈጠኑ፡ለመጻፍ
እንደሚመች፡አሻሽለው፡"ሂየሮቲክ"፡የቀሳውስት፡ፊደል
የተባለውን፡አወጡና፡ይሠሩበት፡ጀመር። ይህም፡መሻሻል፡የመ
ይበቃ፡ሆኖም፡ስለተገኘ፡በ፯፻ ዓመት፡ላይ፡ከዚህ፡ይበልጥ፡ተሻ
ሽሎ፡እንደ፡ሕዝብ፡ሁሉ፡እያፈጠነ፡ለመጻፍ፡እንዲመች፡
"ዴሞቲክ"፡የሕዝብ፡ፊደል፡የተባለው፡ወጣ። ይህም፡በመጨረሻ
ተሻሽሎ፡የወጣው፡የሕዝብ፡ፊደል፡የተሠራው፡መሠረት፡
ሆመሪቦትክናማት፡(ሞኔባይ)ተነሥቶ፡ግብጽንም፡ሊቢያን
ቃናን፡እስያም፡ግማሽ፡አገር፡ጨምሮ፡ይገዛ፡በነበረው፡ታርሐ
(ቲርሐቅ)፡በሚባለው፡በኢትዮጵያዊው፡ንጉሥ፡ዘመን፡ነው
ሱም፡የነበረበት፡ዘመን፡፯፻፲ እስከ፡፯፻፹ ዓመት፡ነው፡ከዚ
በቲገኙ፡የሚያወጡትም፡የሚያወርዱትም፡ነኩ።

ይሁን፡እንጂ፡ይህ፡የተሻሻለው፡ሁለቱም፡ዓይነት፡እ



ጠኑ፡ለመጻፍ፡ቢመች፡ባለ፡የቀድሞው፡መልኩና፡አቀማመጡ፡የ
ሚያምረው፡መልኩ፡በከጠፋ፡በሐውልትና፡በመቃብር፡ሕንጻ
ላይ፡የሚቀረጸው፡በቀድሞው፡የሥእል፡ፊደል፤ ለሥራና፡ለመ
ልእክት፡ለመጽሐፍ፡አሁን፡ሁለት፡ጊዜ፡በተሻሻለው፡ፊደል፡በመ
ሉና፡በፓፒሩስ፡(የልጥ፡ወረቀት)፡ላይ፡ይጻፍ፡ጀመር።


እንዲዚህ፡ሆኖ፡ሲኖር፡ትልቁ፡እስክንድር፡የፋርስን፡መ
ንግሥት፡አስወግዶ፡ግብጽን፡በያዘና፡የርሱ፡ተከታዮቹ፡እነ፡ፕቶሎ
ሚ፡(በጥሎሞስ)፡ግብጽን፡እያስተዳደሩ፡የግሪክን፡ሥልጣኔ፡ማስ
ፋፋት፡በጀመሩበት፡ዘመን፡የሠተኛውም፡የተሻሻለውም፡የግብጽ፡ፊደል፡ቀረና፡ከግሪክ
ና፡ከዲሞቲክ፡ተቀላቅሎ፡የወጣው፡ኮፕት፡የሚባለው፡ፊደልና፡ጽ
ሑፍ፡ተተክቶ፡ይሠራበት፡ጀመር። ይኸም፡የነገሥት፡ፊደል
ከክርስቶስ፡በፊት፡ከ፫፻ ዓመት፡ጀምሮ፡ከክርስቶስ፡ልደት፡በኋላ
እስከ፡፯ኛው፡መቶ፡ዓ፡ም፡ሕረት፡ከቆየ፡በኋላ፡የመሐመድ፡ተከ
ታዮች፡የቁስጥንጥንያን፡ግዛት፡አየቀሙ፡በአፍሪካ፡በሚገኘ
ብተው፡ግብጽንም፡ይዘው፡በስተዳደሩ፡ጊዜ፡በኮፕቶች፡ቤተ
የሉባቸው፡የአረብኛ፡ፊደልና፡ጽሑፍ፡እንዲገባ፡አደረጉ። ይኸም
እስከ፡ዛሬ፡ጸንቶ፡እነሆ፡ይሠራበታል።

የኮፕቶችና፡የአረብኛ፡ፊደል፡በየተራ፡ከገባ፡ወዲህ፡ይኸን
የእንስሳና፡የዕቃ፡ሥእል፡የሚያመለክተውን፡ፓንታዊ፡የግብጽ፡ፊ
ደል፡ለባቸው፡ግብጾቹ፡ስለማያውቁት፡የአውሮፓ፡ሊቃውንት፡
በጥንቱ፡ከተማ፡በቴብ፡በመምፊስና፡በሉክሶር...በየሀውልቱ፡
በየመቃብሩ፡አምዱና፡ግድግዳ፡ላይ፡እየተመለከቱ፡ሕንጻውን፡በ
ሚያደንቁበት፡ጊዜ፡ጽሑፉን፡እያዩ፡ጽሕፈቱ፡ሆነ፡ወይስስ
እል፡ይሆን፡እያሉ፡ብዙ፡ዘመን፡ሲቸገሩበት፡ኖሩ። ግማሾቹ

ስንኳ፡ነው፡ብለው፡ከእነሱ፡በኋላ፡ነገሩን፡በጥብቅ፡የተከታተሉት፡ሊቃውንት፡ KIRCHER, WARBURTON, ZOEGA, AKERBLAD, DE SACY, YOUNG፡ድሖፉ፡መሆኑን፡ቢረዱም፡ባንዳንዱ፡ስርመንገድ፡ከመፍታት፡ቢቀናቸውም፡ትክክለኛውን፡የፊደሉ፡መንገድ፡ስላላገኙት፡እንደምኞታቸውን፡እስከ፡አቅሙ፡ድረስ፡አድካሚውን፡ስራ፡እየቆረጡ፡ከተዉት፡በኋላ፡አንዳንዶችም፡ትዕግሥታቸውን፡በሚቀጥሉበት፡ጊዜ፡ከንዱ፡እሱ፡ቁጥር፡1821 (፲፰፻፳፩) ዓ፡ም፡ሻምፖሊዮን (CHAMPOLLION) የሚባል፡የፈረንሳዊ፡ተወላጅ፡በድንገት፡ፈታው።

ለመፍታት፡የረዳው፡ብዙ፡ቋንቋና፡ድሖፉ፡ከዚያውም፡የኮፕቶን፡ማወቁ፡ብቻ፡ሳይሆን፡ሮዜታ፡በሚባለው፡ከተማ፡ባንድ፡ጥርብ፡ድንጋይ፡ላይ፡የተገኘው፡ድሖፉ፡ነው። በዚህ፡ድንጋይ፡ላይ፡በዚሁ፡በሂሮግሊፍ (ቅዱስ፡የሌዲሊ፡ቅርጽ)፡በዲሞቲክ፡(የሕዝብ፡ፊደል)፡በግሪክ፡በሶስት፡ዓይነት፡ቋንቋ፡ተጽፏል። የሂሮግሊፉን፡እንደተቻለኝ፡ከዚህ፡በታች፡ለአንባቢ፡ጉዳዩን፡ለማብራራት፡ስል፡ጽፌዋለሁ፡(ስጽፌዋለሁ)።

1 2



ያንዱ፡ቁጥር፡ምልክት፡ባፊረዓሁበት፡ጊርጊ፡ያለውን፡የፊረክኛውን፡አንባቢ፡የግብጹን፡ንጉሥ፡የጥቁሎሚን፡ስም፡የሚናገር፡መሆኑን፡በተረዳ፡ጊዜ፡ይኸኛውም፡የዓይ፡የርሱ፡ስም፡መሆን፡አለበት፡ቢሎ፡ገመተና፡ምርመራውን፡ዳንቱ፡ይቀጥል፡ዠመር። ከድንጋይ፡ላይ፡ቀድሞ፡ወደቤቱ፡ወስዶ፡ለጸጥታ፡እያስተያየ፡መረመረ



ዐፐ፡ ⌓ት፡ [hieroglyphs] ለ═መ፡ ፃኢ፡ ፆስ፡ነው፡ብሎ፡ፈታው[1]፡ከዚያው፡የ፪ቁጥር፡ምልክት፡ያደረባሁበትን፡ከሌላኛው፡ከጥቁሎሚስ፡ጋር፡እያስተያየ፡ሲመረምር፡በሁለተኛው፡ድሖፍ፡ውስጥ፡በሌተኛው፡ውስጥ፡የነበሩ፡የ"ፐ፡ተ፡ለ፡ኦ"ን፡አሌት፡ፊደሎች፡የሚያመለክቱትን፡ስእሎች፡በሁለተኛው፡ውስጥ፡ባገኘ፡ጊዜ፡ይኸኛው፡ሁለተኛው፡የክሌዎፓትር፡ስም፡ነው፡ብሎ፡ገለጸና፡በነዚህ፡ስሞች፡ብዙ፡ዘመን፡የተዘጋውን፡የስንኳ፡ፊደል፡ቁልፍ፡አገኘ። ከዚያ፡እርሱ፡ባዘጋጀው፡ፊደል፡በሐውልትም፡በመቃብርም፡ላይ፡የተቀረጸ፡በብራና፡በፓፒሩስ፡ላይ፡በእጅም፡የተጻፈው፡እንደሆነ፡ወደእንግሊዝኛ፡ወደ፡ጀርመን፡ወደፈረንሳይ፡በየቋንቋው፡ይተረጎም፡ጀመር።

(1) በዚያን፡ጊዜ፡ክጦሌሚዎስ፡ፕቶሎሚ፡ፕቶሎመኢዎስ፡ይባሉ፡ነበር፡

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

### ዓባይና ፡ የቀድሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡— የግብፅ ፡ ገዥነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡— ራምሲስ ፡ ፪ኛ ።

የዚህ ፡ የጥንታውያን ፡ ግብፆች ፡ የሥዕል ፡ ፊደል ፡ ብዛቱን ፡ግማሹ በ፸፪ ፡ ሲያቆመው ፡ ግማሹ ፡ በየጊዜው ፡ ከሚገኘው ፡ ምልክት ፡ ጋር ፡ እስከ ፡ ፫ሺ ፡ የሚያደርሰው ፡ አለ ። የፊደሉ ፡ የሰዋሰው ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ይኸን ፡ በትክክል ፡ ለመረዳት ፡ ለኔም ፡ ላንባቢም ፡ ሰፊ ፡ ጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ አጭር ፡ አሳቡን ፡ ከተረዳን ፡ በኋላ ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ የቀድሞ ፡ ፈርዖኖች ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደምን ፡ እንደገዙ ፡ ዓባይም ፡ ለኑብያና ፡ ለግብፅ ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥቅምና ፡ በነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ክብር ፡ ወደ ፡ መመልከት ፡ እንለፍ ።

ከሚያምር ፡ አዳራሹ ፡ ወጥቶ ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጦ ፡ እየተጉሳመመ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የደስታ ፡ ድምፅ ፡ ለሚያሰማው ፡ ሕዝብ ፡ ፈገግታ ፡ እያሳየ ፡ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ እንደሚገዝ ፡ መሰፍን ፡ የዓባይም ፡ ውሃ ፡ ከአዳራሹ ፡ ከጣና ፡ ወጥቶ ፡ ለኑብያና ፡ ለግብፅ ፡ መሬት ፡ ሕይወት ፡ እየሰጠ ፡ ከረዥም ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ እዘመዱ ፡ እሜዲቴራኔ ፡ ባሕር ፡ ይገባል ። ሁል ፡ ጊዜ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ለእሻዋማው ፡ አገር ፡ ለግብፅ ፡ ያፈር ፡ ስንቅ ፡ እንዳቀበለ ፡ ይኖራል ። ለዚህ ፡ ውለታ ፡ ግብፃውያኑም ፡ ኑብያዎቹም ፡ ሳይቀሩ ፡ ለዓባይ ፡ የአምላክነት ፡ ደረጃ ፡ ሰጥተው ፡ በሕይወት ፡ ላይ ፡ ሕይወት ፡ ከምትጨምርላቸው ፡ ከፀሐይ ፡ እኩል ፡ እያመለኩ ፡ የነጭ ፡ በሬ ፡ መሥዋዕት ፡ ሲያቀርቡለት ፡ ኖረዋል ።

ዓባይ ፡ የቀድሞው ፡ የኛ ፡ የግዕዝ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓባዊ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ፈለገ ፡ ግዮን ፡ ሲለው ፡ ይገኛል ፤ ፈረንጆች ፡ «ኒል» ፡ ከሚሉት ፡ ጋር ፡ ግጥሚያ ፡ የለውም ። ጥንታውያን ፡ ግብፆች ፡ ከኛ ፡ ይበልጥ ፡ ዓባይን ፡ በመውደድና ፡ በማክበር ፡ ያመልኩበታል ። ስሙን ፡ የአማልክቶቻቸው ፡ ካህናት ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የቀለም ፡ ሰዎች ፡ የሆኑት ፡ «ሐፒ — ቅዱሰው ፡ ወንዝ» ፡ የሚሉትን ፡ ያልተማረው ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ «አቱር ፡ ወይም ፡ አውር — ወንዝ» ፡ ብለውት ፡ ይገኛል ።



የግብፅ ፡ አገር ፡ ራሱ ፡ የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ አገር ፡ እንደሚባለው ፡ ንጉሡም ፡ (ፈርዖኑ) ፡ የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ እንደሚባል ፡ ዓባይንም ፡ የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ ዓባይ ፡ ብለው ፡ ምስሉን ፡ ለምስም ፡ ነገር ፡ በራሳቸው ፡ ባሥሩ ፡ በእጃቸው ፡ ለአማልክት ፡ የሚሰጥ ፡ የፍራፍሬ ፡ ስጦታ ፡ በያዙ ፡ ሰዎች ፡ ተስሎ ፡ ይታያል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብቻውን ፡ ይሳላል ። ከምስሉ ፡ ፪ቱ ፡ በሉቭር ፡ የተቀመጡትን ፡ ተመልክቻለሁ ። የአማልክቱ ፡ ካህናት ፡ ዓባይ ፡ ከኦሲሪስ ፡ (በጎ ፡ አድራጊው ፡ አምላክ) ፡ ከንድ ፡ እየፈሰሰ ፡ ለፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሕይወትን ፡ የሚሰጥ ፡ ራሱ ፡ ከፀሐይ ፡ የሚወዳደር ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለዚሁ ፡ ለበጎው ፡ ተግባርና ፡ ለአምላክነቱ ፡ የሚገባ ፡ መዝሙር ፡ ደርሰውለት ፡ መዝሙሩን ፡ ማስፔር ፡ የሚባለው ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተርጕሞታል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የአማልክት ፡ አገር ፡ ከሚባለው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ከሚመነጨው ፤ ዓባይ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ደጅ ፡ የሚጠኑ ፡ የጥንት ፡ ከተሞች ፡ መርዌ ፤ ናፓታ ፡ ቴብ ፡ ሔሊዎፖሊስ ፡ መምፊስ ፡ . . . በሚያልፍበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተኰልኩለው ፡ ይታያሉ ። ከነዚሁ ፡ መርዌና ፡ ናፓታ ፡ የኢትዮጵያ ፡ (የኑብያ) ፡ ሔሊዎ ፡ ፖሊስ ፡ መምፊስ ፡ የግብፅ ፡ ከተሞች ፡ ናቸው ። ባለመቶው ፡ በር ፡ ከተማ ፡ ብሉ ፡ ሄሮዶቱስ ፡ የሰየመው ፡ የቴብ ፡ (ጠባይድ) ፡ ከተማ ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ሆና ፡ የደከመ ፡ ግብፃዊ ፡ ፈርዖን ፡ ሲለቀው ፡ የበረታ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ሲይዘው ፡ እንደ ፡ ካምቤዝ ፡ ሶርያዊ ፡ ንጉሥ ፡ የጨከነ ፡ ወራሪ ፡ ሲያፈርሰው ፡ ያገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ንጉሥ ፡ መልሶ ፡ ሲጠግነው ፡ ኖሯል ። የጠላትን ፡ አፍራሽነት ፡ ያገር ፡ ተወላጅን ፡ ጠጋኝነት ፡ እንደ ፡ ቴብ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ የታዘበ ፡ ከተማ ፡ አይገኝም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እሁለት ፡ አገር ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ ከተማ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ አውድማ ፡ የጕበዝ ፡ ጕራ ፡ መሆኑ ፡ በቴብ ፡ አልተዠመረምና ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ።

የኢትዮጵያ ፡ ዝርዝሩ ፡ ነገድ ፡ ግማሹ ፡ በዋሻ ፡ ግማሹ ፡ በበረሃ ፡ የቀረው ፡ በጎጆ ፡ ሲኖር ፡ የሠለጠኑት ፡ ወገኖች ፡ ዛሬ ፡ ጀበል ፡ ባርጋ

በሚባለው ፡ አጠገብ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ናፓታ ፡ የሚባለውን ፡ ከተማ ፡ ከትመው ፡ ከናፓታም ፡ በፊት ፡ ሌሎች ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ባልሆኑ ፡ መንደሮች ፡ በያለበት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ፡ ፡ ከ፪ ፡ ሺ ፡ እስከ፡ ፰፻፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ድረስ ፡ የአክሱም ፡ ድምፅ፡ ገና ፡ አልተሰማም ፤ ምናልባት ፡ መኖሩ፡ እንኳን ፡ ባይካድ ፡ እንደኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ዕውቅ ፡ አልሆነም ።

የዚያን ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ በግብፆች ፡ ዘንድ፡ ኩሽ ፡ በነቢያቱና ፡ በዓረቦች ፡ ዘንድ ፡ ሳባ ፡ በግሪኮች ፡ ዘንድ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩት ፡ ናቸው።ነቢያቱ ፡ እነኢሳይያስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኩሽ ፡ ብለው ፡ መልሰው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ብለው ፡ የሚጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ መኖሩን ፡ የቀሩት ፡ እንኳን ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ስማቸውን ፡ ብቻ ፡ እየጠቀሱ፡ ቢያልፉ ፡ ግሪኮቹ ፡ እነሆሜር ፡ እነሄሮዱቱስ ፡ እነዴዮዶር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ጠቀስነው ፡ ስለጥንቶቹ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የጠባይ፡ ዝርዝር ፡ ሲሰጡ ፡ «ኢትዮጵያውያን ፡ መልካቸው ፡ ያማረ ፤ ቁመናቸው ፡ ረጋ፝ሮም ፡ እንግዳ ፡ ተቀባዮች ፤ በአፋቸው ፡ አሰት ፡ የማይገባ ፡ እርጅተው ፡ የሚሞቱ ፤ አማልክት ፡ የሚያፈቅሯቸው ፤ በማንም ፡ ተገዝተው ፡ የማያውቁ ፡ . . . . » እያሉ ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ በባሕርዩ ፡ ያለውን ፡ ጉድለቱንና ፡ ምላቱን ፡ እንደዛሬ ፡ ማበጠር ፡ ምንም ፡ ያህል፡ ባልተለመደበት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደህነኛ ፡ የሆነውን፡ ቅጽል ፡ ሁሉ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ አሸክመው ፡ እንዳለፉ ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ራሳቸው ፡ ጢንዚዛ ፡ ወይም ፡ ዝኖን፡ የሚመስሉ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ፡ እያሉ ፡ የጻፉትን ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ በሰፊው ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ግዛት ፡ ብለው ፡ ግሪኮቹ ፡ የሚጠሩትን ፡ ግብፆቹ ፡ የደቡብ ፡ ምድር ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ የሚሉትን ፡ ወሰኑን፡በትክክል፡ መለየት፡ ይቸግራል። ቢሆንም፡ ከሰሜን፡ ግብፅ ፡ ከአንደኛው ፡ የዓባይ ፡ ፈሳሽ ፡ ውድቀት ፡ ( ካታራክት ) ፡ ይዋሰንና ፡ ከምሥራቅ ፡ የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ከአዱሊስ ፡ እስከታች ፡ እስከ ፡ ኤል ፡ ማንደብ ፡ ድረስ ፡ ነው ። ከደቡብና ፡ ከምዕራብ ፡ ወገን፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ የታወቀና ፤ የሚከላከል ፡ መንግሥት ፡ ስለአልነበረ ፡ እዙፋን ፡ እንደወጡት ፡ ነገሥታት ፡ ድካምና፡






ዳግማዊ ፡ ራምሴስ ፡ በሠረገላ ፡ ሆኖ ፡ የኑብያን ፡ ወታደር ፡ በቀስት ፡ ሲወጋ ፡
( ቤት ፡ አል ፡ ዋሊ ። )




ከድሉ ፡ በኋላ ፡ ከ፲ ፡ አገሮች ፡ የኑብያ ፡ መልክተኞች ፡ ያመጡለትን ፤ ግብርና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሲቀበል ።
( ቤት ፡ አል — ዋሊ ። )

CITY - HALL LIBRARY of ADDIS ABABA

ኃይል፡ በየጊዜው፡ ሲሰፋም፡ ሲጠብም፡ የኖረ፡ ይመስላልና፡ የዚያን፡ ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደዛሬው፡ የፖለቲካ፡ ወሰኑን፡ በትክክል፡ መለየት፡ አይቻልም ።

በግምት፡ ከ፱፡ ፻፡ ዓመት፡ ዠምሮ፡ በኢትዮጵያውያንና፡ በግብፃውያን ወሰን፡ መካከል፡ ጠብ፡ ፍቅር፡ ዝርፊያ፡ ግድያ፡ ምርኮ፡ ሲፈራረቅ፡ ኖሯል። ከክርስትና፡ በፊት፡ ከ፩፻፭፻፹፡ ዓመት፡ ወዲህ፡ ግብፆች፡ ዕድል፡ አጋጠማቸውና፡ ከቀድሞ፡ ዠምሮ፡ ያልበረደው፡ ሥልጣኔያቸው፡ በዚህ፡ ጊዜ፡ ይበልጥ፡ ተስፋፋ ። ከመካከላቸው፡ እሕሞሲስ፡ አንደኛ፡ ተከታዩ፡ አሜንሆቴብ፡ አንደኛ፡ ከነርሱ፡ ወዲህ፡ የተነሡት፡ እነቱትሞሲስ፡ ፫ኛ፡ ከጊዜ፡ ወደ፡ ጊዜ፡ ኃይል፡ ማግኘትና፡ መግነን፡ ዠመሩ ። ግራና፡ ቀኝ፡ በመካከለኛው፡ ምሥራቅና፡ በሊቢያ፡ ሲስፋፉ፡ ወደ፡ ደቡብ፡ እየመጡ፡ ኢትዮጵያንም፡ ለመውረር፡ አቆበቆቡ ።

በነዚህ፡ ፈርዖኖች፡ የዘመን፡ እኳያ፡ የነበሩት፡ የኑብያ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ነገሥታት፡ እነአሜኔምሖት፡ እነፃውዕ፡ በዚህ፡ ጊዜ፡ የነበራቸው፡ ኃይልና፡ ሥልጣኔ፡ ከግብፆቹ፡ ያነሠ፡ ነው ። ሥልጣኔ፡ ቢኖራቸውም፡ ያው፡ ከግብፅ፡ የመነጨ፡ ሥልጣኔ፡ በመሆኑ፡ ከነዚህ፡ ከግብፆች፡ ፈርዖኖች፡ ለመወዳደርና፡ ለመመከት፡ የዚያን፡ ዘመን፡ አቅማቸው፡ አልፈቀደላቸውም ።

ግብፃውያኑ፡ ከነዚህ፡ ፈርዖኖች፡ በፊት፡ ሄክሶስ፡ የሚባሉት፡ የሴፍን፡ ባለሟልና፡ መጋቢ፡ አድርገውት፡ የነበሩት፡ ከምሥራቅ፡ አገር፡ መጥተው፡ ይገዙዋቸው፡ በነበረ፡ ጊዜ፡ «ከጠላት፡ ቀንበር፡ አድነን »፡ እያሉ፡ አማልክቶቻቸውን፡ ፕታህን፤ኦሲሪስን፤.... ይለምኑ፡ ነበር ። ገዥዎቻቸው፡ ወጥተው፡ ነፃነታቸውን፡ አግኝተው፡ በአሁኑ፡ ጊዜ፡ ኃይል፡ ሲሰማቸው፡ ደግሞ፡ የምንገዛው፡ ሰፊ፡ ግዛት፡ ስጠን፡ ድል፡ አድራጊነትን፡ አጐናጽፈን፡... እያሉ ¹ በስለት፡ ለነዚያው፡ አማልክት፡ መሥዋዕት፡ ያቀርቡ፡ ዠመር ። አማልክቶቻቸው፡ የፊተኛው፡ ፕታህና፡ የኋለኛው፡ አሞንም፡ በነቢያቶቻቸውና፡ በካህናቶቻቸው፡ እንደበት፡ «የምሥራቅን፡ አገር፡ እንድትመታ፤ የኑብያን፡ አገር፡ እንድትወጋ፡ ፈቀድሁልህ፡ .....ከንዴ፡፡ ካንተ ጋራ፡ ናት፡ .....» እያሉ፡ ለፈርዖኖቹ፡



ይነግሩ፡ ዠመር ። ከባርነት፡ ከወጡ፡ በኋላ፡ ሌላውን፡ ባሪያ፡ ለማድረግ፡ መነሣት፡ በግብፃውያን፡ አልተዠመረም ። ባቢሎንም፡ አሶርም፡ ፋርስም፡ ግሪክም፡ ሮማም፡ ዓረብም፡ የዛሬም፡ ፈረንጆች፡ በሌላው፡ ሲገዙ፡ ኖረው፡ ሌላውን፡ መልሰ፡ ለመግዛት፡ በመመኘት፡ በዚህ፡ ረገድ፡ ያላቸው፡ የታሪክ፡ መሥመር፡ የሁሉም፡ አንድ፡ ዓይነት፡ ነው ። ካልደከመና፡ ካልፈራ፡ በቀር፡ ሲቻለው፡ የራሴ፡ አገር፡ ይበቃኛል፡ ብሎ፡ በራሱ፡ አገር፡ ተሰብስቦ፡ የኖረ፡ ሕዝብና፡ መሪ፡ በታሪክ፡ ውስጥ፡ አይገኝም ። በሰው፡ መገዛት፡ መሮኛልና፡ እኔም፡ የሰው፡ አገር፡ አልወርም፡ የሚል፡ ለመውረር፡ አቅሙን፡ ያልተማመነው፡ ብቻ፡ ነው ።

ስለዚህ፡ እሕሞሲስ፡ የሚባለው፡ ፈርዖን፡ በ፩፻፡ ፭፻፹-፩፻፡ ፭፻፶፯፡ መካከል፡ የኢትዮጵያን፡ ወሰን፡ እያለፈ፡ መውጋትና፡ መዝረፍ፡ ዠመረ ። ተከታዮቹም፡ አሜንሖቴብ፡ አንደኛ፡ ቱትሞሲስ፡ አንደኛ፡ ከርሱ፡ ይበልጥ፡ እየገፉ፡ ብዙ፡ አገር፡ ያዙ ። ከነርሱ፡ በኋላ፡ የተነሣው፡ ቱትሞሲስ፡ ፫ኛ፡ የሚባለው፡ ፩፻፭፻-፩፻፬፻፶፡ ዓመት፡ ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት፡ መካከል፡ የነገሠው፡ ፈርዖን፡ ከነርሱ፡ በበለጠ፡ በያለበት፡ ጦር፡ እየላከ፡ የኢትዮጵያን፡ (ኑብያን)፡ አገር፡ አስያዘ ። በምሥራቅ፡ በኩል፡ ብዙ፡ አገሮች፡ አስገብሮ፡ ግብፅን፡ አማግነን፡ አደረሰ ። ከያለበት፡ በዘረፋም፡ በግብርም፡ የሚገባው፡ ዕቃ፡ ብር፡ ወርቅ፡ የግብፅን፡ መንግሥት፡ አከበረው፡ «ወርቅ፡ ባንተ፡ ዘንድ፡ እንዳሸዋ፡ ነውና፡ አባክህን፡ ላክልን»፡ እያሉ፡ የባቢሎን፡ ነገሥታት፡ ይለምኑት፡ ዠመር ።

ሻምፖሊዮን፡ የሚባለው፡ የፈረንሳዊ፡ ተወላጅ፡ የጥንቱን፡ የግብፆችን፡ ፊደል፡ ያፈታቱን፡ ምሥጢር፡ እስኪገልጸው፡ ድረስ፡ እነዚህ፡ የግብፅ፡ ነገሥታት፡ ባገራቸው ውስጥና፡ ካገራቸው፡ ውጪ፡ የሠሩት፡ ብዙ፡ ታሪክ፡ ተደብቆ፡ ይኖር፡ ነበር ። በኋላ፡ ግን፡ ባለፈው፡ እንደተመለከትነው፡ የፊደሉ፡ ፍቺ፡ ከታወቀ፡ በኋላ፡ ብዙ፡ የጀርመንና፡ የእንግሊዝ፡ የፈረንሳዊና፡ የአሜሪካ፡ ሊቃውንት፡ በጓድ፡ በጓድ፡ እየሆኑ፡ ወደጥንታውያኑ፡ ከተማ፡ ወደ፡ መምፊስቴብ፡ ሉክሶር፡ ካርናቅ፡ እየመጡ፡ በየሐውልቱ፡ በየቤተ፡ መቅደሱ፡ በየቤተ፡ መንግሥቱ፡ ያጻራሽ፡ ግድግዳ፡ ላይ፡ የፈርዖ



ዳግማዊ ፡ ራምሴስ ፡ የሦርያን ፡ ምርኮኞች ፡ እየመታ ፡ሲሠዋ ። ( ገር ፡ ገር ፡ ክሴር ። )



ኖቹ ፡ አጽም ፡ እሚሸፈንበት ፡ የንጨትና ፡ የድንጋይ ፡ ልባስ ፡ በው ስጡና ፡ በውጭውም ፡ እንደ ፡ ሥዕል ፡ ተጽፎ ፡ ከሚገኘው ፡ ላይ ፡ ግማሹ ፡ ሊቃውንት ፡ ሲገለብጥ ፡ የቀረው ፡ ሊቃውንት ፡ ወደ ፡ የቋንቋው ፡ ከተረጐመው ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ የፈርዖኖቹ ፡ የጦርነት ፡ የመንግሥትና ፡ የነገሥታት ፡ የአማልክትና ፡ የካህናት ፡ ታሪክ ፡ ከነ ሥርዓቱ ፡ መገኘት ፡ ቻለ ።

ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ፈርዖኖቹ ፡ እነቱትሞሲስ ፡ እነራምሲስ ፡ ኑብያን ፡ ያስገበሩበት ፡ ታሪክ ፡ አብሮ ፡ ተገኘ ። በዚሁ ፡ ታሪክ ፡ በእ ስራኤል ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በነቢያቱ ፡ አማካይነት ፡ ለመ ሳፍንቱ ፡ ለነሶምሶን ፡ ለነጌዴዎን ፡ ለነገሥታቱ ፡ ለነሳኦል ፡ ለነ ዳዊት ፡ . . . . ፍልስጥኤምንና ፡ አሞንን ፡ ሞአብንና ፡ አማሌቅን ፡ በእጅህ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ፡ ውጋቸው ፡ ፍጃቸው ፡ እንደሚ ለው ፡ እንደዚሁ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ስሙን ፡ ያነሣነው ፡ አሞን ፡ የሚ ባለው ፡ መቅደሱ ፡ በካርናቅ ፡ (ቴብ) ፡ የሚገኘው ፡ የግብፃውያን ፡ አምላክ ፡ ልጄ ፡ ወዳጄ ፡ ለሚላቸው ፡ ለነቱትሞሲስ ፡ ለነራምሴስ ፡ የምሥራቅን ፡ አገር ፡ የኑብያን ፡ ምድር ፡ ሰጥቼሃለሁና ፡ ውጋቸው ፡ እያለ ፡ የተናገራቸውና ፡ እነርሱ ፡ የመለሱት ፡ የምስጋና ፡ ቃል ፡ የሚያቀርቡለት ፡ ስለትና ፡ መሥዋዕት ፡ ሁሉ ፡ አብሮ ፡ ተገኘ ።

ቱትምሲስ፡(ቱትህሜስ-ትሑትህሜስ) ፡ በአሥራ፡ስምንተኛው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ከነገሡት ፡ ዋነኞች ፡ ነገሥታት ፡ የሚ ቆጠር ፡ ታላቅ ፡ ፈርዖን ፡ ነው ። በካርናቅ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ግድ ግዳ ፡ ላይ ፡ ተገኝቶ ፡ የተተረጐመው ፡ ታሪኩ ፡ በምሥራቅ ፡ አገር ፡ አሶራውያንን ፡ ፊንቃውያንንም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ የኑብያን ፡ አገር፡ ማስገበሩ ፡ እንደዚሁም ፡ የርሱ ፡ እኅት ፡ የምትሆን ፡ ሐታሱ ፡ (ሐሸ ፐሱዊት) ፡ የምትባለው ፡ የሥልጣን ፡ ተካፋዩ ፡ ሆና ፡ ለብቻዋ ፡ ጦር፡ አዘጋጅታ ፡ፑንት ፡ የሚባለውን፡ አገር ፡ ወግታ ፡ የከበረ ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ እንጨት ፡ ዕጣን ፡ ሽቱ ፡ እንዳስመጣች ፡ ታወቀ ። ፑንት ፡ የተባለው፡ አገር ፡ ሰሜናዊው ፡ ኢትዮጵያችን ፡ እስከ፡ ኤል ፡ ማንደብ ፡ ያለውና፡ የየመንንም ፡ ግዛት ፡ ጭምር ፡ ነው ።

ይኸን፡ጽሑፍ፡ከጥንቱ፡ፊደል፡(ሂዬሮግሊፍ)፡ላይ፡የገለበጡትና ፡ የተረጐሙት ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ በታሪካዊ ፡ የከተማ ፡ ፍራሾች ፡ በሉ ክሶርና ፡ በካርናቅ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በጥናት ፡ የኖሩት ፡ ሙሴ፡አጉስት ፡



ሙሴ ፡ በቤቱ ፡ ያደገው ፡ ዳግማዊ ፡ ራምሴስ ፡ በዙፋኑ ። ሐውልቱ ፡ በቶሪኖ ፡ የሚገኝ።
( ፕራምፖሊኒ ። )



ኤድዋርድ ፡ ማሪዬት ፡ (AUGUSTE EDUARD MARIETTE) የሚባሉትና ፡ ሙሴ ፡ ቪኮንት ፡ ኤማኑኤል ፡ ደ ፡ ሩገ ፡ (VICOMPTE EMANOUEL DE ROUGÉ) ናቸው (፩) ።

ከነርሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ስተረጐመው ፡ በዚያው ፡ በተገኘው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ አሞን ፡ አምላኩ ፡ ለፈርዖኑ ፡ ለቱትሞሲስ ፡ እንደዚህ ፡ ሲለው ፡ ይነበባል ።

«ና ፡ ወደኔ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ያደረግሁልህን ፡ ተመልክተህ ፡ በደስታ ፡ ዝለል ። በዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ የተመላኸው ፡ ተበቃዩ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደሴ ፡ ስትመጣ ፡ ልቤ ፡ በደስታ ፡ ይመላል ፡ . . . . . በሁሉም ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ድልን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ በልባቸው ፡ ፍርሃትና ፡ ድንጋጤ ፡ አሳድራለሁ ። ባንተ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ከንዴን ፡ ለጥበቃ ፡ እዘረጋለሁ ፡ የኑብያን ፡ አገር ፡ (ኢትዮጵያን፡) በሺና፡ በእልፍ ፡ የሚቆጠሩትን ፡ አገሮች ፡ ባንድነት ፡ አሥሬ ፡ እሰጥሃለሁ። የምሥራቅን ፡ አገር ፡ የኑብያን ፡ ምድር ፡ እንድትመታ ፡ ፈቅጄልሃለሁ ። ኃይልህን ፡ ዘርጋ ፤ እንደ ፡ ወንድሞችህ ፡ የመሰለውን ፡ ግርማዊነትህን ፡ አሳያቸዋለሁ ፡ . . . ላንተ ፡ ጽናትና ፡ ኃይል ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የነሱን ፡ ክንድ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ጨምሬዋለሁ ፡ . . . ጠላቶችህን ፡ በጫማህ ፡ ሥር ፡ ጣልኋቸው ፤ . . . እንደትእዛዜ ፡ ዓለም ፡ በወርዱም ፡ በስፋቱም ፡ ምዕራቡም ፡ ምሥራቁም ፡ ያንተ ፡ ነው ። . . . . በረጋ ፡ ልብ ፡ በሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ትገባለህ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ስለምመራህ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ትእዛዝህን ፡ ሊቃወም ፡ አይችልም ። የሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ነሥቻቸዋለሁና ፡ ድምፅህን ፡ ጩኸትህን ፡ እስከ ፡ ዋሻቸው ፡ ድረስ ፡ አሰማቸው ፡ . . . . በግንባርህ ፡ ያለው ፡ አምላካዊ ፡ መንፈሴ ፡ ይገለባብጣቸዋል ፤ በጠጉራቸውም ፡ አስተሳስሮ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ያመጣቸዋል ። የአክሊል ፡ ብርሃን ፡ በዜጎችህ ፡ ላይ ፡ ያበራል ። ከሰማይ ፡ በታች ፡ ማንም ፡ ሽፍታ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ሊነሣ ፡ አይችልም ። ሁሉም ፡ ግብራቸውን ፡ በዠርባቸው ፡ ተሸክመው ፡ እንዳገኑበሱ ፡ ወዳንተ ፡ ይመጣሉ ። በግርማዊነትህ ፡ ፊት፡ ይሰግዳሉ ።

---

(፩)VICOMPTE DE ROUGÉ – ETUDE DIVVERS MONUMENTS: DU RÉGNE DE TOUTMOSIS III ገጽ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ፡

መቼም ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ንግግር ፡ በቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ በራምሲስ ፡ ፪ኛ ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ የአሞን ፡ ሊቃነ ፡ ካህናትና ፡ ነቢያት፡ እነአህሞሴ፡ እነአቡኔፍ፡ በጥበብ፡ ሐውልቱን ፡ እናግረው፡ ወይም ፡ ራሳቸው ፡ ከአሳባቸው፡ እያመነጩ፡ የጻፉት ፡ ነው ፡ እንጂ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ዓይን ፡ ቦሙ ፡ ወኢይሬእዩ ፤ አፍ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይነቡ ፡ የሚላቸው ፡ እነአሞን ፡ ይኸን ፡ ባለፈው ፡ ያነበብነውን ፡ ቃል ፡ ተናግረው ፡ አለመሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዘመኑ፡ ልማድ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ለውጊያ፡ ወደ ፡ ሌላው፡ አገር ፡ ለመሔድ ፡ ሲያስብ ፡ ለአምላኩ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ መሥዋዕት ፡ በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ውጭ ፡ ሲያቀርብና ፡ የሚዘምትበትን ፡ አገር ፡ ለማሸነፍ ፡ መቻል፡ አለመቻሉን ፡ ሲጠይቅ፡ የጣዖቱ ፡ ነቢያትና ፡ ካህናት ፡ የተማሩ ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸውና ፡ እላይ ፡ ያነበብነውን ፡ የመሰለ ፡ አነጋገር ፡ በሕልም ፡ ዓይተው ፡ ወይም ፡ ከአሳባቸው ፡ ቀርጸው ፡ ለንጉሡ ፡ ይነግሩታል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ፈርዖን ፡ ቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ በጦር ፡ መሣሪያና ፡ በሠራዊት ፡ ብዛት፡ ኢትዮጵያን ፡ እየወጋ ፡ ብዙ፡ አገር ፡ መያዙ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። በወጣትነቱ ፡ ወራት ፡ እንደነገሠ ፡ አሳቡ ፡ ሁሉ ፡ ግዛት ፡ በማስፋት ፡ ጉዳይ ፡ ስለተያዘ፡ በግማሹ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ሰው ፡ እየላከ ፡ በቀረው ፡ ራሱ ፡ እየዘመተ ፡ ከአባቶቹ ፡ የተረፈውን ፡ የኑብያን ፡ አገር ፡ አስገበረ ። ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ ለግብፅ ፡ እንገዛም ፡ ብለው ፡ ሁልጊዜ ፡ የፈርዖኖቹን ፡ ኃይል ፡ ይመልሱ ፡ የነበሩት ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተሸንፈው ፡ ገበሩ ። የቀሩት ፡ የዘወትር፡ ውጊያና ፡ ዘረፋ ፡ ስለአጠቃቸው ፡ ወደ፡አትባራ ፡ ወደ ፡ ተከዜ ፡ ሸሹ ። ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ የግብፅ ፡ ጦር ፡ ወደዚሁ ፡ አገር ፡ ባይቀመጥ ፡ እንኳን ፡ በየብስ ፡ በባሕር ፡ በመርከብ ፡ መጥቶ ፡ የተረፉትን ፡ ተዋግቶ ፡ ብዙ ፡ ባላባቶች ፡ ማርኮ ፡ ተመልሷል ።

የገበሩት ፡ አገሮች ፡ ከየአገራቸው ፡ ከሚገኘው ፡ የቀንድ ፡ ከብትም ፡ ከአራዊትም ፡ ከአትክልትና ፡ ከፍራፍሬ ፡ ይዘው ፡ ብርም ፡ ወርቅም ፡ ዕጣንም ፡ ከርቤም ፡ በመርከብ ፡ እየወሰዱ ፡ ለኃያሉ ፡ ፈርዖንና ፡ ለአምላኩ ፡ ለአሞን ፡ ይገብሩ ፡ ዠመር ። ያመጡትንም ፡ ግብርና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ አስቀምጠው ፡ «ዐሕዩ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፤ ለተቀደሰው ፡ ሰውነትህ ፡ ሰላምታ ፡ እናቀርባለን ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ግብፅን ፡ አናውቅም ፡ ነበር ፤ አባቶቻችንም ፡ ወደዚህ ፡ አልመጡም ። የሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ስጠን ፤ መሬት ፡ ሁሉ ፡ ከሚገዛህ ፡ በታች ፡ ናት ፡» እንደሚሉት፡ ከሐውልቱ ፡ ላይ ፡ ይነበባል ።



በቴብ ፡ ከተማ ፡ በካርናቅ ፡ የአሞን፡ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጠኛ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ ራሜን ፡ ኬፔር ፡ (ደጉ ፡ አምላክ) የሁለቱ ፡ አገር ፡ (የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ የኩሽና ፡ የግብፅ ፡) ንጉሥ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖረው ፡ በጦር ፡ ያስገበራቸው ፡ አገሮች ፡ ተብሎ፡ የ፲፭ ፡ አገሮች ፡ ስም ፡ በዝርዝር ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። ከነዚህም ፡ በመዠመሪያው፡ መሥመር፡ የሚገኘው ፡ የኛው ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ነው፡ በተዘረዘሩት ፡ አውራጆች ፡ ውስጥ ፡ አዱሊት ፡ (ዐትሊት)፤ ቃካሩ፡ ሐማሱ ፤ ቃና ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ስለአለበት ፡ አዱሊስ ፡ ትግሬ ፡ አማሴን ፡ ማና ፡ ማለቱ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ተብሎ ፡ ተገምቷል ። ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ ደጉ ፡ አምላክ ፡ እየተባለ ፡ መጠራቱ፡ ልማድ ፡ ነው ። ከዝርዝሩ ፡ ጐን ፡ ደግሞ፡የኢእሉእ ፡ የፑንት ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የገበሩበት ፡ ሥዕል ፡ ይታያል ።

በቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የጠቀስናት ፡ ሐታሱ ፡ (ሐት ፡ ሰሄፕሱ-ሐትሸፕሱት ፡ ) አንዳንድ፡ ጊዜ ፡ ራማካ ፡ ወይም፡ማካሬ ፡ የምትባል ፡ የቱትሞሲስ ፡ ፩ኛ ፡ ልጅ፡ የቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ እኅትና ፡ ወዲያውም ፡ ሚስት ፡ ነበረች። ይህቺ፡ ሴት ፡ ኃይለኛና ፡ ጥበበኛ ፡ ስለሆነች ፡ በዘመኗ ፡ በፊት ፡ ከቱትሞሲስ ፡ ፪ኛ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ከቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ ጋር ፡ ሆና ፡ የንጉሥነት ፡ ሥልጣን ፡ እየተሻማች ፡ እንደ፡ ንግሥት ፡ ሆና፡ ለራሷ፡ ሐውልት ፡ በራሷ ፡ ስም ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡እያሠራች ፡ እንደዚሁም፡ የራሷን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እየላከች ፡ አገር ፡ ማስወጋቷ ፡ ምርኮ ፡ ማግኘቷ ፡ ተጽፎአል ።

ሐታሱ ፡ ጦር ፡ የላከችበት ፡ አገር ፡ ፑንት ፡ ይባላል። እርሱም ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ የባብ ፡ ኤል፡ማንዴብና ፡ የደቡብ ፡ ዓረብ ፡ (የመን) ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ተብሏል። ይህች ፡ የቤት ፡ ንግሥት ፡ በቴብ ፡ ከተማ ፡ ለአምላኳ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ ካሠራች፡ በኋላ ፡ ለዚሁ፡

CITY - HALL LIBRARY
of
ADDIS ABABA



ሐታሱ ፡ (ሐትስ ፡ ሐፕሱዊት ፡ ) ሻምዱር ።



ቤት ፡ መቅደስ ፡ አገልግሎት ፡ የሚውል ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ ሽቱ ፡ ሌላም ፡ የከበረ ፡ ነገር ፡ እንዲያመጡላት ፡ ጦር ፡ አዘጋጀች ። አዘጋጅታ ፡ ከጨረሰች ፡ በኋላ ፡ እንደደንቡ ፡ በሊቀ፡ካህኑ ፡ አማካይነት፡ ዘመቻው ፡ የሚቀናት ፡ መሆኑን ፡ አምላኳን ፡ ብትጠይቀው ፡ የተስጣት ፡ መልስ ፡ ፑንትን ፡ ሰጥቼሻለሁ ፡ እስከዛሬ፡ እስከ ፡ አማልክት፡ አገሮች ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ መንገዱን ፡ ማንም ፡ የማያውቀውን ፡ ማንም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ወደ ፡ ዕጣኑ ፡ አገር ፡ የደረሰ፡ የለም።የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ በወሬ ፡ ያወሩት ፡ ከመሰማቱ፡ በቀር፡ከግብፃውያን ፡ ማንም፡ አልሔደበትም ፡ የሚል ፡ ሆነ ።

ስለዚህ ፡ ሐታሱ ፡ ወታደሮቿን ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፩ሺ፭፻፰-፩ሺ፬፻፹፬፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ በ፭ ፡ መርከብ፡ አድርጋ ፡ ወደ፡ ዚሁ ፡ አገር ፡ ልካ ፡ እንዳስመታች ፡ መርከበኞቹም ፡ ደርሰው ፡ ከፑንት ፡ መስፍን ፡ ፓሪሁ ፡ ከሚባለው ፡ ጋር ፡ ተዋግተው ፡ እንዳሸነፉትና ፡ እንደማረኩት ፡ ከዚያ ፡ የሚፈልጉትን ፡ የእንጨትና ፡ የአትክልት ፡ ዛፍ ፡ የዝኆን ፡ ጥርስ ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ፡ ሽቱ ፡ ባሪያ ፡ ድንክ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ወደቴብ ፡ እንደተመለሱ ፡ ዛሬ ፡ ደ ፡ ይር ኤል ፡ ባሕሪ፡ በሚባለው፡ ሥፍራ ፡ የማራኪዎቹና፡ የተማራኪዎቹ ፡ ሥዕል ፡ ፑንት ፡ አገር ፡ ሔዶ ፡ የመጣው ፡ መርከብ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ይዘው ፡ የመጡት ፡ ሽታው ፡ የሚጣፍጥ፡ልዩ ፡ ልዩ ፡ የአትክልትና ፡ የዛፍ ፡ የአዕዋፍና ፡ የዓሣዎች ፡ ሥዕል ፡ የፑንት ፡ አገር ፡ መንደርና ፡ ቤት ፡ ከነመሰላሉ ፡ ይታያል ። እንደዚሁም ፡ ተማርኮ ፡ የመጣው ፡ ፓሪሁ ፡ የሚባለው ፡ መስፍን ፡ አፍንጫው፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጢማም፡ የራስ ፡ ጠጉሩ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ እጀ ፡ ጠባቡን ፡ በቀበቶ ፡ አሥሮ ፡ በቀበቶው ፡ ላይ ፡ ጩቤ ፡ እንዳንጠለጠለ ፡ ያንገቱን ፡ ዙሪያ ፡ ትልልቅ ፡ ዶቃ ፡ ወይም ፡ ቊርበተ ፡ ሐሊም ፡ በሚመስል ፡ ጌጥ ፡ እንዳጌጠ ፡ በግራ ፡ ቅልጥሙ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የተደራረቡ ፡ የወርቅ ፡ አምባሮች ፡ እንዳደረገ ፡ በእጁ ፡ እንደበትረ፡ መንግሥት፡ ያለ ፡ የብረት ፡ ወይም ፡ የጠንካራ ፡ እንጨት ፡ ዱላ ፡ እንደያዘ ፡ ሚስቱን ፡ አቲ ፡ የምትባለዋን ፡ እንዳስከተለ ፡ ይታያል። የሚስቱ፡ የአቲ ፡ ልብስ ፡ ከርሱ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ እንደርሱ ፡ አንገቷን ፡ ቊርበተ ፡ ሐሊም ፡ በሚመስል ፡ ነገር ፡ አጊጣ ፡ ጠጉሯን ፡ በደንብ ፡ ተሠርታ ፡ ትታያለች ።

የባሏና ፡ የሚስትዩዋ ፡ ልብስና ፡ ጌጥ ፡ የጨቤው ፡ ትጥቅ ፡ ካገራች ንና ፡ ከዓረብ ፡ አገር ፡ ባላባቶችና ፡ ሰዎች ፡ ትጥቅና ፡ ልብስ፡ምንም ፡ ያህል ፡ ስለማይራራቅ ፡ የሐታሱ ፡ ሰዎች ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ በመርከብ ፡ መጥተው ፡ የተዋጉት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ፑንት ፡ ያሉት ፡ የዛ ሬውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰሜንና፡ ምሥራቅን፡ የመንንም ፡ ጭምር ፡ መሆኑ ፡ ይታመናል ። ሽቶው ፡ ከዓረብ ፡ እንደሆነም ፡ ዕጣኑና ፡ ከር ቤው ፡ ከውጋዴንና፡ ከአውሳ ፡ ከሱማሌ ፡ አገር ፡ ሊሆን ፡ ይችላል።

ሐታሱ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ምርኮ ፡ ካገኘች ፡ ወዲህ ፡ ለቤተ ፡ መቅ ደሷና ፡ ለራሱዋ ፡ የሚገባውን ፡ ከአከፋፈለች ፡ በኋላ ፡ ፴፪ ፡ የሚሆን ውን ፡ የሽቱ ፡ አትክልት ፡ በቤተ ፡ መንግሥቷ ፡ ዙሪያ ፡ አስተከለ ችው ፡ ይባላል ።

ይህ ፡ ታሪክና ፡ ቃል ፡ ተደብቆ ፡ ሲኖር ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳ መለከትሁት ፡ ሙሴ ፡ አጉስት ፡ ማሪዮት ፡ የፈርዖኖች ፡ ቤተ ፡ መን ግሥትና ፡ የአማልክቱ ፡ መቅደስ ፡ በነበረበት ፡ በካርናቅና ፡ በሉክ ሶር ፡ በሌላውም ፡ ሥፍራ ፡ እያስቆፈሩ ፡ ከየፍራሹ ፡ ጽሑፉን ፡ ሲገ ለብጡ ፡ ሙሴ ፡ ደ ፡ ሮዤ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተርጕመው ፡ የቱትሞ ሲስ ፡ ዜና ፡ መዋዕልና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሐውልት ፡ ጥናት ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ አውጥውታል ። እንደዚሁም ፡ እነምስተር ፡ ስፐሲዮስ ፡ ቤርቺና ፡ ብሩሽግ ፡ በጀርመንና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሉሎችም ፡ በየበኩላቸው ፡ ከሌላው ፡ የግብፅና ፡ የፈርዖኖች ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ እያወጡ ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ በየቋንቋው ፡ እንዲያነበው ፡ አድር ገዋል ።

እንግዲህ ፡ ግብፆች ፡ የተድሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚባለውን ፡ የዛ ሬውን ፡ ሱዳን ፡ ከአስገበሩ ፡ ከአትባራ ፡ ወዲህ ፡ ሰሜኑንና ፡ ምሥ ራቁን ፡ የዛሬውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ እየላኩ ፡ ካስመቱ ፡ በኋላ ፡ የወዲህኛውን ፡ እንኳን ፡ ነዋሪ ፡ ጦር ፡ አስቀምጠው ፡ ጨርሰው ፡ ባይገዙት ፡ የኑቢያውን ፡ (የዛሬውን ፡ ሱዳን ፡) ግዛት ፡ በሙሉ ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ግዛት ፡ ደባልቀው ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ያደርጉበት ፡ ጀመር ። ስዚሁ ፡ ግዛት ፡ የበላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ የፈርዖኑ ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ሆነ ። የማዕርግ ፡ ስሙም ፡ የኩሽ ፡ ንጉሣዊ ገዥ ፡ ተባለ ። በውስጡም ፡ ከቀደምዎቹ፡ ከኢትዮጵያ፡ ነጋሢዎች ፡



ውስጥ ፡ ታማኙ ፡ እየተመረጠ ፡ አብር ፡ ወይም ፡ የበታች ፡ ሆኖ ፡ ይገዛ ፡ ጀመር ። ይኸውም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ሮማውያን ፡ በፓለ ስቲን ፡ ግዛት ፡ ያገር ፡ ተወላጁን ፡ ሄሮድስንና ፡ ሮማዊውን ፡ ጲላጦ ስን ፡ ከሾሙት ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ (ኩሽ ፡) ነገሥታትና ፡ ሕዝብ ፡ የጦር ነቱ ፡ ዝርዝር ፡ እንኳን ፡ ባይገኝ ፡ ጊዜ ፡ በተመቻቸው ፡ ቍጥር ፡ የግ ብፅን ፡ ገዥዎች ፡ እባርረው ፡ የራሳቸውን ፡ ነፃ ፡ መንግሥት ፡ ለማ ቋቋም ፡ የታገሉት ፡ ባጭሩ ፡ በየጽሑፉ ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ ከኃይለኛዪቱ፡ እኅቱ ፡ ከሐታሱ ፡ በኋላ ፡ እየተከታተሉ ፡ የነገሡት ፡ ፈርዖኖች ፡ ይበልጥ ፡ እያየሉ ፡ ስለ ሔዱ ፡ የነፃነት ፡ ተስፋቸው ፡ እየራቀ ፡ ሔደ ።

ከቱትሞሲስ ፡ ፫ኛ ፡ በኋላ፡ ከኃይለኞቹ ፡ ፈርዖኖች ፡ መካከል፡ ይበልጥ ፡ ገናና ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆነው ፡ ራምሲስ ፡ ፪ኛ ፡ (ግሪኮች ፡ ሴሶትሪስ ፡) የሚሉት ፡ ነው ። ራምሲስ ፡ ማለት ፡ ትርጓሜው ፡ የፀ ሐይ ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡ ነው ። እርሱም ፡ አባቱ ፡ ሴቲ ፡ ፩ኛ ፡ ሲሞት ፡ በወጣትነቱ ፡ ጊዜ ፡ በአሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመቱ ፡ ነገሠ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አንዳንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሐውልቱን ፡ ራሱ ፡ በዘመኑ ፡ ሲያስቀ ርጽ ፡ ታሪኩንም ፡ በዘመኑ ፡ ከዜጎቹ ፡ ሊታውንት፡ ውስጥ ፡ ሲያጽፍ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴና ፡ ምስጋና ፡ ማስጨመሩ ፡ አንዳንድ ፡ እውነት ፡ ያልሆነ ፡ ነገርም ፡ ጣልቃ ፡ ማስገባቱ ፡ ባይቀርም ፡ አብዛኛው ፡ ከሐ ውልት ፡ የተገኘው ፡ ታሪኩ ፡ እውነት፡ ነው ። የራምሲስን ፡ ጀግንነ ትና ፡ ድፍረት ፡ የሚናገሩት ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ በዘመኑ ፡ በያለበት ፡ ያስቀረጻቸው ፡ ሐውልቶች ፡ ናቸው ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቤተ ፡ መቅደስና፡ ከተማ ፡ ይልቁንም ፡ ብዙ ፡ ሐውልት ፡ በማሠራት ፡ ራምሲስ ፡ ከሌ ሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ፈርዖኖች ፡ እንደሚበልጥ ፡ ጸሐፊው ፡ ሁሉ ፡ አረጋግ ጧል ። በሕይወቱ ፡ በሉክሶር ፡ ካሠራቸው ፡ ሐውልቶች ፡ አንዱን፡ ሰባስ ፡ የሚባለው ፡ መሐንዲስ ፡ ፓሪስ ፡ ወስዶት ፡ ኮንኮርድ ፡ በሚ ባለው ፡ አደባባይ ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ይታያል ። የቀረው ፡ በመምፊስ፡ በቴብ ፡ በሉክሶር ፡ ግማሹ ፡ ቆሞ ፡ ግማሹ ፡ ተኝቶ ፡ ሲታይ ፡ ከነ ዚሁ ፡ ከተማዎች ፡ የፈርዖኖቹንና ፡ የአማልክቱን ፡ የካህናቱን ፡ ሐው ልትና ፡ መጣሪያ ፡ ግማሹን ፡ የፈረንሳዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥ

CITY - HALL LIBRARY



ዳግማዊ ፡ ራምሴስ ፡ በቀኙ ፡ አሞንን ፡ በግራው ፡ ሙትን ፤ ( ሴት ፡ አምላክ፡) አድርጎ ፡ እርሱ ፡ በመካከል ፡ ተሠልሶ ፡ ያሠራው ፡ ሐውልት ፡ ሐውልቱ ፡ በቶሪኖ ፡ የሚገኝ ( ፕራምፖሲኒ ። )



ታት ፡ በግብፅ ፡ ላይ ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣን ፡ በነበራቸው ፡ ሰዓት ፡ በሊቃውንት ፡ እያስመረመሩ ፡ በመርከብ ፡ አግዘው ፡ ወደየከተማ ቸው ፡ ወስደው ፡ ሙዚውማቸውን ፡ (የታሪካዊ ፡ ዕቃ ፡ ቤታቸውን) አስጊጠውበታል።የቀሩት ፡ ከተሞች ፡ እንደፍሎራንስ ፡ እንደቶሪኖ ፡ እንደሮማ ፡ እንደቤርሊን ፡ ያሉትም ፡ በየበኩላቸው ፡ ባገር ፡ ተወላ ጁና ፡ በታሪካዊ ፡ ጽሑፍ ፡ መሪነት ፡ እየቆፈሩ ፡ ወይም ፡ በግዥ ፡ ያገኙትን ፡ ወደየአገራቸው ፡ አስመጥተዋል ።

ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የራምሲስን ፡ ታሪክ ፡ የያዘው ፡ የካርናቅ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ራምሲስ ፡ ዳግማዊ ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ የምሥራቅ ፡ ግዛቶቹ ፡ በሸፈቱበት ፡ ጊዜ ፡ እንደምን ፡ እንደተዋጋቸው ፡ ከድፍረቱ ፡ ከዠግንነቱ ፡ ጋር ፡ የአሞን ፡ ርዳታ ፡ ጭምር ፡ እየተዘረዘረ ፡ ተጽፎ አል ። በምሥራቅ ፡ አገር ፡ ስለአደረገው ፡ ጦርነት ፡ ከየሐውልቱ ፡ ላይ ፡ የተተረጐመው ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ነው ።

በነገሠ ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ መሳፍንቱንና ፡ መኳንንቱን ፡ አስከትሎ ፡ በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ (ግብፃውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሊቢ ያውያን ፡) ታጅቦ ፡ ሊዋጋ ፡ ሔደ ፤ ኻያ ፡ የሚሆኑ ፡ የኬታ ፡ የሂ ቲቲ ፡ ( ሶርያ ፡ ሜሶፖታምያ ፡ ፓለስቲን ፡ ) ሕዝቦች ፡ በየንገዳቸው ፡ ተሰልፈው ፡ ራምሲስን ፡ ለመመከት ፡ ይጠባበቃሉ ። ራምሲስ ፡ ወደ ነሱ ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ የበድዊን ፡ ሰዎች ፡ በሲና ፡ በምድያን ፡ የሚገኙ ፡ ለኸዚህ ፡ ሰላዮች ፡ ሆነው ፡ መንገድ ፡ በመምራት ፡ ራምሲ ስን ፡ አሳስተው ፡ ከጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ለይተው ፡ በጠላቶቹ ፡ እጅ ፡ ጣሉት ። በአጠገቡ ፡የነበሩት ፡ ወታደሮቹም ፡ በፍጹም ፡ ሸሹ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ራምሲስ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ጮኸ ።

« ቀስተኞቼ ፡ ፈረሰኞቼ ፡ ትተውኝ ፡ ሸሹ ። ከነሱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ስንኳ ፡ በጐኔ ፡ ሆኖ ፡ የሚዋጋ ፡ የለም ፡ አባቴ ፡ አሞን ፡ ሆይ ፡ ሐሳብህ ፡ ምንድን ፡ ነው ? አባት ፡ ልጁን ፡ ይከዳልን ፡ ወይስ ፡ በትእዛ ዝህ ፡ አልሔድሁምን ፡ እንደበትህና ፡ ምክርህ ፡ አልመሩኝምና ፡ በዓ ልህን ፡ በታላቁ ፡ አላከበርሁምን ፡ ቤትህንስ ፡ በምርኮ ፡ አልሞላሁ ምን ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ገጹ ፡ በረከቱን ፡ ሊያቀርብልህ ፡ ይሰበሰባል ፡



የአሞን ፡ በዓል ፡ በሚውልበት ፡ ቀን ፡ ቀሳውስት ፡ ምስሉ ፡ ያለበትን ፡ ታንኳ ፡ ተሸክመው ፡ ሲዞሩ ። ( ዴስክሪፕሲዮን ደ ፡ ሌጂፕት ። )

CITY - HALL LIBRARY
of
ADDIS ABABA



ቤት ፡ መቅደስህን ፡ በርስተ ፡ ጉልት ፡ አከበርሁ ። በሽቶና፡ መዓዛው፡ በሚጣፍጥ ፡ ሳር ፡ ላይ ፡ ፴ሺ ፡ በሬ ፡ ለመሥዋዕት ፡ አረድሁልህ ፡ ቤት ፡ መቅደስህን ፡ በታላላቅ ፡ ሕንፃ ፡ አሠራሁ ። ዘለዓለማዊ ፡ ዓፀ ድም ፡ በዙሪያው ፡ አስተከልሁ ፡ . . . . ትልልቅ ፡ መርከቦች ፡ ላንተ ፡ የሚገባውን ፡ የየአገራቸውን ፡ ግብር ፡ ይዘው ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ይጓ ዛሉ ፡ . . . . አባቴ ፡ ሆይ ፡ ባልታወቁ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ሆኜ ፡ ስምህን ፡ እጠራለሁ ፡ በፊትህ ፡ ብቻዬን ፡ ነኝ ፡ ቀስተኞቼና ፡ ፈረሰ ኞቼ ፡ ርዱኝ ፡ ብዬ ፡ ስጮህ ፡ ትተውኝ ፡ ሸሹ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሺ ፡ ቀስተኛ ፡ ከሺ ፡ ፈረሰኛ ፡ ከአሥር ፡ ሺ ፡ ዠግና ፡ አሞንን ፡ እመርጣ ለሁ ። »

የአምላኩ ፡ የአሞን ፡ መልስ ።

«ራምሲስ ፡ ሆይ ፡ ድምፆችህን ፡ ሰማሁ ፡ እጠገብህ ፡ ነው ፡ ያለሁት ፡ እኔ ፡ ፀሐዩ ፡ አባትህ ፡ ነኝ ፡ ክንዴ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ከብዙ ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ እኔ ፡ እሻልሃለሁ ። በመካከላቸው ፡ ስገባ ፡ የጠ ላቶችህ ፡ ፪ሺ፭፻ ፡ መንኰራኵሮች ፡ በፈረሶችህ ፡ (፩) ። ፊት ፡ ይሰ ባበራሉ ። የጠላቶችህ ፡ ልብ ፡ ይደክማል ፡ ክንዳቸው ፡ ይዝላል ፡ ቀስታቸውን ፡ ለመወርወር ፡ ጦራቸውንም ፡ ለመያዝ ፡ ልብ ፡ አያ ገኙም ። አዞ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እንደሚወረወር ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እወረ ውራቸዋለሁ ፡ አንዳቸው ፡ በአንዳቸው ፡ ላይ ፡ ተነባብረው ፡ ገደል ፡ ይገባሉ ፡ . . . . ከነሱ ፡ ውስጥ ፡ አንዳቸውም ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ እን ዲያዩ ፡ አልፈቅድም ፡ የወደቀም ፡ አይነሣም »

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የራምሲስ ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬ ፡ የጠላት፡ ጦር፡ ከቢ ፡ እየሠራ ፡ ሲመጣ፡ ይመለከት ፡ ነበርና ፡ በተራው ፡ ለጌታው፡ ለንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ አለው፡ «ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ለጋሱ ፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡ በጦርነት ፡ ቀን ፡ የግብፅ ፡ ጠባቂ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በጠላት ፡ ሰልፍ ፡ መካከል ፡ ብቻችንን ፡ ነን ፡ ውጊያህን ፡ አቁም ፡ (ሸሽተን) ፡ ነፍሳችንን ፡ እናድን ፡ ደጉ ፡ ጌታዬ ፡ ራምሲስ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንችላለን ።

(፩) የተቀመጠበትን ፡ ሠረገላ ፡ የሚስቡ ፡ ፈረሶችን ።



የመዋቲ ፡ ጕዞ ፡ በገሐነም ፡

ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ስድስት ፡ ተግባሮችን ፡ የሚያሳይ ፡ ሥዕል ፡ ነው። በመዠመሪያው ፡ የቀበሮ ፡ ገጽ ፡ ያለው ፡ አኑቢስ ፡ የሚሉት ፡ አምላክ ፡ የሞተውን ፡ ሰው ፡ እየመራ ፡ ልብ ፡ ወደሚመዘንበት ፡ ያደርሰዋል።፪ኛው፡አኑቢስ ፡ የሟቹ ፡ ልብ ፡ ንጹሕ ፡ ወይም ፡ ኃጢአተኛ ፡ መሆኑን ፡ በሚዛን ፡ ሲመዝን ። ሌላው ፡ የወፍ ፡ ገጽ ፡ ያለው ፡ ውጤቱን ፡ ሲጽፍ ። በሚዛኑ ፡ አጠገብ ፡ በላተኛው ፡ አውሬ ፡ ምናልባት ፡ የሟቹ፡ልብ ኃጢአተኛ ፡ እንደሆነ ፡ ለመብላት ፡ ውጤት ፡ የሚጽፈውን ፡ አምላክ ፡ እየተመለከተ ፡ ሲጠባበቅ።ሟቹ ፡ ንጹሕነቱ ፡ በሚዛን ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ያሞራ ፡ ገጽ ፡ ያለው ፡ ሆሩስ ፡ የሚባለው ፡ አምላክ ፡ ሟቹን ፡ እየመራ ፡ ምውታንን ፡ ሊያጸድቅ ፡ ወደሚችለው ፡ ኦሲሪስ ፡ ወደሚባለው ፡ የምውታን ፡ አምላክ ፡ ሲወስደው ። ኦሲሪስ ፡ ፪፡የሴት ፡ አማልክት ፡ በኋላው ፡ አቁም ፤ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ ዘውዱን ፡ ደፍቶ ፡ ይጠባበቃል ።

ኤ· ማሉ· ገፎ· ይስሐቅ ።



እንደ ፡ ገና ፡ እያስጨፈለቀ ፡ ወይም ፡ ጽሕፈቱን ፡ አንሥቶ ፡የራሱን፡ ስም ፡ እያሠራ ፡ አጻፈ ። ባለሟሎቹ ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃነ፡ ካህናት ፡ የርሱን ፡ ባለሟልነት ፡ ላለማጣት ፡ በዚህ ፡ ሥራው ፡ ሊወቅሱት ፡ የቻሉ ፡ አይመስልም ።

ዿኤሎች፡ እስኪጮሁ ፡ ድረስ፡ እየተደበደቡ ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ የሸክላ ፡ ጡብ ፡ ይሠሩ ፡ የነበረው ፡ ለዚሁ ፡ ለርሱ ፡ መኩሪያና ፡ መመኪያ ፡ ለሚሆነው ፡ ሐውልትና ፡ ለቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ለቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ሥራ ፡ ነበር ። እስራኤሎች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ፡ በርሱ፡ ዘመን ፡ የተገኙ ፡ ምርኮኞና ፡ ገባር ፡ ወዙን ፡ እያንጠባጠበ፡ በሥራ፡ ማስኗል ።

የራምሲስ ፡ የሚስቶቹና ፡ የቁባቶቹ ፡ ቍጥር ፡ በደንብ ፡ ቢታወቁና ፡ ቢመዘገቡ ፡ ከሰሎሞን ፡ ሳይበልጡ ፡ አይቀሩም ። ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ሦስቱ ፡ እኅቶቹ ፡ ሦስቱ ፡ የገዛ ፡ ልጆቹ ፡ ነበሩ ። ከነርሱም ፡ ፩፻፲፩ ፡ ወንድ ፡ ፶፩ ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። በዚያን ፡ ዘመን፡ ስለ፡ ጋብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ አልነበረም ። የእውነተኛው፡ እግዚአብሔር፡ ሕግና ፡ ትእዛዝ ፡ ገና ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ አልተሰማም ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ ንጉሥ ፡ በሚገዛው ፡ አገር ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ የፈቀደውን ፡ ለማድረግ ፡ ልቡ ፡ የተመኘውን ፡ ለመፈጸም ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ። በአስተዳደርና ፡ ቅጣት ፡ በመስጠት ፡ በዜጎቹ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ መብት ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ በሥጋ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ አንሶት ፡ በነፍስም ፡ ላይ ፡ ሥልጣን፡ለማግኘት ፡ ካህን ፡ መሆን ፡ይችላል። ከዚያ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ አምላክነት ፡ ደረጃ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ። አይገባህም ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ የተነፈሰ ፡ ቢገኝ ፡ መላሱ ፡ ይቆረጣል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ራምሲስ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ያስቈጠረ ፡ ከአማልክቱ ፡ጋር ፡ እንደኋደኛ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ በቀኙ ፡ የአሞንን ፡ በግራው ፡ የሙትን ፡ (ሴት ፡ አምላክ) ፡ እርሱ ፡ በመካከል ፡ ሦስተኛ ፡ ተቀምጦ ፡ ሦስቱ ፡ ተሠልሰው ፡ ክንድና ፡ ክንዳቸውን ፡ አቆላልፈው ፡ በዘመኑ ፡ የተሠራው ፡ ሐውልት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይታያል። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ራምሲስ ፡ በዘመኑ ፡ የንጉሥነት ፡ የአምላክነት ፡ ደረጃን ፡ ያጣመረ ፡ የአሞን ፡ ራ ፡ (የፀሐዩ ፡ የአሞን ፡) ልጅ ፡ ራሱ ፡

አምላክ ፡ ይባል ፡ ነበር ። በመዠመሪያው ፡ ዘመኑ ፡ መንግሥቱም ፡ ለአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሊቀ ፡ ካህን ፡ የሚሾም ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ጠፍቶ ፡ ስለነበረ ፡ የአሞን ፡ በዓል ፡ (ኦፔት) ፡ ባመቱ ፡ በ፪ኛው ፡ ወር ፡ በዋለበት ፡ ቀን ፡ የአሞን ፡ ምስል ፡ የተቀመጠበትን ፡ ከወርቅና ፡ ከጥሩ ፡ እንጨት ፡ የተሠራውን ፡ ቃሬዛ ፡ (መንበር) ፡ ሠላሳ፡ ቀሳውስት ፡ ተሸክመው ፡ ዙረት ፡ (ዑደት) ፡ ሲደረግ፡ ራምሲስ፡ ዳግማዊ ፡ በንጉሣዊ ፡ ልብሱ ፡ ላይ ፡ የሊቀ ፡ ካህኑን ፡ ልብስ ፡ (የድመት ፡ ወይም ፡ የነብር ፡ ቆዳ ) ፡ ደርቦ ፡ በዓሉን ፡ ይመራ ፡ ነበር ። ይኸንንም ፡ የሊቀ ፡ ካህንነት ፡ ሥራ ፡ ደርቦ ፡ በያዘበት ፡ ዘመን ፡ ስያሜው ፡ ቀዳማዊ ፡ የአሞን ፡ ነቢይ ፤ የደቡብና ፡ የሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ሕይወትን ፡ የተመላው ፡ ራምሲስ ፡ ዳግማዊ ፡ ይባላል ። በኋላ ፡ ግን ፡ ነቡኔፍ ፡ የሚባለው ፡ ተመርጦ ፡ የሊቀ ፡ ካህንነቱን ፡ ሹመት ፡ ወሰደ (፩) ።

ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ወሰን ፡ በሌለው ፡ ሥልጣንና ፡ ጌትነት ፡ ራምሲስ ፡ ዳግማዊ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ታላቁ ፡ ራምሲስ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከ፩ሺ፪፻፺፪ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፪፻፳፭ ፡ ዓመት ፡ (ከዚህ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ የሚያደርጉት ፡ ˆ ˜ ) ፡ ግብፃውያንን ፤ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ሊቢያን ፤ የከነዓንንና ፡ የሶርያን ፤ የሜሶፖታሚያን ፡ (ኬታ ፤ ሒቲቲ ፤ ታውሩ) ፡ አገሮች ፡ ፷፯ ዓመት ፡ ገዝቶ ፡ በተወለደ ፡ በ፹፰ ፡ ዓመቱ ፡ ሞተ ። ከርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ከልጆቹ ፡ አንዱ ፡ ከእኅቱ ፡ ከኢሲት ፡ ኖፍሬት ፡ የተወለደው ፡ ሜኔፕታህ ፡ ወይም ፡ መሬንፕታህ ፡ ( የፕታህ ፡ ወዳጅ ) ፡ የሚባለው ፡ ነገሠ ። በርሱም ፡ ዘመን ፡ ፳ኤሎች ፡ በሙሴና ፡ በአሮን፡ እየተመሩ፡ ግብፅን ፡ ለቀው ፡ አባቶቻቸው ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅና ፡ ያዕቆብ ፡ ወደነበሩበት ፡ ወደከነዓን ፡ መጡ (፪) ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ ላስታውስ ፡ የምፈልገው ፡ ብሉይ ፡ ኪዳን ፡ የግብፅን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉንም ፡ ፈርዖን ፡ እያለ ፡ ከመጥራት ፡ በቀር ፡ የየግል ፡ ስማቸውን ፡ አይለይም ። ግብፆቹ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ንጉሣቸውን ፡ «ፓር-እአ ፡ (ወይም) ፡ ፓራ-ኡኦ ፡ ይሉት ፡ ነበር ፡ ትር

(፩) LES GRANDS SACERDOCES D'AMON – GUSTAVE LEFEVRE ፩፻፯ ፡— ፩፻፹ ፡

(፪) ኦሪት ፡ ዘጸአት ፡ ም ፡ ፫—፲፬



ሮሜ—ሮይ ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡ የአሞን ፡ ሊቀ ፡ ካህን ፡ ( ሐውልቱ ፡ በካይሮ ፡ ሙዚወም ። ጉስታቭ ፡ ለፌቨር ። )

ንጊውም ፡ ትልቁ ፡ መንበር ፡ ወይም ፡ ትልቁ ፡ አዳራሽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ፓራ ፡ ኡኦ ፡ ፈርዖን ፡ ወደማለት ፡ አዘነበለ ፡ ምናልባት ፡ ይኸን ፡ የስየሙበት ፡ ምክንያት ፡ ንጉሡ ፡ የአምላክ ፡ ማኅደር ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ በበጥሊሞስ ፡ ፊደላደልፍ ፡ ዘመን ፡ ስብአ ፡ (ሰባ) ፡ የአይሁድ ፡ ሊቃውንት ፡ ብሉይን ፡ ወደግሪክ ፡ (ጽርዕ) ፡ ሲተረጉሙ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ (፪፻፹፫ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡) የግብፆችን ፡ ታሪክ ፡ የያዘው ፡ ፊደል ፡ ምሥጢሩ ፡ ስላልተገለጸ ፡ የየአንዳንዱን ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ ለማወቅ ፡ አልቻሉም ፡ ይሆናልና ፡ ነገሥታቱን ፡ ሁሉ ፡ ፈርዖን ፡ እያሉ ፡ ያለፉት ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ጊዜያችን ፡ ይኸው ፡ ደረሰ ።

ዛሬ ፡ ግን ፡ የአውሮፓ ፡ ትጉሃኑ ፡ ሊቃውንት ፡ የጥንትን ፡ የግብፅ ፡ ከተሞች ፡ እየቆፈሩ ፡ ከሐውልት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ሕንፃ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ፓፒሩስ ፡ ከሚባለው ፡ ከልጥ ፡ ብራና ፡ ላይ ፡ ያገኙትን ፡ ጽሑፍ ፡ ገልብጠው ፡ ተርጉመው ፡ ዘመንን ፡ ከዘመን ፡ አነጣጥረው ፡ ካመሳከሩ ፡ ወዲህ ።

፩ኛ ፡ ሙሴ ፡ ያደገበትና ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ የተባለበት ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ፈርዖን ፡ ብሎ ፡ በጠቅላላው ፡ ያለፈው ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ደንበኛ ፡ የመጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ራምሲስ ፡ (የፀሐይ ፡ ልጅ) ፡ መሆኑ ፡ ሊታወቅ ፡ ቻለ ።

፪ኛ ፡ ፳ኤሎችን ፡ አለቅም ፡ ብሎ ፡ ያስቸገረውንና ፡ በኋላ ፡ ለቀ ፡ አነሱን ፡ ሲያሳድድ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ሰጠመ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ፈርዖን ፡ እያለ ፡ ያለፈውን ፡ ዛሬ ፡ የዚህ ፡ ፈርዖን ፡ ደንበኛ ፡ ስሙ ፡ መኔፕታህ ፡ የፕታህ ፡ ወዳጅ ፡ ወይም ፡ መሬንፕታህ ፡ የፕታህ ፡ መቅደስ ፡ መባሉ ፡ ተገለጸ ። ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ስሙና ፡ የተግባር ፡ ስሙ ፡ ተደባልቆ ፡ ወይም ፡ ተያይዞ ፡ መሬኤን ፡ ፕታህ ፡ ሆቴፕ ፡ ሂማ ፡ (ከእውነት ፡ ጋር ፡ የተዋሐደው ፡ የፕታህ ፡ ወዳጅ) ፡ ይባላል ።

እርሱም ፡ የነዛበት ፡ ዘመን ፡ እንደኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ ከ፩ሺ፪፻፳፭ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፪፻፲፭ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ድረስ ፡ ነው ።



የራምሲስ ፡ ፪ኛና ፡ የመኔፕታህ ፡ የነጋሢነት ፡ የሐረግ ፡ ዘርፍ ፡ (ዲናስቲ) ፡ ፲፱ነኛ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ፳ኛው ፡ የሐረግ ፡ ዘርፍ ፡ እንደነርሱ ፡ የቴብ ፡ ዘር ፡ የሆነው ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ ፳፩ኛው ፡ የታኒትና ፡ የቴብ ፡ ድብልቅ ፡ ዘር ፡ ነው ። ፳፪ኛው ፡ የነጋሢ ፡ ዘር ፡ የሊቢያና ፡ የቡባስቲ ፡ ነገድ ፡ ተብሎ ፡ በየፈራረቃ ፡ ገዝቶ ፡ ፳፫ኛው ፡ የታኒት ፡ ዘር ፡ ፳፬ኛው ፡ የባይስ ፡ ዘር ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ በተራቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ፳፭ኛ ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ ሆነው ፡ ለገዥነት ፡ መግባታቸውን ፡ እነሆ ፡ ወደፊት ፡ እንመለከታለን ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይና ፡ ከግብፅ ፡ የኃያላን ፡ ፈርዖኖች ፡ መካከል ፡ ኢትዮጵያን ፡ የገዙትን ፡ የቱትሞሲስንና ፡ የራምሲስን ፡ አገዛዝ ፡ በዚሁ ፡ እናቆምና ፡ ወደኑብያ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ አባቶቻችን ፡ መልስን ፡ በተለምዶ ፡ በየመጽሐፉ ፡ የሚገኘውን ፡ የነገሥታቱን ፡ ስም ፡ የገዙበትን ፡ ዘመንና ፡ የነበሩበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚያመለክተውን ፡ ዝርዝር ፡ እንመልከት ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፱ ።

### ባገራችን ፡ የተለመደው ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝርና ፡ የዶክተር ፡ ራይዝነር ፡ ዝርዝር ፡ ልዩነት ።

#### ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ እስከ ፡ ባዜን ፡ ያሉት ።

| ስማቸውና ፡ ቍጥራቸው ። | የነገሡበት ፡ ዘመን ። | ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ |
|---|---|---|
| ፩ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ | ፴፩ | በ፩ሺ፲፫፡ ዓመት ፡ |
| ፪ ምኒልክ ፡ ፩ኛ ፡ ( ዳዊት ፡ ) | ፳፭ | ፱፻፹፮ |
| ፫ ሐንድዮን ፡ ---- | ፩ | ፱፻፶፮ |
| ፬ ሲራህ ፡ ፩ኛ ፡ ( ቶማይ ፡ ) | ፳፮ | ፱፻፶፮ |
| ፭ አሜንሆቴፕ ፡ ዘግዱር ፡ | ፶፩ | ፱፻፴--- |
| ፮ አክሱማይ ፡ ራሚሱ ፡ -- | ፳ | ፰፻፹፱ |

CITY - HALL LIBRARY of ADDIS ABABA

ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ እስከ ፡ ባዚን ፡ ያሉት ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ።

| ስማቸውና ፡ ቍራጥቸው ። | | የነገሡበት ፡ ዘመን | ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ |
|---|---|---|---|
| ፯ | ሲራህ ፡ ፩ኛ ፡ (አውስዮ ፡ ) | ፵፰ | ፳፻፳፱ ዓመት ፡ |
| ፰ | ተዋስያ ፡ ፩ኛ ፡ --- | ፳፩ | ፳፻፵፩ |
| ፱ | አብራልዮስ ፡ ፒንያንኪያ ፡ ፪ኛ ፡ | ፵፪ | ፳፻፲ --- |
| ፲ | አክሱማይ ፡ ወረደ ፡ ፀሐይ ፡ | ፳፫ | ፲፻፸፰ |
| ፲፩ | ካስሕታ ፡ ሐንድዮን ፡ ---- | ፲፫ | ፲፻፶፩ |
| ፲፪ | ሳባካ ፡ ፪ኛ ፡ ---- | ፲፪ | ፲፻፺፪ |
| ፲፫ | ኒካንታ ፡ ቅንዳኬ ፡ ፪ኛ ፡ -- | ፲ | ፲፻፹ --- |
| ፲፬ | ጻውዕ ፡ ቲርሐቅ ፡ (ወረደ ፡ ነጋሽ) | ፵፱ | ፲፻፳ --- |
| ፲፭ | አርድአሚን ፡ አውስያ ፡ --- | ፮ | ፲፻፸፩ |
| ፲፮ | ገሰዮ ፡ --- | ፮ | ሰዓት ፡ |
| ፲፯ | ኑአትሚአሙን ፡ ------ | ፬ | ፲፻፳፩ |
| ፲፰ | ቶማድዮን ፡ ፒያንኪያ ፡ ፫ኛ ፡ | ፲፪ | ፲፻፳፩ |
| ፲፱ | አሚንነአስሮ ፡ ፪ኛ ፡ --- | ፲፮ | ፲፻፺፱ |
| ፳ | ፒያንኪያ ፡ ፬ኛ ፡ (አውጥዮ ፡ ) | ፴፩ | ፲፻፵፫ |
| ፳፩ | ዙዋሬ ፡ ንብረት ፡ አስፑርታ ፡ - | ፺፩ | ፳፻፲፱ |
| ፳፪ | ሰይፋይ ፡ ሐርሲአተው ፡ | ፲፪ | ፳፻፲፰ |
| ፳፫ | ረምኃይ ፡ ናስቶሶናን ፡ | ፲፬ | ፳፻፺፮ |
| ፳፬ | ሐንዲው ፡ አብራ ፡ | ፲፩ | ፳፻፵፪ |
| ፳፭ | ሶፌልያ ፡ ነኪቦን ፡ | ፵፩ | ፳፻፳፩ |
| ፳፮ | አግልቡል ፡ ሰዌኮስ ፡ | ፳፩ | ፱፻፯ --- |
| ፳፯ | ጽስመረት ፡ (ወረደ ፡ ነጋሽ) ፡ | ፳፩ | ፱፻፸፱ |
| ፳፰ | አውሲያ ፡ ቡራኮስ ፡ --- | ፲፪ | ፱፻፺፰ |
| ፳፱ | ቀኒዝ ጽስሜስ ፡ - - - | ፲፫ | ፱፻፵፮ |
| ፴ | አጽራስ ፡ - - - | ፲ | ፱፻፳፫ |
| ፴፩ | ካስህታ ፡ ወልደ ፡ እንኑ ፡ | ፳ | ፱፻፲፫ |
| ፴፪ | ኤላልዮን ፡ ተእኒኪ ፡ | ፲ | ፫፻፶፫ |
| ፴፫ | አትሲርክአሚን ፡ ፫ኛ ፡ | ፲ | ፫፻፸፫ |
| ፴፬ | አትሲርክአሚን ፡ ፬ኛ ፡ | ፲ | ፫፻፷፫ |



ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ እስከ ፡ ባዚን ፡ ያሉት ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ።

| ስማቸውና ፡ ቍጥራቸው ፡ | | የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ | ከክርስቶስ ልደት ፡ በፊት ፡ |
|---|---|---|---|
| ፴፭ | ሐዲና ፡ - - - - | ፲ | ፫፻፳፫ ዓመት ፡ |
| ፴፮ | አትሲርክአሚን ፡ ፭ኛ ፡ | ፲ | ፫፻፶፫ |
| ፴፯ | አትሲርክአሚን ፡ ፮ኛ ፡ | ፲ | ፫፻፵፫ |
| ፴፰ | ኒካውላ ፡ ቅንዳኬ ፡ ፫ኛ ፡ | ፲ | ፫፻፴፫ |
| ፴፱ | ባስው ፡ - - - | ፮ | ፫፻፳፫ |
| ፵ | ኒካውሲስ ፡ ቅንዳኬ ፡ ፬ኛ ፡ | ፲ | ፫፻፲፯ |
| ፵፩ | አውጥጥ ፡ አራውራ ፡ | ፲ | ፫፻፯ |
| ፵፪ | አርካሚን ፡ ፪ኛ ፡ | ፲ | ፪፻፺፯ |
| ፵፫ | ክልዓስ ፡ ፪ኛ ፡ (ክሊትሮ) ፡ | ፲ | ፪፻፹፯ |
| ፵፬ | ዙዋሬ ፡ ንብረት ፡ | ፲፯ | ፪፻፸፯ |
| ፵፭ | ሰትዮ ፡ | ፲፬ | ፪፻፷ |
| ፵፮ | ሰይፋይ ፡ | ፲፫ | ፪፻፵፮ |
| ፵፯ | ኒኮሲስ ፡ ቅንዳኬ ፡ ፭ኛ ፡ | ፲ | ፪፻፴፫ |
| ፵፰ | ረምኃይ ፡ አርሚን ፡ ፭ኛ ፡ | ፲ | ፪፻፳፫ |
| ፵፱ | ፌልያ ፡ ሑርኔክሀት ፡ | ፲፭ | ፪፻፲፫ |
| ፶ | ሀንዲ ፡ አውኪራራ ፡ | ፳ | ፩፻፺፰ |
| ፶፩ | አግሀቡ ፡ ብሲሀራን ፡ | ፲ | ፩፻፸፰ |
| ፶፪ | ሡላይ ፡ ክዋውሚኑን ፡ | ፳ | ፩፻፷፰ |
| ፶፫ | መስልኒ ፡ ቁራርሚር ፡ | ፳ | ፩፻፵፰ |
| ፶፬ | ነግሣይ ፡ ብሲኒቲ ፡ | ፲ | ፩፻፴፰ |
| ፶፭ | ኤትቢኑካዊር ፡ | ፲ | ፩፻፳፰ |
| ፶፮ | ሰፌልያስ ፡ አብራሚን ፡ | ፳ | ፩፻፲፰ |
| ፶፯ | ሠናይ ፡ | ፲ | ፺፰ |
| ፶፰ | አወሲና ፡ ንግሥት ፡ | ፲፩ | ፹፰ |
| ፶፱ | ዳዊት ፡ ፪ኛ ፡ | ፲ | ፸፯ |
| ፷ | አግልቡስ ፡ | ፳ | ፷፯ |
| ፷፩ | በዋውል ፡ | ፲ | ፵፱ |
| ፷፪ | በረዋስ ፡ | ፲ | ፴፱ |

ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ እስከ ፡ ባዜን ፡ ያሉት ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ።

| ስማቸውና ፡ ቍጥራቸው ፡ | | የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ | ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ |
|---|---|---|---|
| ፷፫ | ዳኒዳድ ፡ | ፲ | ፴፱ ዓመት ፡ |
| ፷፬ | አሞይ ፡ መሐሲ ፡ | ፭ | ፳፱ |
| ፷፭ | ኒኮትሪስ ፡ ሣንደኬ ፡ ንግሥት ፡ ፪ኛ ፡ | ፲ | ፳፬ |
| ፷፮ | ናልኪ ፡ | ፪ | ፲፬ |
| ፷፯ | ሉዛይ ፡ | ፬ | ፲ |
| ፷፰ | ባዜን ፡ | ፰ | ፰ |

በፊተኞቹ ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ በዚህ ፡ በአሁኑም ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ዠምሮ ፡ በባዜን ፡ በሚጨርሰው ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ በስማቸውና ፡ በገዙበት ፡ ዘመን ፡ ልክ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ እምነት ፡ ሊጣልበት ፡ አይቻልም ። ለምሳሌ ፡ በ፩ኛውና ፡ በ፪ኛው ፡ በ፲ኛው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ምኒልክ ፡ አክሱማይ ፡ ወረደ ፡ ፀሐይ ፡ የሚባሉ ፡ ነገሥታት ፡ በኑብያ ፡ በተለይ ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሉም ። ምናልባት ፡ የወዲያኛው ፡ የሳባና ፡ የወዲህኛው ፡ የኖብያ ፡ ነገሥታት ፡ ተደባልቀው ፡ ተጽፈው ፡ ይሆናል ። እንደዚሁም ፡ በ፪ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከትነውን ፡ አብራልዮስ ፡ ፒያንኪ ፡ የሚባለውን ፡ የነገሠበትን ፡ ዘመን ፡ ይህ ፡ ዝርዝር ፡ ፰፻፲ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሲያደርገው ፡ የዚህን ፡ ንጉሥ ፡ ታሪክ ፡ ሐውልቱንም ፡ የፓፒሩሱንም ፡ (የብራናውንም) ፡ ጽሑፍ ፡ በቅርብ ፡ እየመረመሩ ፡ የጻፉት ፡ እነማሪዬት ፡ እነሩገ ፡ የቀሩትም ፡ ሁሉ ፡ ፷፯ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ወደታች ፡ ዝቅ ፡ ያደርጉታል ።

ሬዝነርና ፡ (REISNER) ሌፕሲዉስ ፡ (LEPSIUS) ከየሐውልቱና ፡ ከየብራናው ፡ ጽሑፍ ፡ መርምረው ፡ ከካስህታ ፡ ጀምረው ፡ የሚስጡት ፡ ዝርዝር ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።



ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ እስከ ፡ ባዜን ፡ ያሉት ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ።

| ስማቸውና ፡ ቍጥራቸው ፡ | | የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ | ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ካስህታ ፡ | » | ፰፻፱ ዓመት ፡ |
| ፪ | ፒያንኪ ፡ | » | ፰፻፵፪ |
| ፫ | ሻባካ ፡ (ሳባካ ፡ ሳባቆን) ፡ | » | ፰፻፲ |
| ፬ | ሻባታካ ፡ | » | ፰፻ |
| ፭ | ታሃርቅ ፡ (ቲሂራቅ ፡ ቲርሃቅ) ፡ | » | ፯፻፹፰ |
| ፮ | ታኑታሜን ፡ | » | ፯፻፷፫ |
| ፯ | አትሌርሳ ፡ | » | ፯፻፶፫ |
| ፰ | ሴንካሜኔስኬን ፡ | » | ፯፻፵፫ |
| ፱ | አንላሜን ፡ | » | ፯፻፳፫ |
| ፲ | አስፔልታ ፡ | » | ፮፻፲፫ |
| ፲፩ | አንትሌክ ፡ | » | ፮፻፷፰ |
| ፲፪ | ማሌኔኬን ፡ | » | ፮፻፶፫ |
| ፲፫ | ኤልማይ ፡ | » | ፮፻፴፰ |
| ፲፬ | ኔታክላታታሜን ፡ | » | ፮፻፴፫ |
| ፲፭ | ካርጋሜን ፡ | » | ፮፻፲፫ |
| ፲፮ | አስታጋርካሜን ፡ | » | ፮፻፫ |
| ፲፯ | አሻሴህራቅ ፡ | » | ፭፻፹፰ |
| ፲፰ | ናሳክህማት ፡ | » | ፭፻፶፰ |
| ፲፱ | ማሌዊባሜን ፡ | » | ፭፻፶፫ |
| ፳ | ታልክሃርሜን ፡ | » | ፭፻፳፫ |
| ፳፩ | ሄሬኑታርካሜን ፡ | » | ፭፻፲፰ |
| ፳፪ | ባግካክሬን ፡ | » | ፬፻፲፰ |
| ፳፫ | ሄርሳቴፍ ፡ | » | ፬፻፴፯ |
| ፳፬ | ፓንክሃሌር ፡ | » | ፬፻፳፯ |
| ፳፭ | አክሃራታን ፡ | » | ፬፻፺፪ |
| ፳፮ | ናስታሴን ፡ | » | ፬፻፴፰ (፩) |

(፩) A HISTORY OF ETHIOPIA — WAL. BUDGE
አንደኛ ፡ ቮሊዩም ፡ ገጽ ፡ ፲፭ ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እንፈይዝነር ፡ የሠሩት ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝ ርና ፡ በተለምዶ ፡ ባገራችን ፡ እስካሁን ፡ የሚደረደረው ፡ ዝርዝር ፡ በዘመኑም ፡ በስሙም ፡ ስለሚለያይ ፡ ዘመኑ ፡ እጅግ ፡ የራቀው ፡ የነ ዚህ ፡ የነገሥታት ፡ ስምና ፡ ዝርዝር ፡ ምናልባት ፡ ሰፊ ፡ ጊዜ ፡ ተገ ኝቶ ፡ እስኪጣራ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ እንለፈውና ፡ ከነዚሁ፡ውስጥ፡ ያንዳንዶቹን ፡ ነገሥታት ፡ በተለይ ፡ ግብፅን ፡ የገዙትን ፡ አጭጭር፡ ታሪክ ፡ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ከፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ።

ከፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እንዳሉ ፡ ዝርዝሩ ፡ ያሳየናል ። ንግሥተ ፡ ሳባንና ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክንም ፡ እዚያው ፡ ውስጥ ፡ እንዲያውም ፡ የዝርዝሩ ፡ መዠመሪያ ፡ አድርጓ ቸዋል ። ንግሥተ ፡ ሳባንም ፡ ከፊተኛው ፡ ተከታትሎ ፡ ሲመጣ ፡ ፶፪ኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ አድርጓታል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንግ ሥተ ፡ ሳባና ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ፩ሺ፱፻ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ ፳፩ኛው ፡ የታኒትና ፡ የቴባውያን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናሲቲ) ፡ የሚባሉት ፡ ( ስሜ ንዴዝ ፡ ፕሱሴኒስ ፡ ፩ኛውና ፡ ፪ኛው ፡ አሜን ፡ ሆቴፕ ፡ ፫ኛውና ፡ ፬ኛው ) ፡ የሚገዙበት ፡ ዘመን ፡ ነው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጨርሶ ፡ የግብፅ ፡ ገዢነት ፡ የተነቀለ ፡ አይመስልም ። በፓለስቲን ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሰሎሞን ፡ ከነዚሀ ፡ አላይ ፡ ከጠቀስና ቸው ፡ የግብፅ ፡ ነገሥታት ፡ ያንዱን ፡ የፕሱሴኔስን ፡ (ፓኒትፓሴብ ካኒት ) ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ታላቁን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚሠራበት ፡ መንግሥቱን ፡ በገናንነት ፡ የሚያስተዳድ ርበት ፡ ዘመን ፡ ነው ።

በዚህ ፡ በ፲ኛውና ፡ በ፱ኛው ፡ በ፰ኛውም ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክ ርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኋላ ፡ የገነነውና ፡ አሁን ፡ ገናንነቱን ፡ በሐውልቱና ፡ በጽሑፉ ፡ የምናውቀው ፡ የአክ ሱም ፡ መንግሥት ፡ እስካሁን ፡ አለመነሣቱን ፡ የሰባውያንና ፡ የአክ



ሱምን ፡ ታሪክ ፡ የመረመሩት ፡ ሊቃውንት ፡ ሁሉ ፡ አረጋግጠዋል። ከአትባራ ፡ ወንዝ ፡ ወዲያ ፡ በኑብያ ፡ ግን ፡ እነዚያው ፡ በኢትዮጵያ ዊነት ፡ የምንጠራቸው ፡ መዠመሪያ ፡ ነፃ ፡ ሆነው ፡ በኋላ ፡ እነቱ ትሞሲስ ፡ ቀጥሎም ፡ እነራምሲስ ፡ ፪ኛ ፡ ካስገበርዋቸው ፡ ወዲህ ፡ አሁንም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከግብፅ፡ እየተነጠሉ፡ አንዳንድ፡ ጊዜም ፡ እነሱ ፡ እያጠቁ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በግብፃውያኑ፡ እየተገዙ፡ ኑሯ ቸውን ፡ ይቀጥላሉ ። የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ከፊተኛው፡ ዝርዝር፡ ተከታትሎ ፡ ከመጣውና ፡ ባሁኑ ፡ ዝርዝር ፡ ከሚታዩት ፡ ውስጥ ፡ ዋነኞቹ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። ከነርሱም ፡ አብዛኞቹ ፡ በፊት ፡ በቴብና ፡ (ካርናቅ) ፡ በናፓታ ፡ ለሚገኘው፡ ለአሞን ፡ መቅደስ ፡ የቀ ሳውስት ፡ አለቃ ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ አንዳንዶቹ ፡ የኛ ፡ ሊቃ ውንት ፡ እንደሚሉት ፡ በአሪትና ፡ በእግዚአብሔር ፡ የሚያመልኩ ፡ አልነበሩም ። በዝርዝር ፡ ላይ ፡ ፺፫ኛ ፡ ሆኖ ፡ የምንመለከተው ፡ ሐር፡ ሆር ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ ከግብፅ ፡ ፈርዖን ፡ ከራምሲስ ፡ አራተኛ ፡ ሴት ፡ ልጁና ፡ አሜን ፡ ሆቴብ ፡ ከተባለው ፡ ከአሞን ፡ ካህን ፡ የተ ወለደ ፡ ነው ። እርሱም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከግብፅ ፡ ንጉሥና ፡ ከኢ ትዮጵያው ፡ ካህን ፡ በመወለዱ ፡ ሁለቱን፡ አገሮች፡ ደርቦ ፡ እንደገዛ ፡ ይተረካል ። ስሙ ፡ባንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ሐር ፡ ሆር ፡ ሲል ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አሜንሲ ፡ ሐር ፡ ሆር ፡ ወይም ፡ ሜይ ፡ አሙ ሐር ፡ ሆር ፡ ይባላል ። ትርጓሜው ፡ ካህኑ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ የአ ሞን ፡ ወዳጅ ፡ ማለት ፡ ነው (፩) ። እርሱም ፡ እላይ ፡ እንዳመለከት ነው ፡ የነራምሲስ ፡ ወገኖች ፡ ከታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ድካምና ፡ ውድ ቀት ፡ሲሰማቸው ፡ የአሞን ፡ ሊቀ ፡ ካህንነቱና ፡ መንፈሳዊ፡መሪነቱ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የራምሲስ ፡ ተወላጅነቱ ፡ ስለረዳው ፡ ታሕታይንና ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ ደርቦ ፡ ለመግዛት ፡ ቻለ ። የገዛበት ፡ ዘመን ፡ ፲፮ ዓመት ፡ የነበረበት ፡ ዘመን ፡ ፩ሺ ፡ ፩መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ መሆኑ ፡ ባንዳንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ይጠቀሳል ።

የሐር ፡ ሆር ፡ ተከታዩ ፡ ፒያንኪያ ፡ ፩ኛ ፡ የተባለውና ፡ የቅ ርብ ፡ ተከታዮቹ ፡ ናፓታን ፡ እንጂ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ መግዛታ

(፩) J. MORIE — HIST. D'ETHIOPIE ፩ኛ ፡ ቮሊዩም ፡ ገጽ ፡ ፻፲፰—፻፲፱ ።

ቸው ፡ እጽሐፍ ፡ ላይ ፡ አይገኝም ። ክርሱ ፡ ወዲህ ፡ አትቤርክ ፡ አሜን ፡ በዝርዝሩ ፡ ላይ ፡ ቊጥር ፡ ፫ ፡ ሐንድዮ ፡ የሚለው ፡ ይገኛል ። ካሰፉት ፡ ነገሥታትና ፡ ከሔር ፡ ሆር ፡ ወዲህ ፡ በመ ፡ ጥርነት ፡ ያለው ፡ ይኸው ፡ አስተርከ ፡ አሜን ፡ ሐንድዮ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ንጉሥነት ፡ ብዙ ፡ አከራካሪ ፡ ነገር ፡ አለ ። የኛዎቹ ፡ የቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ልጅና ፡ አሪታዊ ፡ ያደርጉታል ። አሪታዊ ፡ አለመሆኑ ፡ ግን ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ሮከ ፡ አሜን ፡ እርሱም ፡ የአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አገልጋይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሙሉና ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሚያምን ፡ አልነበረም ። አስተርከ ፡ አሜን ፡ ማለትም ፡ ስሙ ፡ የአሞን ፡ አገልጋይ ፡ ወይም ፡ ወዳጅ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ይህ ፡ አስተርከ ፡ አሜን ፡ ወደፓለስቲን ፡ አገር ፡ ዘልቆ ፡ ይሁዳንና ፡ እስራኤልን ፡ ሰማርያን ፡ የወረረው ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ። ዚራክ ፡ ማለትም ፡ የግብፅ ፡ ፈርዖን ፡ አቦርከሆን ፡ ፪ኛ ፡ የተባለው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ የመላ ፡ ክር ክር ፡ አለ ። ከዘመኑ ፡ ርቀትና ፡ ከማስረጃ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ እስካሁንም ፡ ውሳኔ ፡ አላገኘም ። ዚራክ ፡ የተባለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ በ፲ኛው ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ በ፫፻ ሠረገላ ፡ የተቀመጡ ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ ግብፅን ፡ እንደ ፡ ወረረ ፡ ከዚያም ፡ የግብፅን ፡ ሀብት ፡ ጨምሮ ፡ ወደ ፡ ፓለስቲን ፡ ዘምቶ ፡ መሸነፉ ፡ ተጽፏል ። ፪ኛ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፬ ፡ ቊጥር ፡ ፱ ፡ እስከ ፡ ፲፫ ፡ ተመልከት ።

ከአስተርከ ፡ አሚን ፡ ወይም ፡ ከዜራክ ፡ ቀጥሎ ፡ አሜን ፡ ሆቴፕ ፡ ነገሠ ። እርሱም ፡ በዝርዝሩ ፡ ፭ኛ ፡ ቊጥር ፡ የተመለከትነው ፡ ነው ። ቶማ ፡ ጽዮንም ፡ ይሉታል ፡ ቶማ ፡ ጽዮን ፡ ማለትም ፡ የጽዮን ፡ ፀሐይ ፡ ወይም ፡ የጽዮን ፡ ንጉሥ ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ አሪታዊ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዋነኛው ፡ በሙ ፡ አሜን ፡ ሆቴፕ ፡ ስለሆነ ፤ እንደዚያው ፡ እንደአባቶቹ ፡ እንደ ፡ ናፓታ ፡ የቀብ ውስት ፡ ነገሥታት ፡ የአሞን ፡ አገልጋይና ፡ አማኝ ፡ ይመስላል ። አን ዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አሜን ፡ ሆቴፕ ፡ ሜይ ፡ አሙን ፡ ይባላል ፡ በግብፃው ያን ፡ ጥንታዊ ፡ ቋንቋ ፡ አሚን ፡ ሆቴብ ፡ ማለት ፡ ትርጓሜው ፡ የአሞን ፡ ፍቅረኛ ፡ ማለት ፡ ነው ፡



የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ራሚሱ ፡ ወይም ፡ ዘግዱር ፡ እንደግማሾቹ ፡ አክሱማይ ፡ የተባለው ፡ ነገሠ ፤ በቀን ፡ ብዛት ፡ ራሚሱ ፡ ተባለ ፡ እንጂ ፡ በሙ ፡ እንደግብፆቹ ፡ ነገሥታት ፡ ራምሲስ ፡ የፀሐይ ፡ ልጅ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፤ ዘግዱር ፡ ሲል ፡ ግዕዝኛውን ፡ የግዱር ፡ በሰሚመስል ፡ ወደ ፡ ሳባዊነት ፡ የሚጠጋ ፡ ይመስላል ። ዘግዱር ፡ ትርጓሜው ፡ ገፊ ፡ ማለት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በተወለደ ፡ በወሩ ፡ እናቱ ፡ በሰሞተችበት ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። እርሱም ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ገዝቶ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በርሱ ፡ ምትክ ፡ አውሰዮ ፡ ነገሠ ፡ እርሱም ፡ በዝርዝሩ ፡ ላይ ፡ በ፯ኛ ፡ ቊጥር ፡ የሚታየው ፡ ነው ። በሙ ፡ ሴራህ ፡ ፩ኛ ፡ አስተርከ ፡ አሜን ፡ ፩ኛ ፡ ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ወረደ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ዜራክ ፡ ወይም ፡ ሴራህ ፡ ፩ኛ ፡ ወደ ፡ ፓለስቲን ፡ አገር ፡ ዘምቶ ፡ የተሸነፈ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አልቀው ፡ ነበርና ፡ የነርሱን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ወደ ፡ ፓለስቲን ፡ ሄዶ ፡ ከዮራም ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ አገሩን ፡ አጠፋፍቶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሷል ፡ ይላሉ ። ፪ኛ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ፳፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፮-፲፯ ፡ ቊጥር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ የሚለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አጠገብ ፡ ያሉትን ፡ ዓረቦች ፡ አስነሣበት ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተዋግተው ፡ አሸነፉት ፡ አይልም ። ከአውሰዮ ፡ ወይም ፡ ከሴራህ ፡ ፪ኛ ፡ ቀጥሎ ፡ ሳባካ ፡ ፩ኛ ፡ ( ሻባካ - ሰበቆን ፡) ነገሠ ። የሳባካ ፡ ፩ኛ ፡ ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ እንደ ፡ ሴራህ ፡ ፪ኛ ፡ ወረደ ፡ ፀሐይ ፡ መሆኑን ፡ ትውልዱም ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ አትራምን ፡ አትራም ፡ አብራልዮስን ፡ ሲወልድ ፡ አብራልዮስ ፡ ክአሞን ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ዘር ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አግብቶ ፡ ሳባካን ፡ ወለደ ፡ ይላሉ ። ከዚሁ ፡ አያይዘው ፡ ሳባካ ፡ በዘመኑ ፡ መንግሥቱ ፡ የአሪትን ፡ ካህናትና ፡ የአሞንን ፡ ካህናት ፡ አከራክሮ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ አሪታዊነቱን ፡ ከዶ ፡ ወደ ፡ ናቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ አምልኮ ፡ ዞር ፡ እንዲያን ፡ እንዳጠቃቸው ፡ በሙሴ ፡ ዣን ፡ ሞሪዮ ፡ መጽሐፍ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ የግብፅና ፡ የቴብ ፡ የናፓታና ፡ የመርዌ ፡ ታሪክ ፡ በየበኩሉ ፡ ተጽፎ ፡ በተገኘው ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ ከሔር ፡ ሆር ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ድረስ ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሪታዊ ፡ መንግሥሥ ፡ አልተጻፈም ፡ ወይም ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ የተጻፈ ፡ አላየሁም ።



ድል ፡ አድራጊው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ፒያንኪ ፡ ሜሪያሚን ፡ ሥዕሉ ፡ በዘመኑ ፡ አለባበስና ፡ አቅዋም ፡ በ፳ኛው ፡ ሠዓሊ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ተክሌ ፡ እጅ ፡ የተሳለ ።



እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታት ፡ መቀመጫቸውን ፡ በናፓታ ፡ በርታ ፡ ያሉት ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ በቴብ ፡ አድርገው ፡ ከግብፆቹ ፡ እየተዋጉም ፡ እየታረቁም ፡ እየተጋቡም ፡ እምነታቸውንም ፡ እንደግብፃውያኑ ፡ በአሞንና ፡ በሌሎች ፡ የጣዖት ፡ አማልክት ፡ አድርገው ፡ እንዲያውም ፡ አማኝ ፡ ከመሆን ፡ አልፈው ፡ ራሳቸው ፡ ሚስቶችና ፡ እኅቶቻቸው ፡ ጭምር ፡ የጣዖታቱ ፡ የነአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የቀሳውስት ፡ አለቃ ፡ እየሆኑ ፡ ስለሚያገለግሉ ፡ የታሪኩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ ቀሳውስቱ ፡ ነገሥታት ፡ እያለ ፡ ይጠራቸዋል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ የመንፈሳዊና ፡ የሥጋዊ ፡ ሥራ ፡ ደርበው ፡ በመሥራትና ፡ እያደሩ ፡ በመግነን ፡ የግብፅን ፡ ግዛት ፡ ከአገራቸው ፡ ከናፓታ ፡ ከነቀሉ ፡ ወዲህ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ እየወረሩ ፡ ሲያስቸግሩ ፡ ቆይተው ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ የሲራህ ፡ ፪ኛ ፡ ልጁ ፡ ፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ የሚባለው ፡ ፈጽሞ ፡ ላዕላይና ፡ ታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ ወርሮ ፡ እንደገዛትና ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ) ፡ ለዋና ፡ ፈርዖንነት ፡ እንዳበቃቸው ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ ከደንበኛ ፡ የሐውልት ፡ ታሪኩ ፡ ተተርጕሞ ፡ ከወጣው ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ ወደአማርኛ ፡ የተረጐምሁትን ፡ እንመለከታለን ።

## የኢትዮጵያውያን ፡ ገዥነት ፡ በግብፅ ፡ ላይ ።

### ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

### ፒያንኪ ፡ ሜሪአሙን ፡ በተፍነክታ ፡ ላይ ፡ ያገኘው ፡ ድል ፡ አድራጊነት ።

የግብፅ ፡ ግዛት ፡ ከመነቀሉ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በናፓታ ፡ ከተማ ፡ ኢትዮጵያውያኑ ፡ ማየል ፡ ጀምረው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይልቁንም ፡ በአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የካህንነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማዕርግ ፡ በመያዛቸው ፡ በግብፆቹም ፡ በኢትዮጵያውያኖቹም ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣንም ፡ ክብርም ፡ እንደነበራቸው ፡ ግብፆች ፡ ሲለቁ ፡ የመንግሥታቸውን ፡ መደብ ፡ በዚሁ ፡ በናፓታ ፡ እንዳለ ፡ አድርገው ፡ ከሔር ፡ ሆር ፡ ከቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥና ፡ ከፒያንኪ ፡ ፩ኛ ፡ የወረዱት ፡ እነርክ



ንምሩድ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ፈረሱን ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ጸናጽል ፡ እንደያዘ ፡ ወደ ፡ ድል፡ አድራጊው ፡ ወደ ፡ ፒያንኪ ፡ ሲቀርብ ፡ (ገር· ገር ክሌር ፡) ከጭንቅላቱ ፡ በላይ ፡ በክበቡ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ አራት ፡ ፊደሎች ፡ በጥንቱ ፡ ፊደል ፡ (ሂዬሮግሊፍ ፡) የተጻፈው ፡ የንምሩድ · ስም ፡ ነው ። (ገብርኤል ፡ ሐኖቶ ።)



አሚን ፡ እነአስተርክ ፡ አሚን ፡ እንሜአን ፡ ሆቴፕ ፡ እነሴራህ፡ ሲገዙ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ የኢትዮጵያውያኖች ፡ ገዥነት ፡ ለፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ ደረሰ ። እርሱም ፡ በንጉሥነቱ ፡ ላይ ፡ በአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሊቀ ፡ ካህናትነት ፡ ደረጃ ፡ ስለያዘ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ፡ መጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ፒያንኪ ፡ ወይም ፡ ፒያንኪያ ፡ ሲሆን ፤ በዚህ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ክህናት ፡ ስም ፡ ሜሪአሙን ፡ «የሕይወት ፡ መቅደስ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ካህኑ ፡ ንጉሥ» ፡ ይባላል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ፒያንኪ ፡ ሜይ ፡ አሙን ፡ «ፒያንኪ ፡ ፍቁሩ ፡ ለአሞን» ፡ ይባላል ። በዘመኑ ፡ በግብፃዊ ፡ አጻጻፍና ፡ ኢትዮጵያውያኖችም ፡ በሚሠሩበት ፡ በዘመኑ ፡ ፊደል ፡ (ሂዬሮግሊፍ) ፡ ስሙ ፡ ሲጻፍ ፡ አንድ ፡ የበርጩማ ፡ አንድ ፡ የመስቀል ፡ (ሕይወት) ፡ ሁለት ፡ የቅጠል ፡ ምልክት ፡ ተደርጎ ፡ እንደዘመኑ ፡ ተጽፎ ፡ ሲነበብ፡ ፒያንኪ ፡ ተብሎ ፡ ይነበባል ፤ በኛ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትና ፤ በዝርዝሩ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ ፒያንኪያ፡ ወይም ፡ ሕዝባይ ፡ ፩ ፡ አንዱም ፡ አብራልዮስ ፡ ሲለው ፡ እናያለን ።

እርሱም ፡ የሴራህ ፡ ፪ኛ ፡ (አውስዮ) ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ሃይማኖቱ ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ በአሞን ፡ ጣዖት ፡ መሆኑን ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው እንመለከታለን ፡ በርሱና ፡ በአምላኩ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ፍቅር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደነበረ ፡ ወደፊት ፡ ከምናገኘው ፡ ጽሑፍ ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ሲያመሰግነው ፡ በተናደደ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ሲምልበት ፡ እንረዳለን ። ፒያንኪ ፡ የራሱን ፡ መንግሥት ፡ በሰላም ፡ በሚመራበት ፡ ጊዜ ፡ በኛ ፡ በጕንደር ፡ መንግሥታችን ፡ ጊዜ ፡ እንደደረሰው ፡ ግብፆቹ ፡ ባገራቸው ፡ ብቻ ፡ ተሰብስበው ፡ በአንድ ፡ ፈርዖን ፡ መገዛት ፡ እንኳን ፡ አቅቷቸው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ከደልታ ፡ ከሳይስ ፡ ከየአውራጃው ፡ ብዙ ፡ መሳፍንት ፡ ፈርዖንነት ፡ ለመያዝ ፡ እየተነሡ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ በመጨረሻ ፡ ተፍነክታ ፡ ወይም ፡ ተውኔክህት ፡ የሚባለው ፡ የሳይሱ ፡ መስፍን ፡ የቀሩትን ፡ መሳፍንት ፡ አሸንፎ ፡ ፈርዖን ፡ መሆኑን ፡ አውጆ ፡ ተቀመጠ ።

ከመሳፍንቶቹ ፡ ይበልጦቹ ፡ ለተፍነክታ ፡ ገብረው ፡ ሲቀመጡ፡ አንድ ፡ አንዶቹ ፡ የተፍኔክታን ፡ ገዥነት ፡ አንቀበልም ፡ ብለው ፡



ቀ፣ ፯. መ።

ኢትዮጵያን ከግብፅ ከመካከለኛው ምሥራቅና ከዓረብ አገሮች ጋር የሚያሳይ (በስኬል ያልተሠራ ።)



እምቢ ፡ ብለው ፡ ለጦርነት ፡ በተሰለፉ ፡ ጊዜ ፡ መጥቶ ፡ ወይም ፡ ጦር ፡ ልኮ ፡ እንዲረዳቸው ፡ ወደ ፡ ፒያንኪ ፡ ላኩ ፡ ይባላል ። ምናል ባት ፡ እርሱም ፡ ከልመናው ፡ በቀር ፡ ግብፅን ፡ ለመግዛት ፡ ምኞት ፡ ሳይኖረው ፡ የቀረ ፡ አይመስልምና ፡ የታውኔከት ፡ ጦር ፡ ከታችኛው፡ ግብፅ ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ ግብፅ ፡ የቀረውን ፡ አገር ፡ ለማሳመን ፡ ሲመጣ ፡ ፒያንኪም ፡ ፑአርማና ፡ ኡአሜሪስኪን ፡ በሚባሉ ፤ በሁለት የጦር ፡ አለቆቹ ፡ የሚታዘዝ ፡ ጦር ፡ ከናፓታ ፡ ወደ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ልኮ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ በከተማው ፡ ተቀምጦ ፡ የቀረውን ፡ ዋናውን ፡ ጦር ፡ ያደራጅ ፡ ነበር ።

ፒያንኪ ፡ እንደምን ፡ ግብፅን ፡ ድል ፡ እንደአደረገ ፡ የሚያስረዳው ፡ በየታሪኩ ፡ ከተጻፈው ፡ በቀር ፡ ጥንት ፡ ናፓታ ፡ ዛሬ ፡ ጃበል ፡ ባርካ ፡ በሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ራሱ ፡ ባሠራው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ። ሙሴ ፡ ማሪዬት ፡ የሐውልቱን ፡ መጠን፡ ለከተው ፡ ጽሑፉን ፡ እንደ ፡ ገለበጡትና ፡ ሙሴ ፡ ደ ሩገና ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ እንደተረጐሙት ፡ የሐውልቱ ፡ ርዝመት ፡ አንድ ፡ ሜትር ፡ ከሰማንያ ፡ ስፋቱ ፡ አንድ ፡ ሜትር ፡ ከሰማንያ ፡ አራት ፤ ውፍረቱ ፡ አርባ ፡ ሦስት ፡ ሳንቲም ፡ ነው ። በላዩ ፡ በሁለቱ ፡ ፊት ፡ ከላይ ፡ በኩል ፡ በቱ-አብ ፡ ( ንጹሕ ፡ ተራራ ) ፡ የሚቀመጠው ፡ የዓለም ፡ ዙፋን ፡ ጌታ ፡ የአሞን ፡—ራ ፤ በፊቱ ፡ የንጉሡ ፡ የፒያንኪ ፡ በኋላው ፡ የሐትሆር ፡ (ሴት ፡ አምላኪት) ፡ ምስል ፤ በፒያንኪ ፡ ፊት ፡ ወደፊት ፤ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲያስገብራቸው ፡ የምናየው ፡ ፫ ፡ የግብፅ፡ ነገሥታት ፡ ተንበርክከው ፡ ሲሰግዱለት ፡ ነምሩድ ፡ የሚባለው ፡ ግን ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ለግብር ፡ ያመጣለትን ፡ የራሱን ፡ ፈረስ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ጸናጽል ፡ እንደያዘ ፡ አማላጁን ፡ ሚስቱን ፡ ከፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ይታያል ። ከነዚህ ፡ ሥዕሎች ፡ በታች ፡ በሐውልቱ ፡ በሁለቱም ፡ ፊት ፡ ላይ  አንድ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ መሥመሮች ፡ ላይ ፡ በዚያው ፡ በጥንቱ ፡ የግብፃውያን ፡ አጻጻፍ ፡ ( ሂዩሮግሊፍ ) ፡ የተጻፈውን ፡ ታሪኩን ፡ ይዘረዝራል ።

በዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያው ፡ መሥመር፡ ላይ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ «ዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ የሆነው ፡ ፒያንኪ ፡ ሜሪአሚን ፡ የታሕታይና ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ በ፳፩ኛው ፡ ዓመት ፡

በቶት ፡ ወር ፡ ግርማዊነቱ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፤ ካባቶቼ ፡ ይበልጥ ፡ የሠ
ራሁትን ፡ ስሙ ፡ በቱም ፡ (በማታ ፡ ፀሐይ ፡ የሚመስል ፡ አምላክ) ፡
አምሳል ፡ ከአማልክት ፡ የሠረፀሁ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ» ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ «ከናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ለንጉሥነት ፡ የተመ
ረጠ ፡ . . . መሳፍንት ፡ ያከበሩት ፡ በአማልክት ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡
ራሱ ፡ ደግ ፡ አምላክ ፤ የፀሐይ ፡ ልጅ ፡ ፀሐይ ፡ በገዛ ፡ እጆቹ ፡ የፈጠ
ረው ፡ ፒያንኪ—ሜሪአሚን» ፡ የሚለው ፡ ይገኛል ።

ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ በቴብ ፡ ያሉት ፡ የጦር ፡
አለቆቹ፡ የላኩበት ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይቀጥላል ፡ «የምዕራብ ፡ መስ
ፍን፤የኑተር ፡ ከተማ ፡ አገረ ፡ ገዥ፡ ታፍኒቅህት፡ መምፊስን፡ ሐፒን ፡
ካሐስቢን፡ (ልዩ ፡ ልዩ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ከተሞች) ፡ ያዘ። ቍጥር፡
የሌለው ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይጓዛል ፤ በየአውራጃው ፡
ያሉት ፡ ነገሥታትና ፡ መሳፍንት ፡ የከተማ ፤ አገረ ፡ ገዥዎችና ፡
የጦር ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ እንደውሻ ፡ ወደቁ ። በም
ሥራቅም ፡ በምዕራብም ፡ ያሉት ፡ ከተሞቻቸውን ፡ ሲዘጉበት ፡ አል
ቻሉም ። . . . የሔራቅሌዎፖሊስንም ፡ ከተማ ፡ ከቦ ፡ አስጨንቋ
ታል ። የሚገባም ፡ የሚወጣም ፡ የለም. . . » በቴብ ፡ ካሉት ፤ መኳን
ንቶች ፡ መልእክት ፡ በቀር ፡ የፒያንኪ ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ መሳፍንትና ፡
መኳንንት ፡ «ዝም ፡ ያልህ ፡ እንደሆን ፡ የደቡብ ፡ (የላዕላይ ፡ ግብፅ)
ከተማዎች ፡ መጥፋታቸው ፡ ነው ። ታፍነቅታ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይገሠ
ግሣል ፡ የሚቋቋመውም ፡ የለም ። ነምሩድ ፡ የሐዊር ፡ አለቃ ፡ (የሔ
ርሞፖሊስ ፡ ንጉሥ) ፡ ከተዋጋና ፡ ከተከበበ ፡ በኋላ ፡ ፈርቶ ፡ ግርማ
ዊነትህን ፡ ከድቶ ፡ ወደርሱ ፡ ተደርቧል ። እርሱም ፡ ብዙ ፡ ከተማ
ሰጥቶ ፡ አስደስቶታል» ፡ እያሉ ፡ ላኩበት ። ፒያንኪ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ
ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ለጦር ፡ አለቆቹ ፡ ለፑአርማና ፡ ለአሚሬስካኒ ፡ እንደ
ዚህ ፡ ብሎ ፡ ላከ ። «ወደሔርሞፖሊስ ፡ (የነምሩድ ፡ ከተማ) ፡ ሒዱ
ተዋጉ ፤ ሰውንም ፡ ከብቱንም ፡ በወንዝ ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ጀል
ዎች ፡ ሁሉ ፡ ማርኩ ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ወጥቶ ፡ እ
ሥራ ፤ ገበሬም ፡ አይረስ ፤ ከተማዋን ፡ ክበቡ ፡ ያለስንፍናም ፡ ውጊት

ይኸን ፡ መልእክት ፡ ቴብ ፡ ያሉት ፡ የጦር ፡ አዛዦቹ ፡ ከላከ
በኋላ ፡ ለነርሱ ፡ የሚሆን ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ጦር ፡ ከናፓታ ፡ ለ



ላከ ፡ አዘጋጀ ። ለጦር ፡ ሠራዊቱም ፡ ጉዞ ፡ ከመጀመራቸው ፡ በፊት ፡
ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ነገራቸው ፡ « እንደ ፡
ጨዋታ ፡ በሌሊት ፡ አትውጉ ፡ (፩) ። ነገር ፡ ግን ፡ ወታደሩን ፡ ሰብ
ስቦ ፡ ወደእናንተ፡ ሲጓዝ፡ ተዋጉት ፡ . . . ጦርነቱም፡ ሊጀመር ፡ ሲል፡
አሞን ፡ አምላክ ፡ እንደላከን ፡ (፪) ። አስቡ ፡ ( ተዘከሩ ) ። በቴብ ፡
ከተማ ፡ ስትደርሱ ፡ ቀስትና ፡ ጦራችሁን ፡ አስቀምጣችሁ ፡ በአፒ ፡
(ሐፒ ፡ -ኩርማው ፡ አምላክ) ፡ ትይዩ ፡ ባለው ፡ ወንዝ ፡ ተንከራችሁ፡
ታጥባችሁ ፡ በጥምቀት ፡ ሰውነታችሁን ፡ አንጹ ። ከመካከላችሁ ፡
ማናቸውም ሹም ፡ የጌታን ፡ (የአሞንን) ፡ ቃል ፡ አይጣስ ። ያለርሱ፡
ማንም ፡ ወታደር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። የተሰበረውን ፡ ክንድ ፡ አሸናፊ፡
ሊያደርገው ፡ ይችላል ። ብዙዎቹን ፡ ያደክማል ፤ አንዱን ፡ ሰው ፡
ከብዙ ፡ ሺ ፡ ሰው ፡ ያስተካክላል ። . . . በምሥዋዑ ፡ ፊት ፡ ባለው ፡
ውሃ ፡ ታጠቡ ። በፊቱም ፡ ተደፍታችሁ ፡ እንደዚህ ፡ በሉት ፡ በሰይ
ፍህ ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፡ ለመዋጋት ፡ የምንችልበትን ፡ መንገድ ፡ ምራን ።
. . . የምትልከው ፡ ልጅ ፡ (፫) ። ብዙዎቹን ፡ ያስፈራውን ፡ ( ታፍና
ቅትን ? ) ፡ ያሰደነብራል ።

ይኸን ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ ወታደሮቹ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡
ብለው ፡ በፊቱ ፡ ተደፉ ፤ «ለኛ ፡ ሰይፋችን ፡ ስምህ ፡ ነው ።

ጥበብህ ፡ ሠራዊትህን ፡ ትመራለች ፡ ኀብስትህ ፡ በአካላችን ፡
ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ስንጓዝ ፡ ስንቅ ፡ ነው ፡ ወይንህም ፡ ጥማችንን ፡
ያረካል ፡ . . . . . . . ድል ፡ አድራጊ ፡ ንጉሥ ፡ ነህ . . . . . . »

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወታደሩ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ጉዞውን ፡ ጀመረ ።
በመርከብ ፡ ያባይን ፡ ወንዝ ፡ እየተከታተሉ ፡ ሲጓዙ ፡ ከሰሜን ፡ የፒ
ያንኪን ፡ ጦር ፡ ለመውጋት ፡ በመርከብ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡
ከሚመጡት ፡ ጋር ፡ ድንገት ፡ ተገናኝተው ፡ ውጊያ ፡ ተጀመረ ።
ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ የሰሜኖቹ ፡ ተሸን
ፈው ፡ ተማረኩ ። የፒያንኪም ፡ ወታደሮች፡ የማረኩትን ፡ ሰውንም ፡
መሣሪያውንም ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ልከው ፡ እነሱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡
ቀጥለው ፡ በኬኔንሱ ፡ (ሔራክሌዎፖሊስ ፡) ከተማ ፡ ደረሱ ።

---

(፩) እንደ ፡ ፈሪ ፡ አዘንግታችሁ ፡ ሌሊት ፡ አትውጉት ፡ ማለቱ ፡ ይመስላል ።
(፪) ላከን ፡ ብላችሁ ፤
(፫) ስለፈሩ ፡ ይናገራል ።

ታፍኔቅት ፡ የፕታህ ፡ (የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ዋነኛ ፡ አምላክ) ፡ ካህን ፤ የኔት ፡ (ባገሩ ፡ በሳይስ ፡ የምትከበር ፡ ሴት ፡ አምላክ) ፡ ነቢይ ፤ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ከተሞች ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ የምዕራብ ፡ አገር ፡ ትልቁ ፡ ሹም ፡ የሚባለው ፡ ብዙ ፡ ንግሥታትና ፡ መሳፍንት ፡ ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቀውን ፡ ነምሩድን ፡ ጨምሮ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ነበርና ፡ ከደቡብ ፡ የፒያንኪ ፡ ጦር ፡ መድረሱን ፡ ስማ ። በበኩሉ ፡ እርሱም ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ እየተጓዘ ፡ መጣና ፡ ተጋጠማቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከጭፍሮቹ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሲያልቅበት ፡ ሲያይ ፡ የፓ ፡ ፔካን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ ወደታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ተመለሰ ። ከርሱ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ነምሩድ ፡ የሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ ሂርሞፖሊስ ፡ የሚባለው ፡ የራሱ ፡ ከተማ ፡ ተያዘ ፡ ማለትን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከታፍኔቅት ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ መጣ ። የፒያንኪ ፡ ጦር ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ በመርከብ ፡ እባሕር ፡ ላይ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሖርሞፖሊስ ፡ ደርሶ ፡ ከብቱንም ፡ ሰውንም ፡ ዘርፎ ፡ ወታደሩንና ፡ ቤተሰቡን ፡ ሰብስቦ ፡ እከተማው ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መሽጎ ፡ ተቀመጠ ። የፒያንኪ ፡ ወታደሮች ፡ ይኸን ፡ ሲሰሙ ፡ ከየጀልባቸው ፡ ወርደው ፡ ያለበትን ፡ ከተማ ፡ በአራት ፡ ማዕዘን ፡ ከበቡ ። እንደከበቡም ፡ ለንጉሣቸው ፡ ለፒያንኪ ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ላኩበት ። እርሱ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በመደሰት ፡ ፈንታ ፡ የታፍኔቅትን ፡ ማምለጥ ፡ የነምሩድንም ፡ መሽጎ ፡ መቀመጥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ተቆጣ ፡ እንደዚህም ፡ አለ ፡ «ለወሬ ፡ ነጋሪ ፡ ከታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ወታደር ፡ ካተረፉ ፡ ሁሉንም ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ መምታት ፡ ካቃታቸው ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ እንደምሔድ ፡ በሕይወቴ ፡ በራሴ ፡ (በፀሐይ ፡ አምላክ) ፡ ፍቅር ፤ አባቴ ፡ አሞን ፡ ባደረገልኝ ፡ ቸርነት ፡ እምላለሁ ። ወርጄም ፡ የሠራውን ፡ ሁሉ ፡ አፈራርሠዋለሁ ። ጦርነቱንም ፡ በቃኝ ፡ እንዲል ፡ አደርገዋለሁ ። ባመቱ ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ሥርዓተ ፡ ክህነቴን ፡ (ቅዳሴዬን) ፡ ፈጽሜ ፡ በክብሩ ፡ በሚወጣበት ፡ (በዓሉ ፡ በሚውልበት) ፡ ጊዜ ፡ ለአባቴ ፡ ለአሞን ፡ ስለቴንና ፡ እምኃዬን ፡ በሚያምረው ፡ በዓሉ ፡ ቀን ፡ አቀርብለታለሁ ፡ . . . በደመቀ ፡ በዓልም ፡ ወደቴብ ፡ ገብቶ ፡ በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አደርገዋለሁ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ቅጣቱን ፡ እንዲያጣጥም ፡ አደርገዋለሁ ።»



የጦር ፡ አለቆቹ ፡ የንጉሣቸውን ፡ ቁጣ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በሥጋትና ፡ ባዲስ ፡ ኃይል ፡ ተቀስቅሰው ፡ እየተዋጉ ፡ ብዙ ፡ ዠብዱ ፡ መሥራታቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ከተማ ፡ መያዛቸውንም ፡ ጨማምረው ፡ ላኩበት ። እሱ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ተደስቶ ፡ ከቁጣው ፡ አልበረደም ።

ስለዚህ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ሔዶ ፡ በሠራዊቱ ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ የጦር ፡ እቅድ ፡ እየሰጠ ፡ ካልመራው ፡ የድሉ ፡ ነገር ፡ በቶሎ ፡ እንደማይከናወን ፡ ተረዳው ። ስለዚህ ፡ ቶት ፡ (የጥበብና ፡ የዕውቀት ፡ አምላክ ፡) በገባ ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ በመሳፍንቱ ፡ ታጅቦ ፡ ከናፓታ ፡ ተነሣ ፡ በመርከብ ፡ ተጉዞ ፡ ወደ ፡ ቴብ ፡ ከተማ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ዘውዱን ፡ እንደደፋ ፡ ከመርከቡ ፡ ወረደ ፤ ተዘጋጅቶ ፡ በቀረበለት ፡ በሚያምረው ፡ ሠረገላ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ሖርሞፖሊስ ፡ ሔደ ። በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡ ፍርሃት ፡ ገባ ፤ የግርማውም ፡ ብርሃን ፡ እስከ ፡ እስያ ፡ እንጸባረቀ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የግርማዊነቱ ፡ ዝና ፡ እስከ ፡ ምሥራቅ ፡ ድረስ ፡ ተሰማ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በፊቱ ፡ ለቆሙት ፡ የጦር ፡ ሹማምንቱ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ፡ «በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እየተዋጋችሁ ፡ የትእዛዜን ፡ ፍጻሜ ፡ የምታዘገዩት ፡ ከሆነ ፡ የማደርገውን ፡ ሸብር ፡ ለታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ አሳያታለሁ ፡ . . . »

ንጉሡ ፡ ፒያንኪ ፡ ይኸን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ሠፈሩን ፡ በተከበበችው ፡ ከተማ ፡ ምዕራብ—ደቡብ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ በየቀኑ ፡ ያስወጋት ፡ ዠመር ። ነምሩድና ፡ ጦሩ ፡ ከቅጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ስለተሸሸጉና ፡ ለዓመታት ፡ ስላስቸገሩ ፡ በቅጥሩ ፡ ዙሪያ ፡ አፈርና ፡ ጓል ፡ እየሰበሰባችሁ ፡ ረዥዥም ፡ ድድቅ ፡ ሥሩ ፡ የንጪት ፡ መሰላልም ፡ አዘጋጁ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። ድድቁና ፡ መሰላሉ ፡ ተሠርቶ ፡ በቁመት ፡ ከቅጥሩ ፡ መብለጡ ፡ ከተገመተ ፡ በኋላ ፡ ወታደሩ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ እየወጣ ፡ ግማሹ ፡ በቀስት ፡ ግማሹ ፡ በድንጋይ ፡ እየወረወረ ፡ እቅጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ በየቀኑ ፡ ይደበድቡዋቸው ፡ ዠመር ። በ፫ኛው ፡ ቀን ፡ በከተማዋ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ትንፋሽ ፡ አጥተው ፡ ደከሙ ።

ስለዚህ ፡ ወርቅና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ ልብስ ፡ ሰገጻ ፡ በረከት ፡ የሚሆን ፡ የያዙ ፡ መልእክተኞች ፡ ከቅጥሩ ፡ ውስጥ ፡ እየተ

ላኩ ፡ መውጣት ፡ ዠመሩ ። ንጉሡ ፡ ነምሩድም፡ ኔስቴንቴምህ ፡ የም ትባለዋን ፡ ሚስቱን ፡ የፒያንኪን ፡ ሚስቶችና ፡ እኅቶች ፡ ለምና ፡ በነሱ ፡ አማካይነት ፡ ፒያንኪን ፡ እንድታማልደው ፡ ላከት ። እሷም ፡ ከቅጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ወጥታ፡ ወደፒያንኪ፡ ሚስቶችና ፡ እኅቶች፡ ሠፈር፡ መጥታ ፡ በነሱ ፡ ፊት ፡ ተደፍታ ፡ እንደዚህ ፡ ስትል ፡ ለመነቻቸው ። « ወደኔ ፡ ኑ ፡ (፩) ። የንጉሥ ፡ ሚስቶችና ፡ እኅቶች ፡ ልጆችም ፡ የቤተ ፡ መንግሥትን ፡ ጌታ ፡ የሆሩስን ፡ (፪) ። ልብ ፡ አራሩልኝ ፡ መንፈሱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍርዱም ፡ ታላቅ ፡ ናትና ። »

እርሷም ፡ በነርሱ ፡ ልመናና ፡ አማላጅነት ፡ የፒያንኪን ፡ ልብ ፡ ከአለሰለሰች ፡ በኋላ ፡ ባሏ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ቅጥር ፡ ተመለሰች ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነምሩድ ፡ ሚስቱን ፡ አፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ዘውዱን ፡ እን ዳደረገ ፡ ወደፒያንኪ ፡ መጣ ፡ በፊቱም ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፡ «የሕይወትን ፡ መንገድ ፡ ዘጋህ ፤ እንደ ፡ ፍላፃ ፡ ወደሰማይ ፡ እንኳ ፡ ብበር ፡ ትደርስብኛለህ ። የደቡብ ፡ አገሮች ፡ ተሸንፉ ፤ የሰሜኖቹም፡ እጕነበሱ ፤ በጥላህ ፡ ሥር ፡ መኖር ፡ እንችላለን ፤ ? . . . እነዚህ ፡ የገበሩልህ ፡ ይቆጠርና ፡ እኔ ፡ ከነሱ ፡ የበለጠ ፡ እሰጣለሁ» ።

ይኸን ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ዕንቍ ፡ መሣሪያ ፡ ብረት ፡ በያይነቱ ፡ ስጠና ፡ ግምጃ ፡ ቤቱን ፡ መላው ። ቀጥሎ ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ በቀኝ ፡ እጁ፡ ፈረሱን፡ (የጭኑን ? ፡) በግራ ፡ እጁ ፡ በሰማያዊ ፡ ዕንቍና፡ በወርቅ፡ የተሠራ፡ ጸናጽል፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ ለንጉሡ ፡ ለፒያንኪ ፡ አቀረበ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ፒያንኪ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ቶት ፡ ቤተ፡ መቅደስ ፡ ሔደ ። ካህናቱም፡ ወታደሩም፡ በደስታ፡ ተቀበሉት ። ከዚያ፡ ወደ፡ ነምሩድ፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ ሔዶ፡ ክፍሉን ፡ ሁሉ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱንም ፡ የፈረስ ፡ ቤቱንም ፡ ጐበኘ ፡ ሚስ ቶቹንና ፡ እኅቶቹንም ፡ አስጐበኛቸው ። በዚህም ፡ መካከል ፡ ፈረሶ ችና ፡ ከብቶች ፡ ተርበው ፡ ዓይቶ ፡ ነምሩድን ፡ በጣም ፡ ወቀሰው ።

(፩) ወደኔ ፡ ኑ ፡ ማለቷ ፡ ቅረቡኝ ፡ አማልዱኝ ፡ ማለቷ ፡ ነው ።

(፪) ሆሩስ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ አምላክ ፡ ጭንቅላቱ ፡ በአሞራ ፡ የሚመስል ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ሲትቀጥ ፡ ፒያንኪን ፡ በራሱጥ ፡ አገር ፡ አምላክ ፡ ስም ፡ መለመኗ ፡ ነው ።



እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ስምን ፡ ፔፋባስት ፡ የሚባለው ፡ የሄራቅ ሌዎፖሊስ ፡ ንጉሥ ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ፒያንኪ ፡ መጣ ፡ በፊቱም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡ « ሆሩስ ፡ ሆይ ፡ ክብር ፡ ላንተ ፡ ይገባል ። ድል ፡ አድራጊ ፡ ሆይ ፡ ኮርማዎችን ፡ የምታባርር ፡ ኮርማ ፡ ነህ ። በጥልቁ ፡ ሲአል ፡ ነበርሁ ፡ በጨለማም ፡ ተውጬ ፡ ነበር ፡ . . . በችግሬ ፡ ቀን ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ የደረሰልኝ ፡ የለም ። ድል፡ አድራጊው ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፤ ጨለማ ፡ ከኔ ፡ እንዲርቅ ፡ አባረርህልኝ፡ ከሁብቴ ፡ ጋር ፡ አገልጋይህ ፡ነኝ ። ሔራቅሌዎፖሊስ፡ ለቤተ፡ መንግ ሥትህ ፡ ይገብራል ። እነሆ ፡ ከከዋክብት፡በላይ ፡ የሖርማኪስ ፡ (፩) ። ምስል ፡ የሱ ፡ ሕይወት ፡ ያንተ ፡ ሕይወት ፡ ነው ። እሱን ፡ ችግር ፡ እንደማይገጥመው ፡ አንተም ፡ ለዘለዓለም ፡ የምትኖረው ፡ ፒያንኪ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ አይደርስብህም » ።

የዚህ ፡ ጕዳይ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊነቱ ፡ (ፒያንኪ) ፡ ሮህን ፡ ወደምትባል፡ ከተማ፡ ሔደ ። በደረሰም፡ ጊዜ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ብዙ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ወታደሮች ፡ ነበሩባት ። ቅጽሮም ፡ ረግ ኸዋም ፡ መዚጊያዎቿም ፡ በጽኑ ፡ የተዘጉ ፡ ናቸው ፡ ማለትን ፡ በማ ። ሌሎቹ ፡ ትልልቅ ፡ ከተሞችና ፡ ነገሥታቶች ፡ ያልመከቱትን ፡ ይቺ ፡ ቲንሽ ፡ ከተማ ፡ ለመመከት ፡ በመሞከሯ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ፒያንኪ ፡ የተገረመ ፡ ወይም ፡ የተናደደ ፡ ይመስላል ። ለነሱም ፡ አላከው ፡ መል እክት ፡ ውስጥ ፡ የጥንት ፡ ፈርዖኖች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስገበርን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ « ምስኪኖቹን ፡ አስገበርን » ብሰው ፡ የተናገሩበ ትን ፡ የበድብና ፡ የማኮሰስ ፡ ቃል ፡ አሁን ፡ ፒያንኪ ፡ በነዚህ ፡ ግብፃ ውያን ፡ ላይ ፡ መልሶ ፡ ሠራበት ። ቢሆንም ፡ ስድብ ፡ ጨምሮ ፡ ቢል ክም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ፡ አለአቅማቸው፡ ለመመከት ፡ ስላሰቡ ፡ አዝኖላቸው ፡ ምክርም ፡ ጨምሮ ፡ ከማስጠንቀቅ ፡ አልቦዘነም ። ቃሉም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ «እናንት ፡ በሞት ፡ የምትኖሩ ፡ ደካሞች ፡ . . . ምስኪኖች ፤ መዝጊያችሁን ፡ ሳትከፍቱ ፡ ቲንሽ ፡ ጊዜ ፡ ያለፈ ፡ እን ደሆነ ፡ በማደርገው ፡ እልቂት ፡ ፈራጆች ፡ (ኃላፊዎች) ፡ ትሆናላ

፩ኛ- ፤ ሖርማክሂስ ፡ የቤቷ ፡ አምላክ ፡ የሖትሖር ፡ (ሐጸር) ፡ ባል ፡ የሄራቅሌዎፖሊስ ፡ አምላክ ፡ በጽርሕ ፡ እርያም ፡ የሚኖረው ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ የሚዞ ጠው ፡ ፀሐይ ።

ችሁ ፡ . . . . . ለሕይወት ፡ የከፈትሁላችሁን ፡ መዝጊያ ፡ አትዝጉ ፡ . . . . ሞትን ፡ አትምረጡ ፡ በአገር ፡ ፊት ፡ ሕይወትንም ፡ አትናቁ ።

ይኸን ፡ ቃል ፡ ሲሰሙ ፡ እነሱም ፡ ምንም ፡ ሳያመነቱ ፡ በቶሎ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ላኩ ፡ «የአምላክ ፡ ጥላ ፡ በራስህ ፡ ስለ አለ ፡ የኑትም ፡ ልጅ ፡ (፩) ። ከንዱን ፡ ከሰጠህ ፡ ቃልህ ፡ ከአምላክ ፡ አንደበት ፡ እንደወጣ ፡ ተቆጥሮ ፡ ወዲያው ፡ ይፈጸማል ፡ አምላክም ፡ እንደወለደህ ፡ በሥራህ ፡ ሁሉ ፡ ይታወቃል ። ከተማዋና ፡ መዝጊያዎቿ ፡ ከሥልጣንህ ፡ በታች ፡ ናቸው ፡ እንደልባችን ፡ አስወጣን ፡ አስገባን» ፤

ይህ ፡ ቃል ፡ በደረሰው ፡ ጊዜ ፡ ፒያንኪ ፡ ጦርነቱን ፡ አቁሞ ፡ ልመናቸውን ፡ ሰምቶ ፡ በሰላም ፡ እንዲወጡ ፡ ፈቀደላቸው ።

ከነርሱም ፡ መካከል ፡ የታፍኔቅት ፡ ልጅ ፡ አብሮ ፡ ነበር ፡ የንጉሡም ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ከተማዋ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ። አንድ ፡ ነፍስ ፡ እንኳን ፡ አላጠፉም ።

በሰላም ፡ ለሚማረክ ፡ ጠላት ፡ ፒያንኪ ፡ ርኅሩኅ ፡ ነው ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ካልተገደደ ፡ በቀር ፡ የማንንም ፡ ነፍስ ፡ በከንቱ ፡ ማጥፋት ፡ አይወድም ፡ ነበር ። የሚዋጋውንም ፡ አገርና ፡ ከተማ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሚገባ ፡ ሳይመክርና ፡ ሳያስጠነቅቅ ፡ ውጊያ ፡ አይዠምርም ፡ ነበር ፤ የጦር ፡ አለቆቹም ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ እንዲሠሩ ፡ ጥብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቷቸዋል ። ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ ፒያንኪ ፡ አምላኩን ፡ የሚፈራ ፡ የሕሊና ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያስረዳል ። ትእዛዝም ፡ ምክርም ፡ ሲሰጥ ፡ ያነጋገሩ ፡ ቅርጽ ፡ በምሳሌ ፡ በፍልስፍና ፡ የተቀረጸ ፡ ነው ። ፍልስፍና ፡ ቢጨመርበትም ፡ ዘወርዋራና ፡ ጥምዝ ፡ ወይም ፡ ጥልቅ ፡ ሳይሆን ፡ አነጋገሩ ፡ ለማንም ፡ ተርታ ፡ ሰው ፡ የሚገባ ፡ ግልጽና ፡ ቍርጥ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ከተመለከትነው ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሚይዛቸው ፡ ከተሞች ፡ ላይ ፡ ለምክርና ፡ ለማስጠንቀቂያ ፡ የሚልካቸው ፡ ቃሎች ፡ ያስረዱናል ።

የሮኅን ፡ ከተማ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊነቱ ፡ ሚሬትም ፡ ወደ ፡ ምትባለዋ ፡ ከተማ ፡ አመራ ፤ ይህቺም ፡ ከተማ ፡ ሶካሪስ ፡ የሚባለው ፡

(፩) እሞን ።



ንጉሥ ፡ የነበረባት ፡ ከተማ ፡ ናት ። ሰሞኑንም ፡ የሶካሪስ ፡ ጦርና ፡ የፒያንኪ ፡ ጦር ፡ ሲዋጋባት ፡ በንብቷል ። አሁን ፡ ግን ፡ ዘለዓለም ፡ የሚኖረው ፡ የሁለቱም ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ የአሞን ፡ ልጅ ፡ ፒያንኪ ፡ መጥቷል ፡ ማለትን ፡ በምተው ፡ ፍርሃት ፡ ይዟቸው ፡ የከተማዋን ፡ ቅጥር ፡ ዘጋግተው ፡ ተቀምጠዋል ። ፒያንኪም ፡ ከነሠራዊቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከማስወጋቱ ፡ በፊት ፡ እንደልማዱ ፡ ቊርጠኛ ፡ መልእክቱን ፡ እንደዚሁ ፡ ሲል ፡ አስቀደመ ፡ « በፊታችሁ ፡ ሁለት ፡ የመንገድ ፡ መሥመር ፡ አስቀምጡ ፤ እንደፍላጎታችሁም ፡ ምረጡ ፡ ብትከፍቱ ፡ ሕይወትን ፤ ብትዘጉ ፡ ሞትን ፡ ታገኛላችሁ ። ግርማዊነቴ ፡ በተዘጋ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ማለፍ ፡ አይችልም » ፡ እነሱም ፡ ወዲያው ፡ ከተማዋን ፡ ከፈቱና ፡ የፒያንኪ ፡ ጦር ፡ በሰላም ፡ ገባባት ። ፒያንኪም ፡ ገብቶ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ ሁሉ ፡ ከጐበኘ ፡ በኋላ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ለሚገኘው ፡ አምላክና ፡ ለራሱም ፡ ለአሞን ፡ መሥዋዕትና ፡ ስጦታ ፡ አቅርቦ ፡ ጨረሰ ። ከዚያ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ቶታዊ ፡ ከተማ ፡ ደረሰ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ወታደሮች ፡ በርከተው ፡ ቢገኙባት ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ከተሞች ፡ ቅጥራቸውን ፡ ዘግተው ፡ ለመከላከል ፡ አልደፈሩም ። ስለዚህ ፡ ፒያንኪ ፡ እንደደረሰ ፡ መዝጊያቸውን ፡ ከፍተው ፡ በፊቱ ፡ ተደፍተው ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ ተቀበሉት ፡ « አባትህ ፡ የውርሱን ፡ ቅርስ ፡ ላንተ ፡ አዘጋጅቶልሃል ፡ (፩) ። የሁለቱ ፡ ዓለሞች ፡ (ኢትዮጵያና ፡ ግብፅ) ፡ ጌታ ፡ እንደመሆንህ ፡ እነሆ ፡ ግንዘቦችህ ፡ ናቸው ። ዓለምን ፡ የምትገዛ ፡ ጌታ ፡ ነህ » ፡ ይኸን ፡ ብለው ፡ ከተማዋን ፡ ከነሀብቷ ፡ ሲያስረክቡት ፡ እሱም ፡ ወደቤተ ፡ መቅደሳቸው ፡ ሔዶ ፡ ለመሥዋዕት ፡ የሚያደርጉትን ፡ በሬ ፡ ኮርማ ፡ ዳክዬ ፡ ሌላውንም ፡ በያይነቱ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሰጣቸው ።

ፒያንኪ ፡ እንደዚህ ፡ እያደረገ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ በተቀበሉት ፡ ከተሞች ፡ በሰላም ፡ እምቢ ፡ ባሉት ፡ ላይ ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ እየገባ ፡ ብዙ ፡ የታሕታይን ፡ ግብፅ ፡ ከተሞች ፡ ያዘ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ አስቀድም ፡ በጥበብ ፡ በምሳሌ ፡ እያደረገ ፡ ሳይመክርና ፡ ሳያስጠነቅቅ ፡ አንድም ፡ ከተማ ፡ እንዳልመታም ፡ እንዳላስመታም ፡

(፩) አሞንን ፡ ወይም ፡ ሶካሪስን ፡ ማለታቸው ፡ ይሆን ? ።

ይኸው ፡ ታሪኩ ፡ ይነግርለታል ። ይኸም ፡ የርሱ ፡ አያያዝ ፡ ከርሱም ፡ ከነዚያም ፡ ወገን ፡ በከንቱ ፡ የሚጠፉውን ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ያድናል ። በገባበት ፡ ከተማ ፡ ያገኘውን ፡ የሕዝቡን ፡ ባይሆን ያመጠበትን ፡ (የሸፈተበትን) ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ሹም ፡ ሀብት ፡ ግማሹን ፡ ለራሱ ፡ አምላክና ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወርሶ ፡ ግማሹን ፡ ደግሞ ለዚያው ፡ ለገባበት ፡ ከተማ ፡ አምላክ ፡ አድሎ ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ የየከተማውን ፡ አምላክ ፡ ሳይንቅ ፡ በአክብሮት ፡ ተሳልሞ ፡ ነገሥታቶቻቸው ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ በትክክል ፡ ፈጽሞ ፡ ሕዝቡንም ፡ ካህናቱንም ፡ ያስደስታል ። ይኸም ፡ ይዞታው ፡ ገዥነቱን ፡ ዝናውን ፡ አስተዳደሩን ፡ አቃንቶለታል ። የርሱንም ፡ መንገድ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ከ፩፻፶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የግሪክ ፡ ንጉሥ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ በ፫፻፴፮—፫፻፳፫ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ በወረራቸው ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተከተለውና ፡ እንደተጠቀመበት ፡ ይታያል ። እስክንድርን ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ የአመራር ፡ ዘዴ ፡ የመከረው ፡ መምህሩ ፡ አሪስቶት ፡ (አርስጣጣሊስ ፡) ሲሆን ፡ ፒያንኪን ፡ የመከረው ፡ ሌላ ፡ መምህር ፡ መኖሩን ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ለራሱ ፡ መምህር ፡ ሆኖ ፡ በሚገባና ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ እንደተመራ ፡ ጽሑፉ ፡ አይናገርም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሁንም ፡ ከተማዎቹ ፡ ጨርሰው ፡ አልተያዙም ። ብዙ ፡ ከተሞች ፡ ቢያዙም ፡ ብዙ ፡ መሳፍንትና ፡ አስፈሪ ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ነምሩድ ፡ ቢገቡም ፡ ገና ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ዋናው ፡ ፈርዖን ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ሠራዊትም ፡ ነገሥታትም ፡ ይዞ ፡ የሚጠብቀው ፡ ታፍነቅት ፡ ገና ፡ አልገባም ። እርሱም ፡ በበኩሉ ፡ ለውጊያ ፡ ብዙ ፡ ድርጅት ፡ አድርጓል ። ከርሱ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ነምሩድ ፡ ብቻ ፡ ተሸንፎ ፡ ሲገባ ፡ የቀሩት ፡ ሶካሪስ ፤ እሶርኮን ፡ የሚባሉት ፡ ሁለት ፡ ነገሥታት ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የጦርነቱን ፡ ጊዜ ፡ ይጠባበቃሉ ። እንደዚሁም ፡ ታላቂቱ ፡ የፈርዖኖቹ ፡ ከተማ ፡ መምፌስ ፡ (፩) ፡ ገና ፡ አልተያዘችም ። ይቺም ፡ የመምፌስ ከተማ ፡ ከቴብ ፡ በፊት ፡ የተመሠረተች ፡ የጥንታውያኑ ፡ ፈርዖኖች ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ናት ። በውስጧም ፡ ያለው ፡

---

፩ ፤ መምፍትስ ፡ ወይም ፡ መንፍ ፡ እያለ ፡ የዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ የሚጠቅሳት ።



የልዩ ፡ ልዩ ፡ አማልክትና ፡ በተለይ ፡ የፕተህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስና ፡ ምስል ፡ የነገሥታቱ ፡ የካህናቱ ፡ ሐውልት ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አዳራሽ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

በቴብና ፡ በናፓታ ፡ የአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡ ደብር ፡ እንደሚቆጠር ፡ በመምፌስ ፡ ደግሞ ፡ የፕታህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ስመጥር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ፒያንኪ ፡ ይቺን ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ለመያዝ ፡ ወደፊት ፡ ገሠገሠ ። ወደ ፡ ከተማዋም ፡ በተጠጋ ፡ ጊዜ ፡ በውስጧ ፡ ለሚኖሩት ፡ መልእክት ፡ አዘጋጀ ። እንደ ፡ ከተማዋ ፡ ታላቅነት ፡ በውስጧ ፡ እንደሚገኙት ፡ እንደክቡራኑ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ እንደ ፡ ልዑላኑ ፡ መሳፍንት ፡ የደረጃ ፡ መጠን ፡ መልእክቱ ፡ የለሰለሰ ፡ አክብሮ ፡ የተጨመረበት ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ለሌሎቹ ፡ ለተርታዎቹ ፡ ከተሞች ፡ እንደላከላቸው ፡ ዓይነት ፡ አለመሆኑ ፡ የሚቀጥለው ፡ የመልእክቱ ፡ ንግግር ፡ ያስረዳል ።

« በዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የምትኖሩ ፡ መዝጊያቻችሁን ፡ አትዝጉ ፤ አትዋጉ ፤ ሱ ፡ አምላክ ፡ (ሱ ፡ ወይም ፡ ስሑ ፡ የፀሐይ ፡ ልጅ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡) በዘመን ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እኔም ፡ እንደሱ ፡ ገብቼ ፡ እወጣለሁ ። እርምጃዬን ፡ ያልገፋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ለፕታህና ፡ በመምፌስ ፡ ከተማ ፡ ለሚገኙት ፡ አማልክት ፡ መሥዋዕቱንና ፡ መባዓዩን ፡ አቀርባለሁ ፡ በሴት ፡ (ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ፀሐይ ፡ አምላክ ፡) ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሶካሪስ ፡ ይፈጽም ፡ የነበረውን ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ እፈጽማለሁ ። ፕታህንም ፡ በጥንታቄ ፡ እመለከታለሁ ። በሰላምም ፡ እመለሳለሁ ፡ ከተማዋን ፡ በመልካም ፡ እይዛታለሁ ፤ ትድንማለች ፡ የሕፃናት ፡ ዋይታ ፡ አይሰማም ፡ ተመልከቱ ፡ የደቡብን ፡ ከተሞች ፡ የአምላክን ፡ ቃል ፡ ካስተሐቀፉት ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ አልተገደለም ። ሥቃይ ፡ የተሠራው ፡ ለኃጥእ ፡ ነው ። »

በዚሁ ፡ መካከል ፡ ታፍናቅታ ፡ ከሰሜን ፡ ወደ ፡ መምፌስ ፡ መጥቶ ፡ የመምፌስ ፡ ከተማ ፡ ኃይለኛ ፡ ናት ፡ ወታደሮቿም ፡ ጉበዞች ፡ ናቸው ። በምሥራቅም ፡ ወገን ፡ በባሕር ፡ የተከበበች ፡ ስለሆነች ፡ ጠላትን ፡ አታስገባም ። ገንዘብ ፡ ስንቅ ፡ ዘይት ፡ በሰሜን ፡ ላሉት ፡ ወታደሮች ፡ ስጥቼ ፡ ከሰሜን ፡ ተመልሼ ፡ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ መክቱ ፡

ብሎ ፡ ለሹማምንቱ ፡ መክሮ ፡ ሥረገባውን ፡ ትቶ ፡ በፈረሱ ፡ ተጋ ብቶ ፡ ሔዶ ፡ ነበርና ፡ የመምፈስ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ የፒያን ኪን ፡ ምክር ፡ ሰምተው ፡ (ትጥሩን ፡) ሊከፍቱ ፡ አልፈለጉም ።

ስለዚህ ፡ ፒያንኪ ፡ የዚህኑ ፡ እርግጠኛነት ፡ ሲያውቀው ፡ ወደ ከተማዋ ፡ ተጠግቶ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ የወንዙ ፡ ውሃ ፡ እስከ ፡ ቅጥሯ ፡ መሙላቱን ፡ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ከተማዋ ፡ ከቀድሞው ፡ በቀር ፡ ባዲስ ፡ ሥራ ፡ በደንብ ፡ የተመሸገችና ፡ የማትደፈር ፡ መሆኗን ፡ እየዞረ ፡ ተመለከተ ። በቅጥሯ ፡ ዙሪያም ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚቻል ፡ ሹማ ምንቱ ፡ ብዙ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ። በመጨረሻም ፡ በሔርሞፖሎስ ፡ እንደ ፡ አደረጉት ፡ በቅጥሯ ፡ ልክ ፡ ድድቅና ፡ መሰላል ፡ ሥርተን ፡ እንገባለን ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ አቀረቡ ። ፒያንኪም ፡ የቀረበው ፡ ምክር ፡ ሁሉ ፡ ሰውነቱን ፡ አላስደሰተውም ፡ የጉዳዩም ፡ መራዘም ፡ እንደነበር ፡ አስቆጣው ። እንዲህም ፡ «አለ ፡ በሕይወቴ ፡ በራ ፡ (ፀሐይ) ፡ ፍቅር ፡ ባአባቴ ፡ በአሞን ፡ ቸርነት ፡ (ጺጋ ?) ፤ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ያደረግሁት ፡ በአሞን ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ። ይህ ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ንግግር ፡ ነው ። . . . . አሞንን ፡ በልባቸው ፡ አላስቀመጡትም ፤ ትእዛዙንም ፡ አላወ ቁም ፡ ይኸንንም ፡ ሁሉ ፡ አሞን ፡ ያደረገው ፡ (ልባቸውን ፡ ያጸናው) ፡ የሸብሩን ፡ ኃይል ፡ ለማስሚት ፡ ሲል ፡ እውቁ ፡ ነው ። እንግዴህ ፡ ይቺን ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ማዕበል ሆኜ ፡ እንደ ፡ እንግት ፡ አብቴ ፡ እሞን ፡ እዚል ። »

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፒያንኪ ፡ ጀልባዎችን ፡ ታንኳዎችን ፡ መርከቦ ችንም ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። በባሕሩ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ እንደሚገቡ ፡ ዝግጅቱ ፡ ከተፈ ጸመ ፡ በኋላ ፡ ለሚገቡት ፡ ወታደሮች ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ መሪና ፡ አዛዥ ፡ ሆኖ ፡ በመርከብ ፡ ገባ ፤ ማንባር ፡ ቀደም ፡ ለሆኑት ፡ ወታደሮቹም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ፤ አሁን ፡ ግማሻችሁ ፡ ከተማዋን ፡ ውጉ ፡ ግማሻችሁ ፡ ደግሞ ፡ በበር ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ግቡ ፡ የሚማረክ ፡ ሹም ፡ ስታገኙ ፡ አይገባምና ፡ እንዳትገድሉት ፡ ደቡብንና ፡ ሰሜንን ፡ ከያዝን ፡ ወዲህ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ በዚች ፡ በመምፈስ ፡ ተቀምጠን ፡ እረፍት ፡ እናደርጋለን» ይኸን ፡ ከተናገረ በኋላ ፡ ወታደሮቹ ፡ ተሸጉድጉደው ፡ ከመርከቡና ፡ ከየጀልባቸው ፡



ላይ ፡ እየወረዱ ፡ ወደ ፡ ከተማዋ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ። ብዙም ፡ ሰው ፡ ፈጁ ። ቀጥሎም ፡ ራሱ ፡ ፒያንኪ ፡ ከነጦሩ ፡ ገብቶ ፡ ትልቋን ፡ ከተማ ፡ መም ፊስን ፡ ያዛት ።

ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ እንደሚለው ፡ በማግሥቱ ፡ ብዙ ፡ ሹማምንት ፡ ከነሕይወታቸው ፡ ተማርከው ፡ እፊቱ ፡ ቀረቡ ። ንጉሡም ፡ ቤተ ፡ መቅ ደሱ ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ላከና ፡ ቀጥሎ ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ ሔዶ ፡ ለሐ ፡ ቃ ፡ ፕታህ ፡ ጌታ ፡ እንደነገሥታቱ ፡ ልማድ ፡ ወይኑን ፡ አቀረበ ። መምፊስንም ፡ በዕፕታህ ፡ ጌታ ፡ እንደ ነገሥታቱ ፡ ልማድ ፡ ወይኑን ፡ አቀረበ ። በዕጣኒና ፡ በሽቱ ፡ ቀደሳት ። ካህናቱንም ፡ በየቦታቸው ፡ እንዲገቡ ፡ ፈቀደላቸው ። ቀጥሎ ፡ ወደ ትልቁ ፡ ወደፕታህ ፡ የአማልክት ፡ አባት ፤ የመምፊስ ፡ ጠባቂ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሔዶ ፡ በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ እንደልማዱ ፡ ሰው ነቱን ፡ አነፃ ። ከዚያ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ገብቶ ፡ ለአባቱ ፡ ለፕ ታህ ፡ የበሬ ፡ ወይፈን ፡ የዳክዬ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። ከቤተ ፡ መቅ ደሱ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ አዳራሹ ፡ ሔደ ፡ . . . በዚያም ፡ ባለ ፡ በመምፊስ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉት ፡ የህሪፔቲኒ ፡ የፒኒናው ፡ ፺፱ ፡ . . . አገር ፡ ተከላካ ዮች ፡ መጥፋታቸውንና ፡ የየከተማቸው ፡ መግቢያ ፡ ክፍት ፡ መሆ ኑን ፡ ሰማ ። ቀጥሎ ፡ የማሱአለ ፡ . . . አለቆችና ፡ ንጉሡ ፡ ኡአፑት ፡ ሁሉም ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ሹማምንት ፡ ግብራቸውን ፡ እየያዙ ፡ መጥተው ፡ የግርማዊነቱን ፡ ብርሃን ፡ ለማየት ፡ መጡ ።

ግርማዊነቱም ፡ የመምፊስን ፡ ከተማ ፡ ሀብት ፡ ለአሞንና ፡ ለፕታህ ፡ . . . አከፋፈለ ።

ቀጥሎ ፡ ንጉሡ ፡ ወደምሥራቅ ፡ አመራ ፡ በኬሮ ፡ ለሚቀመጠው ፡ ለቱም ፡ (የሌሊት ፡ ፀሐይ) ፡ ለሌሎቹም ፡ አማልክት ፡ በአማሕ ፡ (ምውታን ፡ የሚወጡበት ፡ በር ፡) ለሚቀመጡትም ፡ ማናቸውንም ፡ መፋፋትና ፡ ደስታ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ የሆነው ፡ ፒያንኪ ፡ የበሬና ፡ የወይፈን ፡ የዝዪ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፡ . . . ያቀረቡለትን ፡ ሀብትና ፡ ከብት ፡ ግማሹን ፡ ለአሞን ፡ ግማሹን ለፕ ታህ ፡ የቀረውንም ፡ ለቀሩት ፡ አማልክት ፡ አደላድሎ ፡ ሲጨርስ ፡ ወደ ፡ ሔሌዎፖሊስ ፡ ሔደ ። በዚያም ፡ ለፀሐይ ፡ አምላክ ፡ ጉህ - ሲቀድ ፡ (ፀሐይ ፡ ጮራዋን ፡ በምትፈነጥቅበት ፡ ጊዜ) ፡ የንጭ ፡ በሬ ፡

መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። . . . ከዚህም ፡ ጋር ፡ ወተት ፡ ሽቱ ፡ ከርቤ ፡ ዕጣን ፡ ሰጠ ። የመሥዋዕቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሲያልቅ ፡ ወደ ፡ ራፀሐይ ፡ ወደ ፡ ቱም ፡ ( ጨርቃ ) ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ የመዝጊያውን ፡ ቁልፍ ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ ከፍቶ ፡ ምስላቸው ፡ (ሐውልታቸው ) ፡ ወዳለበት ፡ ብቻውን ፡ ተጠግቶ ፡ ጸሎቱንና ፡ ስግደቱን ፡ ጨርሶ ፡ ወጣ ፡ ካህናቱም ፡ አመሰገኑት ። ስለርሱም ፡ ደኅንነት ፡ ጸሎት ፡ አደረሱ ።፥ . . . »

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ አትሪቢስ ፡ ወንዝ ፡ በተለይ ፡ በከሃኒ ፡ ደቡብ ፡ ድንኳን ፡ አስተክሎ ፡ ሠፈር ፡ አደረገ ። በዚህም ፡ ሳለ ፡ የሰሜን ፡ ነገሥታት ፡ አሶርኮን ፡ ፩ኛው ፡ የቡባስቲ ፡ ንጉሠ ፤ ኡአፑት ፡ የቲንቴ ፡ ሬሙ ፡ ንጉሥ ፡ ሌሎችም ፡ መሳፍንት ፡ የጦር ፡ ሹማምንትና ፡ መኳንንት ፡ ካህናትና ፡ ነቢያትም ፡ ከየግል ፡ አገራቸው ፡ መታያቸውንና ፡ ግብራቸውን ፡ ፈረስ ፤ የጋማና ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ ልብስ ፤ ሽቶ ፤ ጥዋ ፤ አምባር፡ ያንገት ፡ ጌጥ ፡ በያይነቱ ፡ እየያዙ ፡ መጥተው ፡ ገብሩለት ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ፔቴሲሲ ፡ የሚባለው ፡ የአትሪቢስ ፡ መስፍን ፡ በስጦታውም ፡ በንግግሩም ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኘው ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ዋናው ፡ የፒያንኪ ፡ ጠላት ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በውስጡ ፡ አብረው ፡ የነበሩት ፡ ታፍኔቅት ፡ ሰማ ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታት ፡ ለፒያንኪ ፡ ከገቡ ፡ ከተሞቹና ፡ አውራጃቹም ፡ ሁሉ ፡ በየተራ ፡ ተይዘው ፡ ካለቁ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ፒያንኪን ፡ መከላከል ፡ በፍጹም ፡ የማያዛልቅ፡ መሆኑን፡ ባለበት ፡ ሰሜናዊ ፡ ሥፍራ፡ ሆኖ ፡ አመዛዘነ ።

ስለዚህ ፡ ታላቂቱ ፡ የመምፊስ ፡ ከተማ ፡ ከተያዘችና ፡ የየአውራጃው ፡ ነገሥታትና ፡ መሳፍንት ፡ ግብርና ፡ መታያ ፡ እየያዙ ፡ ወደ ፒያንኪ ፡ እየገቡ ፡ መገበራቸውን ፡ አርግጡን ፡ ከተረዳ ፡ ወዲህ ፡ እሱም ፡ የሚያሳዝን ፡ የምሕረት ፡ ቃል ፡ ጨምሮ ፡ መልክተኛ፡ ላከ፡ ቃሉም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ «ከቁጣህ ፡ ታገሥ ፤ በኀፍረቴ ፡ ዘመን ፡ አላየሁህም ፤ በነበልባል ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አልችልም ፤ በግለትህ ፡ ተሸንፍሁ ፤ በደቡብ ፡ ኑብቲ ፡ (ለነገሥታቱ ፡ የጦርነት ፡ መላ ፡ የሚያስተምር ፡ ) አምላክ ፡ ነህና፡ አሸናፊው ፡ (ሞንት) ፡ ኮርማ፡ ሆይ ፡ አንድ ፡



ነገር ፡ ስትፈልግ ፡ የሚቃወምህ ፡ ነገር ፡ አታገኝም ። ወደ ፡ ባሕር ፡ ደሴት ፡ ሸሸሁ ፡ ከዚች ፡ የግለት ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ መንፈስህን ፡ ተጠራጠርሁ ። አንድ ፡ ጠላት ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ተነሥቷል ፤ በኔ ፡ ላይ ፡ የተነሣው ፡ ልብህ ፡ አሁንስ ፡ አልቀዘቀዘምን ? አሁን ፡ ግን ፡ በውነቱ ፡ ምስኪን ፡ ነኝ ፡ በወንጀሌ ፡ ጥፋት ፡ ውስጥ ፡ አትጣለኝ ። የሚዛን ፡ ልክ ፡ ቂናንሾችን ፡ ስብርባሪዎች ፡ ያውቃል ፡ (ይለያል፡ ) እነዚህን፡ ለኔ ፡ በይቅርታህ ፡ አብዛቸው ፡ ዘር ፡ ብትዘራ ፡ በጊዜው ፡ ፍሬውን፤ ታገኛለህ ። ፍሬ ፡ የሚያፈራውን ፡ ዛፍ፡ ገና፡ በአበባው ፡ አታጥፋው ፡ ፍርሃትን ፡ በልቤ ፡ አሳደርህ ፤ ሽብርም ፡ በአካሌ ፡ ውስጥ ፡ ተነዛ ፤ በመጠጥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አልቆምም ፤ በገናዬንም ፡ (ለጨዋታ ፡ ) አያመጡልኝም ። በራበኝ ፡ ጊዜ ፡ ከደረቅ፡ ዳቦ፡ በቀር ፡ አልበላም ፡ ሲጠማኝም ፡ የምጠጣው፡ ውሃ፡ ብቻ፡ ነው ። ስሜን ፡ ከሰማህበት ፡ ቀን ፡ ( ስምህን ፡ ከሰማሁበት ? ) ፡ ዝምር ፡ ፍርሃት ፡ በአጥንቶቼ ፡ ውስጥ ፡ ዘለቀ ። አእምሮዬ ፡ ተቃጥሎአል ፤ ልብሶቼ ፡ ተበጣጥሰዋል ። ወደ ፡ ኔይት ፡ (የራሱ ፡ አገር ፡ የሳይስ ፡ ሴት ፡ አምላክ ፡ ቤተ፡ መቅደስ ፡ ) ሸሽቼ ፡ ተደብቄያለሁ ፡ (ተማጥኜያለሁ ።) ና ፡ ወደኔ ።

ፊትህን ፡ እኔ ፡ ወዳለሁበት ፡ መልስ ፡ የካድሁት፡ ነገር ፡ እንዳለ፡ ተመልከት ። አገልጋይ ፡ ( ወንጀለኛ ፡ ? ) በይቅርታ ፡ አይነጻምን ፡ ? ያለኝ ፡ ሁሉ ፤ ወርቅና ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ በመልካም ፡ ዕቃ ፡ ያጌጡት ፡ ፈረሶቼ ፡ ሁሉ ፡ ይወሰዱ ፤ ወደ ፡ ግምጃ ፡ ቤትህም ፡ ይግቡ። ፍርሃትን ፡ ከልቤ ፡ የሚያጠፋ ፡ መላክተኛ ፡ ይላክልኝ ፤ ከርሱም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሔጄ ፡ ቅዱስ ፡ መሐላዬን ፡ ልፈጽም ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሲሰማ ፡ ፒያንኪ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዋና ፡ ተፎካካሪ ፡ ጠላቱ ፡ ሲወድቅለት ፡ ደስታ ፡ ቢሰማው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ እንደርሱ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ የነበረው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተሸንፎ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡ ለመጻፍ ፡ መገደዱ ፡ ሳያሳዝነው ፡ አይቀርም ። ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ እኔም ፡ ዘንድ ፡ ይምጣ ፡ እምቢ ፡ ካለም ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ውጊት ፡ ብሎ ፡ ያላዘዘውም ፡ ስለዚህ ፡ ይሆናል ። ቢሆንም ፡ የዘውድና ፡ የግዛት ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ርኅራኄው ፡ ሰፊ ፡ ሲሆን ፡ አይችልምና ፡ ፒያንኪ ፡ የታፍናቅትን ፡ መልእክት ፡ እንደሰማ፡ ለመሐላው ፡ አፈጻጸም ፡ ትልቁን፡

ሊቀ ፡ ካህን ፡ ፔታምኔስቶ ፡ የሚባለውን ፤ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ የሚረከብ ፡ የጦር ፡ አለቃውን ፡ ፑአርማን ፡ ባንድነት ፡ ላካቸው ። ታፍኔቅታም ፡ እነሱን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ወርቁንም ፡ ብሩንም ፡ ልብሱንም ፡ ጌጡንም ፡ መሣሪያውንም ፡ ሁሉ ፡ በያይነቱ ፡ ከአስረከባቸው ፡ በኋላ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሄዶ ፡ የአምላኩን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ማለ ፤ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ አልጥስም ፡ ከቃሉም ፡ አልፍ ፡ አልልም ። እሱም ፡ ሳይፈቅድ ፡ ማናቸውንም ፡ ሹም ፡ አልጐዳም ። እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ቃልና ፡ ትእዛዝ ፡ እፈጽማለሁ ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ታሪኩ ፡ ባይጠቅሰው ፡ ታፍኔቅታ ፡ ለፒያንኪ ፡ እየገበረ ፡ በዚያው ፡ በጥንታዊ ፡ ግዛቱ ፡ በሳይንስ ፡ ብቻ ፡ ሊቀመጥ ፡ ድርድር ፡ አቅርቦ ፡ ፒያንኪም ፡ ይኸንኑ ፡ ፈቅዶ ፡ የተስማሙ ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በመሐላው ፡ ላይ ፡ እሱ ፡ ሳይፈቅድ ፡ ማናቸውንም ፡ ሹም ፡ አልጐዳም ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ምናልባት ፡ የፒያንኪ ፡ ሹማምንት ፡ ለግብር ፡ አገባበርና ፡ ለመቆጣጠርም ፡ በውስጡ ፡ እንዲቀመጡ ፡ የተደረገ ፡ ይመስላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ፒያንኪ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ከማንም ፡ መንግሥታት ፡ ይበልጥ ፡ የገነነውንና ፡ የሠለጠነውን ፡ አባቶቹና ፡ ወገኖቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሲገብሩለት ፡ የኖሩለትን ፡ የግብፅ ፡ መንግሥት ፡ አሸንፎ ፡ ለአገሩ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ገባር ፡ ሲያስደርግ ፡ በሕይወቱ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ ፈጸመ ፡ ማለት ፡ ነው ። ታፍኔቅታ ፡ እሜን ፡ ብሎ ፡ ሲገብር ፡ በግብፅ ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ ፒያንኪን ፡ ሊቃወም ፡ የሚነሣ ፡ አልተገኘም ። አገሩ ፡ በሙሉ ፡ በፒያንኪ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሆነ ። ታሪኩ ፡ ራሱ ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ አጻጻፍ ፡ ምን ፡ እንደሚል ፡ እንመልከት ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ የምሥራቁም ፡ የምዕራቡም ፡ የሰሜኑም ፡ የደቡቡም ፡ አገር ፡ ከተገዛለት ፡ በኋላ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ሁለት ፡ ነገሥታት ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ሁለት ፡ ነገሥታት ፡ አራቱም ፡ (ከዚህ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡) ግራና ፡ ቀኝ ፡ የሁለት ፡ አባብ ፡ ምልክት ፡ ያለበትን ፡ ዘውዳቸውን ፡ እንደደፉ ፡ ለግርማዊነቱ ፡ መንፈስ ፡ ለመስገድ ፤ ግርማ ፡ ሞገሱን ፡ ለማየት ፡ ወደፒያንኪ ፡ መጡ ። እነሱም ፡ ሲራመዱ ፡ ቅልጥማቸው ፡ እንደሴት ፡ ቅልጥም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በግርማዊነቱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተከለከለውን ፡ ዓሣ ፡ በመብላት ፡ የረከሱ ፡ ስለሆኑ ፡ ፎቱ ፡ ወደ ፡ ግርማዊነቱ ፡ አዳራሽ ፡ አልገቡም ። ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ነምሩድ ፡ ብቻ ፡ ዓሣ ፡ የማይበላ ፡ ንጹሕ ፡ ስለነበረ ፡ መግባት ፡ ተፈቀደለት ።

የድል ፡ አድራጊነቱን ፡ ሥራ ፡ አከናውኖ ፡ ሲጨርስ ፡ ነገሥታቱንና ፡ መሳፍንቱንም ፡ አነጋግሮ ፡ በየሥራቸው ፡ ደልድሎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ሲመለስ ፡ የሆነውንም ፡ የጉዞ ፡ ታሪክ ፡ በሐውልቱ ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ የተተረጐመው ፡ ይኸው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ይቀጥላል ።

ፒያንኪ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ያለውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የሶርያንም ፡ ሀብት ፡ ልብስና ፡ ጌጥ ፡ ቆዳ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ በመርከቡ ፡ አስጭኖ ፡ ጉዞውን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ዠመረ ። ልቡ ፡ በደስታ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ። ከምዕራብ ፡ እስከ ፡ ምሥራቅ ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ተደስቷል ። ንጉሥ ፡ በነበረበትም ፡ አገር ፡ (ናፓታ) ፡ አስቀድሞ ፡ እንደተዘጋጀው ፡ የደስታ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት ። ተቀባዮቹም ፡ እንደዚህ ፡ እያሉ ፡ በደስታ ፡ ጮሁ ፡ «ድል ፡ አድራጊው ፡ ንጉሥ ፡ መጣህ ፡ ግዛትህ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ተዘረጋ ፡ ወንዶችን ፡ እንደሴት ፡ አደረግኻቸው ። አሁን ፡ ደስታ ፡ ይኸን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ወለደችው ፡ እናት ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። እሱም ፡ በአን ፡ (መንበረ ፡ አሞን) ፡ የሚቀመጥ ፡ (አሞን) ፡ ሕይወት ፡ ሰጠህ ፡ ክብርም ፡ ያንተ ፡ ነው ። ይኸን ፡ ኮርማ ፡ የወለደች ፡ ላም ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ ቴባይድን ፡ የምትወድ ፡ ሥልጣንህና ፡ ኃይልህ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ። አንተም ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ትኖራለህ »

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ በሁለት ፡ ቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ቃሎች ፡ እንዚያው ፡ በሐውልቱ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ሲሆኑ ፡ ባንድ ፡ ቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ ለመግለጫ ፡ የተቀነፉትና ፡ በፍጹም ፡ ያልተቀነፉት ፡ ቃላት ፡ የራሴ ፡ አስተያየትና ፡ አገላለጽ ፡ መሆናቸውን ፡ አመለክታለሁ ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በሐውልቱ ፡ የተገኘው ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪኩን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ይፈጽማል ። ፭፻ ፡ ዓመት ፡ እንደሌሎቹም ፡ ፯፻ ፡ ዓመት ፡ አገሩን ፡ ኢትዮጵያን ፡ (ኑብያን) ፡ እየወጉ ፡ ያስገበሩትን ፡ የኃያላኑ ፡ ፈርዖኖች ፡ የነቱትሞሲስን ፡ የነራምሲስን ፡ ፎኛውን ፡ አገር ፡ ታላ

ቂቱን ፡ ግብፅን ፡ ፒያንኪ ፡ የኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አስገብሮ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጨመራት ። የታላላቆቹ ፡ ከተሞች ፡ የመምፊስና ፡ የቴብ ፡ ክብር ፡ ወደናፓታ ፡ ዞረ ። የፈርዖኖቹን ፡ ልጆች ፡ ለርሱና ፡ ለተከታዮቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንዲገብሩ ፡ አደረጋቸው ።

ፒያንኪ ፡ በሐሳቡ ፡ ጥብቅ ፡ የጦር ፡ መላ ፡ አዋቂ ፡ የጐበዞች ፡ መሪ ፡ መሆኑ ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ ሲታወቅ ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ የግድ ፡ እምቢ ፡ ብሎ ፡ ተጋፍቶ ፡ ከተዋጋው ፡ በቀር ፡ የሰውን ፡ ደም ፡ በከንቱ ፡ ማፍሰስ ፡ የማይወድ ፤ የማንኛውም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ሲቀንስ ፡ የሚያዝን ፡ ሰው ፡ ስለነበረ ፤ የገበሩለትን ፡ ነገሥታትና ፡ መሳፍንት ፡ ሳይቋድልም ፡ ሳያስርም ፡ ሁሉንም ፡ በየአባት ፡ አገራቸው ፡ ምስፍናቸውን ፡ እያጸደቀ ፡ ተዋቸው ። ዋናውን ፡ ጠላቱን ፡ ታፍኔቅታን ፡ እንኳ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ተዋግቶ ፡ በመጨረሻ ፡ አሳዛኝ ፡ የምሕረት ፡ ቃል ፡ በመላከተኛ ፡ እጅ ፡ ከላከበት ፡ በኋላ ፡ የጠየቀውን ፡ ከመፈጸም ፡ በቀር ፡ ሄጀ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ላጥፋው ፡ ወይም ፡ እፊቱ ፡ ቀርቦ ፡ እጅ ፡ ይንሣኝ ፡ ማለቱ ፡ በታሪካዊው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ የለም። ፈርቶ ፡ ነው ፡ እንዳይባልም ፡ ለጊዜው ፡ በፒያንኪ ፡ ፊት ፡ በግብፅ ፡ የሚመከት ፡ እንዳልነበረ ፡ ተረጋግጧል ። ታፍኔቅታም ፡ ጨርሶ ፡ ድል ፡ መሆኑን ፡ ባይረዳውና ፡ የመቃወሚያ ፡ ቂንሽ ፡ ተስፋ ፡ ቢኖረው ፡ ኖሮ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ አሳዛኝ ፡ የምሕረት ፡ ቃል ፡ ለመላክና ፡ ተገዥነቱን ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ በመሐላ ፡ ለማረጋገጥ ፡ አይገደድም ፡ ነበር ። ፒያንኪ ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ፡ ናፓታ ፡ ከተመለሰ ፡ ወዲህ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ግብፅን ፡ ከመውረሩ ፡ በፊት ፡ ፳፩ ፡ ዓመት ፡ በድምሩ ፡ ፴፩ ፡ (እንደ ፡ ግማሾቹ ፡ ፴፱ ፡) ዓመት ፡ ያህል ፡ ከ፯፻፶፩ ፡ እስከ ፡ ፯፻፳፩ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ድረስ ፡ ገዝቶ ፡ ሞተ ፡ በመንግሥቱም ፡ ሰጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አማቹ ፡ ካሽታ ፡ ከተከተለው ፡ ወዲህ ፡ በኑብያና ፡ በግብፅ ፡ ግዛት ፡ ሻባቃ ፡ ነገሠ ።

ፒያንኪን ፡ የመሰለ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ከመሔዱ ፡ በፊትና ፡ ተመልሶም ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ግብፅን ፡ በገዛበት ፡ ጊዜ ፡ የሠራው ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ በጽሑፍ ፡ ስላልተገኘ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማግባት ፡ አልቻልንም ።



በዚህ ፡ መካከል ፡ ቂንሽ ፡ ላንባቢ ፡ ላስታውስ ፡ የምፈልገው ፡ ስለዘመኑ ፡ አነጋገርና ፡ አጻጻፍ ፡ ነው ።

በፊት ፡ ዳግማዊ ፡ ራምሲስ ፡ ወደ ፡ ሶርያና ፡ ወደ ፡ ፓለስቲን ፡ የዘመተ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቹ ፡ ሸሽተውበት ፡ እርሱ ፡ ብቻውን ፡ ተጋጠመ ፡ ከሚለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ አምላኩን ፡ አሞንን ፡ እንደምን ፡ እንደለመነው ፡ አሞን ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ መልስ ፡ እንደሰጠው ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ፒያንኪ ፡ ለነምሩድና ፤ ለታፍኔቅት ፡ የሚልከው ፡ ወታደሮቹን ፡ ተዋጉ ፡ ብሎ ፡ ሲልክ ፡ የተናገረው ፡ ወታደሮቹና ፡ ታፍኔቅት ፡ ለርሱ ፡ የሚሰጡት ፡ ያነጋገር ፡ ሁኔታ ፡ ልክ ፡ እስራኤሎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ወይም ፡ ከእውነተኛው ፡ አምላካቸው ፡ ጋር ፡ ከሚያደርጉት ፡ ንግግርና ፤ ጸሎት ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላል ። የግብፅ ፡ ፈርዖኖችና ፡ የጣዖት ፡ ካህናት ፡ ለአማልክቶቻቸው ፡ የሚያቀርቡት ፡ የጸሎትና ፡ የልመና ፡ የንግግር ፡ ቅርጽ ፡ የእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ እነዳዊት ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከሚያቀርቡት ፡ ንግግር ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይነቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የፒያንኪና ፡ የታኒከታን ፡ አነጋገር ፡ የመሰለ ፡ በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ይገኛል ።

እስራኤሎች ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ በግብፅ ፡ ሲኖሩ ፡ የግብፅን ፡ ሥልጣኔ ፡ አጻጻፍና ፡ አነጋገር ፡ መውረሳቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በተለይ ፡ የእስራኤሎች ፡ የመዠመሪያው ፡ መሪ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ጽፎ ፡ የሰጣቸው ፡ ሙሴ ፡ በዳግማዊ ፡ ራምሲስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የፈርዖኑ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ እየተባለ ፡ የግብፆችን ፡ ማናቸውንም ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ እየተማረ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ ሕጉንና ፡ ሥርዓቱን ፡ እርሱም ፡ ሌሎችም ፡ ሊቃውንት ፡ እነአሮን ፡ ከግብፅ ፡ የወረሱትን ፡ ዕውቀት ፡ ለወገኖቻቸው ፡ ለእስራኤል ፡ ሰጥተው ፡ ይህ ፡ ዕውቀት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡ ደርሶ ፡ ይሠራበት ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ የኢትዮጵያዊው ፡ የፒያንኪ ፡ ያባቶቹና ፡ የተከታዮቹ ፡ ሥልጣኔና ፡ ልማዳቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ሃይማኖታቸው ፡ ንግግርና ፡ አጻጻፋቸው ፡ በሙሉ ፡ የግብፆች ፡ መሆኑ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ የናፓታና ፡ የመርዌ ፡ ነገሥታት ፡

በግብፃውያን ፡ የጣዖት ፡ አማልክት ፡ በነአሞን ፡ በነፕታህ ፡ ማምለክ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ነገሥታቱ ፡ ለአማልክቱ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ እየሆኑ ፡ የሠሩትን ፡ በአሪት ፡ እንደሚያምኑ ፡ እውነተኛውን ፡ እግዚአብሔርን፡ እንደሚያመልኩ ፡ አድርገው፡ያገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ የጻፉት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ «የኢትዮጵያ፡ ነገሥታት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ እያመኑ ፡ እውነተኛውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያምኑ ፡ ነበር» ፡ እየተባለ ፡ ይነበባል ። ይኸንንም ፡ የናፓታንና ፡ የመርዌን ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ ከማጥናቴ ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ እምን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምናልባት ፡ ዛሬ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ በሰሜን ፡ ወይም ፡ በበጌምድር ፡ ግዛት ፡ እንደሚገኙት ፡ ፈላሾች ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ የነዚህ ፡ አባቶች ፡ ከእስራኤል ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ እያመኑ ፡ ባንዱ ፡ ክፍል ፡ እንዳንድ ፡ ነገድ ፡ ሆነው ፡ ተቀምጠው ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ሕዝቡ ፡ ከነንጉሡ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በአሪት ፡ ሕግና ፡ በእውነተኛው ፡ አምላክ ፡ የማያምኑ ፡ መሆናቸውን ፡ የሐውልቱም ፡ የብራናውም ፡ (ፓፒሩስ) ፡ ጽሑፍ ፡ ያስረዳል ። ያንዳንዶቹ ፡ ስም ፡ አስተርካሚን ፤ አርድ ፡ አሚን ፤ አሚን ፡ አስሮ ፤ አርክአሚን ፡ ሲል ፡ የአሞን ፡ « አሚን » ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አገልጋይነታቸውንና ፡ የዚህ ፡ ጣዖት ፡ ፍቅረኛ ፡ መሆናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ። እንኳን ፡ እነርሱ ፡ የመዠመሪያ ፡ ካማዊ ፡ ንጉሥ ፡ የምናደርገው ፡ ሰፕታህ፡ የሚባለው ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ዋነኛ ፡ አምላክ ፡ በፕታህ ፡ የሚያምን፡ መሆኑ ፡ ስሙ ፡ ያስረዳል ።

አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ እንተውና ፡ ወደ፡ ታሪኩ ፡ እንመለስ ።

ፒያንኪ ፡ ከግብፅ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ከመምፊስ ፡ ከተመለሰ፡ ወዲህ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ (እንደ ፡ ግማሾቹ ፡ ፲፱) ፡ ግብፅን ፡ ከመውረሩ፡ በፊት ፡ በናፓታ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ በመደረብ ፡ ፰ ፡ ዓመት ፡ በድምሩ ፡ ፴፩ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ከ፯፻፵፩ ፡ እስከ ፡ ፯፻፰ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ገዝቶ ፡ ሞተ ።

በመንግሥቱ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ፡የእኅቱ ፡ ባል ፡ አማቹ ፡ ካስሀታ ፡ ከተከተለው ፡ በኋላ ፡ በኑብያና ፡ በግብፅ ፡ መንግሥት ፡ ሻባቃ ፡



ነገሠ ። ፒያንኪን ፡ የመሰለ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ከመዝመቱ ፡ በፊት ፡ ከግብፅም ፡ ተመልሶ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ የሥራው ፡ ዝርዝር ፡ ታሪኩ ፡ በጽሑፍ ፡ ስላልተገኘ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የቀረውን ፡ ታሪኩን ፡ ለማግባት ፡ አልቻልንም ። ነገር ፡ ግን፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ለተጻፈው ፡ ታሪኩ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ የድሉ ፡ ታሪክ ፡ የተጻፈበትን ፡ ታሪክ ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ተፈላልገው ፡ ያገኙትን ፡ ሙሴ ፡ ማሪዬትን ፡ በመተርጐምና ፡ በማብራራት ፡ የደከሙትን ፡ ሙሴ ፡ እማኑኤል ፡ ደሩዠን ፤ ሙሴ ፡ ብሩግሽን ፡ ሳናመሰግን ፡ ማለፍ ፡ አይገባንም ፡ (፩) ።

CITY - HALL LIBRA
of
ADDIS ABABA

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

የሻባካ ፡ (ሰባቆን) ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

የሻባካና ፡ የቦኮንራፍ ፡ (ቦኮሪስ) ፡ ጦርነት — እፍ ፡ አውጥቶ፡ የተናገረው ፡ በግ— የጣዖቱ ፡ ኮርማ ፡ በሬ ፡ ከተራ ፡ ኮርማ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንደ ፡ ተሸነፈ ።

ፒያንኪ ፡ በፊት ፡ ዙፋኑን ፡ ለመውረስ ፡ የሚችል ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ስለአልነበረውና ፡ ሚስቱ ፡ እርጉዝ ፡ ስለነበረች ፡ እንደታመመ ፡ ለልጁ ፡ ባል ፡ ለካሽታ ፡ ( ካስሀታ ) ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ተናዘዘ ፡ ይላሉ ። «ሚስቴ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡ እንደሆነ ፡ ልጄ፡ አልጋዬን ፡ ባንተ ፡ ሞግዚትነት ፡ ይውረስ ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ያልወለደች ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ከልጄ ፡ የምትወልዳቸው ፡ ልጆችህ፡ ልጆቼ ፡ ናቸውና ፡ መንግሥቴን ፡ ላንተ ፡ ሰጥቼሃለሁ» ፡ አለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፒያንኪ ፡ በሞተ ፡ በ፲፩ኛው ፡ ቀን ፡ ሚስቱ ፡ ወንድ፡ ልጅ ፡ ወለደችለትና ፡ ስሙ ፡ አክሱማይ ፡ ተብሎ ፡ በሕፃንነቱ ፡ ነገሠና ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በካሽታ ፡ ሞግዚትነት ፡ እንደገዛ ፡ በወጣትነት ፡ ጊዜው ፡ በድንገት ፡ ስለሞተ ፡ የፒያንኪ ፡ የልጁ ፡ ባል ፡ መንግሥትን ፡ ያዘ ፡ ይላሉ ።

---

(፩) VICOMPTE DE ROUGE – STEL DU ROI ETHIOPIEN. PIANKI – MERIAMEN ገጽ ፡ ፩ ፡— ፶ ፡

በግብፃውያን ፡ የጣዖት ፡ አማልክት ፡ በነአሞን ፡ በነፕታህ ፡ ማም ለክ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ነገሥታቱ ፡ ለአማልክቱ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ እየሆኑ ፡ የሠሩትን ፡ በአሪት ፡ እንደሚያምኑ ፡ እውነተኛውን ፡ እግ ዚአብሔርን፡እንደሚያመልኩ ፡ አድርገው፡ያገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ከቀድሞ ፡ ዝምሮ ፡ የጻፉት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ «የኢትዮጵያ፡ነገ ሥታት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ እያመኑ ፡ እውነተኛ ውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያምኑ ፡ ነበር» ፡ እየተባለ ፡ ይነበባል ። ይኸ ንንም ፡ የናፓታንና ፡ የመርዌን ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ ከማጥናቴ ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ አምን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምናልባት ፡ ዛሬ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ በሰሜን ፡ ወይም ፡ በበጌምድር ፡ ግዛት ፡ እንደሚገኙት ፡ ፈላሾች ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ የነዚሀ ፡ አባቶች ፡ ከእስራኤል ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ እያመኑ ፡ ባንዱ ፡ ክፍል ፡ አንዳንድ ፡ ነገድ ፡ ሆነው ፡ ተቀምጠው ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ሕዝቡ ፡ ከንጉሡ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በኦሪት ፡ ሕግና ፡ በእውነተ ኛው ፡ አምላክ ፡ የማያምኑ ፡ መሆናቸውን ፡ የሐውልቱም ፡ የብራና ውም ፡ (ፓፒሩስ) ፡ ጽሑፍ ፡ ያስረዳል ። ያንዳንዶቹ ፡ ስም ፡ አስተር ካሚን ፤ አርድ ፡ አሚን ፤ አሚን ፡ አስሮ ፤ አርክአሚን ፡ ሲል ፡ የአ ሞን ፡ « አሚን » ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አገልጋይነታቸውንና ፡ የዚሀ ፡ ጣዖት ፡ ፍቅረኛ ፡ መሆናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ። እንኳን ፡ እነ ርሱ ፡ የመዠመሪያ ፡ ካማዊ ፡ ንጉሥ ፡ የምናደርገው ፡ ስፕታህ፡ የሚ ባለው ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ዋነኛ ፡ አምላክ ፡ በፕታህ፡የሚያምን፡ መሆኑ ፡ ስሙ ፡ ያስረዳል ።

አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ እንተውና ፡ ወደ፡ ታሪኩ ፡ እንመለስ ።

ፒያንኪ ፡ ከግብፅ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ከመምፊስ ፡ ከተመለሰ፡ ወዲህ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ (እንደ ፡ ግማሾቹ ፡ ፲፪) ፡ ግብፅን ፡ ከመውረሩ፡ በፊት ፡ በናፓታ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ በመደረብ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ በድምሩ ፡ ፴፭ ፡ ዓመት ፡ ያሀል ፡ ከ፯፻፵፭ ፡ እስከ ፡ ፯፻፳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ገዝቶ ፡ ሞተ ።

በመንግሥቱ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ፡የእኅቱ ፡ ባል ፡ አማቹ ፡ ካስሀታ ፡ ከተከተለው ፡ በኋላ ፡ በኑብያና ፡ በግብፅ ፡ መንግሥት ፡ ሻባቃ ፡ ነገሠ ። ፒያንኪን ፡ የመሰለ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ከመዝመቱ ፡ በፊት ፡ ከግብፅም ፡ ተመልሶ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ በገዛበት ፡ ዘመን ፡ የሠራው ፡ ዝርዝር ፡ ታሪኩ ፡ በጽሑፍ ፡ ስላልተገኘ ፡ በዚህ ፡ መጽ ሐፍ ፡ የቀረውን ፡ ታሪኩን ፡ ለማግባት ፡ አልቻልንም ። ነገር ፡ ግን፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ለተጻፈው ፡ ታሪኩ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ የድሉ ፡ ታሪክ ፡ የተጻፈበትን ፡ ታሪክ ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ተፈላልገው ፡ ያገኙ ትን ፡ ሙሴ ፡ ማሪዬትን ፡ በመተርጐምና ፡ በማብራራት ፡ የደከሙ ትን ፡ ሙሴ ፡ አማኑኤል ፡ ደሩዠን ፤ ሙሴ ፡ ብሩግሽን ፡ ሳናመሰ ግን ፡ ማለፍ ፡ አይገባንም ፡ (፩) ።



CITY - HALL LIBRAR
of
ADDIS ABABA

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

የሻባካ ፡ (ሰባቆን) ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

የሻባካና ፡ የቦኮንራፍ ፡ (ቦኮሪስ) ፡ ጦርነት — አፍ ፡ አውጥቶ፡ የተናገረው ፡ በግ— የጣዖቱ ፡ ኮርማ ፡ በሬ ፡ ከተራ ፡ ኮርማ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንደ ፡ ተሸነፈ ።

ፒያንኪ ፡ በፊት ፡ ዙፋኑን ፡ ለመውረስ ፡ የሚችል ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ስለአልነበረውና ፡ ሚስቱ ፡ እርጉዝ ፡ ስለነበረች ፡ እንደታ መመ ፡ ለልጁ ፡ ባል ፡ ለካሽታ ፡ ( ካስሀታ ) ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ተና ዘዘ ፡ ይላሉ ። «ሚስቴ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡ እንደሆነ ፡ ልጄ፡ አልጋዬን ፡ ባንተ ፡ ሞግዚትነት ፡ ይውረስ ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ያልወ ለደች ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ከልጄ፡ የምትወልዳቸው ፡ ልጆችህ፡ ልጆቼ ፡ ናቸውና ፡ መንግሥቴን ፡ ላንተ ፡ ሰጥቼሃለሁ» ፡ አለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፒያንኪ ፡ በሞተ ፡ በ፲፭ኛው ፡ ቀን ፡ ሚስቱ ፡ ወንድ፡ ልጅ ፡ ወለደችለትና ፡ ስሙ ፡ አክሱማይ ፡ ተብሎ ፡ በሕፃንነቱ ፡ ነገሠና ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በካሽታ ፡ ሞግዚትነት ፡ እንደገዛ ፡ በወጣት ነት ፡ ጊዜው ፡ በድንገት ፡ ስለሞተ ፡ የፒያንኪ ፡ የልጁ ፡ ባል ፡ መን ግሥትን ፡ ያዘ ፡ ይላሉ ።

---

(፩) VICOMPTE DE ROUGE – STEL DU ROI ETHIOPIEN. PIANKI – MERIAMEN ገጽ ፡ ፩ — ፺ ፡

ከሂዬሮግሊፍ ፡ ጽሑፍ ፡ ግን ፡ እስካሁን ፡ የአክሱማይን ፡ መንግሥ ፡ የሚናገር ፡ አላየሁም ። የካሽታ ፡ ንጉሥነት ፡ ግን ፡ በትክክል ፡ ይገኛል ። እንደዚሁም ፡ ይህ ፡ ካሽታ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ፈርዖንነት ፡ የያዘውን ፡ የአሰርኮን ፡ ፪ኛን ፡ ልጅ ፡ ሻፒናፒት ፡ የምትባለዋን ፡ አግብቶ ፡ እንደነበረ ፡ በየመጽሐፉ ፡ ይገኛል (፩) ። አሜኒሪቲስ ፡ የምትባለው ፡ የታወቀችው ፡ ንግሥትና ፡ ይኸው ፡ በአርእስቱ ፡ የተጻፈው ፡ ሻባካ ፡ የካሽታ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ካሽታ ፡ የስሙ ፡ ትርጓሜ ፡ «የኩሹ» ፡ መንግሥትን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ የሚስቱ ፡ አባት ፡ ፒያንኪ ፡ ስለሞተ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ቀድሞ ፡ ለፒያንኪ ፡ የተገዙት ፡ ለርሱ ፡ እንገዛልህም ፡ ብለው ፡ እንደተዋጉት ፡ ተጽፏል ። ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የታፍናክት ፡ ልጅ ፡ በኮንራፍ ፡ በግሪኮች ፡ አጠራር ፡ (ቦኮሪስ ) ፡ የሚባለው ፡ ሌሎችን ፡ ሁሉ ፡ መሳፍንት ፡ ደምስሶ ፡ እርሱ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ የፈርዖንነቱን ፡ ዙፋን ፡ ያዘ ። ነገር ፡ ግን ፡ በየጊዜው ፡ መሳፍንት ፡ ከጉኑ ፡ ከታሕታይ ፡ ግብፅ ፤ ከላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ካሽታ ፡ ስለተነሡበት ፡ በዘመኑ ፡ ዕረፍትና ፡ ሰላም ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅና ፡ በናፓታ ፡ ካሽታ ፡ ወይም ፡ ካስሀታ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ እላይ ፡ ስሙን ፡ የጠቀስነው ፡ የታፍናክት ፡ ልጅ ፡ የ፳፬ኛው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ መሥራች ፡ የሚባለው ፡ በኮንራፍ ፡ ሁለቱም ፡ እየተዋጉ ፡ ሁለቱም ፡ ፈርዖንነቱን ፡ የያዝሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲባባሉ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ ሻባካ ፡ የሚባለው ፡ የካሽታ ፡ ልጅ ፡ የፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ በኮንራፍን ፡ ገድሎ ፡ ዋናውን ፡ የፈርዖንነት ፡ ሥፍራ ፡ ይዞ ፡ ፳፭ኛውን ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ መሠረተ ፡ እነሆ ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመለከታለን ።

ሻባካ ፡ ባለፈው ፡ እንዳመለከትነው ፡ የድል ፡ አድራጊው ፡ የፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የካሽታ ፡ ልጅ ፡ የአሚኒሪቲስ ፡ ወንድም ፡ ነው ። ታሪክ ፡ ከመጣራቱ ፡ በፊት ፡ የፒያንኪ ፡ ወንድምና ፡ ተከታይ ፡ ያደርጉት ፡ ነበር ። የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግን ፡ ሻባካ ፡ የፒያንኪ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የካሽታ ፡ ልጅነቱን ፡ ያረጋግጣሉ ፡ የሬይዝነርን ፡ የዋላስ ፡ ባጅን ፡ የካታዊን ፡ ፓሻ ፡ መጻሕፍት ፡ በየሥፍራው ፡ ተመልከት ።

(፩) COUP D'OEIL SUR LA CHRONOLOCIE DE LA NATION EGӀPT.
J. CATTAUI ገጽ ፡ ፺፮ ፡



ከርሱ ፡ በፊት ፡ ሻባካ ፡ የሚባል ፡ ስለነበረ ፡ ሻባካ ፡ ፪ኛው ፡ ተብሎ ፡ ተመድቧል ። ሬይዝነር ፡ የሚባሉት ፡ ጸሐፊ ፡ በሻባካ ፡ ላይ ፡ ኔፈርካራ ፡ የሚባል ፡ ጭማሪ ፡ ስም ፡ እንደነበረው ፡ ከነጽሑፉ ፡ አሳይተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠራበት ፡ ስሙ ፡ ይኸው ፡ ሻባካ ፡ ነው ። በግብፅ ፡ ጥንታዊ ፡ አጠራር ፡ ሻባካ ፡ ሲባል ፡ ካ ፡ ሳይጨመር ፡ ሻባ ፡ ማለት ፡ ሳባ ፡ ማለት ፡ ነው ። በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ በነርሱ ፡ አጠራር ፡ ካ ፡ ሲጨመር ፡ ዘርፍ ፡ እያያዥ ፡ ሆኖ ፡ የሻባው ፡ (የሳባው) ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። የብሩግሺን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልከት ። ይኸም ፡ ከኩሽ ፡ ወገን ፡ ካለው ፡ የሳባ ፡ ወገን ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

በስሙ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ካህናት ፡ ነገሥታት ፡ አባቶቹ ፡ «ሚይ ፡ አሙን ፡ የአሞን ፡ ወዳጅ» ፡ ይባላል ። ይኸንኑ ፡ ሻባካን ፡ የግሪኮቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ማኔቶን ፤ ሄሮዶቱስ ፤ ዲዮዶር ፤ ሳባኮስ ፡ ወይም ፡ ሳባኮን ፡ ይሉታል ። የኒቅዩ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዮሐንስ ፡ በስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ መድብር ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ሰዋኬን ፡ ንጉሠ ፡ ሕንድ ፡ ብሎ ፡ በስሕተት ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ እንዳደረገው ፡ ወደፊት ፡ እናገኘዋለን ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በአማርኛው ፡ ሶዋ ፡ በግዕዙ ፡ ሰጐል ፡ የሚለው ፡ እርሱኑ ፡ ነው (፩) ።

ነገር ፡ ግን ፡ ገብርኤል ፡ ሀኖቶ ፡ የሚባለው ፡ የግብፅ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ፪ኛ ፡ ቮሊም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱሱ ፡ ሶዋ ፡ ያለውን ፡ የደልታ ፡ መስፍን ፡ ብሎታል ፤ ቢሆንም ፡ ይህንኑ ፡ ሻባካን ፡ መሆኑ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሶዋ ፡ ያለበት ፡ ምክንያቱ ፡ የግብፆች ፡ ቃል ፡ አሰካክ ፡ ካ ፡ ሳይጨምር ፡ ሳባ ፡ ወይም ፡ ሳዋ ፡ (ዋ) ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ በመከተል ፡ ነው ።

ሻባካ ፡ ወደ ፡ ዙፋን ፡ ከመውጣቱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በነበረው ፡ ጊዜ ፡ አባቱ ፡ ካሽታ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ በሚያስተዳድርበት ፡ ዘመን ፡ ለአያቱ ፡ ለፒያንኪ ፡ እገዛልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ምሎ ፡ የነበረው ፡ ታፍኔ

(፩) ፪ኛ ፡ ነገሥት ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፩—፮

ክታ፡ ፒያንኪ፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ ለአማቹ ፡ ለካሽታ ፡ አልገዛም፡ ብሎ፡ ተነሥቶ፡ የታሕታይ፡ ግብፅን፡ ነፃነት፡ አቋቁሞ፡ ለልጁ፡ ለቦኮንራፍ፡ (ባክ፡ ኤን፡ ራንው)፡ ስለሰጠው፡ ቦኮንራፍ ፡ በአጠገቡ፡ ያሉትን፡ የደልታን፡ መሳፍንት፡ ደምስሶ ፡ ከዚህ፡ በፊት፡ እንዳልነው፡ ከካሽታ፡ ሲጋጭ፡ ኖሮ፡ አሁን፡ ወደ፡ ሻባካ፡ ዘመን፡ መንግሥት ተላለፈ ።

ቦኮንራፍ፡ (ቦኮሪስ)፡ እንደ፡ ቀድሞዎቹ ኃያላን፡ ፈርዖኖች፡ የበሜንና፡ የደቡብ፡ የላዕላይና፡ የታሕታይ፡ ግብፅ፡ ፈርዖን፡ ሳይሆን፡ ነኝ፡ እያለ፡ በታሕታይ፡ ግብፅ፡ ብቻ፡ ነግሦ ፡ በሚያስተዳድርበት፡ ዘመን፡ ሁለት፡ ጭንቅላት፡ ያለው፡ በግ፡ ተወልዶ፡ የታሕታይ፡ ግብፅን፡ ለዘለቄታ፡ መጥፋት፡ አፍ፡ አውጥቶ፡ ተናገረ፡ ይላሉ ። ይኸውም፡ ወደፊት፡ እንደምናገኘው፡ ሻባካና፡ ቦኮንራፍ፡ ተዋግተው፡ ሻባካ፡ ቦኮንራፍን፡ ከነሕይወቱ፡ ባቃጠለውና፡ ታሕታይ፡ ግብፅን፡ በወረረ፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ተፈጸመ፡ ተቆጥሯል፡ ይባላል ። የበጉ፡ ትንቢት ፡ ቢካድም ፡ ቢታመንም ፤ ከዚህ፡ ጊዜ፡ ዠምሮ፡ ታላቂቱን፡ ገናናዪቱን፡ የግብፅን፡ ግዛት፡ ድል፡ አድራጊ፡ በመፈራረቅ፡ ከኢትዮጵያውያን፡ አሶር፡ ከዚያ፡ ባቢሎንና፡ ፋርስ፡ ቀጥሎም፡ ግሪክና፡ ሮማ፡ ዓረብና፡ ቱርክ፡ እስከ ፡ ቅርብ፡ ጊዜ፡ ድረስ፡ ፈረንሳዊና፡ እንግሊዝ፡ እየተከታተሉ፡ ይገዟት፡ ዠመር ።

ቀድሞ፡ በነቱትሞሲስ፡ በነራምሲስ፡ ፪ኛ፡ ጊዜ፡ ተገዥ፡ የነበሩት፡ የአሶርና ፡ የአካባቢው ፡ (ቀድሞ፡ ኪታ፡ ሒቲቲ፡ የሚባሉት)፡ አገሮች፡ አሁን፡ ከግብፅ፡ አጥቂነት፡ ወጥተው፡ እነርሱ፡ በዙሪያቸው፡ ያለውን፡ አገር ፡ እመውረርና ፡ እማጥቃት፡ ላይ፡ መሆናቸውን፡ እንመለከታለን ። በሻባካ፡ ዘመን፡ (፯፻፲፮—፯፻፩፡ ዓመት፡ ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት)፡ አሶርን፡ ከሰልምናጽር፡ ፭ኛ፡ በኋላ፡ የነገሠው፡ ሳርጎን፡ ፪ኛ፤ ይሁዳን፡ ሕዝቅያስ፤ እስራኤልን፡ ሆሼአ፡ (ሆሴዕ)፡ ይገዙበት፡ የነበረው፡ ጊዜ፡ ነው ። ነቢዩ፡ ኢሳይያስ፡ የነበረበትም፡ ዘመን፡ ይኸው፡ ነው ።

በመዠመሪያ፡ ቦኮንራፍ፡ ታሕታይ፡ ግብፅን፡ በሚያስተዳድርበት፡ ጊዜ፡ በብልህነቱ፡ በአስተዳደሩ፡ የተመሰገነ፡ ነበር ። ነገር፡ ግን፡ ከብልህነቱ፡ የተነሣ ፡ ከዚህ ፡ በፊት፡ ለተረከነው፡ ሐፒ፡ ለሚባለው፡ የበሬ፡ ኮርማ፡ ግብፃውያኑ፡ መስገዳቸው፡ ጸጽቶት፡



ኖሮ፡ እንደ፡ አምላክ፡ የሚሰግዱለት፡ የበሬ፡ ኮርማ ፡ ከሌላው፡ በሬ፡ ምንም፡ ልዩነት፡ እንደሌለው፡ ለማስረዳት፡ ሲል፡ ሕዝብ፡ በተሰበሰበበት፡ አደባባይ፡ የሚመለከውን፡ ኮርማና፡ አንድ፡ ገርጋራ፡ ተራ፡ በሬ፡ ከውጪ፡ አስመጥቶ፡ አዋጋ ። በውጊያውም፡ ላይ፡ ገርጋራው፡ በሬ፡ የሚመለከውን ፡ ኮርማ፡ በኃይል፡ በቀንዱ፡ ወግቶ፡ ገደለው ። ይኸን፡ በመመልከት፡ እሱ፡ ተስፋ ፡ እንዳደረገው፡ የኮርማውን ፡ (የሐፒን)፡ ከንቱነት፡ በመረዳት፡ ፈንታ፡ ለዚሁ፡ አምልኮ፡ የቀናው፡ ሕዝብና፡ ይልቁንም፡ ካህናቱና፡ ነቢያቱ፡ በአምላካችን፡ ላይ፡ የሚሳለቅ፡ ከሐዲ፡ (ዓላዊ)፡ ንጉሥ፡ ነው፡ ብለው፡ እያጕረመረሙ፡ ተነሡበት ። ስለዚህ፡ ፀናፓታና፡ በላዕላይ፡ ግብፅ፡ ወዳለው፡ ወደኢትዮጵያዊው ፡ ንጉሥ ፡ ወደ፡ ሻባካ፡ ናና፡ ተበቀልልን፡ ብለው፡ ላኩበት ።

እሱም፡ በፒያንኪ፡ እግር፡ የተተካው፡ የላዕላይና፡ የታሕታይ፡ ግብፅ፡ ፈርዖን፡ ነኝ፡ ብሎ፡ ወደሰሜን፡ ዘልቆ፡ ቦኮንራፍን፡ ለማስገበር፡ የሚዘጋጅበት፡ ጊዜ፡ ነበርና፡ ይኸንንም፡ ምክንያት፡ ስላገኘ፡ ደስ፡ ብሎት፡ ከናፓታ፡ ወደ፡ ሰሜን፡ ተጓዘ ። የቀሩትም፡ መሳፍንት፡ ገብረው፡ በውስጡ፡ ስለአበሩለት፡ ከቦኮንራፍ፡ ጋር፡ ተዋግቶ፡ ከአሸነፈው፡ በኋላ፡ ማርኮ፡ ከነሕይወቱ፡ በእሳት፡ አቃጠለው፡ ይላሉ ። ያቃጠለው፡ የሚመለከውን፡ ኮርማ፡ በተራ፡ በሬ፡ አስወግቶ፡ በድፍረት፡ በማስገደሉ፡ ካህናቱ፡ « ስቀለው፡ አቃጥለው » ፡ እያሉ፡ ጮኸው፡ ይሁን፡ ወይም፡ እባትህ፡ ታፍናክህት፡ ለአያቴ፡ ለፒያንኪ ፪ኛ፡ ሊገዛ፡ በሳይስ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ በጦር፡ አለቃው፡ በፑአርማና፡ በሊቀ፡ ካህኑ፡ በፔታምኔስቶ፡ ፊት፡ ምሎ፡ የነበረውን፡ አፍርሰህ፡ ተዋጋኸኝ፡ በማለት፡ እሱው፡ ፈርዶበት፡ ይሁን፡ አይታወቅም ። ባንዳንድ፡ ጽሑፍ፡ ደግሞ፡ ቦኮንራፍ፡ ከአሶራውያን፡ ጋር፡ ሲዋጋ፡ ተማርኮ፡ ኃይለኞቹ፡ አሶራውያን፡ እንደልማዳቸው፡ በሕይወቱ፡ ቆዳውን፡ ገፈው፡ ገደሉት፡ ይላሉ (፩) ። ነገር፡ ግን፡ ለግብፅ፡ ታሪክ፡ መሠረታዊ፡ ጸሐፊ፡ የሆነው፡ ሁሉ፡ ቦኮንራፍ፡ በሻባካ፡ እጅ፡ መሞቱን፡ ያረጋግጣል ።

---

(፩) G. HANOUTEAU – HISTOIRE – DE LA NATION EGYPT. ገጽ፡ ፩፻፴፩፡

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሻባካ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ ከላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ሊቢያንም ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ግዛት ፡ ከደረበ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ናፓታ ፡ በመመለስ ፡ ፈንታ ፡ እዚያው ፡ በሰሜን ፡ ተቀምጦ ፡ ያስተዳድር ፡ ዠመር ። ስመ ፡ ጥሩዬቱን ፡ እኅቱን ፡ ንግሥት ፡ አሜኔሪቲስ ፡ (ትርጓሜው ፡ የአሞን ፡ ዓይን ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ነው ፡) የምትባለውን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶ ፡ ከሱ ፡ በታች ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ቡቴብ ፡ ላይ ፡ አነገሣት ። እሷም ፡ ብልህ ፡ ኃይለኛ ፡ ስለነበረች ፡ በርሱና ፡ ከርሱ ፡ ቀጥለው ፡ በነገሡት ፡ ፫ ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ እንደሞግዚት ፡ ሆና ፡ መላውን ፡ ግብፅን ፡ አስተዳድራለች ።

በአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ የነበራት ፡ መንፈሳዊ ፡ ( ቤተ ፡ ክህነታዊ) ፡ ሥልጣን ፡ በቴብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለነበረ ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ንግሥት ፡ ከመባል ፡ ጋር ፡ የአሞን ፡ ታላቂቱ ፡ ካህኒት ፡ ትባል ፡ ነበር ። ሻባካ ፡ ለእኅቱ ፡ ትልቅ ፡ ሥልጣን ፡ በቴብ ፡ ሰጥቶ ፡ እርሱ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ኃያላን ፡ ፈርዖኖች ፡ በገናንነት ፡ ያስተዳድር ፡ ዠመር ። በዘመኑ ፡ ብዙ ፡ ሐውልትና ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አሠራ ፤ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ብዙ ፡ መሳፍንት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እየተነሡ ፡ የፈርዖንነቱን ፡ ዙፋን ፡ ለመያዝ ፡ ባደረጉት ፡ ጦርነት ፡ የፈረሰውን ፡ ሁሉ ፡ እየጠገነና ፡ እያሳደሰ ፡ አቋቋመ ። ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጠውን ፡ የውሃ ፡ ቦይና ፡ ግድብ ፡ መንገድ ፡ በማሠራት ፡ ተመሰገነ ።

በሕግና ፡ በዳኝነት ፡ ረገድ ፡ በሙሉ ፡ አልተጻፈለትም ፡ እንጂ ፡ የሠራው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ይኸን ፡ ንጉሥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትሁት ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ የተተረጐመው ፡ የዮሐንስ ፡ መደብር ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲፰ኛው ፡ ክፍል ፡ ያነሣዋል ። ስሙን ፡ እንደግብፆቹ ፡ ሻባካ ፡ እንደግሪኮቹ ፡ ሳባኮን ፡ ወይም ፡ ሳባኮስ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ሰዋኬን ፡ ይለዋል ፤ የኑብያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ በማለት ፡ ፈንታም ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ብሎታል ። የነገሠበትንም ፡ ዘመን ፡ ፲፮ቱን ፡ ዓመት ፡ ፶ ፡ ዓመት ፡ አድርጎታል ። ይኸንንም ፡ ፶ ፡ ዓመት ፡ መንገሡን ፡ መሠረት ፡ ያደረገው ፡ የሄሮዱቱስን ፡ መጽሐፍ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የዮሐንስ ፡ መደብርን ፡ መጽሐፍ ፡ ከግዕዝ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ የተ



ረጐሙት ፡ ሙሴ ፡ ዞቴንቤርግ ፡ እርሱ ፡ በስሕተት ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ያለውን ፡ በቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ብለው ፡ አርመውታል ።

ይኸንንም ፡ ከአስረዳን ፡ በኋላ ፡ በዮሐንስ ፡ መደብር ፡ ስለሻባካ ፡ የተጻፈውን ፡ በቀጥታ ፡ ከግዕዙ ፡ እንመልከት ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ (፩) ነግሠ ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ግብፅ ፡ ሰዋኬን ፡ ንጉሠ ፡ ሕንድ ፡ ፶ ፡ ዓመተ ፡ ወኮነ ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፤ ወኢይፈቅድ ፡ ከዒወ ፡ ደም ፡ በዓመፃ ። ወውእቱ ፡ አንበረ ፡ ሕገ ፡ በምስር ፡ ከመዝ ፤ ኵሎ ፡ ዘይኤብስ ፡ ኢይሙት ፡ ወኢይቅትልዎሙ ፡ ባሕቱ ፡ ይሕየው ፡ ወኵሉ ፡ ለለ ፡ ፩ ፩ ፡ ከመ ፡ አበሳሁ ፡ አዘዘ ፡ ይኩስትሩ ፡ ምድረ ፤ ወያስተጋብኡ ፡ መሬተ ፡ ወይደዩ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ። ወሶበ ፡ ጐንደዩ ፡ በዝንቱ ፡ ምንዳቤ ፡ ወበዝ ፡ ኂዋዌ ፡ ርኁቀ ፡ ማያተ ፡ ፈለግ ፡ እምነ ፡ ምድር ። ወረሰዩ ፡ ሀገሮሙ ፡ መልዕልተ ፡ በእንተ ፡ ፍርሃተ ፡ ማያት ፡ ከመ ፡ ኢይስጠሙ ። ወበመዋዕሊሁ ፡ ቅድመ ፡ ለሳሶጦትሪትም ፡ (፪) ። ኮኑ ፡ ማያት ፡ ያስጥሙ ፡ እምቅድመ ፡ ይክርዩ ፡ ምድረ ፡ ለፈለግ ፡ ወዘገብሩስ ፡ ውዲየ ፡ መሬት ፡ ላዕለ ፡ ማይ ፡ ኢተፈጸሙ ፡ ሎሙ ፡ ሥምረቶሙ ፡ በእንተ ፡ ብዝኃ ፡ ውኂዘ ፡ ፈለግ ። ወሰዋኬንስ ፡ ንጉሠ ፡ ሕንድ ፤ ረሰየ ፡ ሎሙ ፡ ማኅደረ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ልዑል ፡ በትዓሕተ ፡ ልብ» ፡ ትርጓሜው ፡ ባጭሩ ፡ «ሻባቃ ፡ በግፍ ፡ የሰው ፡ ደም ፡ እንዲፈስ ፡ የማይፈልግ ፡ ሰውን ፡ የሚወድ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ማናቸውንም ፡ ጥፋት ፡ ያጠፋ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ውሃው ፡ እየሞላ ፡ ሰውን ፡ እንዳይወስድ ፡ (እንዳያሰጥም) ፡ የባሕሩን ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ረግረጉን ፡ አፈር ፡ እያጋዘ ፡ መሬቱ ፡ ከውሃው ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ እየደለደለ ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ መጠን ፡ በመሥራት ፡ ይቀጣ ፡ እንጂ ፡ በሞትም ፡ በሥቃይም ፡ አይቀጣ ፡ ሲል ፡ ሕግ ፡ አወጣ ። ከርሱ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ በሴስትሪስ ፡ (በኮንራፍ) ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ሕዝቦቹ ፡ ግድብ ፡ ከማበጀታቸው ፡ በፊት ፡ ማዕበል ፡ መጥቶ ፡ ያጠፋባቸው ፡ ነበር ። ከወሃው ፡ ብዛትም ፡ የተነሣ ፡ የመገደቡን ፡ አሳባቸውን ፡ ሊያከናውኑ ፡ አልቻ

(፩) ከቦኮሪስ ፡ በኋላ ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

(፪) ሴሶስትሪስ ፡ (እንደ ፡ ሄሮዱቱስ ፡ አጻጻፍ) ፡ የራምሲስ ፡ ፪ኛው ፡ ስም ፡ የነበረውን ፡ ብዙ ፡ ፈርዖኖች ፡ ይጠሩበታል ።

ሉም ፡ ነበር ። የሕንዱ ፡ (የኢትዮጵያው) ፡ ንጉሥ ፡ ለዋኬን ፡ (ሻባካ) ግን ፡ በሙሉ ፡ ልባዊ ፡ ትጋት ፡ ከፍተኛ ፡ መኖሪያ ፡ እንዲያገኙ ፡ አደረገላቸው ። ባጭሩ ፡ የሞትን ፡ ቅጣት ፡ በሥራ ፡ ለወጠው ፡ ማለት ፡ ነው (፩) ።

ሻባካ ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የሐውልት ፤ የቤት ፤ የመንገድ ፡ የቦይ ፡ የከተማ ፡ ሥራ ፡ በአስተዳደር ፡ የሕግና ፡ የዳኝነት ፡ ደንብ ፡ ከአከናወነ ፡ በኋላ ፡ አሳቡን ፡ ግዛት ፡ ወደማስፋፋት ፡ አቀና ። አሳቡም ፡ ያረፈው ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ፈርዖኖች ፡ እነራምሲስ ፪ኛ ፡ ይገዙት ፡ ወደነበረው ፡ ወደፍልስጥኤም ፡ ወደ ፡ አሶርና ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወደ ፡ ጢሮስና ፡ ወደ ፡ ሲዶና ፡ ነው ። እነዚህን ፡ አገሮች ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ፈርዖኖች ፡ ይገዙዋቸው ፡ ከነበረ ፡ እኔ ፡ በነሱ ፡ አገር ፡ ከነገሥሁ ፡ መግዛት ፡ አለብኝ ፡ የማለት ፡ መንፈስ ፡ በርሱም ፡ በተከታዮቹም ፡ በነታሐርቃ ፡ አድሮባቸው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ የምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ በቀድሞዎቹ ፡ ፈርዖኖች ፡ ዘመን ፡ የነበሩበት ፡ የሥልጣኔ ፡ የኃይል ፡ ደረጃ ፡ በአሁኑ ፡ እነሻባካ ፡ ከደረሱበት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ከነዚሁ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ቡተለይ ፡ እንደብረት ፡ የጸናውና ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ያየለው ፡ የአሶሩ ፡ መንግሥት ፡ በነስልምናጽር ፡ በነሳርጎን ፡ እየተመራ ፡ ከተማውን ፡ በነነዌ ፡ አድርጎ ፡ በሥልጣኔ ፡ በኃይልም ፡ የገነነ ፡ ከሆነ ፡ ቆይቷል ። በሰማርያ ፡ ያለውን ፡ የእስራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ከቦ ፡ አስጨንቆታል ። የቀሩትንም ፡ ፍልስጥኤምን ፤ ፊንቂን ፤ ሞዓብን ፡ ለመያዝ ፡ እየተዘጋጀ ፡ እማስፈራራት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ግብፅንም ፡ ሳይወር ፡ አይቀርም ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ ለሻባካ ፡ በየጊዜው ፡ ስለደረሰው ፡ ሻባካ ፡ አሶርን ፡ ለመግዛት ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎችን ፡ ግዛቶች ፡ ለመፋለም ፤ ወይም ፡ ወደኔ ፡ ሳይመጣ ፡ እኔ ፡ ሄጄ ፡ ካልወደቁት ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ሆኜ ፡ ልውጋው ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የአሶርን ፡ ወረራ ፡ የፈራው ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሆሼእ ፡ ወይም ፡ ሆሴዕ ፡ ለሻባካ ፡ ርዳኝ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። እርሱም ፡ በጠላቱ ፡ በአሶር ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የጦር ፡ ኃይልና ፡ የሠራዊት ፡ ብዛት ፡ ሳያመዛዝን ፡ ከግብፅና ፤ ከኢትዮጵያም ፡ የበረከተ ፡

(፩)፤የዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ ዘተንበርግ ፡ ያሳተመው ፡ ክፍል ፡ ፲፰ ።



ጦር ፡ ሳይሰበስብ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅንና ፡ የላኩበትን ፡ አገሮች ፡ ኃይል ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ በቶሎ ፡ ሊዋጋ ፡ ሔደ ። የጦር ፡ መላ ፡ የሚያውቀው ፡ የአሶሩ ፡ ንጉሥ ፡ ሳርጎን ፡ ግን ፡ ሻባካ ፡ ከግብፅ ፡ ደርሶ ፡ አንድነት ፡ ከማበራቸው ፡ በፊት ፡ የሐማትን ፡ ንጉሥ ፡ ያውሚድን ፡ ለብቻው ፡ በቶሎ ፡ ገጠመውና ፡ ተዋግቶ ፡ ማረከው ። ከማረከው ፡ በኋላ ፡ ለመቀጣጫ ፡ እንዲሆን ፡ ሲል ፡ በሕይወቱ ፡ የሰውነቱን ፡ ቆዳ ፡ አስገፍፎ ፡ ገደለው ፡ ይባላል ። ከዚያ ፡ የፍልስጥኤሙን ፡ ንጉሥ ፡ ሐኑንና ፡ የግብፁን ፡ ፈርዖን ፡ ሻባካን ፡ በተራቸው ፡ ጦርነት ፡ ገጥሞ ፡ አሸነፋቸው ፤ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ የፍልስጥኤሙ ፡ ንጉሥ ፡ ተማረከ ። ሻባካ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ሸሽቶ ፡ ብቻውን ፡ (ባንድ ፡ እረኛ ፡ መሪነት ?) ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደቴብ ፡ ተመለሰ ። እንደተመለሰም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሳይቀመጥ ፡ በ፯፻፲፪ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሞተና ፡ በመንግሥቱ ፡ ልጁ ፡ ሻባቶካ ፡ በግሪኮች ፡ አጻጻፍ ፡ ሰቢኮስ ፡ የሚባለው ፡ ተከተለው ።

እስከ ፡ ሻባካ ፡ ድረስ ፡ በግብፅ ፡ ዙፋን ፡ የነገሡትን ፡ የሳይስ ፡ ወይም ፡ የቡባስቲ ፡ ነገሥታት ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ የ፳፬ኛ ፡ ዲናስቲ ፡ (ሥርወ ፡ መንግሥት) ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በሻባካ ፡ ጀማሪነት ፡ የኢትዮጵያውያኑን ፡ ገዥዎች ፡ ፳፭ኛ ፡ ዲናስቲ ፡ አድርገንቸዋል ። ከፒያንኪ ፡ የሚጀምሩ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፤ ወደናፓታ ፡ ከተመለሰና ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ ካሻባካ ፤ በፊት ፡ ታፍናኽትና ፡ ልጁ ፡ በኮሪስ ፡ ጣልቃ ፡ ገብተው ፡ ስለገዙና ፡ በቀጥታ ፡ ሻባካ ፡ ከፒያንኪ ፤ ገዥነትን ፡ ሳይቀበል ፡ ስለቀረ ፤ አብዛኞቹ ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ዲናስቲ ፡ መሥራች ፡ ሻባካን ፡ አድርገውታል ።

CITY - HALL LIB
of
ADDIS ABA

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

### የሻባቶካ ፡ (ሰቢኮስ ፡) ዘመነ ፡ መንግሥት ።

ታርሐቃና ፡ ሕዝቅያስ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ከአሶሩ ፡ ንጉሥ ፡ ከሰናክሬም ፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ የጦር ፡ ሠልፍ ።

ባገራችን ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ወዲህ ፡ በተደረገው ፡ ዝርዝር ፡ እንደተመለከትነው ፡ ከሻባካ ፡ ሁለተኛ ፡ ቀጥሎ ፡ ኒካንታ ፡ ቅንዳኬ ፡

የምትባል ፡ ሴት ፡ ንግሥት ፡ ሲያስከትል ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሬይዝነር ፡ ሌፕሲዩስ ፡ ሌሎችም ፡ የግብፅንና ፡ የኑብያን ፡ ታሪክ ፡ ያጠኑ ፡ ሊቃውንት ፡ ከሻባካ ፡ ሁለተኛ ፡ ሻባቶካን ፡ ልጁን ፡ እንጂ ፡ ኒካንታ ፡ ቅንዳኬ ፡ የምትባለዋን ፡ አያስከትሉም ። መቼም ፡ በና ፓታ ፡ (ኑብያ ፡) በራሱ ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ግብፅን ፡ ደርቦ ፡ በዋናው ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ከተማ ፡ በመምፊስ ፡ ተቀምጦ ፡ የገዛው ፡ ኢት ዮጵያዊና ፡ በናፓታ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በቴብ ፡ ተቀምጦ ፡ የገ ዛው ፡ ንጉሥ ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ የሆኑ ፡ ለየብቻ ፡ ባንድ ፡ ጊዜም ፡ በየተራም ፡ አሉ ። ሁልጊዜ ፡ እንደ ፡ ፒያንኪ ፡ ሁለተኛ ፡ በወረራ ፡ ታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ አሸንፎ ፡ ተመልሶ ፡ በአባቶቹ ፡ መደብ ፡ በና ፓታ ፡ ተቀምጦ ፡ ታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ ጭምር ፡ በወኪል ፡ ወይም ፡ ባገሩ ፡ መስፍን ፡ አማካይነት ፡ የሚገዛ ፡ አለ ። እንደ ፡ ሻባካ ፡ ደግሞ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ከተማ ፡ በመምፊስ ፡ ተቀምጦ ፡ የላዕ ላይ ፡ ግብፅንና ፡ የናፓታውን ፡ ለእኅቱ ፡ ወይም ፡ ለወንድሙ ፡ አለ ዚያም ፡ ለልጁ ፡ ሰጥቶ ፡ የሚያስተዳድር ፡ አለ ። ያገራችን ፡ ዝር ዝር ፡ ከሻባካ ፡ ሁለተኛ ፡ ያስከተላት ፡ ስሟን ፡ ኒካንታ ፡ ቅንዳኬ ፡ (ሕንደኬ) ፡ የሚላት ፡ በአለፈው ፡ በሻባካ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ ስሟን ፡ ያነሣው ፡ እኅቱ ፡ አሜኒሪቲስ ፡ የምትባለዋ ፡ ናት ።

የእርሷም ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ብዙዎቹ ፡ ነገሥታት ፡ ስም ፡ እየበረ ከተ ፡ አንባቢንና ፡ ጸሐፊን ፡ ማደናገሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ወንድሟ ፡ ሻባካ ፡ የላዕላይና ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ዋና ፡ ፈርዖን ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ እርሷ ፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅና ፡ በናፓታ ፡ ንግሥ ... መጫዋን ፡ በቴብ ፡ አድርጋ ፡ ትገዛ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በፊት ፡ እ... ዳልነው ፡ ሄሮዱቱስ ፡ ባለመቶው ፡ በር ፡ ከተማ ፡ ብሎ ፡ የሰየመው ... የቴብ ፡ ከተማ ፡ በዚያ ፡ የሚገኘው ፡ የካርናክ ፡ የአሞን ፡ ቤት ፡ መ... ደስ ፡ ገናና ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ስለነበረ ፡ አሜኒሪቲስ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጣ ... የላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ንግሥት ፡ ለአሞን ፡ የምትሰግድ ፡ የአሞን ፡ ታ... ቂቱ ፡ ካህን ፡ እየተባለች ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱንና ፡ የቤተ ፡ ክህ... ቱን ፡ ሥልጣን ፡ ደርባ ፡ ይዛ ፡ ስትገዛ ፡ የቆየች ፡ ናት ። እርሷንም ... አንዳንድ ፡ የቀድሞ ፡ ሊቃውንት ፡ በተለይ ፡ ያገራችን ፡ ጸሐፊዎ... በእውነተኛው ፡ እግዚአብሔር ፡ የምታምን ፡ እራታዊት ፡ ያደር... ታል ።



ነገር ፡ ግን ፡ በኑብያ ፡ በመጨረሻው ፡ ዘመን ፡ በተገኘው ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ የሚነበበው ፡ ሁሉ ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ በንግ ሥትነቷ ፡ ላይ ፡ የአሞን ፡ (ጣዖት ፡) ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ታላቂቱ ፡ ካህን ፡ እየተባለች ፡ በስምም ፡ በግብርም ፡ የዚያው ፡ ጣዖት ፡ አገል ጋይ ፡ መሆኗን ፡ እንጂ ፡ እሪታዊነቷን ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ የለም ። በርሷም ፡ ስም ፡ ቅንዳኬ ፡ ሕንደኬ ፡ የሚባሉ ፡ የሴት ፡ ነገሥታት ፡ በመርዌ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ወደፊትም ፡ በምዕራፉ ፡ በንደርስ ፡ እን መለከታለን ።

ዋናው ፡ ፈርዖንና ፡ ወንድሟ ፡ ሻባካ ፡ ከአሦሩ ፡ ንጉሥ ፡ ከሳር ጎን ፡ ሸሽቶ ፡ እንደተመለሰ ፡ መንግሥቱን ፡ ለልጁ ፡ ለሻባቶካ ፡ ሰጥ ቶት ፡ ሞተና ፡ ሻባቶካ ፡ በአባቱ ፡ እግር ፡ ተተክቶ ፡ ይገዛ ፡ ጀመር ። እንደዚሁም ፡ በሻባቶካ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ አላይ ፡ ስሟን ፡ የጠ ራነው ፡ ግብፆች ፡ አሜኒሪቲስ ፡ ግሪኮች ፡ ቅንዳኬ ፡ የኛ ፡ የግዕዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ሕንደኬ ፡ የሚላት ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ግዛቷን ፡ እንደ ፡ ቀጠለች ፡ ነው ።

ሻባቶካ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ነገሥታት ፡ ከመጠሪያው ፡ ስሙ ፡ ከሻባቶካ ፡ በቀር ፡ የክህነት ፡ ስሙ ፡ ከስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ነው ። ራ-ታት-ካው ፡ (ቲትካውራ ፡) ሲባል ፡ ግሪኮቹ ፡ ደግሞ ፡ ከሻ ባቶካ ፡ ቲንሽ ፡ ለወጥ ፡ አድርገው ፡ በቢኮስ ፡ ብለውት ፡ ይገኛል ።

አባቱ ፡ ሻባካ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ የዋናውን ፡ የፈርዖንነቱን ፡ ሥፍራ ፡ ቢያዘበት ፡ ዘመን ፡ ሻባቶካ ፡ ከአክስቱ ፡ ከአሜኒሪቲስ ፡ ጋር ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣን ፡ ሳይካፈል ፡ የቀረ ፡ አይመስልም ፤ በመጀመሪያ ፡ የነገሠውም ፡ በኢትዮጵያና ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ነበር ። በባርጎንና ፡ በሻባታ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ስለሰጣቸው ፡ በደልታ ፡ በሳይስ ፡ በመምፊስ ፡ ያሉት ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ግብፃውያን ፡ ፈርዖኖች ፡ የወረዱት ፡ የታች ኛው ፡ ግብፅ ፡ መሳፍንት ፡ ፈርዖንነትን ፡ ለመያዝ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እየተነሡ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲከራከሩ ፡ ነበር ። ባንድ ፡ ወገን ፡ የሳይሱ ፡ መስፍን ፡ የታፍናክት ፡ የልጁ ፡ ልጅ ፡ የቦከሪስ ፡ ልጅ ፡ ታፍናክት ፡ ፪ኛ ፡ ፈርዖን ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ በአገሩ ፡ አውጆ ፡ ተቀመጠ ። የ፳፫ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ ንጉሥ ፡ የነበረው ፡ የሲቲ ፡ ፪ኛ ፡ የልጁ ፡ ልጅ ፡

ደግሞ ፡ ሴቲ ፡ ፩ ፡ (እንደ ፡ ግሪኮቹ ፡ ሴቶስ ፡) የታኒስ ፡ ንጉሥ ፡ ፈር
ዖንነትን ፡ ከታፍናከት ፡ ፫ኛ ፡ ወስዶ ፡ ለራሱ ፡ ማድረጉን ፡ ባንድ ፡
ወገን ፡ አውጇዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኃይለኞችና ፡ የሥልጡኖች ፡
አገር ፡ የነበረው ፡ በኃያላን ፡ ነገሥታት ፡ በነቱትሞሲስ ፡ በነራም
ሲስ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥልጣን፡ ውስጥ ፡ ኅብረትና ፡ አንድነት ፡ የነበረው ፡
የግብፅ ፡ አገር ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ከያውራጃው ፡ ደካሞች፡ ነገሥታት፡
እየተነሡ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመዋጋትና ፡ በመፋጀት ፡ ብዙ ፡
ደም ፡ ተፋሰሱ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ትልቁ ፡ የእስራኤል ፡ ነቢይ ፡ ኢሳ
ይያስ ፡ ስለዚህ ፡ ዘመን ፡ ግብፅ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በመግ
ለጽ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ «የምሥርንም ፡ ሰዎች ፡ አውካለሁ፡ እርስ፡
በርሳቸው ፡ እስነሣለሁ ፡ ወንድም ፡ ወንድሙን፡ ይወጋል ፡ ሰውም፡
በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ ይነሣል ። አገርም ፡ ባገር ፡ ላይ ፡ መንግሥትም፡
በመንግሥት ፡ ላይ ፡ የምሥር ፡ መንፈስም ፡ ባዶ ፡ ይሆናል ፡ ምክራ
ቸውንም ፡ አጠፋለሁ ፡ ከጣዖታቸውም ፡ ይጠይቃሉ ፡ ካስማተኞቻ
ቸውም ፡ . . . ምሥርንም ፡ በጽኑ ፡ ጌታ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣ
ለሁ ፡ ጽኑ ፡ ንጉሥም ፡ ይገዛቸዋል (፩) ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሻባቶካ ፡ (ኢትዮጵያዊው ፡) በታርሐካ ፡ እየ
ተረዳ ፡ ግማሾቹን ፡ አሸንፎ ፡ የቀሩትንም ፡ እንዳሉ ፡ ባሉበት፡ አገር፡
ትቶ ፡ ከአባቱ ፡ ከሻባካ፡ የወረደለትን ፡ የፈርዖንነት ፡ ዙፋን ፡ ይዞ ፡
ያስተዳድር ፡ ገመር ። በዚህም ፡ ዘመን ፡ ያሉት ፡ ኢትዮጵያውያን፡
ፈርዖኖች ፡ እዙፋን ፡ ከወጡና ፤ የሁለት ፡ አገር ፡ ንጉሥ፡ እየተባሉ
በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በአሳባቸው ፡ የሚመጣው ፡ የቀድ
ሞዎቹ ፡ ፈርዖኖች ፡ እነ ፡ ራምሲስ ፡ ይገዙት ፡ የነበረው ፡ የታናሽ ፡
እስያ ፡ ግዛት ፡ ነው ። በነ ፡ ራምሲስ ፡ ጊዜ ፡ የአሶር ፡ መንግሥት ፡
እንደ ፡ ዛሬ ፡ ኃይለኛ ፡ ሳይሆን ፡ እንደነዚያው ፡ እንደ፡ ጉረቤቶቹ
እንደነባቢሎን ፡ እንደነ ፡ ሲዶና ፡ እንደነ ፡ ፍልስጥኤም፡ የሚቈጠር
ተራ ፡ መንግሥት ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ታሪኩን ፡ ወደፊት፡ ባንድ
ምዕራፍ ፡ እንደምንጽፈው ፡ በጣም ፡ ሥልጡን ፡ ይልቁንም ፡ ኃይ
ለኛ ፡ ሆኖ ፡ እንኳን ፡ የኢትዮጵያውያንን፡ ገዥነት፡ ሊያስገባ ፡ እሱ

---

(፩) ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ፲ ፡ ፲፱ ።



ራሱ ፡ በስልምናጽር ፡ ቀጥሎም ፡ በሳርጎን ፡ ዘመን ፡ ባጠገቡ ፡
ያሉትን ፡ መንግሥታት ፡ በሰማርያ ፡ ያለውንም ፡ የእስራኤልን ፡
መንግሥት ፡ በጦርነት ፡ ይዞ ፡ ግባር ፡ አድርጎአቸዋል ። ከሁሉም ፡
አልገባም ፡ ከግብፅ ፡ ፈርዖኖቹም ፡ አልደባለትም ፡ ብሎ፡ የነበረው፡
የይሁዳ ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ ከሰማርያ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡
ለአሶሩ ፡ መገበሩ ፡ ሳይቀር ፡ በነፃነትና ፡ በሰላም ፡ ተቀምጦ፡ ነበር፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሰላም ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ሳይረዝም ፡ እነሆ ፡
አሁን ፡ መከበብ ፡ እንደሚደርስበት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ እናነባ
ለን ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ባርጎን ፡ ሞቶ ፡ ልጁ ፡ ሰናክሬም ፡ (ሴናኬሪብ
-ቤን ፡ አኬ ፡ ሪብ )፡ በ፯፻፭ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ነግሦ ፡ በአሶር ፡ መንግ
ሥት ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጧል ። እሱም ፡ ከነጦሩ ፡ ሰፈሩን ፡ በይሁዳ ፡
መንግሥት ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም፡ አቅራቢያ ፡ በላኪሽ ፡ አድርጎ፡
፫፻ ፡ ታላንት ፡ መክሊት ፡ (፳፯፡ ኪሎ ፡) ብር ፡ ፴ ፡ መክሊት ፡ ታላ
ንት ፡ ወርቅ ፤ ገብርልኝ፡ ብሎ፡ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ላከ
በት ፡ ሕዝቅያስም ፡ ሰናክሬምን ፡ ለመውጋትና ፡ ለመመለስ ፡ የማ
ይችል ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳው ፡ ከርሱም፡ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከቤተ፡
መቅደስም ፡ አንደ ፡ ምንም ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ አጠራቅሞ ፡ የጠየ
ቀውን ፡ ግብር ፡ ላከለት ። ሰናክሬም ፡ ግን ፡ ለውጊያው ፡ ምክን
ያት ፡ አንጂ ፡ ግብር፡ ከልቡ ፡ አልፈለገ ፡ ኖሮ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ኢየሩ
ሳሌምን ፡ ለመከበብ ፡ ወደፊት ፡ ይጓዝ ፡ ገመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቅያስ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ተስፋ ፡ በመቍ
ረጥ ፡ ለግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ለሻባቶካ ፡ ርዳኝ ፡ ብሎ ፡ ልኮበት ፡ ኖሮ ፡
የግብፃውያንና ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ጦር ፡ በታርሐቃ ፡ እየተ
መራ ፡ ሕዝቅያስን ፡ ለመርዳት ፡ ወደ ፡ ፓለስቲን ፡ ተጓዘ ። ሕዝቅ
ያስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ። ይኸንንም ፡ ሲሰማ ፤ ሰናክ
ሬም ፡ ተሳልቆ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ደብዳቤ ፡ ላከበት ፡
. . . ይህ፡ የምትታመንበት፡ መጸጊያ ፡ ምንድን፡ ነው ፤ ነገርህ፡ ከንቱ፡
ነው ፤ ለመዋጋት ፡ ኃይልና ፡ ምክር ፡ አለኝ ፡ ትላለህና ፡ አሁንም ፡
በኔ ፡ ላይ ፡ ለማመጽ ፡ ትደፍር ፡ ዘንድ ፡ በማን ፡ ትታመናለህ ፤ በተ
ቀጠቀጠውና ፡ ሰው ፡ በተደገፈው ፡ ጊዜ ፡ ተሰብሮ ፡ ስንጣሪው ፡

እጅን ፡ በሚወጋው ፡ በግብፅ ፡ የሸምበቆ ፡ በትር ፡ ትታምናለህን ፡ ፈርዖን ፡ ግን ፡ የምሥር ፡ ንጉሥ ፡ ለሚታመንበት ፡ ይኸው ፡ ነው (፩) ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሕዝቅያስና ፡ ይልቁንም ፡ ከግብፅ ፡ የሔደው ፡ ታርሐቃ ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ለውጊያ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ሰናክሬምም ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ በትልቅ ፡ ትምክህትና ፡ ኵራት ፡ ታርሐቃን ፡ ለመውጋት ፡ ከላኪሽ ፡ ተነሥቶ ፡ በሠፈረበት ፡ ሌሊት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደምናገኘው ፡ እግዚአብሔር ፡ በተአምራት ፡ ቀሠፈው ።

ሰናክሬም ፡ የላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከመልእክተኞቹ ፡ እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ አነበበው ፤ ወዲያው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ፈጥኖ ፡ መጣ ። በዚያም ፡ በመቅደሱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጸለየ ፤ «እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፤ ሰማይንና ፡ ምድርንም ፡ አንተ ፡ ፈጠርህ ፡ ጆሮህን ፡ ጣል ፡ አቤቱ ፡ ስማም ፡ ዓይንህን ፡ ክፈት ፡ አቤቱ ፡ ተመልከት ፡ ሕያው ፡ አምላክነትህን ፡ ይሳደብ ፡ ዘንድ ፡ የላከውንም ፡ የሴንሄሬብንም ፡ (የሰናክሬምንም) ፡ ቃል ፡ ስማ ፤ . . . . እግዚአብሔርም ፡ የሕዝቅያስን ፡ ልመና ፡ ሰምቶ ፡ ሰናክሬምን ፡ ለማጥፋት ፡ የላከበትን ፡ ቃል ፡ ጭምር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በነበረው ፡ ነቢይ ፡ በኢሳይያስ ፡ አፍ ፡ ነገረው ። ቀጥሎም ፡ ሰናክሬም ፡ በሠፈረበት ፡ ሌሊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክተኛ ፡ መጣ ፤ ከአሶራውያንም ፡ ጭፍራ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ገደለ ፤ ማልደውም ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ሁሉም ፡ በድኖች ፡ ነበሩ ፡ . . . (፪) ።

ስለዚህ ፡ ሰናክሬም ፡ በዚሁ ፡ በደረሰበት ፡ አደጋ ፡ ተደናግጦ ፡ የተረፈውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ አሦር ፡ ተመለሰ ። በቤተ ፡ መቅደሱም ፡ ገብቶ ፡ በአምላኩ ፡ (ጣዖት) ፡ ፊት ፡ ሲጸልይ ፡ የገዛ ፡ ልጆቹ ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉትና ፡ ሞተ ። በርሱም ፡ ምትክ ፡ አግ ርሐዶን ፡ ነገሠ ።

---

(፩) ፪ኛ ፡ ነገሥት ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱ ፡— ፳፩ ።
(፪) ፪ኛ ፡ ነገሥት ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ. ፲፭ ፡— ፴፭ ።



ከሰጉበት ፡ ከሰናክሬም ፡ ውጊያ ፡ ሕዝቅያስንም ፡ ታርሐቃንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ገላገላቸው ። ሕዝቅያስም ፡ ይኸን ፡ ላደረገለት ፡ ለእሥራኤል ፡ አምላክ ፡ ምስጋናውን ፡ አቀረበ ፤ ታርሐቅና ፡ የላከው ፡ ሻባቶካም ፡ የኛ ፡ አምላክ ፡ አሞን ፡ ወይም ፡ ፕታህ ፡ ሰናክሬምን ፡ የአይጥ ፡ መንጋ ፡ ልኮ ፡ አጠፋልን ፡ ማለታቸው ፡ አልቀረም ። በነርሱ ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ሄሮዱቱስ ፡ የሚባለው ፡ የግሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ ትንሽ ፡ ለየት ፡ አድርጎ ፡ ይተርካል ። እርሱም ፡ በዘመኑ ፡ አረማዊ ፡ ወይም ፡ የግሪኮችን ፡ ጣዖታት ፡ እንዜውስን ፡ እነአርጤሚስን ፡ የሚያመልክ ፡ ስለሆነ ፡ በሰናክሬም ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ጥፋት ፡ ለግብፅ ፡ አማልክት ፡ ሰጥቶታል ፤ ቃሉን ፡ በትክክል ፡ እንመልከት ።

«ግብፅ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በፕታህ ፡ (ሔፋይስቶስ) ፡ ቄስ ፡ በሰቶስ ፡ (ሻባታካን) ፡ ትገዛ ፡ ነበር ። እሱም ፡ በሻባካ ፡ ዙፋን ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ወታደርን ፡ አይወድም ፡ ነበር ። እነሱንም ፡ እየናቀ ፡ መሬታቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ወርሶ ፡ ለሌላ ፡ ሰጥቶባቸው ፡ ነበር ። ሰናክሬም ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ተዋጉ ፡ ቢላቸውም ፡ ወታደሩ ፡ ሁሉ ፡ አልዋጋም ፡ ብሎ ፡ እምቢ ፡ አለው ። ሰናክሬምም ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ እስከሚያደርበው ፡ በር ፡ ደረሰ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሰቶን ፡ (ሻባቶካ) ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ (ፕታህ) ፡ ጸለየ ። በጸለየበትም ፡ ሌሊት ፡ አምላኩ ፡ በሕልም ፡ ተገልጾ ፡ ታሸንፋለህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወታደሩ ፡ እምቢ ፡ ስላለው ፡ በአምላኩ ፡ ተማምኖ ፡ የሱቅ ፡ ነጋዴዎችን ፡ አንጥረኞችን ፡ . . . ብቻ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ፔሉዝ ፡ ሔዶ ፡ ከሰናክሬም ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ተሰለፈ ። በማግሥቱ ፡ ሊዋጉ ፡ ሲሉ ፡ ሌሊቱን ፡ የአይጥ ፡ መንጋ ፡ በሰናክሬም ፡ ጦር ፡ ሠፈር ፡ ገብቶ ፡ ቀስትና ፡ ፍላጻቸውን ፡ ጋሻና ፡ ጦራቸውን ፡ ቀረጣጥሞ ፡ ጨረሰው ። ስለዚህ ፡ የአሶራውያን ፡ ጦር ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ሲሸሽ ፡ በየመንገዱ ፡ አለቀ ። ዛሬም ፡ ይኸ ፡ ንጉሥ ፡ በአምላኩ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አጠገብ ፡ ሐውልቱን ፡ አሠርቶ ፡ በእጁ ፡ አንድ ፡ አይጥ ፡ እንደያዘ ፡ በግርጌው ፡ «የሚመለከተኝ ፡ ጻድቅ ፡ መሆን ፡ አለበት» ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ አጽፎ ፡ ይታያል ። የሄሮዱቱስን መጽሐፍ ፡ ጂጌ ፡ (GIGUET) የተረጐመውን ፡ ከገጽ ፡ ፩፻፴፱ ፡ እስከ ፡ ፩፻፵ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ተመልከት ።

ኃይለኛው ፡ ሰናክሬም ፡ ሳይዋጋ ፡ የተመለሰበትን፡ የመጽሐፍ፡ ቅዱስንም ፡ የሄሮዱቱስንም ፡ ቃል ፡ እየዘለለ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተ ነሣ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ሰናክሬም ፡ በሠፈሩ ፡ ድንገተኛ ፡ በሽታ ፡ ገብቶ ፡ ጦሩ ፡ ስለታመመበት ፡ በፊቃዱ ፡ ተመለሰ ፡ የሚል ፡ አለ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ታርሐቃ ፡ የሻባቶካ ፡ እንደራሴና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አስፈሪው ፡ሰናክሬም ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ በላኪሽ ፡ (ኢየሩሳሌም ፡ አጠገብ) ፡ ተሠ ልፈው ፡ ሳለ ፡ በአይጥ ፡ ወይም ፡ በበሽታ ፡ ይሁን ፡ ሳይዋጋ ፡ ሰና ክሬም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመልሶ ፡ ልጆቹ ፡ ገድለውት፡ አሣርሐዶን ፡ ነገሠ ። በግብፅም ፡ ታርሐቃ ፡ ሻባቶካን፡ ተዋግቶ ፡ ከማረከ ፡ በኋላ፡ ገደለውና ፡ በፈርዖንነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ። የሻባቶካ ፡ ግዛትም ፡ ከ፺፻፩ ፡ እስከ ፡ ፮፻፹፱ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ነው ። የሌሎ ቹን ፡ የነሻባካን ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የሱንም ፡ ከዚህ ፡ በላይም ፡ ከዚህ ፡ በታችም ፡ የሚያደርጉት ፡ አሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

### የታርሐቃ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

የሚቀጥለው ፡ የአሜኔሪቲስ ፡ (ሕንደኬ) ፡ ሥልጣን — የታር ሐቃና ፡ የአሣርሐዶን ፡ ጦርነት — ሁለቱ ፡ ለየግላቸው ፡ ያሠሩት ፡ ሐውልት—የታርሐቃ ፡ ፍጻሜ ።

በሻባቶካና ፡ በታርሐቃ ፡ ዘመን ፡ ፒያንኪ ፡ ፫ኛ ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ በዝርዝሩ ፡ ውስጥ ፡ ፲፰ኛ ፡ ሆኖ ፡ ተመድቦ ፡ ቶማ ፡ ጽዮን ፡ ተብሎ ፡ ይነበባል ። እሱም ፡ እንደትልቁ ፡ ፒያንኪ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ሊሆን ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ። ነገር ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ ሥራውም ፡ ሥልጣኑም ፡ ያለፈው ፡ በደቡብ ፡ በኢትዮጵያና ፡ ሲበዛም ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ አል ገዛምና ፡ እንደ ፡ ሻባቶካ ፡ ወይም ፡ እንደታርሐቃ ፡ እፈርዖንነት ፡ ደረጃ ፡ አልደረሰም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባንዳንድ ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ በሻባካና ፡ በሻባቶካ ፡ በታርሐቃ ፡ መካከል ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ ንጉ ሥነቱን ፡ ገናናነቱን ፡ የሚገልጽ ፡ በድንጋይ ፡ ሐውልት ፡ የተቀረጸ



የታርሐቃ ፡ ( ታሃርቃ ፡ ) ካንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ የሐውልት ፡ ቅርጽ ፡ ( ካይሮ—ገር ፡ ብሪመር ። )

መኖሩን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያረጋግጣሉ ። ከርሱ ፡ በበለጠ ፡ ደግሞ፡ ስሟ በብዙ ፡ ሐውልት ፡ የተቀረጸው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሻባካና ፡ በሻባ ቶካ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ስሟን ፡ ያነሣነው ፡ የካሽታ ፡ ልጅ ፡ አሜኔሪቲስ ፡ የምትባለው ፡ ንግሥት፡አሁንም፡የንግሥትነት፡ ሥልጣኗ፡ እንደ ፡ ቀጠለ ፡ ነው ። እሷም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ቪክቶሪያ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ እንደ ፡ ካቴሪን ፡ የመስ ኮብ ፡ ንግሥት ፤ ወይም ፡ እሩቅ ፡ ሳንሔድ ፡ ባገራችን ፡ እንደ፡ አፄ፡ በካፋ ፡ ባልቤት ፡ እንደ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ እንደ፡ እቴጌ፡ጣይቱ፡ የምትቈጠር ፡ ኃይለኛ ፡ ብልህ ፡ አስተዳዳሪ፡ ነበረች ። በሁሉ፡ዘንድ፡ የመፈራትና ፡ የመከበር ፡ ዕድል ፤ በሁሉ ፡ ጕዳይ ፡ የመግባት ፡ ሥል ጣን ፡ ነበራት ። ዋና ፡ ደንበኛ ፡ ግዛቷ ፡ የቴብ ፡ ከተማና፡ የቴባይድ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ግን ፡ የሚያስከብራት፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ በዚሁ ፡ በቴብ ፡ ባለው ፡ በት ልቁ ፡ በአሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የነበራት ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ።

እሷም ፡ በዘመኗ ፡ ሁሉ ፡ ለፒያንኪም ፡ ለሻባካም ፡ ለ፪ኛው ፡ ፒያንኪም ፡ ሚስትም ፡ እኅትም ፡ ሞግዚትም ፡ እየሆነች ፡ በሁሉም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜዋን ፡ በትልቅ ፡ ሥልጣንና ፡ መፈራት ፡ ያሳ ለፈች ፡ የሴት ፡ ንግሥት ፡ ናት ። በፊት ፡ የናፓታንና ፡ የላዕላይ ፡ ግብ ፅን ፡ ብቻ ፡ ዘውድ ፡ ታደርግ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ የላዕላይንም፡የታ ሕታይንም ፡ ግብፅ ፡ ዘውድ ፡ አደረገች ።

ከፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ የወለደቻት ፡ ሻፕ ፡ አን ፡ አፕ ፡ የምትባለዋ ፡ ልጅዋ ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ የግብፅን ፡ ንጉሥ ፡ ፕሳሜቲኩስ ፡ ፩ኛ ፡ የተባለውን ፡ አግብታ ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ በኋላ ፡ ለገባው ፡ ለ፳፮ ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ (ሥርወ ፡ መንግሥት) ፡ ተከታይ ፡ በመስጠት ፡ ከግ ብፅ ፡ ግዛት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘር ፡ እንዳይጠፋ ፡ አድርጋለች ።

ስለ ፡ አሜኔሪቲስ ፡ በቴብ ፡ ከተማ ፡ (በካርናቅ) ፡ የተሠራውን ፡ የዕብነ ፡ በረድ ፡ ሐውልት ፡ ከነጽሑፉ ፡ ሙሴ ፡ ማሪዬት ፡ የሚባሉት፡ የፈረንሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ተመልክተው ፡ ተደንቀውበታል ። ከመጽሐፋ ቸው ፡ በ፩፪፫፯ ፡ ገጽ ፡ ከመሐከለኛው ፡ የሳሎን ፡ ክፍል ፡ ፩፪፴፰-፩፪ ፴፱ ፡ ተመልከት ። አሁን ፡ ግን ፡ የፒያንኪን ፡ ፪ኛና ፡ የአሜሪቲ



ታርሐቃ ፡ በጦርነት ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲመለስ ፡ ስለመታሰቢያ ፡ ያሠራቸው ፡ የድል ፡ ዓምዶች ፡ ( ሸብርዬ ። )

ስን ፡ ታሪክ ፡ እንተውና ፡ እንደፒያንኪ ፡ ፪ኛ ፡ ከሌሎቹ ፡ ከሻባካና ፡ ከሻባቶካ ፡ ይበልጥ ፡ ኃይለኛና ፡ ገናና ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ንጉሥ ፡ የሆነ ውን ፡ የታርሐቃን ፡ ታሪክ ፡ እንመልከት ።

ታርሐቃ ፡ ገና ፡ በሻባካ ፡ ጊዜ ፡ ዝምር ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ አድርጎ ፡ በመንግሥቱ ፡ ሥራና ፡ ይልቁንም ፡ በጦርነት ፡ ተመስግ ኗል ። በሻባቶካም ፡ ጊዜ ፡ የእሶሩን ፡ ንጉሥ ፡ ሰናከሬምን ፡ ለመው ጋት ፡ ሔዶ ፡ መመለሱን ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ። ስሙም ፡ በመጽ ሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ተጠቅሶ ፡ እናገኘዋለን (፩) ። በዚያም ፡ ላይ ፡ ታር ሐቃን ፡ «ቲርሐቅ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ» ፡ ይለዋል ። ቲርሐቅ ፡ ያለ ውም ፡ በዚያም ፡ በነሱ ፡ በዕብራይስጥ ፡ አነጋገር ፡ ነው ። የኑብያ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ያጠናው ፡ ሬይዝነሬ ፡ « ኩንፈርቴምራ ፡ ታር ሀክ» ፡ ብሎታል ። በተረፈ ፡ ያንዱን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ በየ ቋንቋው ፡ እየለያየ ፡ መጥራት ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የእሶ ሩን ፡ ንጉሥ ፡ የኛ ፡ የግእዝ ፡ ሊቃውንት ፡ ሰናክሬም ፡ ይሉታል ። ዕብራውያን ፡ ሳንኪሪብ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሰንሄሪብ ግብፆቹ ፡ ወይም ፡ አሶራውያኖቹ ፡ ሲን ፡ አከሂ ፡ ኢሪብ ፡ ይሉታል ። ያገር ፡ አጠራርም ፡ እንደዚሁ ፡ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ አገር ፡ ሲይዝ ፡ የነበረውን ፡ ያገር ፡ የተወላጁን ፡ ስያሜ ፡ እየተወ ፡ በራሱ ፡ ቋንቋ ፡ ስለሚሰይ መው ፡ ለእንግዳ ፡ ደራሽ ፡ ጸሐፊና ፡ አንባቢ ፡ እየተዘባረቀ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ችግርን ፡ ይፈጥራል ። እንደዚሁም ፡ የታርሐቃ ፡ ሥሩን ፡ ምንም ፡ ያኸል ፡ ሳይለቅ ፡ «ተሐርቃ ፤ ታሩቃሀ ፤ ተሐርቁ ፤ ታሐርቃ ፤ ታሐ ርቆስ ፤ ቲርሐቅ » ፡ የሚለው ፡ ብዙ ፡ ነው ። እሶራውያን ፡ ደግሞ ፡ ታርኩ ፡ ብለውታል ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ የሚገባውን ፡ የግብፃውያንን ፡ አጻጻፍ ፡ ከየሐውልቱ ፡ ላይ ፡ እየለ ቀሙ ፡ የተረጐሙት ፡ ሊቃውንት ፡ እነለፕሰዩስ ፤ እነማሪዬት ፡ ታር ሐካ ፡ ብለውታልና ፡ እኛም ፡ ስእንደበት ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ካን ፡ ቤታ ፡ ለውጠን ፡ ታርሐቃ ፡ ብለን ፡ እንጽፋለን ። አንዳንድ ፡ ጊዜም በብርቅ ፡ ታሕርቅ ፡ ብለውት ፡ ይገኛል ። ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ደግሞ ፤ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፳ ፡ ጸውዕ ፡ ቲርሐቅ ፡ ወረደ ፡ ነጋሽ ፡ ብለውታል ። ቲርሐቅ ፡ ያሉት ፡

---

(፩) ፪ኛ ፡ ነገሥት ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፱ ።



ሙቹም ፡ የዕብራይስጡን ፡ የስሙን ፡ መንገድ ፡ ይዘው ፡ ነው ። ጸው ዕና ፡ ወረደ ፡ ነጋሽ ፡ ከምን ፡ እንደተጨመረ ፡ ገና ፡ አልገባኝም ። ስሙ ፡ በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ በሚዠምረው ፡ የነገሥታ ቶቻችን ፡ ዝርዝር ፡ ፲፩ኛ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። እርሱም ፡ ከአገልጋይ ፡ የተወለደ ፡ የፒያንኪ ፡ ፫ኛ ፡ ወይም ፡ ፪ኛ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ የለም ፡ ሻባካ ፡ ከዕቁባቱ ፡ የወለደው ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

ከሻባካ ፡ ዕቍባት ፡ ተወለደ ፡ የሚሉት ፡ ከሻባቶካ ፡ ጋር ፡ ስላደ ረገው ፡ ጦርነት ፡ እንደዚህ ፡ ይላሉ ፡ «ታርሐቃ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በነ ገሠ ፡ በ፲፩ ፡ ዓመቱ ፡ ሻባቶካ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ በነገሠ ፡ በ፳፩ ኛው ፡ ዓመት ፡ ታርሐቃ ፡ ወደምሥር ፡ ዘመተ ፡ የዚህንም ፡ ወሬ ፡ ሻባቶካ ፡ በመስማቱ ፡ እኔ ፡ የንጉሡ ፡ የሻባካ ፡ ዋና ፡ ልጁና ፡ የመ ንግሥቱ ፡ ወራሽ ፡ ሆኜ ፡ ይህ ፡ የድኃ ፡ ልጅ ፡ ዲቃላ ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ መጣ ፡ አሁንም ፡ በጂ ፡ የወደቀ ፡ እንደሆነ ፡ ቆራርጨ ፡ ለአሞራ ፡ እስ ጠዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ታርሐቃ ፡ ይኸንኑ ፡ ሰምቶ ፡ በንዴት ፡ ገሥ ግሦ ፡ መጥቶ ፡ ጦርነት ፡ ገጠመውና ፡ ማርኮ ፡ ገደለው» ፡ ይላሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ታርሐቃ ፡ በ፯፻፲፯ ፡ ዓመት ፡ በሻባቶካ ፡ ሥፍራ ፡ የፈር ዖንነት ፡ ዘውድ ፡ ከጫነ ፡ ወዲህ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በደልታና ፡ በሳይስ ፡ የሚቀበቀሉትን ፡ የግብፅ ፡ መሳፍንት ፡ ከደመሰሰ ፡ በኋላ ፡ በ፳ ፡ ዓመት ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ የሊቢያን ፡ ከዚያም ፡ አልፎ ፡ እስከ ፡ ዛሬው ፡ ጂብራልታር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የአፍሪካን ፡ ሰሜን ፡ በሙሉ ፡ አስ ገብሯል ። እስከ ፡ አውሮፓም ፡ ድረስ ፡ ተሻግሯል ፡ የሚሉ ፡ ጸሐፊ ዎች ፡ አሉ ። በዚሁ ፡ በቴብ ፡ (በካርናቅ) ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ የራሱ ፡ ሐው ልት ፡ በትልቅ ፡ ሆኖ ፡ ከዚያም ፡ በርሱ ፡ አጠገብ ፡ እሱ ፡ እየተዋጋ ፡ የማረካቸው ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ የእስያ ፤ አሥራ ፡ አራት ፡ የአፍሪካ ፡ ሰዎች ፡ (ነገሥታት ፡ ወይም ፡ መሳፍንት) ፡ እንደታሠሩ ፡ ቆመው ፡ ይታያሉ ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ የባቢሎንና ፡ የእሶር ፡ መሳፍንት ፡ አሉ በት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ፈርዖኖች ፡ እንደነቴት ሞሲስ ፡ እንደነራምሲስ ፡ ሐውልቱን ፡ ያስቀረጸው ፡ ራሱ ፡ በዘመኑ ፡ ስለሆነ ፡ ያሳስገበራቸውንም ፡ ነገሥታት ፡ አስገበርሁ ፡ እያለ ፡ ሳይ ጨምር ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ተጠራጥረ ዋል ። የታርሐቃ ፡ ስም ፡ በመድኔ ፡ ሀቡ ፡ በኤድፉ ፡ በዋዲ ፡ ሐማ

ማት ፡ በታኒስ ፤ ስሙ ፡ በየሐውልቱ ፡ በየመቅደሱ ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ። ይልቁንም ፡ ቀድሞ ፡ ደርቆ ፡ ወይም ፡ እንቦ ፤ ረኃብ ፡ በአገሩ፡ እሥንሥቶ ፡ የነበረው ፡ የዓባይ ፡ ወንዝ ፤ አሁን ፡ እርሱ ፡ በነገሠበት፡ ዘመን ፡ ሞልቶ ፡ ስለተትረፈረፈ ፡ የጻድቅነቱ ፡ የደግነቱ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ፡ ያከብረውና፡ ይወደው ፡ ዠመር። ከነገሠ፡ ዠምሮ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ክብርና ፡ ደስታ፡ ሲኖር ፡ አሁን ፡ በፊቱ ፡ አንድ ፡ ኃይለኛ ፡ የቆየ ፡ ጠላት ፡ ተፈጠረበት ። ይኸውም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ስሙን ፡ የጠቀስነው ፡ አሣርሐዶን፡ (አሱር ፡ አኬ ፡ ኢዲን)፡ የሚባለው ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የሰናክሬም ፡ ልጅ ፡ ነው ።

የአሶር ፡ መንግሥት ፡ ባላፈው ፡ እንደተጻፈው ፡ ወደፊትም ፡ በዝርዝር ፡ እንደምንጽፈው ፡ ገና ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በነስልምናሶር ፡ በነሳርጎን ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈራና ፡ የገነነ ፡ ሆኖ ፡ በአጠገቡ ፡ ያሉትን ፡ ባቢሎንን ፡ ጢሮስን ፡ ሲዶናን ፡ እስራኤልን ፡ ሁሉ ፡ ከወረረና ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ በሰናክሬም ፡ ላይ ፡ በደረሰበት ፡ አደጋና ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ እንደመቀዝቀዝ ፡ ብሎ ፡ ከተያዙት ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ፡ እነባቢሎን ፡ እነጢሮስ ፡ ተንቀሳቅሰው ፡ ነፃነታቸውን ፡ ለማግኘት ፡ ችለው ፡ ነበር ። ታርሐቃም ፡ በሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ አገሮች ፡ እንደቀድሞዎቹ ፡ ፈርዖኖች ፡ ለመግዛት ፡ ተስፋ ፡ እያደረገ ፡ በእሳብና ፡ በመላላክ ፡ ይደግፋቸው ፡ ነበር ።

እሣርሐዶንም ፡ በዚያው ፡ በአገሩ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህኑ ፡ የሸፈቱበትን ፡ አገሮች ፡ ባቢሎን ፡ ጢሮስንና ፡ ሲዶናን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እያለ ፡ በጦርነት ፡ ከመደምሰስ ፡ በቀር ፡ በግብፅ ፡ ላይ ፡ ለመነሣት ፡ ጊዜ ፡ አላገኘም ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከ፮፻፸፯ ፡ እስከ ፡ ፮፻፸፫ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ጢሮስንም ፡ ሲዶናንም ፡ እየተዋጋ ፡ መልሶ ፡ ከደመሰሳቸው ፡ ወዲህ ፡ የአሶር ፡ ገናናነት ፡ የነነዌ ፡ ከተማ ፡ ድምቀት ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እያደገ ፡ ጠላቶቹንም ፡ እያስፈራ ፡ ይሔድ ፡ ዠመር ። ስለዚህ ፡ በ፮፻፸፩ ፡ ዓመት ፡ እነዚሁ ፡ አገሮች ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርጉትን ፡ የግብፅን ፡ ፈርዖን ፡ ታርሐቃን ፡ ለመውጋት ፡ ጉዞውን ፡ በሲና ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ዠመረ ። በመንገድም ፡ በሲና ፡ በረሃ ፡ ጥንት ፡ እስራኤሎችን ፡ የፈጀው ፡ መንታ ፡ ጭንቅላት ፡



ያሰው ፡ የበረሃ ፡ እባብ ፡ እየነከሰ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ውስጥ ፡ ቢጨርስበትም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በሲና ፡ አውራጃ ፡ የሚኖሩ ፡ የዘላን ፡ ሕዝብ ፡ ሹማምንት ፡ ከነጭፍራቸው ፡ እየመጡ ፡ ስለተደባለቁለት፡ በነሱ ፡ ጭምር ፡ እየተረዳ ፡ እግብፅ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ እመምፊስ ፡ ደረሰ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በሰሜናዊ ፡ ግብፅ፡በደልታና ፡ በሳይስ፡ያሉት ፡ የግብፃውያን ፡ መሳፍንት ፡ በኢትዮጵያዊው ፡ በታርሐቃ ፡ ፈርዖንነት፡ ይቀኑ ፡ ስለነበረ፡ ከአሶሩ፡ ንጉሥ ፡ጋር ፡ ስለተባበሩ ፡ በታርሐቃ፡ ላይ፡ የጦርነቱ ፡ ሁኔታ ፡ ከፉኛ ፡ ሊከብደው ፡ ቻለ ። ቢሆንም ፡ በመምፊስ ፡ ከተማ ፡ ሆኖ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ በሚገባ ፡ ከተዋጋ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደቴብ ፡ ቀጥሎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ናፓታ ፡ የተረፈውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ሸሸ ። ሚስቶቹና ፡ ልጆቹ ፡ ቍጥር ፡ የሌለው፡ መሣሪያና ፡ ዕቃው ፡ በጠቅላላው ፡ በሙሉ ፡ የመምፊስ ፡ ከተማ ፡ በአሶራውያን ፡ እጅ ፡ ወደቀች ። የመምፊስንም ፡ ከተማ ፡ ይዘው ፡ ከተረጋገጡ፡ በኋላ ፡ የአሶር ፡ ሠራዊት ፡ ከነሹማምንቱ ፡ እስከ ፡ ቴብ ፡ ድረስ ፡ ወርደው ፡ በመምፊስ ፡ ካደረጉት ፡ ይበልጥ ፡ ቴብን ፡ በዘበዙት ። በቴብ ፡ ከተማ ፡ የተገኘውን ፡ የአማልክቱን ፡ የንእሞንን ፡ የካህናቱንም ፡ የሴቱንም ፡ የወንዱንም ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ መሣሪያ ፡ ማናቸውንም ፡ ኀጥና ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ እየዘረፉ ፡ ሰብስበው ፡ ወደ፡ አገራቸው ፡ ወደአሶር ፡ ያግዙ ፡ ዠመር ። በቴብ ፡ ዋና ፡ እምላክ ፡ በእሞን ፡ በወንዱ ፤ በሐትሆር ፡ በሴቲቱ ፡ ፈንታም ፡ የራሳቸውን ፡ የእስታርትን ፡ የሴቷን ፡ የአሱርን ፡ የወንዱን ፡ የአማልክቶቻቸውን ፡ ምስል ፡ አደረጉ ።

አሣርሐዶን ፡ በመምፊስ ፡ ሳለ ፡ የታሕታይም ፡ የማዕከላይም፡ ግብፅ ፡ መሳፍንት ፡ መታያቸውን ፡ እየያዙ ፡ መጥተው ፡ እጅ ፡ እየነሡ ፡ ገቡለት ። በሩቅም ፡ ያሉት ፡ ገብረናል ፡ እያሉ ፡ መልእክታቸውን ፡ አስቀደሙ ፡ አሣርሐዶንም ፡ የኢትዮጵያውያኑን ፡ ዘር ፡ ከግብፅ ፡ አጠፋሁ ፡ ብሎ ፡ ፎከረ ። እሱም ፡ ቀድሞ ፡ የአሶር ፡ የአካድ ፡ የሱሜር ፡ ንጉሥ ፡ በሚባልበት ፡ ላይ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ደግሞ ፡ የሙስሬ ፡ (ግብፅና) ፡ የኩሹ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ ንጉሥ ፡ መባልን ፡ እየጨመረ ፡ የማዕርጉን ፡ ስያሜ ፡ በመዘርዘር ፡ አሰረከተ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አለያይተህ ፡ ግዛ ፡ የተባለውን ፡ የፖለቲካ ፡ አስተዳደር ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሊጠቀምበት ፡ አሰቦ ፡ አማርሐዶን ፡ በተያዘው ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ ቍጥራቸው ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ የሚደርሱትን ፡ መሳፍንት ፡ ለየብቻቸው ፡ ነፃነት ፡ ሰጥቶ ፡ ግብራቸውን ፡ ለየብቻ ፡ በቀጥታ ፡ እንዲገብሩ ፡ አድርጎ፡ በየአውራጃቸው፡ ላይ ፡ አነገሣቸውና ፡ የራሱን ፡ ሹማምንትና ፡ ጦር ፡ ትቶ ፡ አማርሐዶን ፡ በደስታ ፡ ወደሀገሩ ፡ ወደነነዌ ፡ ተመለሰ ።

ሲመለስም ፡ ሰንጀርሊ ፡ በሚባለው ፡ ግዛቱ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ የድል ፡ አድራጊነቱን ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ አሠራ ። በዚህም፡ የመታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ የራሱን ፡ ምስል ፡ በሚያምር ፡ ንጉሥ ፡ በሎልቱ ፡ አሠርቶ፡ በግርጌው ፡ ታርሐቃን፡ ባንድ ፡ ትንሽ ፡ ጥቁር ፡ አፍሪቃዊ ፡ መልክ ፡ አድርጎ ፡ ተንበርክኮ ፡ ምሕረት ፡ እንደሚለምነው ፡ አድርጎ ፡ አሠራው ። እንደእውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ፡ ታርሐቃ ፡ እንኳን ፡ ተንበርክኮ ፡ ምሕረት ፡ ሊለምነው ፡ ከአሶሩ ፡ ንጉሥ ፡ ከአማርሐዶን ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ አልተገናኙም ። ቢገናኙ ፡ ኖሮ ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ በጦርነት ፡ ያስቸገረውን ፡ ኃያል ፡ ፈርዖን ፡ በጭካኔ ፡ እንደ ፡ አሶራውያን ፡ ልማድ ፡ ከነሕይወቱ ፡ ቆዳውን ፡ እንኳን ፡ ባያስገፍፈው ፡ ሳያስገድለው ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በሐውልቱ ፡ ላይ ፡ አማርሐዶን ፡ ያሠራው ፡ የታሐርቃ ፡ ምሕረት ፡ መለመን ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ጸሐፊው ፡ ሁሉ፡ ተገንዝቦታል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አማርሐዶን ፡ ግብፅን ፡ ወርሮ ፡ የራሱን፡ የጦር ፡ ሹማምንትና ፡ ወታደር ፡ ለተቆጣጣሪነትና ፡ ለጠባቂነት ፡ ግብፅ ፡ አገር ፡ ትቶ ፡ መሳፍንቱንም ፡ በየአውራጃቸው ፡ አንግሦ ፡ ወደከተማው ፡ ወደነነዌ ፡ ተመለሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታርሐቃ ፡ አሱርባኒፓል ፡ መምፊስ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ሸሽቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደናፓታ ፡ (ወደ ፡ ኢትዮጵያ) ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ እንደገና ፡ ከአሶራውያን ፡ አስጥሎ ፡ ለመያዝ ፡ ይዘጋጅ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ መካከልም ፡ ግብፃውያኑ ፡ ራሳቸው ፡ ከአሶራውያኑ ፡ ግዛት ፡ በሃይማኖት ፡ በልማድ ፡ በቋንቋ ፡ በጽሕፈት ፡ የሚመሳሰሉዋቸው ፡



ኢትዮጵያውያኑ ፡ እንደሚሻሉዋቸው ፡ አመዛዘኑ ። ስለዚህ ፡ የአሶራውያን ፡ ግዛት ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደቆየ ፡ ናና ፡ በላያችን ፡ መሪ ፡ ሆነህ ፡ ከአሶራውያን ፡ ቀንበር ፡ አድነን ፡ ሲሉ ፡ ወደታርሐቃ ፡ ላኩበት ። እርሱም፡ ይህን ፡ መልእክት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ። ወደሰሜንም ፡ ገሥግሦ ፡ ከአሶራውያን ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ፡ አሸነፈና ፡ የመምፊስን ፡ ከተማ ፡ ይዞ ፡ እንደቀድሞው ፡ ያስተዳድር ፡ ጀመር ።

በመዲኔ ፡ ሐቡ ፡ ላይ ፡ የድል ፡ አድራጊነቱን ፡ ሐውልት ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ በፋንታው ፡ አሠርቶ ፡ በሐውልቱ ፡ ግርጌ፡ ጽሑፍ፡ ሲያስቀርጽ ፡ «የሁለቱ ፡ አገር ፡ የኑብያና ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ» ፡ በሚባልበት ፡ ላይ ፡ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ የሚል ፡ አስጨምሮ ፡ አስቀረጸ፡ ይኸም ፡ አማርሐዶን ፡ ታርሐቃን ፡ በሐሰት ፡ ተንበርክኮ፡ ምሕረት፡ እንደለመነው ፡ አስመስሎ ፡ካሠራው ፡ ሐውልት ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ ከእውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ የዘለለ ፡ የልብ ፡ ምኞት ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ታርሐቃ ፡ አሶርን ፡ አልገዛም ። ምናልባት ፡ አማርሐዶን ፡ በግብፅ ፡ ትቷቸው ፡ የሔዱት ፡ ዘወትር ፡ ውጊያና ፡ ሽሽት ፡ የሰለቻቸው ፡ አሶራውያን ፡ ተገዝተውለት ፡ እንደሆነ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ለመባል ፡ አያበቃም ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአማርሐዶንና ፡ በታርሐቃ፡ የሐውልት፡ሥራ፡ ላይ ፡ እንደምንገነዘበው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የታሪክ ፡ መሠረት ፡ ሐውልት ፡ ቢሆንና ፡ ዝርዝር ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪክ ፡ በመሸከሙ ፡ የሐውልት ፡ አገልጋይነት ፡ ባይካድ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ፡ ንጉሥ፡ በዘመኑ ፡ ራሱ ፡ የራሱን ፡ ታሪክ ፡ በሐውልት ፡ ላይ ፡ ሲያስቀርጽ ፡ ለከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ሲል ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ ይደባልቃልና፡ የሐውልት፡ ጽሑፍ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ የባዕድ ፡ ጽሑፍ ፡ እስኪደግፈው ፡ ድረስ ፡ መታመንን ፡ የሚያጣበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። አሁን ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ ትተን ፡ ወደዋናው ፡ አሳብ ፡ እንመለስ ።

ታርሐቃ ፡ ከናፓታ ፡ ተመልሶ ፡ መምፊስን ፡ ይዞ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ሁሉ ፡ እንደፈጸመ ፡ ነነዌ ፡ ከተማው ፡ እንዳለ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ አማርሐዶን ፡ ከአሶር ፡ ወደግብፅ ፡ጉዞ ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ።

ዳኑ ፡ ግን ፡ በመንገድ ፡ ሞተ ፡ በመንግሥቱም ፡ ልጁ ፡ አሱርባኒፓል ፡ (አሱር — ባን — ሀባል)፡ ተከተለው ። ታርሐቃ ፡ ከደቡብ፡ ወደሰሜን ፡ ተመልሶ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ እንደገዛ ፡ አሱርባኒፓልም፡ ያባቱን ፡ መንግሥት ፡ በ፫ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ በ፬ ኛው ፡ ዓመት ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወደ ፡ ግብፅ፡ ላከ ። የተላከውም ፡ ጦር ፡ ታርሐቃን ፡ አሸንፎ፡ እንደገና፡ መምፌስ ፡ ገባ ። ታርሐቃም ፡ ሁለተኛ ፡ ወደቴብ ፡ መሸሽ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። የዴልታ ፡ መሳፍንትም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለራሳቸውም ፡ ለታርሐቃም ፡ ሲሉ ፡ አሶራውያንን ፡ ምንም ፡ በርትተው ፡ ቢዋጉ ፡ አልሆነላቸውምና ፡ ተሸንፈው ፡ ወደ ፡ አሶራውያን ፡ ገቡ ።

የአሶሩ ፡ የጦር ፡ መሪም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ከታርሐቃ፡ ጋር ፡ ያበሩትን ፡ መሳፍንት ፡ እየያዘ ፡ ለመቀጣጫ ፡ እንዲሆኑ ፡ በጭካኔ ፡ እየቀጣ ፡ ኒካዎንና ፡ ሻርሉዳሪ ፡ የሚባሉትን ፡ ብቻ ፡ ወደጌታው ፡ ወደ ፡ አሱርባኒፓል ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ላካቸው ። ታርሐቃንም ፡ ከመምፌስ ፡ እስከ ፡ ቴብ ፡ ድረስ ፡ ዓባይ ፡ ላባይ ፡ እያሳደደ ፡ ከቴብም ፡ አስወጥቶ ፡ ወደ ፡ አባቶቹ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ናፓታ ፡ እንዲሸሽ ፡ አስገደደው ።

በዚሁ ፡ መካከል ፡ ከታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ተማርከው፡ ከነበሩት፡ ነገሥታት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ስሙን ፡ የጠቀስነው ፡ ኒካዎ ፡ ከታርሐቃ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ሲዋጋ ፡ በአሶራውያን ፡ ተማርኮ ፡ ወደ፡ነነዌ ፡ ከተላከ ፡ ወዲህ ፡ ንጉሡ ፡ አሱርባኒፓል ፡ ለፖለቲካና ፡ ለአስተዳደር ፡ ሲል ፡ ከጓደኞቹ ፡ መሳፍንት ፡ ኒካዎ ፡ ከላይ ፡ ከታፍነከታ ፡ የወረደ ፡ የቦኮንራፍ ፡ ልጅ ፡ የሳይስ ፡ መስፍን ፡ በመሆኑ ፡ ሽልማትና ፡ ዘውድ ፡ ሰጥቶ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ አሰዳስቶ ፡ ወደ ፡ ታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ከተማ ፡ ወደመምፌስ ፡ ተልኮ ፡ መጣ ። በርሱም ፡አጠገብ ፡ አሶራዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ አብሮ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ጲላጦስና ፡ እንደ ፡ ሄሮድስ ፡ ስለሚያስተዳድሩ ፡ በግብፅ ፡ የአሶር ፡ ግዛት ፡ እስከ ታኑታሙን ፡ ድረስ ፡ ለጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ጸድቆ ፡ ቆየ ። ኃይለኛውና ፡ እስፈሪው ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ፈርዖን ፡ ታርሐቃም ፡ ወደናፓታ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳይቆይ ፡ ስለሞተ ፡ በርሱ ፡



እግር ፡ ታኑታሙን ፡ ነገሠ ። ስለታርሐቃ ፡ አሟሟት ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ።

«የአሞንን ፡ ካህናት ፡ ጭንቅላት ፡ በሰይፍ ፡ እስቆርጠህ ፡ ካላስጨረስክ ፡ መንግሥትህ ፡ አይረዝምም» ፡ የሚል ፡ ራእይ ፡ በሕልሙ ፡ ዓይቶ ፡ እንደነበረና ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ዓመፅ ፡ ሠርቼ ፡ መንግሥቴ ፡ ከሚረዝም ፡ የመንግሥቴን ፡ ማጠር ፡ እወዳለሁ ፡ ብሎ ፡ መንግሥቱን ፡ ለካህናት ፡ አስረክቦ ፡ እርሱ ፡ እገሩ ፡ ናፓታ፡ ሔዶ ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ እንደቆየ ፡ መሞቱን ፡ ይገልጻል ። የሆነ ፡ ሆኖ፡ ይህ ፡ ታላቅ፡ፈርዖን፡ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በ፮፻፷፬ ፡ ዓመት፡ሲሞት፡ ግብፅንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ ደርቦ ፡ ኻያ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ገዝቷል ። ከፈርዖንነቱ ፡ በፊት ፡ በናፓታ ፡ ብቻ ፡ ፳፫ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ነግሧል ።

ስለዚህ ፡ በድምሩ ፡ እሥልጣን ፡ ከወጣ ፡ ፵፱ ፡ ዓመት ፡ ይሆነዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ታርሐቃ ፡ እንደፒያንኪ ፡ እንደሻባቃ፡ የጎነነ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር። በዘመኑም ፡ በግብፅ ፡ እስከ ፡ እርሱ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሲሠራበት ፡ የኖረው ፡ ባለፈው ፡ የተመለከትነው ፡ ሂዬሮግሊፍ ፡ የሚባለው ፡ የዕቃን ፡ የእንስሳን ፡ የአዕዋፍን ፡ ሥዕል ፡ እየቀረጹ ፡ የማናገር ፡ ፊደል ፡ ቀርቶ ፡ ዴሞቲክ ፡ የሚባለውን ፡ አዲስ ፡ ፊደል ፡ አውጥቶ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የርሱ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ እዲስ ፡ ፊደል ፡ በዘመኑም ፡ ቀጥሎው ፡ ባሉትም ፡ ነገሥታት ፡ የተስፋፋ ፡ አይመስልም ። ከነርሱ ፡ ወዲህ ፡ ሐውልቶቻቸውን ፡ ካስቀረጹ ፡ ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ በ፭፻ ፺፫ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ አስፔርታ ፡ የሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ ለአምላኩ ፡ ለአሞን ፡ ለራሱም ፡ ሐውልት ፡ ሠርቶ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ለአምላኩ ፡ በየጊዜው ፡ የሰጠውን ፡ ስለት ፡ በጥንቱ ፡ ፊደል ፡ የተጻፈውን ፡ ወደፊት ፡ እናገኛለን ። ነገር ፡ ግን ፡ የዴሞቲኩ ፡ ጽሑፍ ፡ በፍጥነት ፡ ለመጻፍ ፡ ብቻ ፡ ሲቀና ፡ የፊደሉ ፡ መልክ ፡ እንደፊተኛው ፡ እያምርምና ፡ ምናልባት ፡ ሕዝቡና ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በዴሞቲኩ ፡ ፊደል ፡ ለሥራ ፡ ብቻ ፡ ሲጠቅም ፡ ለሐውልትና፡ ለቅርጽ፡ የፊተኛውን ፡ የሂዬሮግሊፍ ፡ ቅርጽ ፡ እየመረጡ ፡ የሚሠሩበት ፡ ይመስላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

## ታኑታሙን ።

በታርሐቃና ፡ በታኑታሙን ፡ መካከል ፡ አርድ ፡ አሚን ፡ የሚባል ፮ ፡ ዓመት ፡ ገሥሦ ፡ የሚባል ፡ ፮ ፡ ሰዓት ፡ መንገሣቸውን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ዝርዝራቸውን ፡ አግብተዋል ። (ገጽ ፡ ፳) ፡ ሙሴ ፡ ሞን ፡ ሞሪዮ ፡ ደግሞ ፡ ገሥዮንን ፡ ትቶ ፡ አርድ ፡ አሚንን ፡ አግብቷል ። ታሪኩንም ፡ ሲቀጥል ፡ ከታርሐቃ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ነገሡና ፡ እስከ ፡ ሰሜናዊው ፡ ግብፅ ፡ ደርሶ ፡ አሶራውያን ፡ እንደ ፡ አባረሩት ፡ ከዚያም ፡ ተመልሶ ፡ በናፓታ ፡ እንደሞተና ፡ ክርሱ ፡ መንግሥትን ፡ ታኑታሙን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ጽፏል (፩) ። ሙሴ ፡ ሞሪዮም ፡ ብላቴን ፡ ጌታም ፡ ይኸን ፡ ቃል ፡ የወሰዱበት ፡ አንድ ፡ የታሪክ ፡ ምንጭ ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ የግብፅንና ፡ የኑብያን ፡ ታሪክ ፡ ሐውልቱንም ፡ ጽሑፋንም ፡ የመረመሩ ፡ በግብፅና ፡ በሎንዶን ፡ በፓሪስም ፡ የጥንታዊ ፡ ዕቃ ፡ በሙዜውም ፡ ጥበቃ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የነበሩ ፡ ሊቃውንት ፡ ፈረንሳውያን ፡ እጉስት ፡ ማሪዮት ፡ ሙሴ ፡ ኤቲዩን ፡ ድሪወቶን ፡ ሙሴ ፡ ሞክ ፡ ቫንዲዮ ፡ ግብፃዊ ፡ ካታዊ ፡ ፓሻ ፡ ጀርመናዊው ፡ ምስተር ፡ ለፕሲዩስና ፡ እንግሊዛዊው ፡ ዋላስ ፡ ባጅ ፡ የቀሩትም ፡ ብዙዎቹ ፡ ከታርሐቃ ፡ ታኑታሙንን ፡ ያስከትላሉ ። በስም ፡ ዝርዝር ፡ በዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ መለያየቱ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ሆኗል ። ቢሆንም ፡ ትያይዞ ፡ የመጣን ፡ ዝርዝርና ፡ ስም ፡ እየተከተሉ ፡ ከሚገለብጡት ፡ ሐውልትን ፡ የመረመሩትን ፡ መከተል ፡ ቲንሽ ፡ ሳይሻል ፡ አይቀርም ። በታርሐቃና ፡ በእማርሐዶን ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ እንደተገነዘብነው ፡ በሐውልቱም ፡ ላይ ፡ ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ እንደወደደና ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፡ እያስቀረጸ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ከእውነት ፡ መዝለሉ ፡ ባይቀር ፡ ስምንና ፡ ዓመትን ፡ ይጠነቅቃል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ታኑታሙን ፡ እንመለስና ፡ የንግሡን ፡ ዜና መዋዕል ፡ እንመልከት ። ታኑታሙን ፡ እንደ ፡ አባቶቹ ፡ ስሙ ፡ ብዙ

(፩) J. MORIE — HIST. D'ETHIOPIE ፻፶፱ ፡— ፻፷፩ ፡



ነው ። አሜን ፡ ሜሪኑት ፡—ኑእት ፡ ሚይአሙን ፡— ባካራ ፡— ራባካ ፡ ይባላል ።

ታኑታሙን ፡ በናቱ ፡ የታርሐቃ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የሻባቶቃ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ ግማሾቹ ፡ የሻባካ ፡ ወይም ፡ የአርድ ፡ አሚን ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የታርሐቃ ፡ የጉድፈቻ ፡ ልጅ ፡ ይሉት ፡ የነበረው ፡ ስሕተት ፡ ሆኗል ። በዚሁ ፡ በጀበል ፡ ባርካ ፡ ሙሴ ፡ ማሪዬትና ፡ ሙሴ ፡ ሩዤ ፡ ሙሴ ፡ ለፕሲዩስ ፡ ከተረጐሙት ፡ ከእምስቱ ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ነገሥታት ፡ ሐውልት ፡ አንዱ ፡ የዚሁ ፡ የታኑታሞን ፡ (አሜን ፡ ሜሪኑት ፡— ራባካ) ፡ ነው ። ይኸም ፡ ሐውልት ፡ «የሕልም ፡ ሐውልት» ፡ የሚባል ፡ ስያሜ ፡ ተሰጥቶታል ። የሐውልቱ ፡ ርዝመት ፡ አንድ ፡ ሜትር ፡ ከ፴፱ ፡ ስፋቱ ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ሳንቲም ፡ ሆኖ ፡ ጽሑፉን ፡ የያዙት ፡ መሥመሮች ፡ ላይ ፡ «የፀሐይ ፡ ልጅ ፡ የአሞን ፡ ልጅ ፡— ዘላለም ፡ የሚኖረው ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ (የኢትዮጵያና ፡ የግብፅ ፡) ንጉሥ ፡ . . . . . » የሚባለው ፡ የዘወትር ፡ ደንበኛ ፡ ንጉሣዊ ፡ የእርእሱ ፡ ንግግር ፡ ይዠምራል ። ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ « በሕልሜ ፡ አንድ ፡ እባብ ፡ ከቀኜ ፡ አንድ ፡ እባብ ፡ ከግራዬ ፡ በኩል ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፡ ይኸንን ፡ ተርጕሙልኝ» ፡ ብሎ ፡ ሲነጋ ፡ አዋቂዎቹን ፡ የጠየቀበት ፡ እነሱም ፡ ሁለቱ ፡ እባቦች ፡ ደቡብን ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሰሜን ፡ ግብፅን ፡ ወደፊት ፡ የመግዛትህ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የተረጐሙለት ፡ ንጉሡም ፡ ይኸን ፡ ሲሰማ ፡ በሕልሙ ፡ አፈታት ፡ ተደስቶ ፡ ለካህናቱና ፡ ለመኳንንቱ ፡ ግብር ፡ ያገባበት ፡ በናፍ ፡ ላለው ፡ ላባቱ ፡ ለአሞን ፡ መሥዋዕቱን ፡ ያቀረበበት ፡ ይቀጥላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ሐውልት ፡ የተጻፈው ፡ ንግግር ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ታኑታሙን ፡ ከከተማው ፡ ከናፓታ ፡ ተነሥቶ ፡ ኤሌፋንቴን ፡ ከዚያም ፡ ተጉዞ ፡ ቴብ ፡ ደረሰ ። በምዕራብም ፡ በምሥራቅም ፡ ደስታ ፡ ሆነ ። በያለበትም ፡ የደስታና ፡ የዕልልታ ፡ ጩኸት ፡ ተሰማ ። ቀጥሎም ፡ ወደሰሜን ፡ ተጉዞ ፡ መምፌስ ፡ ደረሰ ፡ ጠላቶቹንም ፡ አጠፋ ፡ ወደ ፡ ፕታህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ለፕታህ ፡ ሶካሪስና ፡ ለወዳጁ ፡ ለፓስኪት ፡ መሥዋዕቱን ፡ አቀረበ ። ወደ ፡ ሰሜን ፡ እሁንም ፡ ጉዞውን ፡ ቀጥሎ ፡ የደልታን ፡ መሳፍንት ፡ አስገበረና ፡ ወደመምፌስ ፡ ተመለሰ ። በዚያም ፡ ሳለ ፡ የጠላት ፡ አለቆች ፡

መጥተዋል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ እሱም ፡ «ሲወጉኝ ፡ ወይስ ፡ ባሮቼ ፡ ለመሆን ፡ ነው ፡ የመጡት» ብሎ ፡ ጠየቀ ፡ «የሰም ፡ ምሕረት ፡ ለመ ለመን ፡ ነው ፡ የመጡት » ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አል ሞት ፡ የነበረው ፡ ሕልምና ፡ ፍቺው ፡ ትግ ፡ አለው ፡ ለአሞንም ፡ ምስ ጋና ፡ አቀረበ ። ሽፍተውብት ፡ የነበሩት ፡ አለቆቹም ፡ ቀርበው ፡ በፊቱ ፡ ተንበርክከው ፡ «ለአምላክህና ፡ ላንተ ፡ ፈቃድ ፡ እንገዛለን» ፡ ሲሉ ፡ ቃላቸውን ፡ ሰጡት ። እሱም ፡ በንግግራቸው ፡ ተደስቶ ፡ ምሕ ረት ፡ አድርጎ ፡ በየአገራቸው ፡ ሰደዳቸው ። ከቀረቡት ፡ የመዠመ ሪያ ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ፓከን ፡ የሚባለው ፡ የፓ ፡—ስፔት ፡ (ዓረብያ ?) ፡ ሹም ፡ ነው ።

ታኑቷሙን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከአደረገ ፡ በኋላ ፡ ምርኮውን ፡ እን ደያዘ ፡ በደስታ ፡ ከሰሜናዊ ፡ ግብፅ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደናፓታ ፡ ተመ ለሰ ።

ይህ ፡ አተራረክ ፡ ራሱ ፡ በዘመኑ ፡ እንደፈቃዱ ፡ በሠራው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ራሱ ፡ ያስቀረጸው ፡ ንግግር ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳመለከትነው ፡ የጥንት ፡ ነገሥታት ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ ሰው ፡ ካልተ ረከባቸው ፡ በቀር ፡ ራሳቸው ፡ በሚያስቀርጹት ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚያጽፉት ፡ ታሪክና ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ ከብራቸውን ፡ ድል ፡ አድራጊነታቸውን ፡ ጻድቅነታቸውን ፡ ሐቀኛ ፡ ፈራጅነታ ቸውን ፡ ኢያጋነኑ ፡ ከማስቀረጽና ፡ ከማጻፍ ፡ በቀር ፡ ከሠሩት ፡ በጎ ፡ ተግባር ፡ ጋር ፡ የሠሩትን ፡ ስሕተት ፡ ይኸም ፡ ቢቀር ፡ በድል ፡ አድ ራጊነታቸው ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰባቸውን ፡ ድል ፡ መሆን ፡ በፍጹም ፡ አይጠቅሱም ። በጥንትም ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ታሪ ክም ፡ በአገራችን ፡ በአክሱምና ፡ በላስታ ፡ በሸዋና ፡ በጐንደር ፡ የነ በሩ ፡ ነገሥታትም ፡ እንደዚሁ ፡ ያውሮፓና ፡ የምሥራቅ ፡ ነገሥታ ትም ፡ «በጦርነት ፡ ተሸንፌ ፡ ሸሸሁ ፤ ፈርቼ ፡ ተማረኩሁ ፤ ሳይቀናኝ ፡ ቀርቶ ፡ ድል ፡ ተመታሁ» ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በዘመናቸው ፡ በሚጻፈው ፡ ዜና ፡ መዋዕልና ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ተቀርጾም ፡ ተጽፎም ፡ አይገ ኝም ። ከነርሱ ፡ ሹመትና ፡ እንጀራ ፡ የሚጠብቀውም ፡ ጸሐፊና ፡ ሠራተኛ ፡ ደስ ፡ የሚላቸውን ፡ ንግግር ፡ በምስጋና ፡ በውዳሴ ፡ በማ ጋነን ፡ እየተፈላለገ ፡ ከመጻፍ ፡ በቀር ፡ ከፉውን ፡ ከደጉ ፡ ከብሩን ፡ ከሐሣሩ ፡ ቀላቅሎ ፡ እየበረዘ ፡ መጻፍ ፡ አይቻለውም ። በዚህ ፡ ፈንታ ፡



ስለነገሥታቱ ፡ በየዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ አሁንም ፡ ባለፈውም ፡ በሚ መጣውም ፡ ተጽፎ ፡ ሲነገር ፡ የምንሰማው ፡ ንጉሡ ፡ የአምላክ ፡ ልጁና ፡ ወዳጁ ፤ ጠላቶቹ ፡ በፊቱ ፡ የማይቆሙ ፤ ብቻውን ፡ ወይም ፡ ቲንሽ ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ሺውን ፡ የሚያባርር ፤ ለወዳጁ ፡ ቸር ፤ ለጠ ላቱ ፡ የማይበገር ፡ እየተባለ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ማናቸውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የተደረገ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በምስጋና ፡ ቢሸፈንም ፡ በቃለ ፡ አጋኖ ፡ ቢከለልም ፡ ምሥጢሩ ፡ የሚገለጽበት ፡ ምክንያትና ፡ ጊዜ ፡ አይጠፋም ። ንጉሡ ፡ ሲሞት ፡ ነዋሪው ፡ አዛውንት ፡ ከታሪኩ ፡ እየ ለየ ፡ ያወራዋል ። በዚህም ፡ ላይ ፡ በወሰን ፡ የሚገኝ ፡ ባላጋራም ፡ ወዳጅም ፡ የሆነ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ከሁሉም ፡ ባዕድ ፡ የሆነ ፡ ሹመትና ፡ እንጀራ ፡ ደጅ ፡ የማይጠና ፡ ሰው ፡ እውነት ፡ የመ ሰለውን ፡ ተፈላልጎ ፡ ሲጽፈው ፡ ምውታኑ ፡ ነገሥታት ፡ በሕይወታ ቸው ፡ ያጻፉት ፡ ጨርሶ ፡ ከመሠረቱ ፡ እንኳን ፡ ባይፈርስ ፡ ከውስጡ ፡ የሚመዛዘንና ፡ የሚመሳሰል ፡ መንገድ ፡ ይገኝበታል ።

አሁንም ፡ ታኑታሙን ፡ በራሱ ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ያስቀረጸው ፡ ሕልሙና ፡ ፍችው ፡ ከናፓታ ፡ ተነሥቶ ፡ በኤሌፋንቲንና ፡ በቴብ ፡ አድርጎ ፡ መምፌስ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ መግባቱ ፤ የታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ማስገበሩ ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ ከአስ ገበረ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ አባቶቹን ፡ ሻባካንና ፡ ታር ሐቃን ፡ የአሦር ፡ ነገሥታት ፡ እነሳርጎንና ፡ እነአሣርሐዶን ፡ እንዳባ ረሩዋቸው ፡ እሱንም ፡ የአሦሩ ፡ ንጉሥ ፡ አሱርባኒፓል ፡ ከታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ በጦርነት ፡ አሸንፎ ፡ እንዳባረረው ፡ ሐውልቱ ፡ አይገልጽም ። ዛሬ ፡ ከአሱርባኒፓል ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ከግብፃውያኑም ፡ ራሱም ፡ ከአስቀረጸው ፡ ሐውልት ፡ ተዋጥቶ ፡ እየተመረመረ ፡ የተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ ስለርሱ ፡ የሚለው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተጻፈው ፡ ዓይነት ፡ ነው ። ከዚሁ ፡ ግማሹ ፡ ያለፈውን ፡ አተራረክ ፡ የሚያጸድቅ ፡ እንጂ ፡ ጨርሶ ፡ የሚያፈርስ ፡ አይደለም ።

ታኑታሙን ፡ አንድ ፡ እባብ ፡ በግራዬ ፡ አንድ ፡ እባብ ፡ በቀኜ ፡ ሲወጣ ፡ በሕልሜ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ነቢያትና ፡ ሕልም ፡ ፈችዎች ፡ ሁለቱን ፡ አገር ፡ የመግዛትህ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተርጕመውለታል ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ትልቁ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡

ታርሐቃ ፣ ሲሞት ፣ ገና ፣ አስቀድሞ ፣ ሥልጣንና ፣ ግዛት ፣ ሲካፈል፣ ቆይቶ ፣ ነበርና ፣ በናፓታ ፣ ከነገሠ ፣ በኋላ ፣ ጉዞውን ፣ ወደኤሌፋንቲን ፣ ቀጥሎ ፣ ከዚያ ፣ ቴብ ፣ ገብቷል ። ይኸ ፣ ሁሉ ፣ አገር ፣ ከብዙ ፣ ጊዜ ፣ ዠምሮ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ነገሥታትና ፣ የአምላካቸው ፣ የአሞን፣ ይዞታ ፣ (አጥቢያ) ፣ ስለሆነ ፣ እስከ ፣ ቴብ ፣ ድረስ ፣ የሚቃወመው ፣ አላገኘም ። እንዲያውም ፣ በየመንገዱ ፣ «በሰላም ፡ ግባ ፣ ለግብፅ ፣ ሕይወት ፣ ስጥ ፣ የወደቁትን ፣ ቤተ ፣ መቅደሶች ፣ አንሣ ፣ ሐውልቶችንና ፣ ምስሎችን ፣ አቃና ፣ ስአማልከቱ፣መሥዋዕታቸውን ፣ አቅርብ። ስለታቸውን ፣ ስጥ ፣ በበዓላቸው ፣ ይከበሩ ፣ ዘንድ ፣ ካህናቶችን ፣ በየቤተ ፣ መቅደሳቸው ፣ አስማራ» ፣ እንዳሉት ፣ ተጽፏል ። ከቴብ፣ ተነሥቶ ፣ መምፌስ ፣ ሲደርስ ፣ ግን ፣ በአሶር ፣ መንግሥት ፣ ሥልጣን ፣ ውስጥ ፣ የነገሡት ፣ ኺያ ፣ የሚሆኑት ፣ የሰሜናዊው ፣ ግብፅ ፣ ነገሥታት ፣ ከነዋሪው ፣ ከአሶር ፣ ወታደር ፣ ጋር ፣ ሆነው ፣ ተዋጉት ። ነገር፣ ግን ፣ ድል ፣ አድርጐአቸው ፡ እስከ ፣ ዴልታ ፡ ድረስ ፣ አባረራቸው ። በዚያም ፣ እምሽጋቸው ፣ ገብተው ፣ ስለተደበቁ ፣ ወደ ፣ መምፌስ ፣ ተመለሰ ። መምፌስ ፣ ሳለ ፣ እነዚሁ ፣ ነገሥታት ፣ እላይ ፣ ሐውልቱ፣ እንደገለጸው ፣ ከመካከላቸው ፣ ፓኬሩሪ ፣ የሚባለውን ፣ የፓስፒድን፣ መስፍን ፣ መሪ ፣ አድርገው ፣ ባንድነት ፣ ምሕረትን ፣ ለምነው ፣ ገቡለት ። በፊቱም ፣ እንደዚህ ፣ ሲሉ ፣ ተናገሩ « ፣ የሕይወት ፣ መንፈስ፣ ስጠን ፣ አንተን ፣ የከበደ ፣ ሕይወት ፣ የሰውምና ፣ በነገሥህበት ፣ ቀን፣ እንደተናገርኸው ፣ በበታችህ ፣ እንዳሉት ፣ ሰዎች ፣ እንሆናለን ፣ . . . . . » እንደሐውልቱ ፣ አነጋገር ፣ ግርማዊነቱ ፣ ይኸን ፣ ሲሰማ ፡ ልቡ ፣ በደስታ ፣ ተመላ ፣ መብልና ፣ መጠጥም ፣ አዘዘላቸው ።

አሱርባኒፓል ፣ አንግሦ ፣ የላከው ፣ ኒካዎ ፣ ግን ፣ ስለተዋጋው ፣ ማርኮ ፣ ገደለው ፣ ኒካዎም ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ ልጁ ፣ ፕሳሜቲክ ፣ ከመምፌስ ፣ ሸሽቶ ፣ ወደ ፣ ነነዌ ፣ ሂዶ ፣ ከአሱርባኒፓል ፣ ጋር ፣ ተገናኝቶ ፣ የሆነውን ፣ ሁሉ ፣ በዝርዝር ፣ ነገረው ። ኃይለኛው ፣ አሱርባኒፓል ፣ የአሶር ፣ ንጉሥ ፣ በከተማው ፣ በነነዌ ፣ ሳለ ፣ ታኑታሙን ፣ ያደረገውን ፣ ሁሉ ፣ በሰማ ፣ ጊዜ ፣ ተናዶ ፣ ራሱ ፣ ጦሩን ፣ እየመራ ፣ ወደ ግብፅ ፣ መጣ ። በዚያን ፣ ጊዜ ፣ ታኑታሙን ፣ ቀደም ፣ ብሎ ፣ ምርኮውን ፣ ሁሉ ፣ እንደያዘ ፣ ወደቴብ ፣ ተመልሶ ፣ ነበርና ፣ ከአሱርባኒፓል ፣ አልተገናኘም ። ነገር ፣ ግን ፣ የአሶራውያን ፣ ጦር ፣ የታኑታሙንን ፣ ጦር ፣ እያባደደ ፣ ታኑታሙንን ፣ በቴብ ፣ ስለደረሰበት ፣ ቴብን፣ ለቆ ፣ ወደ ፣ አባቶቹ ፣ አገር ፣ ወደ ፡ ናፓታ ፣ መጣ ።



ታኑታሙን ፣ ከነሠራዊቱ ፣ የለቀቀውን ፣ በጣም ፣ ስመ ፣ ጥር ፣ የሆነውን ፣ የቴብን ፣ ከተማ ፣ የአሞንን ፣ ቤተ ፣ መቅደስና ፣ የሚያማምረውን ፣ ቤተ ፣ መንግሥት ፣ ሁሉ ፣ የአሶር ፣ ወታደሮች ፣ ከፉኛ ፣ በዘበዙት ። ከቤተ ፣ መንግሥትና ፣ ከቤተ ፣ መቅደስ ፣ የተገኘውንም ፣ ዓይነት ፣ ወርቅና ፣ ብር ፣ ልብስና ፣ መጣሪያ ፣ እየተዘረፈ ፣ ከሐውልቱ ፣ ጋር ፣ ወደነነዌ ፣ ተጋዘ ።

በዚያ ፣ ዘመን ፣ (፯፻፷፯ ፣ ዓመት ፣ ከክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በፊት)፣ ቴብን ፣ ያገኛት ፣ እልቂትና ፣ ዘረፋ፤ እስከ ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ ድረስ ፣ እንዳታንሰራራ ፣ አድርጓት ፣ ነበር ። ይኸውም ፣ ይታወቅ ፣ ዘንድ ፣ ከሃምሳ ፣ ዓመት ፣ በኋላ ፣ በእስራኤል ፣ የተነሣው ፣ ናሆም ፣ የሚባለው ፣ ነቢይ ፣ በዘመኑ ፣ በራዕይ ፣ በነነዌ ፣ ከተማ ፣ ወደፊት ፣ የሚደርስባትን ፣ ውድቀት ፣ ሲገልጽ ፣ በአሁኑ ፣ ሰዓት ፣ በቴብ ፣ የደረሰውን፣ አንሥቶ ፣ እንደዚህ ፣ ይላል « ፣ እነሆ ፣ እኔ ፣ ባንቺ ፣ (በነነዌ)፣ ላይ ፣ ነኝ ፣ ይላል ፣ እግዚአብሔር ፣ የሠራዊት ፣ ጌታ ፣ ልብስሽንም ፣ በፊትሽ ፣ እገልጣለሁ ፣ ለአሕዛብም ፣ ራቁትሽን ፣ አሳየሁ ፣ ለመንግሥታትም ፣ ነውርሽን ፣ . . . . . የሚያይሽም ፣ ሁሉ ፣ ካንቺ ፣ እየሸሸ ፣ ነነዌ ፣ ተፈታች ፣ ይላል ፣ . . . አንቺ ፣ ከነአሞን ፣ (ከአሞን ፣ ከተማ) ፣ ትበልጫለሽን ፣ በፈሳሾች ፣ መካከል ፣ ከተቀመጠችው ። ውሃም ፣ በዙሪያዋ ፣ ነበራት ፣ ቅጥርዋም ፣ በባሕር ፣ ውስጥ ፣ ነበር ። ኩሽና ፣ ምሥር ፣ ( ኢትዮጵያና ፣ ግብፅ ) ፣ የማይቈጠሩ ፣ ኃይሉዋ ፣ ነበሩ ። ፉጥ ፣ (ፓንታ ፣ ግብፅ) ፣ የማይቈጠሩ ፣ ሉቢም ፣ (ሊብያም) ፣ እርሳቸው ፣ የሚረዱሽ ፣ ነበሩ ። ነገር ፣ ግን ፣ እርስዋ ፣ ተጋዘች ፣ ምርኮም፣ ተማረከች ፣ ሕፃናትዋም ፣ ሁሉ ፣ በመንገድ ፣ ራስ ፣ ላይ ፣ ተፈጠፈጡ ። በጌትዎችዋም ፣ ላይ ፣ ዕፃ ፣ ተጣጣሉ ። ታላላቆችዋም ፣ ሁሉ ፣ በሠንሠለት ፣ ታሠሩ - - - » ትንቢተ ፣ ናሆም ፣ ምዕራፍ ፣ ፫ ፣ ቍጥር ፣ ፰—፲ ።

በውነትም ፣ ይህ ፣ ነቢይ ፣ እንዳመለከተው ፣ የአሞን ፣ መቅደስ፣ ያለበት ፣ ይህ ፣ የቴብ ፣ ከተማ ፣ ከቀድሞ ፣ ዠምሮ ፣ ኃያላኑ ፣ ፈርዖ

ኖች ፡ እንቱትሞሲስ ፡ እንራምሴስ ፡ እንቱትአንካሙን ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ ሕንፃና ፡ ሐውልት ፡ ያስጌጡት ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ የማይፈርስ ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እስፈሪውና ፡ ኃይለኛው ፡ ሕዝብ ፡ ተመልሶ ፡ ፈሪ ፡ ምስኪን ፡ እንደሚሆን ፡ የደመቀ ፡ ከተማ ፡ ፈርሶ ፡ ያልደመቀው ፡ መንደር ፡ እንደገና ፡ የደመቀ ፡ ከተማ ፡ ይሆናልና ፡ የዚሁ ፡ ዕጣ ፡ ቴብን ፡ ሲገጥማት ፡ ነቢዩ ፡ እንዳለው፡ የአፍራሾቹን፡ የአሶራውያንን ፡ ከተማ ፡ ነነዌን ፡ ደግሞ ፡ በተራዋ ፡ ሲእክሳር ፡ የሚዶን ፡ ንጉሥ ፡ ከ፶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አፈራርሶ ፡ ራሱን ፡ የአሶርን ፡ መንግሥት ፡ ሲጥለው ፡ ወደፊት ፡ እናገኛለንና ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ እናልፈው ።

የመጨረሻው ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ንጉሥ ፡ ታኑታሙን ፡ ከአሶራውያን፡ ጦር ፡ እየሸሸ፡ከመምፌስ ፡ ወደ ፡ ቴብ ፡ ከቴብ ፡ ወደናፓታ፡ ሔዶ ፡ እንደተቀመጠ ፡ በ፮፻፶፮ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ሞተ ። እንግዲህ ፡ የላዕላይና ፡ የታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ እሶር ፡ ስለያዘው ፡ በናፓታ ፡ በራሳቸው ፡ በኢትዮጵያውያኑ ፡ ( ኑብያ ፡ ) ግዛት ፡ ሽማግሌው ፡ ፒያንኪ ፡ ፫ኛ ፡ የሚባለው ፡ የአሚሪቲስ ፡ ባል ፡ ከታኑታሙን ፡ ቀጥሎ ፡ ነገሠ ። ስለዚህ ፡ ከታኑታሙን ፡ በኋላ ፡ በግብፅ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ገዥነት ፡ ተወግዶ ፡ ሌሎች ፡ ኃያላን ፡ አገሮች ፡ ባቢሎን ፡ ፋርስ ፡ ግሪክ ፡ ሮማ ፡ ዓረብ ፡ ቱርክ ፡ ይፈራረቁባት ፡ ዠመር ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

በግብፅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ፍጻሜ-የኢትዮጵያ ፡ የግዛት ፡ ዘመን ።

ባለፉት፡ምዕራፎች፡እንደ፡ እነበብነው ፡ ግብፆች ፡ ኢትዮጵያውያንን፡ገዝተው ፡ ሲያስገብሩ ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ፡ኢትዮጵያውያን ፡ ደግሞ፡ መልሰው ፡ ግብፅን ፡ ገዙ ። ግብፅንም ፡ የገዙት ፡ የነዚህን ፡ ነገሥታት ፡ ዝርዝርና ፡ የገዙበትን ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞ ፡ ጸሐፊ ፡ እንደመሰለው፡ ሲጽፍ ፡ ያንዱ ፡ ከሌላው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በቲንሹ ፡ በአተራረክ ፡



እምብዛም ፡ ሳይራራቅ ፡ በዘመን ፡ ቊጥር ፡ ይለያያል ። እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፹ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በበጥሊሞስ ፡ ፊላደልፍ ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ ማኔቶን ፡ ( MANETHON ) የሚባለው ፡ በግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ባዘጋጀው ፡ የግብፅ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የጠፋው ፡ ጠፍቶ ፡ በተገኘው ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፤

፩ኛ ፡ ሰበቆን ፡ (ሻባካ) ፡ ፰ ፡ ዓመት ፡

፪ኛ ፡ ሰቢኩስ ፡ (ሻባታቃ) ፡ ፲፬ ፡ ዓመት ፤

፫ኛ ፡ ታርቆስ ፡ ወይም ፡ ታራቆስ ፡ (ታርሐቃ) ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በድምሩ ፡ ሦስት ፡ ነገሥታት ፡ ፵ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ መግዛታቸውን ፡ ይጽፋል ።

የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ እነሙሴ ፡ ማሪዬት ፤ ሙሴ ፡ ሩዠ ፤ ለፕስዩስና ፡ ሬይዝነር ፡ ካታዊ ፡ ፓሻ ፡ ድሪዮቶንና ፡ ሻንድዮ ፡ የቀሩትም፡ ሁሉ ፡ በግብፅ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የተገኘውን ፡ በመከተል ፡ ከ፯፻፶፭-፯፻፲፮ ፡ ዓመት ፡ የገዛውን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ንጉሥ ፡ ፒያንኪንም፡ የ፳፭ኛው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ) ፡ መሥራች ፡ ሳያደርጉ ፡ ከሻበቃ ፡ ዠምረው ፤

፩ኛ ፡ ሻባካ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ከ፯፻፲፮ ፡ እስከ ፡ ፯፻፩ ፡ ዓ፡ከክ፡ል፡በፊት፡
፪ኛ ፡ ሻባታካ ፡ ፲፪ ፡ » ከ፯፻፩ ፡ እስከ ፡ ፮፻፹፱ ፡ » »
፫ኛ ፡ ታርሐቃ ፡ ፳፮ ፡ » ከ፮፻፹፱ ፡ እስከ ፡ ፮፻፷፬ » »
፬ኛ ፡ ታኑታሙን ፡ ፰ ፡ » ከ፮፻፷፬፡እስከ ፡ ፮፻፶፮ ፡ » »
ድምር ፡ የአራቱ ፡ ነገሥታት ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ ፷፩ ፡ ዓመት ፡ ይሆናል ።

ሙሴ ፡ ዠን ፡ ሞሪዬ ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንደቀሩት ፡ ነገሥታት ፡ እዚያው ፡ ተቀምጠው ፡ እደላድለው ፡ ባይገዙ ፡ ወረራ ፡ ከዠመሩት ፡ ከነዜራክ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ እሚን ፡ እሰሮ ፡ ፪ኛ ፡ ድረስ ፡ እንደርሳቸው ፡ እሳብ ፡ ዘመኑ፡ ከ፱፻፹፬ ፡ እስከ ፡ ፯፻፶፭ ፡ ዓመት ፡ አድርገው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዥነት ፡ በግብፅ ፡ የቆየበትን ፡ ዘመን ፡ ፪፻፳፱ ፡ ዓመት ፡ አድርሰውታል ።

እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ተመልክቶ ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ የሚጠጋ ፡ መከካለኛ ፡ መንገድ ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የቀድሞዎቹን ፡ ጸሐፊ

ዎች ፡ የነማኔቶን ፡ ወይም ፡ የሞሪዩን ፡ የመጨረሻ ፡ ምርመራ ፡ በላፈረሰው ፡ እንደደንቡ ፡ የ፳፭ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ መሥራች ፡ ፒያንኪ ፡ ፪ኛው ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። እላይ ፡ እንዳልነው ፡ መሥራች ፡ የሚያደርጉት ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የነገሠውን ፡ ሻባካን ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በፒያንኪና ፡ በሻባቃ ፡ መካከል ፡ ታፍናክታና ፡ ልጁ ፡ በኮሪስ ፡ ጣልቃ ፡ ገብተው ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ግብፅን ፡ ገዝተው ፡ ፳፬ኛውን ፡ የሳይንስ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ መሥርተዋል ፤ በማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በፒያንኪና ፡ በታናፍክታ ፡ መካከል ፡ ሊቀ ፡ ካህን ፡ ባለበት ፡ የተፈጸመውን ፡ መሐላ፤በሻባቃና ፡ በቦኮሪስ፡መካከል ፡ በዚህ ፡ መሐላ ፡ መፍረስ ፡ የተነሣ ፡ የደረሰውን ፡ ጦርነትና ፡ በቦኮሪስ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመውን ፡ ቅጣት ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ፡ በመሐላ ፡ የተወሰነው ፡ እርቅ ፡ እንደሚረጋ ፡ መመልከት ፡ አለብን ፡ ይኸም ፡ ሲሆን ፡ የ፳፭ኛው ፡ ዲናስቲ ፡ መሥራች ፡ ፒያንኪ ፡ ነው ። የርሱም ፡ ግዛት ፡ ዘመን ፡ ከ፯፻፶፩ ፡ እስከ ፡ ፮፻፶፮ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ፺፮ ፡ ዓመት ፡ (እንደሌሎቹ ፡ ፺፩ ) ፡ ሲሆን ፡ ከዚሁ ፡ ፳፩ ፡ ዓመት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ነግሦ ፡ ይሆናልና ፡ የግዛታቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ድምሩን ፡ እንመልከት ።

፩ኛ ፡ ፒያንኪ ፡ ፴፩ ፡ ዓመት ፡
፪ኛ ፡ ሻባካ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡
፫ኛ ፡ ሻባታቃ ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡
፬ኛ ፡ ታርሐቃ ፡ ፳፮ ፡ ዓመት ፡
፭ኛ ፡ ታኑታሙን ፡ ፰ ፡ ዓመት ፤

የፒያንኪ ፡ የኑብያ ፡ ግዛቱ ፡ ፳፩፡ዓመት ፡ ሳይቈጠር ፡ በግብፅ ፡ ላይ ፡ የቆየውን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ግዛት ፡ በድምሩ ፡ ፸፭ ፡ ( ሰባ ፡ አምስት ፡ ) ዓመት ፡ ግድም ፡ ማድረግ ፡ የተሻለ ፡ ይመስላል ።

እንግዲህ ፡ ግብፅን ፡ ከገዙት ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ የመጨረሻው ፡ ንጉሥ ፡ ታኑታሙን ፡ ከግብፅ ፡ ተመልሶ ፡ በናፓታ ፡ በ፮፻፶፫፡ ዓመት ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ከፒያንኪ ፡ ፫ኛ ፡ ቀጥሎ ፡ አሚን ፡ አስሮ ፡ የሚባለው ፡ አደላድሎ ፡ የናፓታን ፡ መንግሥት ፡ ያዘ ፤ ለመጀመሪያውም ፡ ጊዜ ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ ከቀድሞው ፡ አባቶች ፡ ሲያያዝ ፡



እንደመጣው ፡ ከያዘና ፡ ከዚያም ፡ አልፎ ፡ ታሕታይ ፡ ግብፅን ፡ ለመጨመር ፡ ሲል ፡ ከግብፃውያኑ ፡ ተዋግቶ ፡ ሲሸነፍ ፡ እንዲያውም ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ ጭምር ፡ ለቆ ፡ በአገሩ ፡ በኑብያ ፡ (ኢትዮጵያ ፡) ብቻ ፡ ተጠቅልሎ ፡ ተቀመጠ ።

ከግብፅ ፡ አሱርባኒፓል ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ አባሮ ፡ መምፊስንም ፡ ቴብንም ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ይዞ ፡ በዘረፋም ፡ በምርኮም ፡ እያስጨነቀ ፡ ከአስገበረ ፡ በኋላ ፡ በበፊው ፡ ግዛቱ ፡ ያሉ ፡ የከለዳውያንና ፡ የኤላም ፡ የዋራርቶ ፡ ሕዝቦች ፡ ሸፍተዋልና ፡ ድረስ ፡ የሚል ፡ መልእክት ፡ ስለመጣበት ፡ በግሥጋሜ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ።

ስለዚህ ፡ ግብፃውያኑ ፡ ከአሶራውያኑም ፡ ከኢትዮጵያውያኑም፡ የነፃነት ፡ ከፍት ፡ ጊዜ ፡ በማግኘታቸው ፡ የሳይሱን ፡ ንጉሥ ፡ የኒቃዎን ፡ ልጅ ፡ ፔሳሜቲክ ፡ ፩ኛ ፡ የተባለውን ፡ አነገሡ ። በርሱ፡ውስጥ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ አሶራውያን ፡ የደለደሉዋቸው ፡ የየአውራጃው ፡ ኻያ ፡ ነገሥታት ፡ ወይም ፡ እንደሄሮዶቱስ ፡ አጻጻፍ ፡ ዶዴካርሸ ፡ ( የ፲፪ ፡ ነገሥታት ፡ ግዛት ) የሚላቸው ፡ ፲፪ ፡ ነገሥታት ፡ አብረውት ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ፡ ቢሆንም ፡ ከመካከላቸው ፡ አንጋፋው ፤ እንደፈርዖን ፡ የተቈጠረው ፡ ፕሳሜቲክ ፡ ስለሆነ ፡ በጊዜው ፡ የግብፅን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ፡ የተቻለውን፡ ሁሉ ፡ አደረገ ። በውስጡም ፡ ከግሪክ ፡ አውራጃ ፡ ይበልጥ ፡ ዋጋ ፡ ለበጣቸው ፡ ወገን ፡ እየተገዙ ፡ የሚዋጉ ፡ ዠግኖቹን ፡ የግሪክ ፡ ተወላጆችን ፡ ቀጥሮ ፡ የሚቀናቀኑትን ፡ በነሱ ፡ እያስመታ ፡ በተረፈ ፡ ራሱ ፡ በሰላማዊ ፡ አስተዳደር ፡ ይደክም ፡ ጀመር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ግሪኮች ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ባለሙዋልነትን ፡ አግኝተው ፡ በሥራ ፡ ሲረዱት ፡ የግብፃውያኑና ፡ የሊብያዎቹ ፡ ተወላጆች ፡ በግሪኮቹ ፡ ባለሙዋልነት ፡ ቅር ፡ ስለአላቸው ፡ ውስጡን ፡ ለአስተዳደሩ ፡ አልተባበሩለትም ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ ፖለቲካው ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ችግር ፡ ሲፈጥርበትና ፡ እርሱም ፡ ችግሩን ፡ በትግልና ፡ በብልሐት ፡ ለማሸነፍ ፡ ሲጣጣር ፡ ሊያሸንፈው ፡ ያልቻለው ፡ በታናሽ ፡ እስያ ፡ ከአሶር ፡ በኋላ ፡ የተነሣውን ፡ የባቢሎንን ፡ ወራሪነት ፡ ነው ። ኢትዮጵያውያን ፡ ለዘለቄታ ፡ በአገራቸው ፡ በናፓታ ፡ ሲቀሩለት ፡ በአሶር ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ የባቢሎን ፡ መንግሥት ፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ሁሉንም ፡ አገሮች ፡ ከወረራቸው ፡ በኋላ ፡ ወደግብፅ ፡ መጣ ፡ ያመጣጡን ፡ ከመተረካችን ፡ በፊት ፡ ከአሶራውያን ፡ ጋር ፡ የተጣመረውን ፡ አጭር ፡ ታሪኩን ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

### የመዠመሪያው ፡ የባቢሎን ፡ መንግሥትና ፡ ንጉሡ ፡ ሐሙራቢ— የጐረቤቱ ፡ የአሶር ፡ መንግሥት ፡ መነሣት ።

ግብፅ ፡ ኃያል ፡ ሥልጣን ፡ ጥበበኛ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ሌሎች ፡ የሠለጠኑ ፡ አገሮች ፡ ነበሩ ። እነርሱም ፡ በጤግሮስና ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዞች ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በመገኘታቸው ፡ ግሪኮች ፡ «ሜሶፖታሚያ ፡ በሁለት ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ » ብለው ፡ የሰየሟቸው ፡ የባቢሎንና ፡ የአሶር ፡ አገሮች ፡ ናቸው ። ከነርሱም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ከለዳውያን ፡ አሉ ። የነዚህም ፡ ከተሞች ፡ የአሶራውያን ፡ ነነዌ ፤ የባቢሎናውያን ፡ ባቢሎን ፤ የከለዳውያን ፡ ኡር ፡ ስመ ጥርነታቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል።

ከነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ በሰሜን ፡ በጤግሮስ ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ አሶር ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በሐሙራቢ ፡ ጊዜ ፡ ደካማ ፡ ስለነበረ ፡ ለባቢሎን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አውራጃ ፡ ይቈጠር ፡ ነበር ። ከሐሙራቢ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አሶር ፡ ኃይለኝነትን ፡ አግኝቶ ፡ ባቢሎንና ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመለከታለን ።

በባቢሎንና ፡ በአሶር ፡ ነምሩድ ፡ የሚባል ፡ አደን ፡ የሚወድ ፡ ኒኑስ ፡ የሚባል ፡ የነነዌን ፡ ከተማ ፡ የከተመ ፡ ሰሚራሚስ ፡ የምትባል ፡ የባቢሎንን ፡ ከተማ ፡ ያስጌጠች ፡ ተዋጊ ፡ ንግሥት ፡ ሰርዳናፓል ፡ የነነዌ ፡ ከተማ ፡ በጠላት ፡ ቢከበብበት ፡ ሀብቱንና ፡ ቤቱን ፡ ሰብስቦ ፡ በፈቃዱ ፡ ከእሳት ፡ ነበልባል ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሞተ ፡ የሚሉት ፡ ነገሥታት ፡ እንደነበሩ ፡ በጥንት ፡ የግሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድና ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ይገኛል ።



ስለአሶርና ፡ ባቢሎን ፡ ሕዝብ ፡ በየታሪኩ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚገኘው ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ከወደ ፡ ሰሜን ፡ የወረዱ ፡ ሱሜሪያን ፡ የሚባሉት ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ አካድያን ፡ የሚባሉ ፡ ዘራቸው ፡ ሴማዊ ፡ የሆነ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ይዘው ፡ ሱሜሪያን ፡ የተባሉት ፡ የኡርን ፡ ከተማ ፡ አካድያን ፡ የተባሉት ፡ የአካድን ፡ ከተማ ፡ ከትመው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከነዚሁ ፡ ከሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ አካድያን ፡ የተባሉት ፡ የሴም ፡ ዘሮች ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተሻገሩት ፡ ጋር ፡ የፊደልና ፡ የቋንቋ ፡ የዘር ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ እንዳለ ፡ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያምናሉ ።

እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ ከዋነኛው ፡ ንጉሥ ፡ ከሐሙራቢ ፡ በፊት ፡ ከሦስት ፡ ሺ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ መንግሥት ፡ እቁመው ፡ በነገሥታት ፡ መመራታቸው ፡ በዛሬ ፡ መርማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ታውቋል። ሱመሪያን ፡ በነበሩበት ፡ ክፍል ፡ በተለይ ፡ ቴሎ ፡ በተባለው ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ ጉዴያ ፡ የተባለ ፡ መስፍን ፡ (ንጉሥ ?) ኒን ፡ ጊርሱ ፡ ለሚባለው ፡ አምላኩ ፡ የሚያሠራውን ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፤ ፕላን ፡ በእጁ ፡ እንደያዘ ፡ ሐውልቱ ፡ ተሠርቶ ፡ በሐውልቱ ፡ ላይ ፡ ንጉሡ ፡ ለአምላኩ ፡ እንደዚህ ፡ ሲለው ፡ ይነበባል ። « ንጉሥ ፡ ሆይ ፤ ኒን ፡ ጊርሱ ፡ ሆይ ፡ ጐርፍን ፡ (መዓትን ?) የምታቆም ፡ . . . ፡ ትእዛዝህን ፡ በትክክል ፡ እፈጽማለሁ ። ኒን ፡ ጊርሱ ፡ ሆይ ፡ ቤተ ፡ መቅደስህን ፡ በደስታ ፡ አሠርቼ ፡ ወደ ፡ ዚያ ፡ አገባኻለሁ ። . . . ባርከው ፡ ባርከው ፡ . . . » ይልና ፡ ቀጥሎ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ የተመረቀበት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ሙሉ ፡ በዓል ፡ ተደርጎ ፡ በዚህ ፡ በዓል ፡ ሰሞን ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ገረድ ፡ ከእመቤቷ ፡ አሽከር ፡ ከጌታው ፡ የእኩልነት ፡ መብት ፡ አግኝተው ፡ በደስታ ፡ እንደዋሉ ፡ እንደዚሁ ፡ ክፉ ፡ ነገሮች ፡ ወደ ፡ ደግ ፡ እንደ ተለወጡ ፡ ያመለክታል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሱሜርና ፡ አካድ ፡ በተባሉት ፡ ዘሮች ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ ሴማዊ ፡ ዘሮች ፡ በየጊዜው ፡ እየተደባለቁ ፡ የከለዳውያንና ፡ የባቢሎንን ፡ የመዠመሪያውን ፡ መንግሥት ፡ ከቀድሞው ፡ የበለጠ ፡ አቋቋሙ ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ ተደጋግማ ፡ የተ

ነግቸው ፡ የባቢሎን ፡ ከተማ ፡ በሁለት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ እና፡ በሁለት ፡ ሺ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ተመሥርታ ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየደመቀች ፡ ሄደች ። ከአሶር ፤ ከሜዶን ፤ ከሕንድ ፡ ከፋርስና ፡ ከአ ርመን ፤ ከግብፅ ፡ ለሚመጡ ፡ ነጋዴዎች ፡ ዋና ፡ መገናኛና ፡ የሸቀጥ ፡ መገበያያ ፡ መደብር፡ሆነች። እንደዚሁ ፡ ሆና ፡ በደመቀችበት ፡ ጊዜ ፡ ሐሙራቢ ፡ የሚባል ፡ ኃይለኛነትን ፤ ዐዋቂነትን፡ከሕግ ፡ ሐጋጊነት ፡ ጋር፡አጣምሮ ፡ የያዘ ፡ ንጉሥ ፡ ተነሣላቸው ። እርሱም ፡ ለባቢሎን ፡ መንግሥት፡ለመዠመሪያው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ) ፮ኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ። ይህ ፡ ንጉሥ ፡ የነበረበትን ፡ ዘመን ፡ የቀድሞ ፡ ሊቃ ውንት ፡ ፪ሺ ፡ ፩፻ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ሲያደርጉት ፡ የቆዩትን ፡ ያሁን፡ ሊቃውንት ፡ እነቦታ ፡ ( Botta ) እነደላፖርት ፡ ( Delaporte ) እነሞ ርጋ ፡ (Morgan) ፪ሺ፩፻ ፡— ፩ሺ፱፻፷፩ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ከከር ቡትና ፡ በፊት ፡ ላይ ፡ አሳርፈውታል ።

ሐሙራቢ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ነገድ ፡ የሚቈጠሩ ትን ፡ አካድንና ፡ ሱሜርን ፡ በአንድነት ፡ አዋሕዶ ፡ የአሶርን ፤ የኤላ ምን ፤ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ እየወጋ ፡ የባቢሎን ፡ ወይም ፡ የከለዳውያን ፡ መንግሥት ፡ የሚባለውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው ።

ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የሐሙራቢ ፡ በመ ፡ ጥርነት ፡ ሕግና፡ ፍትሐ፡ ነገሥት ፡ በማውጣት ፡ ነው ። እርሱ ፡ የሕግና ፡ የሰላም ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ያወጣቸው ፡ ሕጎች ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንደሚሉ ፤ በምን ፡ ቋንቋ ፤ በምን ፡ ፊደል ፤ እምን ፡ ላይ ፡ እንደተጻፉ ፡ መርማ ሪው ፡ ሁሉ ፡ ከቀድሞው ፡ በበለጠ ፡ በትክክል ፡ ለመረዳት ፡ በሚፈ ላለግበት ፡ ጊዜ ፡ ሞርጋን ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሳዊ፡ተወላጅ ፡ እንደ ኤው ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፱፻፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሱስ ፡ በሚባል ፡ (በኤላም፡ አገር፡ የከተማ ፡ ፍራሽ ፡ ውስጥ ፡ ከሐሙራቢ ፡ ሕጎች ፡ አጋማሹን ፡ ፪ ፡ ሜትር ፡ ከ፳፭ ፡ ሳንቲም ፡ ቁመት ፡ ባለው ፡ ባንድ ፡ ጥቁር፡ ደንጊያ፡ ላይ ፡ ተቀርጾ ፡ አገኘው ። በዚሁ ፡ ደንጊያ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ወገን ፡ ሻማሽ ፡ (ወይም ፡ ስሀ ፡ ማስሀ) የሚባለው ፡ የፍርድ ፡ አምላክ ፡ በዙ ፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ጸሐፊ ፡ ብርዕ ፡ ጨብጦ ፡ በፊቱ ፡ ንጉሡ ፡ ሐሙራቢ ፡ በትሕትና ፡ ቆሞ ፡ ሕግ ፡ እንደሚጠይቀ ውና ፡ አምላኩ ፡ እንደሚነግረው ፡ ዓይነት ፡ ይታያል ። በላዩ ፡ ላይ ፡



ሐሙራቢ ፡ ከአምላኩ ፡ ተቀብሎ ፡ በለቤተ ፡ ሰብ ፡ አኗኗር ፡ ስለግል ፡ ሀብት ፡ ስለሥራ ፤ ስለመቃጸርንት ፡ ለሕዝቡ ፡ የሰጠው ፡ ሕግ ፡ በጥ ንቱ ፡ የባቢሎናውያን ፡ ፊደል ፡ ተጽፎ ፡ ተገኘ ። ከዚያ ፡ በየጊዜው፡ ከባቢሎናውያን ፡ ቋንቋ ፡ ወደየቋንቋቸው ፡ ተተረጐሙ ። ወደፈረን ሳዊ ፡ ከተተረጐሙው ፡ ውስጥ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ስንመል ሰው ፡ በውስጡ ፡ ሐሙራቢ ፡ ንጉሥ ፡ በዘመኑ ፡ ያወጣው ፡ ሕግ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገኛል ።

## የሐሙራቢ ፡ ሕግ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ የመሬቱን ፡ ግድብ ፡ ከመሥራት ፡ ቸል፡ ብሎ፡ የውኃ ፡ ጉርፍ ፡ በርሱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ የሌላውን፡ መንደር፡ ስንዴ ፡ ( ሰብል ) ፡ ያበላሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቸልተኛው ፡ ይከፍላል ። መክፈል ፡ ቢያቅተው ፡ እርሱ ፡ ከነንብረቱ ፡ ይሸጥና ፡ መንደረተ ኞቹ ፡ ይካፈሉ ።

አንድ ፡ ባለመሬት ፡ መሬቱን ፡ እንዲያርስለት ፡ ላንድ ፡ ገበሬ ፡ ሰጥቶ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ሲያርስና ፡ እርሻውን ፡ ሲያስለልሰው ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ገበሬውና ፡ ባለመሬቱ ፡ ሰብሉን ፡ እኩል ፡ ይካፈሉ ።


አንድ ፡ ሰው ፡ ከሌላው፡በሬ ፤ ወይም፡አህያ ፡ ተውሶ ፡ በሜዳ ፡ ሳለ ፡ አንበሳ ፡ መጥቶ ፡ ከብቱን ፡ የበላበት ፡ እንደሆነ ፡ ባለቤቱ ፡ ሊከፍለው ፡ አይችልም ።

አንድ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ የመታ ፡ እንደሆነ ፡ እጁን ፡ ይቆረጥ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ነፃ ፡ የሆነውን ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ዓይን ፡ አን ቁሮ ፡ ያጠፋው ፡ እንደሆነ ፡ የርሱንም ፡ ያጥፉበት ።

አንድ ፡ ሐኪም ፡ በጠና ፡ የታመመውን ፡ ነፃ ፡ ሰው ፡ በመዳብ፡ ወስፌ ፡ አከምቶ ፡ የገደለው ፡ እንደሆነ ፡ እጁን ፡ ይቆረጥ ።

አንድ ፡ መሐንዲስ ፡ ያነጹን ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ በጥንካሬ ፡ ሳይሠ ራስት ፡ ቀርቶ ፡ ያ ፡ ቤት ፡ ወድቆ ፡ ባለቤቱን ፡ የገደለው ፡ እንደሆነ መሐንዲሱ ፡ ይገደል ። የባለቤቱ ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡ የሞተው ፡ የመ



ሐሙራቢ ፡ ከፀሐዩ አምላክ ፡ ከሻ
ማሽ ፤ ሕግን ፡ እየሰማ ፡ ሲቀበል ፡
ሎቭር ።



ሐንዲሱ ፡ ልጅ ፡ ይገደል ። ሰው ፡ ሳይሞት ፡ በቤቱ ፡ መፍረስ ፡ ዕቃ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ የተበሸላው ፡ መሐንዲሱ ፡ ዕቃውን ፡ ይተካና ፡ ቤቱን ፡ በከሣራው ፡ መልሶ ፡ ይሥራለት ።

አንድ ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ወይም ፡ ወታደር ፡ ክተት ፡ ተብሎ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ያልመጣ ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡ ምትክ ፡ የላከ ፡ እንደሆነ ፡ ይገደል ። የርሱንም ፡ ቤት ፡ በምትክ ፡ የመጣው ፡ ሰው ፡ ይውሰድበት ።

እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ከጊዜያችን ፡ አራት ፡ ሺ ፡ ዓመት ፡ ለራቀው ፡ ዘመን ፡ የሚገቡ ፡ ምናልባትም ፡ አስደናቂ ፡ የሆኑ ፡ ለዛሬው፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ያልተጣሩና ፡ ጉድለት ፡ ያላቸው ፡ የሚመስሉንን ፡ ሕግ ፡ ትልቁ ፡ ሐሙራቢ ፡ በዘመኑ ፡ እያዘጋጀ ፡ ሕዝቡን ፡ በደንብና ፡ በሥርዓት ፡ ያስተዳድር ፡ ነበር ። የቀረው ፡ ቀርቶ ፡ በተገናኛችሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰላም ፡ ይሁንልህ ፡ ወይም ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ተባባሉ ፡ ብሎ ፡ ማዘዝ ፡ የዠመረ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ይባላል ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ሐሙራቢ ፡ ሕግ፡ አጋጊው ፡ (ሠሪው) ንጉሥ ፡ ከመባል ፡ ጋር ፡ የሰላም ፡ ንጉሥ ፤ የጽድቅ ፡ ንጉሥ ፡ መባልን ፡ አግኝቷል ።

የእስራኤል ፡ የነገድ ፡ አባት ፡ አብርሃም ፡ መገርመሪያ ፡ የሚቀመጠው ፡ የሐሙራቢ ፡ ከተማ ፡ በምትሆን ፡ በኡር ፡ ነበር ። የኡር ፡ ከተማ ፡ የምትገኘው ፡ በከለዳውያን ፡ ውስጥ ፡ ከባቢሎን ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ነው ። አብርሃም ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ከከለዳውያን ፡ ጋር ፡ ሲኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገልጾለት ፡ «ካገርህ ፡ ውጣ ፡ ከዘመዶችህም ፡ ካባትህም ፡ ቤት ፡ ተለይ ፡ እኔ ፡ ወደማሳይህ ፡ ምድር ፡ (ወደከነአን) ፡ ሲል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን፡ በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ ተጽፏል ።

ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ በዚሁ ፡ በዘፍጥረት፡ በምዕራፍ፡ ፲፬ ፡ አብርሃምን ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፤ የሚባል ፡ የሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህን ፡ የነበረ ፡ እንደባረከው ፡ አብርሃምም ፡ ለዚሁ ፡ ለሰላም ፡ ንጉሥ ፡ ከከብቱ ፡ ሁሉ ፡ ከአሥር ፡ አንድ ፡ (አሥራት)፡ አውጥቶ ፡ እንደገበረለት ፡ ይናገራል ። አንዳንድ ፤ ጸሐፊዎች፡ አብርሃም ፡ የገበረለት ፡ የሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ የተባለው ፡ ሐሙራቢ ፡

ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ የተጠራጠሩ ፡ አሉ ። በእውነትም ፡ ሐሙራቢ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥና ፡ አብርሃም ፡ የነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ፳ኛውና ፡ ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ስለሆነ ፡ ሐሙራቢም ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ሁሉን ፡ ጠቅሎ ፡ የሚገዛ ፡ የሳሌም ፤ ( ሰላም)ና ፡ የጽድቅ ፡ ( ፍርድ ) ንጉሥ ፡ ስለሆነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የተባለው ፡ ሐሙራቢ ፡ ይሆን ፡ ይሆናልና ፡ አሁን ፡ ወደ ታሪኩ ፡ እንመለስ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

የግብፃችና ፡ የአሶራውያን ፡ ልዩነት ፡ የአሶራውያን ፡ ጭካኔ ።

ሐሙራቢ ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በላይ፡ገዝቶ ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ እየተከታተሉ ፡ በነገሡበት ፡ ዘመን ፡ የባቢሎን ፡ መንግሥት ፡ ድካም ፡ ተሰማው ፡ ሊያደክሙት ፡ የቻሉትም ፡ የርሱ ፡ ተገዥ ፡ የነበሩት ፡ በሰሜን ፡ ያሉት ፡ አሶራውያን ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ሕዝቦች ፡ እነ ራምሲስ ፡ ዳግማዊ ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፤ የተዋጉዋቸው ፡ የሂቲቲ ፡ የኬታ ፡ ነገዶች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ካሲት ፡ ከተባሉት ፡ ጋር ፡ ኅብረት ፡ አድርገው ፡ በከተማቸው ፡ በአሱር ፡ ሲኖሩ ፡ በኋላ ፡ በሺ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ግድም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወርደው፡ ከሕዝቡ፡ ተዋግተው ፡ የባቢሎንን ፡ ከተማ፡ ዘርፈው ፡ የሐሙራቢን ፡ ገናናውን ፡ የባቢሎንን ፡ መንግሥት ፡ መልሰው ፡ የአሶር ፡ መንግሥት ፡ አውራጃ ፡ አደረጉት ። እንደዚሁም ፡ በአጠገቡ ፡ ካሉት ፡ አገሮች ፡ መካከል፡የሚዶን፡መንግሥት ፡ እየለና ፡ ግዛት ፡ ለግዛት፡ሲቀማሙ ፡ ቆይተው ፡ እንደዚሁም፡ባቢሎናውያንም ፡ እየሸፈቱ ፡ ከአሶር ፡ ተገዥነት ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ ሲታገሉ ፡ አሶራውያኑ ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እያየሉ ፡ ሔዱ ። ነገሥታቶቻቸው ፡ ስልምናጽር ፤ ሳርጎን ፤ ሰናክሬም ፤ አሳርሐዶን ፤ አሱርባኒፓል ፡ ኃይላቸውንና ፡ ገናንነታቸውን ፡ በጭካኔ ፡ አረጋገጡ ። በዙሪያቸው ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ባቢሎንን ፡ ኤላምን ፡ ሰማርያንና ፡ ይሁዳን ፡ ፍልስጥኤምን ፡ ሞዓብን ፡ ሐማትን ፡ እየተዋጉ ፡ በማሸነፍ ፡ የማረኩትን ፡ ነገሥታት ፡ ከነሕይወታቸው ፡ ቆዳቸውን ፡ እየገፈፉ ፡ በመቅጣት ፡ የቀረውንም ፡ ምርኮኛ ፡ በጅምላ ፡ በወታደር ፡



በግራ ፡ ክፉዩት ፡ በቀኝ ፡ ደጉ ፡ መንፈስ ፡ ( ማርዱክና ፡ ቲአማት ? ) ለትግል ፡ ጠብ ፡ ሲገጥሙ ።

CITY - HALL LIBRARY
of
ADDIS ABABA

እያንጋጉ ፡ ወንዱንና ፡ ሴቱን ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ እየወሰዱ ፡ ሥራ ፡ በማሠራት ፡ ግዛታቸውን ፡ አጸኑ ።

ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ ሳርጎን ፡ ከኢትዮጵያዊው ፡ ፈርዖን ፡ ከሻባካ ፡ (ሰባኮን) ጋር ፤ ልጁ ፡ ሰናክሬም ፡ ደግሞ ፡ ከሻባቶካና ፡ ከታርሐቃ ፡ ጋር ፡ አሣርሐዶን ፡ ከታርሐቃ ፡ ጋር ፤ አሱርባኒፓልም ፡ ከታኑታሙን ፡ ጋር ፡ ያደረጉትን ፡ ጦርነት ፡ ተመልክተናል ።

በጠባይና ፡ በመልክ ፡ ግብፃውያንና ፡ አሶራውያን ፡ በጣም ፡ ይለያያሉ ። አሶራውያን ፡ በየታሪኩ ፡ በየሐውልቱ ፡ ላይ ፡ እንደሚታዩት ፡ ፊታቸው ፡ ረዥምም ፡ አፍንጫቸው ፡ ዘለግ ፡ ያለ ፤ ጢማሞች ፤ ሰውነታቸው ፡ ጠንካራ ፡ ጥብቅ ፡ ሲሆን ፡ ግብፃውያኑ ፡ ፊታቸው ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ክብነት ፡ ያደላል ። በጠባይ ፡ ደግሞ ፡ አሶራዊ ፡ ለሰው ፡ የማይሳሳ ፡ ጨካኝ ፡ ለምርኮኛው ፡ የማይራራ ፡ በመዋጋትና ፡ ደም ፡ በማፍሰስ ፡ ደስታ ፡ የሚሰማው ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሥጋዊነት ፡ ወደ ፡ ጥቅም ፡ የሚያዘነብል ፡ ሲሆን ፡ ግብፃዊው ፡ በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ ርቀት ፡ መንፈሳዊነት ፡ የቀለም ፡ ሰውነት ፡ ይስማዋል ። ባለፈው ፡ ታሪኩ ፡ እንዳነበብነው ፡ ግብፃዊ ፡ በገዥነት ፡ መዋጋቱ ፡ ከማረካቸው ፡ ውስጥ ፡ ለየአማልክቱ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ልማድ ፡ እየመታ ፡ ወይም ፡ እያረደ ፡ መሠዋቱ ፡ ባይቀር ፡ በጅምላ ፡ በምርኮኛ ፡ ላይ ፡ እንደአሶራዊ ፡ ጭካኔና ፡ የዕብሪት ፡ አገዳደል ፡ አይፈጽምም ።

ስለአሶራውያን ፡ ተዋጊነትና ፡ ጭካኔ ፡ ለመረዳት ፡ አሡር ፡ ናዚር ፡ አባል ፡ የሚባለው ፡ በ፰፻፹፬ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ግድም ፡ የነገሠው ፡ ንጉሥ ፡ ራሱ ፡ በዘመኑ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወደ ፡ ሸፈተ ፡ አገር ፡ ዘምቶ ፡ ሲመለስ ፡ በደንጊያ ፡ ላይ ፡ ያስቀረጸውን ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ስንመለከት ፡ የአሶራውያንን ፡ ጭካኔ ፡ ያስረዳናል ።

« ተራራውን ፡ አልፌ ፡ ሔድሁ ፡ ወደ ፡ ሁላይ ፡ ምሽግ ፡ ወደ ፡ ኪናቡ ፡ ደረስሁ ፤ እንዳንድ ፡ የነፋስ ፡ ማዕበል ፡ ተወርውሬ ፡ በከተማዩቱ ፡ ላይ ፡ ወድቄ ፡ አሸነፍኋት ። ፮፻ ፡ የሚሆኑትን ፡ ተዋጊዎቹዋን ፡ በሰይፍ ፡ አስገደልኋቸው ፤ ፫ሺ ፡ የሚሆኑትን ፡ ከእሳት ፡ ነበልባል ፡ ላይ ፡ አስጣልኋቸው ። ሁላይን ፡ ( አለቅዮውን ) ግን ፡





ፊቱ ፡ የሰው ፡ ክንፋማው ፡ ኮርማ ፡ አማሱ ። ከሳርጎን ፡ ዳግማዊ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ (ሉቭር ። )


እኔው ፡ ራሴ ፡ አስተኝቼ ፡ ከነሕይወቱ ፡ ቆዳውን ፡ በገዛ ፡ እጄ ፡ ገፍፌ ፡ እግንቡ ፡ ላይ ፡ ለጠፍሁት» ይላል፡፡ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ አልፎ ፡ ሱዝ ፡ ወደምትባለው ፡ የኤላም ፡ ከተማ ፡ ዘምቶ ፡ ከተማዪቱን ፡ ከቦ ፡ ካስጨነቀ ፡ በኋላ ፡ የኤላም ፡ ነገሥታት ፡ ሀብት ፡ ያለበትን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘርፎ ፡ ባገሪቱ ፡ ያደረገውን ፡ ግፍና ፡ ዕብሪት ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ በመፎከር ፡ ግፉን ፡ ይመካበታል ፡ « . . . የኤላም ፡ ነገሥታት ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ያከማቹትን ፡ የብር ፡ የወርቅ ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ ፡ የነገሥታት ፡ ጌጥና ፡ ልብስ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ መብሊያና ፡ መጠጫቸውን ፡ . . . ሁሉ ፡ ዘርፌ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ወሰድሁት ፡፡ ፴፪ ፡ የሚሆኑትን ፡ ከወርቅ ፡ ከብር ፡ ከመዳብ ፡ የተሠሩትን ፡ የንጉሡን ፡ ሐውልቶች ፡ ሌሎቹንም ፡ የወንድና፡ የሴት፡ አማልክት ፡ ሐውልት ፡ አፈራርሼ ፡ አመድ ፡ አድርጌ ፡ ለነፋስ ፡ ሰጠኋቸው ፡፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ከ፳፭ ቀን ፡ ጉዞ ፡ አገሪቱን ፡ በሙሉ ፡ በዝብዤ ፡ ጨውና ፡ እሾህ ፡ ነሰንስሁባት ፡፡ የነገሥታቱን ፡ ልጆችና ፡ እኅቶች ፡ መኳንንቱንና ፡ ሹማምንቱን ፡ ቀስተኛውንና ፡ ሠረገላ ፡ ነጅውን ፡ . . . ሴቱንም ፡ ወንዱንም ፡ ወጣቱንም ፡ ሽማግሌውንም ፡ ከነከብቱ ፡ እንዳንበጣ ፡ የበረከተውን ፡ ሕዝብ ፡ እያንጋጋሁ ፡ ማርኬ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ አመጣሁት ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ኤላምን ፡ ገዝቼ ፡ የደስታና ፡ የተድላ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማበት ፡ የነበረውን ፡ አገር ፡ የሜዳ ፡ አህያና ፡ የአውሬ ፡ መፈንጫ ፡ አደረግሁት ፡፡ »

የቡዳህ ፡ ምክር ፡ የክርስትና ፡ ትምህርት ፡ ያላለሰለሰው ፡ ርኅራኄን ፡ ደግነትን ፡ ከሥንፍና ፡ ውጊያን ፡ ደም ፡ ማፍሰስን ፡ ባላጋራ ፡ ማሠቃየትን ፡ ከጀግንነት ፡ የሚቈጥረው ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ የአሶር ፡ ሕዝብ ፡ በሜዳ ፡ ላይም ፡ በተራራም ፡ ለመዋጋት ፡ ደፋር ፡ የሆነውን ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ ከተማ ፡ ከቦ ፡ በማስጨነቅ ፡ የተከበበውን ፡ ከተማ ፡ ጥሶ ፡ በመግባት ፡ በውስጥ ፡ ያገኘውን ፡ ሕዝብ ፡ በማንጫጫት ፡ የታወቀው ፡ የአሶር ፡ ወታደር ፡ እነሆ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ አስጨንቆ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፡፡ የእስራኤልን ፡ መንግሥትና ፡ የሰማርያን ፡ ከተማ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደያዘውና ፡ ሕዝቡን ፡ ለምርኮ ፡ ወደነነዌ ፡ እንደወሰደው ፡ የእስ





የአሦር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ በሠረገላ ፡ ታጅቦ ፡ ሲሔድ ፡፡



የአሦሩ ፡ ንጉሥ ፡ አሱርባኒፓል ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ እያባረረ ፡ በቀስት
አውሬ ፡ ሲያድን ፡፡

ራኤል ፤ (ሰማርያ) ፡ ነገሥታት ፡ አነአክዓብ ፡ እነዮአስ ፡ እነአሕዝያ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደተዋጉ ፡ በመጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ይገኛል (፩) ።

መቼም ፡ ቆዳ ፡ መግፈፉ ፡ ይበዛል ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነገሥታት ፡ ከነወታደሮቻቸው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በየትም ፡ አገርና ፡ ሥፍራ ፡ ያሉት ፡ አረማውያኑም ፡ በኋላም ፡ የተነሡት ፡ ክርስቲያኖች ፡ በምርኮና ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ መሥራታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የምሥራቅ ፡ ንጉሥ ፡ ደግሞ ፡ ጠላቱን ፡ ሳይጨርስ ፡ ጠላቴን ፡ ጨረስሁት ፡ ማለት ፡ ልማዱ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ከክርስትና ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ቅርቡ ፡ እስከ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ካንድ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ያንድ ፡ ነገድ ፡ ሕዝብ ፡ አምፆባቸው ፡ ሲዋጉ ፡ ካሸነፉ ፡ በኋላ ፡ የዚህኑ ፡ ድል ፡ ለወዳጅ ፡ ዘመድ ፡ በቃልም ፡ በጽሑፍም ፡ ሲገልጹ ፡ ጠላቴን ፡ አንድ ፡ ሳላስቀር ፡ ፈጀሁት ፡ ማለትን ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። በርኅራኄና ፡ በአስተዳደር ፡ የሚመሰገኑት ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እንኳን ፡ በ፲፰፻፹፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከተደረገው ፡ ከዓድዋ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ የጦርነቱን ፡ የምሥራች ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለሚቀመጠው ፡ ለፈረንሳዊው ፡ ወዳጃቸው ፡ ለሙሴ ፡ ሞንዶን ፡ ቪዳዬ ፡ ሲጽፉለት ፡ ጣልያንን ፡ አንድም ፡ ሳላስተርፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ፈጀሁት ፤ ያሉት ፡ ትዝ ፡ ይለናል ። እንደእውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በዓድዋ ፡ ጦርነት ፡ የሞተው ፡ ሞቶ ፡ ከሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ በላይ ፡ ተማርኮ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ የሚሆነው ፡ ደግሞ ፡ ቆስሎም ፡ ሳይቆስልም ፡ እየሸሸ ፡ ወደ ፡ አሥመራ ፡ ገብቷል ። ነገር ፡ ግን ፡ ዘር ፡ ከገመድ ፡ ይስባል ፡ እንደሚባለው ፡ የአሶራውያን ፡ ዘር ፡ ሴማዊ ፡ ሲሆን ፡ ከነዚያ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መጥቶ ፡ ከዚያ ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ ወደ ፡ ዛሬይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብቶ ፡ የዛሬይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ መሪና ፡ አስተማሪ ፡ ሲሆን ፤ ክርስትና ፡ ያለሰለሰው ፡ ንጉሥ ፡ ያልጨረሰውን ፡ ጠላቱን ፡ አንድ ፡ ሳላስቀር ፡ ጨረስሁት ፡ ማለትን ፡ ካባቶቹ ፡ ከሴማውያን ፡ እንደ ፡ ወረሰ ፡ ይሰማናል ።

(፩) መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ፩ኛ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ በመጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ፪ኛ ፡ ም ፡ ፲፰ ።



ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ።

አሶራውያን ፡ እንደኢትዮጵያውያን ፡ ከጦርነትና ፡ ከዕረፍት ፡ የሚተርፈውን ፡ ጊዜያቸውን ፡ በአደን ፡ ያሳልፉ ፡ ነበር ። በአደኑት ፡ አውሬ ፡ በጣም ፡ መፎከርና ፡ መመካት ፡ ይወዱ ፡ እንደነበረ ፡ ያደኑትን ፡ አውሬና ፡ ያደኑን ፡ አኳኋን ፡ የሚያሳይ ፡ ሐውልት ፡ በዘመናቸው ፡ ያሠሩት ፡ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ ከሐውልት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ግብፅን ፡ ፈርዖን ፡ ሆኖ ፡ ከገዛው ፡ ከታኑታሙን ፡ ጋር ፡ ለጦርነት ፡ የተባለፈው ፡ ታላቂቱን ፡ የላዕላይ ፡ ግብፅን ፡ ከተማ ፡ ቴብን ፡ በዝብዞ ፡ ያፈራረሳት ፡ የአሳርሐዶን ፡ ልጅ ፡ አሱርባኒፓል ፡ ባንደኛው ፡ የአደን ፡ ሐውልቱ ፡ ሥር ፡ እኔ ፡ አሱርባኒፓል ፡ የሠራዊት ፡ ንጉሥ ፡ የአሦር ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ሁለት ፡ አንበሳ ፡ ገደልሁ ። የአስታርን ፡ የጦርነትን ፡ አምላክ ፡ ኃይለኛ ፡ ቀስት ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ደገንሁባቸው ፡ የመጠጥና ፡ የበለት ፡ መሥዋዕትም ፡ አቀረብሁባቸው ፡ ብሎ ፡ ያስቀረጸው ፡ በነነዌ ፡ ከተማ ፡ ይታያል ። ኤ ፡ ማሴና ፡ ገ ፡ ይበሐቅ ፡ የሚባሉት ፡ ሁለት ፡ ሊቃውንት ፡ ምሥራቅና ፡ ግሪክ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ለትምህርት ፡ ያዘጋጁትን ፡ መጽሐፍ ፡ ከገጽ ፡ ፶፰ ፡ እስከ ፡ ፷፩ ፡ ተመልከት ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

ሁለተኛው ፡ የባቢሎን ፡ መንግሥት ፡ እነሣሥና ፡ ሲአከባር ፡ የሜዶን ፡ ንጉሥ ፡ — የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርና ፡ የእስራኤል ፡ ምርኮ ።

የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ አሱርባኒፓል ፡ ከአባቶቹ ፡ ከነአሣርሐዶን ፡ ከነሰናክሬም ፡ የበለጠ ፡ የአሶርን ፡ መንግሥት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ነበር ፡ ጥንት ፡ የግብፅ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ እነቱትሞሲስ ፡ እነ ፡ ራምሴስ ፡ ወደኑብያም ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ ወደ ፡ መካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ወደነኬታ ፡ ወደነሂቲቲ ፡ ሶርያ ፡ ፓለስቲን ፡ እየዘመቱ ፡ ከየከተማው ፡ በዘረፉት ፡ ሀብት ፡ ከብረው ፡ እንደነበር ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በፋንታቸው ፡ አሶራውያን ፡ ግብፅን ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ የታወቁትን ፡ ከተማዎች ፡ እነቴብን ፡ ይዘው ፡ ባፈራረሷት ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡

ያለውን ፡ የፈርዖኖችን ፡ የአማልክቱን ፡ የካህናቱን ፡ የደለበ ፡ ሀብት ፡ ዘርፈው ፡ በመውሰድ ፡ በአጠገባቸው ፡ ካሉት ፡ ከተሞች ፡ ከባቢሎን ፡ ከሱር ፡ (ከአሶሮውያን) ፡ ከሱዝ ፡ (ኤላም) ፡ ከሜዶን ፡ ከልዳ ፡ የተገኘውን ፡ ሀብትና ፡ መግሪያ ፡ ሁሉ ፡ ግንድነት ፡ ወደነነዌ ፡ እያጋዙ ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸውን ፡ አከበሩት ፡ የነነዌን ፡ ከተማ ፡ ታላቅ ፡ እንድትሆን ፡ አደመቁት ።

አሁን ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ እየተቀጠቀጡ ፡ እየተበረሩ ፡ ሲገዙ ፡ የነበሩት ፡ የባቢሎን ፡ የግብፅ ፡ የኤላምና ፡ የሜዶን ፡ አገሮች ፡ ኃይለኛው ፡ አሱርባኒፓል ፡ ሲሞትላቸው ፡ የአሶርን ፡ የአገዛዝ ፡ ቀንበር ፡ ጥለው ፡ የራሳቸውን ፡ ነፃነት ፡ ለማቋቋም ፡ መንቀሳቀስ ፡ ዠመሩ ፡ ከሐሙራቢ ፡ ሞት ፡ ወዲህ ፡ ደክሞ ፡ ለአሶር ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አውራጃ ፡ ሆኖ ፡ የነበረው ፡ ባቢሎን ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የትንሣኤው ፡ ጊዜ ፡ ተቃረበ ። የመጀመሪያው ፡ ትንሣኤ ፡ በሐሙራቢና ፡ በአባቶቹ ፡ ጊዜ ፡ ስለተፈጸመ ፡ የባቢሎን ፡ የአሁኑ ፡ ትንሣኤ ፡ ዳግም ፡ ትንሣኤ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ለመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ከነዚህ ፡ የአሶር ፡ ተገዥ ፡ ከነበሩት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ለጊዜው ፡ የመንግሥት ፡ ዕድል ፡ ያጋጠመው ፡ የሜዶኑ ፡ ንጉሥ ፡ ፍራኦርቴስ ፡ ነው ። እርሱም ፡ በአገሩ ፡ ኃይል ፡ ቢሰማው ፡ የኃይለኛው ፡ የአሱርባኒፓል ፡ ልጅ ፡ ሳራኮስ ፡ ደካማ ፡ መሆኑን ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ አነሣበት ፡ ቢሆንም ፡ ሁለቱም ፡ ፈጽመው ፡ ሳይሸናነፉ ፡ ፍራኦርቴስ ፡ ሞተና ፡ በመንግሥቱ ፡ የተከተለው ፡ ልጁ ፡ ሲአክሳር ፡ ከአባቱ ፡ የበለጠ ፡ አይሎ ፡ ሳራኮስንና ፡ የአሶርን ፡ መንግሥት ፡ አስጨነቃቸው ።

የአሶሩ ፡ ንጉሥም ፡ ሲአክሳርን ፡ ለመመለስ ፡ አቅም ፡ ስላነሰው ፡ በሰሜን ፡ የሚኖሩትን ፡ ክፉ ፡ ሕዝቦች ፡ (መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጎግ ፡ ማጎግ ፡ የሚላቸውን ?) ለርዳታ ፡ ጠቀሰበት ። እነሱም ፡ በካውካዝ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ በመንገዳቸው ፡ ያገኙትን ፡ አገርና ፡ ሕዝብ ፡ እያጠፉ ፡ መጡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሲአክሳር ፡ የሜዶኑ ፡ ንጉሥ ፡ ጠላቶን ፡ ይዞ ፡ በድፍረት ፡ ወጊያ ፡ ገጠመና ፡ አሸንፎ ፡ አባረራቸው ። ከየአገሩ ፡ በዝርፊያ ፡ የሰበሰቡትንም ፡ ሀብትና ፡ መግሪያ ፡ ሁሉ ፡ ቀማቸው ። እነሱንም ፡ ካጠፋ ፡ በኋላ ፡ ፊቱን ፡ እነሱን ፡ ወደጠፋዊ



ቸው ፡ ወደአሶራውያን ፡ አዞረ ። በተራቸውም ፡ አሶራውያን ፡ ተሸንፈው ፡ ሲአክሳር ፡ ነነዌን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ያለቀውን ፡ ነቢዩ ፡ ናሆም ፡ አንቀፀው ፡ አሶራውያን ፡ ተደምጦ ፡ የአሞንን ፡ ከተማ ፡ ቴብስን ፡ እስከ ፡ መሠረቷ ፡ እሁን ፡ ደጋግሞ ፡ በጭካኔነት ፡ ከቴብ ፡ የማትበልጠው ፡ ነነዌ ፡ በተራዋ ፡ በሲአክሳር ፡ ጦር ፡ ተበዘበዘች ። ትንቢተ ፡ ናሆም ፡ ምዕራፍ ፡ ፫–፬ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባቢሎንን ፡ የሚገዛው ፡ የናቡከደነፆር ፡ አባት ፡ ናቦፖላሳር ፡ የሚባለው ፡ ነው ። ሲአክሳር ፡ የሜዶኑ ፡ ንጉሥና ፡ ናቦፖላሳር ፡ ኃበኞች ፡ ስለነበሩ ፡ በዘመናቸው ፡ በጣም ፡ ወዳጅና ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኞች ፡ ነበሩ ። ሲአክሳር ፡ በድል ፡ የአሶርን ፡ አገር ፡ ሲይዝ ፡ እንደአሶር ፡ ግዛት ፡ ይቆጠሩ ፡ የነበሩትን ፡ የፓለስቲናን ፡ የሦርያን ፡ የግብፅን ፡ ግዛት ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቦፖላሳር ፡ ሰጠው ። በዚህም ፡ ዘመን ፡ ኢዮአቄም ፡ በይሁዳ ፡ የፕሳሜቲክ ፡ ልጅ ፡ ኒካዎ ፡ በግብፅ ፡ ከአሜን ፡ አሥር ፡ በኋላ ፡ የነገሠው ፡ አስፕርታ ፡ የሚባለው ፡ በናፓታ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ የየግል ፡ መንግሥታቸውን ፡ ይዘው ፡ ይመሩ ፡ ነበር ።

የናፓታው ፡ መንግሥት ፡ ሩቅ ፡ በመሆኑ ፡ እነዚሁ ፡ ኃይለኞች ፡ አገሮች ፡ ዕጣ ፡ አልተጣጣሉበትም ፡ ግብፅና ፡ ይሁዳ ፡ ግን ፡ በመጀመሪያ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ግብፅ ፡ ልግዛ ፡ የኢዮስያስ ፡ ይሁዳ ፡ አልገዛም ፡ በማለት ፡ ሁለቱ ፡ ሲዋጉ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ኒካዎ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ማጊዶ ፡ (ከሊዶና ፡ ደቡብ) ፡ ላይ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ገድሎ ፡ በደስታ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ወደከተማው ፡ ወደ ፡ ሜምፊስ ፡ ተመልሶ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ ሥራውን ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ በሜዶኑ ፡ ንጉሥ ፡ በሲአክሳር ፡ ፈቃድ ፡ የግብፅ ፡ የይሁዳ ፡ ግዛት ፡ ወደባቢሎን ፡ መንግሥት ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰደ ። ስለሰነበረ ፡ ይሁዳን ፡ ከሰመነ ፡ በኋላ ፡ ግብፅን ፡ ደግሞ ፡ ለማስመን ፡ የባቢሎኑ ፡ ንጉሥ ፤ ናቦፖላሳር ፡ ልጁን ፡ ናቡከደነፆርን ፡ ጦር ፡ አስይዞ ፡ ላከው ፡

በበኩሉ ፡ የግብፁ ፡ ንጉሥ ፡ ኒካዎም ፡ ሁልጊዜም ፡ የፓለስቲናን ፡ የይሁዳን ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ግዛቴ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ናቡከደነፆርን ፡ ለመግጠም ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ፡ ካርኬሚሽ ፡ መጥቶ ፡ ጦርነት ፡

ተጋጠሙና ፡ ናቡከደነጸር ፡ ኒቃዎን ፡ አባረረው ። የራሱንም ፡ የግብፅን ፡ ግዛት ፡ ወደባቢሎን ፡ ለመደረብ ፡ ኒቃዎን ፡ ሲያባርር ፡ በመካከል ፡ በባቢሎን ፡ ከተማ ፡ አባቱ ፡ መሞቱን ፡ ሰማ ። ስለዚህ፡የራሱን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ለመፈጸም ፡ ናቡከደነጸር ፡ በቶሎ ፡ ወደባቢሎን ፡ ተመለሰ ። ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ ለግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ለኒቃዎ ፡ ትንሽ ፡ የተስፋ ፡ ጊዜ ፡ ሰጠው ። እንደገና ፡ ለማንሠራራትና ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ ለማግኘትም ፡ ከኢዮአስ ፡ ወዲህ፡በኢዮአቄም ፡ ጊዜ ፡ ከፋኛ ፡ በከለዳውያኑ ፡ ተመትቶ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ እየገበረ ፡ በሰላም ፡ የተቀመጠውን ፡ የይሁዳን ፡ መንግሥት ፡ አለሁልህ ፡ እያለ ፡ በባቢሎን፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲነሣ ፡ ይጐተጉተው ፡ ጀመር ።

በዚህም ዘመን ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ሰባቱ ፡ ሊቃውንት ፡ እነሶሎን ፡ ሌሎቹም ፡ እነፒታጎራ ፡ በቅርቡ ፡ ደግሞ ፡ በይሁዳ ፡ ስመ ፡ ጥሩዎቹ ፡ ነቢያት ፡ እነኤርምያስ ፡ እነዳንኤል ፡ የነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ነው ። ግሪኮቹ ፡ ፊንቂዎች ፡ ካርታጎች ፡ ሮማውያንም ፡ መንግሥታቸውን ፡ አቋቁመው ፡ የየግል ፡ አገራቸውን ፡ መምራት ፡ የጀመሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ናቡከደነጸር ፡ ከግብፅ ፡ ወደባቢሎን ፡ ተመልሶ ፡ ያባቱን ፡ ዙፋን፡ ከያዘ ፡ ወዲህ ፡ የይሁዳንና ፡ የሶርያን ፡ መሸፈት ፡ ሰማ ። የጦር ፡ ሠራዊቱንም ፡ ራሱ ፡ እየመራ ፡ መጥቶ፡ሁለቱንም ፡ አገሮች ፡ መታቸው። ከሁለቱም ፡ ይበልጥ ፡ በይሁዳና ፡ በከተማዋ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ብዙ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ፈጸመበት ። ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቦ ፡ አስጨንቆ ፡ ከያዛት፡ በኋላ ፡ የንጉሡን ፡ የሴዴቅያስን፡ዓይን፡በጉጠት ፡ አስወጣው ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹንና ፡ ልጆቹንም ፡ አስገደላቸው ። በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ አምሮ፡ የተሠራውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡አስፈርሶ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ በቤተ ፡ መቅደሱም ፡ የተገኘው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ መጣሪያውም ፡ ሁሉ ፡ ተዘረፈ ። እስራኤሎችም ፡ ከነሹማምንቶቻቸው ፡ ተይዘው ፡ በወታደር ፡ እየተነዱ ፡ እየተደበደቡ ፡ በምርኮ ፡ ወደባቢሎን ፡ ሄዱ ። እነዳንኤልም ፡ አብረው ፡ ምርኮኛ ፡ ሁነው ፡ ሲሄዱ ፡ ኤርምያስ ፡ ብቻ ፡ ወደግብፅ ፡ ሸሽቶ ፡ ስቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፡ የሚባለውን ፡ የኀዘን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው።ይህ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የፈረሰበትና ፡ እስራኤሎች ፡ የተማረኩበት ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭፻፹፯ ፡ ዓመት ፡ ነው ።



ስለኒቃዎና ፡ ስለኢዮስያስ ፡ ጦርነት ፡ ይልቁንም ፡ ስለናቡከደነጸር ፡ ጦርነት ፡ ስለእስራኤሎች ፡ ምርኮ ፡ በመጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፡ ከምዕራፍ ፡ ፳፫–፳፭ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ተመልከት ። ስትንቢተ ፡ ዳንኤልም ፡ በዜና ፡ መዋዕልም ፡ በየምዕራፉ ፡ በመጠኑ ፡ ይገኛል ።

እስራኤላውያን ፡ በባቢሎን ፡ ተማርከው ፡ በናቡከደነጸር ፡ በናቡኒክ ፡ በቤልሻጽር ፡ ( ቤልሻሩሱር ) ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱሳችን ፡ ብልጣሶር ፡ በሚለው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ግዞተኛ ፡ ሆነው ፡ እንዳንዶቹም ፡ ከመካከላቸው ፡ ባለሟልነት ፡ እየገጠማቸው ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደኖሩ ፡ ለነርሱ ፡ የሚራራ ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስነሣላቸው።ይኸውም ፡ ቂርስ ፡ የተባለው ፤ ንጉሥ ፡ ነው ። እሱም ፡ ባባቱ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ የካምቢዝ ፡ ፩ኛ ፡ ልጅ ፡ በናቱ ፡ የሜዶን ፡ ንጉሥ ፡ የሲአክሳር ፡ ልጅ ፡ የአስቲአግስ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ቂሮስ ፡ ከሁለት ፡ ነጋሢ ፡ ቤት ፡ ከፋርስና ፡ ከሜዶን፡ ተወልዶ ፡ በአስቲአግስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት፡አሥር ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ እየተማረ ፡ ከአደገ ፡ በኋላ ፡ ያባቱን፡ መንግሥት፡ ይዞ ፡ በባቢሎን ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ተነሣበት ። የናቡከደነጸር ፡ ልጅ ፡ ናቡናድርና ፡ ልጁ ፡ ቤልሻጽርም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተከላከሉት ። በመጨረሻ ፡ የኤፍራጥስን ፡ ወንዝ፡ዞግቶ ፡ አስጨንቆ ፡ ባቢሎንን ፡ በ፭፻፴፰ ፡ ዓመት ፡ ከክ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ያዛት ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለታሠሩት ፡ ለየአገሩ ነገሥታትና፡ መሳፍንት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ የአገራቸው ፡ እንዲገቡ ፡ ነፃነት ፡ ሲሰጥ ፡ የ፳ኤል ፡ ሹማምንት ፡ እነዘሩባቤል ፡ እነነህምያ ፡ እነዕዝራ ፡ ድል ፡ አድራጊው ፡ ፊት ፡ የምርኮኛነታቸውን፡ታሪክ ፡ ተረኩለት ። እሱም ፡ አዘነላቸው ፡ ሕዝባቸውንም ፡ የተዘረፈባቸውንም ፡ ዕቃ ፡ መጣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ይዘው ፡ ወደአገራቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ መልሰው ፡ እንዲሠሩ ፡ ፈቀደላቸው ። ስለዚህ ፡ እስራኤል ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ በምርኮ ፡ ከኖሩበት ፡ ከባቢሎን ፡ ተመልሰው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገቡ ። ለፋርስም ፡ መንግሥት ፡ እየገበሩ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ከተማና ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ መልሰው ፡ ሠሩ ። መጽሐፈ ፡ ዕዝራን ፡ በሙሉ ፡ ተመልከት ።

አሁን ፡ ግን ፡ የፋርስን ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ እስከምንቀጥል ፡ ድረስ ፡ የአሶርንና ፡ የባቢሎንን ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ እናገኛለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የአሶርና ፡ የባቢሎን ፡ የከለዳውያን ፡ ፊደልና ፡ ጽሑፍ ። አንዳንድ ፡ ልማድና ፡ ሃይማኖታቸው ።

ቀደም ፡ እንደተመለከትነው ፡ በመቅድሙ ፡ የአሶርና ፡ የባቢሎን ፡ ሕዝብ ፡ የሚጠቀምበት ፡ በውስጡ ፡ ሱመር ፡ አካድ ፡ አሶር ፡ ከለዳ ፡ ባቢሎን ፡ የሚባል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ልማድና ፡ ሃይማኖታቸው ፡ መሰያየቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሴማዊው ፡ ዘር ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየበረታ ፡ በመሔዱ ፡ በካም ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ እየተደባለቀ ፡ የምዕራብና ፡ የምሥራቅ ፡ ሴማዊ ፡ እየሆነ ፡ የምሥራቁ ፡ ሴማዊ ፡ አካድ ፡ የምዕራቡ ፡ የከነዓናውያን ፡ ወገን ፡ ራስ ፡ ሽምራ ፡ ዕብራውያን ፡ ፊንቄ ፡ ሲሆኑ ፡ ደግሞ ፡ አራማውያን ፡ የተባሉት ፡ ፍልስጤማውያን ፡ ፓልሚራውያን ፡ ናባጥያን ፡ ሲሪያን ፡ እየተባሉ ፡ የዘር ፡ ትውልዳቸው ፡ በበረከተ ፡ መጠን ፡ የልማዳቸው ፡ የሃይማኖታቸው ፡ የፊደላቸው ፡ የመንግሥታቸው ፡ ልዩነት ፡ በያለበት ፡ እየበረከተ ፡ ሔዷል ።

ከሱመርም ፡ ጋር ፡ ከወደ ፡ ምሥራቅና ፡ ከወደ ፡ ሰሜን ፡ የሚ ገኙ ፡ ሂንዱ ፡ አውሮፓ ፡ የተባለው ፡ ከሶርያ ፡ በኩል ፡ እስ ርኖቹ ፡ ወደ ፡ ... ፡ እስከ ፡ ግሪክ ፡ እየደረሱ ፡ የዘሩን ፡ ዘርም ፡ ልማድ ፡ አበዝቶት ፡ ሥልጣኔውንም ፡ አትረፈው ።

አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ትተን ፡ የተነሣንበትን ፡ የአሶርንና ፡ የባቢሎንን ፡ ስለሃይማኖታቸው ፡ ከመጻፋችን ፡ በፊት ፡ ስለፊደላ ቸው ፡ በጥቂቱ ፡ እንመልከት ።

እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ ከመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የሚሠሩ በት ፡ ፊደል ፡ ከግብፆች ፡ በአንዳንድ ፡ ሁኔታ ፡ የተለየ ፡ ነው ። ግብ ፆች ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ እንስሳንና ፡ የቤት ፡ ዕቃን ፡ የሰውን ትን ፡ አካል ፡ ሁሉ ፡ ለፊደልነት ፡ ሲጠቀሙበት ፡ እንደነበረ ፡ ከሱ መር ፡ በተቀበሉት ፡ መሠረት ፡ አሶራውያንም ፡ በመጀመሪያ ፡ ፊደል ፡ ማግኘት ፡ ስለአልቻሉ ፡ አሳባቸውን ፡ በንዳንድ ፡ የዕቃና ፡ የነገር ፡ ሥዕል ፡ ሲገልጹ ፡ ቆይተው ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ምስማር ፡ ያለው ፡ ጭንቅላቱ ፡ ፫ ፡ ማዕዘን ፡ ያለው ፡ ምልክት ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ እየተደባለቀ ፡ ራሱንም ፡ ችሎ ፡ ይሠራበት ፡ ጀመር ። ይህ ፡ ምል ክት ፡ ሥዕል ፡ እንደዚህ ፡ ፡ ነው ።

▷— ይህ ፡ ሥዕል ፡ በጐኑ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ሲጋ ደም ፡ ተዘቅዝቆ ፡ ወይም ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ሲሣል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፊደል ፡ ዓይነት ፡ እየወሰደ ፡ ይነበባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ብቻውን ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ፪ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ እየሆኑ ፡ አቀማመጣቸውን ፡ በስውጡ ፡ ቍጥር ፡ ስማቸው ፡ እየተለዋወጠ ፡ ወይም ፡ ከብዙዎቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ቆሞ ፡ ሌላው ፡ በጐኑ ፡ ሲጋደምበት ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ እየተሰጣ ቸው ፡ በፊደልነት ፡ ሲሠራባቸው ፡ ኖረ ።

የዚህን ፡ ፊደል ፡ ስም ፡ ላቲኖች ፡ «ኩኔይፎርም-ማዕዘንማ መልክ» ፡ ብለው ፡ ሰይመውታል ። በዚህ ፡ ፊደል ፡ የአሶርና ፡ የባ ቢሎን ፡ ነገሥታት ፡ ካህናትና ፡ ሊቃውንት ፡ ሲጠቀሙበት ፡ ኖረው ፡ በኋላ ፡ በግብፆቹ ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ የአራማይክና ፡ የሲሪ ያክ ፡ ደንበኛ ፡ ፊደል ፡ ለወጠው ። አራማይኩንና ፡ ሲሪያኩን ፡ ደግሞ ፡ ከከርበትና ፡ ወዲህ ፡ የግሪኮችና ፡ የሮማውያን ፡ ከዚያም ፡ የዓረብና ፡ የቱርክ ፡ ወረራ ፡ በየአገራቸው ፡ ሲፈራረቅ ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ከሲሪያክ ፡ ወደላቲን ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ዓረብኛ ፡ ፊደል ፡ መለወጥ ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ።

### ሃይማኖት ።

የአሶርና ፡ የባቢሎን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ግብፃውያን ፡ ሃይማኖት ፡ በብዙ ፡ በማይታዩ ፡ አማልክት ፡ እያመለኩ ፡ የማይታዩትን ፡ በሚ ታዩ ፡ በሰውና ፡ በእንስሳ ፡ በፍጥረት ፡ መልክ ፡ ይቀርጿቸውማል ፡ በግብፆች ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የፀሐይና ፡ የበሬ ፡ ኮርማ ፡ አምልኮ ፡ በነ ዚህም ፡ ዘንድ ፡ መልኩንና ፡ ስሙን ፡ ለውጦ ፡ ይመጣል ። ሌሎችም ፡

አማልክት ፡ እየተባዙ ፡ ይከታተላሉ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የዘራቸው ፡ ሐረግ ፡ መጥቶ ፡ ከተዋለዱ ፡ በኋላ ፡ የበረከቱት ፡ ከበረከቱ ፡ በኋላ ፡ የሚዋጉት ፡ የስማቸው ፡ ዝርዝር ፡ እንደዚሁ ፡ እያለ ፡ ይመጣል ።

፩ ፤ አፕሱ — የሚባል ፡ በወንድ ፡ የሚጠራ ፡ ድብልቅልቅ ፡ የሆነ ጣፋጭ ፡ ውሃ ፡ ያለበት ፡ ጥልቅ ፡ ቀላይ ።

፪ ቲአማት — በሴት ፡ የምትጠራ ፡ የባሕር ፡ ውሃ ።

፫ ሙሙ ፡ የአፕሱና ፡ የቲአማት ፡ ልጅ ፡ የማዕበል ፡ ወግ ።

ከአፕሱና ፡ ከቲአማት ፡ በአባብ ፡ መልክ ፡ ላከሀሙ ፡ (ወንድ) ላከሀሙ ፡ (ሴት ፡ ተወለዱ ፡ ከነዚህም ፡ ከሁለቱ ፡ ደግሞ ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ የተባለው ፡ አንሻርና ፡ የመሬት ፡ አምላክ ፡ የተባለችው ፡ ኪሻር ፡ ተወለዱ ። ከነዚህ ፡ ደግሞ ፡ አኑ ፡ (ሰማይ) ፡ ኤአ ፡ (ባሕር) ኢንሊል ፡ (መሬት) ፡ ተወልደው ፡ በአማልክትነት ፡ ሲሰገድላቸው ፡ ቆይቶ ፡ ከነዚህ ፡ ደግሞ ፡ በአሶራውያን ፡ ቤል ፡ በሴማውያን ፡ በዓል ፡ (ትርጓሜው ፡ ጌታ) ፡ የሚባለው ፡ ከማርዱክና ፡ ከአሡር ፡ ጋር ፡ ተወለዱና ፡ እነዚሁ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ በየከተሞቹ ፡ በነነዌ ፤ በባቢሎን ፤ በኡር ፡ አማልክትነታቸውን ፡ አጸደቁ ።

እስራኤሎች ፡ ከሁለት ፡ ተከፍለው ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አሥሩ ፡ ነገድ ፡ ሰብቻ ፡ የእስራኤል ፡ መንግሥት ፤ የደቡቦቹ ፡ የይሁዳን ፡ መንግሥት ፡ አቋቁመው ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በአሶራውያንና ፡ በባቢሎናውያን ፡ አማልክት ፡ በነበዓል ፡ (ብዔል) ማምለካቸውን ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየተቆጣ ፡ ለጠላቶቻቸው ፡ አሣልፎ ፡ እንደሰጣቸው ፡ በመጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ በዜና ፡ መዋዕል ፡ በየቦታው ፡ ይገኛል ።

አማልክቱ ፡ እንደዘሬ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ከተዋለዱ ፡ በኋላ ፡ እንደ አቤልና ፡ ቃኤል ፡ መጣላታቸው ፡ መዋጋታቸው ፡ ያሸነፉት ፡ በተሸነፉት ፡ ደምና ፡ ሥጋ ፡ ዓለምን ፡ እንደፈጠሩ ፡ በዘመናቸው ፡ ተጽፏል ።

ከአሱርባኒፓል ፡ አዳራሽ ፡ ከከርሰትና ፡ በፊት ፡ በ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ የአማልክት ፡ ታሪክና ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የተ



ጻፈበት ፡ ሰባት ፡ የድንጋይ ፡ ገበታ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ተገኝቶ ፡ በዚሁ ፡ ባንደኛው ፡ ገበታ ፡ ቲአማት ፡ የድብልትልቅ ፡ ቀላይ ፡ አምላክ ፡ የነበረችው ፡ የአጋንንት ፡ የመሳፍንት ፡ እመቤት ፡ ሆና ፡ ከደጉ ፡ አምላክ ፡ ከማርዱክ ፡ ጋር ፡ ያደረገችው ፡ ጦርነት ፡ ተጽፏል ።

ማርዱክ ፡ ከርሷው ፡ ዘር ፡ የመጣ ፡ ሆኖ ፡ አጠብ ፡ ያደረሳቸው ፤ በዓለም ፡ የመዠመሪያ ፡ አፈጣጠር ፡ ጊዜ ፡ አፕሱና ፡ ሙሙ ፡ ድብልቅልትና ፡ ማዕበላዊ ፡ ውሃ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ በኋላ ፡ የተወለዱት ፡ ለዓለምና ፡ ለፍጥረት ፡ ሥርዓትና ፡ መልክ ፡ እየሰጡ ፡ ማስተዳደር ፡ ስለዠመሩ ፡ የፊተኞቹ ፡ በኋለኞቹ ፡ ተቀይመው ፡ ሊያጠፏቸው ፡ አድማ ፡ ስለአደረጉ ፡ መሆኑ ፡ ተጽፏል ። የአድማውን ፡ ወሬ ፡ ኤአ ፡ ሰማችና ፡ እነዚህን ፡ የመዠመሪያ ፡ ፍጥረቶች ፡ ገደለቻቸው ። ቲአማት ፡ ቀድሞውንም ፡ ለፍጥረት ፡ ሥርዓትና ፡ መልክ ፡ እያሰፈልግም ፡ ያሉትን ፡ እንፍጃቸው ፡ ተብሎ ፡ ሲመከር ፡ አሳባቸውን ፡ አልተቀበለችም ፡ ነበር ። አሁንም ፡ የነርሱን ፡ መሞት ፡ ስትሰማ ፡ በጣም ፡ ተናደደች ። ከነኤአም ፡ ጋራ ፡ ለመዋጊያ ፡ የሚያስፈሩ ፡ ጥርሳቸው ፡ የሾለ ፡ የዘንዶና ፡ የአባብ ፡ ሠራዊት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወለደች ። ከነርሱም ፡ ጋር ፡ ከንፋማውና ፡ የሚያንጸባርቀውን ፡ ደራጎን ፤ ያበደ ፡ ውሻን ፤ እንደ ፡ ጊንጥ ፡ በጭራው ፡ የሚናደፈውን ፡ በግሩ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ የሚራገጠውን ፡ በእጁ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ በመርዝም ፡ ተበት ፡ እየነደፈ ፡ የሚገድለውን ፡ (ስበድዓት ?) ፡ ሁሉ ፡ ከወለደቻቸው ፡ የአባብና ፡ የዘንዶ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ለጦርነት ፡ አሰለፈቻቸው ። የነዚህን ፡ ሁሉ ፡ መሪነት ፡ የዕድልን ፡ ገበታ ፡ በልቡ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ ለኪንጉ ፡ ሰጠችው ።

የቲአማትን ፡ ጦር ፡ ድርጅት ፡ ኤአ ፡ (ባሕር) ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ለአባቷ ፡ ለአንሻር ፡ (ሰማይ) ፡ ነገረችው ። አንሻር ፡ (ወይም ፡ አንባር) ፡ ይኸን ፡ ሰምቶ ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ በንዴት ፡ እየተቃጠለ ፡ ጥርሱን ፡ ሲያፋጭ ፡ ጓደኞቹ ፡ አማልክት ፡ ተሰብስበው ፡ ቲአማትን ፡ ማን ፡ ነው ፡ ሔዶ ፡ የሚገጥም ? ማን ፡ ይሁን ? እያሉ ፡ ይመከሩ ፡ ዠመር ። ማርዱክ ፡ «የአማልክት ፡ ዋና ፡ መሪ ፡ ብላችሁ ፡ ከሾማችሁኝ ፡ እኔ ፡ ለመግጠም ፡ የተዘጋጀሁ ፡ ነኝ ፡ » ሲል ፡ አስታወቀ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አማልክቱ ፡ «አብሱኪና» ፡ በሚባለው ፡ ሠፈራቸው ፡

ሆነው ፡ ግብሩ ፡ ገብቶ ፡ እየተበላ ፡ እየተጠጣ ፡ ሲመከር ፡ «ማር ዱክ» ፡ ወደፊት ፡ ዓለምን ፡ ለመግዛት ፡ ዕድልና ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ አምላክ ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዱት ፡ አባቡን ፡ ተቀብለው ፡ ማንም ፡ ሊመልሰው ፡ የማይችለውን ፡ በጦር ፡ መሣሪያነቱ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለውን ፡ መብረቅን ፡ በጥተው ፡ ታላቅ ፡ በዓልና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አድርገው ፡ ከሾሙት ፡ በኋላ ፡ « ሒድና ፡ ቲአማትን ፡ ግደል ፤ ነፋሳ ትም ፡ ደሟን ፡ ወደሲኦል ፡ ያውርዱት » ፡ ብለው ፡ አዘዙት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማርዱክ ፡ ቀስቱንና ፡ ፍላጻውን ፡ ዱላውን ፡ እንደጨበጠ ፤ መብረቅ ፡ በደረቱ ፡ ላይ ፡ አሥሮ ፤ ቲአማትን ፡ የሚይዝበት ፡ ወጥመድ ፡ ይዞ ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ዓለም ፡ ያሉትን ፡ ነፋሳት ፡ አስከትሎ ፡ ሌሎችን ፡ ውሽንፍርንና ፡ አውሎ ፡ ነፋስን ፡ የሚቀሰቅሱትን ፡ ሰባት ፡ ነፋሳት ፡ በትሎ ፡ ፈጥሮ ፡ ወደ ፡ ቲአማት ፡ ለመሔድ ፡ ተነሣ ። አፈራራሹ ፡ ምሕረተ ፡ ቢሱ ፤ አደገኛው ፤ ፈጣኑ ፡ በሚባሉት ፡ መርዘኛ ፡ ጥርስ ፡ ባላቸው ፤ ሰውን ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ ረጋግጠው ፡ መግደልን ፡ በተማሩ ፡ በአራት ፡ ፈረሶች ፡ በሚሳበው ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ወጣ ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ በሩቅ ፡ እያብረቀረቀና ፡ እያስፈራራ ፡ ቲአማትና ፡ የጦር ፡ አሰቃዋ ፡ ኪንጉ ፡ ወደሚገኙበት ፡ ሥፍራ ፡ ደርሶ ፡ ቲአማትን ፡ «ነይ ፡ እንግዲህ፡ እንጋጠም» ፡ አላት ፡ እርሷም በድንጋጤ ፡ የጦርነት ፡ አማልክት ፡ እንዲረዷት፡ ጩኸቷንና ፡ አዝሚዋን ፡ ለቀቀችው» ፡ እያለ ፡ በአሱርባኒፓል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተገኘው ፡ የድንጊያ ፡ ጽሑፍ ፡ የአሶርና፡ የባቢሎንን፡ የአማልክት፡ ተረት ፡ ይተርክና ፡ ውጊያቸውን ፡ ደግሞ ፡ በግጥም ፡ መልክ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይቀጥላል ።

«ቲአማትና ፡ ማርዱክ ፡ ተያይዘው ፡ ተጨመዳድደው ፡ ይተናነቁ ፡ ዠመር ።

አምላኩ ፡ (ማርዱክ) ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወጥመዱን ፡ ወርውሮ ፡ ጠቀለለና ፡ ያዛት ። በፊቱዋም ፡ ላይ ፡ በኋላው ፡ የተከተለውን ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ ጣለባት ። ቲአማትም ፡ አፏን ፡ በርግዳ፡ ከፈተችው ።

ነፋሱም ፡ እየተዥጐደጐደ ፡ በአፏ ፡ ገብቶ ፡ ከንፈሯን ፡ እንዳትዘጋ ፡ ከለከላት ፤ ሆዷም ፡ ከፋኛ ፡ ተወጠረ ። ልቧም ፡ ተጨነቀ ፤ በአፏም ፡ መተንፈስ ፡ አልሆንላትም ።



በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ማርዱክ፡ ቀስቱን ፡ ገትሮ ፡ ወረወረና ፡ በፍላጻ ፡ ሆዷን ፡ በጠረቀው ። አንዠቷንም፡ በጣጥሶ ፡ ልቧን ፡ በነጠቀው ። የሞተውን ፡ ሰውነቷን ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ወርውሮ ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፡ ሔደበት ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ያዩት ፡ የርሷ ፡ ሠራዊት ፡ ከመሪያቸው ፡ ከኪንጉ ፡ ጋር ፡ ሲሸሹ ፡ ማርዱክ ፡ ሁሉንም ፡ እያባረረ ፡ በዚያው ፡ በወጥመዱ ፡ ይዞ ፡ በገሃነም ፡ የግዞት ፡ ሥፍራ፡ አስቀመጣቸው ። ከዚያ፡ ወደቲአማት ፡ ሬሳ ፡ ተመልሶ ፡ አካሏን ፡ ከነጭንቅላቷ ፡ ከሁለት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ ግማሹን ፡ አካሏን ፡ ወደላይ ፡ ግማሹን ፡ ወደታች ፡ አድርጎ ፡ ለሰማይና ፡ ለምድር ፡ ዋልታና ፡ ወጋግራ ፡ አድርጎ ፡ ሠራበት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማርዱክ ፡ በሰማይ ፡ ለሮቱ ፡ ታላላቅ፡ አማልክት፡ ለአኑ ፤ ለቤል ፡ (ብኢል) ፤ ለኤአ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ሠራላቸው ። በዚያም ፡ ሳሉ ፡ የሚሰግድላቸው ፡ ሰው ፡ ስለጠፋ ፡ ማዘናቸውን ፡ ገለጡለት ። ስለዚህ ፡ አፈርን ፡ በኪንጉ ፡ (የቲአማት ፡ የጦር ፡ አስቃ ፡ የነበረው ፡ ) ደም ፡ አቡክቶ ፡ በኤአ ፡ (ባሕር) ፡ እየተረዳ ፡ የመዠመሪያውን ፡ ሰው ፡ ሠራላቸው ። አማልክቱም፡ ለዚህ፡ ውለታ ፡ እርሱ ፡ በመረጠው ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሠሩለት ። የቤተ ፡ መቅደሱንም ፡ ሥራ ፡ ድንጋዩን ፡ እየጠረቡ ፡ ጡቡን ፡ አቡክተው ፡ ጠፍጥፈውና ፡ አድርቀው ፡ የሠሩት ፡ አኑናኪ ፡ የሚባሉ ፡ ታናናሽ ፡ አማልክት ፡ ናቸው ። ሠርተው ፡ ሲጨርሱ ፡ አማልክት ፡ በሙሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ለማርዱክ ፡ ዝማሬ ፡ እየዘመሩ ፡ በዓሉን ፡ አከበሩ ።

ለዚሁ ፡ ለማርዱክ ፡ (ሜሮዳክን) ፡ በየጊዜው ፡ የተደረገለት ፡ መዝሙርና ፡ ጸሎት ፡ ብዙ ፡ ነው ። በንዳንድ ፡ ሥፍራም፡ ነገሥታቱ፡ የጸለዩት ፡ በየድንጋዩ ፡ ቅርጽ ፡ ላይ ፡ የተገኘውን ፡ የዛሬ ፡ ሊቃውንት ፡ ወደየቋንቋቸው ፡ ተርጉመውታል ። ከዚሁ ፡ አሱርባኒፓል ፡ የሚባለው ፡ ታሪኩን ፡ ባለፈው ፡ እንዳነበብነው፡ ከኢትዮጵያዊው፡ ንጉሥ ፡ ከታኑታሙን ፡ ጋር፡ ለውጊያ ፡ የተሰለፈው ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ጸሎቱን ፡ ለማርዱክ ፡ አቅርቧል ። «በማክበር ፡ ስምህን ፡ አመሰግናለሁ ። ማርዱክ ፡ ሆይ ፡ ከአማልክት ፡ ይበልጥ፡ ኃያል ፡ የሆንኸው፡ በሰማይንና፡ ምድርን ፡ የምትመራው፡ . . . የአኑ፡ የኤንሊል ፤ የኤአ ፡ ክብር ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነው ። ግዛትና ፡ ጌትነት ፡

ዕውቀት ፣ የኃይል ፣ ፍጹምነት ፣ ያንተ ፣ ነው ። በሰማይ ፣ ከፍ ፣ ያል ኸው ፣ በምድር ፣ የነገሥኸው ፣ ከአማልክት ፣ ሁሉ ፣ ይበልጥ ፣ አዋቂው ፣ ሆይ ፣ አገርን ፣ መኖሪያን ፣ መሥርት ፣ ወሰንን ፣ ጠፈርን ፣ ያዝ . . . » እንደዚሁም ፣ ለብዔል ፣ (ጌታው) ፤ ለአስታርት ፣ የደረሰው ፣ መዝሙር ፣ በሌላ ፣ ቦታ ፣ ይገኛል (፩) ።

እነሆ ፣ ታሪካቸው ፣ በብሉይ ፣ ኪዳን ፣ በመጽሐፈ ፣ ነገሥትና፣ በዜና ፣ መዋዕል ፣ በትንቢተ ፣ ዳንኤልና ፣ በመጽሐፈ ፣ አስቴር ፤ ከነ ስማቸው ፣ የምናገኘው ፣ የአሶርና ፣ የባቢሎን ፣ ነገሥታት ፣ እነናቡ ከደነጾር ፣ በማርዱክና ፣ በሌሎችም ፣ በብዔል ፤ በአስታር ፤ በናናር ፣ በሲን ፤ በሌሎችም ፣ በዚሁ ፣ ላይ ፣ ዘርዝረን ፣ በማንጨርባቸው ፣ በሺ ፣ በሚቆጠሩ ፣ ታላላቅና ፣ ታናናሽ ፣ አማልክት ፣ ለየአንዳንዱ ፣ እንደማብያችኛ ፣ እንደማሪኮች ፣ የግል ፣ ተግባር ፣ እየሰጡ ፣ ያመልኩ፣ ነበር ።

የእስራኤል ፣ ነገሥታትና ፣ ሕዝብ ፣ በጉርብትና ፣ በመገዛት ፣ የአሶራውያንና ፣ የባቢሎናውያን ፣ የነርሱ ፣ ዘርፍና ፣ ቅርንጫፍ ፣ የሆኑት ፣ የጢሮስና ፣ የሲዶና ፣ አምልኮ ፣ እያሸነፋቸው ፣ የአባቶቻቸውን ፣ የአብርሃምን ፣ የይስሐቅንና ፣ የያዕቆብን ፣ አምላክ ፣ እየተዉ ፣ የነዚህን ፣ አገሮች ፣ አማልክት ፣ እነብኤልን ፤ እነአስታርን ፣ በማምለክ ፣ ከነቢያቱ ፣ ከነኤልያስ ፣ ከነኤርምያስ ፣ ጋር ፣ ያደረጉትን ፣ ጠብ ፣ በመጽሐፈ ፣ ነገሥት ፣ ቀዳማዊና ፣ ካልዕ ፣ በሌላውም ፣ ሥፍራ ፣ እናገኛለን ። ለምሳሌ ፣ ያህል ፣ በመጽሐፈ ፣ ነገሥት ፣ አክአብ ፣ የእስራኤል ፣ ንጉሥና ፣ ሚስቱ ፣ ኤልዛቤል ፣ ባመለኩት ፣ በብዔል ፣ ምክንያት ፣ በኤልያስና ፣ በብኤል ፣ ነቢያት ፣ መካከል፣ የተደረገውን፣ ጠብና ፣ ፉክክር ፣ ከፉክክሩም ፣ በኋላ ፣ አራት ፣ መቶ ፣ የሚሆኑትን ፣ የብዔልን ፣ ነቢያት ፣ ኤልያስ ፣ እንደ ፣ አሰፈጀ ፣ እንመለከት (፪) ።

የአሶራውያንና ፣ የባቢሎናውያን ፣ የከለዳውያን ፣ አማልክት ፣ በዙሪያቸው ፣ ወይም ፣ በበታቾቻቸው ፣ እኛ ፣ ዛሬ ፣ ባገራችን ፣ እሉ፣ እንደምንለው ፣ ግማሾቹ ፣ ሰውን ፣ የሚቃወሙ ፣ መጥፎዎች ፣ መና

---

(፩) MYTHOLOGIA... PRAMPOLINI ገጽ ፣ ፻፶፩ ፣— ፻፶፪ ፣

(፪) መጽሐፈ ፣ ነገሥት ፣ ፩ኛ ፣ ም ፣ ፲፰ ።



ፍስት ፣ ወይም ፣ ሰጋንንት ፣ እነቱኩ ፣ እሉ ፣ – ኢኪሙ – ራቢሱ – ጋሉ–» የሚባሉ ፣ ለሰው ፣ ልጅ ፣ የበሽታን ፣ ነፋስ ፣ ከደሱብ ፣ የሚልኩ ፤ ቅዝትን ፤ ፅብደትን ፤ ከፋትን ፤ ጦርነትን ፣ የሚፈጥሩ ፣ ሌሎች ፣ ደግሞ ፣ በነዚሁ ፣ ጐን ፣ ጽዱ ፣ ወይም ፣ ሲዲ ፤ ላማሱ ፣ የሚባሉ ፣ ከነዚያ ፣ እየተከላከሉ ፣ የሰውን ፣ ልጅ ፣ ከክፉ ፣ ነገር ፣ የሚጠብቁ ፣ ደጋግ ፣ መናፍስት ፣ መኖራቸውን ፣ ያምናሉ ። እነዚህንም ፣ ደጋግ ፣ መናፍስት ፣ ምስላቸውን ፣ ሲሠሩ ፣ አካላቸውን ፣ በበሬ ፣ ኮርማ ፣ ወይም ፣ በአንበሳ ፣ አድርገው ፣ ሁለት ፣ ክንፍ ፣ ግራና ፣ ቀኝ፤ ከፊታቸው ፣ የሰውነት ፣ መልክ ፣ ያላቸው ፣ እያስመሰሉ ፣ እየሳሉ ፣ በቤተ ፣ መንግሥትና ፣ በቤተ ፣ መቅደስ ፣ ደጃፍ ፣ እያስቀመጡ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ መዝጊያቸውን ፣ ራሱን ፣ በዚሁ ፣ ምስል ፣ ይሠሩታል ። በጦርነትና ፣ በጉዞ ፣ ጊዜ ፣ ይኸው ፣ ምስል ፣ አይለይም ። በሥዕሉ ፣ ላይ ፣ የሰውነቱ ፣ መልክ ፣ አዋቂነቱን ፣ አንበሳው ፣ ወይም ፣ ኮርማው ፣ ጠንካራነቱን ፤ ክንፉ ፣ ፈጥኖ ፣ ደራሽነቱን ፣ ያሳያል ። ከሳርጎን ፣ ፪ኛ ፣ ቤተ ፣ መንግሥት ፣ በራፍ ፣ ላይ ፣ ከነበረው ፣ ፈረንሳዮች ፣ አግኝተው ፣ ወደፓሪስ ፣ ወስደው ፣ በሉቭር ፣ ያስቀመጡት ፣ የዚሁ ፣ የአማሱ ፣ (ጠባቂው ፣ መንፈስ) ፣ የክንፉማው ፣ ኮርማ ፣ ሐውልት ፣ ተመልካችን ፣ እንዳስደነቀ ፣ ነው ።

እንደዚሁም ፣ ክፉዎቹ ፣ መናፍስት ፣ እንዳይቀርቡ ፣ ናሙ ፣ (የተቀደሰችው ፣ ውሃ ፣ እመቤት) ፤ ኒናክ ፣ ሃኩዱ ፣ (የንጽሕና ፣ እመቤት) ፣ በድግምት ፣ እየተለመኑ ፣ ውሃው፣ በካህን ፣ ይረጫል ። ብዙ፣ ጊዜ ፣ ካህናቱ ፣ ወይም ፣ አማልክቱ ፣ በግራ ፣ እጃቸው ፣ ውሃ ፣ በማሠሮ ፣ በቀኝ ፣ እጃቸው ፣ የሚረጩበትን ፣ መሣሪያ ፣ እንደያዙ ፣ ሐውልታቸው ፣ ተሠርቶ ፣ ይታያል ። ይኸውም ፣ ካህናት ፣ በአማልክት ፣ ተመስለው ፣ ወይም ፣ ተወክለው ፣ ቅዱሱን ፣ ውሃ ፣ እየረጩ ፣ መናፍስት ፣ ርኩሳንን ፣ ለማራቅ ፣ እነሱም ፣ ሲርቁ ፣ መናፍስት ፣ ቅዱሳን ፣ በቤተ ፣ መቅደስና ፣ በቤተ ፣ መንግሥት ፣ በየሰዉ ፣ ቤት፣ ሁሉ፣ አድረው ፣ መልካም ፣ የሆነውን ፣ ተግባር ፣ ሁሉ ፣ እንዲፈጽሙ ፣ በመመኘት ፣ ነው ። በዚህም ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የአማልክት ፣ ስምና ፣ ድግምት ፣ ያለበት ፣ ክታብ ፣ ወይም ፣ ጠልሰም ፣ ባንገት ፣ ማሠር ፣ በነርሱ ፣ ዘንድ ፣ የተለመደ ፣ ነው ።

እስራውያን ፡ የሞተውን ፡ ሁሉ ፡ መቅበር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ግብፃውያን ፡ የብረትና ፡ የእንጨት ፡ ሳጥን ፡ እያበጁ ፡ በየቤቱ ፡ መቅደሱ ፡ ማስቀመጥን ፡ አይወዱም ። ሳይቀበር ፡ የሚቀረው ፡ ሰው ፡ እመፀኛና ፡ ጠላት ፡ ነው ። እንዱን ፡ መዋቲ ፡ ሰው ፡ ሳይቀብሩ ፡ መተው ፡ ለአውሬና ፡ ለአሞራ ፡ ማስበላት ፡ መዋቲውንና ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ለማዋረድ ፡ ሲፈለግ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸንና ፡ ሌላውን ፡ እላይ ፡ ያመለከትነውን ፡ ልማድ ፡ ሁሉ ፡ ሴማዊ ፡ ዘራችን ፡ ከመነጨበት ፡ ከነርሱ ፡ እንደወረስን ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንደዚሁ ፡ ሰው ፡ ሞቶ ፡ አይቀርም ፡ የሚሉ ፡ እምነት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ስለአደረባቸው ፡ ሰምውታን ፡ ምግብ ፡ እያሉ ፡ ወደየመቃብር ፡ ቤታቸው ፡ ያግዙላቸው ፡ ነበር ። ይኸንንና ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ተግባር ፡ ባንፈጽምላቸው ፡ ምውታኑ ፡ በምትሐት ፡ መልክ ፡ በሕልም ፡ እየመጡ ፡ ሕያዋንን ፡ (ቤተ ፡ ሰባቸውን) ፡ ያሠቃያሉ ፡ (ያቃዣሉ) ፡ እያሉ ፡ ይፈሩት ፡ የነበረው ፡ ልማዳቸው ፡ ለኛም ፡ የማቲሪዬል ፡ ዕውቀትና ፡ የሲግሞንድ ፡ ፍረድን ፡ ምርመራ ፡ ላልተማርነው ፡ ደርሶናል ።

እስራውያን ፡ ከሃይማኖትና ፡ ከጦርነት ፡ ሥራቸው ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ግብፃውያን ፡ ድንጊያ ፡ እየጠረቡ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሕንፃ ፡ የሰውና ፡ የአማልክት ፡ የነገሥታት ፡ ሐውልት ፡ እያሳመሩ ፡ በመሥራት ፡ በከዋክብት ፡ ቈጠራ ፡ በሂሣብ ፡ በጥንቆላ ፡ ይኸን ፡ በመሰለው ፡ ዕውቀት ፡ የሠለጠኑ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

### በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሁናቴ ፡ ካምቤዝ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥና ፡ ናቡቶሴኔን ፡ የኢትዮጵያ ፡ (ናፓታ ፡ ) ንጉሥ— ፡ እርአን ዲዝና ፡ ሔዳስፕ ፡ (ሐድ-እስ—ኤው) ።

ቂሮስ ፡ የባቢሎንን ፡ መንግሥት ፡ ትቶ ፡ የፋርስን ፡ መንግሥት ፡ ኃይልና ፡ ገናናነት ፡ መሥርቶ ፡ ፴፩ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደ ገዛ ፡ ሞተ ፡ በመንግሥቱም ፡ ልጁ ፡ ካምቢዝ ፡ ፪ኛው ፡ ነገሠ ። ይኸም ፡ ከአባቱ ፡ ከቂሮስ ፡ ይበልጥ ፡ የፋርስን ፡ መንግሥት ፡ አስፋ ። ካምቢዝ ፡ ፰ ፡ ዓመት ፡ የራሱን ፡ የፋርስን ፡ የባቢሎንና ፡ የሶርያን ፡ የፓለስ



ቲን ፡ ግዛቱን ፡ እያደላደለ ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፡ በ፭ኛው ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ግብፅን ፡ ለማስገበር ፡ መጣ ። የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ አማሲስ ፡ ከመጋጠሙ ፡ በፊት ፡ ሞተ ፡ በመንግሥቱ ፡ የተከተለውም ፡ ልጁ ፡ ፕሳሜቲክ ፡ ፫ኛ ፡ በፔሉዝ ፡ ቲንሽ ፡ ተዋግቶ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ወደ ፡ መምፌስ ፡ ሸሸ ። ካምቢዝም ፡ እግር ፡ በእግር ፡ እየተከታተለ ፡ ደረሰበት ፤ መምፌስንም ፡ ያዛት ። ንጉሡም ፡ ተማርኮ ፡ ቲንሽ ፡ ዘመን ፡ እንደቆየ ፡ ሞተ ። የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ እስራውያን ፡ እንደ ፡ አደረጉት ፡ ደርሶ ፡ መመለስ ፡ ሳይሆን ፡ ተደላድሎ ፡ በሙሉ ፡ በግብፅ ፡ ግዛት ፡ ገባና ፡ ፳፯ኛውን ፡ የራሱን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ ፡) መሠረተ ፡ ከካምቢዝ ፡ ቀጥለው ፡ የነገሡት ፡ የፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ዳርዮስ ፡ ፩ኛ ፤ አርታሪክሴክስ ፡ ፩ኛ ፤ ዳርዮስ ፡ ፪ኛ ፤ ግብፅን ፡ ገዙ ። በዳርዮስ ፡ ፪ኛ ፡ ዘመን ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ሌሎችን ፡ አገሮች ፡ እንደያዘ ፡ ግሪክንም ፡ ለማስገበር ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሞከረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ግሪኮቹ ፡ በስመ ፡ ጥሩዎቹ ፡ የጦር ፡ አለቆቻቸው ፡ በነሚትርያድ ፡ በነቴሚስቶክል ፡ በነፔሪክል ፡ በነሌዎኒዳ ፡ እየተመሩ ፡ በማራቶን ፤ በሳላሚስ ፡ በፕላቴዎስ ፡ ላይ ፡ ከ፬፻፺ ፡ እስከ ፡ ፬፻፸፱ ፡ ዓመት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እየተዋጉ ፡ ፋርሶችን ፡ መለሷቸው ።

በስዚህ ፡ ፋርሶቹ ፡ በዚህ ፡ ግንባር ፡ ግሪኮቹን ፡ ለማስገበር ፡ በሚጣጣሩበት ፡ ጊዜ ፡ በግብፅ ፡ ግዛታቸው ፡ ላይ ፡ ግዛታቸውንና ፡ ተቈጣጣሪነታቸውን ፡ በላላሉ ፡ ግብፆቹ ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ አጋጠማቸው ፡ ከመካከላቸው ፡ ኢናሮስ ፡ የሚባለውን ፡ የፕሳሜቲክን ፡ ልጅ ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ ፪ኛ ፡ በፋርሱ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ላይ ፡ ተነሡ ። በግብፅ ፡ የሚገኙ ፡ ግሪኮችም ፡ ፋርስ ፡ የአገራቸው ፡ ባላጋራ ፡ ስለሆነ ፡ በግብፃዊው ፡ መሪ ፡ ውስጥ ፡ አብረው ፡ ፋርሶቹን ፡ ለመውጋት ፡ ተዘጋጁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግብፆቹና ፡ ግሪኮቹ ፡ ፋርሶቹን ፡ ወግተው ፡ አሸንፋና ፡ ዋናውን ፡ ከተማ ፡ መምፌስን ፡ ያዙ ። በዚያም ፡ ነፃነታችንን ፡ አቋቁመናል ፤ ብለው ፡ አውጀው ፡ በራሳቸው ፡ ንጉሥ ፡ መተዳደር ፡ ጀመሩ ። አርታክሲስ ፡ የፋርስ ፡ ትልቁ ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ ወታደር ፡ ላከ ። ይኸንንም ፡ ደግሞ ፡ የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ሲሰማ ፡ ለግብፆቹ ፡ ርዳታ ፡ በመርከብ ፡ ወታደር ፡ ላከ ። እነዚህም ፡ ከግብፃውያኑ ፡ ተደባልቀው ፡ በፋርሶቹ ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ውጊያ ፡



ከዚህ ፡ በላይ ፡ የሚታየው ፡ የግብፆችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ጽሑፍና ፡ ፊደል ፡ ተቀብ ለው ፡ ከሚሠሩበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ( ኑብያ ) ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ አስፑርታ ፡ ( የኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ዘዋሬ ፡ ንብረት ፡ አስፑርታ ) የሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ ለአምላኩ ፡ ለአሞን-ራ ( ፀሐዩ ፡ አሞን ) ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ስለት ፡ ሲሰጥ ፡ የተጻፈበት ። በጽሑፉ ፡ አናት ፡ ያሉት ፡ የአምላኩ ፡ የአሞን ፡ የንጉሡ ፡ የአስፑርታ ፡ እንደዚሁም ፡ የሴት ፡ አማልክ ትና ፡ የንጉሡ ፡ ሚስቶች ፡ ምስል ፡ ነው ፡ ( ዋላስ ፡ ባጅ ፡ ፩ኛ ፡ ቮሊም ፡ ገጽ ፡ ፺፪)




ፋርሶቹን ፡ አሸነፉ ። ከውጊያውም ፡ በኋላ ፡ የግሪኮቹ ፡ መሪ ፡ ሻርቴ መድና ፡ የፋርሱ ፡ መሪ ፡ አሾሜንስ ፡ ሬሳቸው ፡ በአንድነት ፡ ተገኘ ። እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ ግብፆቹ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ሆነው ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ድረስ ፡ ነፃነታቸውን ፡ አግኝተው ፡ ዲና ስቲና ፡ ንጉሥ ፡ ከራሳቸው ፡ እየለዋወጡ ፡ ፫፻፵ኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ እንደደረሱ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ፋርሶች ፡ መልሰው ፡ ያዙዋቸውና ፡ በአርጣክሲስ ፡ ፫ኛ ፡ በአርክሴስ ፡ በዳርዮስ ፡ ፫ኛ ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ። ከዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዠምረው ፡ ወደፊት ፡ ግብፆቹ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ዕድል ፡ ሳያገኙ ፡ ኃይል ፡ አግኝቶ ፡ የተነሣው ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ይፈራረቅባቸው ፡ ዠመር ።


ፋርሶቹን ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ሲጥላቸው ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ በግ ሪኮች ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በሮማውያን፡ ፬፻፳፩ ፡ ዓመት ፤ በቍስጥንጥ ንያ ፡ ፪፻፵፩ ፤ በዓረብ ፡ ፰፻፸፯ ፤ በቱርኮች ፡ ፭፻፲፯ ፡ ዓመት ፡ እየተ ገዙ ፡ ነፃነታቸውን ፡ አጥተው ፡ ኖሩ ። የታናሽ ፡ እስያ ፡ አገሮችና ፡ እስራኤሎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ባሸናፊ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳልፉ ፡ ዠመር ። ይኸንንም ፡ ወደፊት ፡ በዚሁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እየተያያዘ ፡ ተጽፎ ፡ እናገኛለን ።

እስከዚያ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሁኔታ ፡ ነገሥታቱ ፡ እነናስቶሴኔን ፡ የፋርሱን ፡ ነገሥታት ፡ እነካም ቤዝን ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ተዋግተው ፡ እንደመለሱ ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመልከት ።

ፋርሶች ፡ በካምቢዝ ፡ እየተመሩ ፡ ግብፅን ፡ ከመውረራቸው ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ የግብፅ ፡ ገዥነ ታቸውን ፡ ትተው ፡ በናፓታ ፡ ከተቀመጡ ፡ ወዲህ ፡ ግብፆቹና ፡ ኢት ዮጵያውያን ፡ በፊት ፡ የአሶርና ፡ የባቢሎን ፡ የፋርስ ፡ ኃይል ፡ ደግሞ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ስለአሰጋቸው ፡ በመካከላቸው ፡ ያንድነት ፡ ዝም ድና ፡ ለማድረግ ፡ የሞከሩ ፡ ይመስላል ። ደግሞ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኢት ዮጵያውያኑ ፡ ግብፅ ፡ ጥንት ፡ ያባቶቻችን ፡ የነፒያንኪ ፡ የነሻባቃ ፡ የነበረው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በአሜን ፡ አሥሮ ፡ ጊዜ ፡ ግብፅን ፡ ለመውረር ፡ ግብፆችም ፡ በበኩላቸው ፡ የደቡብ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ጥንት ፡ ያባቶቻችን ፡ የፈርዖኖቹ ፡ የነቱትሞሲስ ፡ የነራምሴስ ፡



አማኒ ፡ ሻኽቴ ፡ የምትባል ፡ የመሮዌ ፡ ንግሥት ፡ የታሠ ሩትን ፡ ምርኮኞች ፡ እንደያዘች ፡ (ከለፕሲዩስ ፡ መጽሐፍ ፡)



አሚንሁተብ ፡ (ኔብ ፡ ማኣት ፡ ራ) ፡ የሚባል ፡ የመ ርዌ ፡ ንጉሥ ፡ (ከለፕሲዩስ ፡ መጽሐፍ ፡)



ግዛት ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ በፕሳሜቲክ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ ሞክረዋል ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በግብፅ ፡ ያለው ፡ ፈርዖን ፡ ከናፓታው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጋብቻ ፡ ውስጥ ፡ የመጣሁ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ የኢትዮጵያዊው ፡ ንጉሥም ፡ ይኸንኑ ፡ ጭምር ፡ እያመካኘ ፡ የወሰን ፡ ግጭት ፡ እያደረጉ ፡ ወደየሥፍራቸው ፡ ከመመለስ ፡ በቀር ፡ አንደኛው ፡ ሌላውን ፡ ሊወረው ፡ አልቻለም ። እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ ሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ዝምድናን ፡ ጠብን ፡ እያፈራረቁ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንደቆዩ ፡ ባለፈው፡ ምዕራፍ ፡ ስማቸውን ፡ ባነሳነው ፡ በካምቢዝ ፡ ፩ኛ ፡ የተመሠረተው ፡ በስመ ፡ ጥሩው ፡ ንጉሥ ፡ በቂሮስ ፡ የገነነው ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ ኃይሉን ፡ እያበዛ ፡ ግዛቱን ፡ እያሰፋ ፡ መጥቶ ፡ በቂሮስ ፡ ልጅ ፡ በካምቢዝ ፡ ሁለተኛ ፡ ዘመን ፡ ይኸው ፡ ካምቢዝ ፡ ራሱ ፡ ጦሩን ፡ እየመራ ፡ መጥቶ ፡ የግብፅን ፡ መንግሥት ፡ በ፭፻፳፭ ፡ ዓመት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ወረረ ። ግብፅንም ፡ ከወረረ ፡ በኋላ ፡ ለካምቢዝ ፡ ሁለተኛ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ያስገበረው ፡ የባቢሎን ፡ የአሶር ፡ የይሁዳ ፡ የእሥራኤል ፡ የጢሮስ ፡ የሲዶና ፡ የግብፅ ፡ የሲና ፡ የዓረብ ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ አልበቃውም ።

ስለዚህ ፡ ግብፅን ፡ ወርሮ ፡ ከተደላደለበት ፡ በኋላ ፡ ከግብፅ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚገኘውን ፡ የኑብያን ፡ (የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ለመውረር ፡ አሰበ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከመውረሩ ፡ በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ኃይል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መሆኑን ፡ ለመገመት ፡ በስላይ ፡ በኩል ፡ ለመረዳት ፡ እንደሚገባ ፡ አመዛዘነ ። በኢትዮጵያም ፡ (በናፓታም) ፡ ከአሜን ፡ አሥሮ ፡ ቀጥሎ ፡ ፒያንኪ ፡ ፬ኛ ፡ ከፒያንኪም ፡ በኋላ ፡ አስፔርታ ፡ ከአስፔርታም ፡ ቀጥሎ ፡ ሆር—ሴአትው ፡ ፩ኛ ፡ ነግሠዋል ።

ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ አስፔርታ ፡ ለንጉሥነት ፡ አምላኩ ፡ አሞን ፡ በካህናቱ ፡ በኩል ፡ ማን ፡ ይግዛን ፡ በማለት ፡ ለተሰበሰበውና ፡ ለጠየቁት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ አስፔርታ ፡ ይግዛችሁ ፡ ብሎ ፡ እንደመረጠው ፡ የሚናገር ፡ ሐውልት ፡ በዚያው ፡ በናፓታ ፡ (በጀበል ፡ ባርካ ፡) እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለ ። ከአስፔርታ ፡ በኋላ ፡ የነገሠው ፡ ሐርሴአ

ቲፍ ፣ (ው) ፣ በምሥራቅ ፣ በኩል ፣ (ምናልባት ፣ በዛሬው ፣ በትግሬ ፣ በከረን ፣ በበጌምድር ) ፣ ያሉ ፣ ነጋዴዎች ፣ ሸፍተውበት ፣ እን ደምን ፣ ተዋግቶ ፣ ድል ፣ እንዳደረጋቸውና ፣ ለዚሁም ፣ ለአምላኩ ፣ ለአሞን ፣ ያቀረበውን ፣ መሥዋዕትና ፣ በለት፡ የሚዘረዝር፡ ሐውልት፣ በዚሁ ፣ በጀበል ፣ ባርካ ፣ አለው ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ሆርሴአተው ፣ በዘመኑ ፣ መንግሥቱ ፣ መጨረሻ ፣ ከመርዌ ፣ ውስጥ ፣ ናስቶሴኔን ፣ የሚባለው ፣ ተነሥቶበት ፣ መንግሥቱን ፣ ገልብጦ ፣ ወደመርዌ ፣ ወሰደው ። ከዚህም ፣ ጊዜ ፣ ዠምሮ ፣ የናፓታ ፣ ከተማ ፣ እየቀዘቀዘ ፣ የመርዌ ፣ ከተማ ፣ እየደመቀ ፣ ሔደ ።

ስለዚህ ፣ ናስቶሴኔን፣ በናፓታ ፣ ነጋሢዎች ፣ እግር ፣ ተተክቶ ፣ ከተማውን ፣ መርዌ ፣ አድርጎ ፣ የምሥራቁንና ፣ የምዕራቡን ፣ አገር ፣ ( ኢትዮጵያ) ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ነገድ ፣ የተከፈለውን ፣ ሕዝብ ፣ እየጨ መረ ፣ ይገዛ ፣ ዠመር ። ስለዚሁ ፣ የግሪኮችና ፣ የሮማውያኑ ፣ ጸሐፊ ዎች ፣ እነሔሊዎዶር ፣ የጻፉት ፣ እንደሚለው ፣ ካምቢዝ ፣ ግብፅን ፣ በወረረበት ፣ ናስቶሴኔን ፣ በመርዌ ፣ በነገሠበት ፣ ዘመን ፣ ካምቢዝ ፣ የፋርሱ ፣ ንጉሥ ፣ በወዳጅነት ፣ መታየ ፣ ይዘው ፣ ሔደው፣ የኢትዮጵ ያን ፣ ንጉሥ ፣ የናስቶሴኔን ፣ ኃይል ፣ መረምረው ፣ እንዲነግሩት ፣ ያገ ሩን ፣ የመርዌን ፣ ቋንቋ ፣ የሚያውቁትን ፣ በአምብል ፣ የሚኖሩ ፣ ኢክ ቲዎፋጅ ፣ የሚባሉትን ፣ ሰዎች ፣ መርጦ ፣ ከኤሌፋንቲን ከተማ ፤ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ንጉሥ ፣ ላካቸው ። እነሱም ፣ ከኤሌፋንቲን፣ ወደ፣ መርዌ ፣ መጥተው ፣ « እነሆ ፣ ወዳጅነትህን ፣ የሚፈልገው፣ የፋርሱ፣ ትልቁ ፣ ንጉሥ ፣ ካምቢዝ ፣ የላከልህ ፣ ገጸ ፣ በረከት » ፣ ብለው ፣ ልብስ ፣ የአንገትና ፣ የእጅ ፣ ጌጥ ፣ ሽቱና ፣ መጠጥ ፣ አቀረቡለት ። እሱም ፣ መታያውን ፣ በዝርዝር ፣ አይቶ ፣ ከተቀበለ ፣ በኋላ ፣ ለመልክ ተኞቹ ፣ እንደዚህ ፣ አላቸው ፣ የፋርስ ፣ ንጉሥ ፣ ይኸንን ፣ ገጸ ፣ በረ ከት ፣ እሲዞ ፣ የላካችሁ ፣ የመንግሥቴን ፣ ኃይል ፣ መርምራችሁ ። ተመልሳችሁ ፣ እንድትነግሩት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በእውነት ፣ የእኔን ፣ ወዳጅነት ፣ ፈልጎ ፣ አይደለም ፣ . . . አሁንም ፣ ከኔ ፣ ወገን ፣ ይኸን ፣ ቀስት ፣ ወስዳችሁ ፣ ለፋርስ ፣ ንጉሥ ፣ ስጡት ፣ እንደኔም ፣ ይኸን ፣ ቀበት ፣ የሚዘረጋ ፣ ከፋርስ ፣ ውስጥ ፣ ጕበዝ ፣ የተገኘ ፣ እንደሆነ ፣ ከዚያ ፣ ወዲያ ፣ መጥተው ፣ ይውጉኝ ፣ ሲል ፣ እርሱ ፣ ራሱ፣ በነሱው፣



ፊት ፣ ቁልማማውን ፣ ቀስት ፣ ዘርግቶ ፣ አሳይቶ ፣ መልሶ ፣ የዘረጋ ውን ፣ ቆልምሞ ፣ ሰጣቸው ፤ እነሱም ፣ ያመጡለትን ፣ ልብስና ፣ ወርቅ ፣ ከተመለከተ ፣ በኋላ ፣ ይኸ ፣ ሁሉ ፣ በኔ ፣ ዘንድ ፣ ርካሽ ፣ ነው ፣ እስረኞዬን ፣ እንኳን ፣ በወርቅ ፣ እግር ፣ ብረትና ፣ ሰንሰለት ፣ ነው ፣ የማስረው ፣ ሲል ፣ እወህኒ ፣ ቤት ፣ ድረስ ፣ መልክተኞቹን ፣ ራሱ ፣ ወስዶ ፣ አሳያቸው ፣ ይባላል ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ መልክተኞቹ ፣ ተሰናብተው ፣ ወደ ፣ አገራቸው፣ ተመለሱ ። ያዩትንም ፣ የሰሙትንም ፣ ሁሉ ፣ ነገሩት ፤ ይልቁንም ፣ የቀስቱን ፣ አላላክና ፣ ማስፈራራት ፣ በሰማ ፣ ጊዜ ፣ ካምቢዝ ፣ ተና ደደ ። ከፋርስና ፣ ከባቢሎን ፣ ሌላ ፣ ጭፍራም ፣ ሳይጨምር፣በንዴት፣ በአጠገቡ ፣ የሚገኘውን ፣ ጦር ፣ ብቻ ፣ ይዞ ፣ ኢትዮጵያን ፣ ለመው ጋት ፣ ተነሥቶ ፣ ጉዞውን ፣ ወደመርዌ ፣ ዠመረ ። ግማሹን ፣ ጦር ፣ በዓባይ ፣ በኩል ፣ ልኮ ፣ ግማሹን ፣ ጦር ፣ ራሱ ፣ እየመራ ፣ ውሃ ፣ በሌ ለበት ፣ በኮርስኮ ፣ በረሃ ፣ በኩል ፣ መጣ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ በበረሃ ፣ መካ ከል ፣ ሲገባ ፣ ሠራዊቱ ፣ በውሃ ፣ ጥም ፣ የተነሣ ፣ መንዝ ፣ አቃተው፣ ስንቅም ፣ አለቀበት ። ስለዚህ ፣ ለወታደሩ ፣ የድንፋታም ፣ የሚያበ ረታታም ፣ ቃል ፣ እየተናገረ ፣ ቢያዝ ፣ የጦር ፣ ሠራዊቱ ፣ ችግሩን ፣ ማለፍ ፣ በጭራሽ ፣ የማይቻለው ፣ ሆነ ።

ይኸንንም ፣ ራት ፣ ጭምር ፣ ስለተረዳው ፣ እንደተናደደ ፣ ሳይ ወድ ፣ በግድ ፣ ተመልሶ ፣ ወደቴብ ፣ ከተማ ፣ ሔደ ። ነገር፣ ግን፣ከዚሁ እንደ ፣ ተመለሰ ፣ አሳቡ ፣ ሳይሳካለትና ፣ ኢትዮጵያን ፣ ሳይወጋና ፣ ሳያስገብር ፣ በመቅረቱ ፣ ብስጭት ፣ አድሮበት ፣ ስለነበረ ፣ እስኪ ሞት ፣ ድረስ ፣ በግብፃውያኑም ፣ በፋርሶቹም ፣ ብዙ ፣ የጭካኔ፣ሥራ፣ ሠራ ። ብዙም ፣ ደም ፣ አፈሰሰ ። ከኢትዮጵያ ፣ ንጉሥ ፣ ተልኮ ፣ የነ በረውን ፣ ቀስት ፣ መዘርጋት ፣ ሁሉ ፣ አቅቶት ፣ እሱ ፣ ብቻ ፣ የዘረጋ ውን ፣ ባርዲያ ፣ የሚባለውን ፣ የገዛ ፣ ዘመዱን ፣ አንቆ ፣ ገደለው ። የግብፅ ፣ ንጉሥ ፣ የነበረው ፣ ፕሳሜቲክ ፣ ፫ኛ ፣ የሚባለውንም ፣ አስ ገድሎ ፣ የግብፅን ፣ ግዛት ፣ ለእኅቱ ፣ ባል ፣ ለአርአዴንስ ፣ ( አርንዳ ቲስ) ፣ ሰጠው ። እንደዚህም ፣ እያደረገ ፣ በብስጭትና ፣ በጭካኔ ፣ ደም ፣ በማፍሰስ ፣ ከኢትዮጵያ ፣ መልስ ፣ አንድ ፣ ዓመት ፣ ተኩል ፣ ያህል ፣ እንደቆየ ፣ ሞተና ፣ ልጁ ፣ ዳርዮስ ፣ አንደኛ ፣ በመንግሥቱ ፣ ተከተለው ።

በዚሁ ፡ በካምቢዝና ፡ በዳርዮስ ፡ ፩ኛ ፡ በአርቅሴስ፡ በአርታክስሲስ ። አንደኛ ፡ በዳርዮስ ፡ ፪ኛ ፡ ዘመን ፡ ( ፭፻፳፪—፬፻ ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ) ላይ ፡ የፋርስ ፡ ግዛት ፡ ከመቼውም ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ ሰፍቶ ፡ ኃያል ፡ ሆነ ። የግዛቱ ፡ ስፋት ፡ ከሕንድ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሊብያ ፡ በደቡብ ፡ እስከ ፡ ናፓታ ፡ ወሰን ፡ ደረሰ ። ይኸንንም ፡ የሰፋውን ፡ ግዛት ፡ ዳርዮስ ፡ በ፳ ፡ ታላላቅ ፡ አገር ፡ ከፈለው ፡ በያንዳንዱ ፡ (አገር ፡ ሳትራፕ ፡ ያገር ፡ ጌታ) ፡ የሚባል ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ የሚገዛ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ሾመ ።

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በየግዛታቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ግብር ፡ እያስወጡ ፡ ወታደር ፡ እየመለመሉ ፡ ለትልቁ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ዳርዮስ ፡ ላለው ፡ በቀጥታ ፡ እየገበሩ ፡ ይገዛሉ ። ስለዚህ ፡ ከ፳ዱ ፡ የግዛት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ግብፅ ፡ አንደኛዋ ፡ ስለሆነች ፡ አርአንዲስ፡ በፋርስ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ተሾሞ ፡ ይገዛት ፡ ጀመር ። እሱም ፡ እንደጌታውና ፡ እንደአማቹ ፡ እንደካምቢዝ ፡ ኃይለኛ ፡ ሆኖ ፡ በልስላሴ ፡ ግብፅን ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ያዘዘውን ፡ የዳርዮስን ፡ ቃል ፡ እየጣሰ ፡ በግብፆቹ ፡ ላይ ፡ የአገዛዝ ፡ ቀንበር ፡ አጸናባቸው ። እንደዚሁም ፡ የመርዌዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ከካምቢዝ ፡ የተላላከው ፡ ንጉሣቸው ፡ ናስቶሴኔን ፡ ስለሞተ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሙ ፡ ሐዳስጥ ፡ (ሐድ ፡ አስ ፡ ኤው—ሐንዲው ፡ አብራ ፡ ) የሚባለው ፡ ነግሦ ፡ በነፃነት ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ያስተዳድራል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ በካምቢዝ ፡ ጊዜ ፡ የከሸፈውን ፡ አሁን ፡ አርአንዲስ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ የሐዳስጥን ፡ መንግሥት ፡ በፋርስ ፡ ተደግፎ ፡ ሊያስገብር ፡ መምጣቱን ፡ እንመለከታለን ።

በግብፁ ፡ ንጉሥ ፡ በአርአንዲስና ፡ በመርዌው፡ (ኢትዮጵያ ፡) ንጉሥ ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ ታሪክ ፡ የጻፈው ፡ ሄሌዎዶር ፡ የሚባል ፡ የግሪክ ፡ (የፊንቄ ? ) ተወላጅ ፡ በ፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ የነበረ ፡ ነው ። እሱም ፡ በግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ « ኤትዮፒኮ—ኢትዮጵያውያንና ፡ ወይም ፡ ቴያዠንና ፡ ካሪክሌ » በሚል ፡ አርእስት ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፏል ። ይኸን ፡ መጽሐፉን፡ ምንም፡ እንኳ ፡ የጽሑፉ ፡ አሰካክ ፡ አስደሳች ፡ ቢሆን ፡ ታሪኩ ፡ ልብ ፡ ወለድ፡ ይሆንን ፡ በማለት ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊና ፡ አንባቢ ፡ ለንግግሩ ፡



መሠረት ፡ ለመስጠት ፡ ይቸገርበታል ። ግማሾቹ ፡ ሄሊዎዶር ፡ ሲጽፍ ፡ አተራረኩን ፡ ከራሱ ፡ እየሞላ፡ ስለአጋነነው፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ታሪኩ ፡ ከመሠረቱ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለዋል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ተረት ፡ የመሰለውን ፡ የካሪክሌንና ፡ የቴያዥንን ፡ ጉዳይ ፡ ወደጐን ፡ ትተን ፡ እውነት ፡ የሚመስለውን ፡ የግብፅን ፡ ገዥና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ንጉሥ ፡ ጦርነት ፡ ከዚህ ፡ እንቀጥላለን ።

ፋርሶች ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ( ናፓታንና ፡ መርዌን ፡ ) እንደሌላው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ባይዙ ፡ ከግብፅ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ እንደዚሁም ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ አንዳንድ ፡ አገር ፡ መያዛቸው ፡ አልቀረም ፡ ከኢትዮጵያውያንም ፡ ውስጥ ፡ በፋርስ፡ ውስጥ፡ ወታደርነት ፡ እየተቀጠሩ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ እየሔዱ ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ ፋርሶች ፡ ግሪኮችን ፡ ለማስገበር ፡ በዳርዮስ ፡ ተከታይ ፡ በአክሳርኬስስ ፡ (፬፻፷፭—፬፻፳፭ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ) የሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ በተጓዘ ፡ ጊዜ ፡ በውጊያው ፡ ከነበረው ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ከተጠራቀመው ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ የአንበሳና ፡ የነብር ፡ ለምድ ፡ ለብሰው ፡ ከዓረቦች ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ በዳርዮስ ፡ ልጅ ፡ በአርሰቶን ፡ እየታዘዙ ፡ ተሰልፈው ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ ፋርስ ፡ ሙሉውን ፡ እንኳን ፡ ባይሆንለት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰሜናዊ ፡ ጠረፍ ፡ መግዛቱን ፡ ያስረዳል ። በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡ ዋና ፡ ጠብ ፡ ያበቀለው ፡ ወርቅና ፡ ማዕድን ፡ የሚገኝበት ፡ በሬላዬ ፡ ከተማ ፡ ዙሪያ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ነው ።

ይኸ ፡ ሥፍራ ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ በኢትዮጵያውያኑ ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በፋርሶቹ ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ ከተማይቱ ፡ በፋርስ ፡ ወታደር ፡ ትጠበቃለች ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ሐድ ፡ አስ ፡ ኤው ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ሔዶ ፡ የፋርሶቹን ፡ ወታደሮች፡ አባሮ ፡ ይቺን ፡ ከተማ ፡ አርአንዲስ ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ እጅ ፡ አደረገ ። አርአንዲስም ፡ ይኸን ፡ ሲሰማ ፡ ከቴብ ፡ ወታደሩን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቢዩን ፡ ከተማ ፡ መጣ ፡ ኢትዮጵያውያኑም ፡ ወደዚያው ፡ ሔደው ፡ ውጊያ ፡ ገጠሙ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ግብፆቹ ፡ አስቀድመው ፡ በከተማው ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ስለነበሩ ፡ ለኢትዮጵያውያኑ ፡ ማጥ

ቃት ፡ አልሆነላቸውም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡
የሚያደርገው ፡ ቢያጣ ፡ ያባይን ፡ ውሃ ፡ እያስቆፈረ ፡ በቦይ ፡ አው
ጥቶ ፡ ከተማውን ፡ እንዲያጥለቀልቅና ፡ የአርአንዲስ ፡ ጦር ፡ ከው
ስጥ ፡ እንዲወጣ ፡ ማስገደጃ ፡ ብልሃት ፡ ሠራ ። ስዚያን ፡ ጊዜ ፡ አር
አንዲስ ፡ ከከተማዋ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ወጥቶ ፡ ለመዋጋት ፡ ወሰነ ።
እሱንም ፡ በተከተለው ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የፋርስ ፡ የሜዶን ፡ የሊብያ ፡
የግብፅ ፡ ወታደር ፡ ፈረሰኛውም ፡ እግረኛውም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ከኢ
ትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ እነዚያ ፡ በዋሻ ፡ ነዋሪ ፡ በበረሃ ፡ ነዋሪ ፡
የሚባሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የበጃ ፡ የብሌመይ ፡ የዓረብ ፡
ተወላጆች ፡ ናቸው ። ከእነሱም ፡ ውስጥ ፡ በቀስት ፡ አደጋገንና ፡
አወራወር ፡ በግር ፡ ሩጫ ፡ በዝኆንና ፡ በግመል ፡ግልቢያ ፡ የተመሰ
ገኑ ፡ ሞልተዋል ።

እንደዚህ ፡ የበረከተው ፡ የሁለቱ ፡ ወገን ፡ ጦር ፡ ከተቀራረበ ፡
በኋላ ፡ የፋርስ ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ሽምጡን ፡ ለቆ ፡ መጣ ። ኢትዮጵ
ያውያንም ፡ በንጉሣቸው ፡ የጦር ፡ መላ ፡ አዋቂነት ፡ እየተመሩ ፡
በዝግታ ፡ የፋርስን ፡ ጦረኛ ፡ ተቀብለው ፡ ፈረሰኛው ፡ ከፈረሰኛው ፡
እግረኛው ፡ ከእግረኛው ፡ ዝኆን ፡ ተቀማጩም ፡ ባለጦሩም ፡ ባለቀ
ስቱም ፡ ሁሉም ፡ ተደባልቆ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። የፋርሱ ፡ መሪ ፡
ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የተማመነው ፡ የፈረሰኛውን ፡ ጦር ፡ ነበር ። ይኸ
ንንም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለአወቁት ፡ በተለይ ፡ የብሌሜይ ፡ አገር ፡
ተዋጊ ፡ ጩቤውን ፡ እንደያዘ ፡ አፈረሰኛው ፡ መሃል ፡ ገብቶ ፡ ተዋጊ
ውን ፡ ትቶ ፡ አባሮ ፡ የሚመታበትን ፡ ሸሽቶ ፡ የሚያመልጥበትን ፡
የፈረሱን ፡ ሆድ ፡ ሆዱን ፡ በጩቤ ፡ እየዘረከተ ፡ ረፈረፈው ። የፋ
ርስ ፡ ወታደርም ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ከወደቀ ፡ በኋላ ፡ የለበሰው ፡ የብ
ረት ፡ ልብስና ፡ የራሱ ፡ ጥሩር ፡ ለሩጫም ፡ ለመዋጋትም ፡ ስለከለ
ከለው ፡ ብለሜዎቹ ፡ እንደልባቸው ፡ እየደበደቡ ፡ ፈጁት ፡ የቀረው
ንም ፡ የፋርስን ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ኢትዮጵያውያኑን ፡ የያዘው ፡ የዝ
ኆኑ ፡ አጐዳ ፡ በላያቸው ፡ እየሮጠ ፡ ሲፈጅ ፡ በዝኆኑ ፡ ላይ ፡ የተ
ቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ቀስታቸውን ፡ እየደገኑ ፡ በወስፈንጥራ
ቸው ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ ፈጁ ። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ የፋርሶችና ፡ የግብፆቹ ፡
መሪ ፡ የነገሩን ፡ አያያዝ ፡ ቢያመዛዝነው ፡ እንደማያዛልቅ ፡ ስለተረ



ዳው ፡ በወርቅ ፡ ሠረገላው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ እየተመለከተ ፡ ሲያ
ዋጋ ፡ ቆይቶ ፡ የነገሩን ፡ ማስፈራት ፡ ሲረዳው ፡ ከሠረገላው ፡ ወርዶ ፡
በፈረሱ ፡ ላይ ፡ ተጋብቶ ፡ ሸሸ ። እሱ ፡ ከሸሸ ፡ በኋላ ፡ ተራው ፡ የግ
ብፅና ፡ የሊብያ ፡ የሜዶን ፡ ወታደር ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ተዋጋ ። በኋላ ፡
ግን ፡ የንጉሣቸውን ፡ መሸሽ ፡ የታመኑበትን ፡ የፈረሰኛውን ፡ ማለቅ ፡
ሲሰሙ ፡ ከሞት ፡ የተረፉት ፡ ግማሾቹ ፡ ሸሹ ፡ የቀሩትም ፡ ተማረኩ ።
የኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ፡ ድሉ ፡ ወደራሱ ፡ መሆ
ኑን ፡ ስለተረዳው ፡ እዚህ ፡ እየተዋጋችሁ ፡ መፋጀታችሁን ፡ ትታ
ችሁ ፡ ሔዳችሁ ፡ ሌሎቹ ፡ የሚሸሹበትን ፡ መንገድ ፡ ያዙ ፡ ብሎ ፡
አዞ ፡ ኖሮ ፡ እነዚሁ ፡ የተላኩት ፡ በዓባይ ፡ ዳር ፡ ያለውን ፡ በሩን ፡
ስለያዙባቸው ፡ ግማሾቹ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እየገቡ ፡
ሞቱ ። በፈረስ ፡ የሸሸውም ፡ ንጉሡ ፡ አርአንዲስ ፡ ተመትቶ ፡ እንደ ፡
ተማረከ ፡ ደሙን ፡ እያዝረከረከ ፡ ዕድል ፡ አድራጊው ፡ ንጉሥ ፡ እሌ
ዳስፕ ፡ ፊት ፡ ቀረበ ። የኢትዮጵያዊው ፡ ንጉሥም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡
ራራለት ፤ ብዙም ፡ የሚያጽናና ፡ ንግግር ፡ አደረገለት ። ቍስሉንም ፡
አከሙት ፡ ብሎ ፡ ለመድኃኒት ፡ አዋቂዎች ፡ አዘዘ ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምርጥ ፡ በሆነው ፡ በወርቅ ፡ ዕቃ ፡ በተጫነው ፡
ዝኆን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ እንደታጀበ ፡ በየመንገዱ ፡
ዕልልታና ፡ ደስታ ፡ እየተፈራረቀለት ፡ ወደሲዬን ፡ ከተማ ፡ ገባ ።
እንደዘመኑ ፡ ልማድ ፡ ለዓባይ ፡ አምላክ ፡ ነጭ ፡ በሬ ፡ አርዶ ፡ የምስ
ጋና ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። የኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡ የድሉን ፡
በዓል ፡ የመሥዋዕቱን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከምርኮ
ኞቹ ፡ ውስጥ ፡ ባርነት ፡ ያላቸውን ፡ ለወታደሩና ፡ ለሹማምንቱ ፡
አደላቸው ። የጨዋ ፡ ወገን ፡ የሚባሉትን ፡ ሁሉ ፡ ነፃነት ፡ ሰጥቶ ፡
ለቀቃቸው ። ቈስሎ ፡ ለተኛው ፡ ለግብፁ ፡ ንጉሥ ፡ ለፋርሱ ፡ ገዥ ፡
ለአርአንዲስ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ላከበት ። የዚህ ፡ የጦርነት ፡ ምክን
ያት ፡ የሆነውን ፡ የፊላዬን ፡ ከተማና ፡ የማዕድኑን ፡ ሥፍራ ፡ በእጄ ፡
አደርጋለሁ ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ከንቱ ፡ የግዛት ፡ ፍላጎት ፡ የለኝም ።
ራሱ ፡ በጠባዩ ፡ በዓባይ ፡ የተከለለው ፡ የጥንት ፡ አገሬ ፡ ይበቃኛል ።
ፍርድንና ፡ ሕግንም ፡ ለማክበር ፡ ስል ፡ አንተንም ፡ በነፃነት ፡ ለቅቄ
ሃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለወደፊቱ ፡ ከወሰንህ ፡ አትለፍ ። ለፋርሱ ፡ ንጉ

ሥም ፡ እንደዚህ ፡ ብለህ ፡ ጸፍለት ፡ «ወንድምህ ፡ ሒዳስፕ ፡ (ሒድ አስ—ኤው ) ድልን ፡ በጨበጣ ፡ ውጊያ ፡ አግኝቷል ። ነገር ፡ ግን ፡ የራስህን ፡ አገር ፡ መልሶ ፡ ለቆልሃል ። ይኸንንም ፡ ማድረጉ ፡ ወዳጅ ነትህን ፡ ፈልጎ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ፍቅር ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ከዕ ንቍ ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ ነውና ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የጦርነት ፡ ምልክት ፡ በምትሰጥበት ፡ ቀን ፡ ለመዋጋት ፡ እምቢ ፡ አይልም » ።

ይኸንንም ፡ ሁሉ ፡ አድርጎ ፡ ሲጨርስ ፡ ወደራሱ ፡ ከተማ ፡ ወደመርዌ ፡ በደስታ ፡ ተመለሰ ። ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ የቆየውን ፡ ያገር ፡ ልምድ ፡ በመከተል ፡ ለፀሐይ ፡ አምላክ ፡ አራት ፡ ነጭ ፡ ፈረ ሶችና ፡ አንድ ፡ ከሴት ፡ ያልደረሰ ፡ የሰው ፡ ወጣት ፡ ለጨረቃ ፡ አም ላክ ፡ ሁለት ፡ ነጫጭ ፡ በሬዎችና ፡ አንዲት ፡ ከወንድ ፡ ያልደረሰች ፡ ልጅ ፡ አገረድ ፡ ሠዋ ፡ ይባላል ።

ይኸም ፡ የሰው ፡ መሥዋዕት ፡ ልማድ ፡ በአፍሪካና ፡ በእስያ ፡ በምሥራቅ ፡ አውሮፓ ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ የተለመደ ፡ ነበር ። የመ ርዌም ፡ የግብፃውያንም ፡ የአሶራውያንና ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በርታ ፡ ያለ ፡ ችግርና ፡ ጦርነት ፡ ሲገጥማቸው ፡ ለአማልክቶቻቸው ፡ ስለት ፡ የሚያደርጉት ፡ ሲደርስላቸውም ፡ የሚ ሠዉት ፡ የሰው ፡ መሥዋዕት ፡ ነበር ። እንኳን ፡ እነሱ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ምርጥ ፡ የሚባሉት ፡ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ እስራኤሎች ፡ እን ኳን ፡ ይኸንን ፡ ልማድ ፡ የተከተሉበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ዮፍታሄ (ይፋ ትህ) ፡ የሚባለው ፡ የእስራኤል ፡ መስፍን ፡ የአሞን ፡ ንጉሥ ፡ አገ ሩን ፡ ፓለስቲንን ፡ ሊቀማው ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ በተንዘበት ፡ ጊዜ ፡ «የአሞንን ፡ ልጆች ፡ በጄ ፡ አሳልፈህ ፡ ብትሰጠኝ ፡ ድል ፡ አድርጌ ፡ ስመለስ ፡ ከቤት ፡ ሊቀበለኝ ፡ መዠመሪያ ፡ የሚወጣውን ፡ እሠዋል ሃለሁ » ፡ ብሎ ፡ ተሳለ ። ከአሞናውያን ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲመለስ ፡ ከቤቱ ፡ የሚወዳትና ፡ የወለዳት ፡ ልጁ ፡ ከበሮዋን ፡ እየመ ታች ፡ ልትቀበለው ፡ ወጣች ። ባያትም ፡ ጊዜ ፡ ደንግጦ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፤ እንዲህም ፡ አላት ፡ «አወይ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ አጥብቀሽ ፡ አሳ ዘንሺኝ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አፌን ፡ ከፍቻለሁና ፡ ከዚያም ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ (የተሳልሁትንም ፡ አስቀር ፡ ዘንድ) ፡ አይቻለኝም» አላት ። እሷም ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ መለሰችለት «አባቴ ፡ ሆይ ፡ አፍ



ህንስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከከፈትህ ፡ እንደተሳልህ ፡ አድርግብኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጥቼ ፡ ለብላቴንነቴ ፡ (ለወጣትነቴ) ከንደኞቼ ፡ ጋር ፡ እንዳለቅስ ፡ ፍቀድልኝ» አለችው ። እሱም ፡ ፈቀደላት ፡ ወደተራራው ፡ ሔዳ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ከአለቀሰች ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አባቷ ፡ ተመለሰች ፡ እሱም ፡ እሷን ፡ ሠዉቶ ፡ ስለቱን ፡ ፈጸመ » (፩) ።

ወደ ፡ ታሪኩ ፡ እንመለስ ።

የኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡ ሒዳስፕ ፡ በመርዌ ፡ ከተማ ፡ የድሉን ፡ በዓል ፡ የመሥዋዕቱን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በውስጡ ፡ የሚ ገዙ ፡ አገሮች ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ አለህ ፡ ለማለት ፡ የሴርን ፡ ሰዎች ፡ የነ ጭና ፡ የቀይ ፡ ባሕር ፡ ሰዎች ፡ የየመን ፡ ሰዎች ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ፡ ከኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ያሉት ፡ ወርቅና ፡ ጥንድ ፡ አንበሶች ፡ ብሌ ሜይ ፡ ቀስትና ፡ ወስፈንጥር ፤ አክሱሞች ፡ (በተገዥነት ፡ ሳይሆን ፡ በወዳጅነት) ፡ ቀጭኔ ፡ አመጡለት ። እሱም ፡ የድሉን ፡ በዓል ፡ ለማ ክበር ፡ መታያ ፡ እየያዙለት ፡ ለመጡት ፡ ሁሉ ፡ ሽልማትም ፡ ስጦ ታም ፡ እየሰጠ ፡ አስደስቶ ፡ በያገራቸው ፡ ሰደዳቸው ። በዚህ ፡ ሰሞን ፡ ለታሠረ ፡ እሥረኛና ፡ ወንጀለኛ ፡ ሁሉ ፡ ምሕረት ፡ አድርጎ ፡ ሁሉ ንም ፡ አስደሰተ ፡ ይባላል (፪) ።

ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ታሪኩ ፡ እንደሚለው ፡ በቅን ፡ ፍርድና ፡ በትክ ክለኛነት ፡ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ በ፬፻፶፱ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ሞተ ። በመንግሥቱም ፡ ዘመዱና ፡ ወራሹ ፡ ቤሩአ —ኤም—ሔብ ፡ ከሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ እስኪነግሥ ፡ ድረስ ፡ ታአኬን ፡ ነገሠ ። ከታአኬን ፡ በኋላም ፡ ሕንደኬ ፡ ንግሥት ፡ የምትባለዋ ፡ በመርዌ ፡ ነገሠች ። በሷም ፡ ዘመን ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ተነ ሥቶ ፡ ትልቁን ፡ የፋርስን ፡ መንግሥት ፡ ገልብጦ ፡ የራሱን ፡ የቄ ሣር ፡ ግዛት ፡ አቆመ ። የዚህንም ፡ ታሪክ ፡ ከግሪክ ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ አያይዘን ፡ ከሥር ፡ ዠምረን ፡ ቀጥሎ ፡ በሚገኘው ፡ ምዕራፍ ፡ እን መልከት ።

---

(፩) መጽ ፡ መሳፍንት ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፴—፵ ።

(፪) J. MORE – HIST. d'ETHIOPIE ፩ኛ ፡ ቮሊዩም ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፩ ፡

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

## ግሪኮች ።

ዛሬ ፡ «ግሪክ» ፡ በሚባለው ፡ ስም ፡ የተጠቀለለው ፡ ሕዝብ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዘሩም ፡ ቋንቋውም ፡ የተለያየ ፡ ነበር ። የኑሮውም ፡ ጊዜ ፡ በግምት ፡ የሚታወቀው ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከ፩ሺ ፡ ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ነው ።

ግሪኮች ፡ የሚባሉት ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ ደግሞ ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡት ፡ የዮኒክ ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ዛሬ ፡ አቴና ፡ ባለበት ፡ አቲካና ፡ አውቢያ ፡ በሚባለው ፡ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ተቀመጡ ። እነዚህም ፡ የአቴንን ፡ ከተማ ፡ የመሠረቱ ፡ ናቸው ። ደግሞ ፡ ግማሾቹ ፡ ከላይ ፡ ከሰሜን ፡ ከቴሳሊያን ፡ ከትራቺያ ፡ መጥተው ፡ እስከ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ያዙ ። እነዚህም ፡ ለየግላቸው ፡ ሦስት ፡ ቋንቋ ፡ (ዲያሌክት) ፡ ለየራሳቸው ፡ የሚናገሩ ፡ ሕዝቦች ፡ በያሉበት ፡ ተቀምጠው ፡ ጥቂት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ እንደኖሩ ፡ አሁንም ፡ ከሰሜን ፡ ዶሪክ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ቋንቋቸውም ፡ የራሳቸው ፡ የሆነ ፡ የዶርያ ፡ ሕዝቦች ፡ አገራቸውን ፡ ትተው ፡ በተሳልያ ፡ አልፈው ፡ የዛሬውን ፡ ደቡብ ፡ አገር ፡ የፔሎፖኒን ፡ የላቆኒን ፡ አገር ፡ ያዙ ። ከዚያም ፡ አብረዋቸው ፡ ከተደባለቋቸው ፡ ግሪኮች ፡ ጋር ፡ እያለፉ ፡ ከሬትና ፡ ፕሮን ፡ የሚባለውን ፡ አገር ፡ አቀኑ ። የስፖርታንም ፡ ከተማ ፡ ከተሙ ።

ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ዩኒክ ፡ የሚባሉት ፡ የአቴንን ፡ ከተማ ፡ የከተሙት ፡ ግሪኮች ፡ የባሕር ፡ መንገድና ፡ ዋናን ፡ ሌላም ፡ ሥልጣኔ ፡ ከፊንቂዎች ፡ ተምረው ፡ ሠልጥነው ፡ ነበርና ፡ ከአድሪያቲክ ፡ ባሕር ፡ እየተሻገሩ ፡ በነአልችቢያድ ፡ እየተመሩ ፡ ከኢጣልያ ፡ አገር ፡ ሲሲሊንና ፡ ከፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ማርሴይን ፡ አቅንተው ፡ ከዚያም ፡ አልፈው ፡ እስከ ፡ ኤስፓኝ ፡ ጫፍ ፡ ደረሱ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ ሕዝቦቹ ፡ በጠቅላላው ፡ በአገሩ ፡ ስም ፡ ግሪኮች ፡ እየተባሉ ፡ ከመጠራት ፡ ይልቅ ፡ በየከተማቸው ፡ ስም ፡ መጠራት ፡ ልማድ ፡ ስለነበረ ፡ ዛሬ ፡ በመላው ፡ ግሪኮች ፡ የሚባሉት ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የአቴና ፡ ሕዝቦች ፡ ትግል ፡ ሩጫ ፡ አመታትና ፡



ምከት ፡ በጣም ፡ ያውቁ ፡ ነበር ። አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ደንብ ፡ ሆኖ ፡ ጥፋት ፡ ባይኖርባቸው ፡ ዠግንነትን ፡ መከራና ፡ ሥቃይን ፡ ለመማር ፡ ሲሉ ፡ ይገረፋሉ ። በግርፋቱም ፡ ጊዜ ፡ ያለቀሰ ፡ ወይም ፡ በፊቱ ፡ የኃዘን ፡ መልክ ፡ ያሳየ ፡ ተመልካቹ ፡ ሕዝብ ፡ ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ እየሳቀ ፡ ይሳለቅበታል ። ሳያለቅስ ፡ የደስታ ፡ መልክ ፡ እያሳየ ፡ ግርፋቱን ፡ የፈጸመ ፡ ጐበዝ ፡ ጨካኝ ፡ ተብሎ ፡ የወንድነት ፡ ስም ፡ ይሰጠዋል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጥሪት ፡ በውነታቸውን ፡ ከድካምና ፡ ከልስሳሴ ፡ አድነው ፡ ጠላት ፡ በተዋጋቸው ፡ ጊዜ ፡ የቀን ፡ ሐሩር ፡ የሌት ፡ ቁር ፡ የጠላት ፡ በትር ፡ ሳያስፈራቸው ፡ እነሱ ፡ ጠላት ፡ አጥቅተው ፡ ለመመለስ ፡ እንዲጸኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እስፓርታዎች ፡ በትግል ፡ በሩጫ ፡ በጠቅላላው ፡ በመሬት ፡ ጦርነት ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌላቸው ፡ ነበሩ ። አቴናዎች ፡ ደግሞ ፡ በውሃ ፡ ዋናና ፡ በመርከብ ፡ ጦርነት ፡ የሚችላቸው ፡ አልነበረምና ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ቢዋጉ ፡ ከሩቅ ፡ የመጣው ፡ ይልቁንም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እየደጋገመ ፡ የሚደርስባቸውን ፡ የፋርስን ፡ ወረራ ፡ በመሬት ፡ ጦርነት ፡ ስፓርቶች ፡ በባሕር ፡ ጦርነት ፡ አቴናዎች ፡ እየተባበሩ ፡ አግደዋል ። በመጨረሻም ፡ በፍጹም ፡ አሸንፈው ፡ ጠላትን ፡ መልሰዋል ።

ከፋርስ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እዚያው ፡ አጠገብ ፡ ያለው ፡ የሜዶን ፡ መንግሥት ፡ ትልቅ ፡ ስም ፡ እንደነበረው ፡ እንደዚሁም ፡ ከአቴናዎች ፡ በፊት ፡ ስፓርቶች ፡ በማቸውም ፡ ኃይለኝነታቸውም ፡ በጣም ፡ የገነኑ ፡ ነበር ። ንጉሥም ፡ ነበራቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደዛሬው ፡ ዘመን ፡ የዲሞክራሲ ፡ አስተዳደር ፡ ማናቸውንም ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚቈርጡት ፡ ያገር ፡ ሽማግሌዎችና ፡ አዋቂዎች ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ ንጉሣቸው ፡ ወይም ፡ መሪያቸው ፡ እንደፈቃዱ ፡ የልቡን ፡ ለመሥራት ፡ መብት ፡ አልነበረውም ፡ ትልቅ ፡ የውስጥ ፡ የአስተዳደር ፡ ወይም ፡ የጦርነት ፡ ጉዳይ ፡ መዠመሪያ ፡ እነዚህ ፡ አዋቂዎች ፡ ከመከሩበት ፡ በኋላ ፡ አባባቸው ፡ ለንጉሡ ፡ ይቀርባል ። ንጉሡም ፡ የሽማግሌዎቹን ፡ አሳብ ፡ ይዞ ፡ ሕዝብ ፡ ወደሚሰበሰብበት ፡ ሸንጎ ፡ ሔዶ ፡ ሕዝቡን ፡ በአዋጅ ፡ ሰብስቦ ፡ ከአዋቂዎች ፡ የቀረበለትን ፡ አሳብ ፡ በመግለጽ ፡ የሕዝቡን ፡ ውሳኔ ፡ ይጠይቃል ። ሕዝቡም ፡

ነገሩን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ እሺ ፡ ወይም ፡ እምቢ ፡ የማለት ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ፡ ይባላል ።

ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ በነፃው ፡ ዓለም ፡ በእንግሊዝ ፡ በፈረንሳዊ ፡ በአሜሪካ ፡ በሌሎችም ፡ አገር ፡ ያለውን ፡ የዲሞክራሲን ፡ (የሕዝብ ፡ መንግሥት) ፡ አስተዳደር ፡ የሕጉንና ፡ የሥርዓቱን ፡ መሠረት ፡ ያጠኑት ፡ የቀድሞው ፡ የግሪክ ፡ ሕዝቦች ፡ ይሠሩበት ፡ ከነበረው ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ተወስዶ ፡ በማሻሻል ፡ ነው ። ለስፓርታዎች ፡ በዲሞክራሲ ፡ ደንብ ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ አዘጋጅቶ ፡ የሰጣቸው ፡ ሊኩርጎስ ፡ የሚባል ፡ የተማረ ፡ ሊቅ ፡ ነበር ። ባለፈው ፡ ታሪኩን ፡ ያነበብነው ፡ ሐሙራቢ ፡ ለባቢሎናውያን ፡ እንደሆነው ፡ ሊኩርጎስ ፡ በሊቅነቱና ፡ በሕግ ፡ ሐጋጊነቱ ፡ በስፓርታ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ስም ፡ አሰው ።

የአቴናዎችን ፡ ደግሞ ፡ ባጭሩ ፡ እንመልከት ። ያገሩ ፡ ታሪክ ፡ እንደሚለው ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡት ፡ ሕዝቦች ፡ አቴን ፡ ያለበትን ፡ ሥፍራ ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ ዮን ፡ የሚባለው ፡ የአጽሉን ፡ ልጅ ፡ (የዮናናውያን ፡ ዘር ፡ አባት) ፡ እነዚህኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ፲፪ ፡ ነገድ ፡ ከፍሎ ፡ ፲፪ ፡ መንደር ፡ አበጅቶላቸው ፡ ነበር ። ከነዚህም ፡ ፲፪ኛው ፡ የአቴን ፡ ከተማ ፡ ነው ። በአቴንም ፡ ንጉሡ ፡ ይቀመጥባት ፡ ስለነበረ ፡ ከሌሎች ፡ የበለጠች ፡ ዋና ፡ የሕዝብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ከተማ ፡ ሆነች ። ሕዝቦቿም ፡ በእርሷ ፡ ስም ፡ አቴናዎች ፡ ይባሉ ፡ ዠመር ። በሕይወታቸው ፡ ከጐረቤቶቻቸው ፡ ከስፓርታዎች ፡ ከፔሎፒኒሶች ፡ ከዶርያዎች ፡ ጋር ፡ ውጊያ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። ከነዚያ ፡ ጋር ፡ ሲዋጉ ፡ ከድርብ ፡ የሚባለው ፡ የተወደደው ፡ ንጉሣቸው ፡ አገሩን ፡ ለማዳን ፡ እጦርነት ፡ ላይ ፡ ሕይወቱን ፡ ሰውቶ ፡ ሞተ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቴናዎች ፡ ከሱ ፡ ቀጥሰው ፡ ሥልጣን ፡ የሚይዙት ፡ «አርኮንት ፡ የአዋቂ ፡ አስተዳዳሪ» ፡ ይባሉ ፡ እንጂ ፡ እንደርሱ ፡ ንጉሥ ፡ ተብለው ፡ አይጠሩም ፡ ብለው ፡ ንጉሣዊ ፡ ግዛትን ፡ አስቀሩ ። ይኸም ፡ ውሳኔ ፡ በገሚሶቹ ፡ አተራረክ ፡ ሟቹን ፡ ንጉሥ ፡ ለማክበርና ፡ የሱ ፡ ተከታይ ፡ አይገኝም ፡ በማለት ፡ የተደረገ ፡ ሲመስል ፤ በቀሩት ፡ አተራረክ ፡ ደግሞ ፡ ሀብታሞችና ፡ የከፍተኛ ፡ ተወላጆች ፡ (አሪስቶክራቶች) ፡ የሆኑት ፡ ቀድሞ ፡ የንጉሡን ፡ መኖር ፡ ይቃወሙ ፡ ነበርና ፡ አሁንም ፡ ሕዝብ ፡



በየጊዜው ፡ በሚመርጠው ፡ አዋቂ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ እንገዛ ፡ ብለው ፡ ወስኑ ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

የሆን ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ ተቈረጠና ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፮፻ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ሶሎን ፡ የተባለው ፡ ከሰባቱ ፡ ሊቃውንት ፡ አንዱ ፡ ሊቅ ፡ «አርኮንት» ፡ ተብሎ ፡ ተመረጠ ። እሱም ፡ ሕዝቡ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ሰጥቶ ፡ ያስተዳድራቸው ፡ ዠመር ። ሕዝቡም ፡ በሶሎን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ተሰኘ ። ከዚያ ፡ ፒስትራት ፡ የሚባለው ፡ ተመረጠና ፡ የአቴናዎችን ፡ ኃይልና ፡ ኑሮ ፡ ከሌሎቹ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ሲደክም ፡ ኖሮ ፡ በ፭፻፳፯ ፡ ዓመት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ሞተ ። በሥልጣኑም ፡ ሔፒያና ፡ ሂፓርኮ ፡ የሚባሉት ፡ ልጆቹ ፡ ተከተሉት ። ነገር ፡ ግን ሕዝቡን ፡ ለመምራት ፡ ያላቸው ፡ ችሎት ፡ በቂ ፡ ስለአልነበረ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ የልጅነት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ሕዝቡ ፡ አልወደዳቸውም ፡ ነበርና ፡ ሂፓርኮንን ፡ አድመው ፡ ገደሉት ። ሂፒያ ፡ ግን ፡ ከአቴን ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ሔደ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በከፍተኛውና ፡ በተርታው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ በአስተዳደርና ፡ በሥልጣን ፡ መያዝ ፡ ምክንያት ፡ ትልቅ ፡ ሁከት ፡ ተነሣ ። ከፍተኞቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ዝቅተኛውን ፡ አሸንፈው ፡ መንግሥቱን ፡ ለማያዝ ፡ ከስፓርታዎች ፡ ርዳታ ፡ ጨምረው ፡ ኢፓጎር ፡ በሚባለው ፡ እየተመሩ ፡ እነዚህን ፡ ለመደምሰስ ፡ ሲነሡ ፡ የተርታው ፡ ሕዝብ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ክሊስቴን ፡ የሚባለውን ፡ ይዞ ፡ ተነሣ ። ውጊያም ፡ ዠምረው ፡ የተርታው ፡ ሕዝብ ፡ ወገን ፡ ተሸንፎ ፡ የሀብታሞቹ ፡ ወገኖች ፡ መንግሥቱን ፡ በ፭፻፰ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ለጊዜው ፡ እጅ ፡ አደረጉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ገዥነታቸው ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይቆይ ፡ ክሊስቴን ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ኢታጎርን ፡ ከነወገኖቹ ፡ አስወጥቶ ፡ የአቴንን ፡ ሥልጣን ፡ ያዘ ። የእርሱም ፡ አገዛዝ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ቆየ ። በዕውቀት ፡ በፍልስፍና ፤ በግጥም ፡ በሕክምና ፤ በታሪክ ፡ ጽሑፍ ፡ እነሄሮዱቱስ ፡ እነሶክራት ፡ እነሂፖክራት ፡ እነፕላቶን ፡ እነአሪስቶት ፡ ለአገራቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ እንደሰጥዋት ፡ በጦርነት ፡ ደግሞ ፡ እነቴሚስቶክል ፤ እነአሪስቲዴ ፤ እነፔሪክል ፡ እየተነሡ ፡ አገርን ፡ ከጠላት ፡ (ፋርስ) ፡ በመከላከል ፡ የጦር ፡ ድርጅት ፡

በማበጀት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ሆኑ ። እነሱም ፡ በየጊዜያቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የባሕር ፡ ጦር ፡ እያዘጋጁ ፡ ፋርሶች ፡ ይፀውት ፡ የነበረውን ፡ ደሴት ፡ ሁሉ ፡ አስለቀቁ ። ፔሪክል ፡ ደግሞ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ በማሳመሩ ፡ ሕዝቡንና ፡ ፫፻ ፡ የሚሆኑትን ፡ ከተማዎች ፡ አንድነት ፡ እንዲገብሩ ፡ አደረጋቸው ። እንደዚሁም ፡ አሪስቲድ ፡ ከፋርሶቹ ፡ ጋር ፡ በመዋጋት ፡ ተመስግኗል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ አቴኖዎች ፡ ብዙ ፡ ችግርና ፡ ፈተና ፡ ደረሰባቸው ። ባጠገባቸው ፡ ካሉት ፡ ወገኖቻቸው ፡ ከስፓርታዎች ፡ ሲዋጉ ፡ ከፋርስ ፡ ቢከላከሉ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አድሪአቲክንና ፡ ሜዲቴራኒያን ፡ እያለፉ ፡ ያቀኑት ፡ የሲሲል ፡ የማርሴይ ፡ አገር ፡ እየሸፈተባቸው ፡ ወደዚያ ፡ እየሔዱ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ እየሮጡ ፡ የሸፈተውን ፡ ለማሳመን ፡ ልውረር ፡ የሚለውን ፡ ለመከላከል ፡ ልደባልቃችሁ ፡ የሚለውን ፡ ለማገድ ፡ ብዙ ፡ ደከሙ ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እያሸነፉ ፡ ሲመለሱ ፡ እየተሸነፉም ፡ በስፓርታዎች ፡ የተገዙበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። የስፓርታና ፡ የአቴን ፡ ሕዝቦች ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ኅብረትና ፡ መከፋፈል ፡ ድል ፡ መሆንና ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ እየተፈራረቀባቸው ፡ ሲኖሩ ፡ በመጨረሻ ፡ ሁሉንም ፡ ደምስሶ ፡ በመግዛት ፡ የሚገላግላቸው ፡ ጉበዝ ፡ ከመቄዶንያ ፡ ተነሣ ። ይኸም ፡ ሰው ፡ የፊልጶስ ፡ ልጅ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ነው ። የርሱንም ፡ አነሣሥ ፡ ወደፊት ፡ እስክንመለከት ፡ ድረስ ፡ የግብፃውያንን ፡ የአሶራውያንንና ፡ የባቢሎናውያንን ፡ ሃይማኖት ፡ እንደተመለከትን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የግሪኮችን ፡ ሃይማኖት ፡ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## የግሪኮች ፡ አማልክት ።

በፍልስፍና ፤ በዕውቀት ፤ በቤት ፡ ሥራ ፤ በሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ከሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ የመሻል ፡ ሁኔታ ፡ እንዳላቸው ፡ በእምልኮም ፡ በብዙ ፡ ሳይሆን ፡ በመጠኑ ፡ ከነርሱ ፡ በፊትና ፡ በነርሱ ፡ ዘመን ፡ ካሉት ፡ ከግብፆች ፡ ከአሶራውያንና ፡ ከባቢሎናውያን ፡ ከቻይናና ፡ ከሕንድ ፡



የመሻል ፡ መንገድ ፡ ያሳያሉ ። እነዚያ ፡ የሰውን ፡ አምላክነት ፡ ወይም ፡ የማይታየውን ፡ አምላክ ፡ በሚታይ ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ መቅረጻቸው ፡ ባይቀር ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኮርማ ፡ በሬን ፤ አሞራን ፤ ፀሐይን ፤ ጨረቃን ፤ አማልክት ፡ ወይም ፡ የአማልክት ፡ ማደሪያ ፡ ሲያደርጉ ፡ ግሪኮች ፡ ግን ፡ አማልክት ፡ የሚያደርጉዋቸው ፡ በአስተዳደርና ፡ በጀግንነት ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆኑትን ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በፊት ፡ ቀንደኞችና ፡ ጀግኖች ፡ በኋላ ፡ አማልክት ፡ ያደረጓቸው ፡ ሰዎች ፡ መኖራቸው ፡ እውነትም ፡ ሐሰትም ፡ ቢሆን ፡ በእርእያ ፡ ሰው ፡ የተመሰሉና ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ የመዋደድ ፡ የመጣላት ፤ የመዋጋት ፤ የመጋባት ፡ የመፋታት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። ወደፊት ፡ እንደምናስረዳው ፡ የነሱም ፡ ነገዳቸውና ፡ ቍጥራቸው ፤ ተረታዊ ፡ የሆነ ፡ ታሪካቸውም ፡ ሰፊ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የታወቁትንና ፡ ያንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ወገን ፡ የሆኑትን ፤ ሥራቸውንና ፡ ስማቸውን ፡ ብቻ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የነዚሁ ፡ የአማልክቱ ፡ ታሪክ ፡ የሚለውን ፡ ተከትለን ፡ ባጭሩ ፡ እንጽፋለን ።

### ፩ኛ ፤ ዜውስ ፡ (በላቲን ፡ ዡፒተር) ።

ዜውስ ፡ የክሮኖና ፡ የሬአ ፡ ልጅ ፡ የኤራ ፡ ባል ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ የአማልክትና ፡ የሰው ፡ አባት ፡ ነው ። በልጅነቱ ፡ አባቱ ፡ ሊውጠው ፡ ሲያስብ ፡ እናቱ ፡ ወደ ፡ ክሬት ፡ አምጥታ ፡ ደበቀችው ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ ከክሬት ፡ ወደ ፡ ኦሊምፒያ ፡ ተራራ ፡ (የአማልክቱ ፡ መቀመጫ) ፡ ሔዶ ፡ አባቱን ፡ አብርሮ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ጌትነት ፡ ከወንድሞቹና ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ተካፈለ ። የርሱም ፡ ዋና ፡ የጦርነት ፡ መሣሪያው ፡ መብረቅ ፡ ነው ። በአየራት ፡ ያሉ ፡ ነጐድጓድ ፡ ነፋሳት ፤ ደመናት ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚተዳደሩ ፡ ናቸው ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ዘመድ ፡ ሆነው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የርሱና ፡ ያባቶቹ ፡ ባለጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ቲታኒ ፡ የሚባሉትን ፡ አማልክት ፡ ተዋግቶ ፡ ወደ ፡ እንጦርጦስ ፡ (ታርታር) ፡ የሰደዳቸው ፡ በመብረቅ ፡ በትር ፡ ነው ። ለአዝርዕትና ፡ ለአብቍልት ፡ ነፋስን ፤ ዝናብን ፤ ፀሐይን ፤ እንደ ፡ ጊዜው ፡ እያደላደለ ፡ የሚሰጥ ፤ ለሰው ፡ ለክፉው ፡ እንደክፋቱ ፤ ለደጉ ፡ እንደ ፡ ደግነቱ ፡ እየሰጠ ፡

ዕድሉን ፡ የሚወስን ፡ ርሱ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ ከርሱ ፡ በላይ ፡ በግሪክ ፡ « ሞይራ » ፡ በላቲን ፡ ፋቶ ፡ የሚባል ፡ የጨለማ ፡ አምላክ ፡ አለና ፡ ዜውስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ መጣላትና ፡ ማሸነፍም ፡ አይሆንለትም ። ዜውስ ፡ በተቈጣና ፡ ጭንቅላቱን ፡ ባወዛወዘ ፡ ጊዜ ፡ የኦሊምፒያ ፡ ተራራ ፡ በሙሉ ፡ ይነቃነቃል ።

ለዜውስ ፤ በግሪክ ፡ አገር ፡ በኦሊምፒያ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በዘመኑ ፡ ትልቅ ፡ የሚያምር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተሠርቶ ፡ በውስጡ ፡ የርሱ ፡ ሐውልት ፡ በትልቁ ፡ ተቀርጾ ፡ ይሰገድለታል ። ሐውልቱም ፡ በሕይወቱ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፡ የሚባለውን ፡ በመከተል ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ መብረቅ ፤ በግራ ፡ እጁ ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ ይታያል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ዋና ፡ ሚስቱ ፡ ሔራ ፡ ብትሆን ፡ ከቀሩት ፡ የሴት ፡ አማልክት ፡ ከነኢዮ ፤ ከነኤውሮፓ ፡ በመዋደዱ ፡ ምክንያት ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ የቅናት ፡ ክርክርና ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ነው ። ወደ ፡ ፊትም ፡ ተጽፈው ፡ የሚገኙት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አማልክት ፡ እርሱ ፡ ከሚስቱና ፡ ከውሽሞቹ ፡ የወለዳቸው ፡ የርሱ ፡ ልጆችና ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ናቸው ።

## ፪ኛ ፡ ሔራ ፡ ወይም ፡ ሔራሶ ፡ ( ጁኖን ፡ )

ሔራ ፡ የዜውስ ፡ ሚስትና ፡ እኅት ፡ ናት ። በቀጥታ ፡ ወይም ፡ ከባሏ ፡ ጋራ ፡ በመሳተፍ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ንግሥት ፤ የጋብቻ ፤ የትዳር ፡ የልደት ፤ የሕፃናት ፡ ጠባቂ ፡ ትባላለች ። እሷ ፡ ከባሏ ፡ ከዜውስ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ የማታውቅ ፡ በትዳሯ ፡ የታመነች ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ ባሏ ፡ ዜውስ ፡ ግን ፡ አማልክት ፡ የሆኑም ፡ ያልሆኑም ፡ ሌሎች ፡ ሴቶች ፡ እየወደደ ፡ በቅናት ፡ ምክንያት ፡ ያደረገችው ፡ ጦርነት ፡ በአማልክቱ ፡ የተረት ፡ መጽሐፍ ፡ ( ሚቶሎጊ ) ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ ተጽፏል ። ዜውስ ፡ ከወደዳቸው ፡ ሴቶች ፡ ውስጥ ፡ ዋነኞቹ ፡ «ኢዮ ፡ የምትባለዋ ፡ የቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ካህኒት ፡ ኤውሮፓ ፡ የምትባለዋ ፡ የፊንቄ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ናቸው» ።

አማልክቱ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የሚወዱትና ፡ በስለትም ፡ በመሥዋዕትም ፡ የሚቀበሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እንስሳና ፡ ፍራፍሬ ፡ አለ ።



ይኸውም ፡ ለየክፍላቸው ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ እንስሳና ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ዛፍ ፡ ይቈጠራል ። ለሔራ ፡ የሚቀርበው ፡ ስለትና ፡ ወይም ፡ ለርሷ ፡ የተቀደሱ ፡ እንስሶች ፡ ፍየልና ፡ በፈረንሳዊ ፡ ፓሽን ፡ የምትባል ፡ (በአገራችን ፡ የሌለች) ፡ ትልቅ ፡ ወፍ ፡ ናቸው ።

## ፫ኛ ፤ ሔፌስቶ ፡ ( ቮልካኖ ) ።

ሔፌስቶ ፡ የዜውስና ፡ የሔራ ፡ ልጅ ፡ የእኅቱ ፡ የአፍሮዲት ፡ ባል ፡ የእሳተ ፡ ገሞራ ፤ የብረታብረት ፡ አምላክ ፡ የቀጥቃጮችና ፡ የአንጥረኞች ፡ ጠባቂ ፡ ነው ። መልክ ፡ ጥፉና ፡ አንካሳ ፡ በመሆኑ ፡ እናቱ ፡ ሔራ ፡ ስለ ፡ ጠላችው ፡ ከኦሊምፒያ ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ወረወረችው ፡ ይባላል ። ደግሞ ፡ አባቱ ፡ ዜውስ ፡ ከሚስቱ ፡ ከሔራ ፡ ጋራ ፡ በቅናት ፡ የተነሣ ፡ በሚከራከሩበት ፡ ጊዜ ፤ ለናቱ ፡ እየረዳ ፡ ስላስቸገረው ፡ ዜውስ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ያውዘገዘገው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

## ፬ኛ ፡ አፍሮዲት ፡ ( ቬኑስ ፡ ቮኔሬ ) ።

አፍሮዲት ፡ የውበትና ፡ የፍቅር ፡ አምላክ ፡ ነች ። ገሚሱ ፡ የዜውስ ፡ ልጅ ፡ ሲያደርጓት ፤ ገሚሱ ፡ ደግሞ ፡ የኡራኖስ ፡ አባለ ፡ ዘር ፡ ተቆርጦ ፡ ከተጣለበትና ፡ ደሙ ፡ ከተንጠባጠበበት ፡ ከባሕር ፡ ዐረፋ ፤ ተወለደች ፡ ይላታል ። መልካም ፡ ቆንጆና ፡ መዘዞ ፡ ሆና ፡ ሳለ ፡ ለአንካሳውና ፡ ለአስከፊታው ፡ ለሔፌስቶ ፡ የተዳረችበትን ፡ ምክንያት ፡ ተራኪዎቹ ፡ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ ይገልጹታል ።

አንደኛው ፤ ዜውስ ፡ የፍቅር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ቢጠይቃትና ፡ እንቢ ፤ ብትለው ፡ ተናዶ ፡ ለአንካሳው ፡ ለሔፌስቶ ፡ ዳራት ፡ ይላሉ ። ሁለተኛው ፡ ሔፌስቶ ፡ መብረቅን ፡ ሠርቶ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሆነው ፡ ለዜውስ ፡ ቢሰጠው ፡ በስጦታው ፡ ተደስቶበት ፡ ነበርና ፡ ለዚሁ ፡ ውለታ ፡ ቈንጆዪቱን ፡ ዳረለት ፡ ይላሉ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ደንበኛ ፡ ባሏ ፡ ሔፌስቶ ፡ ቢሆን ፡ ከነአሬስ ፡ (ማርስ) ፡ ከነሔርሜስ ፡ (ሜርኩሪዮ) ፡ ጋራ ፡ ያደረገችው ፡ የፍቅር ፡ ግንኙነት ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ የርሷ ፡ ትልልቅ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በቆጵሮስ ፡ (ቺፕሮስ) ፡ በቆሮንቶስ ፡ በአርጎ ፡ ተሠርቶ ፡ በውስጡም ፡

የሷ ፡ ሐውልት ፡ በሚያምር ፡ ተሠርቶ፡ ይሰገድላት ፡ ነበር ። ለሷም ፡ የሚቀርበው ፡ ስለት ፡ ርግብና ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ነው ። በዚሁ፡ መሠረት፡ ይሆናል ፡ ዛሬም ፡ የተዋደደ ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ የጽጌ ፡ ረዳ ፡ አበባ ፡ የሚለዋወጥበት ፡ ምክንያት ።

## ፳ኛ ፤ ሔርሜስ ፡ ( ሜርኩሪዮ ) ።

ሔርሜስ ፡ የአማልክት ፡ መልክተኛ ፡ የነጋዴና ፡ የነጣቂ ፡ የመንገደኛ ፡ ጠባቂ ፡ ነው ። የምውታንንም ፡ ነፍስ ፡ እየመራ ፡ ወደ፡ ሲኦል ፡ (እንጦርጦስ) ፡ የሚወስድ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ከሌሎች ፡ አማልክት ፡ እየሰረቀም ፡ እየቀማም ፡ ብዙ ፡ ነገርና፡ ሴቶች ፡ ለራሱም ፡ ለሌሎች ፡ አማልክትም ፡ ይወስዳል ።

አባቱ ፡ ዜውስ ፡ ባለፈው ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ በሚስቱ ፡ በኤራ ላይ ፡ ኢዮ ፡ የምትባለዋን ፡ ወዶ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ሚስቱ ፡ ተቆጥታ ፡ ኢዮን ፡ ወደ ፡ ላም ፡ ለወጠቻት ። ቀጥሎም ፡ አርጎ ፡ ለሚባለው ፡ መቶ ፡ ዐይን ፡ ሰጥታ ፡ አሥሮ ፡ እንዲጠብቃት ፡ አዘዘችው ። የአርጎ ፡ መቶ ፡ ዐይኖችም ፡ ዕንቅልፍ፡ በያዛቸው ፡ ጊዜ ፡ ሃምሳው፡ ይከደናሉ ፡ ሃምሳው ፡ ክፍት ፡ ሆነው ፡ በየፈራረቃ ፡ ይጠብቃሉ ። ሔርሜስ ፡ ሔዶ ፡ አርጎን ፡ ገድሎ፡ እሥረኛዋን ፡ ነፃ ፡ እንዲያወጣ፡ ከዜውስ ፡ ታዘዘ ። እርሱም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አርጎን ፡ እንዴት ፡ እንደሚገድል ፡ ወይም ፡ ሳይገድል ፡ እንዴት ፡ ኢዮን ፡ ለመውሰድ ፡ እንደሚችል ፡ ተጨነቀ ። የአርጎ ፡ ተመልካቾቹ ፡ መቶ ፡ ዐይኖች ፡ ናቸውና ፡ አዘንግቶ ፡ ለመውሰድ ፡ አልተቻለውም ። እንዲሁም ፡ ዐይኖቹ ፡ እያዩ ፡ ሊገድለው፡ አልደፈረም ። ስለዚህ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ፡ በሙዚቃ ፡ ቃና ፡ ዕንቅልፍ ፡ ሊያስወስደው ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረገና ፡ በሰላማዊ ፡ መልክ ፡ ተጠግቶ ፡ የዜማውን ፡ ቃና፡ እየለዋወጠ፡ ሙዚቃውን ፡ ሲመታ ፡ በሙዚቃው ፡ ድምፅ ፡ ልቡ ፡ ተመስጦ ፡ የአርጎ ፡ መቶውም ፡ ዐይኖቹ ፡ እያደር ፡ ጨርሰው ፡ ተዘጉ ። በዚህ፡ ጊዜ፡ ሔርሜስ ፡ በድንጋይ ፡ መትቶ ፡ ገደለውና ፡ ኢዮን፡ አስፈታት ። ኢዮ፡ ግን ፡ በኤራ ፡ ሥልጣን ፡ ከላምነት ፡ ወደ ፡ ሰውነት ፡ አልተለወጠችም ፡ ነበርና ፡ በያለበት ፡ እየተቅበዘበዘች፡ ስትኖር ፡ እግብፅ፡ አገር ፡ ስትደርስ ፡ ዜውስ ፡ የሰውነት፡ መልኳን ፡ ሰጣት ፡ ይባላል ። ደግሞ ፡



ይህቺ ፡ ናት ፡ አርጤሚስ ፡ የኤፌሶኒቱ ።
( ሐውልቱ ፡ በናፖሊ ። )

CITY - HALL LIBRARY of ADDIS

ባንድ ፡ ወገን ፡ ሚስቱ ፡ በቅናት ፡ እንዳትገልበት ፡ እግብፅ ፡ እስክት ደርስ ፡ ድረስ ፡ ከሰውነት ፡ ወደ ፡ ላምነት ፡ የለወጣት ፡ ራሱ ፡ ዜውስ ነው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

ሔርሜስ ፡ ሰውነቱ ፡ እንደ ፡ ጉልማሳ ፡ በው ፡ ሆኖ ፡ በገጥ ፡ ግንዱና ፡ እቁርጭምጭሚቱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ትንንሽ ፡ ክንፎች ፡ ተደ ርገውለት ፡ ሐውልቱም ፡ በዚሁ ፡ ይቀረጻል ። ይኸውም ፡ ፈጣን ፡ የመ ልእክት ፡ አምላክ ፡ መሆኑን ፡ ለማመልከት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የወይራ ፡ በትር ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ከዚህም ፡ በተረፈ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ እየሆነ ፡ ሐውልት ፡ ተሠርቶለት ፡ ይታያል ።

## ፮ኛ ፡ ኤስቲያ ፡ ቬስታ ።

ኤስቲያ ፡ የትዳር ፡ የንብረት ፡ አምላክ ፡ ትባላለች ። ርሷም ፡ ድንግል ፡ ናት ።

## ፯ኛ ፡ አርቴሚድ ፡ ( ድያና ) ።

አርቴሚድ ፡ (እንደ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አነጋገር ፡ አርጤምስ) ፡ የአደንና ፡ የበረሃ ፡ የጨረቃም ፡ አምላክ ፡ ናት ። በሕፃንነቷ ፡ አባቷ ፡ ዜውስ ፡ ታቅፏት ፡ ባለ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ድንግልናንና ፡ የተራራን ፡ የበረሃን ፡ ግዛት ፡ ስምና ፡ አስፈቅዳ ፡ በዚሁ ፡ በድንግልና ፡ ስትኖር ፡ ክብርናዋን ፡ በኃይል ፡ ሊወስድ ፡ የፈተነውን ፡ ትልቁን ፡ የበረሃ ፡ አዳኝ ፡ አርዮን ፡ ( የዳዊት ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ አይደለም ) ፡ በክሬታ ፡ ላይ ፡ መዠመሪያ ፡ በቀስት ፡ ወግታ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በጊንጥ ፡ አስ ነክሳ ፡ ገደለችው ፡ ይባላል ። የአርጤምስም ፡ ሥራና ፡ ሐውልት ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ይገለጻል ። አብዛኛው ፡ ግን ፡ ባንዲት ፡ በምታምር ፡ ቆንጆ ፡ ሆኖ ፡ በእጅዋ ፡ ተመርውር ፡ የማይስተውን ፡ ቀስቷን ፤ እንደ ያዘች ፡ ውሻ ፡ ወይም ፡ ኂየል ፡ አስከትላ ፡ ይታያል ። እንደ ፡ ወንድሟ ፡ እንደ ፡ አጵሎን ፤ ግብሯንና ፡ ስሟን ፡ እየለዋወጡ ፡ በልዩ ፤ ብአር መን ፡ በታውሪድ ፡ (ክሪሚያ) ፡ ያመልኳታል ። በግሪክም ፡ አገር ፡ በተለይ ፡ በስፓርታና ፡ በላቆን ፡ በኤውብያ ፤ በኤፌሶን ፡ ቤተ ፡ መቅ ደስም ፡ ሐውልትም ፡ ተሠርቶላት ፡ መሥዋዕትም ፡ ስለትም ፡ እየቀ



ረበላት ፡ ትከበራለች ። ኤፌሶን ፡ ባላት ፡ ቤተ ፡ መቅደሷ ፡ ምክንያት ፡ ስሟ ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ (የሐዋርያት ፡ ሥራ) ፤ ተጠቅሷል ።

ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕርገት ፡ በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከጢሞቴዎስና ፡ ከሲላስ ፡ ጋራ ፡ በግሪክ ፡ ከተሞች ፡ በአ ቴንና ፡ በቆሮንቶስ ፤ በተሰሎንቄ ፡ እየዞረ ፡ ሲያስተምር ፡ እንደዚ ሁም ፡ ከኤፌሶን ፡ ከተማ ፡ ደርሶ ፡ የነዚህን ፡ አማልክት ፡ ከንቱነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብንና ፡ የልጁን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መድ ኃኒትነት ፡ እያስተማረ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ሲያሳምን ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ በኤፌሶን ፡ ከተማ ፡ መቅደስ ፡ ተሠርቶላት ፡ የምትመለከው ፡ ዋናዋ ፡ አርጤምስ ፡ ነበረችና ፡ የርሷ ፡ አምልኮና ፡ የመቅደሱም ፡ ሥራ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ጥቅማቸው ፡ በመነካቱ ፡ ባንድ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ክሌብ ፡ ያመልኳት ፡ ስለነበረ ፡ እውነተኛው ፡ ቅና ትም ፡ ተጨምሮ ፡ የአርጤምስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ካህናቱም ፡ አናጢ ዎቹም ፡ ሕዝቡን ፡ አሳድመው ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ላይ ፡ አስነሱ በት ። ሕዝቡም ፡ ለአርጤምስ ፡ አምልኮ ፡ ቀናዒ ፡ በመሆኑ ፡ በከተ ማው ፡ እየዞረ ፡ «ታላቅ ፡ ናት ፡ አርጤምስ ፡ የኤፌሶኒቱ» ፡ እያለ ፡ ጮኸ ፡ ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ ሥፍራ ፡ ለስብከት ፡ ሲመጣ ፡ ሊደበድቡት ፡ አስበው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወዳጆቹ ፡ ወደ ፡ ጨዋ ታው ፡ ሥፍራ ፡ እንዳይሔድ ፡ አስጠነቀቁት (፩) ።

## ፰ኛ ፤ አሬስ ፡ ( ማርስ ) ።

አሬስ ፡ የዜውስና ፡ የኤራ ፡ ልጅ ፤ የመሬትና ፡ የጦርነት ፡ አም ላክ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ አምልኮው ፡ ምንም ፡ ያኸል ፡ አልተስፋፋም ። በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ የማ ርስ ፡ ስም ፡ በጣሙን ፡ የገነነ ፡ ነው ። የመዠመሪያዎቹ ፡ የሮም ፡ ነገሥታት ፡ የነሮሞሉም ፡ አባት ፡ ያደርጉታል ።

## ፱ኛ ፡ አቴና ፡ ወይም ፡ ፓላድ ፡ (ሚኔርቫ) ።

አቴና ፡ መዠመሪያ ፡ እናቷ ፡ ሜቲስ ፡ አርግዛት ፡ ሳለ ፤ የናቷ ፡ የመ ዠመሪያ ፡ ባል ፡ ዜውስ ፡ እርጉዟን ፡ ዋጣት ። ምክንያቱም ፡ ክርሷ ፡

---

(፩) የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍጥር ፡ ፳፫—፵ ፡ ተመልከት ።

የሚወለደው ፣ ልጅ ፣ ከዙፋንህ ፣ ያወርድኻል ፣ የሚሉ ፣ ንግርት ፣ ነበርና ፣ ይኸንኑ ፣ ለማስወገድ ፣ ነው ። ዳሩ ፣ ግን ፣ እርጉዟን ፣ (የአቴናን ፣ እናት) ፣ ከዋጠ ፣ ቀን ፣ ዠምሮ ፣ ኃይለኛ ፣ በሆነ ፣ የራስ ፣ ምታት ፣ ይሠቃይ ፣ ዠመር ። ከሥቃዩም ፣ ለመዳን ፣ ኤፌስቶን ፣ (ቡልካንን ፣ ጠራና ፣ በኤፌስቶ ፣ እጅ ፣ ማኸል ፣ ራሱን ፣ ተፈለጠ ። ያን ፣ ጊዜ ፣ ከራሱ ፣ ውስጥ ፣ የተረገዘችዋ ፣ አቴና ፣ ጋሻና ፣ ጦሯን ፣ እንደ ፣ ያዘች ፣ ብቅ ፣ አለች ፣ (ተወለደች) ። ከዚያ ፣ ወዲህ ፣ አቴና ፣ የጦርነት ፤ የዠግንነት ፤ የድል ፣ አምላክ ፤ የአቴና ፣ ከተማ ፣ መሥራችና ፣ ጠባቂ ፣ ስትባል ፣ ኖራ ፤ በመጨረሻ ፣ ደግሞ ፣ የዕውቀትና ፣ የጥበብ ፣ አምላክ ፣ ሆናለች ።

ግሪኮችና ፣ ላቲኖች ፣ ሄርኩል ፣ ገደለው ፣ የሚሉት ፣ እኛ ፣ ኢትዮጵያውያንና ፣ የክርስቲያን ፣ አገር ፣ ቅዱስ ፣ ጊዮርጊስ ፣ ወይም ፣ ቅዱስ ፣ ሚካኤል ፣ ገደለው ፣ የምንለው ፣ ደራጎን ፣ ለርሷ ፣ የተቀደሰ ፣ አውሬ ፣ ነው ። እርሱም ፣ በሊብያ ፣ ውስጥ ፣ ዜውስና ፣ ሚስቱ ፣ ኄራ ፣ የተጋቡበት ፣ ከመሬት ፣ የፈለቀውን ፣ የወርቅ ፣ (ወርቅማ) ፣ ፍሬ (ቲማቲም ?) ፣ ታዞ ፣ ይጠብቃል ። ደራጎን ፣ ሥዕሉ ፣ እንደሚያስረዳው ፣ ከአፉ ፣ ወገን ፣ ውሻ ፣ የሚመስል ፣ ግራና ፣ ቀኝ ፣ ትልልቅ ፣ የሌት ፣ ወፍ ፣ ክንፍ ፣ ያለው ፣ ትልቅ ፣ ዘንዶ ፣ ነው ። በትንፋሹ ፣ አየርን ፣ ይመርዛል ፤ በአፉ ፣ የእሳት ፣ ነበልባል ፣ ይተፋል ፣ ይባላል ።

## ፲ኛ ፣ ዴሜትራ ፣ (ቼሬሬ) ።

ዴሜትራ ፣ የክሮኖና ፣ የሬአ ፣ ልጅ ፣ የዜውስ ፣ እኅት ፣ የእርሻ ፣ የፍራፍሬ ፣ በጠቅላላው ፣ የአዝርዕት ፣ አምላክ ፣ ነች ። የውድማ ፣ የእሸት ፣ የእንጐቶ ፣ የምርት ፣ የአዝመራ ፣ አምላክነትም ፣ ለርሷ ፣ ይሰጣል ።

አዴስ ፣ (ፕሉቶን) ፣ የሚባለው ፣ ጥቁርና ፣ አስቀያሚ ፣ የሆነው ፣ የገሃነም ፣ አምላክ ፣ ከዚሁ ፣ ከመልኩ ፣ መጥፎነት ፣ የተነሣ ፣ የምታገባው ፣ ሴት ፣ አጥቶ ፣ሲኖር ፣ የዴሜትራ ፣ ልጅ ፣ ፔርሴፎን ፣ ከጓደኞቿ ፣ ጋራ ፣ አበባ ፣ ስትለቅም ፣ ጠልፎ ፣ ይዟት ፣ ወደ ፣ አገሩ ፣ ወደ ፣ ገሃነም ፣ ሔደ ። ዴሜትራ ፣ የልጅቷን ፣ ፍጻሜ ፣ ተጨንቃ ፣ ስትፈልግ ፣ «ሶሌ» ፣ ፀሐይ ፣ እውነቱን ፣ ገለጠችላት ፣ (አበራችላት) ።



ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ዴሜትራ ፣ በዚሁ ፣ ተናዳ ፣ ከአማልክቱ ፣ ተለይታ ፣ ወጣችና ፣ መሬት ፣ እህል ፣ እንዳታበቅል ፣ አዘዘች ። በኋላ ፣ ግን ፣ በዜውስ ፣ አስገዳጅነት ፣ ልጅቷ ፣ ተመለሰችላትና ፣ እርሷም ፣ መሬት ፣ እህል ፣ እንድትሰጥ ፣ አደረገች ። የዴሜትራም ፣ ሐውልት ፣ ሲሠራ ፣ በራሷ ፣ ላይ ፣ የእሸት ፣ አክሊል ፣ በእጅዋም ፣ የእሸት ፣ ጭብጥ ፣ እንደ ፣ ያዘች ፣ ነው ።

## ፲፩ኛ ፣ ዲዮኒሶ ፣ (ባኮ) ።

ዲዮኒሶ ፣ የዜውስና ፣ የሴሜል ፣ ልጅ ፣ የመጠጥና ፣ የወይን ፣ የደስታ ፣ አምላክ ፣ ነው ።

## ፲፪ኛ ፤ ፖሴይዶኔ ፣ (ኔቱኖ) ።

ፖሴይዶኔ ፣ የዜውስ ፣ ወንድም ፣ የአንፊትሪት ፣ ባል ፣ የባሕር ፣ የቀለያት ፣ የወንዛወንዝ ፣ (የውሃ) ፣ አምላክ ፣ ነው ። በግዛቱ ፣ በባሕር ፣ ላይ ፣ የሚሔድበት ፣ ሠረገላ ፤ የሚቀመጥበት ፣ የሚያንጸባርቅ ፣ አዳራሽ ፣ አለው ። በፈለገ ፣ ጊዜ ፣ ማዕበልን ፣ ሞገድን ፣ የመሬት ፣ መነቃነቅን ፣ ሊቀሰቅስ ፣ ይችላል ። እርሱም ፣ ከሌላው ፣ አገር ፣ ይበልጥ ፣ በቆሮንቶስ ፣ ይከበር ፣ ነበር ።

## ፲፫ኛ ፣ አዴስ ፣ (ፕሉቶን) ።

የቀሩት ፣ አማልክት ፣ ግዛት ፣ ሲካፈሉ ፣ ሞትና ፣ ሲኦል ፣ (ገሃነም) ለአዴስ ፣ በዕጣ ፣ ስለ ፣ ደረሱት ፣ የገሃነምና ፣ የሞት ፣ አምላክ ፣ ይባላል ። ምውታን ፣ እንዳይወጡ ፣ ሕያዋን ፣ እንዳይገቡ ፣ የሚጠብቅ ፣ በአንገቱ ፣ የእባብ ፣ ጥምጥም ፣ ማተብና ፣ የሦስት ፣ ውሻ ፣ ጭንቅላት ፣ ያለው ፣ እንስሳ ፣ አለው ። ስለ ፣ መልኩ ፣ ሁናቴ ፣ በዴሜትራ ፣ ክፍል ፣ አስረድተናል ። ሐውልቱ ፣ ሲሠራ ፣ በራሱ ፣ ላይ የዞጲ ፣ (ጥቁር ፣ ዕንጨት) ፣ እንደ ፣ አክሊል ፣ ያደርጋል ፤ በእጁ ፣ ብዙ ፣ የበር ፣ ቁልፍ ፣ ይይዛል ። የሚቀመጥበትም ፣ ጥቁር ፣ ሠረገላ ፣ እሳት ፣ በሚተፉ ፣ አራት ፣ ጥቁሮች ፣ ፈረሶች ፣ ይሳባል ።

### ፲፬ኛ ፤ ቴሚስ ፡ (ጁስቲሲያስ) ።

የፍርድና ፡ የሕሊና ፡ የቅንነትና ፡ የሥርዓት ፡ አምላክ ፡ ነች ፡ ሥዕሏም ፡ በቀኝ ፡ እጅዋ ፡ ሚዛን ፡ እንደ ፡ ያዘች ፡ ይሠራል ።

### ፲፭ኛ ፡ አጵሎን ፡ (አፖሎ) ።

አጵሎን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በግሪክ ፡ አገርና ፡ በጥንታዊ ፡ አምልኮ ፡ የታወቀ ፡ ቢሆን ፡ ዘሩ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ አማልክት ፡ ግሪክ ፡ መሆኑ ፡ አልተረጋገጠም ። ገሚሱ ፡ ከሰሜን ፡ ገሚሱ ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ገሚሱ ፡ ያገር ፡ (የግሪክ) ፡ ተወላጅ ፡ ነው ፡ ይለዋል ። ግሪኮችና ፡ ትሮያን ፡ በእሌኒ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተጽፎ ፡ እንደሚገኘው ፡ ባብተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ ለምሥራቆቹ ፡ ረዳ ፡ ስለሚባል ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ ይበረክታሉ ። አምልኮውም ፡ እንደ ፡ እኅቱ ፡ እንደ ፡ አርጤምስ ፡ ከግሪክ ፡ አገር ፡ ውጭም ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ገሚሱ ፡ የትንቢትና ፡ የዕውቀት ፡ አምላክ ፡ ገሚሱ ፡ የእርሻና ፡ የመንጋ ፡ ጠባቂ ፡ መንጋን ፡ የሚተናኰለውን ፡ እንደ ፡ ተኩላ ፡ የመሰለውን ፡ አውሬ ፡ አጥፊ ፡ ያደርገዋል ። ገሚሱ ፡ የሙዚቃ ፡ የዘፈን ፡ የመርከበኞችና ፡ በመርከብ ፡ እየሔዱ ፡ ለሚነግዱ ፡ ነጋዴዎች ፡ ጠባቂ ፡ ያደርገዋል ። ገሚሱ ፡ ሁሉንም ፡ ደርቦ ፡ ያመልከዋል ። የአጵሎን ፡ ቀስት ፡ እንደ ፡ እኅቱ ፡ እንደ ፡ አርጤምስ ፡ ከቅርብም ፡ ከሩቅም ፡ ቢወረወር ፡ የማይስት ፡ ነው ፡ ይባላል ።

በአገራችን ፡ በመሥዋዕት ፡ እያመካኘ ፡ ሰው ፡ እየበላ ፡ ያስቸግር ፡ የነበረውን ፡ አጋቦስ ፡ የሚባለውን ፡ ዘንዶ ፡ ገብገቦ ፡ የሚባለው ፡ የሐማሴን ፡ በው ፡ ገድሎ ፡ ነገሠ ፡ እንደምንለው ፡ የጂአን ፡ (የመሬት) ፡ ልጅ ፡ ፒቶኔ ፡ የሚባለውንና ፡ በዴልፎ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ እየበላ ፡ ያስገብር ፡ የነበረውን ፡ ትልቅ ፡ ዘንዶ ፡ አጵሎን ፡ ገድሎ ፡ የርሱን ፡ አምላክነት ፡ ወሰዷል ። በዚሁ ፡ በዴልፎም ፡ (አርካዲያ) ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለአጵሎን ፡ ተሠርቶ ፡ ይሰገድለት ፡ ነበር ። ለመቅደሱም ፡ ብዙ ፡ የሴት ፡ ደናግል ፡ ካህናት ፡ ነበሩት ። ሲቢሌ ፡ (ሳቤላ ፡) ከሚባሉት ፡ ከ፲፪ቱ ፡ የሴቶች ፡ ካህናቶች ፡ (መናንያት ፡ ደናግል) ፡ ውስጥ ፡ የአንዷቱ ፡ ስም ፡ ኤሪትሬያ ፡ ይባላል ።



### ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

### የሆሜር ፡ ድርሰቶች–የአማልክቱ ፡ የዘር ፡ ግንዶች ።

እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባጭሩ ፡ ሆኖ ፡ ስማቸውና ፡ ሥራቸው ፡ ካ፩ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ድረስ ፡ (ከዜውስ ፡ እስከ ፡ አጵሎን) ፡ ከተዘረዘሩት ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ስማቸውንና ፡ ታሪካቸውን ፡ ያልዘረዘርነው ፡ ገሚሶቹ ፡ የነዚህ ፡ አማልክት ፡ ባላንጣዎች ፡ ገሚሶቹ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችና ፡ ጭፍሮች ፤ ገሚሶቹ ፡ አማልክት ፡ ገሚሶቹ ፡ ግማሽ ፡ አማልክቶች ፤ (መትሕተ ፡ አማልክት ፡ መልዕልተ ፡ ሰብእ ፡ የሆኑ) ፡ ገሚሶቹ ፡ የአውራጃ ፤ ገሚሶቹ ፡ የመንደር ፤ ገሚሶቹ ፡ የቀላያት ፡ የወንዝ ፡ የምንጭ ፤ ገሚሶቹ ፡ የደን ፡ የቍጥቋጦ ፡ የተራራ ፡ የሸለቆ ፡ የሆኑ ፤ ገሚሶቹ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ምስፍናና ፡ ባላባትነት ፡ ወይም ፡ ቀንደኛነት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ አማልክትነት ፡ የሌላቸው ። ገሚሶቹ ፡ አገራቸውን ፡ ከጠላት ፡ በመከላከል ፤ ወይም ፡ የጠላት ፡ አገር ፡ በመውረር ፡ ዠግንነት ፡ የሠሩ ፡ ሞልተዋል ። እነዚህም ፡ እንደነዑቅያኖስ ፤ እንደነአትላንት ፡ እንደነሔርኮል ፤ እንደነኤውሮፓ ፤ እንደነሲሬና ፡ እንደነዲዮስቆሮስ ፡ እንደነአጋሜኖን ፤ እንደነዑሊስ ፡ እንደነአኪላ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። የነዚህ ፡ ቀርቶ ፡ አላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ እንኳን ፡ ስማቸውን ፤ ዋና ፡ ግብራቸውንና ፡ ታሪካቸውን ፡ ከመጥቀስ ፡ በቀር ፡ የአማልክቱን ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ ከነቅርንጫፉ ፡ «ቴዮጎንያ» ፡ በሚባል ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪካቸውን ፡ ጨምሮ ፡ እንደ ፡ ጸፈው ፡ እንደ ፡ ኢሲዎዶስ ፡ ወይም ፡ በትሮያ ፡ ጦርነት ፡ በሌላም ፡ ምክንያት ፡ ኢሊያድና ፡ ኦዲሴያ ፡ (ኢሊያስና ፡ ኦዲሴውስ) ፡ በሚባሉት ፡ በቅኔ ፡ መጻሕፍቶቹ ፡ (አሠረ ፡ ንጉሥ) ፡ ሆሜር ፡ የሚባለው ፡ የታወቀው ፡ ጸሐፊ ፡ ውጊያቸውንም ፤ ክርክራቸውንም ፡ ፍቅራቸውንም ፡ ኀሳራቸውንም ፡ ክብራቸውንም ፡ እንደ ፡ ተረከው ፡ አልዘረዘርንም ። እንባቢም ፡ በዚህ ፡ ባጭሩ ፡ አገላለጣችን ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ጕዳዩን ፡ በሙሉ ፡ ተመራምሮ ፡ ለመጥገብ ፡ ሲፈልግ ፡ ወደነዚሁ ፡ ጽሑፎች ፡ ቢሔድ ፡ የሚበቃውን ፡ ያህል ፡ ይረዳል ። ይኸውም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ ታሪኩ ፡ «ከተረትና» ፡ «ከይባላል» ፡ የሚዘል ፡ ነገር ፡ የለውም ። ጫፍና ፡ ምልክት ፡ እን

ኳን ፡ ባይጠፋ ፡ የነገሩ ፡ ውጥንና ፡ ፍጻሜ ፡ በመካከሉ ፡ ተደረገ ፡ የሚባለው ፡ ሁሉ ፡ በአገራችን ፡ አንዳንድ ፡ ቀሳውስት ፡ ላንዳንድ ፡ ደስ ፡ ለተሰኙባቸው ፡ ሊያከብሯቸውና ፡ ዝናቸውን ፡ ለማስደነቅ ፡ ለፈለጋቸው ፡ ጻድቃን ፡ እንደሚጽፉላቸው ፡ ድርሳንና ፡ ገድል ፡ እንዲሁ ፡ ሆሜርም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ኢሲዮዶስ ፡ የነዚህን ፡ አማልክትና ፡ ዠግኖች ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ በሌለበት ፡ ገድልና ፡ ድርሳን ፡ የጋብቻና ፡ የፍቅራቸውን ፡ የግድያቸውንና ፡ የሥራቸውን ፡ ታሪክ ፡ እያገነነ ፡ ጽፎላቸዋል ። የነገሩን ፡ አኳኋን ፡ ለመገመት ፡ ያህል ፡ ዛሬም ፡ ባገራችን ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘውን ፡ የዜና ፡ እስክንድርን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ይረዳል ፡ ደንበኛ ፡ ታሪኩን ፡ ከዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ቀጥሎ ፡ የምናገኘው ፡ እስክንድር ፡ እሞራንና ፡ ፈረስን ፡ አጋብቶ ፡ ከነሱ ፡ በተወለደው ፡ ክንፋም ፡ ፈረስ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ወጥቶ ፡ ዕፀ ፡ ገነትን ፡ ይዞ ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተመለሰ ። የሚለው ፡ የአተራረኩ ፡ መንገድ ፡ ከነዚህ ፡ አማልክት ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ ይመሳሰላል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ሆሜር ፡ የአማልክቱን ፡ ተረታዊ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ታሪክ ፡ ቢጽፍ ፡ ለታሪካቸው ፡ ቀርቶ ፡ እንዲያውም ፡ ለመኖራቸው ፡ እንኳ ፡ የመካከለኛውም ፡ የአዲሱም ፡ የዛሬውም ፡ ዘመን ፡ ሊቃውንቶችና ፡ መርማሪዎች ፡ ማስረጃ ፡ ስላጡበት ፡ ስማቸውንና ፡ ታሪካቸውን ፡ በዲክሲዮኔርና ፡ በእንሲክሎፔዲ ፡ ( መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ወዜና ፡ መዛግብት) ፡ ሲጽፉ ፡ ተረትነቱን ፡ ከማጽደቅ ፡ በቀር ፡ ዜውስንም ፡ ቢሆን ፡ ሌሎቹንም ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ተወለዱ ፤ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ ሞቱ ፡ ብለው ፡ አረጋግጠው ፡ አይጽፉላቸውም ። ይኸውም ፡ የተረታዊ ፡ አምልኮና ፡ የአማልክቱ ፡ ታሪክ ፡ ከእውነተኛው ፡ አምላክ ፤ ዠግኖቹም ፡ በዓለም ፡ ከነበሩት ፡ ከእውነተኞቹ ፡ ዠግኖች ፡ የማይደባለቁበትንና ፡ የማይሳከሩበትን ፡ የጽሑፍ ፡ መደብ ፡ ለማድረግ ፡ ለነዚህ ፡ አማልክት ፡ ላምልኳቸውም ፡ ለሥራቸውም ፤ «ሚቶሎዢ» ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ሰይመው ፡ ገድበውታል ። ሚቶ ፡ በግሪክ ፡ ተረት ፡ ሎዢ ፡ ወይም ፡ ሎጎስ ፡ ንግግር ፡ ነውና ፤ ሁለቱ ፡ ቃላት ፡ ተያይዘው ፡ ተረታዊ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ታሪክ ፡ ማለትን ፡ ያሳያሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የዓለም ፡ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እያወቁ ፡



አልፈው ፡ ነገሩን ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ከመመልከትና ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ በየቋንቋቸው ፡ ተርጕመው ፡ ከማጥናት ፡ አልቦዘኑም ፡ ምክንያቱም ፡ የነዚህን ፡ አማልክትና ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ታሪካቸውን ፡ ያነበብነውን ፡ የጥንት ፡ የገናና ፡ መንግሥቶች ፡ የግብፅን ፡ የባቢሎንን ፡ የአሶርን ፡ የፋርስን ፡ የጥንት ፡ ሥልጣኔያቸውን ፡ የታሪካና ፡ የመርከብ ፡ ሥራቸውን ፤ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ የልብሳቸውንና ፡ የጦር ፡ መላቸውን ፤ የሥርዓተ ፡ ጋብቻቸውንና ፡ ፍቺያቸውን ፡ ለመመርመር ፡ በጣም ፡ ስለሚያግዛቸው ፡ ይኸን ፡ ጽሑፍ ፡ በጣም ፡ አክብረው ፡ ይዘውታል ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ እውስጡ ፡ ባለው ፡ ፍልስፍና ፡ ከግሪኮች ፡ በኋላ ፡ የተነሡት ፡ ሮማውያን ፡ (ላቲኖች) ፡ የላቲኖቹም ፡ ቅርንጫፍ ፡ የሆኑት ፡ የምዕራብ ፡ ኤውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ለሥልጣኔያቸው ፡ መሠረት ፡ አድርገውታል ። እንግሎ ፡ ሳክሶን ፡ የሚባሉት ፡ የጀርመንና ፡ የእንግሊዝ ፡ ዐዋቂዎችም ፡ ሳይቀሩ ፡ ተጠቅመውበታል ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ አማልክት ፡ ከወዴት ፡ መጡ ፡ ወዴትስ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለሚጠይቅ ፤ አሁንም ፡ ተረትነቱን ፡ ሳንዘነጋ ፤ መጡ ፡ የሚባልበትን ፡ የአሳብ ፡ አቀጣጫና ፡ በሕይወታቸው ፡ ዘመን ፡ ተዋጉ ፡ የተባሉትን ፡ አንዱን ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ የኢሲዮዶስንና ፡ የሆሜርን ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንጠቅሳለን ።

መጀመሪያ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ « ካኦስ » ፡ ነበረ ። ካኦስ ፡ ማለት ፡ ባዶ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይኸን ፡ ዓለም ፡ «እምኀበ ፡ አልቦ ፡ ኀበ ፡ ቦ ፤ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ አመጣው» ፡ እንደምንለው ፡ «አልቦ» ፡ ብቻ ፡ ከምንለው ፡ ጋራ ፡ ይመሳሰላል ። ወይም ፡ ካኦስ ፡ ማለት ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ባሕርና ፡ መሬቱ ፡ (የብስና ፡ ቀላዩ) ፡ ሰማይና ፡ ጠረፉ ፡ ሌትና ፡ ቀኑ ፡ በየመልኩ ፡ ሳይለይ ፡ ተደባልቆና ፡ ተዘባርቆ ፡ የነበረውን ፡ ሁኔታ ፡ ካኦስ ፡ ይሉታል ። መሬትን ፡ ሰማይን ፡ ባሕርን ፡ ዕንቅልፍን ፤ ትዝታን ፡ ሞትን ፤ ሕይወትን ፤ ዕውቀትን ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሁሉ ፡ የሰው ፡ ወይም ፡ የአምላክነት ፡ አምሳል ፡ እየሰጡ ፡ እንደሚጠሯ

ቸው ፡ «ካኦስንም» ፡ ሥፍራውና ፡ ሁኔታው ፡ በዝርዝር ፡ ሳይገለጥ፡ እንደ ፡ መዠመሪያ ፡ መስፍን ፡ ይቈጥሩታል ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ «ጀአ» ፡ መሬት ፡ «ኤሮስ» ፡ ፍቅር ፡ ፍጥረትን፡ አገናኝና ፡ አዋሐጅ ፡ ተሰዩ ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ከዚያው ፡ ከካኦስ ፡ «ኤሬቦ» ፤ ጨለማና ፡ «ኒክስ» ፡ ሌሊት ፡ ተወለዱና ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ «ኤቴርን» ፡ ጽርሐ ፡ አርያምንና ፡ «ሔሜራን» ፡ ቀንን ፡ ወለዱ ። መሬት ፡ ደግሞ ፡ ያለባት ፡ «ኡራኖስን ፡ ከዋክብት ፡ ያሉበትን ፡ ሰማይና ፡ «ጰንጦስን» ፡ ባሕርን ፡ ተራራንም ፡ ወለደች ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከጀአና ፡ ከኡራኖስ ፡ « ከመሬትና ፡ ከሰማይ » ፡ ሦስቱ ፡ (ቺኮሎፒ) ፡ የሚባሉት ፡ መልካቸው ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ የተገለጸው ፤ ተወለዱ ፤ እነዚህም ፡ የአማልክት ፡ መልክ ፡ ይዘው ፡ ሳለ ፡ ዐይናቸው ፡ ብቻ ፡ ፩ ፡ ሆኖ ፡ ያውም ፡ እግንባራቸው ፡ ማኸል ፡ በመሆኑ ፡ ይለያሉ ። ከነሱም ፡ ጋራ ፡ ሦስቱ ፡ «ኤካቶንኪሬ» ፡ የሚባሉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ መቶ ፡ እጅ ፡ ሃምሳ ፡ ጭንቅላት ፡ ያላቸው ፡ የአውሬም ፡ የሰውም ፡ የጉድ ፡ መልክ ፡ ያላቸውና ፡ ግዙፍ፡ የሆኑ ፡ ተወለዱ ። እነሱም ፡ በቡልካኖስ ፡ የብረት ፡ ማቅለጫ ፡ ቤት ፡ የሚሠሩና ፡ ዓለምን ፡ ለመደባለቅ ፡ የሚያስፈሩ ፡ (ገፋዕተ ፡ ደመናት ፡ ወረዐይት ) ፡ ተብለዋል ። ከነዚህ ፡ በቀር ፡ ከጀአና ፡ ከኡራኖስ ፡ (ከመሬትና ፡ ከሰማይ) ፡ ፮ቱ ፡ ወንዶችና ፡ ስድስቱ ፡ ሴቶች ፡ የሆኑ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ ቲታኒ ፡ ተወለዱ ። የወንዶቹ፡ ስም ፡ ዑቅያኖስ ፤ ቆዮስ ፤ ክሪዎ ፤ ኢፔሪዮኔ ፤ ጀአፒቶ ፤ ክሮኖ ፤ የሴቶቹ ፡ ቼአ ፤ ሬአ ፤ ቴሚስ ፤ ምኔሞዚን ፤ ቴቲስ ፡ ፌቤ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ከሰማይ ፡ ከባልዮውና ፡ ከመሬት ፡ ከሚስትዮዋ ፡ የተወለዱት ፡ ወንድምና ፡ እኅቶች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጋብተው ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የሆኑና ፡ የሰውም ፡ የአማልክትም ፡ አባት ፡ የተባሉት ፡ ናቸው ። ዜውስና ፡ ሚስቱ ፡ ወይም ፡ እኅቱ ፡ ኤራ ፡ የክሮኖና ፡ የሬአ ፡ ልጆች ፡ የጀአና ፡ የኡራኖስ ፡ (የመሬትና ፡ የሰማይ) ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

እንግዴህ ፡ ኡራኖስ ፡ ገሚሶቹን ፡ በመፍራት ፡ ገሚሶቹን ፡ በመጥላት ፡ በልጆቹ ፡ ደስ ፡ አልተሰኘም ። በፍጥረታቸው ፡ የጠላቸውን፡ እነችክሎፒን ፡ እነኤካቶንኪሬን ፡ ዕመቀ ፡ ዕመቃት ፡ አውርዶ ፡ አሠ



ራቸው ፤ የቀሩትንም ፡ ለመግደል ፡ ይፈልጋቸው ፡ ዠመር ። እናታቸው ፡ ጀአ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ልጆቿ ፡ በባሏ ፡ ተናዳ ፡ እርሱን ፡ ለመግደያ ፡ አንድ ፡ የብረት ፡ ማጭድ ፡ ሠራችና ፡ አባታችሁን ፡ ግደሉ ፡ ብላ ፡ ብትሰጣቸው ፡ የቀሩት ፡ ፈሩ ። ክሮና ፡ ግን ፡ ተቀበለና ፡ ኡራኖስ ፡ በሚስቱ ፡ አጠገብ ፡ ተኝቶ ፡ ዕንቅልፍ ፡ ወስዶት ፡ ሳለ ፡ በማጭድ ፡ አባለ ፡ ዘሩን ፡ ቈርጦ ፡ ቢጥለው ፡ ከደሙ ፡ ውስጥ ፡ ኤሪኒና ፡ ጂጋንት ፡ ኅልያዶችና ፡ ተቢቃዮች ፡ የሚባሉ ፡ ረዥሞም ፡ ጦር ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ከኒንፌ ፡ (የባሕር ፡ የወንዝ ፡ የጫካ ፡ ትናንሽ ፡ አማልክት ) ፡ ጋራ ፡ ተወለዱ ። እንደዚሁም ፡ እባሕር ፡ ከፈሰሰው ፡ አባለ ፡ ዘር ፡ አፍሮዲት ፡ ተወለደች ፡ ይላሉ ።

ክሮኖ ፡ አባቱን ፡ ኡራኖስን ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ከሚስቱ ፡ ከሬአ ፡ ጋራ ፡ በታላቅ ፡ ጌትነት ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ይገዛ ፡ ዠመር ። ዳሩ ፡ ግን፡ ከቤትህ ፡ ከሚወለዱት ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ከሥልጣንህ ፡ ያወርድሃል፡ የሚሉ ፡ ንግር ፡ ነበርና ፤ ሚስቱ ፡ የምትወልዳቸውን ፡ ሁሉ ፡ ዕለቱን ፡ እየተቀበለ ፡ ይውጣቸው ፡ ዠመር ። ከእናታቸው ፡ ማሕፀን ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ሆድ ፡ የገቡ ፡ (የተዋጡ) ፡ ኤስቴያ፡ ዴሜትራ ፡ አዴስ ፤ ፖሲዶን ፡ ናቸው ። እናትየዋ ፡ ሬአ ፡ በልጆቿ ፡ መዋጥ ፡ ስትጸጸት ፡ የመጨረሻ ፡ ልጅዋ ፡ ዜውስን ፡ እርግዛ ፡ ከወለደች ፡ በኋላ ፡ በቶሎ ፡ ደበቀችና ፡ በርሱ ፡ ምትክ ፡ ድንጋይ ፡ በጨርቅ፡ ጠቅልላ ፡ ለባሏ ፡ ሰጠችው ። እርሱም ፡ ድንጋዩን ፡ ልጄ ፡ መስሎት፡ ዋጠው ።

ዜውስም ፡ ተወልዶ ፡ በተደበቀበት ፡ በክሬት ፡ ደሴት ፡ በጥበብ ፡ አደገ ፤ ኃይልም ፡ ተሰማው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባባቱ ፡ በክሮና ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ አነሣበትና ፡ ውጊያ ፡ ገጠመው ። አባቱንም ፡ አሸንፈና ፡ እነዚያ ፡ አስቀድመው ፡ የተዋጡትን ፡ ወንድሞቹንና ፡ እኅቶቹን ፡ አስተፋው ። ቢሆንም ፡ ሌሎቹ ፡ ወንድሞቹ ፡ ላባቱ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ዜውስን ፡ ክፉኛ ፡ ተቋቁመውት ፡ ነበርና ፡ ጦርነቱ ፡ በቴሳልያ ፡ ውስጥ ፡ በኦሊምፒያ ፡ አጠገብ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ አቆየ ። ነገር ፡ ግን ፡ አባቱ፡ ክሮኖ፡ አሥሮ ፡ ዕመቀ ፡ ዕመቃት ፡ የሰደዳቸውን ፡ ቺክሎፒንና ፡ ኤካቶንኪሬን ፡ ፈትቶ ፡ ወደሱ ፡ ወገን ፡ አደረጋቸው ። እነርሱም ፡ ለጦር ፡ መሣሪያ ፡ መብረቅ ፡ ሠርተው ፡ ሰጡትና፡ በዚያ፡

አባቱንና ፡ የአባቱን ፡ ወገኖች ፡ አሸነፈ ። ገሚሶቹንም ፡ ገደላቸው ። የቀሩትንም ፡ ከንሕይወታቸው ፡ እያሠረ ፡ ወደ ፡ እንጦርጦስ ፡ (ታር ታር ፡ ) ሰደዳቸው ። ጠባቂም ፡ እነዚህን ፡ ሃምሳ ፡ ራስ ፡ መቶ ፡ እጅ ፡ ያላቸውን ፡ ግዙፍ ፡ ፍጥረቶች ፡ አደረገባቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዜውስ ፡ ባባቱ ፡ ሥፍራና ፡ ሥልጣን ፡ ተተክቶ ፡ መቀመጫው ፡ ሁለመናው ፡ ያንጸባርቃል ፡ በተባለው ፡ በኦሊም ፒያ ፡ ተራራ ፡ አድቲን ፡ አላይ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ ልጆቹም ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በደስታ ፡ ይገዛ ፡ ዠመር ፡ ይሉታል ። እንዲሁም ፡ በርሱ ፡ ዘመን ፡ ከተፈጸመው ፡ ተረታዊ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ባንድ ፡ ፍሬና ፡ ባንዲት ፡ ቈንጆ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ውን ፡ የትሮያን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ጠቅሰን ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ታሪክ ፡ እንሻገራለን ።

ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

አከራካሪዋ ፡ ፍሬና ፡ የትሮያ ፡ ጦርነት ።

ከሴት ፡ አማልክት ፡ ውስጥ ፡ ኤሪስ ፡ (ዲስኮርድ) ፡ የምትባል ፡ ነበ ረች ። ርሷም ፡ በአማልክቱ ፡ መካከል ፡ ሁከትና ፡ የሚለያይ ፡ ነገር ፡ እየፈጠረች ፡ ስምምነት ፡ የምትነሣ ፡ በመሆንዋ ፡ በዜውስ ፡ ትእዛዝ ፡ ከኦሊምፒያ ፡ ተራራ ፡ (መካነ ፡ አማልክት) ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተጣለ ችና ፡ ከማኅበራቸው ፡ ተለየች ። በምድር ፡ ሳለች ፡ ቲቲና ፡ ፒሊዎ ፡ (የዠግናው ፡ የአኪል ፡ አባትና ፡ እናት) ፡ በተጋቡበት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሠርጉ ፡ ሳትጠራ ፡ በመቅረቷ ፡ በጣም ፡ ተበሳጭታ ፡ ነበርና ፡ የሚ ሉን ፡ ፍሬ ፡ (ይኸንንም ፡ ፍሬ ፡ የኢዲሲዮን ፡ ላበር ፡ ኢንሲክሎፔዲ ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ወደ ፡ ሳቱበት ፡ የበለስ ፡ ፍሬ ፡ ያስጠጋዋል) ፡ በእ ጅዋ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ሠርጉ ፡ አዳራሽ ፡ ገብታ ፡ ለሠርጉ ፡ በተቀመጡት ፡ አማልክት ፡ መካከል ፡ ጣለችው ። በፍሬውም ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ ነበረበት ፤ « ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ቈንጆ ፡ ለሆን ችው » ፡ ይኸውም ፡ ከመካከላችሁ ፡ ቈንጆ ፡ የሆንችው ፡ ይኸን ፡ ፍሬ ፡ ወስዳ ፡ ትብላ ፡ ማለቷ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዜውስ ፡ ባለቤት ፡ ኤራ ፤ ከባሕር ፡ አረፋ ፡ ተወለደች ፡ የምትባለዋ ፡ አፍሮዲት ፤ ከዜውስ ፡



ጭንቅላት ፡ የተወለደችው ፡ አቴና ፡ ሦስቱም ፡ ተነሡና ፡ እኔ ፡ ቈንጆ ፡ ነኝና ፡ ይህችን ፡ ፍሬ ፡ ለመውሰድ ፡ ይገባኛል ፡ ሲሉ ፡ እርስ ፡ በርሳ ቸው ፡ ተፎካከሩ ። ስለዚህ ፡ ዋናው ፡ አምላክ ፡ ዜውስ ፡ ከመካከላ ችሁ ፡ በቊንጅና ፡ የምትበልጠውንና ፡ ይህችን ፡ ፍሬ ፡ ለመውሰድ ፡ የሚገባትን ፡ አሌክሳንድር ፡ (ፓሪድ ፡ ወይም ፡ ፓሪስ ) ፤ ይመስክር ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ።

ስዚህም ፡ አሌክሳንድር ፡ አስበት ፡ ድረስ ፡ ወስዶ ፡ እንደ ፡ ጭብጥ ፡ ዳኛ ፡ የሚያመላክር ፡ ሒርሜስ ፡ (ሜርኩር) ፡ የሚባለው ፡ የመልእክትና ፡ የጉዞ ፡ አምላክ ፡ ታዘዘ ። ሒርሜስ ፡ ሦስቱን ፡ ቈንጆ ችት ፡ ይዞ ፡ አሌክሳንድር ፡ ከብት ፡ ይጠብቅበት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ትሮያ ፡ (ትሩዋ) ፡ ከተማ ፡ ሔደ ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ለአንደኛዋ ፡ ሲመሰክር ፡ ሁለቱ ፡ እንዳይጠሉት ፡ ስለ ፡ ፈራና ፡ ፍርዱ ፡ ከባድ ፡ ስለ ፡ ሆነበት ፡ አልመሰክርም ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ኤራ ፡ ለኔ ፡ ብትመሰክርልኝ ፡ የመላ ፡ እስያን ፡ ግዛት ፡ «ሀብተ ፡ ምኵናን» ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብላ ፡ አባበለችው ። አቴና ፡ ደግሞ ፡ ለኔ ፡ ብትመሰክር ፡ በጦርነት ፡ ግንባር ፡ ሁሉ ፡ ድልን ፡ እንድታገኝ ፡ « ኃይለ ፡ መዊዕ » ፡ አበጥሃለሁ ፡ አለችው ፡ አፍሮዲስ ፡ ግን ፡ በሰው ዩው ፡ ባሕሪ ፡ ያለውን ፡ ተመራምራ ፡ ለኔ ፡ ብትመሰክር ፡ « ፍቅረ ፡ አንስት » ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ወይም ፡ ከዓለም ፡ ቈንጆ ፡ የሆንችው ፡ እን ድትወድህ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብላ ፡ ለመነችው ። እርሱም ፡ በነገሩ ፡ በብዙ ፡ ከተጨነቀበት ፡ በኋላ ፡ ከግዛትና ፡ ከድል ፡ አድራጊነት ፡ ይልቅ ፡ የመጨረሻው ፡ ፍቅር ፡ ደስ ፡ ስለ ፡ አለው ፡ በቊንጅና ፡ አፍ ሮዲት ፡ ትበልጣለችና ፡ ለርሷ ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ፍሬውን ፡ ሰጣት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ሴቶች ፡ አማልክት ፡ በአሌክሳንድር ፡ ተናደው ፡ ቂማቸውንም ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ በቊጣ ፡ ወደ ፡ ሥፍራቸው ፡ ተመለሱ ።

አሌክሳንድር ፡ የትሮያ ፡ ንጉሥ ፡ የፕሪአም ፡ ልጅ ፡ ነበረና ፡ በልጅነቱ ፡ ወራት ፡ ከብት ፡ ሲጠብቅ ፡ ኖሮ ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ባባቱ ፡ እልጋ ፡ ተቀመጠ ። እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ተስፋ ፡ በአፍ ሮዲት ፡ አባባይነት ፡ (አማካይነት) ፡ የስፓርታን ፡ ንጉሥ ፡ የሜኔላ ኦን ፡ ሚስት ፡ (ኤሌኒን) ፡ ወደደ ። ከባሏም ፡ ቤት ፡ ቀምቶ ፡ ጠልፎ ፡

እምጥቶ ፡ በሚስትነት ፡ ለማግባት ፡ አሰበ ፡ ስለዚህ ፡ የስፓርታ ፡ ንጉሥ ፡ ሜኔላአ ፡ መንገድ ፡ በሔደበት ፡ ሰዓት ፡ ከትሮያ ፡ ወደ ፡ ስፓርታ ፡ ስሌላ ፡ ጉዳይ ፡ የመጣ ፡ አስመስሎ ፡ በኋላ ፡ ሚስቱን ፡ እሌኒን ፡ ቀምቶ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ትሮያ ፡ ይዞ ፡ ተመለሰ ። (ትሮያ ፡ የጥር አድ ፡ ከተማ ፡ ቀድሞ ፡ ቢቲንያ ፡ የነበረበት ፡ ዛሬ ፡ በቱርክ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ነው ) ።

ሜኔላኦም ፡ ከመንገድ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገበትን ፡ ዐወቀ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጎረቤቶቹ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ ነገሥታት ፡ አብረው ፡ ሔደው ፡ በትሮያ ፡ እንዲዋጉና ፡ ጥቃቱን ፡ እንዲወጡለት ፡ ለመናቸውና ፡ እሺ ፡ አሉት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የጦር ፡ ጓደኞቹንና ፡ ወንድሙን ፡ አጋሜኖን ፡ ወዳጆቹን ፡ እነአኪላን ፣ እነኡሊስን ፡ ጨምሮ ፡ ሚስቱን ፡ በጦርነት ፡ ሊያስመልስ ፡ ተዘጋጀ ። ጉዞ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ጦርነቱ ፡ እንደሚቀናቸው ፡ ሊመለመን ፡ ወይም ፡ የድልን ፡ ምልክት ፡ ለማየት ፡ ለትንቢት ፡ አምላክ ፡ ለአጵሎን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ። መሥዋዕቱም ፡ በቀረበበት ፡ ሰዓት ፡ በዚያው ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አጠገብ ፡ ከመሬት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ እባብ ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፣ በዛፉም ፡ ላይ ፡ ዘጠኝ ፡ በራሪ ፡ ወፎች ፡ የሰፈሩበትን ፡ የወፍ ፡ ቤት ፡ አግኝቶ ፡ አፈረሰና ፡ ዘጠኙንም ፡ በየተራ ፡ ዋጣቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዚህን ፡ ትርጉም ፡ እንዲፈታ ፡ ደንበኛው ፡ ትንቢት ፡ ፈቺ ፡ ካልካንት ፡ ተጠርቶ ፡ መጣና ፡ ይህ ፡ የሚሔድበት ፡ የትሮያ ፡ ጦርነት ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ማቄየቱንና ፡ በአሥረኛው ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ እንደሚቀናቸው ፡ ተረጐመላቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ዘመቻው ፡ ጉዞ ፡ ሲጀምሩ ፡ ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፣ ተነሥቶ ፡ መርከባቸውን ፡ ያውከው ፡ ጀመር ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ነቢይ ፡ የሚባለውን ፡ ያንኑ ፡ ካልካንትን ፡ ጠየቁት ። እርሱም ፡ ዋናው ፡ አዝማች ፡ አጋሜኖን ፡ ልጁን ፡ ኤፍጂኒን ፡ ለአርጤምስ ፡ (ዲያና) ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ካልሠዋት ፡ ነፋሱና ፡ ማዕበሉ ፡ አይቆምም ፡ ሲል ፡ ተናገረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጋሜኖን ፡ ልጁን ፡ ይዞ ፡ ለመሠዋት ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ሳለ ፡ አርጤምስ ፡ የኤፍጂኒን ፡ ውበት ፡ አይታ ፡ ራራችላት ። ስለዚህ ፡ በርሷ ፡ ፈንታ ፡ የአጋዘን ፡ (የኃየል) ፡ መሥዋዕት ፡ ተቀበ



ለችና ፡ እርሷን ፡ የቤተ ፡ መቅደሷ ፡ አገልጋይ ፡ እንድትሆን ፡ በሕይወቷ ፡ ለቀቀቻት ። ነፋሱና ፡ ማዕበሉም ፡ ወዲያው ፡ ፀጥ ፡ አለ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ የሚሆኑ ፡ ከየነገዱ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ግሪኮች ፡ በሺ ፡ ፩፻፹፮ ፡ መርከብ ፡ ተጉዘው ፡ በዋናው ፡ አዝማች ፡ በአጋሜኖን ፡ እየተመሩ ፡ ወደ ፡ ትሮያ ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ። የትሮያ ፡ ሰዎችም ፡ ግሪኮችን ፡ ሊመመለስ ፡ ጎረቤቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበርና ፡ ከተገናኙ ፡ ጀምሮ ፡ የፊት ፡ ለፊትም ፡ የደፈጣም ፡ ጦርነት ፡ ሲያደርጉ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ቈዩ ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ኤራና ፡ አቴና ፡ አክራካሪዋን ፡ ፍሬ ፡ ሳያገኙ ፡ በመቅረታቸው ፡ ለግሪኮቹ ፣ አፍሮዲት ፡ ግን ፡ ለትሮያኖቹ ፡ ይረዱ ፡ ነበር ። ግሪኮቹም ፡ ወደ ፡ ትሮያ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ለትሮያኖቹ ፡ ርዳታ ፡ አማዞኒ ፡ የሚባሉ ፡ አርበኝነት ፡ ያላቸው ፡ የሴት ፡ ቈነገዥነት ፡ በዋናዋ ፡ የቈንጆ ንግሥት ፡ በጴንቴሴሊያ ፡ መሪነት ፣ ኢትዮጵያውያን ፡ ደግሞ ፡ በኤኦስ ፡ ልጅ ፡ በሜምኖን ፡ መሪነት ፡ መጥተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ባለፈው ፡ እንደተጻፈው ፡ ኤኦስ ፡ (ትርጓሜው ፡ ጎሕ ፡ ) የ «ፌቦ» ፡ (ትርጓሜው ፡ ፀሐይ ፡ ) እኅት ፡ ናት ። ከእኅቷ ፡ ከፀሐይ ፡ እየቀደመች ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ ብርሃንን ፡ ለሰው ፡ የምትሰጥ ፡ ነች ።

ወደ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ እንመለስ ፣ ትሮያኖቹ ፡ ብዙ ፡ ርዳታ ፡ ቢያገኙም ፡ እውጭ ፡ ሆነው ፡ ለመከላከል ፡ ስላልቻሉ ፡ እከተማቸው ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ይከላከሉ ፡ ነበር ። የከተማቸውም ፡ ዙሪያ ፡ ደኅና ፡ ሆኖ ፡ የተገነባ ፡ ነበርና ፡ ግሪኮቹ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገብተው ፡ ሰዎቹን ፡ አሸንፈው ፡ እሌኒን ፡ ለመውሰድ ፡ ለጊዜው ፡ አልሆነላቸውም ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ተጨንቀው ፡ ሲያወጡ ፡ ሲያወርዱ ፡ በመጨረሻ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ መላ ፡ ተገኘ ። መላውንም ፡ ያገኘው ፡ ኡሊስ ፡ ነው ፣ የሠራው ፡ ግን ፡ ኤፒዎስ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

አንድ ፡ ትልቅ ፡ የፈረስ ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ እንጨት ፡ ሠርተው ፡ በዕንጨቱ ፡ ፈረስ ፡ ውስዋ ፡ ኃይለኞቹ ፡ ተመርጠው ፡ ከነመሣሪያቸው ፡ ገብተው ፡ እነሱ ፡ ከውስጥ ፡ ሲከፍቱት ፡ እንደሚችሉ ፡ ተቈለፈባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይኸንኑ ፡ የዕንጨት ፡ ፈረስ ፡ እከተማው ፡ ቅጥር ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡና ፡ የቀሩት ፡ ግሪኮች ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሸሹ ። በማግሥቱ ፡ ከከተማው ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ከትሮያኖች ፡ ጋራ ፡ የነበረ ፡ ሲኖን ፡ የሚባለው ፡ የግሪክ ፡ ተወላጅ ፡ ይህ ፡ የፈረስ ፡

ሥዕል ፡ ትሮያን፡ ለማሸነፊያ፡ ግሪኮቹ፡ የያዙት ፡ አምላካቸው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለሹማምንቱ ፡ ነገረ ። ሲኖን ፡ ይኸን ፡ መናገሩ ፡ ለአገሩ ፡ ሰዎች ፡ አድልቶ ፡ ትሮያኖችን ፡ ለማሳሳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የግሪኮች ፡ አምላክ ፡ አለመሆኑን ፡ ያውቃል ። ሹማምንቱም ፡ ካዩ ፡ በኋላ ፡ በውነትም ፡ ግሪኮቹ ፡ ጥለውት ፡ ተሸንፈው ፡ የሸሹ ፡ መሰላቸውና ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ አስገቡና ፡ አስቀመጡት ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ መሽቶ ፡ ሰው ፡ በተኛበት ፡ ጊዜ ፡ በፈረሱ ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የግሪክ ፡ ዝግኖች ፡ ወጥተው ፡ ብዙዎችን ፡ የትሮያ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ። በኋላም ፡ ትልቅ ፡ እልቂት ፡ ከሚሆን ፡ በቈንጆዪቱ ፡ በእሌኒ ፡ ምክንያት ፡ ይኸን ፡ ጦርነት ፡ የቀሰቀሱት ፡ እስክንድርና ፡ ባልዋው ፡ ሜኔላኦ ፡ ሁለቱ ፡ ብቻ ፡ ይዋጉ ፡ (ዱዬል ፡ ያድርጉ ፡) አሸናፊውም ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ይሁንና ፡ እሌኒን ፡ ይውሰድ ፡ ተባለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱ ፡ ተጋጥመው ፡ ይደባደቡ ፡ ዠመር ። በመጨረሻም ፡ እስክንድር ፡ ተሸንፎ ፡ ሊወድቅ ፡ ሲል ፡ ፍሬው ፡ ላንቺ ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ የመሰከረላት ፡ አፍሮዲት ፡ (የፍቅር ፡ አምላክ) ፡ ደርሳ ፡ አዳነችው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ፊሎቲት ፡ የሚባል ፡ መርዝ ፡ ባለው ፡ በኤርኮል ፡ ቀስት ፡ ወግቶ ፡ እስክንድርን ፡ ገደለውና ፡ ግሪኮች ፡ አሸነፉ ። እስክንድርም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እሌኒ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድርን ፡ ወንድም ፡ ኤውፎቦንን ፡ አግብታ ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ አትወደውም ፡ ነበርና ፡ ለጠላቶቹ ፡ ለሜኔላኦና ፡ ለኡሊስ ፡ አሳልፋ ፡ ሰጠችው ። እሱንም ፡ ጠላቶቹ ፡ አሠቃይተው ፡ ገደሉት ። ሜኔላኦም ፡ ሚስቱን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ስፓርታ ፡ ከሞት ፡ ከተረፉት ፡ ጓደኞቹና ፡ ሕዝቦቹ ፡ ጋራ ፡ ጕዞ ፡ ዠመረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በተሸናፊዎቹ ፡ በትሮያ ፡ ላይ ፡ በሠሩት ፡ ግፍ ፡ ምክንያት ፡ አማልክቱ ፡ እነዜውስ ፡ በግሪኮቹ ፡ ላይ ፡ ተቆጥተው፡ ስለነበረ፡ መርከቦቻቸውን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እያንገላቱ ፡ እንዲያውኩ ፡ ነፋስንና ፡ ሞገድን ፡ አዘውባቸው ፡ ነበርና ፡ አሸናፊዎቹ ፡ ምንም ፡ መቅኖ ፡ አላገኙም ። ሜኔላኦ ፡ ወደ፡ አገሩ፡ ወደ ፡ ስፓርታ ፡ ሳይገባ ፡ ከክሬት ፡ ወደ ፡ ችፕሮ ፡ (ቆጵሮስ) ፡ ከፊንቂ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሲቅበዘበዝ ፡ ኖሮ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ፡ ገሚሶቹ ፡ ደግሞ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ከተቅበዘበዘ ፡ በኋላ ፡ በ፰ተኛው ፡ ዓመት ፡ አገሩ ፡ ገብቶ ፡ ሞተ ፡ ይላሉ ። ዋናው ፡ አዛማች ፡ አጋሜኖንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ አርጎ ፡ እንደ ፡



ተመለሰ ፡ የገዛ ፡ ሚስቱ ፡ ክሊቴኔስቲራ ፡ ከወዳጅዋ ፡ ከኤጅስቶ ፡ ጋር ፡ ሆና ፡ ገደለችው ።

ግሪኮች ፡ ከራሳቸው ፡ በመነጨው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አምልኮና ፡ ታሪክ ፡ የነርሱንም ፡ እየሰጡ ፡ ከምሥራቅም ፡ ከሕንዶችና ፡ ከቻይናዎች ፤ ከባቢሎንና ፡ ከፋርሶች ፤ ከፊንቂዎችም ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እየተቀበሉ ፡ ደባልቀው ፡ እነሱም ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ያንዱን ፡ ጣዖት ፡ አምላክነት ፡ ለሌላው ፡ እየሰጡና ፡ እየለዋወጡ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አምልኮ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስና ፡ እስከ ፡ ሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ኖሩ ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ባ፭ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ቢታጎራ ፡ የሚባል ፡ ሊቅ ፡ ተነሥቶ ፡ ከሰው ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ የምትተላለፍ ፡ የሕያዊት ፡ ነፍስና ፡ የእውነተኛውንም ፡ አምላክ ፡ መኖር ፡ በጽሕፈት ፡ አድርጎ ፡ አዲስ ፡ ዓይነት ፡ ትምህርት ፡ አስተምሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ተቀባይ ፡ አላገኘም ። ግሪኮች ፡ በዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡ እነዚህን ፡ አማልክት ፡ ከልብ ፡ ያመልኳቸው ፡ ነበር። እነዚህንም ፡ የሚጠራጠር ፡ መናፍቅ ፡ ተብሎ ፡ ይወቀሳል ፡ የሚክድም ፡ ቢኖር ፡ ይገደላል ። ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆነው ፡ ፈላስፋቸው ፡ ስቅራጥስ ፡ (ሶክራት) ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ አለ ፡ በማለቱ ፡ አኒቶስና ፡ ሚሌቶስ ፡ በሚባሉ ፡ ተከሶ ፡ ተፈረደበትና ፡ መርዝ ፡ ጠጥቶ ፡ ሞተ ።

የዚህ ፡ ጣዖት ፡ አምልኮ ፡ በክርስትና ፡ ይለወጥ ፡ ዘንድ ፡ ባለፈው ፡ በግብፃችና ፡ በባቢሎን ፡ እንደተረክነው ፡ የክርስቶስን ፡ መምጣትና ፡ የሐዋርያትን ፡ የነቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ መነሣት ፡ የነቈስጠንጢኖስንና ፡ የነቴዎዶስዮስን ፡ ንግሥ ፡ ጠበቀ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

### የመቄዶንያ ፡ መንግሥትና ፡ ንጉሡ ፡ ፊልጶስ ፡— የትልቁ ፡ እስክንድር ፡ አነሣሥ ።

ከስፓርታና ፡ ከአቴና ፡ በሰሜን ፡ ከቴሳልያም ፡ በላይ ፡ በትራችያና ፡ በኢሊሪክ ፡ መካከል ፡ የመቄዶንያ ፡ ሕዝብ ፡ ነበር ። የነሱም ፡ ኑሮ ፡ በብርዳማው ፡ አገር ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ሰዎቹ ፡ ከተፈጥሮአቸው ፡ በጣም ፡ ኃይለኞችና ፡ ጠንካሮች ፡ ስለነ

በሩ ፣ በየጊዜው ፣ የተነሣባቸውን ፣ ወረራ ፣ እየተዋጉ ፣ መልሰው ፣ በነፃ ፣ ይኖሩ ፣ ነበር ። ስጥቂት ፣ ዘመን ፣ የያዟቸውን ፣ ፋርሶችንም ፣ በጥባቱና ፣ ላይ ፣ አሸንፈው ፣ አስወጥተዋል ። የመቄዶንያ ፣ ሕዝብ ፣ ከታችኛው ፣ የግሪክ ፣ ( አቴኖችና ፣ ስፓርታዎች ) ፣ ሕዝብ ፣ በቋንቋና ፣ በልማድ ፣ የተለዩ ፣ ሕዝቦች ፣ ናቸው ።

እነዚህም ፣ ሕዝቦች ፣ በ፫፻፷፰ ፣ ዓመት ፣ ከክርስትና ፣ በፊት ፣ ፊልጶስን ፣ በደንብ ፣ አነገሡ ። ፊልጶስ ፣ በምርኮ ፣ ስም ፣ ቴብ ፣ ከሚባለው ፣ የግሪክ ፣ ከተማ ፣ (ከአቴን ፣ በላይ ፣ የሚገኝ ፣ በላዕላይ ፣ ግብፅ ፣ ከተማ ፣ ስም ፣ የሚጠራ ) ፣ በነበረ ፣ ጊዜ ፣ የግሪኮቹን ፣ አስተዳደርና ፣ የወታደር ፣ አቅድ ፣ ደኅና ፣ አድርጎ ፣ ተምሮ ፣ ነበር ። በግል ፣ አገሩ ፣ በመቄዶንያ ፣ ከነገሠ ፣ በኋላ ፣ መላውን ፣ የግሪክን ፣ ሕዝብ ፣ ባንድነት ፣ ጠቅልሎ ፣ የመግዛት ፣ ምኞት ፣ አደረበት ። ለዚሁም ፣ ወታደር ፣ እየመለመለ ፣ ለጦርነት ፣ መዘጋጀቱ ፣ በግሪክ ፣ አገር ፣ በአቴናና ፣ በአቲካ ፣ ገና ፣ አስቀድሞ ፣ ተሰምቶ ፣ ነበርና ፣ ሕዝቡ ፣ በሐሳብ ፣ ሁለት ፣ ተከፈለ ። አንደኛው ፣ ክፍል ፣ ዴሞስቴን ፣ የሚባለውን ፣ ንግግር ፣ አዋቂ ፣ መሪ ፣ ይዞ ፣ የመቄዶንያን ፣ ሕዝብና ፣ ፊልጶስን ፣ እንደ ፣ ባዕድ ፣ በመቍጠሩ ፣ ፊልጶስ ፣ የአቴናን ፣ ከተማና ፣ ዙሪያ ፣ እንዳያስገብር ፣ መከላከል ፤ ሁለተኛው ፣ የመቄዶንያ ፣ ሕዝብ ፣ በልማድና ፣ በቋንቋ ፣ ቢለያዩም ፣ ያው ፣ የግሪክ ፣ ሕዝብ ፣ ስለሆነ ፣ ፊልጶስን ፣ እንደ ፣ ንጉሥ ፣ እንቀበለው ፣ እንጂ ፣ አንዋጋው ፣ ብሎ ፣ ኤስኪን ፣ የሚባለውን ፣ መሪ ፣ ይዞ ፣ የተነሣ ፣ ነበር ። በዚህም ፣ ላይ ፣ ፊልጶስ ፣ የወርቅ ፣ ገንዘብ ፣ በስሙና ፣ በመልኩ ፣ አስቀርጾ ፣ ይኸንኑ ፣ ለዋና ፣ ለዋና ፣ ለየቀንደኛው ፣ ሰው ፣ ውስጥ ፣ ውስጡን ፣ እየላከ ፣ እንዲቀበሉት ፣ በገንዘብም ፣ በስብከትም ፣ ያባብል ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ሁሉ ፣ ሲገብርለት ፣ ዴሞስቴን ፣ ብቻ ፣ እምቢ ፣ አለ ። ኤስኪንንም ፣ በገንዘብ ፣ አገሩን ፣ የሸጠ ፣ ከዳተኛ ፣ እያለ ፣ በዲስኩር ፣ ይዘልፈው ፣ ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ይኸው ፣ ዴሞስቴን ፣ ወገኖቹን ፣ ይዞ ፣ ፊልጶስን ፣ ስመከላከል ፣ ሲሔድ ፣ ከልቄዶን ፣ ( ኬልቄዶንያ ) ፣ ላይ ፣ ተሸንፎ ፣ ተመለሰ ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ፊልጶስ ፣ ከነሠራዊቱ ፣ እየገፋ ፣ የአቴንን ፣ ከተማ ፣ ለመያዝ ፣ ይሰናዳ ፣ ጀመር ። የቴብና ፣ የአቴና ፣ ሰዎችም ፣



ደኅና ፣ አድርገው ፣ ለመከላከል ፣ ሁለተኛ ፣ ተዘጋጁ ፤ መሪያቸውም ፣ ዴሞስቴን ፣ የፊልጶስን ፣ ወራሪነት ፣ ለማቆም ፣ የተቻለውን ፣ ሁሉ ፣ ዝግጅት ፣ አደረገ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ የፊልጶስ ፣ ጦር ፣ እነዚህን ፣ ቄሮንያ ፣ ላይ ፣ ድል ፣ አድርጎ ፣ አቴንን ፣ ስለያዘ ፣ በመላው ፣ በግሪክ ፣ አገር ፣ ላይ ፣ ሥልጣኑን ፣ አሳመነ ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ፊልጶስ ፣ ትልቁን ፣ የፋርስ ፣ መንግሥት ፣ ማስገበር ፣ በአሳቡ ፣ መጣበት ፤ ስለዚህ ፣ ከክርስትና ፣ በፊት ፣ በ፫፻፴፯ ፣ ዓመት ፣ በቆሮንቶስ ፣ ከተማ ፣ ላይ ፣ መላው ፣ የግሪክ ፣ ሕዝብ ፣ እንዲሰበሰብ ፣ በአዋጅ ፣ አዘዘ ። ሕዝቡም ፣ ተሰብስቦ ፣ የወረራውን ፣ ዝግጅት ፣ በሚያደርግበት ፣ መካከል ፣ ፊልጶስን ፣ ፓውሳኒያስ ፣ የሚባል ፣ ከጨዋ ፣ ዘር ፣ ወገን ፣ የሆነ ፣ የመቄዶንያ ፣ ሰው ፣ በጩቤ ፣ ወግቶ ፣ ገደለው ። እንዲገድለውም ፣ ያስደረገችው ፣ ኦሊምፒያስ ፣ የምትባለው ፣ ሚስቱ ፣ (የእስክንድር ፣ እናት ) ፣ ናት ። ምክንያቱም ፣ በጠባይዋ ፣ ከልክ ፣ ያለፈ ፣ ተጠራጣሪና ፣ ፈሪ ፣ ስለነበረች ፣ ኢትሆነኝም ፣ ብሎ ፣ ይፈታኛል ፣ ብላ ፣ ሰግታ ፣ ነው ፣ ይላሉ ፣ አንዳንዶቹም ፣ እስክንድር ፣ አስገደለው ፣ ይላሉ ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ ፊልጶስ ፣ ሲሞት ፣ በዙፋኑ ፣ ልጁ ፣ እስክንድር ፣ ተተካ ።

እስክንድር ፣ ከፊልጶስና ፣ ከኦሊምፒያስ ፣ በ፫፻፶፮ ፣ ዓመት ፣ በመቄዶንያ ፣ ከተማ ፣ በፔላ ፣ ተወለደ ፤ እስኪያድግም ፣ ድረስ ፣ መምህሩ ፣ በሊቅነቱ ፣ በፍልስፍናው ፣ ዓለም ፣ ያወቀው ፣ አሪስጦት ፣ (አርስጣጣሊስ ) ፣ ነበር ። አሪስቶትም ፣ ለእስክንድር ፣ አስተማሪው ፣ ብቻ ፣ አልነበረም ፤ ከነገሠ ፣ በኋላም ፣ ወዳጁና ፣ የፖለቲካና ፣ ያስተዳደር ፣ አማካሪው ፣ ነበር ።

እስክንድር ፣ መልኩ ፣ ቀና ፣ ሆኖ ፣ በጠባዩ ፣ ቸርነትም ፣ ጥብቅነትም ፣ ጭካኔም ፣ ድፍረትም ፣ የተደባለቀበት ፣ ኃይለኛ ፣ ወጣት ፣ ነበር ። ይኸን ፣ ጠባይ ፣ ከተፈጥሮው ፣ የያዘ ፣ እስክንድር ፣ በአሪስቶት ፣ ትምህርት ፣ ከተገራ ፣ ወዲህ ፣ የሚያየው ፣ ሁሉ ፣ ይኸ ፣ ወጣት ፣ ወደፊት ፣ ትልቅ ፣ ታሪካዊ ፣ ሥራ ፣ የሚሠራ ፣ ነው ፣ እያለ ፣ አሳቡን ፣ አሣረፈበት ። የድፍረቱም ፣ ምልክት ፣ የታየው ፣ ገና ፣ በልጅነቱ ፣ ነው ።

አባቱ ፣ ፊልጶስ ፣ በሕይወቱ ፣ ባለ ፣ አንድ ፣ ማንም ፣ ሊወጣበት ፣ ያልቻለ ፣ ያልተገራ ፣ ፈረስ ፣ ነበር ። ጉበዛዝት ፣ የተባሉት ፣ ሁሉ ፣

ንጉሡና ፡ ሕዝቡ ፡ ባሉበት ፡ አደባባይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለመውጣትና ፡ ለመጋለብ ፡ ሞክረው ፡ ሲያቅታቸው ፡ እስክንድር ፡ ቆሞ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ከቆመበት ፡ ስየት ፡ ብሎ ፡ ሔደና ፡ ፈረሱን ፡ ተቀብሎ ፡ መዠመሪያ ፡ በእጁ ፡ ዳሰሰው ፤ ከዚያም ፡ ፈረሱ ፡ የገዛ ፡ ጥላውን ፡ እያየ ፡ እንዳይደነብር ፡ ሙሉ ፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ አዞረና ፡ ንጉሡም ፤ ሕዝቡም ፡ ሲመለከቱት ፡ ዘሎ ፡ ወጣበት ፤ ፈረሱም ፡ እጥባቂ ፡ ነበርና ፡ ይዞት ፡ ሽምጥ ፡ ሮጠ ። ይኸ ፡ ፈረስ ፡ በዚህ ፡ ሩጫውና ፡ ደንባሪነቱ ፡ አንድ ፡ ዘንድ ፡ ጥሎ ፡ ይበባብረዋል ፤ እየተባለ ፡ በትልቅ ፡ ሥጋት ፡ ሲጠበቅ ፡ እስክንድር ፡ ፈረሱን ፡ በግልቢያ ፡ አድክሞ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እየጋለበ ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ሔደ ። አባቱም ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ጉብዝናውን ፡ አድንቆ ፡ « ላንተ ፡ መቄዶንያ ፡ አይበቃህምና ፡ (ይጠብሃልና) ፡ ሌላ ፡ ግዛት ፡ ፈልግ » ፡ አለው ፡ ይባላል ፤ አባቱም ፡ ሲሞት ፡ ዕድሜው ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ስለነበረው ፡ በዚሁ ፡ ዕድሜው ፡ በአባቱ ፡ ዙፋን ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቴብ ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፡ ሸፍተውበት ፡ ነበርና ፡ እነሱን ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ አሳምኖ ፡ ከአረጋገጠ ፡ ወዲህ ፡ አባቱ ፡ አስቦ ፡ ሳይፈጽመው ፡ የቀረውን ፡ የትልቁን ፡ ንጉሥ ፡ የዳርዮስን ፡ አገር ፡ ፋርስን ፡ ለመውረር ፡ ይዘጋጅ ፡ ዠመር ። እንደምንም ፡ ፭ሺ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፴ሺ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ከተሰበሰበለት ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፴፫ ፡ ዓመት ፡ በግሪክ ፡ በኢሶስ ፡ ቍጥሩ ፡ የበረከተውን ፡ ዳርዮስ ፡ ልኮት ፡ የነበረውን ፡ የፋርስን ፡ ጦር ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ መለሰ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፈንቄ ፡ ሔዶ ፡ የጢሮስን ፡ ከተማ ፡ ተዋግቶ ፡ ያዘ ። ከዚያም ፡ አልፎ ፡ ከገዥዎቹ ፡ ከፋርሶች ፡ ተዋግቶ ፡ ግብፅን ፡ ወረረ ። የግብፅም ፡ ሕዝብ ፡ ፋርሶችን ፡ ጠልቶ ፡ ነበርና ፡ እስክንድርን ፡ እንደ ፡ ነፃ ፡ አውጭ ፡ ንጉሥ ፡ ቈጠሩት ። ለቀድሞ ፡ ፈርዖኖች ፡ ይሰጡት ፡ የነበረውን ፡ የአሞን ፡ ልጅነትን ፡ ስያሜ ፡ ለርሱ ፡ ሰጡት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስክንድር ፡ አገሩን ፡ ሰላም ፡ አድርጎ ፡ ሲጨርስ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በስሙ ፡ የምትጠራዋን ፡ ከተማ ፡ እስክንድርያን ፡ መሠረተ ። ከዚያ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የፋርስን ፡ አገር ፡ ወረራ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ፊቱን ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ፡ ፋርስ ፡ መለሰ ።



## ምዕራፍ ፡ ፳፮ ፡

ትልቁ ፡ እስክንድርና ፡ ዳርዮስ ፡ በአርቤላ ፡ (አሶር) ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነትና ፡ የዳርዮስ ፡ እግሚት ፡ የፋርሶችና ፡ የመቄዶንያውያን ፡ መቀናናት ፡ የወዳጁ ፡ የክሊቶስ ፡ አሟሟት ፡ የእስክንድር ፡ ምኞትና ፡ ፍጻሜው ።

ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ የግብፅን ፡ ግዛት ፡ ከፋርሶች ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ወስዶ ፡ የራሱ ፡ ግዛት ፡ አድርጎ ፡ አደላድሎ ፡ በያዘበትና ፡ ሕዝቡም ፡ በደስታ ፡ ተቀብሎት ፡ ባገሩ ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አድርጎ ፡ ከካህናቱ ፡ «የአሞን ፡ ልጅ» ፡ የሚባለውን ፡ ስያሜ ፡ በተቀበለበት ፡ ጊዜ ፡ ከግብፅ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ በተለይ ፡ በመርዌ ፡ ከተማ ፡ ሕንደኬ ፡ (ከንዳኬ) የምትባል ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ንግሥት ፡ የራሷን ፡ መንግሥት ፡ ትመራ ፡ ነበር ። እርሷም ፡ የእስክንድርን ፡ አሸናፊነት ፡ የፋርሶችን ፡ ውድቀት ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ መላክተኛ ፡ ልካበታለች ። የዚህንም ፡ ሁኔታ ፡ የእስክንድርን ፡ የወረራ ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ከፈጸምን ፡ በኋላ ፡ በሚቀጥለው ፡ እስክንጽፈው ፡ ድረስ ፡ አሁን ፡ እስክንድር ፡ ዳግመኛ ፡ ዳርዮስን ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ ፋርስ ፡ ጠረፍ ፡ ያደረገውን ፡ ጉዞ ፡ እንመልከት ።

እስክንድር ፡ ከግብፅ ፡ ተመልሶ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ከፋርሱ ፡ ንጉሥ ፡ ከዳርዮስ ፡ ፫ኛ ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ ነገሥታት ፡ (ሡላባ ፡ ሳትራፕ) ፡ ጌታ ፡ የሆነው ፡ ዳርዮስ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ የተጠራቀመ ፡ ቍጥሩ ፡ እስከ ፡ ፩ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚደርስ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ተጠባበቀው ። ቢሆንም ፡ አስቀድሞ ፡ በተደረጉት ፡ ጦርነቶች ፡ የወጣቱ ፡ የእስክንድር ፡ ደፋርነት ፤ የጦር ፡ መላ ፡ አዋቂነቱና ፡ አመራሩ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ጀግንነት ፡ ተገምቶና ፡ አስፈርቶ ፡ ነበርና ፡ ፩ ፡ ሚሊዮን ፡ ጦር ፡ ያስከተለው ፡ ዳርዮስ ፡ ከአርባ ፡ ሺ ፡ እግረኛ ፡ ከ፯፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ የማይበልጥ ፡ ጦር ፡ የያዘውን ፡ እስክንድርን ፡ ዕርቅ ፡ ጠየቀው ። በዕርቁም ፡ « ሴቷን ፡ ልጄን ፡ ለሚስትነት ፡ ልስጥህና ፡ ከኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አንተ ፤ ከወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡

እኔ ፡ ይገር ፡ ግዛት ፡ ተካፍለን ፡ በሰላም ፡ በየአገራችን ፡ እንቀመጥ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። መቼም ፡ እንደ ፡ እስክንድር ፡ ያለ ፡ የ፳ ፡ ዓመት » ፡ ወጣት ፡ እስካሁን ፡ ባንደኛውም ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ተሸንፎ ፡ የማያውቅ ፡ ዓስምን ፡ ጠቅሎ ፡ ለመግዛት ፡ ምኞት ፡ ያለው ፡ የክፍያን ፡ ዕርቅ ፡ መቀበል ፡ እንደማይሆንለት ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ከዳርዮስ ፡ የመጣውን ፡ መልእክት ፡ ከመኳንንቱ ፡ ጋር ፡ ሲመለከት ፡ ባጠገቡ ፡ ያለው ፡ ፓርሜኒዮን ፡ የሚባለው ፡ የጦር ፡ አለቃው ፡ «እኔ ፡ እስክንድርን ፡ ብሆን ፡ ይኸን ፡ ዕርቅ ፡ እቀበል ፡ ነበር» ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡ እስክንድርም ፡ «እኔም ፡ ፓርሜኒዮንን ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ እቀበል ፡ ነበር» ፡ ብሎ ፡ በአምላኩ ፡ በዜውስ ፡ ማለት ። የዚህን ፡ ትርጓሜ ፡ ለአንባቢ ፡ ማብራራት ፡ የሚያስፈልግ ፡ አይመስለኝም ፡ ባጭሩ ፡ የእስክንድር ፡ አሳብ ፡ እንዳንተ ፡ ፈሪ ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ ወይም ፡ አንተን ፡ ፈሪውን ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ዕርቅ ፡ እቀበል ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ደፋር ፡ እስክንድር ፡ ነኝና ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ዕርቅ ፡ አልቀበልም ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

ለፓርሜኒዮን ፡ ይኸን ፡ ከመለሰ ፡ በኋላ ፡ ለዳርዮስ ፡ ደግሞ ፡ «ባንድ ፡ ሰማይ ፡ ሁለት ፡ ፀሐዮች ፡ እሉን ፡ እንሱስ ፡ ተቀራርበው ፡ ሊያበሩ ፡ ይችላሉን ? እንደዚሁም ፡ ሁለት ፡ ነገሥታት ፡ በምድር ፡ ተስማምተው ፡ ሊገዙ ፡ አይችሉም» ፡ ብሎ ፡ የላከበትን ፡ ዕርቅ ፡ አለመቀበሉን ፡ በፀሐይና ፡ በሰማይ ፡ መስሎ ፡ ላከበት ። ስለዚህ ፡ ሁለቱም ፡ ጦራቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ጉዟቸውን ፡ ቀጥለው ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፫፻፴፩ ፡ ዓመት ፡ አርቤላ ፡ ከሚባለው ፡ ከጤግሮስ ፡ ወንዝ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሲል ፡ በአሶር ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ተጋጠሙ ። ውጊያው ፡ ተዠምሮ ፡ ወታደር ፡ ከወታደር ፡ በዘመኑ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በቀስትና ፡ በጐራዴ ፡ በሰይፍና ፡ በጦር ፡ በሚዋጋበት ፡ ጊዜ ፡ የግሪክ ፡ ጦር ፡ እንደለመደው ፡ በሩጫና ፡ በፈረስ ፡ ግልቢያ ፡ የፋርስን ፡ ጦር ፡ ጥሶ ፡ ወደ ፡ መካከል ፡ ገባ ። ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆኖ ፡ ለመምራት ፡ ዘወትር ፡ የሚደፍረው ፡ እስክንድር ፡ ራሱ ፡ አባርሮ ፡ ዳርዮስን ፡ ሊማርከው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዳርዮስ ፡ የጦርነቱን ፡ አዝማሚያ ፡ ሲመለከት ፡



ከወርቅ ፡ ሠረገላው ፡ ላይ ፡ በፍጥነት ፡ ወርዶ ፡ በፈረሱ ፡ ተጋብቶ ፡ በሽምጥ ፡ ግልቢያ ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ሸሸ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሚሊዮን ፡ የተቈጠረው ፡ የዳርዮስ ፡ ጦር ፡ ፍርስርሱ ፡ ወጥቶ ፡ ግማሹ ፡ ሸሸ ፤ የቀረውም ፡ ተማረከ ። እስክንድርም ፡ በወታደሩ ፡ እንደታጀበ ፡ ስመ ፡ ጥሩዒቱን ፡ ከተማ ፡ ባቢሎንን ፡ ያዛት ፤ ሱስ ፤ ፔርሴፖሊስ ፤ ፓሳርጋድ ፡ የሚባሉት ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ከደለበው ፡ ሀብታቸው ፡ ጋር ፡ በግሪኮቹ ፡ እጅ ፡ ወደቁ ። ከዚያ ፡ እስክንድር ፡ ዳርዮስ ፡ የሸሸበትን ፡ ዱካ ፡ እየተከታተለ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ ሲጓዝና ፡ ሊደርስበት ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ ቤሶስ ፡ የሚባል ፡ የፋርስ ፡ ተወላጅ ፡ ያንድ ፡ አውራጃ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ዳርዮስን ፡ ይዞ ፡ ገደለው ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ ለእስክንድር ፡ መጣለት ፡ ዳሞት ፤ በሳአል ፡ ገዳይ ፡ እንዳልተደሰተ ፡ እስክንድርም ፡ አልተደሰተም ። ነገሥታት ፡ ባላጋራቸውም ፡ ቢሆን ፡ አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲሞት ፡ አይፈልጉም ፡ « በኔም ፡ ቀን ፡ ይኸው ፡ ነው » የሚል ፡ መንፈስ ፡ ይመጣባቸዋል ።

ስለዚህ ፡ ቤሶስ ፡ እስክንድርን ፡ ያስደሰተ ፡ መስሎት ፡ የዳርዮስን ፡ ሬሳ ፡ ይዞ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ከአሸናፊው ፡ ያላሰበው ፡ ነገር ፡ ደረሰበት ። እስክንድር ፡ ለዳርዮስ ፡ ሬሳ ፡ ለንጉሥ ፡ የሚገባ ፡ ክብር ፡ ሰጥቶ ፡ በማዕርግ ፡ እንዲቀበር ፡ አደረገና ፡ የዳርዮስን ፡ ወንድም ፡ አስጠርቶ ፡ የወንድምህን ፡ ገዳይ ፡ በፈቀደህ ፡ ዓይነት ፡ አሠቃይተህ ፡ ግደለው ፡ ብሎ ፡ ቤሶስን ፡ አስረከበውና ፡ ተሠቃይቶ ፡ ሞተ ።

ቀጥሎ ፡ እስክንድር ፡ ከድል ፡ ወደ ፡ ድል ፡ እየተራመደ ፡ አሁንም ፡ ግዛቱን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ለማስፋፋት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አራኮዚ ፡ ወደሚባለው ፡ ዛሬ ፡ አፍጋኒስታን ፡ ወደሚባለውና ፡ ወደ ፡ ባክትሪያን ፡ (የዛሬው ፡ ቱርኬስታን) ፡ ጉዞውን ፡ ቀጠለ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በነዚህ ፡ አገሮች ፡ ያለው ፡ የፀሐይ ፡ ሐሩርና ፡ የደጋ ፡ በረዶ ፡ እየተፈራረቀ ፡ የግሪኮችንና ፡ በቅርብ ፡ ኪያስበት ፡ የተመለመለውን ፡ ጦር ፡ አዳከመበት ። ከዚያ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ መስስ ፡ ብሎ ፡ የሕንድን ፡ አገር ፡ ለመውረር ፡ ተዝቀዘቀ ። በዚያም ፡ ፖሮስ ፡ ከሚባል ፡ ካንድ ፡ የሕንዱ ፡ መስፍን ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ ማረከና ፡ ምን ፡ ላድርግልህ ፡ ወይም ፡ እንደምን ፡ አድርጌ ፡ ልያዝህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ያም ፡ «እን

ዳንድ ፡ ንጉሥ ፡ አድርገህ ፡ ያዘኝ» ብሎ ፡ መለሰለት ፡ እስክንድርም ፡
በግዛትህ ፡ ንጉሥነትህን ፡ መርቄልሃለሁ ፡ አለውና ፡ ሁለቱ ፡ ወዳጅ ፡
ሆኑ ፡ ይባላል ።

እስክንድር ፡ አሁንም ፡ ከሒንዱ ፡ ወደ ፡ ጋንዥ ፡ (ሂንዱስታን)
መዝለቅ ፡ ፈለገ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጉዞ ፡ የደከማቸው ፡ ጦር
ነት ፡ የሰለቻቸው ፡ ወታደሮቹና ፡ ሹማምንቱ ፡ እያጉረመረሙ ፡
ጨርሰው ፡ እምቢታቸውን ፡ አስታወቁ ። በዚህም ፡ እስክንድር ፡
አኩርፎ ፡ ፫ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ከሰው ፡ ሳይነጋገር ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡
ተቀመጠ ። በመጨረሻም ፡ የወታደሩን ፡ መድከምና ፡ መጐዳት ፡
ራሱ ፡ ስለተረዳው ፡ ወደፊት ፡ እንግፋ ፡ ብሎ ፡ ወታደሩን ፡ ማስገደ
ድም ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳው ፡ ቅርታውን ፡ በልቡ ፡ እን
ደተሸከመ ፡ ዳርዮስን ፡ ካሸነፈ ፡ ዠምሮ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡
በምሥራቅና ፡ በሕንድ ፡ በማያውቃቸው ፡ አገሮች ፡ ሲጓዝ ፡ ሲዋጋ ፡
ሲያሳምን ፡ ኖሮ ፡ አሁን ፡ በ፫፻፳፯ ፡ ዓመት ፡ ሳይ ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡
በፋርስ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ረኃቡንና ፡ ጥሙን ፡ የበረሃውን ፡
ሐሩር ፡ የደጋውን ፡ በረዶና ፡ ብርድ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ታግሦ ፡ በስንት ፡
ድካም ፡ ተመልሶ ፡ በ፫፻፳፬ ፡ ዓመት ፡ ሱስ ፡ (የኤላም ፡ ከተማ ፡)
ገባ ። ከዚያም ፡ ግብፃውያን ፡ የግሪክ ፡ የጽኤል ፡ የፋርስና ፡ የባቢ
ሎን ፡ የሌላም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብና ፡ ነገሥታት ፡ በተሰበሰቡ
በት ፡ የዓለም ፡ ንጉሥነቱን ፡ አከበረ ። የሕንደኬ ፡ ንግሥት ፡ መል
ክተኞችም ፡ ይኸን ፡ በዓል ፡ ተካፍለዋል ።

ዋናው ፡ የትልቁ ፡ እስክንድር ፡ አሳብና ፡ ምኞት ፡ ከፀሐይ ፡
መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሐይ ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ የሚገኘው ፡ ዓለም ፡
አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሕዝብ ፡ አሕዛብ ፡ ባንድነት ፡ ተቀይጠው ፡ እርሱ ፡
የዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ ነው ። ራሱ ፡ እንደተረዳው ፡ አሪስቲቶ
ትም ፡ እንደሚመክረው ፡ እኔ ፡ መቄዶናዊ ፡ (ግሪክ) ፡ ነኝ ፤ ሌላው ፡
ሕዝብ ፡ አይረባም ፤ የኔ ፡ አምላክ ፡ ዜውስ ፡ ከሌሎቹ ፡ አገሮች ፡
አማልክት ፡ ይበልጣል ፡ ሳይል ፡ በደረሰበት ፡ አገር ፡ ያለውን ፡
ሕዝብ ፡ አክብሮ ፡ ልማዳቸውን ፡ ማጽደቅ ፡ አማልክቶቻቸውን ፡
መሳለም ፡ ይወድ ፡ ነበር ። ኢየሩሳሌም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ (የጀሆ
ባሕ ፡ የጽኤል ፡ አምላክ) ፡ መልክተኛ ፡ ነው ። በግብፅ ፡ የአሞን ፡



ልጅ ፤ በጢሮስና ፡ በሲዶና ፡ በአሶር ፡ የሞሎክ ፡ የአስታርት ፡ ልጅ ፡
ተባለ ። ባጭሩ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በየቋንቋቸው ፡ የአማልክቶቻቸው ፡
ልጅ ፡ አደረጉት ። እርሱም ፡ ከሁሉ ፡ እየመሰለ ፡ ሁሉንም ፡ እስደ
ሰተ ፤ ከፋርስ ፡ አገር ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ ግብር ፡ እየያዙ ፡ እሱን ፡ ለመ
ሳለም ፡ የሚመጡትን ፡ የፋርስ ፡ መሳፍንትና ፡ ሕዝብ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡
ፋርስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንደዳርዮስ ፡ የፋርስን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሶ ፡ ተቀበላቸው ። የነርሱንም ፡ መሳፍንት ፡
በደስታ ፡ እየተቀበለ ፡ በሹመታቸው ፡ እያጸና ፡ ባለሟል ፡ አደረጋ
ቸው ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከአርያን ፡ (ጀርመን) ፡ ዘር ፡ በቀር ፡ የቀረው ፡
አይረባም ፡ ብሎ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከተነሣው ፡ ከሂትለር ፡ እስክን
ድር ፡ ብልጫ ፡ አለው ፡ እስክንድር ፡ ሁሉን ፡ በየወጉ ፡ በየአምል
ኮው ፡ ሲያስደስት ፡ በጠቅላላው ፡ አረመኔና ፡ ጨዋ ፡ ባዕድና ፡
ወገን ፡ ሳይባል ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡
ሆኖ ፤ የዓለም ፡ ንጉሥ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ለመሆን ፡ ምኞት ፡ እንደነ
በረው ፡ በየታሪኩ ፡ ይገኛል ።

የርሱን ፡ ታሪክ ፡ የጻፈለት ፡ ፕሉታርክ ፡ የሚባል ፡ ቅርብ ፡
ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ከሃምሳ ፡ እስከ ፡ ፩፻፳፭ ፡ ዓመት ፡
የነበረ ፡ የግሪክ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰው ፡ ከብዙ ፡ የሞራል ፡
መጽሐፎቹ ፡ መካከል ፡ የእስክንድርን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ በግ
ሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ጽፎት ፡ የነበረው ፡ በኋላ ፡ በየቋንቋው ፡ ተተርጉሟል ።
በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለእስክንድር ፡ ሐሳብ ፡ እንደዚህ ፡
ይላል ። «እስክንድር ፡ ሁሉን ፡ ለመሰብሰብና ፡ ባንድነት ፡ አድርጎ ፡
ለመዳኘት ፡ አምላክ ፡ እንደላከው ፡ ያምን ፡ ነበር ። ዓለም ፡ ሁሉ ፡
እንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እንዲሆን ፡ ይመኝ ፡ ነበር ። በልማድም ፡
በመሣሪያም ፡ በግሪክና ፡ በአረማዊ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ሳይሆን ፡
ደጉ ፡ ሁሉ ፡ ግሪክ ፤ ክፉው ፡ ሁሉ ፡ አረመኔ ፡ እንዲባል ፡ ያስብ ፡
ነበር ። ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ በአንድ ፡ ዋንጫ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡
የፍቅር ፡ ወይኑን ፡ እንዲጠጣ ፡ ያለፈው ፡ ጠላትነትና ፡ ደካማነት ፡
እንዲረሳ ፡ አሳቡ ፡ ነበር ። ታልቦት ፡ ከተረጐመው ፡ ውስጥ ፡ ኤ.
ማሌና ፤ ይስሐቅ ፡ ግሪክና ፡ ምሥራቅ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፤ ያሳተሙ
ትን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፱ ፡ ተመልከት ።

በዚሁ ፡ በፕሉታርክ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚገኘው ፡ እስክንድር ፡ ዳርዮስን ፡ ጥሎ ፡ በግሪክና ፡ በግብፅ ፡ ግዛቱ ፡ ላይ ፡ የፋርስን ፡ የባቢሎንንና ፡ የአሶርን ፡ መንግሥታት ፡ ከያዘ ፡ ወዲህ ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ ጌትነት ፡ ጊዜውን ፡ ያሳልፍ ፡ ጀመር ፤ ያገሩን ፡ የግሪክን ፡ በተለይም ፡ የመቄዶንያን ፡ ልማድ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ እየተወ ፡ የፋርሶችን ፡ ልማድ ፡ በመቀበልና ፡ በመውደድ ፡ ልብስ ፡ መንግሥቱን ፡ ልክ ፡ እንደነ ፡ ዳርዮስ ፡ ሲብሶ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ ከየአገሩ ፡ በተለይም ፡ ከፋርስ ፡ የሚመጡት ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ እየተደፉ ፡ እንደ ፡ ምሥራቅ ፡ ነገሥታት ፡ ልማድ ፡ ይሳለሙት ፡ ጀመር ። የዚህም ፡ ሁኔታ ፡ የቀድሞዎቹን ፡ የጦር ፡ አለቆቹንና ፡ ወገኖቹን ፡ ግሪኮቹን ፡ አላስደሰታቸውም ። በባለሟልነትም ፡ ከግሪኮቹ ፡ ፋርሶቹ ፡ ስለሚቀድሙ ፡ በፋርሶችና ፡ በግሪኮቹ ፡ መካከል ፡ መቀናናት ፡ ተፈጠረ ፡ በዚሁ ፡ መካከል ፡ በእስክንድር ፡ ንጉሥ ፤ ላይ ፡ አድማችኋል ፡ ተብለው ፡ አንዳንድ ፡ የግሪክ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሲታሠሩ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ዳርዮስ ፡ ልጄን ፡ ልዳርልህና ፡ ተስማምተን ፡ አብረን ፡ እንግዛ ፡ ብሎ ፡ ለእስክንድር ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እስክንድርን ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ዕርቅ ፡ እቀበል ፡ ነበር ፡ ብሎት ፡ የነበረው ፡ ፓርሜኒዮን ፡ የሚባለው ፡ ሽማግሌ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ በእስክንድር ፡ ትእዛዝ ፡ ተገደለ ፡ ክሊቶስ ፡ ጥቁሩ ፡ የሚባለውንም ፡ ወዳጁን ፡ ራሱ ፡ እስክንድር ፡ ባንድ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ገደለው ። ይኸም ፡ ክሊቶስ ፡ የተባለው ፡ የእስክንድር ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ የነበረ ፡ በማናቸውም ፡ ጦርነት ፡ የማይለየው ፡ ከዳርዮስ ፡ ጋር ፡ በግራኒክ ፡ የተዋጋለት ፡ ከሞት ፡ ያዳነው ፡ ነው ።

በፕሉታርክ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚገኘው ፡ ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ በታላቅ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ግሪኮቹና ፡ ፋርሶች ፡ ሜዶናውያን ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ እየበሉ ፡ እየጠጡ ፡ ሲጫወቱ ፡ በዚያ ፡ ካሉት ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በተደረገ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ሳይቀናቸው ፡ የቀሩትን ፡ ፩ ፡ እንድ ፡ የመቄዶንያ ፡ የጦር ፡ መኰንኖችን ፡ እያነሱ ፡ ሲቀልዱ ፡ ክሊቶስ ፡ መጠጥ ፡ እንደተጫነው ፡ «የመቄዶንያ ፡ ጠላት ፡ በሆነ ፡ በአረመኔ ፡ ሕዝብ ፡ (ፋርስ ፡ ሜዶን) ፡ ፊት ፡ በመቄዶንያ ፡ ጀኔራሎች ፡ መቀለድ ፡ አይገባም» ፡ ብሎ ፡ ተቆጣ ፡ እስክንድር ፡ ክሊቶስ ፡



ፍርሃት ፡ ላላቸው ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ጠበቃ ፡ ሆኗል ፡ በዚል ፡ እነ ጋገር ፡ ቢመልስለት ፡ ክሊቶስ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ በእርግጥ ፡ እነዚህ ፡ ፈሪ ፡ የምትላቸው ፡ ናቸው ። አንተን ፡ የአማልክት ፡ ልጅ ፡ የምትባለውን ፡ ዠርባህን ፡ ሰጥተህ ፡ ስትሸሽ ፡ ተዋግተው ፤ ያዳኑህ ፡ በመቄዶንያውያን ፡ ደምና ፡ ቍስል ፡ ፊልጶስን ፡ ለመካዳትና ፡ የአሞን ፡ ልጅ ፡ እየተባልህ ፡ ታላቅ ፡ ለመሆን ፡ በቃህ ። መቄዶንያውያን ፡ በሜዶንያውያን ፡ በትር ፡ ሲመቱ ፡ ግሪኮቹ ፡ ወደንጉሡ ፡ ለመግባት ፡ ፋርሶቹን ፡ ደጅ ፡ ሲጠኑ ፡ ሳያዩ ፡ የሞቱት ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው» ፡ ሲል ፡ ተናገረ ። እስክንድርም ፡ በቁጣ ፡ ቢነሣ ፡ ይኸው ፡ ክሊቶስ ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፡ «እባክህ ፡ ዝም ፡ በልና ፡ የፋርሶችን ፡ ቀበቶ ፡ እንደታጠቅህ ፡ ነጩን ፡ ልብሳቸውን ፡ እንደለበስህ ፡ ከሚሰግዱልህ ፡ አረመኔዎችና ፡ ባሮች ፡ ጋር ፡ ኑር» ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስክንድር ፡ በገበታው ፡ ላይ ፡ ለመብል ፡ ከቀረቡት ፡ ፍሬዎች ፡ አንዱን ፡ አንሥቶ ፡ በክሊቶስ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ወረወረ ፤ ለመማታትም ፡ ሰይፉን ፡ ሲፈልግ ፡ ብልሁ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬ ፡ በቀበት ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ ሹማምንት ፡ እየጐተቱ ፡ ክሊቶን ፡ በግድ ፡ ወደውጭ ፡ አወጡት ። ከዚያም ፡ ቲንሽ ፡ ቆይቶ ፡ በሌላ ፡ በር ፡ ተመልሶ ፡ ገባና ፡ «አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ግሪክን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ልማድ ፡ ወረረው» ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እስክንድር ፡ ጦሩን ፡ ጨብጦ ፡ ክሊቶስን ፡ በፊቱ ፡ ሲያልፍ ፡ ተጠባብቆ ፡ ወርውሮ ፡ ገደለው ።

ክሊቶስ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እስክንድር ፡ ወዳጁን ፡ በራሱ ፡ እጁ ፡ በመግደሉ ፡ በጣም ፡ ተጸጸተ ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ላይ ፡ የምናስታውሰው ፡ ባገራችን ፡ ከአብሮ ፡ አደግህ ፡ አትሰደድ ፡ ወይም ፡ የመከራ ፡ ጊዜ ፡ አሽከር ፡ መከራን ፡ መስሎ ፡ ይታያል ፡ እንደሚባለው ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ ለእስክንድር ፡ የጭፍራ ፡ ጓደኛ ፡ ሆነው ፡ በዘመቻ ፡ በጉዞ ፡ ሳይለዩ ፡ አብረው ፡ የኖሩት ፡ የመቄዶንያና ፡ የግሪክ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከሜዶንና ፡ ከፋርስ ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ መሳፍንቶች ፡ ጋር ፡ በመቀናናት ፡ እንደተጣሉ ፡ ፋርሶች ፡ ክብርን ፡ ገናንነትን ፡ ለሚወደው ፡ የአማልክቱ ፡ የነአሞን ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ለሚለው ፡ ለወጣቱ ፡ ለእስክንድር ፡ ለጥ ፡ ሰጥ ፡ ብለው ፡ ሲሰግዱ ፡ ይስበረኝ ፡ ይሰንጥረኝ ፡ እያሉ ፡ በእንደበታቸው ፡ እያቆላመጡ ፡ ውዳሴ ፡

ሲያደርጉለት ፡ ደረቆቹ ፡ ግሪኮች ፡ በወገንነታቸውና ፡ ባስፈ ፡ ርዳ ታቸው ፡ ብቻ ፡ እየተመኩ ፡ እስክንድርን ፡ እንዳላስደሰቱት ፡ ይታ ያል ።

የነዚያ ፡ የምሥራቃውያኑ ፡ አክብሮትና ፡ ቁልምጥ ፡ ለእስክን ድር ፡ መንፈስ ፡ ሲጥመው ፤ የነዚህ ፡ የወገኖቹ ፡ ትምክህትና ፡ ኩራት ፡ ስላበሳጨው ፡ የዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ወዳጁን ፡ እስከ ፡ መግደል ፡ እንዳ ደረሰው ፡ እንመለከታለን ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ከሕንድ ፡ ተመልሶ ፡ መቀ መጫውን ፡ ባቢሎን ፡ ከተማ ፡ አድርጎ ፤ የግሪክና ፡ የፋርስ ፡ ሕዝብ ፡ ሌላውም ፡ ሁሉ ፡ ተደባልቆ ፡ በጋብቻ ፡ በልማድ ፡ እንዲተሳሠር ፡ በምክርም ፡ በትእዛዝም ፡ ሲያስተዳድር ፡ ቆየ ።

ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ሱስ ፡ (የኤላም ፡ ከተማ) ፡ መመላለሱ ፡ ሳይ ቀር ፡ ዋና ፡ መደበኛና ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ያደረገው ፡ ባቢሎንን ፡ ነው ፤ ይቺንም ፡ ከተማ ፡ ጥንት ፡ እነ ፡ ሐሙራቢ ፡ እነ ፡ ናቡከደነ ጾር ፡ ካስጌጧት ፡ የበለጠ ፡ እስክንድር ፡ አዳዲስ ፡ ዕርዓዊ ፡ ሕንፃ ፡ እያስጨመረ ፡ አስጌጣት ። በዚህች ፡ በደመቀች ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተጠቀሰው ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ መልእክተኞች ፡ ግሪኮች ፤ ኢጣሊያኖች ፤ የካርታዥና ፡ የእስፓኝ ፤ የግብፅና ፡ የኢት ዮጵያውያን ፡ መልእክተኞች ፡ ሁሉ ፡ በየአገራቸው ፡ ልብስ ፡ አጊ ጠው ፡ እየመጡ ፡ የዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ለተባለው ፡ ለእስክንድር ፡ እጅ ፡ እየነሱ ፡ ተመለሱ ። እሱም ፡ የመጡትን ፡ ሁሉ ፡ እንደልማዳቸው ፡ እየተቀበለ ፡ ሁሉንም ፡ እያስተናገደ ፡ ሲመልስ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በወታደርነት ፡ ባሽከርነት ፡ ባጃቢነት ፡ የማይለዩት ፡ ያገሩ ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችና ፡ በቅርቡ ፡ የተገዙለት ፡ የፋርስና ፡ የሜዶን ፡ መሳ ፍንትና ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ከባቢሎን ፡ በግዛቱ ፡ በግ ብፅ ፡ አልፎ ፡ በካርታዥ ፡ አድርጎ ፡ ያልገበሩ ፡ አገሮች ፡ እንዳሉ ፡ እነዚያን ፡ አስገብሮ ፡ በሜዲቴራኔ ፡ ባሕር ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ ለመመለስ ፡ ሲመኝ ፡ በመካከሉ ፡ በድንገት ፡ ባንድ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ የትኩሳት ፡ ሕመም ፡ ተነሣበት ። በዚሁ ፡ ሕመም ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ እንደተኛ ፡ በተወለደ ፡ በሠ



ላሳ ፡ ሦስተኛው ፡ በነገሠ ፡ በ፫፻ኛው ፡ ዓመት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በ፫፻፳፫ ፡ ዓመት ፡ በዚሁ ፡ በባቢሎን ፡ ከተማ ፡ ሞተ ። ስለአማ ሟቱ ፡ ግማሹ ፡ ወደ ፡ ሕንድ ፡ በዘመተ ፡ ጊዜ ፡ ወባ ፡ ነድፎት ፡ ነበ ርና ፡ በዚያ ፡ ትኩሳት ፡ ሞተ ፡ ሲሉ ፡ የቀሩት ፡ ጀኔራሎቹ ፡ (አንቲ ፓተር?) ፡ በመድኃኒት ፡ ገደሉት ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በደረሰባቸው ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የከተማቸው ፡ ከተማዎች ፡ ቊጥር ፡ እስከ ፡ ሰባ ፡ ይደርሳሉ ፡ ይባላል ። ከነዚሁ ፡ አሥሩ ፡ በስሙ ፡ እስክንድርያ ፡ የሚባሉ ፡ ናቸው ። ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ እንደኛዪቱ ፡ የግብፅ ፡ እስክንድርያ ፡ እነሆ ፡ በክርስትና ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ የደመቀች ፡ ከተማ ፡ የሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ መቀመጫ ፡ ሆና ፡ ከዘመናችን ፡ ላይ ፡ ደርሳለች ። የእስክንድርም ፡ አፅም ፡ ወደ ዚችው ፡ ከተማ ፡ መጥቶ ፡ በክብር ፡ አረፈ ። ይህች ፡ ከተማ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ መሥርቷት ፡ በስሙ ፡ እስክንድርያ ፡ እየተባለች ፡ ከመ ጠራቷ ፡ በፊት ፡ የቀድሞ ፡ ስሟ ፡ ራኩዲ ፡ እንደነበረ ፡ በዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። እንደሚመስለኝ ፡ ዮሐንስ ፡ መደብር ፡ ራኩዲ ፡ ያለው ፡ ቀድሞ ፡ በግብፃውያኑ ፡ ዘመን ፡ ራካቲ ፡ ይባል ፡ የነበረውን ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ፖል ፡ ፒዬሬ ፡ ያዘጋጀ ውን ፡ የግብፅ ፡ የአርኬዎሎዥ ፡ መዝገበ ፡ ነገር ፡ (ዲክሲዮኔር) ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ተመልከት ። እንደዚሁም ፡ ይኸንኑ ፡ ግብፃውያን ፡ ራካቲ ፡ ይሉት ፡ የነበረው ፡ ሥፍራ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በግሪክኛ ፡ አጠራር ፡ ዓይነት ፡ ራኮቲስ ፡ ይባላል (፩) ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

### እስክንድርና ፡ ዲዎጋን-ከትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ሞት በኋላ ፡ ግዛቱን ፡ የተካፈሉት ፡ አለቆች ።

እስክንድር ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሰፊውን ፡ ግዛቱን ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ «ዲያዶክ—ተከታዮች» ፡ ተብለው ፡ የተሰየሙት ፡ ተካፍለው ፡ ያዙት ። ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ በተወለደ ፡ በ፴፫ ፡ ዓመቱ ፡ በነገሠ ፡ በ፲፫ኛው ፡ ዓመት ፡ መሞቱን ፡ ስንመለከት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በኑሮው ፡

(፩) የዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፻፲፪ ።

በግዛትም ፡ የኖረበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትንሽ ፡ መሆኑን ፡ እንረዳለን ። በዚህም ፡ በትንሽ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ስፊውን ፡ የአፍ ሪካ ፡ ሰሜንና ፡ የመካከለኛ ፡ ምሥራቅ ፡ ዓለም ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ ድረስ ፡ እየዞረ ፡ ታላላቆቹን ፡ መንግሥታት ፡ ይልቁንም ፡ በተለይ ፡ ፴ ፡ መንግሥታት ፡ የገበሩለትን ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ለማስገበር ፡ በየ ጠረፉ ፡ ያስጨነቀውን ፡ የፋርስን ፡ መንግሥት ፡ ጥሎ ፡ የራሱን ፡ ግዛት ፡ ሲያስፋፋ ። በዚህም ፡ ሥራው ፡ ስሙን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሲተ ክል ፡ በትንሽ ፡ ዘመንና ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ መቻሉን ፡ እንረዳለን ። ቢሆንም ፡ እርሱ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ የሠራ ውን ፡ ሰፊ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ለርሱ ፡ የተሰጠውን ፡ የስጦታና ፡ የዕውቀት ፡ ያድፍረትና ፡ የትጋት ፡ ዕድል ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልጋል ።

ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ እንደወጣትነቱ ፡ መጠን ፡ እየጋለበ ፡ እን ደካምቢዝ ፡ አገር ፡ ወራሪ ፤ እንደ ፡ አቲላ ፡ አገር ፡ ዘራፊና ፡ አሸባሪ ፡ እንደኔሮን ፡ ቀብራራ ፡ ወይም ፡ ግፈኛ ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሊያዘው ፡ አገር ፡ አዲስ ፡ ሕግና ፡ አስተዳደር ፡ በመ ስጠት ፡ የቀድሞዎቹ ፡ የፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ የጫኑ ትን ፡ ግብርና ፡ መጥን ፡ በአሶራውያን ፡ እንደተመለከትነው ፡ ባገር ፡ ላይ ፡ የሚያደረገውን ፡ ዘረፋ ፡ በምርኮኛ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸመውን ፡ ግፍና ፡ እብሪት ፡ በማስቀረት ፡ ለምርኮኛ ፡ ምሕረትና ፡ ነፃነት ፡ በመስጠት ፡ ተመስግኗል ። በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በገባበት ፡ በግብፅ ፡ በጢሮስ ፡ በሲዶና ፡ በባቢሎን ፡ በፋርስ ፡ ከተማ ፡ ያጋጠ መውን ፡ ብዔል ፡ አስታርት ፡ አሞን ፡ ሞሎክ ፡ የሚባሉትን ፡ አማ ልክትና ፡ የሕዝብ ፡ አምልኮ ፡ ሳይንቅ ፡ ቤተ ፡ መቅደሳቸውን ፡ ሳያ ፈርስ ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ንጉሥ ፡ የሚፈጸመውን ፡ ሥር ዓት ፡ ክህነት ፡ ወደየቤተ ፡ መቅደሱ ፡ እየገባ ፡ ፈጽሞ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ አስደስቷል ። ይኸንንም ፡ ሁሉ ፡ ሲያደርግ ፡ የተመለከቱ ፡ ካህናቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ይኸስ ፡ የአምላካችን ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አመስግነው ፡ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ አስመስግነው ፡ አገዛዙን ፡ አቃ ኑለት ። በኢየሩሳሌምም ፡ ከተማ ፡ ደርሶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ በተሳለመ ፡ ጊዜ ፡ የአሪት ፡ ካህ ናት ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ይባላል ።



ከዚህ ፡ በቀር ፡ ጸሐፊና ፡ ፈላስፋን ፡ ያከብር ፡ እንደነበረ ፡ የር ሱና ፡ የመምህሩ ፡ የአርስጣጣሊስ ፡ ፍቅርና ፡ ስምምነት ፡ ይገልጻል ። እንደዚሁም ፡ ዓለምን ፡ በመናቅ ፡ የታወቀውን ፡ ፈላስፋ ፡ ዲዎጋ ንን ፡ በማክበሩ ፡ ያስረዳል ። ዲዎጋን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ንቆ ፡ አንድ ፡ ውሻ ፡ እያስከተለ ፡ አንድ ፡ በትርና ፡ አንድ ፡ ቅል ፡ በጁ ፡ ይዞ ፡ በተቀረደ ፡ ኑሮ ፡ እየኖረ ፡ ባርጌ ፡ ቤርሜል ፡ ውስጥ ፡ ይተኛ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የተጠማ ፡ እረኛ ፡ በልቡ ፡ ተኝቶ ፡ ከወንዝ ፡ ወሃ ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ እያፈሰ ፡ ሲጠጣ ፡ አይቶ ፡ «ዛሬ ፡ አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ተማርሁ ፤ ለካ ፡ ይችም ፡ የያዝኋት ፡ ቅል ፡ ትርፍ ኖራለች» ፡ ብሎ ፡ ሰበራት ፡ ይባላል ።

ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ይኸ ፡ ፈላስፋ ፡ አለበት ፡ ድረስ ፡ እየሔደ ፡ ማነጋገርና ፡ መጫወት ፡ ይወድ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። በዚህም ፡ የጦር ፡ አለቆቹና ፡ ዘመናይ ፡ ባለማሉቹ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ ከወፈፌ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አነጋገረህ ፡ እያሉ ፡ ዘወትር ፡ ሲወቅሱት ፡ እስክንድር ፡ ግን ፡ «እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ እስክንድርን ፡ ባልሆን ፡ ኖሮ ፡ ዲዎጋንን ፡ መሆን ፡ እፈልግ ፡ ነበር ፡ እያለ ፡ ይመልስላቸው ፡ ነበር ። እዚህ ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ የተለያዩ ፡ አሳቦች ፡ እናገኛለን ፤ እስክንድር ፡ ከዲ ዎጋን ፡ ጋር ፡ መገናኘቱን ፡ ግምት ፡ ስጥቶታል ፤ ሹማምንቱ ፡ ግን እንደውርደት ፡ ቈጥረው ፡ ይከለክሉታል ፤ ዲዎጋን ፡ ደግሞ ፡ የእስ ክንድርን ፡ ግንኙነት ፡ አልኮራበትም ። ይኸም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እስክንድር ፡ በሹማምንቱ ፡ ታጅቦ ፡ ዲዎ ጋን ፡ እቤርሜሉ ፡ በራፍ ፡ ሆኖ ፡ ፀሐይ ፡ ሲሞቅ ፡ ሊገናኘው ፡ መጣ ፡ በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ እፊቱ ፡ ቆሞ ፡ «ዲዎጋን ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ እንዳደርግ ልህ ፡ ትፈልጋለህ » ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። መቼም ፡ የእስክንድር ፡ ጥያቄ ፡ ሹመት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ለመስጠት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈላስፋው ፡ «አዎን ፡ የምለምንህ ፤ ነገር ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ የምለምንህ ፡ «ፀሐይዋን ፡ ብቻ ፡ እንዳትከለክለኝ ፡ ዘወር ፡ እንድትልልኝ ፡ ነው» ፡ ብሎ ፡ ሌላ ፡ ያልታሰበ ፡ የመልስ ፡ እደጋ ፡ ወረወረበት ። ይኸን ፡ የመሰለው ፡ መልስ ፡ የእስክንድርን ፡ ግምት ፡ በዲዎጋን ፡ ላይ ፡ እየበዛ ፡ እንዲሔድ ፡ አደረገለት ፡ እንጂ ፡ ደፈርኸኝ ፡ ወይም ፡ አዋረድኸኝ ፡ ብሎ ፡ አልተቆጣውም ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡

ዓለምን ፡ ለመያዝ ፡ ሲወጣ ፡ ሲወርድ ፡ ዲዮጋን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዓለምንና ፡ በዓለም ፡ ያለውን ፡ ኑሮ ፡ ፈጽሞ ፡ መናቁ ፡ እየገረመው ፡ በልቡም ፡ እያከበረው ፡ ትቶት ፡ ሔደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በአነጋገሩም ፡ «እስክንድርን ፡ ባልሆን፡ ኖሮ፡ ዲዮጋንን፡ እሆን ፡ ነበር» ሲል ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እስክንድር ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሥልጣንን ፡ ዓለምን ፡ ለጊዜው ፡ ቢይዝ ፡ ሁሉም ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ የዲዮጋንን ፡ ያኽል ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ በመጠኑ ፡ በዚሁ ፡ በወጣትነት ፡ ዕድሜው ፡ ተረድቶት ፡ እሱም ፡ ዓለምን ፡ ለመተው ፡ የመከጀል ፡ ዝንባሌ ፡ እንዳለው ፡ ያስረዳል ።

ነገር ፡ ግን ፡ እስክንድር ፡ እንደምኞቱ ፡ ዓለምንም ፡ ጨርሶ ፡ ሳይዝ ፡ ሚስትንም ፡ ሳይነቅ ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በወጣትነቱ ፡ ዘመን ፡ ነጠቀው ። ዲዮጋን ፡ ደግሞ ፡ ይኸን ፡ ዓለም ፡ ቢመረርም ፡ ቢጠላም ፡ በግድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እስኪያረጅ ፡ ድረስ ፡ ተቀመጠ ፤ ከአረጀ ፡ በኋላ ፡ በዘጠና ፡ ዓመቱ ፡ በ፫፻፳፫ ፡ ዓመት ፡ በቆሮንቶስ ፡ ሞተ ። ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ በዕድሜና ፡ በሥራ ፡ በአሳብ ፡ ዝንባሌ ፡ የተለያዩ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፡ በ፫፻፳፫ ፡ ዓመት ፡ በሞት ፡ ተገናኙ ። ከሁለቱ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ የወደደውንም ፡ የጠላውንም ፡ ማግኘት ፡ አለመቻሉን ፡ በሰውና ፡ በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ የሚፈጽመው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሰውዬው ፡ ዝንባሌ ፡ ያዘዘውና ፡ የፈቀደው ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ እንማራለን ።

እስክንድር ፡ ሊሞት ፡ ሲል ፡ ግዛቱን ፡ በደፈናው ፡ «የሚገባው ፡ ሰው ፡ ይውሰድ» ፡ ብሎ ፡ የማንንም ፡ ስም ፡ ሳያነሣ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ። የጦር ፡ አለቆቹ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ትንሽ ፡ ቀን ፡ በአሳብ ፡ ተተራመሱ ፡ ተዋጉም ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ከሮክሳን ፡ (የባክትሪያን ፡ ልጅ ፡ ) የተወለደው ፡ አሌክሳንድር ፡ ኤጎ ፡ የሚባለው ፡ ልጁ ፡ በመቄዶንያ ፡ ዙፋን ፡ በሞግዚት ፡ የሁሉ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገዛ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የገዛ ፡ ሞግዚቱ ፡ ካሣንድር ፡ ከናቱ ፡ ጋር ፡ ገድሎ ፡ መቄዶንያን ፡ ያዘ ። የቀረውንም ፡ ሰፊ ፡ ግዛቱን ፡ «ዲያዶኩ-ተከታይ» ፡ የተባሉት ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ በከፍያና ፡ እኔ ፡ የበላይ ፡ ልሁን ፡ በማለት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ ፡ ቆይተው ፡ የመጨረሻው ፡ ጦርነት ፡ በ፫፻፩ ፡ ዓመት ፡ በኢፕሱስ ፡



ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ዕርቅና ፡ ሰላም ፡ ሆኖ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚቀጥለው ፡ በስምምነት ፡ ከሦስት ፡ ላይ ፡ ተከፋፈሉት ።

፩ኛ ፡-ግብፅና ፡ አካባቢው ፡ ለፕቶሎሜ ፡ ( በጥሎሚስ) ፡ ሶተር፡ የላጎስ ፡ ልጅ ፡

፪ኛ፡-ሦርያና ፡ አካባቢው ፡ ለሰሌውኩስ ፡

፫ኛ፡- መቄዶንያ ፡ ከካሳንድር ፡ በፊት ፡ ( ለአንቲጎን ?) በኋላ ፡ ለካሳንድር ፡ እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቀጥሎ ፡ እስከ ፡ ሮማውያን ፡ መነሣትና ፡ እስከ ፡ ክሊዎፓትር ፡ ድረስ ፡ የበጥሊሞስ ፡ ዘር ፡ እየተከታተሉ ፡ በግብፅ ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ። የመርዌና ፡ የአክሱም ፡ መንግሥታትም ፡ ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ ግንኙነት ፡ አድርገው ፡ የግሪክን ፡ ሥልጣኔ ፡ በመጠኑ ፡ ማስገባት ፡ የቻሉት ፡ ሸቀጥ ፡ ለሸቀጥ ፡ የተለዋወጡት ፡ ከነዚሁ ፡ ከነበጥሊሞስ ፡ ጋር ፡ ነው ።

የእስክንድር ፡ ታሪክ ፡ ቀድሞ ፡ በዐረብኛ ፡ እነአቡሻክር ፡ ጽፈውት ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ የተተረጐመ፡ አባ፡ ጌራሲሙስና ፡ እንደዚሁም ፡ ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ጎርዮን ፡ በዕብራይስጥ ፡ ጽፈውት ፡ የነበረው ፡ በያይነቱ፡ አለ። በጠቅላላ፡ የዚህ፡ መጽሐፍ፡ ስሙ፡ በግዕዝ፡ «ዜና፡ እስክንድር» ፡ይባላል ። በዚህ፡ ታላቅ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ፡ ከደንበኛውና፡ ከእውነተኛው ፡ ግሪኮቹ ፡ ከጻፉት ፡ ጋር ፡ የማይገናኝ ፡ ስሕተትና ፡ የማይመስል ፡ ነገር ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይገኝበታል ። ሁሉንም ፡ በዝርዝር ፡ ለማስረዳት ፡ ጸሐፊንም ፡ አንባቢንም ፡ ስለሚያሰለቹ ፡ ከአቡሻክር ፡ የተገኘውን ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከመዠመሪያው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስሕተት ፡ እንመልከት ።

« በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ንጽሕፍ ፡ ዜናሁ ፡ ለእስክንድር ፡ ንጉሥ ፡ ዘተረክበ ፡ እምአቡሻክር።

እስክንድር ፡ ወልደ ፡ ፊልጶስ ፡ ዮናናዊ ፡ ዘ፪ ፡ አቅርንቲሁ ፡ ንግሠ ። ፶ ፡ ወ፺ ፡ ዓመት ፡ እንዘ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ፲ ፡ ወ፺ ፡ ዓመት ፡ ወዙሉ ፡ ኍልቈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ፳ ፡ ወ፪ ፡ ዓመት ፡ ውእቱ ፡ ወከማሁ ፡ ይቤ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮምያ ፡ በታሪኩ ፡ ወስዒድስ ፡ ወልደ ፡ በጥራቅ ፡ ወወልደ ፡ መንኩስ ፡ ይብሉ ፡ ኍልቈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ፴ ፡ ወ፪ ፡ ዓመት ፡ ወመዋዕለ ፡ መንግሥቱ ፡ ፲ ፡ ወ፺ ፡ ዓመት ፡ » ይልና ፡ በዘመኑ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እንደተለያዩበት ፡ በመግለጽ ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡

ይቀጥላል ። መቼም ፡ ጠቅላላ ፡ ዘመኑን ፡ ፫፻፪ ፡ ዓመት ፡ የነገሠበትን፡ ፶፯ ፡ ዓመት ፡ ካደረገው ፡ ጸሐፊ ፡ ሙሉ ፡ ዕድሜውን ፡ ፴፪ ፡ ዓመት ፡ የነገሠበትን ፡ ዘመን ፡ ፲፯ ፡ ዓመት ፡ ያደረገው ፡ ከደንበኛ ፡ ታሪኩ ፡ ሊገጥም ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረውም ፡ ፲፯ ፡ ዓመት ፡ ያለውን ፡ ፲፫ ዓመት ፡ ቢል ፡ ኖሮ ፡ ከእውነተኛው ፡ ታሪኩ ፡ ሊገናኝ ፡ ይችል ፡ ነበር ።

ይልቅስ ፡ ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በአጭሩም ፡ ቢሆን ፡ የኒቅያ፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ ፡ የጻፈው ፡ ባገራችን ፡ ወደግዕዝ ፡ የተተረጐመው ፡ ዮሐንስ ፡ መደብር ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ይሻላል ። እርሱም ፡ ባጭሩ ፡ በግዕዝኛው ፡ ቋንቋ ፡ በ፺፱ኛው፡ ምዕራፍ፡ እንደዚህ፡ ይላል።

« ወእስክንድር ፡ ወልደ ፡ ፊልጶስ ፡ መቄዶናዊ ፡ ሶበ ፡ ነግሠ ፡ ሐነፃ ፡ ለሀገር ፡ ዐባይ ፡ እስክንድርያ ፡ በሀገረ ፡ ምስር ፡ ወሰመያ ፡ በስሙ ፡ እስክንድርያ ፡ ወስማሰ ፡ ቅድመ ፡ ራኩዲ ፡ በልሳነ ፡ ምስ ራውያን ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ጾብአ ፡ ለሀገረ ፡ ፋርስ ፤ ወበጽሐ ፡ እስከ ፡ ወሰነ ፡ አውዚዝ ፡ ወሐነፀ ፡ በህየ ፡ መካነ ፡ ኀበ ፡ ተጋብኡ ፡ ሐራሁ ፡ ወለኵሎሙ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወበህየ ፡ ወሀቦሙ፡ወርቀ ፡ ብዙኃ ፡ ለዐበ ይት ፡ ሐራሁ ፡ ወለኵሎሙ ፡ መኳንንቲሁ ፡ ወለሠራዊቱ ፡ ብዙኃን፡ ወሰመያ ፡ ለይእቲ ፡ መካን ፡ አኪርሳቡልስ ፡ ወከመዝ ፡ ይሰምይዋ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ብርንጥያ ። ወሶበ ፡ ፀብአ፡ለፋርስ ፡ እስክንድር ፡ ቀተለ ፡ ብዙኃነ ፡ እምሠራዊተ ፡ ዳርዮስ ፡ እስከ ፡ አኅለቆሙ ፤ ወነ ሥአ ፡ መንግሥተ ፡ ዳርዮስ ፡ ኵሉ ፡ ወተሠልጠ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወዓዲ ፡ ነሥአ ፡ ለወለቱ ፡ ዘስማ ፡ ርኩሳኒ፡ወይእቲ ፡ ኮነት ፡ ድንግለ፡ወረሰያ ፡ ብእሲቶ ፡ ወኢገብረ ፡ ባቲ ፡ እኩየ ። ወለንግሥተ ፡ ኀበሻሂ ፡ ዘስማ ፡ ቅንዳቅስ ፡ ኢያሕሰመ ፡ ላዕሌሃ ፡ በእንተ፡ዕበየ ፡ ልቡናሃ ። እስመ ፡ ይእቲ ፡ ሰምዐት ፡ ዜና ፡ ምግባራቲሁ ፡ ለእስክንድር ፡ ወልማዳቲሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ይዴመር ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ዓይን ፡ ወአኃዘቶ ፡ ወትቤሎ ፡ አንተ ፡ ንጉሥ ፡ ዘአኀዝከ ፡ ኵላ ፡ ዓለም ፡ ወአንተ ፡ ዮም ፡ ተእኀዝከ ፡ በብእሲት ። ወይቤላ ፡ ውእቱ ፤ በእንተ ፡ አእምሮትኪ ፡ ወርቀተ ፡ ልቡናኪ ፡ ወጥበብኪ ፡ አኀዝክኒ ፡ አነ ፡ እምይእዜ ፡ አዓቅ በኪ ፡ ዘእንበለ ፡ እከይ ፡ ለኪ ፡ ወለደቂቅኪ ፡ ወእሬስየኪ ፡ ሊተ ፡ ብእሲተ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዐት ፡ ዘንተ፡ሰገደት ፡ ሎቱ ፡ ታኅተ ፡ እገሪሁ፡



ወተሰነዓወት ፡ ምስሌሁ ፡ ወረሰያ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲተ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ገረሩ ፤ ሎቱ ፡ ሐበሽ ። ወእስክንድርኒ ፡ አመ ፡ ሞተ ፡ ከፈለ፡ መንግሥቶ ፡ ለ፲ ፡ አዕርክቲሁ ፡ እለ ፡ ተራድዕዎ ፡ በውስተ ፡ ፀብእ ፡ ወፊልጶስኒ ፡ እኁሁ ፡ ዘየዐቢ ፡ ነሥአ ፡ ለሀገረ ፡ መቄዶንያ ፡ ወኮነ ፡ ንጉሠ ፡ ውስቴታ ። ወለኵሉ ፡ አውርያ ፡ ወዓዲ ፡ አንገሠ ፡ ለሀገረ ፡ ምስር ፡ በጥሊሞስሃ ፡ ዘተሰምየ ፡ በይላጎስ » ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስለተጻፈው ፡ አንዳንድ ፡ ትርጉም ፡ ሰጥተን ፡ አሳቡን ፡ ማብራራት ፡ ለአንባቢ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ዮሐንስ ፡ መደብር ፡ ተብሎ ፡ በስሙ ፡ የተሰየመውን ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በሻባካ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ዮሐንስ ፡ የኒቅዩ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ይባ ላል ። የነበረበት ፡ ዘመን ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፯ኛው፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በእስክንድርያ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ወንበር ፡ አባ ፡ ዮሐንስና ፡ አባ ፡ ስምዖን ፡ በየተራ፡በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ነው ። ይህ፡ መጽሐፍ ፡ በዓረብኛ ፡ አዘጋጅቶት ፡ ሲኖር ፡ ባዔ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልና፡ ባዔ ፡ ዘርዓ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሺ፩፻፺፯—ሺ፩፻፺፰ ፡ ዓ.ም. ከዓረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተተርጕሟል ።

እንግዲህ ፡ ዮሐንስ፡ከኮፕት ፡ (ግብጢ) ፡ ከግሪክኛ ፡ እየሰበሰበ፡ በዓረብኛ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ከ፰፻ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ሲተረጐም ፡ በየመንገዱ ፡ በየሥፍራው ፡ አንዳንድ ፡ ጉድ ለት ፡ ከመደረጉ ፡ በቀር ፡ የስም ፡ ስሕተትም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይገኛል ።

እላይ ፡ በቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የግዕዝኛ ፡ ታሪክ ፡ ወበጽሐ፡ እስከ ፡ ወሰነ ፡ አውዚዝ ፡ የሚለው ፡ አውሮፓ ፡ ወሰን ፡ ለማለት ፡ ነው ።

«ወሰመያ ፡ ለይእቲ ፡ መካን ፡ አኪሪሳቡልስ ፡ የሚለው ፡ በኬል ቄዶን ፡ አጠገብ ፡ ቢዛንቲን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የሚገኘውን ፡ በግሪክኛ፡ ክሪሶፓሊስ ፡ የሚባለውን ፡ የጥንት ፡ ከተማ ፡ ሲጠቅስ ፡ ነው ። ይቺ፡ ከተማ ፡ ዛሬ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ሆናለች ።

ወከመዝ፡ይሰምይዋ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ብርንጥያ ፡ የሚላቸው፡ ቍስጥንጥንያን፡ከተማ ፡ በ፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትልቁ ፡ ቈስጠን

ጢኖስ ፡ መሥርቶት ፡ በስሙ ፡ ከመሰየሙ ፡ በፊት ፡ በላቲኖችና ፡ በግሪኮች ፡ ዘንድ ፡ አገሪቱ፡ቢዛንቲያ ፡ ወይም ፡ ቢዛንቲዩም ፡ ትባል፡ ነበር ። ይቺም ፡ አገር ፡ ዓረቦች ፡ ብርንጥያ ፡ ብለዋት ፡ የነበረውን ፡ ግዕዝ ፡ ተርጓሚው ፡ እንዳለ ፡ ወስዶ ፡ አገሪቱን ፡ ብርንጥያ ፡ ሰዎቹን ፡ ሰብአ ፡ ብርንጥያ ፡ ብሏቸዋል ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ቱርኮች ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ መንግሥት ፡ ቀምተው ፡ እጅ ፡ ሲያደርጉ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ የሚባለውን ፡ ስም ፡ አስቀርተው ፡ እስጣምቡል ፡ ብለዋታል ።

ወዓዲ ፡ ነሥአ ፡ ለወለቱ ፡ ርሖሳኒ ፡ ብሎ ፡ እስክንድር ፡ ዳርዮስን ፡ ካሸነፈ ፡ ወዲህ ፡ ልጁን ፡ ርሖሳኒ ፡ የምትባለውን ፡ አገባ ፡ ያለው ፡ የልጅቱ ፡ ስም ፡ ሮክሳን ፡ የነበረውን ፡ ርሖሳኒ ፡ በማለት ፡ ቲንሽ ፡ ለወጥ ፡ አድርጎታል ።

ወፊልጶስኒ ፡ እኍሁ ፡ ዘየዓቢ ፡ ነሥአ ፡ ለሀገረ ፡ መቄዶንያ ፡ ወኮነ ፡ ንጉሠ ፡ ውስቴታ ፡ ያለው ፡ ፊልጶስ ፡ የሚለው ፡ ክሳንድርን ፡ ይሆናል ፡ ወለኵሉ ፡ አውርያ ፡ ያለውም ፡ አውሮፓን ፡ ሲል ፡ ነው ። ወአንገሠ ፡ ለሀገረ ፡ ምስር ፡ በጥሊሞስሃ ፡ ዘተሰምየ ፡ በይላጎስ ፡ ያለው ፡ በግብፅ ፡ ከእስክንድር ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ የዘሩን ፡ ሐረግ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የላጂድ ፡ ዲናስቲ ፡ የሚባለውን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥቱን ፡ የተከለውን ፡ ላጉስ ፡ ወይም ፡ ላጎስ ፡ የሚባለውን ፡ የእስክንድርን ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሲጠቅስ ፡ ነው ። ቤይ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ከኋላው ፡ ጨምሮ ፡ ቤይላጐስ ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት፡ ሙሴ፡ ዘተንበርግ ፡ እንዳመለከቱት ፡ የላጎሱ ፡ ለማለት ፡ አንቀጽ ፡ ( አርቲክል) ፡ አድርጎት ፡ ይሆናል ። በተረፈ ፡ በጥሊሞስሃ፡ ዘተሰምየ ፡ በይላጎስ ፡ ያለው ፡ የበጥሊሞስ ፡ ስያሜ ፡ የጀመረው ፡ ሶተር ፡ ከሚባለው ፡ እንጂ ፡ ላጎስ ፡ በጥሊሞስ ፡ አልተባለም ። የርሱ ፡ ስም ፡ ሶተር ፡ ፕቶሌሜውስ ፡ ( በጥሊሞስ ) ሲሆን ፡ ላጎስ ፡ ያባቱ ፡ ስም ፡ ነው ።

በተረፈ ፡ እስክንድር ፡ በድብቅ ፡ ከሰላዮቹ ፡ ጋር ፡ መጥቶ ፡ንግሥት ፡ ቅንዳክስ ፡ (ሕንደኬ) ፡ የምትባለዋን ፡ የሀበሻ ፡ ንግሥት ፡ አገባ ፡ ስላለው ፡ ወደፊት ፡ በሚገኘው ፡ ምዕራፍ ፡ ለብቻ ፡ ጽፈነዋልና ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ መርዌ ፡ መንግሥት ፡ እንለፍ ።



ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

የመርዌ ፡ ንግሥት ፡ የሕንደኬና ፡ የትልቁ ፡ እስክንድር ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡— የመርዌ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ የነፕቶለሚ ፡ (በጥሊሞስ) ፡ ግንኙነት ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የናፓታ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ግብፅን ፡ የሚወር ፡ የውጭ ፡ መንግሥት ፡ ወታደር፡ በየጊዜው፡ ስለሚያጠቃቸው፡ ከላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ይልቁንም ፡ ከናፓታ ፡ ወደመርዌ ፡ መጥተው ፡ መንግሥታቸውን ፡ ይመሩ ፡ ከነበሩት ፡ ውስጥ ፡ ያንዳንዶቹን ፡ ታሪክ ፡ በመጠኑ ፡ ባለፈው ፡ አንብበናል ። ከነዚሁ ፡ ካምቤዝ ፡ የፋርሱ ፡ ንጉሥና ፡ ናስቶሰኔን ፡ የኢትዮጵያ ፡ (መርዌ ፡ )ንጉሥ ፡ ለጦርነት ፡ ተሳልፈው ፡ ሳይዋጉ ፡ ካምቤዝ ፡ ጦሩ ፡ በረኃብና ፡ በጥም ፡ ስለተጐዳበት ፡ መመለሱን ። በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በግብፅ ፡ የነገሠው ፡ አሪአንዴዝ ፡ ከመርዌው ፡ ንጉሥ ፡ ከሂዳስፕ ፡ ጋር ፡ ተዋግተው ፡ ሂዳስፕ ፡ አሸንፎ ፡ እንደመለሰው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተመልክተናል ። ከሂዳስፕ ፡ ቀጥሎ ፡ ዘመዱ ፡ ቤርአ ፡ ኤም ፡ ሔብ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ታአኬን ፡ ሲገዛ ፡ ቆይቶ ፡ ሕንደኬ ፡ ንግሥት ፡ ሁለተኛዪቱ ፡ ነገሠች ። እንደሌሎቹ ፡ ነገሥታት ፡ የግሪኩ ፡ የላቲኑ ፡ የኮፕቱ ፡ የዓረቡ ፡ ቋንቋ ፡ ስሟን ፡ ካንዳስ ፤ ካንታቂህ ፡ ካንዳቂ ፡ የሚላትን ፡ የኛ ፡ ግዕዝኛው ፡ ቋንቋ ። ባንዳንድ ፡ ሥፍራ ፡ ሕንደኬ ፡ ሲላት ፡ የዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ ደግሞ ፡ ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ ቅንዳቅስ ፡ ብሏታል ።

እርሷንና ፡ አገሯን ፡ ለመሰለል ፡ ከግብፅ ፡ ሰላዮች ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ ራሱ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ከሰላዮቹ ፡ ጋር ፡ እንዳንድ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ መ ጥቶ ፡ እንደነበረና ፡ ዐውቃው ፡ « አንተ ፡ ዓለምን ፡ የያዝኸው ፡ እስክንድር ፡ ንጉሥ ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ባንዲት ፡ ሴት ፡ ተያዝህ ፡ እንዳለችውና ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ በዕውቀትሽ ፡ በሕሊናሽ ፡ ጥልቀትና ፡ በጥበብሽ ፡ ያዝሽኝ ፡ ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ አንቺንም ፡ ልጆችሽንም ፡ በደግነት ፡ እጠብቃችኋለሁ ። አንቺንም ፡ ሚስት ፡ አደርግሻለሁ ፡ እንዳላት ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ያነበብነው ፡ የዮሐንስ ፡ መደብር ፡ የግዕዝ ፡ ጽሑፍ ፡ ያመለክታል ። ከዚሁ ፡ ኢያይዞ ፡ ከእስክ

ንድር ፡ እንደበት ፡ ሕንደኬ ፡ ንግሥት ፡ ይኸንን ፡ ስትሰማ ፡ እጅ ፡ ነሥታ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ እንደተስማማች ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የአበሻ ፡ ሕዝብ ፡ ለእስክንድር ፡ እንደተገዛለት ፡ ይገልጸል ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከየመጽሐፉ ፡ ያነበብሁት ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ መጽሐፍ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ከፋርሶች ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ ግብፅን ፡ ከመያዙና ፡ የእስክንድርያን ፡ ከተማ ፡ በ፫፻፴፪ ፡ ዓመት ፡ ከክርስ ትና ፡ በፊት ፡ ከቶም ፡ ወደአሶር ፡ ተመልሶ ፡ በ፫፻፴፩ ፡ ዓመት ፡ በአ ርበላ ፡ ከዳርዮስ ፡ ጋር ፡ መዋጋቱን ፡ እንጂ ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ መርዌ ፡ ከሰላዮች ፡ ጋር ፡ መጥቶ ፡ ሕንደኬ ፡ የምትባለዋን ፡ የመርዌ ፡ ንግሥት ፡ አግብቶ ፡ ተመለሰ፡ የሚሉ ፡ አላየሁም ። ዓባይን፡ የሚመረምሩ ፡ ሰዎች ፡ ልኮ ፡ እንደነበረና ፡ ግማሾቹ ፡ በመንገድ ፡ እንደሞቱ ፤ ግማሾቹም ፦ ተወላጅነታቸው ፡ የሶርያ ፡ ሰዎች ፡ በት ግሬ ፡ ቀርተው ፡ ዛሬ ፡ በትግሬ ፡ ውስጥ ፡ ሲሬ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ እንደተቀመጡና ፡ አገሩም ፡ በነርሱ ፡ ሲሬ ፡ ተብሎ ፡ እንደተጠራ ፡ የሚጽፉ ፡ አሉ ። ሞሪዮ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፭ ፡ ተመልከት ።

ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ የሚመስለው ፡ በመርዌ ፡ ንግሥት ፡ በሕንደ ኬና ፡ በትልቁ ፡ እስክንድር ፡ መካከል ፡ የጋብቻውም ፡ የተገኘነ ቱም ፡ ጕዳይ ፡ በመልእክት ፡ መፈጸሙ ፡ ነው ። መቼም ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ እንደተመለከትነው ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ መስፍን ፡ በጦር ፡ ሊያስፋ ፡ ያልቻለውን ፡ ወይም ፡ ያልፈለ ገውን ፡ ግዛቱን ፡ የሚያስፋው ፡ በጋብቻ ፡ በኩል ፡ ነበር ። የሸዋ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ለግዛትና ፡ ለፖለቲካ ፡ ሲሉ ፡ የየባላባቱን ፡ ልጆች ፡ በሚስትነት ፡ በየአለበት ፡ እያስቀመጡ ፡ ከዚሁ ፡ ጋብቻ ፡ ብዙ ፡ ዘር ፡ ከማግኘታቸው ፡ በቀር ፡ ይኸው ፡ ጋብቻ ፡ በዘመኑ ፡ ለሸዋ ፡ ግዛታቸው ፡ ጠቅሟቸው ፡ ነበር ።

እንደዚሁም ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ እስፈሪውን ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ጥሎ ፡ የራሱን ፡ ግዛት ፡ በግብፅ ፡ ሲመሠረትና ፡ የዓ ለም ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ ሲሰየም ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ በመስማት ፡ እርሷ ፡ ወደ ፡ እስክንድር ፡ እገብራለሁ ፡ የሚል ፡ መልእክተኞች ፡ ስትልክ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ገብሪልኝ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞች ፡ ሲልክ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የጋብቻ ፡ ንግግር ፡ ተደርጎ ፡ ይሆናል ። ከዚያም ፡ እስክንድር ፡



ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ ከአሶር ፡ ወደፋርስ ፤ ከፋርስ ፡ ወደ ሕንድ ፡ አገር ፡ ላገር ፡ እየዞረ ፡ ግዛቱን ፡ ሲያሰፋ ፡ ኖሮ ፡ በኋላ ፡ ወደ ባቢሎን ፡ ተመልሶ ፡ በ፫፻፳፫ ፡ ዓመት ፡ ሲሞት ፡ የሕንደኬና ፡ የእ ስክንድር ፡ ጋብቻ ፡ የወሬ ፡ ጋብቻ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቶ ፡ ይሆናል ። ነገር፡ ግን ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ነበሩት ፡ ከሚባሉት ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ሚስቶችና ፡ ዕቁባቶች ፡ ውስጥ ፡ እንዷቱ ፡ የመርዌ ፡ ንግ ሥት ፡ ሕንደኬ ፡ ናት ፡ እየተባለ ፡ ተጽፏል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደጋብቻው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለእስክን ድር ፡ በመልእክት ፡ መገበራቸውን ፡ «ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ገረረ ፡ ሎቱ ፡ ሀበሽ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሀበሾች ፡ ተገዙለት ፡ » ብሎ ፡ የኒቅዩ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዮሐንስ ፡ ከጻፈው ፡ በቀር ፡ የእስክንድርን ፡ የሕይ ወት ፡ ታሪክ ፡ የጻፈው ፡ ፕሉታርክ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ የድል ፡ አድራጊነቱንና ፡ የዓለም ፡ ገዥነቱን ፡ ባከበረበት ፡ በባቢሎን ፡ ከተማ ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ ተገኝተው ፡ እንደነበረ ፡ ጽፏል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እስክንድር ፡ ባለፈው ፡ ባመለከትነው ፡ ዓይነት ፡ ሞቶ ፡ ግዛቱን ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ ሲካፈሉት ፡ የግብፅ ፡ ግዛት፡ ለፕ ቶሎሜ ፡ ሶተር ፡ (ለፕቶሎሜ ፡ ላጎስ ፡ ልጅ) ፡ ደርሶ ፡ ይኸው ፡ ፕቶ ሎሜ ፡ በግብፅ ፡ ላይ ፡ ነግሦ ፡ በሚያስተዳድርበት ፡ ዘመን ፡ በመር ዌም ፡ ንግሥት ፡ ሕንደኬ ፡ ሞታ ፡ አስተርክ ፡ አሚን ፡ ነገሠ ። (ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት) ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የግ ብፅ ፡ ገዢዎች ፡ ፕቶሎሜ ፡ ሶተርና ፡ ከርሱ ፡ የቀጠለው ፡ ፕቶሎሜ ፡ ፊላደልፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሰሜን ፡ ጠረፍ ፡ ወታደርና ፡ ሰው ፡ መላክ ፡ ዠመሩ ። በተለይ ፡ ፕቶሎሜ ፡ ፊላደልፍ ፡ በምጥዋ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ የባሕር ፡ ወደብ ፡ አሠርቶ ፡ በስሙ ፡ ፕቶሎማይስ ፡ ብሎ ፡ ሰየመው ። እንደዚሁም ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ የነበረው ፡ የአዱሊስ ፡ ከተማ ፡ ወደብ ፡ ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ተሟሙቆ ፡ የግብፅና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሸቀጥ ፡ ማመላለሻ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። ይኸም ፡ ቶፕ ሎሜ ፡ ፊላደልፍ ፡ በ፪፻፸፪ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ከእስራኤል ፡ ሊቃው ንት ፡ ውስጥ ፡ ሰባ ፡ ሊቃውንት ፡ መርጦ ፡ ብሉይን ፡ ከእብራይ ስጥ ፡ ወደጽርዕ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ስለአስተረጐመ ፡ በትርጓ

ሜው ፡ ሥራ፡ ራሱ ፡ አብሮ ፡ ስለሠራ ፡ ሰመ ፡ ጥርነትን ፡ አግኝቷል ። በዚሁ ፡ በዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ በ፳ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እን ደዚህ ፡ ሲል ፡ ተጽፏል ። ወበመዋዕሊሁ ፡ ለበዋሊሞስ ፡ ፊላደል ፊስ ፡ ዘትርጓሜ ፡ ስሙ ፡ መፍቀሬ ፡ አኃው ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ብዙኃ ፡ ንባብ ፡ ወጠቢብ ፡ ወልደ ፡ አግላዎስ ፤ ውእቱ ፡ ተርጐመ ፡ መጻሕ ፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱሳተ ፡ እምልሳነ ፡ ዕብራኒ ፡ ኀበ ፡ ልሳነ ፡ ዮናኒ ፡ ምስለ ፡ ፸ኑ እዕሩግ ፡ በኁልቈ ፡ ፸ወ፪ ፡ መዋዕለ ፡ በእንተ ፡ ዘኮኑ ፡ ፸ ፡ ወ፪ ፡ መተርጕማን ፡ ወ፪ስ ፡ ሞቱ ፡ እምቅድመ ፡ ይተር ጕሙ ።

ከሕንደኬ ፡ ንግሥት፡ ይኸውም፡ ከ፫፻ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በመርዌ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ኃይለኛና ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ንጉሥ ፡ አልተ ነሣም ። አስተርክ ፡ አሚን ፡ አርክ ፡ አሚን ፡ አሩአሞን ፡ ሐርሰ ፡ አቴው ፡ የሚባሉ ፡ ነገሥታት ፡ በዙፋኑ ፡ አልፈዋል ። እነዚህም ፡ ምናልባት ፡ በዘመናቸው ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ይኖርባቸው ፡ ይኖ ራል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ የአርክ ፡ አሚን ፡ በመጠኑ ፡ ሲገኝ ፡ የቀሩት ፡ ሥራቸው ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ሽፍን ፡ ነው ። ስለ ዚህ ፡ ሁሉን ፡ ትተን ፡ አሁን ፡ አሚን ፡ በአሞን ፡ ካህናት ፡ ላይ ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ እንመልከት ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደጋግመን ፡ የጠራነው ፡ የነራምሲስ ፡ የነፒያንኪ ፡ ጌታ ፡ የአሞን ፡ ቤተ፡ መቅደስ ፡ በቴብ ፡ ከዚያም ፡ በናፓታ ፡ እንደሚ ገኝ ፡ በመርዌም ፡ በተለይ፡ አራታ ፡ (አሬዳህ) ፡ በሚባለው፡ ከተማ ፡ ይገኛል ። ከክርስትና ፡ በኋላ ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ የሮማ ፡ ሊቃነ ጳጳሳት ፡ በአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ እንደነበራቸው ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህም ፡ የአሞን ፡ ካህናት ፡ የበለጠ ፡ በሕዝቡና ፡ በነገሥታቱ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ነበራቸው ፡ ብዙም ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ ከራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ንጉሥ ፡ እየሆኑ ፡ ማስተዳደራቸውን ፡ በነፒያ ንኪ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ተገንዝበናል ፡ ከነሱ ፡ መካከል ፡ ባልነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ከውጭ ፡ የመጣውን ፡ እገሌ ፡ ይንገሥ ፡ እገሌ ፡ ከዙ ፋኑ ፡ ይውረድ ፡ እያሉ ፡ በእምባኳቸው ፡ በአሞን ፡ እያመካኙ፡ይሾሙ፡ ይሽሩ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ለንጉሥነት ፡ የተቀባለት ፡ የሚያ ደርገውን ፡ ሥርዓት ፡ ንግሥ ፡ ሙሴ ፡ ማሪዬትና ፡ ሙሴ ፡ ሮገ ፡



በዝበል፡ባርክ፡አግኝተው፡ከተረጐሙአቸው ፡ ሐውልቶች ፡ ውስጥ ፡ ፩ኛው ፡ በመጠኑ ፡ ያስረዳል ። የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ሲሞት ፡ በምትኩ፡ ንጉሥ ፡ እንዲተካ ፡ የሚፈልጉት ፡ የጦር ፡ ኹማምንቶችና ፡ ያገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ቤተ፡መቅደስ፡ይሔዳሉ ።

በዚያም ፡ ጸሎታቸውን ፡ ሲያደርሱ ፡ ውለው ፡ ካህናቱ ፡ ምነው፡ መጥታችኋል ፡ እያሉ ፡ እንዳገራችን ፡ ሠርገኛ ፡ ይጠይቁዋቸዋል ። እነሱም ፡ ሕይወት ፡ የሚሰጠን ፡ ስለታችንን ፡ የምናቀርብለትና ፡ በስሜን ፡ አገር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚሠራ ፡ ንጉሥ 1 አሞን ፡ ይሰ ጠን ፡ ዘንድ ፡ ለማሰመን ፡ መጣን ፡ ብለው ፡ በትሕትና ፡ መልሰው ፡ ያመለክታሉ።ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህናቱና፡ ነቢያቱ፡ለብቻቸው፡ሔደው ፡ የነዚህን ፡ ልመና ፡ ለአሞን ፡ እንደሚያመለክቱ ፡ ወደመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ።ከዚያም ፡ ተመልሰው ፡ እነዚህን ፡ ጠያቂዎችን ፡ እየመሩ ፡ ወደ ፡ ቤተ፡ መቅደሱ፡ ውስጥ፡ ያገቡዋቸዋል ። በአሞን ፡ ሐውልት ፡ ፊት ፡ ሲደርሱም ፡ ሁሉም ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ በግንባራቸው ፡ ይደፋሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሐውልቱ ፡ ራሱ ፡ በብል ሃት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሚናገር ፡ ስለተሠራ ፡ በዋናው ፡ ካህን ፡ አፍ ፡ እንዱን ፡ ካህናቱ ፡ የመረጡትን ፡ እያባየ ፡ እንዲዚህ ፡ ይላቸ ዋል ። « ይኸ ፡ ጌታችሁም ፡ ንጉሣችሁም ፡ ሆኖ ፡ ሕይወት ፡ ይሰ ጣችኋል ። በስሜንም ፡ በደቡብም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይሠራል ። ... የፀሐይ ፡ ልጅ ፡ ዘባለም ፡ የምኖረው ፡ ነኝ ። »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አድማጮች ፡ ሁሉ ፡ በምስጋና ፡ ይጮኻሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነጋሚው ፡ ለብቻው ፡ በአሞንና ፡ በርሱ ፡ በፊት ፡ በነበሩት ፡ በኢትዮጵያውያኑ ፡ ሐውልት ፡ ፊት ፡ ቀርቦና ፡ አሞ ንን ፡ አንግሠኝ ፡ ( ወይም ፡ እንድነግሥ ፡ ፍቀድልኝ ፡ ) ይለዋል ። አሞንም ፡ ንገሥ ፡ ፈቀድሁልህ ፡ ይለዋል ። በዚያን ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ዘውዱንና ፡ በትረ ፡ መንግሥቱን ፡ ከካህናት ፡ ይቀበላል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ለአሞን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ያቀርባል ።

ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ሥርዓት ፡ የአሞን ፡ ካህናትና ፡ ነቢያት ፡ ንጉሥን ፡ እንደፈቀዱቸው ፡ ለማንገሥና ፡ ለመሻር ፡ ሥልጣን ፡ ነበ ራቸው ፡ እነሱን ፡ ሳይጠይቅና ፡ ሳያስፈቅድ ፡ ማንም ፡ ንጉሥ ፡ የጦ ርነትም ፡ የሰላምም ፡ ማናቸውንም ፡ ያገር ፡ ታላቅ ጉዳይ ፡ ራሱ ፡

መወሰን ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ይኸም ፡ ሥልጣን ፡ የመንግሥቱ ፡ መደብ ፡ ናፓታ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አሁንም ፡ ወደ መርዌ ፡ ከተዛወረ ፡ ወዲህ ፡ ጸንቶ ፡ ቆየ ። የአሞን ፡ ካህናት ፡ ናፓታ ፡ ተቀምጠው ፡ የመርዌን ፡ ንጉሥ ፡ በመልእክት ፡ ይሾሙታል ፡ በመልእክት ፡ ይሽሩታል ። ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የሚያስገርመው ፡ በመልእክት ፡ ንጉሡን ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ እስከ ፡ ማስገደል ፡ መድረሳቸው ፡ ነው ።

የመርዌው ፡ ንጉሥ ፡ አንድ ፡ ኃጢአት ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ወይም ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ የማስተዳደር ፡ ሁኔታ ፡ ያሳየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካህናቱ «ይኸን ፡ የሠራኸውን ፡ የበደልና ፡ የግመጥ ፡ ሥራ ፤ አሞን ፡ ስለተመለከተ ፡ እንድትሞት ፡ አዞኻል ፡ ያልሞትህ ፡ እንደሆነ ፡ በሥጋህም ፡ በነፍስህም ፡ ትበደላለህ » ፡ ብለው ፡ ይልኩበታል ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ ይገድል ፡ ወይም ፡ ያስገድል ፡ ነበር ፡ ይባላል ። እንደዚህም ፡ ያለው ፡ ደንብ ፡ ተከብሮ ፡ እስከ ፡ አሁኑ ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ አርክ ፡ አሚን ፡ (ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ፫፻፰—፪፻ ፡ ዓመት ) እንደደረሰ ፡ ጥንት ፡ የሲሲሉ ፡ ዲዮዶር ፡ የጻፈውን ፡ ዝርን ፡ ሞሪዮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ተርጕሞ ፡ ይገኛል (፩) ። ዲዮዶር ፡ የሚባለው ፡ የግሪክ ፡ ተወላጅ ፡ በአውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ በሕይወቱ ፡ እንደዘመኑ ፡ አኳኋን ፡ በመጠኑ ፡ የዓለምን ፡ ታሪክ ፡ የጻፈ ፡ ነው ።

ወደ ፡ ታሪኩ ፡ እንመለስ ፡ አርክ ፡ አሚን ፡ የአስተርክ ፡ አሚን ፡ ፪ኛ ፡ ተከታይ ፡ ሆኖ ፡ በመርዌ ፡ በሚገዛበት ፡ ዘመን ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ ያነሳነው ፡ በጥሊሞስ ፡ ፊላደልፍ ፡ የሚባለው ፡ ነው ። አርክ ፡ አሚን ፡ ምን ፡ እንደ ፡ አጠፋ ፡ አይታወቅም ፡ ምናልባት ፡ ከነርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ለመተዳደር ፡ አምሮት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ስለጕና ፡ መሥዋዕት ፡ አስታጕሎ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሐሚታ ፡ ተሰምቶበት ፡ ይሁን ፡ እንደዚያው ፡ እንደተለመደው ፡ ከናፓታ ፡ የአሞን ፡ ካህናት ፡ ዘንድ ፡ እንድትሞት ፡ አሞን ፡ አዞኻል ፡ የሚል ፡ መላክተኛ ፡ በ፪፻፶ ፡ ዓመት ፡ መጣበት ። አርክ አሚን ፡ ይኸን ፡ ቃል ፡ ከመላክተኛው ፡ ሲሰማ ፡ እንደተለመደ ፡ የታዘዘውን ፡ በመፈጸም ፡ ፈንታ ፡ ተቈጥቶ ፡ በያዘው ፡ እንካሴ ፡

(፩) MORRIE - HIST. ፩ኛ ፡ ቮሊዩም ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶ — ፫፪ ፡



(ወይም ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ? ) ራሱን ፡ ተርክኮ ፡ መላክተኛውን ፡ ገደለው ፡ ቀጥሎ ፡ ወታደሩን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ አራት ፡ ሔደ ፤ ከዚያም ፡ ነቢያቱና ፡ ካህናቱ ፡ ወደሚገኙበት ፡ ተራራማ ፡ ከተማ ፡ ወጥቶ ፡ ወታደሮቹን ፡ እንደአስከተለ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ገብቶ ፡ ካህናቱንም ፡ ነቢያቱንም ፡ እያስያዘ ፡ በወታደር ፡ አስፈጃቸውና ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተከብረውና ፡ ተፈርተው ፡ የሚኖሩትን ፡ ካህናት ፡ አዋርዶ ፡ የጸናውንም ፡ ሕጋቸውን ፡ አፈረሰው ።

አርክ ፡ አሚን ፡ ካህናቱ ፡ በአሞን ፡ ተገን ፡ ሆነው ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ይልቁንም ፡ በመልክት ፡ ማስገደላቸውን ፡ ተቃወመ ፡ እንጂ ፡ የአሞንን ፡ አምልኮ ፡ አልተቃወመም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ካህናቱን ፡ ካስገደለ ፡ በኋላ ፡ በሚቾቹ ፡ ካህናት ፡ አገር ፡ ሌሎች ፡ ሥልጣናቸው ፡ በመንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ሾሞ ፡ እርሱ ፡ የንጉሥነቱን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ይዞ ፡ እንደልቡ ፡ ይገዛ ፡ ዠመር ። ከርሱም ፡ ወዲህ ፡ የነገሥታት ፡ አነጋገሥ ፡ (ሥርዓተ ፡ ንግሥ) ፡ በጦር ፡ አለቆቹ ፡ ልመና ፡ በካህናቱ ፡ ምርጫ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በውርስ ፡ ሆነ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ንጉሡ ፡ ሲሞት ፡ ወይም ፡ ሲያረጅ ፡ የትና ዘዘሉት ፡ ልጁ ፡ ወይም ፡ ዘመዱ ፡ ዙፋኑን ፡ እየወጣ ፡ ይገዛ ፡ ዠመር ፡ ማለት ፡ ነው ። አርክ ፡ አሚን ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከአደረገ ፡ በኋላ ፤ በግዛት ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንደቆየ ፡ ሞተ ። ስሙ ፡ በደቅህ ፡ የቱት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ በአውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ ጕን ፡ ተጽፎ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገኛል ፡ « አርክ ፡ አሚን ፡ የታዛዥ ፡ ሕዝብ ፡ ንጉሥ ፡ ዘወትር ፡ የሚኖረው ፡ የፀሐይ ፡ ልጅ ፡ የኢሲስ ፡ ወዳጅ» ፡ በሌላ ፡ ሐውልት ፡ ደግሞ ፡ «ሳቲ ፡ የወለደው ፡ የኑም ፡ ልጅ ፡ የሚመግበው ፡ የአሲሪስ ፡ ልጅ ፡ . . . » እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አሞን ፡ እንደሐትሆር ፡ የግብፅ ፡ የናፓታ ፡ የመርዌ ፡ ነገሥታት ፡ የሚያምኑባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አማልክት ፡ መሆናቸውን ፡ ባለፈው ፡ ያነበብነው ፡ ትዝ ፡ ይለናል ። ዘመናቸው ፡ ሳይገጥም ፡ በሐውልቱ ፡ ላይ ፡ ስሙ ፡ ከአውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ ጋር ፡ የተደባለቀበት ፡ አይገባኝም ፡ ምናልባት ፡ አርክ ፡ አሚን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሮማውያን ፡ በኑብያ ፡ ሲገቡ ፡ የጌታቸውን ፡ የአውግስጦስን ፡ ስም ፡ በአርክ ፡ አሚን ፡ ጕን ፡ አስጨምረው ፡ አስቀርጸውት ፡ ይሆናል ።

በግብፅ ፡ መንግሥት ፡ ከበጥሊሞስ ፡ ሶጠርና ፡ ከበጥሊሞስ ፡ ፊላደልፍ ፡ ወዲህ ፡ በግብፅ ፡ የነርሱው፡ዘር ፡ እየተከታተለ ፡ እስከ ፡ ፲፫ኛ ፡ በጥሊሞስ ፡ (የክሌዎፓትር ፡ ወንድም) ፡ ከክርስትና፡በፊት ፡ ከ፫፻፴ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ አውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ እንደደረሱ ፡ እንደዚሁም ፡ የኑብያውም ፡ ግዛት ፡ ከመርዌ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ወዲህ ፡ የብለሚይ ፡ የአለዋ ፡ የኖባ ፡ የናባት ፡ የስናር ፡ መሳፍንት ፡ እየተቀባበሉ ፡ ለቲንሽ ፡ ዘመን ፡ መንግሥቱን ፡ ያዙ ።

ዩልዮስ ፡ ቄሣር ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ እንደምንጽፈው ፡ የሮማን ፡ ግዛት ፡ ከሌሎቹ ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ ይበልጥ ፡ አስፍቶ ፡ ባላንጣውን ፡ ፖምፔን ፡ እያባረረ ፡ እስከ ፡ ግብፅ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ የግብፅን ፡ ግዛት ፡ ከአረጋገጠ ፡ ወዲህ ፡ ኑብያንም ፡ ለመያዝ ፡ ሲያስብ ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ እነሆሜር ፡ እነሄሮድቱስ ፡ በማንም ፡ ተገዝታ ፡ የማታውቅ ፡ የጐበዝ ፡ አገር ፡ ትልቁ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ካምቢዝ ፡ ተሸንፎ ፡ የተመለሰባት ፡ ናት ፡ ብለው ፡ አስጠነቀቁት ፡ ይባላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እሱ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ተመልሶ ፡ ከሞተ፡ ወዲህ ፡ አውግስጦስ ፡ አንቷንንና ፡ ክሌዎፓትርን ፡ ሊወጋ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ በመጣበት ፡ ዘመን ፡ የኑብያ ፡ ንግሥት ፡ ሕንደኬ ፡ ፫ኛዋ ፡ ነበረች ፡ በርስዋ ፡ ዘመነ ፡ ካያስ ፡ ፔትሮንዩስ ፡ የሚባል ፡ የሮማ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ በቴብ ፡ በናፓታ ፡ ከኢትዮጵያውያኑ ፡ ጋር ፡ እየተዋጋ ፡ አሸንፎ ፡ ናፓታ ፡ ገብቶ ፡ ከተማውን ፡ ዘረፈ ። ሕንደኬ ፡ ንግሥትም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወታደር ፡ እየላከች ፡ ከአዋጋች ፡ በኋላ ፤ በጦር ፡ የማይበገር ፡ መሆኑን ፡ ስትረዳው ፡ ጦርነት ፡ መቀጠልዋን ፡ ሳትተው ፡ የዕርቅ ፡ አሳብ ፡ ላከችበት ። ሮማዊው ፡ የጦር ፡ አለቃም ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በኃይሉ ፡ ተማምኖ ፡ እምቢ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፤ በመጨረሻ ፡ የርስዋንም ፡ መበርታት ፡ ሲያውቅ ፡ ዕርቁን ፡ ተቀበለና ፡ ጦርነቱ ፡ ቆመ ። ቀጥሎም ፡ የንግሥት ፡ ሕንደኬ ፡ መልእክተኞች ፡ ወደ ፡ ሳሞስ ፡ (ግሪክ ፡ ደሴት ፡) ሔደው ፡ ከአውግስጦስ ፡ ተገናኝተው ፡ ተመለሱ ። በክርስትና ፡ ዘመን ፡ በፊልጶስ ፡ በአርድዕቱ ፡ እጅ ፡ የተጠመቀው ፡ ጃንደረባ ፡ የዚች ፡ የሕንደኬ ፡ ፫ኛ ፡ ተከታይ ፡ ሕንደኬ ፡ አራተኛዪቱ ፡ መሆኑዋ ፡ ነው ።



ነገር ፡ ግን ፡ ጃንደረባው ፡ ወደመርዌ ፡ ተመልሶ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ክርስትና ፡ ሊስፋፋ ፡ አልቻለም ።

ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፶፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የኑብያ ፡ ንጉሥ ፡ ሰልኪ ፡ (ከመርዌ ፡ ወገን ፡ የሆነው) ፡ ክርስትናን፡ በደንብ ፡ ተቀብሎ ፡ በኑብያ ፡ ግዛቱ ፡ አስገባ ፤ ግንኙነቱንም ፡ ከእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ አጠበቀ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ መሐመድ ፡ ተነሥቶ ፡ የመሐመድ ፡ ተከታዮች ፡ ግብፅን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እስላምነት ፡ ሲለውጡት ፡ የኑብያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በነገሥታቶቻቸው ፡ በነሲራክ ፡ በነዘካርያስ ፡ በነጊዮርጊስ ፡ እየተመሩ፡ስለክርስትና፡ሃይማኖታቸው ፡ ሲዋጉ ፡ ሲታገሉ ፡ ኖረው ፡ ዓረቦች ፡ ከግብፅ ፡ እየመጡ፡በጦርነትም ፡ በስብከትም ፡ በየጊዜው ፡ ስለአየሉባቸው ፤ ወደ ፡ እስላምነት ፡ ፈጽሞ ፡ መለወጥ ፡ ግዴታ ፡ ሆነባቸው ። የተለወጡበትም ፡ ዘመን ፡ በ፩ሺ፩፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ግድም ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሲሆን ፡ የኑብያዎቹ ፡ አብዛኞቹ ፡ እስላም ሲሆኑ ፡ የአሎው ፡ (የአለዋ) ፡ ሕዝቦች ፡ በደሴታቸውና ፡ በተራራ፡ ሲመቻቸው ፡ እየተደበቁም ፡ እየሸሹም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ክርስቲያንነታቸውን ፡ ቀጥለዋል ። የቀረው ፡ የኑብያ ፡ አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ግብፅ ፡ በነዚሁ ፡ በዓረቦቹ ፡ ብርታት ፡ በሮም ፡ (ቍስጥንጥንያ ) ፡ መንግሥትና ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ደካማነት ፡ የተነሣ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እስላም ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ። የዚህንም ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ ሰፋ፡ ብሎ ፡ ወደፊት ፡ በሚታተመው ፡ በአክሱም ፡ መንግሥታችን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እናገኘዋለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፴ ።

### የኑብያው ፡ ኢትዮጵያና ፡ የአክሱም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ግንኙነትና ፡ ልዩነት ።

በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ እንደተጻፈው ፡ ባጭሩ ፡ በነዋሪው ፡ ሕዝብ ፡ በካም ፡ ተወላጅ ፡ ላይ ፡ የሴም ፡ ዘር ፡ ከምሥራቅ ፡ በየጊዜው ፡ መግባቱን ፡ ጸሐፊው ፡ ሁሉ ፡ በየመጽሐፉ ፡ ገልጾታል ። በየጊዜው ፡ የገ

ባውን ፡ ሕዝብ ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ እንደአጋጠመው ፡ የኩሽ ፡ ሕዝብ ፡ የባባ ፡ ሕዝብ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ነገደ ፡ አግዓዝያን ፡ ሂሚያሪት ፡ ሳባውያን ፡ ሀበሳን ፡ እያለ ፡ በዝርዝር ፡ ሲጠራው፡ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ አቅፎ ፡ የሚገኘው ፡ ስም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተባለው ፡ ስያሜ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ሲል ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ከግብፅ ፡ በደቡብ ፡ ከኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ እስከ ፡ አትላንቲክ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ አገር፡ ሁሉ ፡ በሰፊው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተባለበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ባንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ ምሥራቁ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምዕራቡ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተብሎ፡ ይገኛል ። ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ለናፓታ ፡ መንግሥት ፡ ብቻውን ፡ ለራሱ ፡ የኢትዮጵያነትን ፡ ስም ፡ ሰጥተውት ፡ ይገኛል ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንደምናስታውሰው ፡ ግብፅን ፡ የገዙትን ፡ እነፒያንኪን ፡ እነሻባካን ፡ የቀድሞ ፡ የግሪክና፡ የሮማ ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ለግብፅ ፡ ግዛት ፡ ፳፭ኛ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ አድርገዋቸዋል ።

ስለዚህ ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ ባሰፈው ፡ ተተርከው ፡ የሚገኙትን ፡ የናፓታንና ፡ የመርዌን ፡ ሕዝብ ፡ ግብፆችና ፡ አሶሮች ፡ ዕብራውያንም ፡ ኩሽ ፡ ሲሉዋቸው ፡ ግሪኮቹና ፡ ሮማውያኑ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ብለውት ፡ ይገኛል።ይኸ ፡ ባንድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ የሚጠራው ፡ ሕዝብ ፡ በውስጥ ፡ አገሩ ፡ በነገድ ፡ በጐሣ ፡ በልማድ ፤ በቋንቋ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እንደሚለያዩ ፡ አሁንም ፡ በምዕራፍ ፡ ሦስት ፡ ያነበብነውን ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። እነ ፡ አጋርታሽድ ፡ የሕዝቡን ፤ ነገድና ፡ ልማድ ፡ በሚባለው ፡ በሚለብሰው ፡ በሚኖርበት ፡ ሥፍራ ፡ በሚመስለው ፡ የእንስሳ ፡ ዓይነት ፡ « ስትሩአፋዥ ፡ አክሪሎፋዥ - ትሮግሎዲት - ሳጐሴፋል - ሔዮራኮሴፋል - ማክሮቢያን . . . . . . . . » እያሉ ፡ ቊጥሩን ፡ እስከ ፡ ፵፯ ፡ ያደረሱት ፡ የሚበዛም ፡ ቢሆን ፡ ባጭሩ ፡ የሕዝቡ ፤ የነገድና ፡ የቋንቋው ፡ ስም ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ እንደሚታወቀው ፡ ሳባ ፤ ናባ ፤ በጀያ ፤ ቅማንት ፤ ቁናማ ፤ ጋላ . . . . እያለ ፡ የካሙና ፡ የሴሙ ፡ ዘር ፡ ይለያል ። እነዚህም ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ስማቸውንና ፡ ቋንቋቸውን ፡ ይዘው ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከውጭ ፡ እየመጣ ፡ የሚደረበው ፡ ሁሉ ፡ የራሱን ፡ ስምና ፡ ቋንቋ ፡ ይዞ ፡ በመኖር ፡ ፈንታ ፡



አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በፊተኞቹና ፡ በነባሮቹ ፡ ተውጦ ፡ ይገኛል ። በነዋሪው ፡ በካም ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ የተባሉትን ፡ አግዓዝያን ፡ በየዘመኑ ፡ ገብተው ፡ በገዥነትም ፡ በነዋሪነትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከተመሠረቱ ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው፡በነሱ ፡ ላይ ፡ የተጨመረው፡ ሕዝብ ፡ ከየታሪኩ ፡ ሲሰቀም ፡ የእሥራኤል ፡ የከነዓን ፡ የፋርስ ፡ የሕንድ ፡ ዘር ፡ በየጊዜው ፡ በየምክንያቱ ፡ እየገባ ፡ እንደ ፡ ተጨመረ ፡ ይታወቃል ።

ፍርሶችና| ፡ በነሱ ¦ አካባቢ ፡ የሚኖር ፡ ሕዝብ ፡ በካምቢዝና ፡ በነዳርዮስ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጠረፍ ፡ በሚገዛበት ፡ ጊዜ ፡ ፋርሶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሲገቡ ፡ ኢትዮጵያውያንም፡ደግሞ ፡ ወደነሱ ፡ አገር ፡ በወታደርነት ፡ሔደው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፤ ፋርሶች ፡ በዳርዮስ፡፪ኛ ፡ ዘመን፡ ከግሪኮች፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የአንበሳና ፡ የነብር ፡ ለምድ ፡ ለብሰው ፡ በፋርሱ ፡ ሹም ፡ እየተመሩ ፡ ስብቻቸው ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ይዘው ፡ ከግሪኮቹ ፡ ተዋግተዋል ፡ ተብሎ ፡ ባለፈው ፡ የተጻፈውን ፡ እናስታውስ ።

የከነዓን ፡ ሕዝብ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ አገራቸውን ፡ ለእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ለማከፋፈል ፡ ሲል ፡ በጦርነት ፡ ባጠፋቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተሰደዋል ፡ ይባላል ።

የእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ደግሞ ፡ በፊት ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰማርያን ፡ በከበበ ፡ ጊዜ ፤ ናቡከደነጸር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ባፈረሰበት ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ሮማዊው ፡ ጢጦስ ፡ በጦርነት ፡ ባስጨነቀበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተዋል ፡ ይባላል ። በተረፈ ፡ በሰላም ፡ ዘመንም ፡ በንግድና ፡ በሌላም፡ምክንያት ፡ ክርስቲያንም ፡ እስላምም ፤ አረመኔም ፡ በመጠኑ ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ፡መግባቱና ፤ መራባቱ ፡ አልቀረም ። ስለዚህ ፡ በሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ እንደሚደርሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገድና ፡ የቋንቋ ፡ ዓይነት ፡ ቢበረክት ፡ የስምና ፡ የልማድ ፡ ዓይነትም ፡ ቢበዛ ፡ አያስደንቅም ። ልማዱ ፤ ቋንቋው ፡ ቢበረክት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያዊነት ፡ ስም ፡ ታስሯልና ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ አሳባችን ፡ እንመለስ ።

እንግዲህ ፡ ከአክሱም ፡ መንግሥት ፡ መነሣት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ባለፈው ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የገነነው፡የናፓታ ፡ መንግሥት ፡ እንደምን ፡ እንደተነሣ ፡ እንደምን ፡ እንደወደቀ ፡ በግብፅ ፡ እንደ፡ ተገዛ ፡ ግብፅንም ፡ መልሶ ፡ እንደገዛ ፡ ከዚያም፡ነፃነቱን ፡ ይዞ ፡ እስከ ፡ ዓረብ ፡ ወረራ ፡ (፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡) ድረስ ፡ እንደ፡ ምን ፡ እንደደረሰ ፡ ያለፈው ፡ ክፍል ፡ በየምዕራፉ ፡ አስረድቶናል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ያርሱ ፡ ገዥነትና ፡ ገናናነት ፡ ሲቀዘቅዝ ፡ በጕኑ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የሚገኘው ፡ አክሱም ፡ በፈንታው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደተነሣ ፡ ልንመለከት ፡ ነው ። የናፓታና ፡ የአክሱም ፡ አገሮች ፡ በአገር ፡ ጕርብትናም ፡ በዘርም ፡ የሚገናኙ ፡ ሁለቱ ፡ በየተራ ፡ የገነኑ ፡ ወንድማማቾች ፡ ናቸው ። ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ በመልክ ፡ ቅርጽ ፡ በቋም ፡ ግባት ፡ በአገር ፡ ካርታ፡አቀማመጥ ፡ በሥርዓትና ፡ በልማድ ፡ በቤትና ፡ በዕቃ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ በሙሉም ፡ ባይሆን ፡ በመጠኑ ፡ ተመሳስለው ፡ በዘር ፡ ተከላልሰው ፡ ይገኛሉ ።

በመዠመሪያ ፡ ናፓታ ፡ ቀጥሎ ፡ መርዌ ፡ በገነነበት ፡ ሰዓት ፡ በአክሱም ፡ ዙሪያ ፡ የሚገኘው ፡ አገር ፡ በነርሱ ፡ መግዛቱ ፡ አክሱም ፡ በገነነ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አብርሃና ፡ ( ኢዛና ) ፡ ተከታዮቹ ፡ ኑብያን ፡ (ናፓታና ፡ መርዌን) ፡ መግዛታቸው፡ የታወቀ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ መገዛዛት ፡ አንድነታቸውን ፡ ጭምር ፡ ያስረዳል ። በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ አብዛኛው ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ ይልቁንም ፡ ያገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ከአክሱም ፡ በፊት ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የነገሡትን ፡ ነገሥታት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እያደረገ ፡ ዝርዝራቸውን ፡ ከነስማቸው ፡ ከአክሱሙ ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ተርታ ፡ እየሰጠ ፡ ደባልቆ ፡ ይጽፋል ። ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይም ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ሌሎቹም ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሁሉ ፡ የካም ፡ ነገሥታት ፡ አድርገው ፡ ዝርዝራቸውን ፡ የምናየው ፡ እነዚህኑ ፡ በኑብያ ፡ (ናፓታና ፡ መርዌ) ፡ የነገሡትን ፡ ነገሥታት ፡ ነው ። በዚያም ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ግብፅን ፡ የገዙት ፡ እነፒያንኪ ፤ እነሻባካ ፤ እነታርሐቃ ፤ እነታኑታሙን ፤ በግብፅ ፡ የተገዙትም ፡ በግብፅም ፡ ሳይገዙ ፡ ግብፅንም ፡ ሳይገዙ ፡ በነፃነት ፡ ባገራቸው ፡ የኖሩትም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ተብለው ፡ ተዘርዝረዋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ዝርዝር ፡ ያመት ፡ ቍጥር ፡ የዘመን ፡ ልክና ፡ ስም ፡ ዛሬ ፡ ታሪካቸውን ፡ በምንመረምርበት ፡ ጊዜ ፡



ከነዋሪው ፡ ዝርዝር ፡ ጋር፡ የማይጠጋም፡ አለ ። ስለዚህ ፡ በምናየው ፡ በነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ እምነት ፡ ሊጣልበት ፡ አይቻልም ። ግብፆቹ ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ የበላይ ፡ የፈርዖኑ ፡ ልጅ ፡ የበታች ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ንጉሥ ፡ ባንድነት ፡ ይገዙ ፡ የነበረውን ፡ ሁለቱንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ እያሉ ፡ ሲያከታትሉት፡እንደዚሁም ፡ ኢትዮጵያውያኑ ፡ ግብፅን ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ ለእኅቶቻቸው ፡ ትልቅ ፡ ሥልጣን ፡ እየሰጡ ፡ በቴብና ፡ በናፓታ ፡ ከተማ ፡ የሾሟቸውን ፡ ሴቶች ፡ ከፈርዖኖቹ ፡ ኢትዮጵያውያን፡ጐን ፡ እያከታተሉ ፡ የቴብን ፡ (ላዕላይ፡ግብፅ) ፡ ገዥዎች ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ቈጥረዋቸዋል ።

ለምሳሌ ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፍ ፡ በኻያኛው ፡ ገጽ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ኒካንታ ፡ ቅንዳኬ ፡ ብለው ፡ ከሳባቃ ፡ (ሻባካ) ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ነገሥች ፡ የጸፉዋት ፡ አሚኒሪት ፡ የተባለችው ፡ የሻባካ ፡ ምግዚትና ፡ የቴብ፡ ገዥ ፡ የነበረችው ፡ ነች ፡ እንጂ ፡ ሻባካ ፡ ሞቶ ፡ በርሱ ፡ እግር፡ ኢትዮጵያንና ፡ ግብፅን ፡ የገዛች ፡ አይደለችም ። እሷንም ፡ ጽፈው ፡ ከርሷ ፡ በኋላ ፡ ታርሐቃን ፤ ( ቲርሐቅ ፡ ወረደ ፡ ነጋሽን ) ፡ ሲያገቡ ፡ በሻባካና ፡ በታርሐቃ ፡ መካከል ፡ በደንብ ፡ በግብፅና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ሻባቶካ ፡ የሚባለው ፡ የሻባካ ፡ ልጅ ፡ ተዘሏል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የናፓታና ፡ የአክሱም ፡ አንድነት፡ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸውና ፡ ይልቁንም ፡ በኢትዮጵያዊነት ፤ ሲገጥም ፡ የሚለያዩበትን ፡ ደግሞ ፡ እንመልከት ።

በዘር ፡ ረገድ ፡ አክሱማውያን ፡ ከሴም ፡ ወገን ፡ ከወረደው ፡ ከዮቅጣን ፡ ሳባ ፡ የመጡ ፡ ሲሆኑ ፡ የኑብያ ፡ (ናፓታና ፡ መርዌ) ፡ ሕዝብ ፡ ከካምና ፡ ከኩሽ ፡ ከወረዱት ፤ ሳባ ፡ የመጡ ፡ ስለሆነ፡በአክሱሞች ፡ ዘንድ ፡ ሴማዊ ፡ በኑብያዎቹ ፡ ዘንድ ፡ የካምና ፡ የኩሽ ፡ ዘር ፡ ይበዛል ።

ናፓታና ፡ መርዌ ፡ ከግብፅ ፡ እንደመዋሰናቸው ፡ መጠን ፡ ቋንቋቸው ፡ ፊደላቸው ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ከግብፅ ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ በትክክል ፡ ከግብፅ ፡ የተወሰደ ፡ ነው ። አክሱም ፡ ደግሞ ፡ ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ ከዓረብ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ጕረቤት ፡ ስለሆነ ፡ በአክሱም ፡ ከነዋሪው ፡ በቀር ፡ በገዥነት ፡ የተ

መሠረቱት ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፤ ከሳባ ፤ ከሐበሳት ፡ ከሒሚያራት ፡ . . . የመጡ ፡ ነገዶች ፡ ስለሆኑ ፡ ቋንቋቸው ፡ ጽሕፈታቸው ፡ ልማዳቸው ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የተወረሰ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ደቡብ ፡ ዓረብ ፤ ደግሞ ፡ ይኸን ፡ አክሱሞች ፡ የወረሱትን ፡ ሥልጣኔ ፡ ከየት ፡ አገኘው ፡ ተብሎ ፡ ሲመረመር ፤ ከባቢሎንና ፡ ከአሶር ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ (አሶር-ባቢሎን-ከለዳውያን-አካድያን) ፡ በየጊዜው ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መጥተው ፡ ሲኖሩ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ እየተሻገሩ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገቡ ። የነርሱም ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ሃይማኖትና ፡ ልማድ ፡ ከአሶራውያንና ፡ ከአካድ ፡ ሲመሳሰል ፡ ከናፓታዎችና ፡ ከመርዌዎች ፡ ከግብፆች ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ጋር ፡ በፍጹም ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ባለፈው ፡ ግብፆችና ፡ የናፓታ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይሠሩበት ፡ የነበረውን ፡ ሂዩሮግሊፍ ፡ እንዳየን ፡ ወደፊት ፡ አክሱሞች ፡ ይሠሩበት ፡ የነበረውን ፡ ለዛሬው ፡ ፊደላችን ፡ እንደ ፡ አባት ፡ የሚቈጠረውን ፡ የሳባ ፡ ፊደል ፡ እንመለከታለን ።

በአምልኮም ፡ ናፓታዎቹ ፡ እንደግብፆቹ ፡ በአሞን ፡ በኦሲሪስ ፡ በሖትሆር ፡ ሲያመልኩ ፡ አክሱሞች ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በማሕረም ፡ በአስታር ፡ (በጨረቃና ፡ በከዋክብት) ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ፤ እነዚህም ፡ አማልክት ፡ የደቡብ ፡ ዓረቦች ፡ የሚያመልኩባቸውና ፡ እነርሱ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይዘዋቸው ፡ የተሻገሩት ፡ አማልክት ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አክሱም ፡ አባትነቱን ፡ አንድነቱን ፡ ይዞ ፡ ሲረጋ ፡ ናፓታና ፡ መርዌ ፡ ግን ፡ በዓረብ ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ መንግሥት ፡ ድካም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተነጥሎ ፡ የዓረቦችን ፡ ሃይማኖትና ፡ ቋንቋ ፡ ይዞ ፡ ዛሬ ፡ ለብቻ ፡ የሱዳንን ፡ መንግሥት ፡ አቁሞ ፡ የጐረቤት ፡ አገር ፡ ሆኗል ።

አክሱም ፡ ግን ፡ ሳይነጠል ፡ ከተማውም ፡ መሬቱም ፡ በዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጅ ፡ ስለሆነ ፡ ዘመኑም ፡ ለጊዜያችን ፡ ስለቀረበ ፡ የሥልጣኔያችን ፡ መነሻ ፡ የገናናነታችን ፡ መታሰቢያነቱ ፡ ከናፓታ ፡ ይበልጥ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይሰማል ። በሃይማኖትና ፡ በዘር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ በየጊዜው ፡ እየፈለሱ ፡ የመጡት ፡ የሳባ ፡



የሒሚያራት ፡ የሀበሳት ፡ ወገኖች ፡ ዛሬ ፡ ላለው ፡ ትግሬና ፡ አማራ ፡ አባትነታቸው ፡ ሲታወቅ ፡ የነርሱ ፡ (የሳባ) ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋም ፡ ለዛሬው ፡ ፊደላችንና ፡ የግዕዝ ፡ ቋንቋችን ፡ አባትነቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ባለፈው ፡ በጻፍነው ፡ ዛሬ ፡ ሱዳን ፡ ቀድሞ ፡ ኑብያ ፡ ወይም ፡ የናፓታ ፡ ሕዝብና ፡ በቀድሞዎቹ ፡ አክሱሞች ፡ በዛሬዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ለመረዳት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲከራከሩበት ፡ ለሚኖሩት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ እንደሚገላግላቸው ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ። ከዚህ ፡ የተረፈውን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውንና ፡ ለብቻ ፡ የታተመውን ፡ የአክሱሞችን ፡ ታሪክ ፡ ፊደላቸውን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ አንባቢ ፡ በሚመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ ካለፈው ፡ ካነበበው ፡ ከናፓታዎቹ ፡ ታሪክና ፡ ሃይማኖት ፡ ከጽሑፍና ፡ ከፊደላቸው ፡ ጋር ፡ ራሱ ፡ እያመዛዘነ ፡ የራሱን ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

ተ ፈ ጸ መ ።